# ክብረ ነገሥት

## ግእዝና አማርኛ



የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

www.ethiopianorthodox.org

# ክ ብ ረ   ነ ገ ስ ት

## ግእዝና አማርኛ

የመፅሃፉ ተርጓሚ፣ አዘጋጅና አርታኢ

ሰርግው ገላው

www.ethiopianorthodox.org

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
መስከረም 1994

www.ethiopianorthodox.org

# መቅድም

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል በኣዲስ ኣበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በ1989 በኣዲስ መልክ ከመዋቀሩ በፊት የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ኣካደሚ በሚል ስያሜ ለ25 ኣመታት ያህል በቋንቋና ስነፅሁፍ መስክ በርካታ የጥናትና ምርምር ስራዎችን ሲያካሂድ የቆየ ተቋም ነው። ኣካደሚው በሃገራችን ልዩ ልዩ ቋንቋዎች የስነ ልሳን ጥናቶችን፣ የመዛግብተ ቃላት ዝግጅቶችን፣ የቃላት ስያሜ ስራዎችን፣ የስነ ቃል ጥናቶችን፣ ወዘተርፈ ኣከናውኗል። በግእዝ ስነፅሁፍ ረገድም ሰፊ የምርምር ስራ ከማካሄዱም በላይ ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ ቅኔያትን ሰብስቦ፣ ወደ ኣማርኛ ተርጉሞና ኣመስጥሮ ሁለት ተከታታይ ቅጂዎችን በማሳተም ለህዝብ ንባብ ኣብቅቷል። የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች ባህላቸውን፣ ወግና ልማዳቸውን ከትውልድ ትውልድ የሚያስተላልፉት በስነ ቃል ኣማካይነት እንደመሆኑ በዚህ ኣቅጣጫም እስከ ኣሁን ድረስ የኣማርኛ፣ የትግርኛ፣ የወላይትኛ፣ የሲዳምኛና የቤተ ጉራጌ የስነቃል መፃህፍትን ኣሳትሟል። ኣሁን ደግሞ እነሆ በኢትዮጵያ የመንግስት ታሪክ ውስጥ ለኣያሌ ምእተ ኣመታት ኣቢይ ሚና ሲጫወት የኖረውንና ታሪካዊ ጠቀሜታው የጎላ የሆነውን የክብረ ነገስት የኣማርኛ ትርጉም ለመጀመሪያ ጊዜ ለኣንባቢዎች ኣቅርቧል። ይህ መፅሃፍ እስከዛሬ ድረስ በኣገሪቱ መግለገያ ቋንቋ ያልቀረበ ስለነበር በኢትዮጵያ የቀድሞ የመንግስት ታሪክ ላይ ጥናትና ምርምር የሚያደርጉ ሰዎች ከግእዙ ቅጂ ሌላ የነበራቸው ምርጫ በሌሎች የባእድ ቋንቋዎች የተዘጋጁትን ቅጂዎች መመልከት ሆኖ ቆይቷል። የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል ይህንን የኣማርኛ ትርጉም ለማዘጋጀት ያቀደውም ይህንን ጉድለት ማስወገድ ተገቢ ሆኖ ስላገኘው ነው። የዚህ መፅሃፍ ዝግጅት የተጀመረው ማእከሉ ወደ ኣዲስ ኣበባ ዩኒቨርሲቲ ከመዛወሩ በፊት ሲሆን መሰናዶው ከዚያ በኋላ በነበሩት ኣመታትም ቀጥሎ ቆይቷል። የዝግጅት ክፍሉ ትርጉሙ በመነኛው ቋንቋ ከቀረበው ፅሁፍ ጋር እኩሌታ እንዲኖረውና መሰረታዊ የሆኑ የእምነት፣ የባህልና የስነፅሁፍ እሴቶች ተጠብቀው እንዲተላለፉ ለማድረግ የተቻለውን ያህል ጥረት ኣድርጓል። ይህ መፅሃፍ የኣገሪቱ ታሪካዊና ስነፅሁፋዊ ቅርስ በመሆኑ ካለው ዋጋ በተጨማሪ ለልዩ ልዩ የቋንቋ፣ የስነፅሁፍ፣ የባህል፣ የእምነት፣ የታሪክ፣ ወዘተርፈ ተመራማሪዎች ከፍተኛ ኣገልግሎት እንደሚሰጥ ይታመናል።

ይህንን መፅሃፍ ኣዘጋጅተው ለውጤት ላበቁት የማእከሉ የግእዝ ቋንቋና ስነፅሁፍ ተመራማሪ ለኣቶ ስርግው ገላው፣ የፅሁፉን ረቂቅ በማንበብ የኣርትኦት ኣስተዋፅኦ ላደረጉ የማእከሉ ባለሙያዎችና ከማእከሉ ውጪ ለሚገኙ ምሁራን እንዲሁም ፅሁፉን በኮምፒዩተር በመፃፍና በሌሎችም ረገድ ቴክኒካዊ ኣስተዋፅኦ ላደረጉ ሁሉ ማእከሉ ከፍተኛ ምስጋና ያቀርባል።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል



# መግቢያ

"ክብረ ነገስት" ቢያንስ ለሰባት መቶ ኣመታት ለኢትዮጵያ እንደ ብሄራዊ ህገ መንግስት ሆኖ ኣገልግሏል። ከ1270 -1966 በኢትዮጵያ የነገሱት ነገስታትን ስልጣን ይወስን የነበረው "ክብረ ነገስት" በሚደነግገው መሰረት ነበር። ኣፄ ዮሃንስ "ኣገሬና ህዝቤ ያለ እሱ ኣይታዘዝልኝምና ክብረ ነገስት የተባለው መፅሃፍ በማን እጅ እንደሆነ ኣፈላልገው ይላኩልኝ* " በማለት ለሎርድ ግራንቪስ በኦገስት 1872 ኣ.ም. የፃፉት ደብዳቤ ይህንኑ እውነታ ያሳያል። ኣፃፃፉም ቢሆን ህገ መንግስትን ለማርቀቅ ታስቦ የታቀደ ይመስላል። ምክንያቱም በውስጡ ስለ መንግስት የስልጣን ምንጭ፣ በትረ ስልጣን መያዝ ስለሚገባቸው ሰዎች ማንነት፣ ስለ ባለስልጣናት የተለያየ ሃላፊነትና የስልጣን ድርሻ፣ ስለ ህዝብ መብትና ግዴታ፣ በነገስታትና በሕዝብ መካከል ስላለውና መኖር ስለሚገባው ህጋዊ ግንኙነት፣ ስለሃገሪቱ መሰረታዊ ህጎች፣ ወሰን፣ በዚያን ዘመን ስለነበሩት መንግስታትና ኢትዮጵያ ከነዚህ መንግስታት ጋር ስላላትና ሊኖራትም ስለሚገባ ታሪካዊና ባህላዊ ግንኙነት፣ ለኢትዮጵያ የተለየች ሃይል ስለሚላት ስለታቦተ ፅዮን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት.....ወዘተርፈ በዝርዝር ይተርካል።

በትረካው መሰረት የመንግስት የስልጣን ምንጭ መለኮታዊ ሃይል ነው። ለዚህም መፅሃፍ ቅዱስን በዋቢነት ይጠራል።

> እድሜህ በተፈፀመና ከኣባቶችህ ጋር ባንቀላፋህ ጊዜ፣ ከወገብህ የሚወጣውን ዘርህን ከኣንተ በሁዋላ ኣስነሳዋለሁ። መንግስቱን ኣፀናለሁ። እኔም ኣባት እሆነዋለሁ። እሱም ልጅ ይሆነኛል። ክፉ ነገርም ቢያደርግ ሰው በሚቀጣበት በትርና በሰው ልጆች መቀጫ እገስፀዋለሁ። ከፊቴም እንደጣልኩት ከሳኦል እንደኣራቅሁ ምህረቴን ከእሱ ኣላርቅም። ቤትህና መንግስትህም በፊቴ ለዘለኣለም ይፀናል። እንደዚሁም ቃል ሁሉ እንደዚሁም ራእይ ሁሉ ናታን ለዳዊት ነገረው (2ሳሙ.7÷12-17)።

> ለባሪያዩ ዳዊት ማልሁ። ዘርህን ለዘላለም ኣዘጋጃለሁ። ዙፋንህንም ለልጅ ልጅ እመሰርታለሁ (መዝ. 89÷4)።

> እግዚኣብሄር ለዳዊት በእውነት ማለ። ኣይፀፀትም እንዲህ ብሎ ከሆድህ ፍሬ በዙፋንህ ላይ ኣስቀምጣለሁ። ልጆችህ

* Sir Ernest Alfred Thompson Wallis Budge. **The Queen of Sheba & her only son Menyelek**. London: Marthin Hopkinson. 1922: p. vii.

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ኪዳኔን፣ ይህንንም የማስተምራቸውን ምክሬን ቢጠብቁ ልጆቻቸው ደግሞ በዙፋንህ ለዘላለም ይቀመጣሉ (መዝ. 132÷11)።

ይህ እንግዲህ የእስራኤል አምላክ ለእስራኤል ንጉስ ለዳዊት የሰጠው መለኮታዊ ቃል ኪዳን ሲሆን ይሁንና ይህ ቃል ኪዳን በምድረ እስራኤል ተፈፃሚ ሲሆን አልታየም።

እንደሚታወቀው የዳዊት ልጅ ንጉስ ሰሎሞን ሞቶ የሰሎሞን ልጅ ሮብአም በ931 ቅ.ል.ክ. ሲነግስ የተስፋው መንግስት ለሁለት ተከፈለ። ደቡቡ ክፍል እስራኤል ሰሜኑ ደግሞ ይሁዳ ተብሎ ሁለት መንግስት ሆነ። የደቡብ መንግስት ከ12 ነገድ ውስጥ 10 ነገድ ሲያካትት ሰሜኑ ደግሞ በሁለት ነገዶች (ይሁዳና ብንያም) ብቻ ቀጠለ። የዳዊት ልጆች ድርሻ የነበረው ይሄው ሁለት ነገዶችን ብቻ ያቅፍ የነበረው የደቡቡ ክፍል ነበር።

በ722 ቅ.ል.ክ. የአሶር ንጉስ ስልምናስር የሰሜኑ ዋና ከተማ የነበረውን ሰማርያን ወሮ ንጉሱን ሆሴእን በወህኒ አሰረው። ህዝቡንም አፈለሰ (2ነገ.17)። በዚህም የእስራኤል (የሰሜኑ ክፍል) መንግስት ፍፃሜ ሆነ።

በ586 ቅ.ል.ክ. የባቢሎን ንጉስ ናቡከደነፆር የደቡቡን ዋና ከተማ ኢየሩሳሌምን ከቦ ንጉሱን ሴዴቅያስን ማረከ። አይኑን አጠፋ። ልጆቹንም በፊቱ አረዳቸው። ህዝቡንም ወደ ባቢሎን አፈለሰ (2ነገ.25)። በመሆኑም የይሁዳ መንግስት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተቋረጠ። እነዚህ ሂደቶች ሲታዩ የእስራኤል አምላክ ለወዳጁ ለዳዊት የሰጠው ተስፋ የት አለ? የሚል ጥያቄ ሊያስነሱ ይችላሉ።

ይህንኑ የዳዊት መንግስት ውድቀት የአስተዋለ የሁዋላ ዘመን መዝሙረኛ በይሁዳ ቤት በፅኑ የሚታመንበትንና እግዚአብሄር ለንጉስ ዳዊት የሰጠውን ቃል ኪዳን ከጠቃቀሰና የተከተለውንም ውድቀት ካስታወሰ በሁዋላ፣

ከንፅህናውም ሻርከው
ዙፋኑንም በምድር ጣልህ
የዙፋኑንም ዘመን አሳነስህ
በእፍረትም ሸፈንከው
አቤቱ እስከ መቼ ፊትህን ትመልሳለህ /መዝ. 89፣20-48/

በማለት ለዳዊት መንግስት አልቅሷል።

እንደ ክብረ ነገስት ፀሃፊዎች ግን እግዚአብሄር ይህንን ቃል ኪዳን ሃገረ እግዚአብሄር በሆነችው በኢትዮጵያ ፈፀመው እንጅ ለዳዊት የሰጠው የተስፋ ቃል አልታጠፈም። በመሆኑም በልዩ ጥበቡ የዳዊትን ተስፋ በኢትዮጵያ ለመፈፀም ያቀደው ልኡል አምላክ የኢትዮጵያ ንግስት የሆነችውን ንግስተ ሳባን ሰሎሞንን በእንቆቅልሽ ትፈትነው ዘንድ ወደ ኢየሩሳሌም አንቀሳቀሳት (1ነገ.10÷1-14፣ዜና 9÷1-13፣ ማቴ.12-42)። እንደ



እግዚአብሄርም ፈቃድ ከንጉስ ሰሎሞንም ዳዊት ወይም እብነ እለሃኪም የተባለውን ፀንሳ ተመለሰች።

እብነ እለሃኪምም 22 አመት ሲሆነው ወደ አባቱ አገር ሂዶ እዚያው ኢየሩሳሌም እንዲነግስ ቢለመን ፈቃደኛ ባለመሆኑ መንግስትን፣ ህግንና ስርአትን፣ ታቦተ ፅዮንንና ካህናትን ይዞ ወደ ትውልድ ሃገሩ ኢትዮጵያ ተመለሰ። ኢትዮጵያ እንደ ደረሰም ሳይውል ሳያድር ስርአተ ንግስ ተፈፀሞለት ነገሰ። በመሆኑም የዳዊት ተስፋ በልጅ ልጁ በእብነ እለሃኪምና በተከታዮቹ አማካኝነት ኢትዮጵያ ውስጥ ተፈፀመ የሚል ነው።

የመፅሃፉ ይዘት በዋናነት በዚህ ዙሪያ እያጠነጠነ የንግስተ ሳባን የጉዞ ሁኔታ፣ በኢየሩሳሌም ያደረገችውን ቆይታና የህፃኑን አስተዳደግ፣ ወደ አባቱ ያደረገውን ጉዞና ታቦተ ፅዮንን፣ ህግንና ካህናትን ይዞ መመለሱን በዋናነት ይተርካል።

ይህ መፅሃፍ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በህዝቡም ሆነ ነገስታቱ ዘንድ ከፍተኛ ግምትና አክብሮት የነበረው ቢሆንም የተፃፈበት ዘመን በትክክል አይታወቅም።

ጥንታውያን የሃገራችን ምሁራን መፅሃፉ በንጉስ ሰሎሞን ዘመን እንደተፃፈ ያምኑ ነበር። ይህንን አስመልክቶ ኢዮብ ሉዶልፍ የተባለ ጀርመናዊ ምሁር ላቀረበላቸው ጥያቄ አባ ጎርጎርዮስ የተባሉ ኢትዮጵያዊ ምሁር በኖቬምበር 30/1650 አ.ም የፃፉለት ደብዳቤ እንደሚከተለው ይነበባል።

ባህቱ እሙር ውእቱ ከመ ተገብረ በዘመነ ኦሪት እመ አምነት ኢትዮጵያ በእግዚአብሔር ወተመጠወት ሕገ በመንግሥቱ ለእብነ እለሐኪም ንጉሠ ኢትዮጵያ ዘውእቱ ወልዱ ለሰሎሞን ንጉሥ ቀዳሚሆሙ ለነገሥታቲነ።

ትርጉም

ኢትዮጵያ በእግዚአብሄር ባመነችበትና ህግን በተቀበለችበት የነገስታቶቻችን መጀመሪያና የንጉስ ሰሎሞን ልጅ በሆነው በእብነ እለሃኪም ዘመን እንደሆነ ግን ይታወቃል።*

በመፅሃፉም ውስጥ ተመሳሳይ ሃሳብ ይነበባል።

ዘንተ ረከብኩ እመጻሕፍት ዘቤተ ሶፍያ ዘቁስጥንጥንያ። ወይቤልዎ እለ ህየ ሊቃነ ጳጳሳት አማንከ ዘተጽሕፈ እመዋዕለ ሰሎሞን ንጉሥ። ወይቤ ደማትዮስ ዘአንጾኪያ እወ ይመስል እስከ ዕለተ ሞቱ ለሰሎሞን ዘተጽሕፈ ወእምድኅረ ሞቱሰ ለሰሎሞን እምባዕዳን ነቢያት ዘተጽሕፈ እምሳሉ።

---

* Carl Bezold. **Kebre Nagest**. Die Herrlichkeit der Könige.(München: 1905 ) p.vii.

www.ethiopianorthodox.org

## ትርጉም

ይህንን ቁስጥንጥንያ ውስጥ በምትገኘው በሶፍያ ቤተ መፃህፍት አገኘሁ። በዚያ ያሉ ሊቃነ ጳጳሳትም "ይህ ነገር እውነት ከንጉስ ሰሎሞን ጀምሮ የተፃፈ ነውን?" አሉት። የአንፆኪያው ደማትዮስም "አዎን እስከ ሰሎሞን እለተ ሞት የተፃፈ ይመስላል። ቀሪውም ከሰሎሞን ሞት በሁዋላ በሌሎች ነቢያት ተፅፏል" አለ (ገፅ 106)።

ይሁንና በንጉስ ሰሎሞን ጊዜ ተፃፈ የሚለው አባባል በአሁኑ ጊዜ ተቀባይነት የለውም። ምክንያቱ በተለይም ግእዙ ክብረ ነገስት ስለ ክርስቶስ ልደት፣ በምስጋና ኢየሩሳሌም ስለመግባቱ፣ ስለይሁዳ፣ ስለ ክርስቶስ ስቅለት፣ ስለትንሳኤው፣ ስለእርገቱና ዳግም ምፅአቱ፣ ስለድንግል ማርያም ከታሪኩ በፊት (በትንቢት መልክ) ሳይሆን ከታሪኩ በሁዋላ እንደሚፅፍ በግልፅ ይታያል። ከዚህም በላይ ፀሃፊው የሃዲስ ኪዳን መፃህፍትን በምንጭነት ተጠቅሟል (የግርጌ ማስታዎሻውን ይመልከቱ)። እነዚህ ማስረጃዎች ክብረ ነገስት የዘመነ ኦሪት (የሰሎሞን ዘመን) መፅሃፍ እንዳልሆነ ያረጋግጣሉ። በተጨማሪም ጎርጎርዮስ ገባሬ መንክራት፣ ደማትዮስ ዘሮም ወይም ዘአንፆኪያ እና 318 አበው የመፅሃፉ አስረጅ ገፃተ-ባህርያት ሆነው ቀርበዋል። እነዚህ ሰዎች የአዲስ ኪዳን አባቶች እንደሆኑ ይታወቃል።

ጎርጎርዮስ ገባሬ መንክራት በቅድስናው ምክንያት ከፍተኛ ተደማጭነትና ተሰሚነት የነበረው የቤተ ክርስቲያን አባት ሲሆን 318 ሊቃውንት በ325 ዓ.ም. በነበረው የኒቅያ ጉባኤ የመጨረሻውን ውሳኔ የሰጡ ናቸው። የእነዚህ አባቶች ለመፅሃፉ አስረጂ ገፃተ-ባህርያት ሆኖ መቅረብ የመፅሃፉን ተአማኒነትና ክብደት ከፍ እንደሚያደርገው አያጠያይቅም።

በክርስትና ሃይማኖት ላይ መንፈሳዊና ሞራላዊ ስልጣን ባላቸው እንደ እነዚህ ባሉ አባቶች ስም መፃህፍትንና ቀኖናዎችን መፃፍ አዲስ ነገር አይደለም። ለምሳሌ እምነተ አትናቴዎስ በመባል የሚታወቀው ትምህርተ ቀኖና በዚህ ሁኔታ የተፃፈ ነው። "ክብረ ነገስት" እነዚህን አባቶች በአስረጅነት ሲጠቅስ በተዘዋዋሪ መፅሃፉ ከእነሱ በሁዋላ ለመዘጋጀቱ ፍንጭ ይሰጠናል። በተጨማሪም በ5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረውን የአብያተ ክርስቲያናት መለያየት በትክክል ከማወቁም በላይ የኢትዮጵያውያን ንጉስ አፄ ካሌብን፣ ልጃቸውን አፄ ገብረ መስቀልን፣ የናግራንና የኢትዮጵያን ጦርነትና የቢዛንታይኑን ንጉስ ዮስቲንን ስለሚጠቅስ (ገፅ148-149) የክብረ ነገስት ዝግጅት ከ7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በሁዋላ እንደሆነ ግልፅ ይሆናል።

"ክብረ ነገስት" የተፃፈው ከሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በሁዋላ ነው ብንልም ቅድመ ዘመነ ላሊበላ በቅብጢ ቋንቋ ለመኖሩና በዘመነ ላሊበላ ደግሞ አባልእዝና አበፈጠረግ በተባሉ ሰዎች አማካኝነት ከቅብጢ ወደ



አረብኛ መተርጎሙን ይገልፃል። ከአረብኛ ወደ ግእዝ የተረጎሙት ሊቅ ይህንን አስመልክቶ በአረብኛው ክብረ ነገስት ተፅፎ አገኘሁ ያሉትን እንደሚከተለው ቃል በቃል ጠቅሰውታል።

ወተብህለ በክታበ ዐረቢ አውፃእናሃ እምልሳነ ቅብጢ ለዐረቢ እመንበረ ማርቆስ ወንጌላዊ መምህር አበ ኩልነ ወአውፃእናሃ በ፬፻ወ፱ ዓመተ ምሕረት ውስተ ሀገረ ኢትዮጵያ በመዋዕለ ገብረ መስቀል ንጉሥ ወሰጓሁ ላሊበላ በመዋዕለ አባ ጊዮርጊስ ጳጳስ ጌር ወአስተተ እግዚአብሔር አውፅእታ ወተርጉሞታ ኀበ ነገረ ሐባሲ።

## ትርጉም

በአረብኛውም መፅሃፍም ከወንጌላዊውና የሁላችንም መምህር ከሆነው ከማርቆስ መንበር በአራት መቶ ዘጠኝ አመተ ምህረት የቅፅል ስሙ ላሊበላ በሆነው በንጉስ ገብረ መስቀል ዘመንና በቸሩ ጳጳሳችን በአባ ጊዮርጊስ ዘመን ከቅብጢ ቋንቋ ወደ አረብኛ ቋንቋ ተረጎምናት ተባለ(ገፅ 149)።

በሌላ በኩል መፅሃፉ ቀደም ሲል በቅብጢ ቋንቋ ተፅፎ መኖሩ ቢጠቀስም በማን እንደ ተፃፈ አይናገርም። ሆኖም በኢትዮጵያ አፈ ታሪክ መነሻነትና በግብፅ ፓትርያርኮች ትእዛዝ ሊሆን እንደሚችል ቀጥሎ ያለው ምንባብ ይጠቁማል።

ከዚያ በሁዋላ ከሰባቱ አንዱ ፓርሚናስ መጣ። እነሱንም አጠመቃቸው። ቀሳውስትና ዲያቆናትንም ሾመላቸው። ሊቀ ጳጳሳቸውም ለወንጌላዊው ማርቆስ ተጠሪ እንዲሆን ወሰነ። ከዚያ በሁዋላ የኦርቶዶክስ ሃይማኖትን በምድረ ኢትዮጵያ ተቀበሉ። ግዛቱም ከዳዊት እስከ ኣለም ፍፃሜ ይሆናል። ውዳሴና ምስጋና ጌትነትና ክብር እንዲሁም ስግደት ለስሉስ ቅዱስ ይገባል። በቀደሙት የግብፅ ቤተ ክርስቲያን አባቶች ዜና መዋእል የተገኘው ይህ ነው።

"ሊቀ ጳጳሳቸውም ለወንጌላዊው ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን መንበር ተጠሪ እንዲሆን ወሰነ" የሚለው በዝግጅቱ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን እጅ እንዳለበት ይጠቁማል።

የቅብጢው ክብረ ነገስት በላሊበላ ዘመነ መንግስት በ409* ዓ.ም. አባልእዝና አበፈጠረግ በተባሉ ሰዎች አማካኝነት ከቅብጢ ወደ አረብኛ

* 409 ዓ. ም. የሚለው ከላሊበላ ዘመነ መንግስት ጋር አይቀራረብም። ይልቁንስ ኣመተ ሂጅራ ይመስላል። ሂጅራ የሚጀምረው በ622 ዓ. ም. ነው። 622+409=1031 ይሆናል።

www.ethiopianorthodox.org

ከተተረጎመ በሁዋላ ወደ ግእዝ ሳይተረጎም ዘመናትን ማሳለፉ ተጠቅሷል። ለዚህም ምክንያቱ ፖለቲካዊ ሊሆን እንደሚችል ወደ ግእዝ የተረጎሙት ፀሃፊ ገምተዋል።

ወሶበ ኀለይኩ ዘንተ ለምንት ኢተርጕምዋ አበልዕዝ ወአበፈጠረግ እለ አውጽእዋ እቤ ዘንተ እስመ ወጽአት በመዋዕለ ዛጓ ወኢተርጕምዋ እስመ ትብል ዛቲ መጽሐፍ እለሰ ይነግሡ እለ ኢኮኑ እስራኤል ተዐድዎ ሕግ ውእቱ። ወሶበ ይከውን በመንግሥተ እስራኤል እምአውእፅእዋ ወተረክበት በናዝሬት።

ትርጉም

እግዚአብሄርም ወደ ኢትዮጵያ መምጣቷንና ወደ አበሻ ቋንቋም መተርጎሟን ችላ አሰኘ። እኔም ያወጧት አባልእዝና አበፈጠረግ ያልተረጎሟት ለምን ይሆን ብዬ ባሰብኩት ጊዜ በዘመነ ዛጓ ስለወጣችና እስራኤላውያን ሳይሆኑ መንገስ ህግን መተላለፍ ነው ስለ ምትል በዚሁ ምክንያት አልተረጎሟትም አልኩ። እስራኤላውያን በነገሱበት ወቅት ቢሆን ግን በተረጎሟት ነበር። በናዝሬትም በተገኘች(ገፅ 149-150)።

እንደ ፀሃፊው "ክብረ ነገስት" መንገስ የሚችሉ ሰሎሞናዊ ስርወ መንግስት ያላቸው ብቻ ናቸው ስለሚልና የዛጓ መንግስታትም ይህንን ስለማያሟሉ በእነሱ ዘመን ድረስ ወደ ነገረ ሃባሲ (ግእዝ) ሳይተረጎም ቆይቷል።

ሆኖም የዛጓ መንግስት ወድቆ ሰሎሞናውያን ስልጣን ሲይዙ ተርጓሚው ይስሃቅ በሌሎች ምሁራንና ያእቢከ እግዚእ በተባለ መስፍን እየተረዱ ወደ ግእዝ እንደ ተረጎሙት ወይም አስፋፍተው እንደ ፃፉት ገልፀዋል።

ወጸልዩ ላዕሌየ ለገብርክሙ ይስሐቅ ነዳይ። ወኢትሒሱኒ በእንተ ኢያርትዖ ነገረ ልሳን። እስመ ብዙኀ ጻመውኩ በእንተ ክብራ ለሃገረ ኢትዮጵያ በእንተ ፀአታ ለጽዮን ሰማያዊት ወበእንተ ክብረ ንጉሠ ኢትዮጵያ። እስመ አነሂ ተስእልክዎ ለመኮንን ርቱዕ ፍቁረ እግዚአብሐር ያዕቢከ እግዚእ። ወአፍቀረ ወይቤለኒ ግበር። ወገበርኩ እንዘ እግዚአብሐር ይረድአኒ ወኢፈደየኒ በከመ አበሳየ። ለገብርክሙ ይስሐቅ ጸልዩ። ወለእለ ጻመው ምስሌየ በፀአተ ዛቲ

---

ስለዚህ በ409 ሂ. ሂጅራ ቢባል 1031 ኣ.ም. ሊሆን ይችላል። ይሁንና በዚህም ሙሉ በሙሉ ስሌቱ ትክክል አይመጣም። ምክንያቱም እንደ ብዙዎቹ የታሪክ ሰዎች የላሊበላ ዘመነ መንግስት ከ1190-1225 ኣ.ም ነውና።



መጽሐፍ እስመ ተመንደብነ ፈድፋደ አነ፣ ወይምርሐነ አብ፣ ወሕዝበ ክርስቶስ፣ ወእንድርያስ፣ ወፊልጶስ፣ ወመሐሪ አብ፣ ይምሐሮሙ እግዚአብሐር በመንግሥተ ሰማያት ምስለ ኵሎሙ ቅዱሳን ወሰማዕት። ወይጽሐፍ ስሞሙ ውስተ መጽሐፈ ሕይወት። ለዓለመ ዓለም አሜን፣ ወአሜን።

ትርጉም

ለእኔም ለባሪያችሁ ለምስኪኑ ይስሃቅ ፀልዩልኝ። በቋንቋውም አለመቃናት አትንቀፉኝ። ስለ ኢትዮጵያ ክብር፣ ስለ ሰማያዊቷ ፅዮን መውጣትና ስለ ኢትዮጵያ ንጉስ ክብር ብዙ ደክሜአለሁና። እኔም ደግሞ ርቱእ ሃይማኖትና የእግዚአብሄር ወዳጅ የሆነውን ያእቢከ እግዚእን ለመንኩት። እሱንም ደስ አሰኘው። አድርግም አለኝ። እግዚአብሄርም እየረዳኝ ፈፀምኩት። እንደ ጥፋቴም አልከፈለኝም። ለእኔ ለባሪያችሁ ለይስሃቅና ይህችን መፅሃፍ ለማውጣት ከእኔ ጋር አብረው ለደከሙና አብረውም ለተቸገሩ ለይምርሃነ አብ፣ ለህዝበ ክርስቶስ፣ ለእንድርያስ፣ ለፊልጶስና ለመሃሪ አብ ፀልዩልን። እግዚአብሄር በመንግስተ ሰማያትና ከሌሎች ቅዱሳንና ሰማእታት ጋር ነፍሳቸውን ይማር። ስማቸውንም በመፅሃፈ ህይወት ይፃፍ። ለዘላለሙ አሜን(ገፅ 150)።

ግእዙን "ክብረ ነገስት" ከአረብኛ ወደ ግእዝ የተረጎሙት ሰው ይስሃቅ የተባሉ የአክሱም ንቡረ እድ እንደ ነበሩና የተተረጎመውም በአፄ አምደ ፅዮን ዘመን እንደ ሆነ ይነገራል። ምክንያቱም መፅሃፉ የሚያውቃቸውን የኢትዮጵያ ነገስታት ቆጥሮ አፄ አምደ ፅዮን ላይ ስለሚያቆምና ስሙ የተጠቀሰው ያእቢከ እግዚእ የተባለው መስፍንም የነበረው በአምደ ፅዮን ዘመን ስለሆነ ነው።

የግእዙ "ክብረ ነገስት" የአረብኛው ቅጅ እንደ ሆነ ብዙዎች ይስማማሉ። ስለ ተባለም ቀጥታ ትርጉም ግን አይመስልም። የአረብኛው "ክብረ ነገስት" በጣም አጭር ከመሆኑም በላይ እንደ ግእዙ "ክብረ ነገስት" ሰፋና ዘርዘር አድርጎ አይተርክም። የግእዙ "ክብረ ነገስት" በአንፃሩ በ117 ምእራፎች የተከፈለ ከመሆኑም በላይ ከአርእስቱም ውጭ በርካታ አርእስተ ጉዳዮችን ይዳስሳል። ይህም የሁለት መፃህፍት ድምር ያስመስለዋል።

ሆኖም በግእዙ "ክብረ ነገስት" ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ አረብኛ ቃላት ምሳሌ ጠቢቂ፣ መባርዲን፣ ሴሮህ፣ ቃህራ፣ አስቀሎባ፣ ተወንያ፣ ክታብ፣ ግረት፣ ቢሐት እና ሌሎችም ከአረብኛው ጋር ግኑኝነት እንዳለው ይጠቁማሉ።

ሁለቱ በሚገናኙበት ርእሰ ጉዳዮቹም ላይ አንድነቶች የመኖራቸውን ያህል ልዩነቶችም ይስተዋላሉ። ለምሳሌ አረብኛው "ክብረ ነገስት" በሰሎሞን ጥበብ ከገነት መጥቶ ቀንድ ይመስል የነበረውን የንግስተ ሳባን

www.ethiopianorthodox.org

የእግር ጥፍር ኣወለቀ ስለሚለው እንጨትም ሆነ ስለ ተጠቀሰው ጥፍር የግእዙ "ክብረ ነገስት" ኣያወሳም።

ይህንና ይህን ከመሳሰሉ ኣንዳንድ ልዩነቶች በቀር ሁለቱም "ክብረ ነገስቶች" በመሰረታዊው ትረካ ለምሳሌ የንጉስ ዳዊትንና የእስራኤልን ኣምላክ ቃል ኪዳን፣ ንግስተ ሳባ ንጉስ ሰሎሞንን ለመጎብኘት ወደ ምድረ እስራኤል በመሄድ የተጠቀሰው ቃል ኪዳን ወራሽ የሆነውን ዳዊትን መውለደን፣ ዳዊትም ኣባቱን ለመጎብኘት ወደ ምድረ እስራኤል መሄዱንና ታቦት ፅዮንና መንግስትን ይዞ መመለሱን፣ በኢትዮጵያም ላይ እሱና ዘሮቹ ለዘላም ስልጣን ያላቸው መሆናቸውን በመተረክ ይመሳሰላሉ። በተጨማሪም ንጉስ ሰሎሞን ኢትዮጵያዊቷን ንግስት በሚያስጠሙ ምግቦች እንዳጠመዳት ሁለቱም "ክብረ ነገስቶች" ይተርካሉ።

ኣንባብያን ተመልክተው በሁለቱ "ክብረ ነገስቶች" መካከል ያለውን ኣንድነትና ልዩነት በማገናዘብ የራሳቸውን ብያኔ ይሰጡ ዘንድ ቤትዞልድ ካርል የተባሉ ጀርመናዊ ምሁር ከፓሪስ ቤተ መፃህፍት ኣግኝተው ያሳተሙትን ኣረብኛ ክብረ ነገስት ከጀርመንኛ ወደ ኣማርኛ ተርጉመን በመፃፉ መጨረሻ ኣባሪ ኣድርገነዋል። ግእዙ "ክብረ ነገስት"ም እኒሁ ሰው ካሳተሙት የተወሰደ ነው።



## ስለ ፊደላት፣ ስርኣተ ነጥብና ኣሃዝ ኣጠቃቀም

በዚህ መፅሃፍ ፊደላትን በተመለከተ በግእዝና በኣማርኛው ምንባቦች ሁለት የተለያዩ ስልቶችን ተጠቅመናል። ግእዙ መሰረታዊውን የግእዝ የኣፃፃፍ ስልት እንዲጠብቅ የተደረገ ሲሆን ኣማርኛው ግን የቀድሞውን የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ኣካዳሚ ጉባኤ ውሳኔ እንዲከተል ተደርጓል። ለምሳሌ "መፅሃፍ" የሚለው ቃል በኣማርኛው "መፅሃፍ" ተብሎ የተሰጠ ሲሆን በግእዙ ግን "መጽሐፍ" ተብሏል። ይህ የሆነው ግን በዘፈቀደ ኣይደለም።

እንደሚታወቀው ኣንድን የፊደል ገበታ የሚጋሩት ግእዝና ኣማርኛ ለኣንድ ድምፅ ከኣንድ በላይ በሆኑ ፊደላት የሚወከሉበት ኣጋጣሚ ኣለ። ለምሳሌ ሀሃ፣ ሐሓ፣ እና ኀኃ፣ ስድስቱም ፊደላት ኣንድን ድምፅ ይወከላሉ። እንዲሁም ኣኣ፣ ዐዓ፣ ሰሠ፣ ጸፀ በኣማርኛ ተመሳሳይ ድምፅ ኣላቸው።

ይህንን ድግግሞሽ የቋንቋ ሳይንስ ምሁራን ኣይደግፉትም። እንደ እነሱ ኣስተያየት ለኣንድ ድምፅ የተለያዩ ፊደላትን መጠቀም ጊዜን፣ ጉልበትንና መዋእለ ንዋይን ከማባከን በቀር ጠቀሜታ የለውም። በመሆኑም የኣማርኛ ቋንቋ ኣንድ ኣይነት ድምፅ ካላቸው ፊደላት ውስጥ

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |

የተባሉትን ብቻ ለመጠቀምና እንዲለመዱ ለማድረግ እንዲሁም "ሀ" በ"ኸ"፣ "አ" በ"ኧ" ፋንታ እንዲተኩ በማለት ህፁፃንና ፍንፅቅ ከሚባሉት ፊደላት መካከልም ሗ፣ ሏ፣ ሟ፣ ሯ፣ ሷ፣ ቷ፣ ሿ፣ ቿ፣ ኗ፣ ኟ፣ ዟ፣ ዧ፣ ዷ፣ ጧ፣ ጯ፣ ጿ፣ ፏ የሚባሉትን ለመጠቀም ወስኖ ተመሳሳይ ድምፅ ያላቸው ሌሎች ፊደላት ግን በኣካዳሚው የስነ ፅሁፍ ስራዎች እንዳይገቡ የቀድሞው ኢትዮጵያ ቋንቋዎች ኣካደሚ (ዛሬ ኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል) ወስኗል። ይህም መፅሃፍ የተዘጋጀው በዚሁ ማእከል ስር ስለሆነ ይህንኑ ውሳኔ እንዲከተል ተደርጓል።

ይህ የኣካደሚው ውሳኔ ግእዙን ኣይመለከትም። ግእዙ ቀድሞውንም ቢሆን ለኣንድ ድምፅ ከኣንድ በላይ ፊደላት ኣልነበሩትም። እርግጥ ዛሬ ግእዙም እንደ ኣማርኛው ለኣንድ ድምፅ ሁለትና ከዚያም በላይ ፊደላት ያሉት ይመስላል። ይህ የሆነው ድምፃቸው ከግእዝ ተናጋሪዎች ጋር በመጥፋቱ እንጂ ከመጀመሪያውም ለኣንድ ድምፅ ሁለት ፊደላት ስለተቀረፁለት ኣልነበረም። ይህንንም የሚያረጋግጠው እነዚህ ድምፆች ኣሁንም ቢሆን በሌሎች ቋንቋዎች (ለምሳሌ በትግርኛ) መገኘትና የፊደሎቹ

www.ethiopianorthodox.org

መለዋወጥም የትርጉም ለውጥ ማምጣቱ ነው። ለምሳሌ በግእዝ "ፀሐይ ሠረቀ" ማለት "ፀሃይ ወጣ" ማለት ሲሆን "ፀሐይ ሰረቀ" ቢል ግን "ፀሐይ ሰረቀ" ማለት ይሆናል። እንዲሁም "ሰአሊ ሰአለ" ሲል "ኣማላጅ ኣማለደ" ማለት ሲሆን "ሰዐሊ ሰዐለ" ቢል ግን "ስእል ሳይ ስእል ሳለ" ማለት ይሆናል። የትርጉሙን ለውጥ ያመጡት ሠ እና ሰ፣ አ እና ዐ ናቸው። ለኣብነት ያህል እነዚህን ጠቀስን እንጂ ሌሎች በርካታ ምሳሌዎችን መደርደር ይቻላል። በዚህና በሌሎችም ምክንያቶች ግእዙ የቆየውን የኣፃፃፍ ስልቱን እንዲጠብቅ ተወስኗል።

በዚህ መፅሃፍም ግእዙ የቆየውን የአፃፃፍ ስልት እንዲጠብቅ የተቻለውን ያህል ጥንቃቄ የተደረገ ሲሆን ኣማርኛው ግን እንደተባለው በኣካዳሚው ውሳኔ መሰረት ኣዲሱን የኣፃፃፍ ስልት እንዲከተል ሆኗል።

ስለዚህ በግእዙ "እግዚኣብሔር" ተብሎ የተፃፈው በኣማርኛው "እግዚኣብሄር"፣ "ክብረ ነገሥት" የተባለው "ክብረ ነገስት" ተብሎ ቢፃፍና ኣንባብያን ግር እንዳይላቸው ኣስቀድመን እናሳስባለን።

ስርኣተ ንጥብን በተመለከተ የተከተልነው ከዚህ የተለየ ኣይደለም። እንደሚታወቀው ኣማርኛ የተለያዩ ስርኣተ ነጥቦችን ከውጭ ቋንቋዎች ተውሷል። ትእምርተ ጥቅስ("") የጥያቄ ምልክት (?).....፣ ቅንፍ ( ) ለምሳሌ ያህል የሚጠቀሱ ናቸው። በመሆኑም የአማርኛው ትርጉም እንደተለመደው እነዚህን ስርኣተ ነጥቦች እንዲያካትት የተደረገ ሲሆን ግእዙ ግን ከትውስት ነፃ በመሆኑ የተጠቀሱትን ስርኣተ ነጥቦች ኣላካተተም።

በተመሳሳይ ሁኔታ ኣማርኛ ኣለማቀፋዊ ባህርይ እየያዙ የመጡትን የኣረብኛ ኣሃዞች ቀስ በቀስ እየተለማመደ ከግእዝ ኣሃዞች ጎን ለጎን በመጠቀም ላይ ሲሆን ግእዝ ግን እነዚህን ኣሃዞች ኣያውቃቸውም። ቢሆንም ቁጥሩን ለማመልከት እነዚህን የኣረብኛ ኣሃዞች በግእዙም ላይ ተጥቅመናል። ምክንያቱም ከተጠቀምንበት ኮምፒውተር ኣንፃር እነዚህን ኣሃዞች መጠቀም ለስራችን ቅልጥፍና ጠቃሚ ሆኖ ስላገኘነው ነው። በመሆኑም የምእራፉን ቅደም ተከተል የሚያሳዩት ቁጥሮች ከዋናው ፅሁፍ እንደተገኘው በግእዝ ኣሃዝ (ምሳሌ ፩ ፪ ፫...) ተሰጥተዋል። የቁጥሩን ኣከፋፈል የሚያሳዩትና በእኛ ኣማካኝነት የተሰጡት ኣሃዞች ግን ለፍጥነት ሲባል በኣረብኛው ኣሃዞች (1፣2፣3...) ተሰጥተዋል።

ክብረ ነገስት በ117 ምእራፎች ይከፈላል። በምእራፍ የከፋፈሉት ደራስያኑ ሲሆኑ በበኩላችን እያንዳንዱ ምእራፍ በቁጥር እንዲከፈል ኣድርገናል። ይህም የግእዝንና የኣማርኛውን ትርጉም በትክክል ለማስተያየት ይጠቅማል በሚል ነው።

ክብረ ነገስት ቅዱሳት ማፃህፍትን በምንጭነት ተጠቅሟል። ይህንኑም ለማሳየት የግርጌ ማስታወሻ ተጥቅመናል። ኣልፎ ኣልፎ በጥያቄ ምልክት (?) የተዘለለ የግርጌ ማስታወሻ ኣለ። ይህም ለጊዜው የጥቅሱን ቦታ ኣላገኘነውም ማለት ነው።

## ምስጋና

የመፅሃፉን ረቂቅ በታይፕና በኮምፒዩተር ለፃፉት ለአቶ መልክአ ክርስቶስ ነቢዩ፣ ለወይዘሮ ስንታየሁ ዘለቀና ለወይዘሪት ትእግስት ግርማ፣ ለደፈ ስላሴ ዮሃንስና ለመሪጌታ ፅጌ ዘሪሁን፣ የግእዙን ፅሁፍ ላናበቡት ለቀሲስ ፈንታሁን ሙጬ፣ የኣማርኛውን ፅሁፍ ኣይተው ጠቃሚ ኣስተያየት ለሰጡት የማእከሉ ሰራተኞች ልባዊ ምስጋና እናቀርባለን።

www.ethiopianorthodox.org

## አርእስተ ነገር


| ምዕራፍ | | ገጽ |
|---|---|---|
| ፩ | በእንተ ክብረ ነገሥት | 1 |
| ፪ | በእንተ እበየ ነገሥት | 2 |
| ፫ | በእንተ መንግሥተ አዳም | 2 |
| ፬ | በእንተ ቅንአተ ቃየል | 2 |
| ፭ | በእንተ መንግሥተ ሴት | 3 |
| ፮ | በእንተ ኀጢአተ ቃየን | 3 |
| ፯ | በእንተ ኖህ | 4 |
| ፰ | በእንተ አይኅ | 4 |
| ፱ | በእንተ ኪዳነ ኖህ | 5 |
| ፲ | በእንተ ጽዮን | 5 |
| ፲፩ | ኀበ ኀብሩ ፫፻፲ወ፰ ርቱአነ ሃይማኖት | 6 |
| ፲፪ | በእንተ ከነአን፡ በእንተ ትዕቢተ ከነአን | 6 |
| ፲፫ | በእንተ አብርሃም በእንተ ፍቅረ አምላኩ ለአብርሃም | 7 |
| ፲፬ | በእንተ ኪዳነ አብርሃም | 8 |
| ፲፭ | በእንተ ይስሐቅ ወያዕቆብ | 8 |
| ፲፮ | በእንተ ሮቤል | 9 |
| ፲፯ | በእንተ ክብራ ለጽዮን | 9 |
| ፲፰ | ኀበ ኀብሩ አበው ጳጳሳት (በእንተ ዘኀብሩ ጳጳሳት) | 11 |
| ፲፱ | በእንተ ኀበ ተረክበት ዛቲ መጽሐፍ | 12 |
| ፳ | በእንተ ክፍለ ምድር | 12 |
| ፳፩ | በእንተ ነገሥተ ኢትዮጵያ | 12 |
| ፳ ፪ | በእንተ ታምሪን ነጋዲ | 13 |
| ፳፫ | ኀበ ገብአ ነጋዴ ኢትዮጵያ | 14 |
| ፳፬ | ኀበ ተደለወት ለሐዊር | 15 |
| ፳፭ | ዘከመ በጽሐት ኀበ ሰሎሞን ንጉሥ | 16 |
| ፳፮ | ኀበ ተናገረ ንጉሥ ምስለ ንግሥት | 17 |
| ፳፯ | በእንተ ገባራዊ | 18 |
| ፳፰ | ዘከመ አዘዛ ለንግሥት | 19 |
| ፳፱ | በእንተ ፫፻፲ወ፰ | 21 |
| ፴ | በእንተ ዘመሐለ ላቲ ንጉሥ ሰሎሞን | 22 |
| ፴ | ፴፩ በእንተ ወሀባ ትእምርተ ለንግሥት | 24 |
| ፴፪ | ዘከመ ወለደት ወበጽሐት ብሔራ | 24 |


## ማውጫ


| ምእራፍ | | ገፅ |
|---|---|---|
| ፩ | ስለ ነገስታት ክብር | 1 |
| ፪ | ስለ ነገስታት ልእልና | 2 |
| ፫ | ስለ ኣዳም መንግስት | 2 |
| ፬ | ስለ ቃየል ቅንኣት | 2 |
| ፭ | ስለ ሴት መንግስት | 3 |
| ፮ | ስለ ቃየን ሃጢኣት | 3 |
| ፯ | ስለ ኖህ | 4 |
| ፰ | ስለ ጥፋት ውሃ | 4 |
| ፱ | ስለ ኖህ ኪዳን | 5 |
| ፲ | ስለ ፅዮን | 5 |
| ፲፩ | ሃይማኖታቸው የቀና ፫፻፲፰ ሊቃውንት እንደ ተባበሩ | 6 |
| ፲፪ | ስለ ከነኣን | 6 |
| ፲፫ | ስለ ኣብርሃም | 7 |
| ፲፬ | ስለ ኣብርሃም ቃል ኪዳን | 8 |
| ፲፭ | ስለ ይስሃቅና ያዕቆብ | 8 |
| ፲፮ | ስለ ሮቤል | 9 |
| ፲፯ | ስለ ፅዮን ክብር | 9 |
| ፲፰ | ኣበው ጳጳሳት ስለ መተባበራቸውና ኣንድ ስለመሆናቸው | 11 |
| ፲፱ | ይህች መፅሃፍ ስለ ተገኘችበት | 12 |
| ፳ | ስለ ምድር ኣከፋፈል | 12 |
| ፳፩ | ስለ ንግሥተ አዜብ | 12 |
| ፳፪ | ስለ ነጋደው ታምሪን | 13 |
| ፳፫ | ነጋደው ወደ ኢትዮጵያ ስለ መመለሱ | 14 |
| ፳፬ | ለመሄድ እንደተዘጋጀች | 15 |
| ፳፭ | ከንጉስ ሰሎሞን ዘንድ እንደ ደረሰች | 16 |
| ፳፮ | ንጉስና ንግስት እንደ ተነጋገሩ | 17 |
| ፳፯ | ስለ ገበሬው | 18 |
| ፳፰ | ንግስቲቱን እንዳዘዛት | 19 |
| ፳፱ | ስለ ሶስት መቶ ኣስራ ስምንቱ | 21 |
| ፴ | ንጉስ ሰሎሞን እንደ ማለላት | 22 |
| ፴፩ | ለንግስቲቱ ምልክት እንደ ሰጣት | 24 |
| ፴፪ | እንደ ወለደችና ኣገሯ እንደ ደረሰች | 24 |


www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

፴፫ በእንተ ወረደ ንጉሠ ኢትዮጵያ 25
፴፬ በእንተ በጽሐ ብሔረ እሙ 26
፴፭ በእንተ ዘለአከ ንጉሥ ሰሎሞን መልእከ ኀይሉ ኀበ ወልዱ 28
፴፮ ኀበ ተራከበ ምስለ ወልዱ ንጉሥ ሰሎሞን 29
፴፯ በእንተ ተሰእሎ ሰሎሞን ለወልዱ 32
፴፰ መከረ ንጉሥ ይፈኑ ወልዶ ምስለ ደቂቆሙ 33
፴፱ እንገሥዎ ለወልደ ሰሎሞን 34
፵ እዘዞ ሳዶቅ ካህን ለዳዊት ንጉሥ 35
፵፩ በእንተ በረከተ ነገሥት 36
፵፪ በእንተ ፲ ቃላት 38
፵፫ ኀበ ተአዘዙ ደቂቀ እስራኤል 40
፵፬ ከመ ኢመፍትው ሐምየ ንጉሥ 41
፵፭ በእንተ ዘበከዩ ወመከሩ እለ ተፈነው 43
፵፮ በእንተ ዘከመ መከሩ በእንተ ጽዮን 44
፵፯ በእንተ መስዋእተ አዛርያስ ንጉሥ 45
፵፰ ኀበ አንስእዋ ለጽዮን 46
፵፱ ኀበ ባረኮ አቡሁ ለወልዱ 46
፶ ኀበ ተፋነወ ምስለ አቡሁ ወለህወት ሀገር 47
፶፩ ኀበ ዘይብሉ ለሳዶቅ ካህን ሑር ወአምጽእ ውእተ ልብሰ ዘላእሌሃ 49
፶፪ ኀበ ዘሐረ ሳዶቅ ካህን 50
፶፫ ተውህበ ሰረገላ ለኢትዮጵያ 50
፶፬ ኀበ ተነበየ ዳዊት ወተሳለማ ለጽዮን 52
፶፭ በእንተ ዘተፈስሑ ሰብአ ኢትዮጵያ 54
፶፮ በእንተ ግብአተ ሳዶቅ ካህን ውሂቦ ሞጻ 55
፶፯ በእንተ ውድቀተ ሳዶቅ ካህን 56
፶፰ ኀበ ተንስአ ሰሎሞን ይቅትሎሙ 56
፶፱ ኀበ ሐተቶ ለግብጻዊ ገብረ ፈርኦን 57
፷ ኀበ ለሐዋ ሰሎሞን ለጽዮን 58
፷፩ በእንተ ግብአተ ሰሎሞን ኢየሩሳሌም 61
፷፪ በእንተ ዘአውስአሙ ሰሎሞን 63
፷፫ ኀበ ኀብሩ አበይተ እስራኤል 64
፷፬ ኀበ አስሐተቶ ለሰሎሞን ወለተ ፈርኦን 65
፷፭ በእንተ ኀጢአተ ሰሎሞን 67

፴፫ የኢትዮጵያ ንጉስ እንደ ወረደ 25
፴፬ እናቱ አገር እንደ ደረሰ 26
፴፭ ንጉስ ሰሎሞን የሃይል አዘዡን ወደ ልጁ እንደ ላከ 28
፴፮ ንጉስ ሰሎሞን ከልጁ ጋር እንደ ተገናኘ 29
፴፯ ሰሎሞን ልጁን እንደ ጠየቀው 32
፴፰ ንጉሱ ልጁን ከልጆቻቸው ጋር ለመላክ እንደ ሞከረ 33
፴፱ የሰሎሞንን ልጅ እንደ አነገሱት 34
፵ ካህኑ ሳዶቅ ንጉስ ዳዊትን እንዳዘዘው 35
፵፩ ስለ ነገስታት በረከት 36
፵፪ አስሩ ቃላት 38
፵፫ የእስራኤል የሃይል ልጆች እንደ ታዘዙ 40
፵፬ ንጉስን ማማት እንዳይገባ 41
፵፭ የተላኩት እንዳለቀሱና እንደ መከሩ 43
፵፮ ስለ ጽዮን እንደ መከሩ 44
፵፯ ስለ አዛርያስና ስለ ንጉሱ መስዋእት 45
፵፰ ፅዮንን እንዳነሷት 46
፵፱ አባት ልጁን እንደ መረቀው 46
፶ ከአባቱ ጋር እንደ ተሰነባበቱና አገሪቱ እንዳለቀሰች 47
፶፩ ካህኑ ሳዶቅን ሂድና በላዩዋ ላይ ያለውን ልብስ አምጣ እንዳለው 49
፶፪ ካህኑ ሳዶቅ እንደ ሄደ 50
፶፫ ለኢትዮጵያ ሰረገላ እንደ ተሰጠ 50
፶፬ ዳዊት ትንቢት እንደ ተናገረና ፅዮንን እንደ ተሳለማት 52
፶፭ የኢትዮጵያ ሰዎች እንደ ተደሰቱ 54
፶፮ ካህኑ ሳዶቅ የበደል መስዋእት አቅርቦ ስለ መመለሱ 55
፶፯ ስለ ካህኑ ሳዶቅ ውድቀት 56
፶፰ ሰሎሞን ይገድላቸው ዘንድ እንደ ተነሳ 56
፶፱ ግብጻዊውን የፈርኦንን አገልጋይ እንደ መረመረ 57
፷ ሰሎሞን ለጽዮን እንዳለቀሰላት 58
፷፩ ሰሎሞን ወደ ኢየሩሳሌም ስለ መመለሱ 61
፷፪ ሰሎሞን እንደ መለሰላቸው 63
፷፫ የእስራኤል ታላላቆች እንደ ተባበሩ 64
፷፬ የፈርኦን ልጅ ሰሎሞንን እንዳሳተች 65
፷፭ ስለ ሰሎሞን ሃጢአት 67


www.ethiopianorthodox.org

| | | |
|---|---|---|
| ፷፮ | በእንተ ትንቢተ ክርስቶስ | 67 |
| ፷፯ | በእንተ ብካየ ሰሎሞን | 69 |
| ፷፰ | በእንተ መድኀኒትነ ማርያም | 71 |
| ፷፱ | በእንተ ስእለተ ሰሎሞን | 73 |
| ፸ | በእንተ ዘነግሠ ሮብአም | 75 |
| ፸፩ | በእንተ ማርያም ወለተ ዳዊት | 77 |
| ፸፪ | በእንተ ንጉሠ ሮም | 78 |
| ፸፫ | በእንተ ቀዳሚ ፍትሑ ለአረሚ ንጉሠ ሮም | 80 |
| ፸፬ | በእንተ ንጉሠ ምድያም | 81 |
| ፸፭ | በእንተ ንጉሠ ባቢሎን | 82 |
| ፸፮ | በእንተ ሰማእተ ሐሰት | 82 |
| ፸፯ | በእንተ ንጉሠ ፋርስ | 85 |
| ፸፰ | በእንተ ንጉሠ ሞአብ | 86 |
| ፸፱ | በእንተ አማሌቅ | 87 |
| ፹ | በእንተ ኢሎፍሊ | 88 |
| ፹፩ | ዘከመ ቀተሎ ወልደ ሶምሶን ለወልደ ንጉሠ ኢሎፍሊ | 89 |
| ፹፪ | በእንተ ርደተ አብርሃም ግብጽ | 90 |
| ፹፫ | በእንተ ንጉሠ እስማኤላውያን | 92 |
| ፹፬ | በእንተ ንጉሠ ኢትዮጵያ ዘከመ ገብአ ሀገሩ | 93 |
| ፹፭ | ኀበ ተፈስሐት ማክዳ ንግሥት | 93 |
| ፹፮ | በእንተ እንገሠቶ ማክዳ ለወልዳ | 94 |
| ፹፯ | በእንተ መሐሉ መኳንንተ ኢትዮጵያ | 94 |
| ፹፰ | በእንተ ዜነውዋ ለእሙ ዘከመ አንገሥዎ | 96 |
| ፹፱ | በእንተ ነገረቶሙ ንግሥት ለደቂቀ እስራኤል | 98 |
| ፺ | በእንተ ወደሳ አዛርያስ ለንግስት ወለሀገራ | 99 |
| ፺፩ | በእንተ ዘይበልኡ ንጹሕ ወርኩስ | 102 |
| ፺፪ | ኀበ ሐደሱ መንግሥቶ ለዳዊት | 103 |
| ፺፫ | ኀበ ዘአማሰኑ ሃይማኖተ ሮም | 104 |
| ፺፬ | በእንተ ቀዳሚ ፀብአ ንጉሠ ኢትዮጵያ | 105 |
| ፺፭ | ኀበ ገብረ ክብሩ ለንጉሠ ኢትዮጵያ | 106 |
| ፺፮ | በእንተ ትንቢት ዘክርስቶስ | 108 |
| ፺፯ | ኀበ አንጉርጕሩ እስራኤል | 111 |
| ፺፰ | በእንተ በትረ ሙሴ ወአሮን | 113 |
| ፺፱ | በእንተ ክልኤቱ አግብርት | 116 |
| ፻ | በእንተ እለ ተአደው መላእክት | 117 |
| ፻፩ | በእንተ ህላዌ ኩሉ | 121 |

| | | |
|---|---|---|
| ፷፮ | ስለ ክርስቶስ ትንቢት | 67 |
| ፷፯ | ስለ ሰሎሞን ልቅሶ | 69 |
| ፷፰ | ስለ መድሃኒታችን ማርያም | 71 |
| ፷፱ | ስለ ሰሎሞን ልመና | 73 |
| ፸ | ሮብኣም ስለመንገሱ | 75 |
| ፸፩ | ስለ ዳዊት ልጅ ስለ ማርያም | 77 |
| ፸፪ | ስለ ሮም ንጉስ | 78 |
| ፸፫ | ስለ ኣረማዊው የሮም ንጉስ የመጀመሪያ ፍርድ | 80 |
| ፸፬ | ስለ ምድያም ንጉስ | 81 |
| ፸፭ | ስለ ባቢሎን ንጉስ | 82 |
| ፸፮ | ስለ ሃሰት ምስክር | 82 |
| ፸፯ | ስለ ፋርስ ንጉስ | 85 |
| ፸፰ | ስለ ሞኣብ ንጉስ | 86 |
| ፸፱ | ስለ ኣማሌቅ ንጉስ | 87 |
| | ስለ ኢሎፍላውያን ንጉስ | 88 |
| ፹፩ | የሶሞሶን ልጅ የኢሎፍላውያንን ንጉስ ልጅ እንደ ገደለው | 89 |
| ፹፪ | ኣብርሃም ግብጽ ስለ መውረዱ | 90 |
| ፹፫ | ስለ እስማኤላውያን ንጉስ | 92 |
| ፹፬ | የኢትዮጵያ ንጉስ ወደ ኣገሩ እንደ ተመለሰ | 93 |
| ፹፭ | ንግስት ማክዳ እንደ ተደሰተች | 93 |
| ፹፮ | ማክዳ ልጅዋን እንዳነገሰች | 94 |
| ፹፯ | የኢትዮጵያ መኳንንት እንደ ማሉ | 94 |
| ፹፰ | እንዳነገሱት ለእናቱ እንደ አበሰራት | 96 |
| | ንግስቲቱ ለእስራኤል ልጆች እንደ ነገረቻቸው | 98 |
| | ኣዛርያስ ንግስቲቱንና ኣገሯን እንደ ኣመሰገናት | 99 |
| | ስለ ሚበሉት ማለት ንፁህና ርኩስ ስለሆነው | 102 |
| ፺፪ | የዳዊትን መንግስት እንዳደሱ | 103 |
| ፺፫ | የሮምን ሃይማኖት እንዳጠፉ | 104 |
| ፺፬ | የኢትዮጵያ ንጉስ የመጀሪያው ጦርነት | 105 |
| ፺፭ | የኢትዮጵያ ንጉስ ክብር እንደ ተባበረ | 106 |
| ፺፮ | ስለ ክርስቶስ ትንቢት | 108 |
| ፺፯ | እስራኤል እንዳጉረመረሙ | 111 |
| ፺፰ | ስለ ሙሴና ስለ ኣሮን በትር | 113 |
| ፺፱ | ስለ ሁለቱ ባሪያዎች | 116 |
| ፻ | የእግዚኣብሄርን ትእዛዝ ስለ ተላለፉ መላእክት | 117 |
| ፻፩ | ምን ጊዜም ስለ መኖር | 121 |


www.ethiopianorthodox.org

፻ወ፪ በእንተ ቀዳሚ 121
፻ወ፫ በእንተ አቅርንተ ምስዋዕ 124
፻ወ፬ በእንተ ታቦት ወነገረ ዕልዋን 125
፻ወ፭ በእንተ አሚነ አብርሃም 127
፻ወ፮ በእንተ ትንቢት በእንተ ምጽአቱ ለክርስቶስ 127
፻ወ፯ በእንተ በአቱ ኢየሩሳሌም በስብሐት 134
፻ወ፰ በእንተ እከየ ይሁዳ ዕልው 136
፻ወ፱ በእንተ ስቅለቱ 138
፻ወ፲ በእንተ ትንሳኤሁ 140
፻፲ወ፩ በእንተ ዕርገቱ ወዳግም ምፅአቱ 141
፻፲ወ፪ በእንተ ዘአርአዩ ነቢያት በሥጋሆሙ 143
፻፲ወ፫ በእንተ ሰረገላ ወመግረሬ ፀር 145
፻፲ወ፬ በእንተ ግብአታ ለጽዮን 146
፻፲ወ፭ በእንተ ቅስተ እስራኤል 147
፻፲ወ፮ በእንተ ሰረገላ ኢትዮጵያ 147
፻፲ወ፯ በእንተ ንጉሠ ሮምያ ወንጉሠ ትዮጵያ 148

፻፪ ስለ መጀመሪያ 121
፻፫ ስለ መሰዊያው ንዋየ ቅድሳት 124
፻፬ ስለ ዳግም ስለ ታሪክና ስለ ከሃዲዎች ነገር 125
፻፭ ስለ አብርሃም እምነት 127
፻፮ ስለ ክርስቶስ መምጣት የተነገረ ትንቢት 127
፻፯ ኢየሩሳሌም በምስጋና ስለ መግባቱ 134
፻፰ ስለ ከሃዲው ይሁዳ ክፋት 136
፻፱ ስለ ስቅለቱ 138
፻፲ ስለ ትንሳኤው 140
፻፲፩ ስለ እርገቱ ዳግመኛም ስለ መምጣቱ 141
፻፲፪ ነቢያት በስጋቸው እንዳሳዩ 143
፻፲፫ ስለ ሰረገላና መግረሬ ፀር 145
፻፲፬ ስለ ፅዮን መመለስ 146
፻፲፭ ስለ እስራኤል ወቀሳ 147
፻፲፮ ስለ ኢትዮጵያ ሰረገላ 147
፻፲፯ ስለ ሮም ንጉስና ስለ ኢትዮጵያ ንጉስ 148


www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

በአኰቴቱ ለእግዚአብሔር አብ አኃዜ ኲሉ፤ ወበወልዱ ኢየሱስ
ክርስቶስ ዘቦቱ ኲሉ ኮነ፣ ወዘእንበሌሁሰ አልቦ ዘኮነ[1]፣ ወበመንፈስ
ቅዱስ ጰራቅሊጦስ ዘይወፅእ እም አብ፤ ወይነሥእ እምወልድ[2] ፩
አምላክ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ[3] ነአምን ወንገኒ ለሥሉስ።

## ፩ በ እ ን ተ ክ ብ ረ ነ ገ ሥ ት

1 ፍካሬ ወዜና ዘ፫፻፲ወ፰ ርቱዓነ ሃይማኖት፣ በእንተ ክብር ወዕበይ
ወተድላ ዘከመ ወሀበ እግዚአብሔር ለደቂቀ አዳም፤ ወፈድፋድሰ
ዘበእንተ ዕበያ ወክብራ ለጽዮን ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር እንተ
ገባሪሃ ወኬንያሃ ለሊሁ በውስተ ጽርሐ መቅደሱ እምቅድመ ኲሉ
ፍጥረት መላእክት ወሰብእ።
2 እስመ በኅብረት ወበሥምረት ወበዕሪና ገብርዋ አብ ወወልድ ወመንፈስ
ቅዱስ ለጽዮን ሰማያዊት ለማኅደረ ስብሐቲሆሙ።
3 ወእምዝ ይቤ አብ ለወልድ ወለመንፈስ ቅዱስ ንግበር ሰብአ በአርአያነ
ወበአምሳሊነ።[4]
4 ወኀብሩ ወሠምሩ በዝ ምክር።
5 ወይቤ ወልድ አነ እለብስ ሥጋሁ ለአዳም።
6 ወይቤ መንፈስ ቅዱስ አነ አኀድር ውስተ ልበ ነቢያት ወጻድቃን።
7 ወዛቲ ኅብረት ወኪዳን ተገብረት በውስተ ጽዮን ማኅደረ
ስብሐቲሆሙ።
8 ወዳዊትኒ ይቤ፣
ተዘከር ማኅበረከ ዘአቅደምከ ፈጢረ።
ለመድኀኒተ በትረ ርስትከ።
በደብረ ጽዮን ዘኀደርከ ውስቴታ።[5]
9 ወገብሮ ለአዳም በዘዚአሁ አርአያ ወአምሳል።[6] ከመ ይንሥቶ ለሰይጣን
በእንተ ትዕቢቱ ምስለ ሠራዊቱ ወያቅሞ ለአዳም ተክለ ዚአሁ ምስለ
ኄራን ደቂቁ ለስብሐቲሁ።
10 እስመ ጕሉቅ ወምቱር ምክረ እግዚአብሔር እንተ ይቤ እከውን ሰብአ
ወአስተርኢ ለኲሉ ዘፈጠርኩ በሥጋ አትገሠሥ። ወበደኃሪ መዋዕል
በሥምረቱ ተወልደ በሥጋ እምዳግማዊት ጽዮን ዳግማዊ አዳም። ዘውእቱ
መድኀኒነ ክርስቶስ።
11 ዛቲ ይእቲ ምክሕነ ወሃይማኖትነ ተስፋነ ወሕይወትነ ጽዮን ሰማያዊት።

---

[1] ዮሐ.1፥3
[2] ዮሐ 15፥16
[3] ማቴ.28፥20
[4] ዘፍጥ.1፥26
[5] መዝ.74፥2
[6] ዘፍጥ.1፥27



ሁሉን የያዘ እግዚአብሄር አብን፣ ሁሉ በእርሱ በኩል የሆነውንና
ያለ እርሱ ምንም ምን ያልሆነ[1] ልጁን እየሱስ ክርስቶስንና ከአብ
የሚወጣና ከወልድ የሚነሳ[2] ጰራቅሊጦስ መንፈስ ቅዱስን በማመስገን፣
አንድ አምላክ ለሚሆን ለአብ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ[3] ለሶስቱም
በመገዛት እንጀምራለን።

## ፩ ስለ ነገስታት ክብር

1 እግዚአብሄር ለአዳም ልጆች ስለሰጠው ክብር፣ ልእልናና ደስታ
ይልቁንም ከፍጥረት ማለትም ከመላእክትና ከሰው ሁሉ በፊት
በመቅደሱ አዳራሽ ውስጥ እርሱ ራሱ እግዚአብሄር ጥበበኛዋና
ሰሪዋ ስለሆነ ስለ እግዚአብሄር ታቦተ ህግ ልእልናና ክብር
ሃይማኖታቸው የቀና የሶስት መቶ አስራ ስምንት ዜናና ትርጉም፤
2 አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ሰማያዊቷ ፅዮንን የመመስገኛቸው
ማደሪያ አድርገው በአንድነት በስምምነትና በእኩልነት ፈጥረዋታል።
3 ከዚህ በሁዋላ አብ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን "ሰውን በአርአያችንና
በምሳሌአችን እንፍጠር"[4] አላቸው።
4 በዚህም ምክር ተስማሙ።
5 ወልድ "እኔ የአዳምን ስጋ እለብሳለሁ" አለ።
6 መንፈስ ቅዱስም "እኔ በፃድቃንና በነቢያት ልብ አድራለሁ" አለ።
7 ይህችም አንድነትና ቃል ኪዳን የምስጋናው ማደሪያ በሆነች በፅዮን
ውስጥ ተደረገች።
8 ዳዊትም፣ አስቀድመህ የፈጠርሃትን ማህበርህን፣
የተቤዠሃትንም የርስትህን በትር፣
በእርስዋ ያደርህባትን የፅዮንን ተራራ አስብ።[5] አለ።
9 ሰይጣንን ስለ ትእቢቱ ከሰራዊቱ ጋር ያፈርሰው ዘንድና አዳምንም
ከደጋግ ልጆቹ ጋር በእርሱ ምትክ ያቆመው ዘንድ በእራሱ
አርአያና አምሳል ፈጠረው።[6]
10 "ሰው እሆናለሁ። ለፈጠርኩት ሁሉ እታያለሁ። በስጋም እዳሰሳለሁ"
ያለው የእግዚአብሄር ምክር የተወሰነና የተቆረጠ ነበርና በሁዋለኛው
ዘመን ዳግማዊ አዳም ከዳግማዊት ፅዮን በስጋ ተወለደ። እሱም
መድሃኒታችን ክርስቶስ ነው።
11 እሷም መመኪያችን፣ መታመኛችን፣ ተስፋችንና ህይወታችን ሰማያዊቷ
ፅዮን ናት።

---

[1] ዮሃ.1፥3
[2] ዮሃ.15፥16፥16፥14
[3] ማቴ.28፥20
[4] ዘፍጥ.1፥26
[5] መዝ 74፥2
[6] ዘፍጥ.1፥27

www.ethiopianorthodox.org

## ፩ በ እ ን ተ ዕ በ የ ነ ገ ሥ ት

1 ሀቡኬ ንግባእ ወነሐስበ ወንውጥን ዘናዐቢ ወናሐፅፅ እምነገሥተ ምድር በሕግ ወሥርዓት በክብር ወበዕበይ እምቀዳሚ እስከ ደኃሪ።

2 ተንሥአ ጎርጎርዮስ ገባሬ መንክር ዘተወድየ ውስተ ግብ በእንተ ፍቅረ ስምሀ ክርስቶስ ዐሠርተ ወኀምስተ ዓመተ ውስተ ምንዳቤ። ውእቱ ይቤ እንዘ ሀለውኩ ውስተ ግብ ኀለይኩ በእንተ ዝ ነገር ወበእንተ ዕበዱ ለንጉሠ አርማንያ።

3 ወእቤ መጠነ ሕሊናየ ምንት ዕበዮሙ በብዝኃ ሠራዊትኑ ወሚመ በክብረ ንዋየ ዓለም ወሚመ በብዝኀ ሚመተ አህጉር።

4 ወዘንተ ሐሊይየ ለለ ተረፈ ጸሎትየ የሀውከኒ ካዕበ ኀሊናየ። ወእኄሊ በእንተ ዕበየ ነገሥት ወአኀዝኩ እውጥን።

## ፪ በ እ ን ተ መ ን ግ ሥ ተ አ ዳ ም

1 ወእም አዳም አልዐልኩ ወእቤ ንጉሥ እግዚአብሔር በአማን ዘሉቱ ይደሉ ስብሐት።

2 ወእምታሕቴሁ ሜሞ ለአዳም ንጉሠ ላዕለ ኩሉ ዘፈጠረ።

3 ወበዕልወቱ አውፅአ እምገነት በጊጠተ ከይሲ በምክረ ዲያብሎስ።

4 ወበውእቱ ዜና ኀዘን ተወልደ ቃየን።

5 ወርእዮ አዳም ለቃየን ዕሡረ ገጽ ጸዋግ ራእዩ/ርእየቱ/ ኀዘነ።

6 ወካዕበ ተወልደ አቤል።

7 ወርእዮ አዳም ለአቤል ከመ ሠናይ ራእዩ ወፍሡሕ ገጹ ወይቤ ዝንቱ ወልድየ ወራሴ መንግሥትየ።

## ፫ በ እ ን ተ ቅ ን ዐ ተ ቃ የ ን

1 ወሶበ ልህቁ ኀቡረ ቀንዐ ላዕሌሁ ሰይጣን ወወደየ ይእተ ቅንሀተ ውስተ ልበ ቃየን።

2 ቀዳሚ ቅንሀቱ በእንተ ቃለ አቡነ አዳም ዘይቤ ዝ ውእቱ ብሩህ ገጽ ይከውን ወራሴ መንግሥትየ።

3 ወዳግምሰ ቅንሀቱ በእንተ እንቲ ዘሠናይ ራእያ እንተ ተወልደት ምስሌሁ ወተውህበት ለአቤል በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ይብዝኁ ወይምልዕዋ ለምድር።

4 ወእንተሰ ተወልደት ምስለ አቤል ትመስል ርእየቶ ለቃየል።

5 ወእስተኀለፈ አቡሆሙ ወወሀቦሙ።

## ፩ ስለ ነገስታት ልእልና

1 ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በህግና በስርኣት በክብርና ልእልና ከምድር ነገስታት የምንበልጥበትንና የምናንስበትን ለማነፃፀር እንጀምር ዘንድ ፍቀዱ።

2 ስለ ክርስቶስ ፍቅር ምስክርነት በጉድጓድ ውስጥ የተጣለውና አስራ ኣምስት ኣመት በችግር የነበረው ታምራት ኣድራጊው ጎርጎርዮስም ተነሳ። ኣለም። "እኔ በጉድጓድ ውስጥ ተጥዬ ሳለሁ ስለዚህ ነገርና ስለ ኣርማንያው ንጉስ ስንፍና ኣሰብኩ።

3 ህሊናየም ሊያስብ የሚችለውን ያህል የነገስታት ከፍታቸው በምንድን ነው? በሰራዊት ብዛት? በዚህ ኣለም ሃብት ባለፀግነት? ወይስ በተሾሙት ኣገር ብዛት ነው?" ኣልኩ።

4 "ከፀሎት በሚተርፈኝ ሰኣት ዘወትር ይህን እያሰብኩ ህሊናዬ ያውከኝ ነበር። ስለ ነገስታት ከብርም ኣስብ ነበር። ለመጀመርም ተነሳሁ።"

## ፪ ስለ ኣዳም መንግስት

1 ከኣዳም ከፍ ብየ ጀመርኩ። "በእውነት ምስጋና የሚገባው እግዚኣብሄር ንጉስ ነው" ኣልኩ።

2 ኣዳምንም በፈጠረው ሁሉ ላይ ከበታቹ ንጉስ ኣድርጎ ሾመው።

3 በከይሲ ሰይጣን ሸንገላና በዲያብሎስ ምክር በመካዱ ከገነት ኣወጣው ።

4 በዚህም የሃዘን ጊዜ ቃየል ተወለደ።

5 ኣዳምም ፊቱ የከፋ፣ መልኩ የጠፋ ሆኖ ኣየው። ኣዘነም።

6 ሁለተኛም ኣቤል ተወለደ።

7 ኣዳምም ኣቤል መልኩ ያማረ፣ ፊቱ የበራ መሆኑን ኣይቶ "የመንግስቴ ወራሽ ልጄ ይህ ነው" ኣለ።

## ፫ ስለ ቃየል ቅናት

1 በኣንድነት እያደጉ ሳሉ ሰይጣን ቀናበት። ይህችንም ቅናት በቃየል ልብ ጨመረ።

2 የመጀመሪያው ቅናቱ ኣባታችን ኣዳም "ይህ መልከ ብሩህ የመንግስቴ ወራሽ ይሆናል" ባለው ቃል ነው።

3 ሁለተኛው ቅናቱ ደግሞ መልከ መልካም ስለሆነችውና ከእሱ ጋር ስለተወለደችው ይበዙና ምድርን ይሞሏት ዘንድ እግዚኣብሄር ባዘዘው መሰረት ለኣቤል ስለተሰጠችው እህቱ ነበር።

4 ከኣቤል ጋር የተወለደችው ቃየልን ትመስል ነበር።

5 ኣባታቸውም ኣስተላልፎ ከቃየል ጋር የተወለደችውን ለኣቤል፣ ከኣቤል ጋር የተወለደችውን ለቃየል ሰጣቸው።

www.ethiopianorthodox.org

6 ወሣልስ ቅንዐቱ በእንተ ዘሦሁ ክልኤሆሙ ወተወክፈ እግዚአብሔር
መሥዋዕተ አቤል ወአስቈረረ መስዋዕቶ ለቃየን።[7]
7 ወበእንተዝ ቅንዐት ቀተሎ[8] እስመ ቀትለ እኁው እምቀዳሚ ተፈጥረ
በቅንዐተ ሰይጣን ላዕለ ደቂቀ አዳም።
8 ወሶበ ቀተለ እኁሁ ኮነ ርዑደ ወድንጉፀ ወምጉነ በኀበ አቡሁ ወበኀበ
እግዚአ።[9]
9 ወተወልደ ሴት።
10 ወርእዮ አዳም ይቤ ይእዜኬ ተሣሀለኒ እግዚአብሔር ወወሀበኒ ብርሃ
ገጽየ በንስሓ አቅርቦ ዋርስየ ዘንቱ።
ወውእቱሰ ቀታሊ ዋርስየ በ፲ ትውልድ ትደመሰስ ስሙ።

## ፭ በእንተ መንግሥተ ሴት

1 ወአዕረፈ አዳም።
2 ወነግሠ ሴት በጽድቅ። ወአዕረፈ ሴት።
3 ወነግሠ ሄኖስ። ወአዕረፈ ሄኖስ።
4 ወነግሠ ቃይናን። ወአዕረፈ ቃይናን።
5 ወነግሠ መላልኤል። ወአዕረፈ መላልኤል።
6 ወነግሠ ያሬድ። ወአዕረፈ ያሬድ።
7 ወነግሠ ሄኖክ በጽድቅ። ወፈርሆ ለእግዚአብሔር ወኀብአ ከመ
ኢይርአዮ ለሞት። ወሀሎ ንጉሥ በሥጋሁ በብሔረ ሕያዋን።
8 ወእምድኅረ ተከብተ ሄኖክ ነግሠ ማቱሳላ። ወአዕረፈ ማቱሳላ።
9 ወነግሠ ላሜህ። ወአዕረፈ ላሜህ።
10 ወነግሠ ኖኅ በጽድቅ። ወአሥመሮ ለእግዚአብሔር በኵሉ ግብሩ።

## ፮ በእንተ ኀጢአተ ቃየን

1 ወውእቱሰ ርጉም ቀታሌ እኁሁ ቃየን አብዝኃ ለእከይ።
2 ወዘርኡኒ ከማሁ እለ አምዕዕዎ ለእግዚአብሔር በእከየሙ ወአልቦሙ
ፍርሀተ እግዚአብሔር ቅድመ አዕይንቲሆሙ። ወኢኀለይዎ ከመ
ፈጣሪሆሙ። ወኢጸለዩ ኀቤሁ። ወኢተጋነዩ ወኢሰአልዎ ወኢተቀነዩ
ሎቱ በፍርሀት ዘእንበለ ዘይበልዑ ወይሰትዩ ወይዘፍኑ ወይትዋነዩ
በመሰንቆ ወበማኅሌት ወበዝሙት ዘእንበለ ሕግ ወዘእንበለ መሥፈርት
ወዘእንበለ ሥርዓት።
3 ወበዝኀ እከዮሙ ለደቂቀ ቃየን እስከ በትዕቢተ ዝሙቶሙ አግብአ
ዘርዐ አድግ ኀበ ፈረስ

---
[7] ዘፍጥ.4፥5
[8] ዘፍጥ.4፥8
[9] ዘፍጥ.4፥11



6 ሶስተኛው ቅናቱ ደግሞ ሁለቱም ስለ ሰውት መስዋእት ሁኖ
እግዚአብሄር የአቤልን መስዋእት ተቀብሎ የቃየልን መስዋእት
በመፀየፉ ነበር።[7]
7 በዚህም ቅናት ምክንያት ገደለው።[8] የወንድማማቾች መጋደል
ከመጀመሪያው በአዳም ልጆች ዘንድ በሰይጣን ቅናት ምክንያት
ነውና።
8 ወንድሙን በገደለ ጊዜ በአባቱና በጌታው ዘንድ ተንቀጥቃጭ፣
ድንጉጥና የተናቀ ሆነ።[9]
9 ሴትም ተወለደ።
10 አዳምም አይቶ "ዛሬ ይቅር አለኝ። በንስሃም ይህንን ወራሼን
በማቅረብ የፊቴን ብርሃን ሰጠኝ። ያ መካከለኛው ግን ወራሼን
ገደለ። ስሙም በዘጠነኛው ትውልድ ትደመሰሳለች" አለ።

## ፭ ስለ ሴት መንግስት

1 አዳምም ሞተ።
2 ሴትም በፅድቅ ነገሰ ። ሴትም ሞተ።
3 ሄኖስም ነገሰ። ሄኖስም ሞተ።
4 ቃይናንም ነገሰ። ቃይናንም ሞተ።
5 መላልኤልም ነገሰ። መላልኤልም ሞተ።
6 ያሬድም ነገሰ። ያሬድም ሞተ።
7 ሄኖክም በፅድቅ ነገሰ። እግዚአብሄርንም ፈራው። ሞትን እንዳያይ
ሰወረው። ንጉሱም ሄኖክ በብሄረ ህያዋን በህይወተ ስጋ አለ።
8 ሄኖክ ከተሰወረ በሁዋላም ማቱሳላ ነገሰ። ማቱሳላም ሞተ።
9 ላሜህም ነገሰ። ላሜህም ሞተ።
10 ኖህም በጽድቅ ነገሰ። እግዚአብሄርንም በስራው ሁሉ አስደሰተው።

## ፮ ስለ ቃየል ሃጢአት

1 የወንድሙ ገዳይ የሆነው ርጉሙ ቃየን ግን ክፋትን አበዛት።
2 በክፋታቸው እግዚአብሄርን ያስቆጡት ዘሮችም እንዲሁ። እግዚአብሄርን
መፍራት በአይናቸው ፊት አልነበረም። ፈጣሪያቸው መሆኑንም አላሰ
ቡም። ያለ ህግ፣ ያለ መጠንና ያለ ስራት ከሚበሉና ከሚጠጡ፣ በመሰ
ንቆና በእልልታ የዝሙት ዘፈን ከሚዘፍኑና ከሚጫወቱት በቀር ወደ
እርሱ አልፀለዩም። አላመሰገኑትም፣ አላመኑትም፣ አልተገዙለትምም።
3 የቃየል ልጆች በዝሙታቸው ትእቢት የአህያውን ዘር ወደ ፈረስ
እስኪመልሱና እግዚአብሄር ያላዘዘውን በቅሎም እስኪሆን ድረስ

---
[7] ዘፍጥ.4፥5
[8] ዘፍጥ.4፥8
[9] ዘፍጥ 4፥11

www.ethiopianorthodox.org

ወኮነ በቃለ ዘኢአዘዘ እግዚአብሔር በከመ እለ ይውህቡ ውሉዶሙ
መሃይምናን ለከሃድያን ወይከውኑ ውሉዶሙ ዘርዐ ገሞራ ርኩሳን
መንፈቆሙ ሠናይ ወመንፈቆሙ ዘርዐ እኩያን።
4 ወእለ ገብርዋ ለእኪት ጽኑሕ ደይኖሙ ወንቡር ጌጋዮሙ።

## ፯ በ እ ን ተ ኖ ኅ

1 ወኖኅሰ ጻድቅ ይፈርሆ ለእግዚአብሔር። ወየዐቅብ ጽድቀ ወዘነገርዎ
አበዊሁ ሕገ። እም አዳም ዐሥር ትውልድ ለሊሁ ኖኅ እንዘ ይዜክር
ወይገብር ሠናየ ወየዐቅብ ሥጋሁ እምዝሙት ወይጌሥጽ ደቂቆ ከመ
ኢይደመሩ ምስለ ደቂቀ ቃየን መግዕልይ* ዕቡይ ነፋቂ መንግሥት።
2 እስመ በምክረ ዲያብሎስ ዘአነረዓ ለእከይ ሖረ ወመሀሮሙ ኵሎ
ዘጸልአ እግዚአብሔር ትዕቢተ፣ ትዝኅርተ፣ ትውዝፍተ፣ ሐሜተ
ውዴተ፣ ወመሐላ በሐሰት። ወፈድፋደሰ በእከየ ዝሙቶሙ ዘእንበለ
ሕግ ወሥርዓት።ብእሲ ላዕለ ብእሲ ያረኩስ ቢጾ። ወአንስት ላዕለ
አንስት ይገብራ ሐሳረ።

## ፰ በ እ ን ተ አ ይ ኅ

1 ወኮነ ዝ ግብር እኩየ በቅድመ እግዚአብሔር። ወውእቱኒ ደምሰሶሙ
በማየ አይኅ ዘይቈርር እምነ አስሐትያ። አርኀወ ኆዋኀወ ሰማይ
ወወረደ አስራበ አይኅ ወተርኅወ አንቅዕት ዘመትሕተ ምድር።
ወተከሥተ አንቅዕተ አይኅ ላዕለ ምድር።
2 ወጠፍኡ ኃጥኣን እስመ አረሩ ፍሬ መቅሠፍቶሙ። ወኀልቁ
ምስሌሆሙ ኵሉ እንስሳ ወአራዊት።[10] እስመ ኵሎሙ ተፈጥሩ በእንተ
ፍሥሓ አዳም ወለክብሩ። ወቦ በእንተ ጽጋቡ። ወቦ በእንተ
ፍሥሓሁ። ወቦ በእንተ አስማት ለሰብሐ ፈጣሪሁ ከመ ያእምሮሙ
በከመ ይቤ ዳዊት ወኵሎ አግረርከ ታሕተ እገሪሁ።[11]
3 በእንቲኣሁ ተፈጥሩ። ወበእንቲኣሁ ኀልቁ ዘእንበለ ፰ ነፍስ ወእምነ
ንጹሕ እንስሳ ወአራዊት በበ፯ ፯ ወእምነ ርኩስ እንስሳ ወአራዊት
በበ፪ ፪።[12]

* መምዕላይም ይላል።
[10] ዘፍ.7፥21
[11] መዝ.8፥6
[12] ዘፍጥ.7፥2-3

- 4 -

ክፋታቸው በዛ። ይህም አማንያን ልጆቻቸውን ለከሃድያን እንደሚሰ
ጡና ልጆቻቸውም የረከሱ የገሞራ ልጆች እንዲሆኑ ማድረግ
ማለት ነው። ግማሹ መልካም ግማሹ ክፉ ዘሮች ማለት ነው።
4 ክፋትን የሚሰሩ ሁሉ መከራ ይጠብቃቸዋል። በደላቸውም
ተቀምጠላቸዋል።

## ፯ ስለ ኖህ

1 ፃድቁ ኖህ ግን እግዚኣብሄርን ይፈራ ነበር። ከኣዳም ጀምሮ
ኣስረኛ ትውልድ የሆነ ይህ ኖህ መልካሙን እያሰበና እያደረገ፣
ስጋውን ከዝሙት እየጠበቀ፣ ልጆቹም መሃላኛ ኩራተኛና
መንግስትን ሻች ከሆነው ከቃየል ልጆች ጋር እንዳይጨመሩ እየገሰ
ፀ ህግንና እውነትንም ሁሉ ይጠብቅ ነበር።
2 ምክንያቱም ቃየን የክፋት ምንጭ በሆነው በዲያብሎስ ምክር
ሄደልና። እግዚኣብሄር የጠላውን ትእቢትን፣ ኩራትን፣ ዋዛ ፈዛዛን፣
ሃሜትን፣ ሰብቅን፣ በሃሰት መማልን ከሁሉም ይልቅ ያለ ህግና
ያለ ስርኣት የሆነውን የዝሙትን ክፋት ሁሉ ኣስተምሯቸዋልና።
ወንድ በወንድ ላይ እያመነዘረ ጓደኛውን ያረክሳል። ሴት በሴት
ላይ እያመነዘሩ ሃሳር በደልንን ያደርጋሉ።

## ፰ ስለ ጥፋት ውሃ

1 ይህም ስራ በእግዚኣብሄር ፊት ክፉ ሆነ። ከበረዶ በቀዘቀዘ
የጥፋት ውሃም ኣጠፋቸው። የሰማይ በሮችንም ከፈተ። የጥፋት
ውሃ ጎርፍም ወረደ። በምድርም ላይ የጥፋት ውሃ ምንጮች
ተከፈቱ።
2 ሃጥኣንም የቅጣታቸውን ፍሬ ተቀብለዋልና ጠፉ። ከእነሱም ጋር
እንስሳትና ኣራዊት ሁሉ ኣለቁ።[10] ሁሉም ለኣዳም ደስታና ክብር
ተፈጥረዋልና። ለምግቡ የተፈጠሩ ኣሉ። ለደስታው የተፈጠሩ ኣሉ።
ዳዊት "ሁሉን ከእግሩ በታች ኣስገዛህለት"[11] ብሎ እንደተናገረው
ሊያውቃቸውና እግዚኣብሄር ይመሰገንባቸው ዘንድ ለስሞች ብቻ
የተፈጠሩ ኣሉ።
3 ስምንቱ ነፍስ ከሆኑ ሰዎችና ንፁሃን ከሆኑ እንስሳትና ኣራዊት
ከያንዳንዳቸው ሰባት ሰባት፣ ርኩስ ከሆኑት እንስሳትና ኣራዊት
ሁለት ሁለት[12] ሲቀር ሁሉም ስለ እርሱ ተፈጠሩ። ሁሉም በእሱ
ምክንያት ኣለቁ።

[10] ዘፍጥ.7፥21
[11] መዝ.8፥6
[12] ዘፍጥ.7፥2-3

www.ethiopianorthodox.org

## ፱ በእንተ ኪዳነ ኖኅ

1 ወእምዝ አዕረፈ ኖኅ ጻድቅ። ወነገሠ ሴም በጥበብ ወበጽድቅ።
እስመ ተባረከ በኀበ ኖኅ እንዘ ይብል ኩን እግዚአ ለአኀቲከ።[13]
2 ወለካምኒ ይቤሎ ኩን ገብረ ለአኀቲከ።[14]
3 ወለያፌትኒ ይቤሎ ተገበር ወተአዛዜ ኩን ለሴም ዋርስየ።[15]
4 ወካዕበ እምድኅረ አይኅኒ ኢኀደገ ተፃርሮቶሙ ዲያብሎስ ፀርነ
ለደቂቀ ኖኅ። አላ አንሥአ ለከንዓን ወልደ ካም ወኮነ መማዕልየ
ዘይነፍቅ መንግሥተ እምደቂቀ ሴም። እስመ ተካፈሉ ምድረ
ወእምሐሎሙ በስመ አምላኩ ከመ ኢይትዓደዉ ደወለ ቢጾሙ ወከመ
ኢይብልኡ ማውታ ወብትከ ወከመ ኢይዘምዉ ዘእንበለ ሕግ ከመ
ኢይትመዐየሙ ዳግመ በአይኅ።
5 ወኖኅኒ ተጋነየ ወሦዐ ወጸውዐ ወገዐረ ወበከየ። ወተናገሮ
እግዚአብሔር።
6 ወይቤ ኖኅ እመሰ ዳግመ ታማስና ለምድር በአይኅ ጠስየኒ
ምስሌሆሙ ለእለ ኀልቁ።
7 ወይቤሎ እግዚአብሔር አነ እትካየድ ምስሌከ ከመ ትንግሮሙ
ለደቂቅከ ከመ ኢይብልዑ ማውታ ወብትከ ወከመ ኢይዘምዉ
ዘእንበለ ሕግ ወአነሂ ከመ ኢያማስና ለምድር ዳግመ በአይኅ ወከመ
እሁቦሙ ለደቂቅከ ክረምተ ወሐጋየ ዘርዐ ወማእረረ ጸደየ ወመጸወ።[16]

## ፲ በእንተ ጽዮን

1 ወእምሕል በርእስየ ወበጽዮን ታቦተ ኪዳንየ እንተ ፈጠርክዋ
ለምሥሃል ወለመድኀኒተ ሰብእ ወአወርዳ በደኀሪ ለዘርከ ወእሠምር
መሥዋዕተ ደቂቅከ በዲበ ምድር ወትሄሉ ምስሌሆሙ ታቦተ ኪዳንየ
ለዓለም።
2 ወሶበ መጽአ ደመና ከመ ኢይፍርሁ ወኢይምሰሎሙ አይኅ አወርድ
እማኅደረ ጽዮን ቀስተ ኪዳንየ ዘይኬልላ ለታቦተ ሕግየ ዝውእቱ
ቀስተ ደመና።[17] ወሶበኒ በዝኀ ኀጢአቶሙ ወፈቀድኩ እትመዐየሙ
እዜክራ ለታቦተ ኪዳንየ ወእሬስያ ለቀስተ ደመና ወአአትት
መዐትየ።

---

[13] ዘፍጥ.9፥25
[14] ዘፍጥ.9፥26
[15] ዘፍ.9፥27
[16] ዘፍ.8፥21
[17] ዘፍ.9፥13



## ፱ ስለ ኖህ ኪዳን

1 ከዚህ በሁዋላ ፃድቅ ኖህ ኣረፈ። ኖህ "ለወንድምህ ጌታ ሁን"[13]
ብሎ መርቆታልና ሴም በጥበብና በእውነት ነገሰ።
2 "ካምንም ለወንድምህ ባሪያ ሁን"[14] ኣለው።
3 ያፌትንም "ስራ ለወራሼ ለሴም ታዛዥ ሁን"[15] ኣለው።
4 እንደገናም ጠላታችን ዲያብሎስ ከጥፋት ውሃ በሁዋላም የኖህ
ልጆችን መውጋቱን ኣልተወም። ከጥፋት ውሃ በሁዋላ የካም ልጅ
ከነኣንን ኣነሳሳው። መንግስትንም ከሴም ልጆች የሚፈልግ
ወንጀለኛ ሆነ። ምድርን ተካፍለዋል። የወንድሞቻቸውን ድንበር
እንዳይሻገሩ፣ የሞተና ያልታረደ እንዳይበሉ፣ ያለ ህግም
እንዳያመነዝሩ፣ በጥፋት ውሃም ዳግም እንዳይቀጣቸው በኣምላኩ
ስም ኣስማላቸው።
5 ኖህም ለኣምላኩ ተገዛ። መስዋእትም ኣቀረበ። የኣምላኩንም ስም
ጠራ። ጮሆም ኣለቀሰ። እግዚኣብሄርም ተናገረው።
6 ኖህም "ዳግመኛ ምድርን በጥፋት ውሃ የምታጠፋት ሲሆን ከጠፉት
ጋር ጨምረህ ኣጥፋኝ" ኣለ።
7 እግዚኣብሄርም "የሞተና ኣባሉ የተመታ እንዳይበሉ፣ ያለ ህግም
ዝሙት እንዳይሰሩ ለልጆችህ እንድትነግራቸው፣ እኔም ደግሞ
ምድርን ሁለተኛ በጥፋት ውሃ እንዳላጠፋት ለልጆችህም ክረምትንና
በጋን፣ ኣዝመራን፣ በልግን፣ መፀውንም እሰጣቸው ዘንድ ከኣንተ
ጋር ቃል ኪዳን ኣደርጋለሁ"[16] ኣለው።

## ፲ ስለ ፅዮን

1 "በራሴና ለመማለጃና ለሰዎች መድሃኒት በፈጠርኳት፣ በሁዋላም
ለዘርህ በማወርዳት፣ በምድር ላይ የልጆችህን መስዋእት
በምቀበልባት የቃል ኪዳን ታቦት ሆና ለዘላለሙ ከእነሱ ጋር
በምትኖር በቃል ኪዳኔ ታቦት በፅዮን እምላለሁ።
2 ደመናም በመጣ ጊዜ እንዳይፈሩና የጥፋት ውሃ እንዳይመስላቸው
ከፅዮን ኣዳራሽ የህግ ታቦቴን የሚጋርዳትን የቃል ኪዳኔን ቀስት
ኣወርዳለሁ። ይህም ቀስተ ደመና ነው።[17] ሃጢኣታቸውም በበዛና
ልቆጣቸውም በፈለግሁ ጊዜ የቃል ኪዳኔን ታቦት ኣስታውሳታለሁ።
ቀስተ ደመናዋንም ኣደርጋታለሁ። መኣቴንም ኣስወግዳታለሁ።

---

[13] ዘፍጥ.9፥25
[14] ዘፍጥ.9፥26
[15] ዘፍጥ.9፥27
[16] ዘፍጥ.8፥21-22
[17] ዘፍጥ.9፥13

www.ethiopianorthodox.org

ወእፌኑ ሣህልየ። ወአንሰ ኢይረስዕ ቃልየ ወኢይሔሱ ዘወጽአ
እምአፉየ ወለእመኒ ኀለፈ ሰማይ ወምድር ወቃልየሰ ኢየኀልፍ።[18]
3 አውሥእዎ ወይቤልዎ እለ ሀየ ሊቃነ ጳጳሳት ለብፁዕ ጎርጎርዮስ
ናሁኬ ይእዜ ለበውነ ጥዩቀ ከመ እምቅድመ ኲሉ ፍጥረት እመኒ
መላእክት ወእምቅድመ ሰማያት ወምድር ወእምቅድመ ምጽንዓታት
ወልጎታተ ባሕር ዘፈጠራ ለታቦተ ኪዳን። ዛቲ ይእቲ እንተ በሰ
ማያት ታንሶሱ ዲበ ምድር።

## ፲ወ፩ ኀበ ኅብሩ ፫፻፲ወ፰ ርቱዓነ ሃይማኖት

1 ወአውሥእዎ ወይቤልዎ እወ አማን ቀደመት ተፈጥሮ ታቦተ ኪዳን።
ወአልቦ ሐሰት ውስተ ቃልከ እሙን። ወርቱዕ ወጽድቅ ውእቱ
ወአልቦ ተውላጥ።
2 አቅዲሙሰ ለጽዮን ፈጠራ ለማኅደረ ስብሐቲሁ። ወምክረ ኪዳኑሰ
ዘይቤ እለብስ ሥጋ አዳም መሬታዊተ ወአስተርኢ ለኲሉ ዘፈጠርኩ
በእደየ ወበቃልየ። ወሶበሰ ኢወረደት ጽዮን ሰማያዊት ወሶበኒ
ኢለብሰ ሥጋ አዳም እመ ኢተርእየ እግዚአብሔር ቃል ወእመ ኢኮነ
መድኀኒተነ።
3 ስምዑ በአምሳል። ጽዮንሰ ሰማያዊት ተመሰለታ ለወላዲተ መድኅን
ማርያም። እስመ ሕንጽተ ጽዮን ወንቡራት ውስቴታ ፲ ቃላት ዘሕግ
እለ ጽሑፋት በእደዊሁ ወውስተ ከርሠ ማርያም ኀደረ ለሊሁ ፈጣሪ
ዘበእንቲኣሁ ኲሉ ኮነ።

## ፲ወ፪ በእንተ ከንአን /በእንተ ትዕቢተ ከንአን/*

1 ወከናአንሰ[19] ዘነፈቀ መንግሥተ እምደቂቀ ሴም ተአዲዎ መሐላ
ዘአበዊሁ ዘአምሐሎሙ ኖኅ።
2 ወደቂቀ ከናአንሰ ፯ ጽኑዓን።
3 ወነሥአ እምድረ ሴም አህጉረ ፯ ዐበይተ። ወሜሞሙ ሀየ ለደቂቁ።
4 ወከማሁ ካዕበ ክፍሉኒ ለርእሱ ገብረ።
5 ወበደኃሪ ተበቀሎሙ እግዚአብሔር ለደቂቀ ከናአን።
6 ወአውረሰ ምድሮሙ ለደቂቀ ሴም።
7 ወእሉ እለ ተዋረሱ ከናኒዎን ወፌርዜዎን ወአዌዎን ወኬጤዎን ወአሞሬዎን
ወኢያቡሴዎን ወጌርሴዎን እሉ እሙንቱ እለ ተኀየለ ከናአን እምዘርአ
ሴም።
8 እስመ ኢርቱዕ ተዓድዎ መንግሥት ወበሊዐ መሐላ ወበእንተዝ ጠፍኡ።
ወዝክሮሙኒ ኀልቀ በተዓድዎ ትእዛዝ ወአምልኮ ጣዖት ወሰጊድ ለእለ
ኢኮኑ አማልክተ።

[18]ማቴ.24፥35

* ከነዓን፡ ከነአን፡ ከናዓን ይላል



ይቅርታዬንም እልካለሁ። እኔም ቃሌን አልረሳም። ከአፌም
የወጣውንም አልዋሽም። ሰማይና ምድር ቢያልፍም ቃሌ ግን
አያልፍም"[18] አለ።
3 በዚያ የነበሩ ሊቃነ ጳጳሳትም ለብፁእ ጎርጎርዮስ መልሰው
"ከፍጥረትና ከመላእክት፣ ከምድርና ከሰማየ ሰማያት፣ ከባህሮቹ
ጥልቀት ሁሉ በፊት ታቦተ ፅዮንን እንደ ፈጠራት እነሆ ዛሬ
አስተዋልን። ይህችም በሰማያት ያለችውና በምድር ላይ የምትመላለሰ
ው ፅዮን ናት" አሉት።

## ፲፩ ሃይማኖታቸው የቀና ሶስት መቶ አስራ ስምንቱ አንድ እንደሆኑ

1 መልሰውም "አዎን በእውነት ታቦተ ኪዳን በመፈጠር ትቀድማለች።
በታመነ ቃልህም ውስጥ ሃሰት የለበትም" አሉት።
2 አስቀድሞ ፅዮንን የምስጋና ቤት አድርጎ ፈጠራት። መሬታዊ
የሆነችውን የአዳምን ስጋ እለብሳለሁ። በእጄና በቃሌ ለፈጠርኩት
ሁሉ እታያለሁ ስላለው የቃል ኪዳን ምክር ግን ሰማያዊቷ ፅዮን
ባልወረደች ኖሮ የአዳምንም ስጋ ባልለበሰ፣ እግዚአብሄር ቃልም
ባልታየ፣ መድሃኒትም ባልሆነ ነበር።"
3 ስሙ። "ሰማያዊቷ ፅዮን የመድህን እናት ማርያምን ትመስላታለች።
ፅዮን ተሰርታለችና። በእጁ የተፃፉ አስሩ የህግ ቃላትም በውስጧ
ተቀምጠዋልና። በማርያም ሆድ ውስጥም ሁሉ በእሱ በኩል የሆነ
ፈጣሪ አደረ።"

## ፲፪ ስለ ከነኣን[19]

1 ከነአን ግን ኖህ የአማላቸውን የአባቶቹን መሃላ ትቶ መንግስትን
ከሴም ልጆች ከፈለ።
2 ሰባቱ የከነኣን ልጆች ብርቱዎች ነበሩ።
3 ከሴም ምድር ሰባት ትልልቅ ሃገሮችን ወሰደ። ልጆቹንም እዚያ
ሾማቸው።
4 እንዲሁም ሁለተኛውንም ክፍል ለራሱ አደረገ።
5 በሁዋላ ግን እግዚኣብሄር የከነኣን ልጆችን ተበቀላቸው።
6 ምድራቸውንም ለሴም ልጆች አወረሰ።
7 እነዚሁም የተወረሱት ከናኔዎን፣ ፌርዜዎን፣ አዊዎን፣ ኬጤዎን፣
አሞሬዎን፣ ኢያቡሴዎንና ጌርጌሴዎን ናቸው።
8 መንግስትን መገልበጥና መሃላን መብላት ቅን አይደለምና በዚሁ
ምክንያት ጠፉ። ትእዛዝን በመተላለፍ፣ ጣኦትን በማምለክና አማልክት
ላልሆኑ በመስገድ መታሰቢያቸው ጠፉ።

[18] ማቴ.24፥35

[19] ዘፍጥ.10፥16

www.ethiopianorthodox.org

9 ወእምድኅረ ሞተ ሴም ነግሠ አርፋክስድ
10 ወእምድኅረ ሞተ አርፋክስድ ነግሠ ቃይናን።
11 ወእምድኅረ ሞተ ቃይናን ነግሠ ሳላ።
12 ወእምድኅሬሁ ነግሠ ዔቦር።
13 ወእምድኅሬሁ ነግሠ ፋሌቅ።
14 ወእምድኅሬሁ ነግሠ ራግው።
15 ወእምድኅሬሁ ነግሠ ሴሮህ።
16 ወእምድኅሬሁ ነግሠ ናኮር።
17 ወእምድኅሬሁ ነግሠ ታራ።
18 ወእሉሰ እንዘ ያሰግሉ ጣዖታተ ወየሐውሩ ኀበ መቃብረ አበዊሆሙ
ወይገብሩ ሥዕለ ዘወርቅ ወብሩር ወብርት ወይትናገሮሙ ጋኔን በውስተ
ውእቱ ሥዕለ አበዊሆሙ ወይብሎሙ እገሌ ወልድየ ሡዕ ሊተ ወልደከ
ዘታፈቅር። ወይዘብሑ ደቂቆሙ ወአዋልዲሆሙ ለአጋንንት
ወይከዕዉ ደመ ንጹሐ ለርኩሳን አጋንንት።

## ፲ወ፫ በእንተ አብራም /በእንተ ፍቅረ አምላኩ ለአብራም/

1 ወወለደ ታራ ወልደ። ወሰመዮ አብራም። ወሶበ ኮነ ሎቱ ፲ወ፪
ዓመተ። ወለአኮ አቡሁ ታራ ከመ ይሚጥ ጣዖተ።
2 ወይቤ አብራም ዝሰ ኢኮነ አምላክ ዘያድኅን። ወወሰደ ከመ ይሚጥ
ጣዖተ በከመ አዘዞ አቡሁ። ወይቤሎሙ ለእለ ይሠይጥ ሎሙ ቦኑ
ዘትሣየጡ ዘኢያድኅን አምላከ ዕፅ ወእብን ወኅፂን ወብርት ዘገብሮ
እደ ኬንያ። ወአበይዎ ለአብራም። እስመ ለሊሁ አርኰሶሙ
ለግልፍዋተ አቡሁ።
3 ወእንዘ የአትዎሙ ተግሕሠ እምፍኖት። ወአንበሮሙ ወነጸሮሙ
ወይቤሎሙ ቦኑ ዘትክሉ ገቢረ ዘእሴአለክሙ አነ ይእዜ። እመ ትክሉ
አብልዑኒ ኅብስተ አው አስትዩኒ ማየ። ወአልቦ ዘአውሥእዎ እስመ
አእባን ወዕፀው እሙንቱ።
4 ወጸዐሎሙ ወፀረፈ ላዕሌሆሙ። ወኢነበብዎ ወቦ ለዘጸፍዖ፣ ወቦ
ለዘረገዖ ወቦ ለዘወገሮ፣ ወሰበሮ በአእባን። ወይቤሎሙ እመሰ
ኢታድኅኑ ርእሰክሙ እምዘ ገፍዐክሙ ወኢታሐሥሙ ለዘአሕሠመ
ለክሙ በአይቴ ትሰመዩ አማልክተ። ወከንቱ እለ ያመልኩክሙ።
ወአንሰ አስተሐቀርኩክሙ ወኢትከውኑኒ አማልክትየ።
5 ወአርአየ ገጾ ለምሥራቅ። ወሰፍሐ እደዊሁ ወይቤ አምላኪየሰ ኩነኒ
አንተ እግዚአ ፈጣሬ ሰማያት ወምድር ፈጣሬ ፀሐይ ወወርኀ ፈጣሬ
ባሕር ወየብስ ገባሬ ሠርጕ ሰማይ ወምድር ዘያስተርኢ ወዘኢያስተርኢ
ገባሬ ኩሉ ኩነኒ አምላኪየ ወኪያከ ተአመንኩ ወባዕደሰ አልብየ
ዘእት አመን ዘእንበሌከ እምዮም።
6 ወእምዝ አስተርአዮ ሰረገላ ዘእሳት ዘይነድድ። ወፈርሀ አብራም
ወወድቀ በገጹ ውስተ ምድር።

- 7 -

9 ሴምም ከሞተ በሁዋላ አርፋክስድ ነገሰ።
10 አርፋክስድ ከሞተ በሁዋላም ቃይናን ነገሰ።
11 ቃይናን ከሞተ በሁዋላም ሳላ ነገሰ።
12 ከእሱም በሁዋላ ኣቤር ነገሰ።
13 ከእሱም በሁዋላ ፋሌቅ ነገሰ።
14 ከእሱም በሁዋላ ራግው ነገሰ።
15 ከእሱም በሁዋላ ሴኖህ ነገሰ።
16 ከእሱም በሁዋላ ናኮር ነገሰ።
17 ከእሱም በሁዋላ ታራ ነገሰ።
18 እነሱ ግን ጣኦታትን ሲያስጠነቁሉ ሳሉ ወደ ኣባታቸው መቃብር
ይሄዱ፣ የወርቅ፣ የብርና የብረት ስእልም ያስሉ ነበር። ጋኔንም
በዚሁ ስእል ኣድሮ ይናገራቸውና ልጄ እገሌ ሆይ የምትወደውን
ልጅህን ሰዋልኝ ይላቸው ነበር። እነሱም ሴቶችና ወንዶች
ልጆቻቸውን ለኣጋንንት ያርዱ፣ ንፁህ ደምንም ለርኩሳን ኣጋንንት
ይሰዉ ነበር።

## ፲፫ ስለ ኣብርሃም

1 ታራም ወንድ ልጅን ወለደ። ስሙንም ኣብራም ብሎ ጠራው። ኣስራ
ሁለት ኣመትም ሲሆነው ኣባቱ ታራ ጣኦትን ይሸጥ ዘንድ ላከው።
2 ኣብራምም "ይህስ የሚያድን ኣምላክ ኣይደለም" ኣለና ኣባቱ
እንዳዘዘው ይሸጥ ዘንድ ጣኦቶቹን ወሰደ። ለገዥዎቹም
"ከእንጨት፣ ከድንጋይ፣ ከነሃስና ከብረት የሰው እጅ የሰራውና
የማያድን ኣምላክ የሚገዛ ኣለን" ይላቸው ነበር። ራሱ የኣባቱን
ጣኦቶች ኣርክሷቸዋልና መግዛትንም እንቢ ኣሉት።
3 ሲመልሳቸውም ከመንገድ ፈቀቅ ብሎ ኣስቀመጣቸው። ኣትኩሮም
እያያቸው "እኔ ዛሬ የምለምናችሁን ማድረግ ይቻላችሁዋል?
ከቻላችሁ እንጀራ ኣብሉኝ ወይም ውሃ ኣጠጡኝ" ኣላቸው።
የመለሰለትም የለም።
4 እንጨቶችና ድንጋዮች ነበሩና ተዘባበተባቸው። በላያቸው ላይም
የስድብ ነገር ተናገረባቸው። ኣላናገሩትምም። በጥፊ ይመታቸውና
ከመሬትም ይጥላቸው ነበር። በድንጋይ የሰበረውም ነበር። እሱም
"ከሚገፋችሁ ራሳችሁን የማታድኑ ከፉ ለሰራባችሁ ክፉ የማትሰሩ
ከሆነ ስለምን ኣማልክት ትባላላችሁ? የሚያመልኳችሁም ከንቱዎች
ናቸው። እኔም ናቅሁዋችሁ። ኣማልክትም ኣትሆኑም" ኣለ።
5 ፊቱንም ወደ ምስራቅ ዞሮ እጆቹንም ዘረጋና "ኣቤቱ ኣምላኬ የሰ
ማያትና የምድር፣ የፀሃይና የጨረቃ፣ የባህሩና የየብሱ ፈጣሪ፣ የሰ
ማዩና የምድሩ ሽልማት ፈጣሪ፣ የምትታይና የማትታይ፣ የሁሉ
ፈጣሪ ኣንተ ኣምላክ ሁነኝ። ኣንተን ታመንኩ። ከዛሬ ጀምሮ ያለ
ኣንተ የምታመንበት ሌላ የለኝም" ኣለ።
6 ከዚህ በሁዋላ የሚነድ የእሳት ሰረገላ ታየው። ኣብራምም ፈራ።
በፊቱም ወደ ምድር ወደቀ።

www.ethiopianorthodox.org

7 ወአንሥአ ወይቤሎ ኢትፍራህ ቁም ርቱዐ ወአእተተ እምኔሁ
ፍርሀተ።[20]

## ፲ወ፬ በእንተ ኪዳነ አብራም

1 ወተናገሮ እግዚአብሔር ወይቤሎ ኢትፍራህ እምዮም ገብርየ አንተ።
ወአቀውም ኪዳንየ ምስሌከ ወምስለ ዘርዕከ እምድኅሬከ። ወአበዝኀ
ዘርዐከ ወአዐቢ ስመከ ፈድፋደ። ወአወርዳ ለታቦተ ኪዳንየ ዲበ
ምድር በ፷ ትውልድ እምድኅሬከ። ወታንሶሱ ምስለ ዘርዕከ
ወትከውን መድኅኒተ ለዘመድከ። ወእምድኅሬሁ እፌኑ ቃልየ
ለመድሀኒተ አዳም ወደቂቁ እስከ ለዓለም። ወይእዜኒ እሉ አዝማዲከ
ዐላውያን እበዩ አምልኮትየ በርትዕ። ወአንተሰ ዕለተ እምዕለት ከመ
ኢያስሕቱከ ነዐ ፃእ እምዛቲ ምድር ምድረ አበዊከ ውስተ ምድር
ዘአርዕየከ አነ ወእሁቦሙ ለዘርዕከ እምድኅሬከ።[21]
2 ወሰገደ አብራም ሊግዚአብሔር። ወተአዘዘ ለእምላኩ።
3 ወይቤሎ ይኩን ስምከ አብርሃም። ወወሀቦ ሰላመ ወዐርገ ውስተ
ሰማያት።
4 ወአብርሃምኒ አተወ ውስተ ማኅደሩ። ወነሥአ ለሣራ ብእሲቱ።
ወወጽአ እንዘ ኢይትመየጥ ኀበ አቡሁ ወእሙ ወቤቱ ወአዝማዲሁ።
ወመነነ በእንተ እግዚአብሔር። ወበጽሐ ውስተ ሀገረ ሳሌም።
ወኀደረ ህየ።ወነግሠ በጽድቅ።ወኢተአደወ እምትእዛዙ ለእግዚአብሔር።
5 ወእግዚአብሔር ባረኮ ፈድፋደ እስከ አጥረየ፲ወ፰* አግብርቲሁ እለ
ይቀውሙ ቅድሜሁ ጽኑዓን ወምሁራነ ጸብእ እለ ይገብሩ ፈቃዶ
እለ ይለብሱ ዲባጋተ ዘወርቅ ወየዐንቁ ብዝጋናተ ዘወርቅ ወይቀንቱ
ቅናታተ ዘወርቅ ወይትቄጸሉ አክሊላተ ዘወርቅ። ወቦሙ ይመውእ
ፀሮ።
6 ወአዕረፈ በክብር በእግዚአብሔር። ወኀየሰ ወተሞገሰ እምእለ
ቅድሜሁ። ኀየሰ ወከብረ ወተለዐለ።

## ፲ወ፭ በእንተ ይስሐቅ ወያዕቆብ

1 ወነግሠ ይስሐቅ ወልዱ። ወውእቱኒ ኢተዓደወ እምትእዛዙ
ለእግዚአብሔር። ወኮነ ንጹሐ በነፍሱ ወበሥጋሁ። ወአዕረፈ በክብር።

[20] ዘፍጥ.15፥1
[21] ዘፍጥ12፥1
* ፫፻፲ወ፰ መባል ነበረበት ዘፀ.14፥14



7 አነሳውና "አትፍራ፣ ቀጥ ብለህ ቁም" አለው። ፍርሃትንም
አስወገደለት።[20]

## ፲፬ ስለ አብርሃም ቃል ኪዳን

1 እግዚአብሄርም ተናገረው። "ከዛሬ ጀምሮ አንተ ባሪያዬ ነህና
አትፍራ። ቃል ኪዳኔን ከአንተና ከአንተም በሁዋላ ከዘርህ ጋር
አቆማለሁ። ዘርህን አበዛለሁ። ስምህንም ከፍ ከፍ አደርጋለሁ።
የቃል ኪዳኔንም ታቦት ከአንተ በሁዋላ በሰባት ትውልድ በምድር
ላይ አወርዳታለሁ። ከዘርህም ጋር ትመላለሳለች። ለዘመድህም
መድሃኒት ትሆናለች። ከዚያ በሁዋላም ለአዳምና ለልጆቹ ለዘላለሙ
መድሃኒት ይሆን ዘንድ ቃሌን እልካለሁ። እነሆ ዛሬም እነዚህ
ዘመዶችህ ከሃዲዎች ናቸው። እኔንም በትክክል ማምለክን እንቢ
ብለዋል። አንተ ግን ቀን በቀን እንዳያስቱህ ከዚህችም የአባቶችህ
ምድር ከሆነችው ሃገር እኔ ወደ ማሳይህ ምድር ውጣ። ከአንተ
በሁዋላ ለዘርህ እሰጣታለሁ"[21] አለው።
2 አብራምም ለእግዚአብሄር ሰገደ። ለአምላኩም ታዘዘ።
3 እሱም "ስምህ አብርሃም ይሁን" አለው። ሰላምታም ከሰጠው
በሁዋላ ወደ ሰማያት አረገ።
4 አብርሃምም ወደ ቤቱ ገባ። ምሽቱን ሳራንም ወሰደ። ወደ
አባቱና ወደ እናቱ ወደ ቤቱና ወደ ዘመዶቹም ሳይሄድ ወጣ።
ሁሉንም ነገር ስለ እግዚአብሄር ናቀ። ሃገረ ኢየሩሳሌምም ደረሰ።
እዚያም አደረ። በእውነትም ነገሰ። ከእግዚአብሄርም ትእዛዝ
አልተላለፈም።
5 እግዚአብሄርም በፊቱ የሚቆሙና ጠንካራ ጦረኞች የሆኑ፣ ፈቃዱን
የሚያደርጉ፣ የወርቅ ግምጃ የሚለብሱ፣ የወርቅ መታጠቂያ
የሚታጠቁ፣ የወርቅ ማርዳ የሚያስሩ፣ የወርቅ አክሊል የሚደፉና
በእነሱም ጠላቶቹን ድል የሚያደርጋቸው አስራ ስምንት*
ባሪያዎቹን እስከ ገዛ ድረስ እግዚአብሄር ፈፅሞ ባረከው።
6 በእግዚአብሄርም ሆኖ በክብር አረፈ። ከእሱም በፊት ከነበሩት
ተሻለ። ባለሟልም ሆነ። ተሻሻለ፣ ከበረ፣ ከፍ ከፍም አለ።

## ፲፭ ስለ ይስሃቅና ስለ ያእቆብ

1 ልጁ ይስሃቅም ነገሰ። እሱም ከእግዚአብሄር ትእዛዝ አልተላለፈም።
በነፍሱም በስጋውም ንፁህ ሆነ። በክብርም አረፈ።

[20] ዘፍጥ.15፥1
[21] ዘፍጥ.12፥1
* ሰስት መቶ አስራ ስምንት መባል ነበረበት።ዘፀ.14፥14

www.ethiopianorthodox.org

2 ወነግሠ ያዕቆብ ወልዱ። ወውእቱኒ ኢተዐደወ እምትእዛዙ
ለእግዚአብሔር። ወኮነ ብዙኀ ንዋዩ ወደቂቁ። ወባረኮ እግዚአብሔር
ወአዕረፈ በክብር።

## ፲ወ፩ በ እ ን ተ ሮ ቤ ል

1 ወእምድኅሬሁ ሮቤል በኵሩ ለያዕቆብ ተዐደወ ትዕዛዘ እግዚአብሔር።
2 ወፈለሰት መንግሥት እምኔሁ ወእምዘርዑ በእንተ ዘአርኰሰ ብእሲተ
አቡሁ እስመ ኢርቱዕ ተዐድዎ ሕግ ዘአዘዘ እግዚአብ.ሔር።[22]
3 ወረገሞ አቡሁ። ወተምዐ እግዚአብሔር።
4 ወኮነ ሕጹጸ እምአኀዊሁ። ወደቂቁ ኮኑ ዝልጉሳነ ወዕቡያነ። ወእንዘ
ለሊሁ በኵር ተሀይደ መንግሥት እምኔሁ።[23]
5 ወነግሠ ይሁዳ እኁሁ ዘይንእስ። ወበእንተዝ ተሰምየ ይሁዳ።
ወተባረከ ዘርዑ ወሠነየ መንግሥቱ ወተባረኩ ደቂቁ።
6 ወእምድኅሬሁ ነግሠ ፋሬስ ወልዱ። ውእቱኒ አዕረፈ።
7 ወነግሠ ኤሳሮም ወልዱ።
8 ወእምድኅሬሁ ነግሠ አርኒ ወልዱ።
9 ወእምድህሬሁ ነግሠ አራም ወልዱ።
10 ወእምድኅሬሁ ነግሠ አሚናዳብ ወልዱ።
11 ወእምድኅሬሁ ነግሠ ነአሶን ወልዱ።
12 ወእምድኅሬሁ ነግሠ ሳላ ወልዱ።
13 ወእምድኅሬሁ ነግሠ ባየስ ወልዱ።
14 ወእምድኅሬሁ ነግሠ ኢዮቤድ ወልዱ።
15 ወእምድኅሬሁ ነግሠ እሤይ ወልዱ።
16 ወመንግሥት ዘእቤ በረከተ አብ ላዕለ ወልድ ከመ ይትባረክ
በሠናይ።
17 ወመንግሥትሰ ላዕለ እሥራኤል እምድኅረ ሞተ እሤይ ነግሠ ዳዊት
በጽድቅ ወበርትዕ ወበየውሀት።

## ፲ወ፪ በ እ ን ተ ክ ብ ራ ለ ጽ ዮ ን

1 ወለጽዮንሰ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር አቅዲሙ ሰማየ ሣረረ።
ወሠምረ ትኩን በምድር ማኅደረ ስብሐቲሁ ፈቂዶ አውረዳ
ለምድር።
2 ወወሀቦ ለሙሴ በአርአያ ይግበራ። ወይቤሎ ግበር ታቦተ እምዕፀ
ዘኢይነቅዝ። ወትለብጦ በወርቅ ንጡፍ። ወታነብር ውስቴታ ቃለ

22 ዘፍጥ.35፡22፡49፡4
23 1ዜ.መ.5፡1



2 ልጁ ያእቆብም ነገሰ። እሱም ከእግዚኣብሄር ትእዛዝ ኣልተላለፈም።
ብዙ ሃብትና ብዙ ልጆችም ሆኑለት። እግዚኣብሄርም ባረከው።
በክብርም ኣረፈ።

## ፲፩ ስለ ሮቤል

1 ከእሱም በሁዋላ የያእቆብ የበኩር ልጅ የእግዚኣብሄርን ትእዛዝ
ተላለፈ።
2 እግዚኣብሄር ያዘዘውን ህግ መተላለፍ ቀና ነገር ኣይደለምና
የኣባቱን ምሽት በማርከሱ[22] መንግስት ከእሱና ከዘሩ ተወሰደች።
3 ኣባቱም ረገመው። እግዚኣብሄርም ተቆጣው።
4 ከወንድሞቹም ሁሉ ያነሰ ሆነ። ልጆቹም እከካሞችና ትቢተኞች
ሆኑ። እርሱም በኩር ሆኖ ሳለ መንግስቱ ከእርሱ ተወሰደች።[23]
5 ትንሹ ወንድሙም ይሁዳ ነገሰ። ስለዚህም ይሁዳ ተባለ። ዘሩም
ተባረከ። መንግስቱም ኣማረ። ልጆቹም ተባረኩ።
6 ከእሱም በሁዋላ ልጁ ፋሬስ ነገሰ። እሱም ኣረፈ።
7 ልጁም ኤስሮም ነገሰ።
8 ከእሱም በሁዋላ ልጁ እርኒ ነገሰ።
9 ከእሱም በሁዋላ ልጁ እራም ነገሰ፤
10 ከእሱም በሁዋላ ልጁ ኣሚናዳብ ነገሰ።
11 ከእሱም በሁዋላ ልጁ ነኣሶን ነገሰ።
12 ከእሱም በሁዋላ ሳላ ነገሰ።
13 ከእሱም በሁዋላ ልጁ ባኦስ ነገሰ።
14 ከእሱም በሁዋላ ልጁ ኢዩቤድ ነገሰ።
15 ከእሱም በሁዋላ ልጁ እሴይ ነገሰ።
16 መንግስትም ያልኩት የተባረከ ይሆን ዘንድ ኣባት ለልጁ የሚሰ
ጠውን ቡራኬ ነው።
17 • በእስራኤል ላይ የነበረው መንግስት ግን እሴይ ከሞተ በሁዋላ
ዳዊት በእውነት በትክክልና በየዋህነት ነገሰ።

## ፲፪ ስለ ፅዮን ክብር

1 የእግዚኣብሄር ታቦተ ህግ ለሆነችው ለፅዮን ግን ኣስቀድሞ ሰማይን
ሰራ። በምድርም የምስጋና ማደሪያ ትሆነው ዘንድ ወደደ።
ፈቅዶም ወደ ምድር ኣወረዳት።
2 ለሙሴም የሚሰራበትን ኣምሳል ሰጠው። "ታቦትንም ከማይነቅዝ
እንጨት ትሰራለህ። በጠራ ወርቅም ትለብጠዋለህ። በውስጧም
ህጌን ይጠብቁ ዘንድ በሁለት የቃል ኪዳን ፅላቶች ላይ በእጆቼ

22 ዘፍጥ.35፡22፡49፡4
23 1ዜ.መ.5፡1

www.ethiopianorthodox.org

ሕግ ዘኪዳን ዘጸሐፍኩ በአጻብዕየ ከመ ይዕቀቡ ሕግየ ክልኤ ጽላተ
ዘኪዳን።[24] ወሰማያዊትኒ ወመንፈሳዊት ውስቴታ ዘኀብራ ወግብራ
ነኪር ትመስል ጥልማ ወውካይ ወወራውሬ ወዘውሀር ወበሉረ
ወብርሃነ ወተሀይድ አዕይንተ ወትከብት ወትሰልብ ልበ።
3 እንተ በሕሊና እግዚአብሔር ተገብረት ወአኮ በእደ ኬንያ ዘሰብእ
አላ ለሊሁ ፈጠራ ለማኅደረ ስብሐቲሁ።
4 ወመንፈሳዊት ይእቲ። ወምልዕተ ምሕረት ሰማያዊት ይእቲ።
ወምልዕተ ብርሃን እግዓዚት ይእቲ። ወማኅደረ መለኮት ዘበሰማያት
ማኅደራ ወበምድር ታንሶሱ። ወምስለ ሰብእ ተኀድር ወምስለ
መላእክት ሀገሪተ ሰብእ መድኀኒት ወለመንፈስ ቅዱስ ማኀደር።
ወውስቴታኒ ጎሞር ዘወርቅ ስፉር መና ዘወረደ እምሰማያት ወበትረ
አሮን እንተ ጸገየት እምድኅረ የብስት ዘእንበለ ይስቅይዋ ማየ።
ወውእቱኒ ሰበረ ክልኤተ ስብረተ። ወኮነት ሠለስተ በትረ እንዘ
አሐቲ ይእቲ።
5 ወቀፈላ በወርቅ ንጡፍ። ወረሰየ ላቲ መጻውረ ወመማስጠ
ወመማስቀ። ወይጸውርዋ ቅድመ ሕዝብ እስከ ያበውእዋ ምድረ
ርስት እንተ ይእቲ ኢየሩሳሌም ሀገረ ጽዮን።
6 ወእንዘ ተዐዱ ዮርዳኖስ ወይጸውርዋ ካህናት ቆመ ማይ ከመ
አረፍት እስከ የዐዱ ኩሉ ሕዝብ። ወእምድኅረ ዐደዉ ኩሉ ሕዝብ
ዐደዉ ካህናት ጸዊሮሙ ታቦተ። ወአንበርዋ ውስተ ሀገረ ይሁዳ
ምድረ ርስት።
7 ወተመልአኩ ነቢያት በውስተ ደብተራ ስምዕ ላዕሌሆሙ ለደቂቀ
እስራኤል።
8 ወካህናትኒ ይጸውሩ ኤፉደ ከመ ይትለአኩ ለደብተራ መርጡል።
9 ወሊቃነ ካህናትኒ የዐርጉ መሥዋዕተ ከመ ያስተስርዩ በእንተ
ኃጢአቶሙ ወእምዝ በእንተ ኃጢአተ ሕዝብ።
10 ወእዘዞሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን ከመ ይግበሩ ንዋየ
ቅድሳት ለደብተራ ስምዕ ዘይሠራዕ በውስተ ቅድስተ ቅዱሳን ንዋየ
ወርቅ ጸሀራተ ወጽዋዐተ ኩሳኩሳተ ወጠረጴዛተ ሰቃስቃተ ወአርእስተ
አዕማዳት ቀናዲለ ወመሳክየ ወመሳቅየ መኃትወ ወመሳውረ መራናተ
ወመማስጠ አእያገ ወአብሕርተ ዲባጋተ ወአልባሰ አክሊላተ
ወአክሚማተ ደርከኖ ወመጺጺተ ብሳጣተ ወኀብረ ከብድ ዕፍረተ
ዘቅብዐ ክህነት ወመንግሥት ወያክንተ ወሜላተ ነተ ክውበ ወቢሱሰ



የፃፍኩትን የኪዳን ህግ ቃል ታስቀምጣለህ።[24] በውስጧ ያለው
የቀለሟ አይነትና ስራዋ ግሩም ድንቅ የሆነችው ሰማያዊቷና
መንፈሳዊቷ ጥልማ የተባለውን ውሃ መልክ እንቁ፤ ወራውሬ
የተባለውን ብሩህና ነጭ እብነ በረድ፤ ዘውሃር የተባለውን እንቁና፤
ብሉር የተባለውን ብርጭቆ መልክ እንቁና ብርሃንን ትመስላለች።
አይንን ታንፀባርቃለች፤ ልብን ትመስጣለች" አለው።
3 በእግዚአብሄር አሳብ ተሰራች እንጂ በተጠባቢ ሰው እጅ
አይደለም። የምስጋናውን ቤት እሱ ራሱ ፈጠራት።
4 መንፈሳዊት ናት። ምህረት የተሞላች ሰማያዊት ናት። ብርሃንን
የተሞላች እመቤት ናት። በሰማያት የሚኖር የመለኮት ማደሪያ
ናት። በምድር ትመላለሳለች። ከሰዎች ጋር ታድራለች።
ከመላእክትም ጋር እንዲሁ። መድሃኒት የሆነች የሰዎች አገር ናት።
የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያም ናት። ከሰማያት የወረደ መና የተሰ
ፈረባት የወርቅ ቀለምሻሽና ከደረቀች በሁዋላ ውሃ ሳያጠጧት
ያበበች የአሮን በትር በውስጧ አሉ። እሱም ሁለት ጊዜ
ሰበራት። አንድም ሳለች ሶስት ብትሮችን ሆነች።
5 በንፁህ ወርቅም ለበጣት። መሸከሚያዎቿን (መሉጊያዎችን)
ቀልፎችንና ጥርቦችን አደረገላት። ምድረ ርስት ማለትም የፅዮን
ሃገር ኢየሩሳሌም እስኪያገቧት ድረስም በህዝብ ሁሉ ፊት
ይሸከሟት ነበር።
6 ዮርዳኖስ ስትሻገርና ካህናቱም ሲሸከሟት ህዝቡ እስኪሻገሩ ድረስ
ውሃው እንደ ግድግዳ ሆኖ ቆመ። ህዝቡ ሁሉ ከተሻገሩ በሁዋላ
ካህናቱም ታቦቷን ተሸክመው ተሻገሩ። ምድረ ርስት በሆነው
በይሁዳ ሃገርም አስቀመጧት።
7 ነቢያትም በምስክሩ ድንኳን ውስጥ በእስራኤል ልጆች ላይ አለቃ
ሆነው ተሾሙ።
8 ካህናት በመሰብሰቢያው ድንኳን ውስጥ ይላኩ ዘንድ ኤፉድ ይለብሳሉ።
9 የካህናት አለቆችም ስለ ሃጢአታቸውና ከዚያም በሁዋላ ስለ ህዝቡ
ሃጢአት ያማልዱ ዘንድ መስዋእትን ያሳርጋሉ።
10 እግዚአብሄርም በምስክሩ ድንኳን በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ
የሚቀመጡትን ከወርቅ የሚሰሩ አፈ ድስቶችን፤ ፅዋና
ኩስኩስቶችን፤ ጠረጴዛዎችን፤ ከብረት ተታቶ እንደ አሳ መረብ
ሆኖ የሚሰራውን መሰዊያ፤ የምሰሶዎችን መደምደሚያ፤ የዘይቱን
ማብሪያ፤ ማንቆርቆሪያውን (ማጠጫ)፤ መቅረዙን፤ የመቅረዙን
መከደኛ፤ ማብሪያውን፤ ቁልፉን፤ ኩሬዎችንና ባህሮችን፤ ግምጃዎችን፤
አልባሳቱን፤ አክሊሉችን፤ የክንድ ልብሶችን፤ ሃምራዊ ልብሶችን፤ ሰ
ማያዊ አረብ መጋረጃዎችን፤ የጥቁር ቀዮችንም (መጋረጃዎች)፤
ለክህነትና ለመንግስት የሚሆነውን ሽቱ፤ ከሰማያዊ (ያክንት)፤ ከጥሩ
ሃር (ሜላት)፤ ከቀይ ቀለም (ነት)፤ ከነጭ ሃር (ቢሶስ)፤ ከፍየል

[24] ዘጸ.25፥10

[24] ዘፀ.25፥10

www.ethiopianorthodox.org

ፀጉረ ጠሊ ወማዕሰ በግዕ ሐሩይ ወእብነ ሰርድዮን ወከርከደን
ወዘሰንፔር ወመረግድ ወውስተ ደብተራ ዘስምዕ ኀበ ትትነበር ጽዮን
ማኅደረ ስብሐቲሁ። ወይግበሩ ላቲ ከርሠ ሐመር ምስለ ክልኤ
ጽላት እለ ጽሑፋት በአጽባዕተ እግዚአብሔር ወትትነበር ጽዮን
ላዕሌሆሙ።
11 ወትገብር ላቲ ታቦተ እምዕፀ ዘኢይነቅዝ ኀበ ትትነበር ጽዮን ዘክልኤ
እመት ወመንፈቀ እመት ኑኃ፡ ወእመት ወመንፈቀ እመት ግድሚ።
ወትለብጦ በወርቅ ንጡፍ እንተ አፍአሁ ወውስጡ ወትገብር
መዓብልቲሃ ወመቃፍልቲሃ በወርቅ ጽሩይ ወሆፃዳትኒ ዐውዳ።
ወትገብር ውስተ ፬ መሳምክቲሃ ፬ ከበሎ መሳከሚሃ ወትገብር
እምነ ዕፅ ዘኢይነቅዝ። ወትለብጦ በወርቅ ንጡፍ። ወቦቱ ትጸውርየ
ለታቦተ ሕግ።
12 ከመዝ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ በደብረ ሲና። ወአርአዮ ግብራ
ወሥርዓታ ወኀብራ ለደብተራ ከመ ይግበር።
13 ወከብረት ወአብየት ፈድፋደ በውስተ እስራኤል። ወበኀበ
እግዚአብሔር ተአመነት ለማኅደረ ስብሐቲሁ። ወይወርድ ለሊሁ
ውስተ ደብረ መቅደሱ። ወይትናገሮሙ ለኅሩያኒሁ። ወይፈትሕ ሎሙ
ለአድኅኖ። ወያድኅኖሙ እምእደ ፀሮሙ። ወይትናገሮሙ በዐምደ
ደመና ከመ ይዕቀቡ ሕጎ ወሥርዐቶ ወይሑሩ በትእዛዙ
ለእግዚአብሔር።

## ፲ወ፰ ኀ በ ኀ ብ ሩ አ በ ው ጳ ጳ ሳ ት[*]

1 ካዕበ አውሥኡ ማኅበረ ፻፲ወ፰። ወይቤሉ አሜን ዛቲኬ ይእቲ
መድኀኒቶሙ ለደቂቀ አዳም። እስመ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር
እምከመ ወረደት ተሰምዩ ሰብአ ቤቱ ለእግዚአብሔር። በከመ ይቤ
ዳዊት ወማኅደሩሂ ውስተ ጽዮን።[25]
2 ወካዕበ ይቤ በአፈ መንፈስ ቅዱስ ወማኅደርየ ዝየ እስመ ኀረይክዋ
ወእባርኮሙ ለካህናቲሃ ወአስተፌሥሖሙ ለነዳያኒሃ ወለዳዊትኒ
/እውህቦ/ ዘርዐ በውስቴታ በዲበ ምድርኒ ዘይከውን ንጉሠ ወበሰ
ማያትኒ ይነግሥ እምዘርዑ በሥጋ ዲበ መንበረ መለኮት ወጸላእቱኒ
ይገብኡ ታሕተ መከየደ እገሪሁ ወይትኀተሙ በማኅተመ ዚአሁ።

[*] በእንተ ዘኀብሩ ጳጳሳትም ይላል።
[25] መዝ.9፥11



ጠጉርና ከለፋ የበግ ለምድና ሰርድዮን፣ ከርከደንና ሰንፔር፣
መረግድ ከተባሉ እንቁዎች የሚሰሩትን ንዋየ ቅድሳት እንዲሰሩና
የምስጋና ማደሪያ ፅዮን በምትቀመጥበት በምስክሩ ድንኳን ውስጥ
እንዲያስቀምጡ በእግዚኣብሄር እጅ ለተፃፉት ለሁለት ፅላቶች
ማስቀመጫ የሚሆን ከርሰ ሃመርም ያደርጉላት ዘንድ ሙሴና
ኣሮንን ኣዘዛቸው። ፅዮንም በእነሱ ላይ ትቀመጣለች።
11 ርዝመቱም ሁለት ክንድ ከስንዝር፣ ቁመቱም ኣንድ ክንድ ተኩል
የሆነ ፅዮን የምትቀመጥበት ታቦትም ከማይነቅዝ እንጨት
ታደርግላታለህ። ውስጡንና ውጬንም በንፁህ ወርቅ ትለብጠዋለህ።
መሳሪያዎቿን እና መለበጫዋን ከጥሩ ወርቅ በዙሪያዋም ቀለበትን
ታደርግለታለህ ። በኣራቱ ማእዘኖችም ኣራት ቀለበትን እና
ችንካርን ታደርጋለህ። ከማይነቅዝ እንጨት ታደርገዋለህ። በጠራ
ወርቅ ትለብጠዋለህ። በእሱም ህጉን ትሸከሙበታላችሁ።
12 እግዚኣብሄርም ሙሴን በደብረ ሲና ኣዘዘው። እንዴት እንደሚሰ
ራትና የድንኳኗንም ስራዋን፣ ስራቷንና ኣይነቷን ኣሳየው።
13 በእስራኤልም ውስጥ ፈጽማ ከበረች። በእግዚኣብሄርም ዘንድ
ለምስጋናው ማደሪያ ሆና ታመነች። በደብረ መቅደሱም ውስጥ
እሱ ራሱ ይወርዳል። ምርጦቹንም ይናገራቸዋል። ለማዳንም
ይፈርድላቸዋል። ከጠላቶቻቸውም እጅ ያድናቸዋል። ህጉንና
ስርኣቱንም ይጠብቁ ዘንድና በእግዚኣብሄርም ትእዛዝ ይሄዱ ዘንድ
በኣምደ ደመና ይናገራቸዋል።

## ፲፰ ኣበው ጳጳሳት ኣንድ ስለ መሆናቸው

1 ደግሞም የሶስት መቶ ኣስራ ስምንቱ ማህበር መለሱ። በእውነት
ይህች ለኣዳም ልጆች መድሃኒታቸው ናት ኣሉ። ዳዊት "ማደሪያው
በፅዮን ውስጥ ነው"[25] እንዳለው የእግዚኣብሄር ታቦተ ህግ
ከወረደች በሁዋላ የእግዚኣብሄር ቤተሰቦች ተብለው ተጠርተዋልና።
2 ደግሞም "ማደሪያየ እዚህ ነው። በመንፈስ ቅዱስ ኣፍ
መርጫታለሁና ካህናቶቿን እባርካለሁ። ደሃዎቿንም ኣስደስታለሁ።
ለዳዊትም በምድር ላይ በውስጧ ንጉስ የሚሆን በሰማይ ላይም
በመለኮት ዙፋን ላይ በስጋ የሚቀመጥ ከዘሩ እሰጠዋለሁ።
ጠላቶቹም የእግሩ መረገጫ ይሆናሉ። በእሱ ማህተምም ይታተማሉ"
ኣለ።

[25] መዝ.9፥11

www.ethiopianorthodox.org

## ፲ወ፱ በእንተ ኀበ ተረክበት ዛቲ መጽሐፍ

ወይቤ ሊቀ ጳጳሳት ዘሮሜ ደማትዮስ አንሰ ረከብኩ መጽሐፈ በውስተ ቤተ ሶፍያ እምውስተ መጻሕፍት ወመዛግብተ ንጉሥ ከመ ኩላ መንግሥተ ዓለም ለንጉሠ ሮሜ ወለንጉሠ ኢትዮጵያ።

## ፳ በእንተ ክፍለ ምድር

1 እመንፈቃ ለኢየሩሳሌም ወእምደቡባ እስከ መስዕ ሠረቃዊ ክፍሉ ለንጉሠ ሮም፤ ወእመንፈቃ ለኢየሩሳሌም እምደቡባ እስከ መስዕ ወሕንድ ዐረባዊ ክፍሉ ለንጉሠ ኢትዮጵያ። እስመ ክልኤሆሙ ዘርአ ሴም ወልደ ኖኅ ዘርአ አብርሃም ዘርዐ ዳዊት ደቂቀ ሰሎሞን እሙንቱ።
2 እስመ እግዚአብሔር ወሀቦሙ ክብረ ለዘርዐ ሴም በእንተ በረከተ አቡሆሙ ኖኅ።[26] ንጉሠ ሮምኒ ወልደ ሰሎሞን ውእቱ። ወንጉሠ ኢትዮጵያ ወልደ ሰሎሞን በኩሩ ውእቱ ዘይልህቅ።

## ፳ወ፩ በእንተ ንግሥተ አዜብ

1 ወዘከመ ተወልደ ውእቱ ረከብኩ ጽሑፍ ውስቴቱ ለውእቱ መጽሐፍ።
እስመ ከመዝ ዘከርዋ ወንጌላውያን ለይእቲ ብእሲት።
2 ወእግዚእነኒ ኢየሱስ ክርስቶስ ይቤ እንዘ ይትዋቀሶሙ ለሕዝበ አይሁድ ሰቃልያን እለ አሜሃ ትውልድ እንዘ ይብል፤ ንግሥተ አዜብ ትትነሣእ አመ ዕለተ ኩነኔ ወትትዋቀሶሙ ወትትፋትሖሙ ወትመውኦሙ ለዛ ትውልድ[27] እለ ኢአምኑ ስብከተ ቃልየ። እስመ ለሊሃ መጽአት እምአጽናፈ ምድር ከመ ትስማዕ ጥበቢሁ ለሰሎሞን።
ወዘይቤ ንግሥተ አዜብ ንግሥተ ኢትዮጵያ ይእቲ።* ወአጽናፈ ምድርሰ ዘተብህለ በእንተ ድካመ ፍጥረት ዘአንስት ወበእንተ ርኅቀተ ፍኖት ወላህበ ፀሐይ ወበእንተ ረኀበ ፍኖት ወጽምአ ማይ።
3 ወይእቲሰ ንግሥተ አዜብ ሠናይት ጥቀ በራእያኒ በላህያኒ ወበአእምሮ ወልቡና ዘወሀባ እግዚአብሔር ከመ ትሑር ኢየሩሳሌም ከመ ትስማዕ ጥበቢሁ ለሰሎሞን እስመ በፈቃደ እግዚአብሔር ተገብረ ዝንቱ ወኮነ ሥምረቱ።

---

[26] ዘፍጥ.9፡26
[27] ማቴ.12፡42፡ሉቃ.11፡31
*ዛቲሰ ንግሥተ አዜብ ርስታ ወምድረ ሙላዳ አክሱም እስመ እምኔሃ ተወልደት የሚልም ተገኝቷል

- 12 -

## ፲፱ ይህች መፅሃፍ ስለተገኘችበት

የሮሙ ሊቀ ጳጳስ ደማትዮስም "መላው የኣለም መንግስት ለሮም ንጉስና ለኢትዮጵያ ንጉስ እንደሆነች ሶፍያ ውስጥ ካለው ከንጉስ መዝገቦችና መፃህፍት ውስጥ ኣግኝቻለሁ" ኣለ።

## ፳ ስለ ምድር ኣከፋፈል

1 ከኢየሩሳሌም መሃል ጀምሮ ደቡቧንና መስዋን ኣድርጎ ምስራቁ ክፍል ለሮም ንጉስ፤ ከኢየሩሳሌም መሃል ጀምሮ ደቡቧንና መስዋን፣ ሰሜኗንና ኣዜቧን፣ ህንድንና ምእራቡን ክፍል ኣድርጎ የኢትዮጵያ ንጉስ ነው። ሁለቱም የኖህ ልጅ የሴም ዘሮች፣ የኣብርሃም ዘሮች፣ የዳዊት ዘሮችና የሰሎሞን ልጆች ናቸውና።
2 እግዚኣብሄር በኣባታቸው በኖህ በረከት ምክንያት ለሴም ዘሮች ክብርን ሰጥቷቸዋልና።[26] የሮም ንጉስ የሰሎሞን ልጅ ነው። የኢትዮጵያ ንጉስም የሰሎሞን በኩሩና ታላቁ ልጅ ነው።

## ፳፩ ስለ ንግስተ አዜብ

1 እሱም ስለ መወለዱ በዚሁ መፅሃፍ ተፅፎ ኣገኘሁ። ወንጌላውያንም ይህችኑ ሴት እንደዚህ ኣስበዋታልና።
2 ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ሰቃዮቹንና የዚያን ጊዜ ትውልዶችን የኣይሁድ ህዝቦች "ሲወቅሳቸው በፍርድ ቀን ንግስተ ኣዜብ ትነሳለች። ይህችንም የቃሌን ትምህርት ያልሰሙትን እነዚያን ትውልዶች ትዋቀሳቸዋለች። ትፋረዳቸዋለች። ታሸንፋቸዋለችም። የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ከምድር ዳርቻ መጥታለችና"[27] ኣለ።
ንግስተ ኣዜብ ያላትም የኢትዮጵያ ንግስት ናት*። የምድር ዳርቻ የተባለበት ምክንያት በሴቶች የተፈጥሮ ድካም በመንገዱ ርቀት፣ በፀሃዩ ሙቀት፣ በመንገዱ ረሃብና በውሃ ጥሙ ምክንያት ነው።
3 ይህች ንግስተ ኣዜብ ግን በመልኳ፣ በደም ግባቷ፣ እግዚኣብሄር ኢየሩሳሌም ትሄድ ዘንድና የሰሎሞንን ጥበብ ትሰማ ዘንድ በሰጣት እውቀትና ማስተዋል ፈፅሞ ያማረች ነበረች። በእግዚኣብሄር ፈቃድ ሆኗልና።

---

[26] ዘፍጥ.9፡26
[27] ማቴ. 12፡42፤ ሉቃ. 11፡ 39
*በሌላ ክብረ ነገስት ደግሞ የዚህች የንግስተ አዜብ ርስቷና የትውልድ ቦታዋ አክሱም ነው። ምክንያቱም ከዚህችው ተወልዳለችና ሲል ተገኝቷል።

www.ethiopianorthodox.org

4 ወይእቲሰ ባዕልት ጥቀ በዘወሀባ እግዚአብሔር ክብረ ወብዕለ ወርቀ
ወብሩረ ወአልባሰ ክቡረ ወአግማለ ወአግብርተ ወነጋድያነ ወይነግዱ
ላቲ ባሕረ ወየብሰ ወሕንደኬ ወአስዋነ።

## ፳ወ፪ በ እ ን ተ ታ ም ሪ ን ነ ጋ ዲ

1 ወሀለወ ፩ ልብው ሊቀ ነጋድያን ዘስሙ ታምሪን። ወይጽዕን
፭፻ወ፳ አግማለ። ወአሕማረኒ ቦቱ መጠነ ሰብዓ ወሠለስቱ።
2 ወሰሎሞን ንጉሥ አሜሃ ፈቀደ ከመ ይሕንጽ ቤተ እግዚአብሔር።
ወለአከ ውስተ ኵሉ ነጋድያን ለምሥራቅ ወለምዕራብ ለደቡብ ወለሰ
ሜን ከመ ይምጽኡ ነጋድያን ወይንሥኡ በኀቤሁ ወርቀ ወብሩረ
ወውእቱኒ ይንሣእ ዘይትፈቀድ ለግብር።
3 ወነገርዎ በእንተ ውእቱ ነጋዲ ኢትዮጵያዊ ባዕል። ወለአከ ከመ
ያምጽእ ሎቱ ዘይትፈቀድ እምብሔረ ዐረብ ወርቀ ቀይሐ ወዕፀ
ዘኢይነቅዝ ጸሊመ ወሰንፔረ።
4 ወሖረ ውእቱ ነጋዲ ዘስሙ ታምሪን ነጋዲሃ ለንግሥተ ኢትዮጵያ
ኀበ ሰሎሞን ንጉሥ። ወነሥአ ኵሎ ዘፈቀደ እምኔሁ ወወሀቦ
ለነጋዲ ዘይፈቅድ አፈድፊዶ እምንዋዩ።
5 ወውቱሰ ነጋዲ ልብው ፈድፋደ ወይሬኢ ጥበቢሁ ለሰሎሞን።
ወያነክር ወይትዐቀብ ከመ ይጠይቅ አውሥአተ ቃሉ ወፍትሐ
ወሣእሣአ አፉሁ ወጣዕመ ነገሩ ወሑረቶ ወንብረቶ ወተንሥኦቶ
ወግብሮ ወፍቅሮ ወሥርዐቶ ወማዕዶ ወሕጎ ወለእለኒ ይኤዝዞሙ
ምስለ ትሕትና ወየውሀት ወሶበኒ አበሱ ይምህሮሙ እስመ በጥበብ
ወበፍርሀተ እግዚአብሔር ይሠርዕ ቤቶ ወያከምስሶሙ በየውሀት
ለአብዳን ወይሴርሖሙ በየውሀት ለአእማት ወይከሥት አፉሁ
በአምሳል ወይጥዕም ቃሉ እምጸቃውዐ መዓር ወኵሉ ግብሩ ፍትው
ወኵሉ ርእየቱ አዳም።እስመ ትትፈቀር ጥበብ በኀበ ማእምራን
ወትትሜነን በኀበ አብዳን።
6 ወዘንተ ኵሎ ርእዮ ያስተዐጽብ ውእቱ ነጋዲ። ወያነክር ፈድፋደ
እስመ ለእለ ይርእይዎ ኵለንታሁ መፍትው ወመምህር ውእቱ።
ወእለኒ በጽሑ ኀቤሁ ኢይፈቅዱ ይእትቱ ወይትገሐሡ እምኔሁ
በእንተ ጥበቡ ወላህዩ ወጣዕመ ነገሩ ከመ ማይ ለጽሙእ፣ ወከመ
ኀብስት ለርኁብ፣ ወከመ ፈውስ ለድውይ፣ ወከመ ልብስ ለዕሩቅ፣
ወከመ አብ ለእጓለ ማውታ። ወይፈትሕ በጽድቅ። ወኢያደሉ ለገጽ።
ወቦቱ ክብር ወብዕል ዘወሀቦ እግዚአብሔር ፈድፋደ ወርቀ ወብሩረ
ወዕንቍ ወአልባሰ ክቡረ ወእንስሳ ወአራዊተ ዘአልቦሙ ኍልቍ።
7 ወበመዋዕሊሁ ለሰሎሞን ንጉሥ ኮነ ወርቅ ከመ ብርት ወብሩር ከመ
ዐረር። ወብርትሰ ወዐረር ወኀፂን ኮነ ብዙኀከመ ዕፀ ባህሩስ ወከመ
ብርዐ ገዳም። ወዕፀ ቄድሮስኒ ብዙኀ ኮነ። ወዘወሀቦ እግዚአብሔር
ክብረ ወብዕለ ወጥበበ ወሞገሰ ዘኢኮኑ ከማሁ እለ እምቅድሜሁ
ወኢይከውኑ እምድኅሬሁ ዘከማሁ።

- 13 -

4 እሷም እግዚኣብሄር በሰጣት ክብርና ብልጥግና፣ ወርቅና ብር፣ በከበሩ
ልብሶች፣ በግመሎች፣ በባሪያዎች፣ በነጋዴዎችም እጅግ የበለፀገች
ነበረች። በየብሱም፣ በባህርም፣ በህንድም፡ በኣስዋንም ይነግዱላት ነበር።

## ፳፪ ስለ ነጋደው ታምሪን

1 ኣንድ ስሙ ታምሪን የተባለ ኣስተዋይ የነጋዴዎች ኣለቃ ነበር።
ኣምስት መቶ ሃያ ግመሎችንም ይጭን ነበር። ሰባ ሶስት ያህል
መርከቦችም ነበሩት።
2 ያን ጊዜ ንጉስ ሰሎሞን የእግዚኣብሄርን ቤት ይሰራ ዘንድ ወደደ።
ነጋዴዎችም መጥተው ከእሱ ወርቅና ብር እንዲቀበሉና እሱም
ከእነሱ ለስራው የሚያሻውን እንዲቀበል በምስራቅና በምእራብ፣
በደቡብና በሰሜን ወደ ኣሉት ነጋዴዎች ሁሉ ተላከ።
3 ስለ ሃብታሙ ኢትዮጵያዊ ነጋደም ነገሩት ። ንጉሱም ከኣረብ ሃገር
የሚያስፈልገውን ቀዩን ወርቅ፣ ጥቁርና የማይነቅዝ እንጨትና
ሰንፔር የተባለውን እንቁ እንዲያመጣለት ላከ።
4 ይህም ስሙ ታምሪን የተባለ የኢትዮጵያ ንግስት ነጋዴ ወደ ንጉስ
ሰሎሞን ዘንድ ሄደ። ንጉሱም ከእሱ የሚሻውን ሁሉ ተቀበለ።
ለነጋዴውም የሚሻውን ሁሉ ከገንዘቡ ኣስበልጦ ሰጠው።
5 ነገዴው ግን እጅግ ብልህ ነበር። የሰሎሞንን ጥበብ ያስተውልና
ያደንቅ ነበር። የቃሉን መልስ፣ ፍርዱን፣ የኣፉን ቅልጥፍና የነገሩን
ጣእም፣ ኣካሄዱን፣ ኣቀማመጡን፣ ኣነሳሱን፣ ስራውን፣ ፍቅሩን፣
ስርኣቱን፣ ማእዱን፣ ህጉን፣ በትህትናና በቅንነት የሚያዛቸውን፣
ሲያጠፉ ሲምራቸው፣ በጥበብና እግዚኣብሄርን በመፍራት ቤቱን
ሲሰራ፣ ለሰነፎች በቅንነት ፈገግ ሲልባቸው፣ ሴቶች ባሪያዎቹን
እንዴት በቅንነት እንደሚያቀናቸው፣ ኣፉንም እንዴት በምሳሌ
እንደሚከፍት፣ ቃሉም እንዴት ከማር ወለላ እንዲጣፍጥ፣ ስራው
ሁሉ የተወደደና ኣስተያየቱ ሁሉ ያማረ እንደሆነ ለመረዳት
ይጠነቀቅ ነበር። ጥበብ በኣዋቂዎች ዘንድ የተወደደች፣ በሰነፎች
ዘንድ የተናቀች ናትና።
6 ይህንን ሁሉ ኣይቶ ነጋደው ይገረምና ይደነቅ ነበር። ለሚያዩት
ሁለንተናው ተወዳጅና ኣስተማሪ ነበርና። ከእሱ ዘንድ የደረሱት
ሁሉ ስለ ጥበቡ፣ ስለ ለዛው፣ ለተጠማ እንደ ውሃ፣ ለተራበ እንደ
እንጀራ፣ ለታመመ እንደ ፈውስ፣ ለተራቆተ እንደ ልብስ፣ ለሙት
ልጅ እንደ ኣባት ስለሆነና ስለ ነገሩ ጣእም ከእሱ ፈቀቅ ለማለት
ኣይፈቅዱም ነበር። በእውነት ይፈርዳል። መልክ ኣይቶ ኣያደላም።
እግዚኣብሄር የሰጠው ክብርና ሃብት ይልቁንም ወርቅ፣ ብር፣ እንቁና
የከበሩ ኣልባሳትና ቁጥር የሌላቸው እንስሳትና ኣራዊት ነበሩት።
7 በንጉሱ በሰሎሞን ዘመንም ወርቅ እንደ ናስ፣ ብርም እንደ ርሳስ ሆነ።
ናስ፣ ርሳስና ብረት ግን እንደ እንጨትና የዱር ገለባ ሆነ። እንደ
የቄድሮስ እንጨትም ብዙ ሆነ። እግዚኣብሄር በሰጠው ክብርና ብእል፣
ጥበብና ሞገስ ከእሱ በፊት እንደዚህ ያልነበሩና ከእሱም በሁዋላም
እንደዚህ እንደማይሆኑ ሆነ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፰ወ፫ ኀ በ ገ ብ አ ነ ጋ ዲ ኢ ት ዮ ጵ ያ

1 ወእምዝ ፈተወ ነጋዲ ታምሪን ከመ ይግባእ ብሔሮ። ወሖረ ኀቤሁ
ለሰሎሞን። ወሰገደ ሎቱ። ወአምኆ ወይቤሎ ሰላም ለዕበይከ።
ፈንወኒ እሑር ብሔርየ ኀበ እግዝእትየ። እስመ ጐንደይኩ በርእየ
ክብርከ፣ ወጥበብከ፣ ወበብዝኀ መባልዕት ዘትጼግወኒ። ወይእዜሰ
አሐውር ኀበ እግዝእትየ። አንሰ እምፈተውኩ እንበር ምስሌከ ከመ
፩ እምአግብርቲከ እምእለ ይቴሐቱ። ብፁዓንሰ እለ ይሰምዑ ቃለከ
ወይገብሩ ትእዛዘከ እስመ እምፈተውኩ እንበር ዝየ ወኢይትፈለጥ
እምኔከ አላ ባሕቱ ፈንወኒ ኀበ እግዝእትየ በእንተ ምዕቅብና
ዘላዕሌየ ከመ አሀባ ንዋያ ወለልየኒ ገብር ላቲ።
2 ወቦአ ሰሎሞን ቤቶ ወወሀበ ኵሎ ዘይትፈቀድ ክብረ ለብሔረ
ኢትዮጵያ ወፈነዎ በሰላም።
3 ወሰገደ ወወጽአ። ወሖረ ፍኖቶ። ወበጽሐ ኀበ እግዝእቱ። ወአወፈያ
ኵሎ ንዋየ ዘአእተወ። ወነገራ ዘከመ በጽሐ ሀገረ ይሁዳ ኢየሩሳሌም
ኀበ ሰሎሞን ንጉሥ ወኵሎ ዘሰምዐ ወዘርእየ ነገራ ዘከመ ይገብር
ፍትሐ ወዘከመ ይትናገር ንጽሐ ወዘከመ ይኤዝዝ ርትዐ በኵሉ
ዘሐተቶ ያወሥእ በየውሀት ወአልቦ ሐሰት በኀቤሁ ወዘከመኒ ሤመ
ነዳእተ ገባር እለ ይጸውሩ ዕፀ አርሶን በበ፺፻ ወወቀርተ እብን ፹፻
እምነ ኵሉ ነጋድያን ወሠያጥያን፣ ዘከመ የኀሥሥ ለኪነ ጥበብ
ወምግባር ወዘከመ ይነሥእ ወይሁብ በካዕበት ወኵሉ ኪኑ ወግብሩ
በጥበብ። ወይነግራ ለለጽብሐት ኵሎ ጥበበ ሰሎሞን ከመ ይገብር
ፍትሐ፣ ወዘከመ ይገብር ርትዐ ወዘከመ ይሠርዕ ማዕደ ወዘከመ
ይገብር ምሳሐ ወዘከመ ይሜህር ጥበበ፣ ወዘከመ ይኤዝዝ
አግብርቲሁ፣ ወኵሉ ሥሩዕ በምክር። ወየሐውሩ በቃሉ። ወአልቦ
ዘይትዔገል ካልእ። ወአልቦ ዘይዔምፅ ንዋየ ቢጹ። ወአልቦ ሐያዲ
ወኢሰራቂ በመዋዕሊሁ። እስመ በጥበብ የአምሮሙ ለእለ ስህቱ።
ወይቀስፎሙ ወያፈርሆሙ። ወኢይደግሙ እኩየ አላ በሰላም ይነብሩ
ምስለ ፍርሀተ ንጉሥ።
4 ወዘንተ ኵሎ ይነግራ ወለለጽብሐት ይዜክር ዘርእየ በኀበ ንጉሥ።
ወይነግር ወታስተደምም በዘሰምዐት እምኀበ ነጋዲ ገብራ። ወትኄሊ
በልባ ከመ ትሑር ኀቤሁ። ወትበኪ እምብዝኀ ፍቅራ በዘነገራ።
ወታፈቅር ፈድፋደ ሐዊረ ኀቤሁ። ወትኄሊ ኀሊና ሐዊረ ኀቤሁ።
ወታስተርሕቅ ወታስተዐጽብ። ወካዕበ ተሐትት። ወይነግራ ካዕበ።
ትፈቱ ወታስተአድም ሐዊረ ከመ ትስማዕ ጥበቢሁ፣ ወትርአይ ገጾ፣
ወተአምኆ ኪያሁ፣ ወትግነይ ለመንግሥቱ፣ ወአጥብዐት ልባ ከመ
ትሑር ኀቤሁ፣ ወእግዚአብሔርኒ አጥብዐ ልባ ከመ ትሑር።
ወአፍተዋ።
5 ወእምዝ አኀዘት ትሥራዕ ቤታ፣ ወተአዝዘ አግብርቲሃ፣ ወትምዕድ
አእማቲሃ፣ ወታስተሴኒ ንዋያ። ወተኀሥሥ ዘይትፈቀድ ለፍኖት
ወለአምኃ ለንጉሥ፣ ወለውሂብ ለመኳንንቲሃ ወለዕሤተ አእማቲሃ።

- 14 -

## ፰፫ ነጋዴው ወደ ኢትዮጵያ እንደ ተመለሰ

1 ከዚህ በሁዋላ ነጋዴው ታምሪን ወደ ኣገሩ ሊመለስ ወደደ። ወደ
ሰሎሞንም ሄደ፤ ሰገደለትም። ሰላምታም ሰጠው። ኣለውም።
"ለገናናነትህ ሰላምታ ይገባል። ክብርህንና ጥበብህን በማየትና
በምትሰጠኝም ብዙ ማእድ ዘግይቻለሁና ወደ ሃገሬ ከእመቤቴ
ዘንድ እንድሄድ ፍቀድልኝ። እንግዲህስ ወደ እመቤቴ እሄዳለሁ።
እኔ ቅሉ ከታናናሽ ባሪያዎችህ እንደ ኣንዱ ሆኜ ከኣንተ ጋር
በተቀመጥኩ ደስ ባለኝ ነበር። ቃልህን የሚሰሙ ትእዛዝህን
የሚያደርጉ ብፁኣን ክቡራን ናቸው። እዚህ በተቀመጥኩ፤ ካንተም
ባልተለየሁ በወደድኩ። ዳሩ ግን ስለ ኣለብኝ ኣደራ ገንዘቧን
ኣስረክባት ዘንድ ወደ እመቤቴ መልሰኝ እኔም እኮ እንጂ የእሷ
ኣገልጋይ ነኝ" ኣለው።
2 ሰሎሞንም ወደ ቤቱ ገባ። ለሃገሩ ለኢትዮጵያም የሚገባውን ክብር
ሰጠው። በሰላምም ላከው።
3 ሰግዶም ወጣ። መንገዱንም ሄደ። ወደ እመቤቱም ደረሰ።
ያመጣውንም ሃብት ሁሉ ሰጣት። ከይሁዳ ኣገር ከኢየሩሳሌም ወደ
ንጉስ ሰሎሞን እንደደረሰና ያየውንና የሰማውን ሁሉ እንዴት
ፍርድ እንደሚያደርግ፣ እንዴት ንፅህናን እንዲናገርና ቅንን
እንደሚያዝዝ ፣ እንዴት ለጠየቀው በቅንነት እንደሚመልስ፣ በእሱ
ዘንድ ሃሰት እንደሌለ፣ የጠርብ እንጨት የሚሸከሙ ሰባት መቶ፣
ድንጋይ የሚጠርቡ ስምንት መቶ ኣሰሪዎችና ለኪነ ጥበብ ስራ
ከነጋዴዋዎችና ሻጮች ሁሉ እንዴት እንደሾመና ለተቀበለው ሁሉ
እንዴት በእጥፍ እንደሚከፍል፣ ስለ ብልሃቱ፣ ስለ ስራውና ጥበቡ
ሁሉ ነገራት። በየቀኑም የሰሎሞንን ጥበብ እንዴት እንደሚፈርድና
ቅን እንደሚሰራ፣ ስለ ማእዱ ኣሰራር፣ ስለ ምሳው ግብዣ፣
እንዴት ጥበብን እንደሚያስተምርና ባሪያዎቹንም እንደሚያዝ
ይነግራት ነበር። ሁሉ በምክር የተዘጋጀ ነበር ። እነሱም በቃሉ
ይሄዱ ነበር። ሌላውን የሚነጥቅ ኣልነበረም። የባልንጀራውን ገንዘብ
የሚቀማ ኣልነበረም። የተሳሳቱትንም በጥበቡ ያውቃቸውና
ይገርፋቸው፣ ያስፈራቸውም ነበር። ንጉሱንም በመፍራት በሰላም
ይኖሩ ነበር እንጂ ስህተቱን ኣይደግሙም ነበር።
4 ይህንንና በንጉሱ ዘንድ ያየውንና ያስታወሰውን በየቀኑ ይነግራት
ነበር። እሷም ኣገልጋይዋ ከሆነው ከዚህ ነጋዴ በሰማችው ትደነቅ፣
በልቧም ወደ እርሱ ለመሄድ ታስብና ከፍቅሯ ብዛት የተነሳ
ታለቅስ ነበር። ወደ እሱም ዘንድ ለመሄድ ታስብና ይርቅባት
ነበር። እንደገናም ትደነቅና ትመራመር ነበር። ደግሞም ጥበቡን
ለመስማት ፊቱን ለማየትና ሰላምታም ልትሰጠው ለመንግስቱም
ልትገዛ ፈፅማ ትሻ ነበር። በልቧም ወደ እሱ ለመሄድ ቆረጠች።
እግዚኣብሄርም ትሄድ ዘንድ ልቧን ኣደፋፈረ። ኣነሳሳትም።
5 ከዚህ በሁዋላ ቤቷን በስርኣት ልታደርግ፣ ወንዶች ባሪያዎቿን
ልታዝ፣ ሴቶች ባሪያዎቿን ልትመክር፣ ንብረቷን ልታደራጅ፣

www.ethiopianorthodox.org

ወአሰተጋብአት ራኩባተ፣ ወአብቅልተ፣ ወአፍራሰ፣ ወአእዱገ፣ ወአሕማረ፣ ወአርማሰ፣ ወመጻፍነ ወአሕሳለ ወመሳንቀ ወመሳትየ ወመጻውረ ወተደለወት ከመ ትሑር ወአዘዘት ለኵሉ መኳንንቲሃ እለ እምታሕቴሃ ከመ ይደለዉ ለፍኖት እስከ ስድስቱ አውራኀ ወይንሥኡ መሳንቀ ወይሥርው አብያቲሆሙ እስመ ርኁቅ ብሔር ኀበ የሐውሩ

## ፳ወ፩ ኀ በ ተ ደ ለ ወ ት ለ ሐ ዊ ር

1 ወትቤሎሙ ስምዑ ቃልየ እሊኣየ ወአፅምዑኒ ነገርየ እስመ አንሰ
እፈቅድ ጥበበ። ወልብየኒ ተኀሥሣ ለአእምሮ። እስመ ተነደፍኩ
በፍቅረ ጥበብ። ወተስሕብኩ በአሕባለ አእምሮ።
2 እስመ ትኄይስ ጥበብ እመዝገበ ወርቅ ወብሩር። ጥበብሰ ትኄይስ
እምነ ኵሉ ዘተፈጥረ ዲበ ምድር። በምንትኬ ያስተማስልዋ ለጥበብ።
በታሕተ ሰማይ ትጥዕም እምነ መዓር። ወታስተፌሥሕ እምነ ወይን።
ወታበርህ እምነ ፀሐይ ወትትፈቀር እምነ ዕንቍ ክቡር። ወታጠልል
እምነ ቅብዕ። ወታጸግብ እምነ መባልዕት ጥዑማት። ወታከብር እምነ
አዕላፍ ወርቅ ወብሩር። መስተፍሥሒት ለልብ። ወመብርሂት
ለአዕይንት። ወከዋው ለእግር። ወድርዕ ለእንግድዓ። ወጌራ ለርዕስ።
ወባዝግና ለክሣድ። ወመቅነቲ ለሐቌያት። ወመስምዒ ለአእዛን።
ወመጥበቢ ለአልባብ። ወትምህርት ለማእምራን። ወመናዝዝት
ለልቡባን። ወወሀቢት ክብረ ለኀሣሥያን።
3 ወመንግሥትኒ ኢይቀውም ዘእንበለ ጥበብ። ወብዕልኒ ኢይትዐቀብ
ዘእንበለ ጥበብ። ወእግርኒ ኢይጸንዕ ኀበ ኬደ ዘእንበለ ጥበብ።
ወልሳንኒ ኢይትፈቀር ዘተናገረ ዘእንበለ ጥበብ።
4 ጥበብሰ ትኄይስ እምነ ኵሉ መዛግብት። ዘዘገበ ወርቀ ወብሩረ
ኢይበቍዕ ዘእንበለ ጥበብ። ወዘዘገበ ጥበበ አልቦ ዘየሀይዶ እምነ
ልቡ። ወዘዘገቡ አብዳን ይበልዑ ጠቢባን። ወበእንተ እከየሙ
ለዐማፅያን ይትዌደሱ ጻድቃን። ወበእንተ ስህተቶሙ ለአብዳን
ይትፈቀሩ ጠቢባን።
5 ጥበብሰ ልዕልት ይእቲ ወብዕልት። አነ አፈቅራ ከመ እም። ወይእቲ
ተሐቅፈኒ ከመ ሕፃና።አነ እተሉ አሠራ ለጥበብ ወይእቲ ተዐቅበኒ
እስከ ለዓለም። አነ አኀሥሣ ለጥበብ። ወይእቲ ትከውነኒ ለዝሉፉ።
እተሉ አሠራ። ወኢይትገደፍ እምኔሃ። አሰምካ ባቲ። ወትከውነኒ
ጥቅመ አድማስ። እጸወን ባቲ። ወትከውነኒ ኀይለ ወጽንዐ።
እትፌሣሕ ባቲ። ወትከውነኒ ሞገሰ ብዙኀ። እስመ ርቱዕ ንትሉ
አሠራ ለጥበብ ወይልኃእ ሰኮናነ ውስተ መድረከ ኆኀቲሃ ለጥበብ
6 ነኀሥሣ ወንረክባ። ናፍቅራ ወኢትርኀቅ እምኔነ። ንዴግና ወንረክባ።
ንስአላ ወንነሥኣ። ንሚጥ ልበነ ኀቤሃ ከመ ኢንርስዓ በኵሉ ጊዜ።
እስመ ለእመ ዘከርዋ ትዜክር ለሊሃ። ወበኀበ አብዳንሰ ኢትዜክር
ጥበብ። እስመ ኢያከብርዋ ወኢታፈቅሮም።ወክብራሰ ለጥበብ አክብሮ
ጠቢብ። ወፍቅራኒ ለጥበብ አፍቅሮቱ ለጠቢብ።



ለመንገድ የሚያስፈልገውንና ለንጉሱ የሚቀርበውን ገፀ በረከት፣ ለመኳንንቱ የሚሰጠውን ስጦታና የሴቶች ባሪያዎቿን \ደመወዝ ልታስብ ጀመረች። የግመል ባዝራዎችን፣ በቅሎዎችን፣ ፈረሶችን፣ ኣህዮችን፣ መርከቦችን፣ ታንኳዎችን፣ የውሃ መቅጃዎችን፣ ዳውላዎችን፣ ስንቆችን፣ መጠጫዎችንና መሸከሚያዎችን ሰበሰበች። ትሄድም ዘንድ ተዘጋጀች ። ከበታቿ ላሉት መኳንንት ሁሉ የሚሄዱበት ኣገር ሩቅ ነውና ለስድስት ወራት መንገድ እንዲዘጋጁና ስንቃቸውን እንዲይዙ ቤቶቻቸውንም ሁሉ በስርኣት እንዲያደርጉ ኣዘዘች።

## ፳፩ ለመሄድ እንደ ተዘጋጀች

1 ኣለቻቸውም። "ወገኖቼ! ነገሬን ኣድምጡኝ። እኔ ጥበብን እሻለሁ።
ልቤም እውቀትን ትፈልጋለች። በጥበብም ፍቅር ተነድፌኣለሁ።
በጥበብ ገመዶችም ተይዣለሁ።
2 "ጥበብ ከወርቅና ከብር መዛግብት ትሻላለች። ጥበብ በምድር
ከተፈጠሩት ሁሉ ትበልጣለች። ጥበብን ከሰማይ በታች በምን
ይመስሏታል? ከማር ትጣፍጣለች። ከወይን ታስደስታለች። ከፀሃይ
ታበራለች። ከጣፈጡ ምግቦች ታጠግባለች። ከመቶ ሺህ ወርቅና
ብር ታከብራለች። ለልብ ኣስደሳች፣ ለኣይኖች መብራት፣ ለእግር
ቅልጥፍና ለደረት ጥሩር፣ ለራስ ኣክሊል ፣ ለኣንገት የወርቅ
ማርዳ፣ ለወገብ መታጠቂያ፣ ለጆሮ ማዳመጫ፣ ለልብ ብልሃት፣
ለምሁራን ትምህርት፣ ለልበኞች መፅናኛና ለሚፈልጉ ክብር ሰጪ ናት።
3 "መንግስት ያለ ጥበብ ኣይቆምም። ሃብትም ያለ ጥበብ
ኣይጠበቅም። እግርም ያለ ጥበብ በቆመበት ኣይፀናም፤ ልሳንም
ያለ ጥበብ የተናገረው ኣይወደድም።
4 ጥበብ ከንብረት ሁሉ ትሻላለች። ወርቅና ብር የሰበሰበ ያለ ጥበብ
ኣይጠቅመውም። ጥበብን የሰበሰበ ከልቡ ማንም ኣይቀማውም።
ሰነፎች የሰበሰቡትን ጠቢቦች ይበሉታል። በበደለኞች ክፋት ቅኖች
ይመሰገናሉ። በሰነፎችም ስህተት ጠቢቦች ይወደዳሉ።
5 ጥበብ ልእልት ናት። እንደ እናት እወዳታለሁ። እሷም እንደ ህፃኗ
ታቅፈኛለች። እኔ የጥበብን ፍለጋ እከታተላለሁ። እሷም እስከ
ዘላለም ትጠብቀኛለች። እኔ ጥበብን እፈልጋታለሁ። እሷም
ለሁልጊዜ ትሆነኛለች። ዱካዋን እከታተላለሁ። ከእሷም ኣልጣላም፤
እጠጋታለሁ፤ እሷም የድንጋይ ግንብ ትሆነኛለች። ሃይልና ብርታትም
ትሆነኛለች። እደሰትባታለሁ፤ ብዙ ሞገስም ትሆንልኛለች። የጥበብን
ዱካ ልንከተል፣ ሸኮናችንም በበሮቿ ደረጃ ሊቸነከር ይገባልና።
6 "እንፈልጋታለን፤ እናገኛታለን፤ እንወዳታለን፤ ከእኛም ኣትርቅም። እናገኛ
ታለን። እንለምናት፤ እንቀበላታለን። ሁልጊዜ እንፈልጋት። ልባችንን ወደ
እሷ እንመልስ። ካሰቧት ታስባለች። በሰነፎች ዘንድ ጥበብ ኣትታሰብም፤
ኣያከብሯትምና እሷም ኣትወዳቸውም። የጥበብም ክብር ጠቢብን ማክበር
ነው። የጥበብም ፍቅር ጠቢብን ማፍቀር ነው።"

www.ethiopianorthodox.org

7 አፍቅሮ ለጠቢብ ወኢትርሐቅ እምኔሁ። ወበርእየ ዚአሁ ትከውን
ጠቢበ። ስማዕ መክሥተ አፉሁ ከመ ትኩን ከማሁ። ወርኢ መከየደ
እገሪሁ ከመ ታንብር ኀበ ኬደ ውእቱ። ወኢትሰስል እምኔሁ ከመ
ትንሣዕ ትሩፋተ ጥበቡ።
8 ወአንሰ በሰሚዕኒ አፍቀርክዎ ዘእንበለ እርአዮ እስመ ኩሉ ዜና ነገሩ
በኀቤየ ኮነ ፍትወ ለልብየ ከመ ማይ ለጽሙዕ።
9 አውሥኡ ወይቤልዋ መኳንንቲሃ፣ወእግብርቲሃ ወእእማቲሃ፣ ወመማክርቲሃ
እግዝእትነ ጥበብሰ ኢተኀጥአ እምኔኪ። ምወበጥበብኪ ዘታፈቅሪ ጥበበ።
ወንሕነሰ እመኒ ሖርኪ ነሐውር ምስሌኪ። ወእመኒ ነበርኪ ንነብር
ምስሌኪ። ወትኩን ሞትነ ምስለ ሞትኪ ወሕይወትነ ምስለ ሕይወትኪ።
10 ወእምዝ ተደለወት ለሐዊር በብዙኅ ክብር ወግርማ፣ በዐቢይ ሥንቅ
ወተድላ። እስመ ፈተወ ልባ በፈቃደ እግዚአብሔር ከመ ትሑር
ኢየሩሳሌም፣ ከመ ትስማዕ ጥበቢሁ ለሰሎሞን፣ እስመ ሰምዐት
ወጽሕቀት። ተደለወት ለሐዊር። ወተፅዕነ ራኩብ ፯፻፺ወ፯። ወበቅልሰ
ወአድግ ዘአልቦ ኍልቍ ተፅዕነ። ወሖረት ወአርትዐት ፍኖታ እንዘ
ይትዌከል ልባ በእግዚአብሔር።

## ፳ወ፭ ዘከመ በጽሐት ኀበ ሰሎሞን ንጉሥ

1 ወበጽሐት ኢየሩሳሌም ወአብአት አምኃ ለንጉሥ ብዙኀ ክብረ
ዘይትፈቀድ ሎቱ። ወውእቱኒ አክበራ። ወተፈሥሐ ወወሀባ ማኅደረ
በታዕካ መንግሥት ዘቅሩብ ኀቤሁ።
2 ወይፌኑ ላቲ ድራረ ወምሳሐ ለለ አሐቲ ጊዜ ፲ወ፭ በመሥፈርተ
ቆሬ* ስንዳሌ ስሉቀ ብሱለ ምስለ ቅብእ ወመጣብቅ ብዙኅ ወ፴
በመሥፈርተ ቆሬ* ስንዳሌ ልቱመ በዘተገብረ ኅብስተ ፫፻ ወ፶
ምስለ ጠቢቅ በዘባድው ወ፲ መግዝአ ላህም ወ፭ አስዋር ወ፶
አባግዕ ዘእንበለ ወይጠል ወሀየል ወቶራ ወመግዝእ ዶርሆ ወጸህበ
ወይን ፷ መሣፍረ ግራት ወከራሚ ፴ ወእምነ መዛርያን ወመዛርያት
በበ፳ ወ፭። ወጸቃውዐ ወመግንጠ ወእምነ ሲሳዩ ዘይበልዕ ወእምነ
ስታይ ዘይሰቲ ወለለ ዕለት ያለብስ ፲ ወ፩ ዘየሐይድ አዕይንተ።
3 ወየሐውር ኀቤሃ ወይትናዘዝ። ወይእቲኒ ተሐውር ኀቤሁ
ወትትናዘዝ።
4 ትሬኢ ጥበቦ ወፍትሖ ወክብሮ ወሞገሶ ወጣዕመ ነገሩ። ወታነክር
በልባ። ወታስተአድም በኅሊናሃ። ወትጤይቅ በአእምሮ። ወታስተሐይጽ
በአዕይንቲሃ ዘከመ መፍትው። ወታስተዐጽብ ፈድፋደ በእንተ
ዘርእየት ወሰምዐት በኀቤሁ ከመ ፍጹም በስንኡ ወጠቢብ
በሕሊናሁ ወፍሡሕ በጸጋ ወላህይ ወግርማ ወቃሉኒ
በጥይቅና ወከናፍሪሁኒ በሥእሥእና ወትዛዙኒ በግርማ ወበሰላም ምስለ

---

* ቆሮስ
* ቆሮስ

- 16 -

7 ጠቢብን ውደደው። ከእሱም አትራቅ። እሱን በማየት ጠቢብ
ትሆናለህና። እንደ እሱ ትሆን ዘንድ ከአፉ የሚወጣውን ስማ።
እሱ በቆመበት ትቆም ዘንድ የእግሩን መጫሚያ እይ። የጥበቡን
ትርፍ ትቀበል ዘንድ ከእሱ ፈቀቅ አትበል።
8 እኔም ሳላየው በመስማት ወደድኩት። በእኔ ዘንድ የነገሩ የምስራች
ውሃ ለተጠማ እንደሆነ በልቤ የተወደደ ሆኗልና።"
9 መኳንንቶቿ፣ ወንዶችና ሴቶች፣ ባሪያዎቿና አማካሪዎቿም
"እመቤታችን ጥበብ እኮ ካንቺ አልታጣም። ጥበብንም የምትወጂ
በጥበብሽ ነው። እኛ ግን አንቺ ብትሄጂ ካንቺ ጋራ እንሄዳለን።
ብትቀመጪ ከአንቺ ጋራ እንቀመጣለን። ሞታችን ከሞትሽ፣
ደህንነታችንም ከደህንነትሽ ጋር ይሁን" ሲሉ መለሱ።
10 ከዚህ በሁዋላ በብዙ ክብርና ግርማ፣ በከፍተኛ ስንቅና ደስታ
ለመሄድ ተዘጋጀች። በፈቃደ እግዚአብሄር የሰሎሞንን ጥበብ ትሰማ
ዘንድ ወደ ኢየሩሳሌም እንድትሄድ ልቧ ወደልና፤ ሰምታም
ተጨንቃለችና ለመሄድ ተዘጋጀች። ሰባት መቶ ዘጠና ሰባት
የግመል ባዝራዎች ተጫኑ። ቁጥር የሌለው በቅሎና አህያም
ተጫነ። ልቧም በእግዚአብሄር እየታመነ ሄደች። መንገዷንም
አቀናች።

## ፳፭ ከንጉሡ ከሰሎሞን ዘንድ እንደ ደረሰች

1 ኢየሩሳሌምም ደረሰች። ለንጉሱም ገፀ በረከትና የሚገባውንም ብዙ ክብር
አቀረበች። እሱም ደግሞ አከበራት። ደስም ተሰኘ። ለእርሱ ቅርብ
ከሆነው ቤተ መንግስት ውስጥም ቤት ሰጣት።
2 ራትና ምሳም ላንድ ጊዜ የተሰለቀና በቅቤ እና በብዙ ማጣፈጫ የበሰለ
አስራ አምስት መስፈሪያ ስንዴ፣ ሶስት መቶ ሃምሳ እንጀራ የሚሆን፣ ሰ
ላሳ መስፈሪያ የተፈተገ ስንዴ በዳውላ ከዶሮ ሙክት ጋር፣ አስር ሺህ
ላሞች፣ አምስት በሬዎች፣ ከፍቆው፣ ከዋልያውና ከአጋዘኑ ሌላ ሃምሳ
በጎች፣ የተሞከቱ ዶሮዎች፣ ስድሳ ማድጋ ያህል የእንጨት በርሜል
ወይን፣ ሰላሳ ማድጋ የኖረ ጠጅ፣ ከወንዶችና ሴቶች ጠማቂዎች
በየአይነቱ ሃያ አምስት ሃያ አምስት የማር ወለላ፣ ከሚበላው ምግብ፣
ከሚጠጣው መጠጥ፣ እንዲሁም በቀን በቀን ለአይን የሚያስጎመጅ አስራ
አንድ ቅያሪ ልብስ ይልክላት ነበር።
3 እሱም ወደሷ ይሄድና ይፅናና ነበር። እሷም ወደ እሱ ሄዳ ትፅናና
ነበር።
4 ጥበቡን፣ ፍርዱን፣ ክብሩን፣ ሞገሱንና የነገሩን ጣእም ትመለከትና በልቧም
ታደንቅ፣ በሃሳቧም ትገረም፣ በአእምሮዋም ትጠይቅ፣ በአይኖቿም
ታስተውልና በእሱ ዘንድ ስላየችውና ስለሰማችው ፈጽሞ ታደንቅ ነበር።
ስለቅንነቱ ፍፁምነት፣ በሃሳቡ ጥበብ፣ በፊቱ ደስተኝነት፣ በፀጋውና
በለዛው፣ ቃሉ በመረዳት በመሆኑ፣ ስለከንፈሩ ቅልጥፍና ትእዛዙም
በግርማና በሰላም መልሱም ከእግዚአብሄር ፍርሃት ጋር ስለመሆኑ
ትደነቅ ነበር።

www.ethiopianorthodox.org

ፍርሃተ እግዚአብሔር አውሥአቶ።
5 ወዘንተ ኵሎ ትሬኢ ወታስተዐጽብ እምብዝኀ ጥበቡ። ወአልቦ
ወኢምንትኒ ንቱግ እምቃሉ ወእምነገሩ አላ ፍጹም ኵሉ ዘተናገረ።
6 ወይትጌበር ለሕንጸ ቤተ እግዚአብሔር ወይትነሣእ ወየሐውር ይምነ
ወጽግመ ቅድመ ወድኅረ ወያርእዮሙ መሳፍረ ወመዳልወ ወመሳውረ
ወለኪነተ ነህብትኒ ይነግሮሙ መሳፍለ ወመዋቅረ ወመኀንጻት
ወለወቀርተ እብንኒ ያርእዮሙ መአዝነ ወመንኰራኵረ ወመሳፍሐ።
7 ወኵሉ ይትገበር በቃሉ። ወአልቦ ዘይትአደው እምቃሉ። እስመ ከመ
ማኅቶት በውስተ ጽልመት ብርሃነ ልቡ ወከመ ኖፃ ብዝኀ ጥበቡ።
ወአልቦ ዘይሰወሮ እምቃለ አራዊት ወአዕዋፍ። ወለአጋንንትኒ ቀነዮሙ
በጥበቡ። ወኵሎ ይገብር በኪን ዘወሀቦ እግዚአብሔር ሶበ ሰአለ
ኀቤሁ። እስመ ኢሰአለ መዊአ ፀሩ ወኢሰአለ ብዕለ ወክብረ አላ ሰ
አለ ጥበበ ወአእምሮ ከመ የሀቦ በዘይኴንን ሕዝቦ ወበዘየሐንፅ
ቤቶ ወበዘያሜኒ ተግባሮ ሊግዚአብሔር በኵሉ ዘወሀቦ ጥበበ
ወአእምሮ።

## ፭ወ፮ ኀበ ተናገረ ንጉሥ ምስለ ንግሥት

1 ወትቤ ንግሥት ማክዳ ለንጉሥ ሰሎሞን ብፁዕ አንተ እግዚእየ
ዘከመዝ ለከ ተውህበ ጥበብ ወአእምሮ አንሰ እምፈተውኩ እኩን
ከመ አሐቲ እንተ ትንእስ እምአእማቲከ ከመ እሕፅብ እገሪከ
ወእስማዕ ጥበበከ ወእለቡ አእምሮተከ ወእግነይ ለመንግሥትከ
ወእትሐሠይ። ሚ መጠነ አደመኒ አውሥኦትከ ወጣእመ ቃልከ
ወሠናይ ሑረትከ ወአዳም ንባብከ ወጣእጣአ ጣእመ ቃልከ።
ወያስተፌሥሕ ልበ። ወያጠልል አዕፅምተ። ወይሜግብ አልባበ።
ወያጠእጥእ ወያሞግስ ከናፍረ። ወያጸንዕ መከየደ። ወእሬእየከ ከመ
በጥበብከ ዘእንበለ መስፈርት ወልቡናከ ዘእንበለ ሕጸት ከመ
ማኅቶት በውስተ ጽልመት ወከመ ሮማን በውስተ ገነት ወከመ
ባሕርይ ዘውስተ ባሕር ወከመ ኮከበ ጽባሕ በውስተ ከዋክብት
ወከመ ብርሃነ ወርኅ በውስተ ጊሜ ወከመ ጎሐ ጽባሕ ወሠርቀ
ፀሐይ በውስተ ሰማይ። ወአንሰ አእኵቶ ለዘአብጽሐኒ ወአርአየኒ
ኪያከ ወዘአኬደኒ ውስተ መድረከ ኆኅቲከ ወአስምዐኒ ቃለከ።
2 አውሥአ ንጉሥ ሰሎሞን ወይቤላ ጥበብሰ ወልቡና እምኔኪ
ሠረፀት። ሊተሰ በዘወሀበኒ አምላከ እስራኤል ዘሰአልኩ ወኀሠሥኩ
በኀቤሁ። ወአንቲሰ እንዘ ኢተአምሪ አምላከ እስራኤል ዘንተ ጥበበ
ዘአሥረፀኪ እምልብኪ ከመ ትርአዪ ኪያየ ትሑተ ገብሩ ለአምላኪየ
ወቀዋሚሃ ለደብተራሁ ዘእቀውም ወእትለአክ ወአንሶሱ ለእግዝእትየ
ታቦቱ ለአምላከ እስራኤል ጽዮን ቅድስት ሰማያዊት።
3 አንሰ ገብሩ ለአምላኪየ። ወኢኮንኩ አግዐዜ። ወኢኮንኩ ዘእትለአክ
በፈቃድየ አላ በፈቃዱ። ወአኮ ዝንቱ ቃል እምኀቤየ አላ ውእቱ
ዘአንበበኒ እነብብ ውእቱ ዘአዘዘኒ እገብር ውእቱ ዘሠርሐኒ
አሐውር ውእቱ ዘመሐረኒ እትናገር ውእቱ ዘአጥበበኒ እሌቡ።



5 ይህን ሁሉ ታይና ከጥበቡም ብዛት ታደንቅ ነበር። የተናገረው
ሁሉ ፍፁም ነበር እንጂ ከቃሉና ከነገሩ የሚጎድል አልነበረም።
6 ለእግዚአብሄር ቤትም ህንፃ ይሰራ ነበር። ይነሳና ወደ ግራና ቀኝ፣
ወደፊትና ወደ ሁዋላ ይሄድና ስፍሩን፣ መለኪያውን፣ የመቅረዙን
አሰራር ለአንጥረኞችም አቀላለጡን፣ አቀራረፁን፣ ለድንጋይ
ጠራቢዎችም ማእዘኑን፣ መንኩራኩሩንና ስፋቱንም ያሳያቸው ነበር።
7 የልቡ ብርሃን በጨለማ ውስጥ እንዳለ መብራት የጥበቡም ብዛት
እንደ አሸዋ ነበርና ሁሉ በቃሉ መሰረት ይሰራ ነበር። ከቃሉም
የሚተላለፍ አልነበረም። ከአውሬዎችና ከወፎችም ቋንቋ የሚሰወረው
አልነበረም። አጋንንትንም በጥበቡ ይገዛቸው ነበር። ወደ እሱ
በለመነ ጊዜ እግዚአብሄር በሰጠው ጥበብ ሁሉን ያደርግ ነበር።
ህዝቡን የሚፈርድበትንና የእግዚአብሄርን ቤት የሚሰራበትና
የእግዚአብሄርንም ስራ የሚያሳምርበትን ጥበብንና እውቀትን ይሰ
ጠው ዘንድ እንጂ ጠላቶቹን ድል ማድረግን፣ ብልፅግናና ክብርን
አልለመነምና።

## ፭፮ ንጉስና ንግስት እንደተነጋገሩ

1 ንግስት ማክዳም ንጉስ ሰሎሞንን አለችው። "እንደዚህ ያለ ጥበብና
እውቀት የተሰጠህ አንተ ጌታዬ ብፁእ ነህ። እኔ እግርህን እንዳጥብ፣
ጥበብህን እንድሰማና እውቀትህንም ልብ እንድል፣ ለመንግስትህ
እንድገዛና በጥበብህም እደሰት ዘንድ ከሴቶች ባሪያዎች ሁሉ
ከምታንሰው እንደ አንዷ በሆንኩ በወደድኩ። መልስህ፣ የቃልህ
ጣእም፣ የአማረው አካሄድህ፣ የተዋበው ንግግርህና የቃልህ ጣእም
ቅልጥፍና ምን ያህል ደስ አሰኘኝ። ልብን ያስደስታል። አጥንትን
ያለመልማል፤ ልብን ይመግባል። ያጠራልም ከንፈሮችን ያስውባል፤
መርገጫዬን ያጠነክራል። ጥበብህ ያለመለኪያ፣ ሐሳብህ ያለ ጉድለት
ነው። በጨለማ ውስጥ እንዳለ መብራት፣ በገነት እንዳለ ሮማን፣
በባህር ውስጥ እንዳለ እንቁ፣ በከዋክብት መካከል እንዳለ የንጋት
ኮከብ፣ በጉም ውስጥ እንዳለ የጨረቃ ብርሃን፣ እንደ ጥባት
ብርሃንና በሰማይ ውስጥ እንዳለ የፀሀይ አወጣጥ እንደሆንክ
አይሃለሁ። እኔን እዚህ ያደረሰኝንና አንተን ያሳየኝ፣ የበርህንም ደጃፍ
ያስረገጠኝንና ቃልህን ያሰማኝን አምላክ አመሰግነዋለሁ።"
2 ንጉስ ሰሎሞንም መለሰ። "ጥበብና ማስተዋል ከአንቺ ነቃች። ለእኔስ
የእስራኤል አምላክ ከእሱ በፈለግሁትና በለመንኩት መጠን ሰጠኝ።
አንቺ ግን የእስራኤልን አምላክ ሳታውቂ፣ የድንኳኑ ጠባቂ ቋሚ
የእስራኤል አምላክ ማደሪያ በሆነች ሰማያዊት ቅድስት ፅዮን ፊት
የምቆም፣ የምላክና የምመላለስ፣ የአምላኬ አነስተኛ ባሪያ የሆንኩ
እኔን ታይ ዘንድ ይህንን ጥበብ ከልብሽ አነቃሽ።
3 "እኔ የአምላኬ ባሪያ እንጂ ነፃ አይደለሁም። በእሱ ፈቃድ እንጂ
በእኔ ፈቃድ የምላክ አይደለሁም። ይህም ከእሱ እንጂ ከእኔ
አይደለም። እሱ ያናገረኝን እናገራለሁ። እሱ ያዘዘኝን አደርጋለሁ።

www.ethiopianorthodox.org

4 እስመ እንዘ መሬት አነ ሥጋ ረሰየኒ ወእንዘ ማይ አነ ሰብአ
ርጡዐ ረሰየኒ። ወእንዘ ነጠብጣብ ንስቲት ምራቅ እንተ ትተፋእ
ዲበ ምድር ወትኤብስ መልዕልተ ምድር በአርአያሁ ለሐኰኒ
ወበአምሳሊሁ ገብረኒ።

## ፳ወ፯ በ እ ን ተ ገ ባ ራ ዊ

1 ወእንዘ ዘንተ ይትናገራ ለንግሥት ርእዮ ለአሐዱ ገባር /ገባራዊ/
እንዘ ይጸውር እብነ ዲበ ርእሱ ወሣዕረ ወማየ ዲበ ክሣዱ ወስንቆ
ወአሣዕኒሁ ውስተ ሐቋሁ። ወለዕፀውኒ ደመሮን ውስተ እደዊሁ።
ወብሉያት ወስጡጣት አልባሲሁ። ወሐፉ ያንጠበጥብ እምነ ገጹ።
ወማየ ሣዕርኒ ይውኅዝ ውስተ ሰኰናሁ። ወኀለፈ እንተ ቅድሜሁ።
ወእንዘ የሐውር ይቤሎ ቁም። ወቆመ።
2 ወተመይጠ ኀበ ንግሥት ወይቤላ ርኢ ዘንተ ምንት ፍድፍድናየ
እምነ ዝንቱ። ወምንት ኀይስናየ እምነ ዝ። ወምንት ክብርየ እምነ
ከመ ዝ። እስመ አነሂ ሰብእ ወሐመድ ዘጌሥመ እከውን ዕፄ
ወጺአተ። ወይእዜ እንከ አስተርኢ ከመ ዘኢይመውት ለዓለም። መኑ
እምአጋዞ ለእግዚአብሐር እመ ወሀቦ ለዝንቱ ከማየ። ወሊተኒ ሶበ
አገበረኒ ከማሁ አኮኑ ክልኤነ ሰንቡእ* ወከመ ሞተዝ ሞትየ። ወከመ
ሕይወተ ዝ ሕይወትየ። ወዝንቱ ይጸንዕ በግብር እምኔየ። እስመ
ይውህቦሙ ኀይለ ለድኩማን በከመ ፈቀደ ለሊሁ። ወይቤሎ ሑር
ኀበ ግብርከ።
3 ወካዕበ ይቤላ ለንግሥት ምንት በቍዔትነ ለእጓለ እመሕያው ለእመ
ኢገበርነ ንስሓ ወምሕረተ በዲበ ምድር። አኮኑ ኵልነ ከንቱ ሣዕረ
ገዳም ዘበጊዜሁ ይየብስ ወያውዕዮ በእሳት በዲበ ምድር። ንትረሰይ
በመባልዕት ጥዑማት ወበአልባስ ክቡራት። እንዘ ሕያዋን ጽዩዓን።
ወንትረሰይ በመዓዛት ወበዕፍረታት። እንዘ ሕያዋን ምውታን
በኀጢአት ወበአበሳት። እንዘ ጠቢባን ኮነ አብዳነ በኢሰሚዕ
ወበዕልወታት። እንዘ ክቡራን ኮነ ኅሡራነ በተጠይሮ ወበሰጊድ
ለጣዖት። ሰብእሰ ክቡር ዘተፈጥረ በአምሳለ እግዚአብሔር። ወለእመኒ
ገብረ ሠናየ ይከውን ከመ እግዚአብሔር። ሰብእሰ ከንቱ። ወለእመኒ
ገብረ ኀጢአተ ይከውን ከመ ዲያብሎስ። ዲያብሎስሰ ዕቡይ ዘአበየ
ተአዝዞ ለፈጣሪሁ። ወኵሎሙ ዕቡያን እምሰብእ የሐውሩ በፍኖቱ።
ወይትኳነኑ ምስሌሁ። ወእግዚአብሐር ያፈቅሮሙ ለትሑታን። ወእለ
ይገብሩ ትሕትና የሐውሩ በፍኖት። ወይትፌሥሑ በውስተ
መንግሥቱ። ወብፁዕሰ ዘአእመረ ጥበበ ዝውእቱ ንሥሓ ወፈሪሀ
እግዚአብሐር።

* ሰንቡእ ብሂል ሰብእ ብሂል ይላል።

- 18 -

እሱ ያበጀልኝን እሄዳለሁ። እሱ ያስተማረኝን እናገራለሁ። እሱ የገለፀልኝን
አስተውላለሁ።
4 እኔ መሬት ሳለሁ ስጋ፤ ውሃ ሳለሁ የረጋ ሰው አደረገኝ። ትንሽ
ነጠብጣብ በምድር ላይ የምትተፋና በምድር ላይ የምትደርቅ ምራቅ
ሳለሁ እንደ እሱ አድርጎ ሰራኝ። በምሳሌውም አደረገኝ።"

## ፳፯ ስለ ገበሬው

1 ለንግስቲቱ ይህንን ሲናገራት ኣንድ ገበሬ በራሱ ላይ ድንጋይ፣
በትከሻው ላይ ሳርና ውሃ፤ በወገቡም ስንቁንና ጫማዎቹን
ተሸክሞ፤ እንጨቶቹንም በእጆቹ ይዞ፤ ልብሶቹም ኣሮጌዎችና
ቀዳዳዎች ሆነው፤ ከፊቱም ላቡ እየተንጠባጠበ፤ በእጁም የውሃ
መያዣ (ከስፌት የተሰራ) ይዞ ሲሄድ "ቁም!" ኣለው። ቆመም።
2 ንጉሱም ወደ ንግስቲቱ ተመልሶ "ይህንን ተመልከቺ። ከዚህ የእኔ
ብልጫ ምንድን ነው? የእኔስ መሻል ከእዚህ በምንድን ነው?
የእኔስ ክብር ከዚህ በምን ይበልጣል? እኔም ነገ ትልና የምሸት
ሰውና ኣመድ ነኝና። እነሆ ዛሬ ለዘላለም እንደማይሞት ሆኜ
እታያለሁ። ለእሱ እንደኔ ያለ እንዳይሰጠው፤ እኔን ደግሞ
እንደእሱ ገበሬ እንዳያደርገኝ እግዚኣብሄርን ያስገደደው ማን
ነው? ወይስ ሁለታችንም ሰዎች ኣይደለንም*? ሞቴም እንደዚህ
ሰው ሞት፤ ህይወቴም እንደዚህ ሰው ህይወት ነው። እሱ በስራ
ከእኔ ይበልጣል። ምክንያቱም እሱ እንደ ወደደ ለደካሞች ሃይልን
ይሰጣቸዋልና" ኣላት። ገበሬውንም "ወደ ስራህ ሂድ" ኣለው።
3 ደግሞም ንግስቲቱን ኣላት። በምድር ላይ ንስሃና ምህረት
ካላደረግን በቀር የሰው ልጆች ጥቅማችን ምንድን ነው? ሁላችንስ
ከንቱዎችና በጊዜው የሚደርቅና በምድር ላይ በእሳት
የሚያቃጥሉት የዱር ሳር ኣይደለንም? ህያዋንና የሸተትን ሳለን
በሚጣፍጡ ምግቦችና በከበሩ ልብሶች እንሸለማለን እናምራለን
ህያዋን ሳለን በሃጢኣትና በበደል ምክንያት ሙቶች ነን። ብልሆች
ሳለን ባለመስማትና በክህደት ምክንያት ሰነፎች ሆን። የከበርን
ሳለን በትእቢት፤ በሟርትና ለጣኦት በመስገድ ጎስቋሎች ሆንን።
ሰው በእግዚኣብሄር ኣምሳል የተፈጠረ ክቡር ነው። መልካም ቢሰራ
እንደ እግዚኣብሄር ይሆናል። ሃጢኣትን ቢያደርግ ግን እንደ
ዲያቢሎስ ከንቱ ነው። ዲያብሎስ የፈጣሪውን ትእዛዝ እንቢ ያለ
ትእቢተኛ ነው። ከሰዎች ትእቢተኞች የሆኑት ሁሉ በመንገዱ
ይሄዳሉ። ከእሱም ጋር ይፈረድባቸዋል። እግዚኣብሄርም ትሁቶችን
ይወዳቸዋል። ትህትናን የሚሰሩ በመንገዱ ይሄዳሉ። በመንግስቱም
ውስጥ ይደሰታሉ። ጥበብን ያወቀ ሰው ብፁእ ነው። ጥበብም ንስሃ
መግባትና እግዚኣብሄርን መፍራት ነው።

* ግዕዙ እኛ ሁለታችን "ሰንቡእ" አይደለንም? ብሎ "ሰንቡእ" ማለት ሰው
ማለት ነው በማለት ይተረጉማል።

www.ethiopianorthodox.org

4 ወዘንተ ሰሚዓ ንግሥት ትቤ ምንተ ሠነየኒ ቃልከ ወእፎ ሐወዘኒ
ነገርከ ወመክሥተ አፉከ። ንግረኒኬ ለዘይረትዕ ለከእሰግድ ሎቱ።
ወንሕነሰ ንሰግድ ለፀሐይ በከመ መሀሩነ አበዊነ እስመ ንብል ውእቱ
ፀሐይ ንጉሦሙ ለአማልክት። ወባዕዳንሂ እለ እምታሕቴነ ቦ እለ
ይሰግዱ ለአእባን ወቦ እለ ይሰግዱ ለአዕዋም ወቦ እለ ይሰግዱ
ለግልፋዋት ወቦ እለ ይሰግዱ ለአምሳለ ወርቅ ወብሩር። ወንሕነሰ
ንሰግድ ለፀሐይ እስመ ውእቱ ያበስል ሲሳየ። ወካዕበ ውእቱ ያበርህ
ጽልመተ ወየአትት ፍርሀተ። ንብሎ ንጉሥነ። ወንብሎ ፈጣሪነ።
ወንሰግድ ሎቱ ከመ አምላክነ። እስመ አልቦ ዘነገረነ ባዕደ አምላከ
ዘእንበሌሁ። ወባሕቱ ሰማዕነ ከመ ብከሙአ ለእስራኤል ካልእ
አምላክ ዘኢነአምኖ ንሕነ። ወዜነዉነ ከመ አውረደ ለክሙ ታቦተ
እምሰማያት።* ወወሀበክሙ ጽላተ ሥርአተ መላእክት በእደ ሙሴ
ነቢዩ ሰማዕነ ዘንተ። ወይወርድእ ኀቤክሙ ለሊሁ ወይትናገረክሙ
ወይኤምረክሙ ፍትሐ ወትእዛዘ።

## ፳ወ፫ በ እ ን ተ ዘ ከ መ አ ዘ ዛ ለ ን ግ ሥ ት

1 ወአውሥአ ንጉሥ ወይቤላ በአማን ርቱዕ ይስግዱ ለእግዚአብሔር
ለዘገብረ ኵሎ ሰማየ ወምድረ ወባሕረ ወየብሰ ፀሐየ ወወርኀ
ከዋክብተ ወፀዳላተ ዕፀወ ወአእባነ እንስሳ ወአዕዋፈ አራዊተ
ወሐርገጻተ ዓሣተ ወአናብርተ ቢሐተ ወዐንጕጊተ ወመባርቅተ
ወፀዓዓተ ደመናተ ወነጐድጓደ ሠናያነ ወእኩያነ ሎቱ ለባሕቲቱ
ንስግድ ይደሉ በፍርሀት ወበረዓድ በፍሥሓ ወበሐሤት እስመ ውእቱ
እግዚእ ኵሉ ፈጣሬ መላእክት ወሰብእ።
2 ወውእቱ ይቀትል ወየሐዩ። ወውእቱ ይቀሥፍ ወይሣህል።
ዘያነሥእ ለነዳይ እምድር።
ወያሌዕሎ እመሬት ለምስኪን።
ወያኀዝን ወያሥተፌሥሕ። የዐርግ ወያወርድ።
3 አልቦ ዘይግዕዞ። እስመ እግዚእ ውእቱ ለኵሉ። ወአልቦ ዘይብሎ
ምንተ ገበርከ። ወሎቱ ይደሉ ስብሐት ወአኰቴት እምኀበ መላእክት
ወሰብእ።
4 ወበእንተ ዘትብሊሰ ወሀበክሙ ታቦተ ሕግ በአማን ተውህበት ለነ
ታቦተ አምላከ እስራኤል እንተ ተፈጥረት እምቅድመ ኵሉ ፍጥረት
በምክረ ስብሐቲሁ። ወትዛዞሂ አውረደ ለነ ጽሒፎ ከመ ናእምር
ፍትሖ ወኵነኔሁ ዘሠርዐ በደብረ መቅደሱ።
5 ወትቤ ንግሥት እምይእዜሰ ኢይሰግድ ለፀሐይ አላ እሰግድ ለፈጣሬ
ፀሐይ አምላከ እስራኤል። ወይእቲ ታቦተ አምላከ እስራኤል ትኩነኒ
እግዝእትየ ሊተ ወለዘርእየ እምድኅሬየ ወለኵሉ መንግሥትየ እለ
እምታሕቴየ። ወበእንተዝ አነ ረከብኩ ሞገሰ በቅድሜከ ወበቅድመ

*ከሰማይ የወረደ ፅላት እንጅ ታቦት አይደለም።ዘጸአ. 31፥18

- 19 -

4 ንግስቲቱም ይህንን ሰምታ አለችው። "ቃልህ እንደት አማረኝ?
ነገርህና የአፍህ አገላለጥስ እንደት አስደሰተኝ? ይሁንና ልሰግድለት
የሚገባውን ንገረኝ አለች። እኛ ግን አባቶቻችን እንዳስተማሩን
ለፀሃይ እንሰግዳለን። ፀሃይም የአማልክት ንጉስ ነው እንላለን።
እንዲሁም ከእኛ በታች ያሉ ሌሎች ለድንጋይ የሚሰግዱ አሉ።
ለዛፎችም የሚሰግዱ አለ ። ለጣኦትም የሚሰግዱ አሉ። ከወርቅና
ከብር ለተሰሩ ምስሎች የሚሰግዱ አሉ። እኛ ግን ለፀሃይ እንሰ
ግዳለን። ምግብ ያበስላል። ጨለማን ያበራልና። ፍርሃትን
ያስወግዳል። ንጉሳችን እንለዋለን። ፈጣሪያችን እንለዋለን። እንደ
ፈጣሪያችንም እንሰግድለታለን። ከእሱ በቀር ሌላ አምላክ የነገረን
የለምና። ዳሩ ግን እናንተ እስራኤላውያን እኛ የማናውቀው ሌላ
አምላክ እንዳላችሁ ሰምተናል። እሱም በነቢዩ በሙሴ እጅ ከሰ
ማያት ታቦትን እንዳወረደላችሁ በመላእክትም ስርአት ፅላትን
እንደሰጣችሁ ሰምተናል። ወደ እናንተ እንደሚወርድና እንደሚናገራችሁ
ፍርዱንና ትእዛዙን እንድሚያመላክታችሁ ይህን ሁሉ ሰምተናል"
አለችው።

## ፳፫ ንግስቲቱን እንዳዘዛት

1 ንጉሡም መለሰ። "ሰማይና ምድርን፣ ባህሩንና የብሱን፣ ፀሃይንና
ጨረቃን፣ ከዋክብትንና ብርሃናትን፣ እንጨቶችንና ድንጋዮችን፣
እንስሳትንና ወፎችን፣ አራዊትንና የባህር እንስሳዎችን፣ አሳዎችንና
ነብሮችን፣ ጉማሬዎችንና አርጃኖዎችን፣ መብረቆችንና ነጎድጓዶችን፣
መልካሞችንና ክፉዎችን ሁሉ ለፈጠረ፣ ለእግዚአብሄር በእውነት
ሊሰግዱለት ይገባል።
2 እሱ ይገድላል፤ ያድናልም። ይቀስፋል፤ ይቅርም ይላል። ደሃውን
ከትቢያ የሚያነሳ፣ ምስኪኑንም ከመሬት ከፍ ከፍ የሚያደርገው፣
የሚያሳዝንም፣ የሚያስደስትም፣ የሚያወጣና የሚያወርድ እሱ ነው።
3 የሁሉ ጌታ ነውና የሚነቅፈው የለም። ምን አደረግክ የሚለው
የለም። ከሰውና ከመላእክት ለእሱ ምስጋና ይገባል።
4 የህጉን ታቦት ሰጣችሁ ስለምትይውስ በምስጋናው ምክር ከፍጥረት
ሁሉ በፊት የተፈጠረችውን ታቦት በእውነት ተሰጥታናለች።
በመቅደሱም ተራራ ያስረዳውን ፍርዱንና ግዛቱንም እናውቅ ዘንድ
ትእዛዙን ጽፎ አወረደልን።"
5 ንግስቲቱም "እንግዲህስ የፀሃይ ፈጣሪ ለሆነው ለእስራኤል አምላክ
እሰግዳለሁ እንጂ ለፀሃይ አልሰግድም። ይህችም የእስራኤል አምላክ
ታቦት ለእኔ እና ከእኔ በሁዋላ ለዘሬ እመቤት ትሆናለች። ከእኔም
በታች ላሉት መንግስቶቼም እንዲሁ። ስለዚህ እኔ በፊትህና
ካንተም ዘንድ ባደረሰኝ፣ ቃልህን ባሰማኝ፣ ፊትህን ባሳየኝና
ትእዛዝህን በገለጠልኝ በፈጣሪየ በእስራኤል አምላክ ፊት ሞገስ
አገኘሁ" አለችው።

www.ethiopianorthodox.org

አምላከ እስራኤል ፈጣሪየ ዘአብጽሐኒ ኀቤከ ወአስምዐኒ ቃለከ።
ወአርአየኒ ገጸከ ወአለበወኒ ትዛዘከ።
6 ወአተወት ቤተ። ወወትረ ተሐውር ወትገብእ ወትሰምዕ ጥበቢሁ
ወተዐቅብ በልባ ወውእቱኒ የሐውር ኀቤሃ ወይነግራ ኵሎ ዘተሰ
አለቶ። ወይእቲኒ ተሐውር ኀቤሁ ወትሴአሎ ወያየድአ ኵሎ
ዘፈተወት።
7 ወእምድኅረ ነበረት ፮ ወርኀ ፈቀደት ገቢአ ብሔራ። ወለአከት
ኀቤሁ እንዘ ትብል ወአንሰአ እምፈተውኩ እንበር ምስሌከ።
ወይእዜሰ በእንተ ኵሉ ሕዝብ እፈቅድ ገቢአ ብሔርየ። ወዘንተ ዘሰ
ማዕኩ ይረስዮ እግዚአብሔር ዘይፈሪ በውስተ ልብየ ወውስተ ልበ
ኵሎሙ እለ ሰምዑ ምስሌየ።
እስመ ኢይመልእ እዝን በአፅምኦ። ወኢይመልእ ዐይን በነጽሮ
ጥበብከ።
8 ወአኮ ይእቲ ባሕቲታ ዘትመጽእ አላ ብዙኃን ይመጽኡ እምአህጉር
ወበሐውርት እምቅሩብ ወእምርትቅ። እስመ አልቦ ዘተረክበ ከማሁ
በጥበብ በውእቱ መዋዕል።
9 ወአኮ ሰብእ ባሕቲቶሙ ዘይመጽኡ ኀቤሁ ወዓዲ አራዊትኒ ወአዕዋፍ
ይመጽኡ ኀቤሁ ወይሰምዑ ቃሎ ወያነክሩ ጥበቦ ወይትናገሩ ምስሌሁ
ወይገብኡ ብሔሮሙ ወኵሉ ያነክር ጥበቢሁ ወያነክር በዘርእየ ወዘሰ
ምዐ።
10 ወሶበ ለአከት ኀቤሁ ከመ ትሑር ብሔራ ኀለየ በልቡ ወይቤ
ዘመጠነ ዝ ላህይት ብእሲት መጽአት ኀቤየ እምአጽናፈ ምድር
ምንተ ኣአምር እመ ይሁበኒ እግዚአብሔር ዘርዐ በውስቴታ በከመ
ትብህለ ውስተ መጽሐፈ ነገሥት።
11 ወሰሎሞንሰ ንጉሥ መፍቀሬ አንስት ውእቱ። ወአውሰበ እምነ
ዕብራውያን ወግብጻውያን ወከነናውያን ወኤዶማውያን ወኢዮባውያን
ወእሞሬፍ ወኮርጕ ወድሚስቆ ወሱርስት ወእምለ ነገርዎ እለ ሠናይ
ላህዮን። ወኮና ንግሥታት ፬፻ ወዕቁባት ፮፻።[28]
12 ወዘንተሰ ዘገብረ አኮ በዘምዎ አላ በኀልዮ ጥበብ ዘወህቦ
እግዚአብሔር ወተዘኪሮ ዘይቤሎ ለአብርሃም አበዝኀ ዘርዐከ ከመ
ኮከበ ሰማይ ወከመ ኆፃ ባሕር።[29]
13 ወይቤ በልቡ ምንተ ኣአምር እመ ይሁበኒ እግዚአብሔር ተባዕተ
ውሉደ በበ፩ ለለአሐቲ እምኔሆን። ወበእንተዝ ተጠቢቦ ገብረ ከመዝ
እንዘ ይብል ደቂቅየ ይረሱ አህጉረ ፀር ወይሥርውዎሙ ለእለ
ያመልኩ ጣኦተ። ወእሙንቱሰ ቀዳሚ ሕዝብ ነበሩ በሕግ ዘሥጋ።
እስመ ኢተውህቦሙ ጸጋ ዘመንፈስ ቅዱስ።
14 ወለእለ እምድኅረ ክርስቶስሰ ተውህቦሙ ይንበሩ በአሐቲ ብእሲት
በሕገ ሰብሳብ። ወሠርዑ ሎሙ ሐዋርያት እንዘ ይብሉ እለ ነሥኡ
ሥጋሁ ወደሞ ኵሎሙ አኀው እሙንቱ። እሞሙ ቤተ ክርስቲያን

[28] 1ነገ.11፥1
[29] ዘፍጥ.22፥17

- 20 -

6 ወደ ቤትም ገባች። ዘወትርም ትሄድና ትመለስ፣ ጥበቡንም ትሰማ፣
በልቧም ትጠብቀው ነበር። እሱም ወደ እሷ ይሄድ፣ የጠየቀችውንም
ሁሉ ይነግራት ነበር። እሷም ወደ እሱ ትሄድና ትጠይቀው ነበር።
እሱም የሻተችውን ሁሉ ይነግራት ነበር።
7 ስድስት ወሮችን ያህል ከቆየች በሁዋላ ወደ ሀገሯ ለመመለስ
ፈለገች። ወደ እሱም "እኔ ካንተ ጋር በተቀመጥሁ ደስ ባለኝ።
ይሁን እንጂ ስለ ህዝቡ ወደ ሀገሬ ለመመለስ እፈልጋለሁ።
ይህንን የሰማሁትን በልቡናየና ከእኔ ጋር በሰሙት ሰዎች ልብ
ውስጥ እንዲያፈራ ያድርገው። ጆሮ በመስማት፣ ኣይንም ጥበብን
በማየት ኣይመላም ስትል" ላከች።
8 ወደ ንጉሱም የምትመጣ እሷ ብቻ ኣልነበረችም። በዚያን ዘመን
በጥበብ እንደሱ ያለ ኣልተገኘም ነበርና ከየኣህጉራቱና ከየኣገሮቹ
ከሩቅና ከቅርብ ብዙዎች ወደ እሱ ይመጡ ነበር።
9 ወደ እሱ የሚመጡት ሰዎች ብቻ ኣልነበሩም። ኣራዊትና ወፎች
ሁሉ ወደ እሱ ይመጡ፣ ቃሉን ይሰሙ፣ ጥበቡን ያደንቁ፣ ከእሱ
ጋር ይነጋገሩና ወደ ሃገራቸው ይመለሱ ነበር፤ ሁሉ ጥበቡን
ያደንቅ፣ በሰማውና ባየውም ይደነቅ ነበር።
10 ወደ ኣገሯም ለመሄድ ወደ እሱ በላከች ጊዜ "እንደዚህ ያለ ደም
ግባት ያላት ሴት ከምድር ዳርቻ ወደ እኔ መጣች። በመጽሐፈ
ነገስት እንደተባለው[28] እግዚኣብሄር ከእሷ ዘርን ይሰጠኝ እንደሁ
ምን ኣውቃለሁ?" ሲል በልቡ ኣሰበ።
11 ንጉስ ሰሎሞን ሴቶችን ወዳጅ ነው። ከእብራውያንም፣ ከግብፃውያንም፣
ከከነኣንያንም፣ ከኤዶማውያንም፣ ከኢዮባውያንም፣ ከኣሞሪፍ፣ ከኮርጎ፣
ከደማስቆሳውያንም፣ ከኣርማናያንም መልከ መልካሞች ናቸው ብለው
ከነገሩት ሁሉ ኣገባ። ንግስታቱ ኣራት መቶ እቁባቱም ስድስት መቶ
ነበሩ።
12 ይህንን ያደረገው ግን በዝሙት ምክንያት ሳይሆን እግዚኣብሄር
የሰጠውን ጥበብ በመሻትና ለኣብርሃምም "ዘርህን እንደ ሰማይ
ኮከብና እንደ ባሕር ኣሸዋ ኣበዛልሃለሁ"[29] ያለውን በማሰብ ነበር።
13 በልቡም "ከእያንዳንዷ እግዚኣብሄር ኣንዳንድ ወንድ ልጅ ይሰጠኝ
እንደሆነ ምን ኣውቃለሁ" ኣለ። "ልጆቼ የጠላትን ኣገር ይውረሱ።
ጣኦታትን የሚያመልኩትንም ይንቀሏቸው" ብሏልና ይህን ሁሉ
በብልሃት እንዲህ ኣደረገ። እነሱ በስጋ ህግ የመጀመሪያ ህዝቦች
ነበሩ። የመንፈስ ቅዱስ ፀጋ ግን ኣልተሰጣቸውም ነበር።
14 ከክርስቶስ ልደት በሁዋላ ግን በኣንዲት ሴት እንዲፀኑ በጋብቻ
ህግ ተደነገገላቸው። ሃዋርያትም "ስጋውንና ደሙን የተቀበሉ ሁሉ
ወንድማማች ናቸው። እናታቸው ቤተ ክርስቲያን፣ ኣባታቸው

[28] 1ነገ.11፥1
[29] ዘፍጥ.22፥17

www.ethiopianorthodox.org

ወአቡሆሙ እግዚአብሔር። ወይጸርሑ ምስለ ክርስቶስ ዘተመጠዉ
እንዘ ይብሉ አቡነ ዘበሰማያት።
15 ወለሰሎሞንሰ ኢሠርዐ ሎቱ በአንስት። ወኢኮኖ ጌጋየ በአውስቦ።[30]
16 ወለመሃይምናንሰ ተውህቦሙ ሕግ ወትእዛዝ ከመ ኢያብዝኑ አንስተ
በከመ ይቤ ጳውሎስ እለሰ ብዙኃተ አንስተ አውሰቡ መቅሠፍተ
ኀሠሡ ለርእሶሙ። ወዘሰ አውሰበ አሐተ ብእሲተ አልቦ
ኀጢአት።ወሕገ አንስት ካልኣት ከላእነ ዘበእንተ ወሊድ ይቤሉ
ሐዋርያት በውስተ ሲኖዶስ።

## ፳ወ፱ በእንተ ፫፻፲ወ፰

1 ወንሕነኒ ሠራዕነ ምስሌሆሙ ጠዪቀነ ዘነበቡ እለ እምቅድሜነ
ሐዋርያት ንሕነ ፫፻፲ወ፰ አርታዕነ ወአስተራታዕነ ሃይማኖተ እንዘ
እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ምስሌነ ወውእቱ ሠርዐ ዘከመ ንሜህር
ወዘከመ ንገብር ሃይማኖተ።
2 ወውእቱሰ ንጉሥ ሰሎሞን ለእከ ላቲ ለንግሥት እንዘ ይብል
እምድኅረ መጻእኪሰ ዝየአ ለምንት ተሐውሪ ዘእንበለ ትርአዪ ሕገ
መንግሥትወዘከመ ይትገበር ድራር ለኅሩያነ መንግሥትነ በአምሳለ
ጻድቃን ወዘከመ ይሰደዱ አሕዛብ በአምሳለ ኃጥአን ወእምኔሁ
ትረክቢ ጥበበ። ንዒ በድኅሬየ ወትነብሪ በፀዳልየ በደባትር
ወእፌጽም ለኪ ወተአምሪ ሕገ መንግሥትኒ እስመ አፍቅርኪያ
ለጥበብ ወትነብር ምስሌኪ እስከ ደኃሪትኪ ወለዓለምኒ እስመ
ትንቢት ያስተርኢ በኀበ ልሳን።
3 ወካዕበ ይእቲኒ ለአከት እንዘ ትብል እንዘ አብድ አነ ኮንኩ ጠባበ
በተሊወ ጥበብከ። ወእንዘ ምንንት አነ እምአምላከ እስራኤል ኮንኩ
ኅሪተ በእንተ ዛቲ አሚኖት እንተ ውስተ ልብየ። ወእምይእዜሰ
ኢያመልክ ባዕደ አምላከ ዘእንበሌሁ። ወበዝንቱሰ ዘትቤ ፈቀድከ
ከመ ትወስከኒ ጥበበ ወክብረ ወእመጽእ በከመ ፈቀድከ።
4 ወተፈሥሐ ሰሎሞን በእንተዝ። ወአልበሶሙ ለኅሩያኒሃ። ወወሰከ
ካዕበተ ዲበ ማዕዱ። ወአዘዘ በአስተጠአጥኦ ኵሎ ሥርዓተ ቤቱ
ወኵሎ ዕለተ እንዘ ድሉት ቤቱ ለሰሎሞን ንጉሥ። ወአሜሃ
አስተዳለወ በክብር ፈድፋደ በፍሥሓ ወበሰላም በጥበብ ወበምሕረት
ምስለ ኵሉ ትሕትና ወየውሃት።
5 ወእምዝ ተሠርዐ ማዕድ ዘንጉሥ በከመ ሕገ መንግሥት።
ወንግሥትኒ ቦአት እንተ መፍልስተ በጸዳል ወበክብር። ወነበረት
አንጻረ ድኅሬሁ ኀበ ትሬኢ ወትትኤመር ወትጤይቅ ኵሎ።
ወታነክር ፈድፋደ በዘርእየት ወበዘሰምዐት። ወትሴብሖ በልባ
ለአምላከ እስራኤል። ወታስተአጽብ ክብረ ቤተ መንግሥት ዘርእየት
እስመ ትሬኢ ለሊሃ። ወላቲሰ አልቦ ዘይሬእያ በከመ ገብረ ላቲ

[30] 1ቆሮ.7 ይመልከቱ።



እግዚአብሄር ነው" ሲሉ ወሰኑላቸው። ከተቀበሉት ከክርስቶስ ጋርም
"በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ" እያሉ ይጮሃሉ።
15 ለሰሎሞን ግን ስለ ሴቶች አልተወሰነለትም ነበርና ጋብቻው
ሃጢአት አልሆነበትም ነበር።
16 ቅዱስ ጳውሎስ "ብዙ ሴቶችን ያገቡ በራሳቸው መቅሰፍትን
ፈለጉ። አንዲት ሴት ያገባ ግን ሃጢአት የለበትም"[30] እንዳለው
ሴቶችን እንዳያበዙ ለምእመናን ህግና ትእዛዝ ተሰጥቷቸዋል።
ሐዋርያትም በሲኖዶስ ስለ መውለድ ምክንያት "የብዙ ሴቶችን ህግ
ከለከልን"[31] አሉ።

## ፳፱ ስለ ሶስት መቶ አስራ ስምንቱ

1 እኛም "ከእኛ በፊት የነበሩት ሃዋርያት ያዘዙትን ተረድተን ከእነሱ
ጋር ደነገግን። እኛ ሶስት መቶዎቹ አፀናን። አስፀናንም። እሱም
እንዴት እንደምናስተምርና ሃይማኖትንም እንዴት እንድናደርግ
ደነገገልን" አሉ።
2 ንጉስ ሰሎሞንም ለንግስቲቱ "እዚህ ከመጣሽ በሁዋላ ህገ መንግስቱንና
ለመንግስቱ ባለስልጣኖችም በፃድቃን ምሳሌ እንዴት የራት ግብዣ
እንደሚደረግ፣ አህዛብም በሃጥኣን ምሳሌ እንዴት እንደሚሰደዱ
ሳታይ ለምን ትሄጃለሽ? ከዚህ ትምህርትን ታገኛለሽና በሁዋላየ
ነይ። በድንኳኖችም ውስጥ በብርሃኔ ትቀመጫለሽ። እጨርስልሻለሁ።
ህገ መንግስቱንም ታውቂያለሽ። ጥበብን ወደሻታልና እስከ መጨረሻው
ድረስና ለዘለኣለሙም ከኣንቺ ጋር ትኖራለች። ትንቢት በንግግር
ይገለጣልና" ሲል ላከባት።
3 እሷም ደግሞ "እኔ ሰነፍ ሳለሁ ጥበብከን በመከተል ጥበበኛ ሆንኩ።
የተናቅሁም ሳለሁ በልቤ ውስጥ ባለችው በዚህች እምነት ምክንያት
ከእስራኤል ኣምላክ ዘንድ የተመረጥኩ ሆንኩ። ከእንግዲህስ ከእሱ
በቀር ሌላ ኣምላክ ኣላመልክም። ጥበብና ክብርን ትጨምርልኝ
ዘንድ ስለ ወደድከው ግን እንደ ፈቃድህ እመጣለሁ" ስትል ላከች።
4 ሰሎሞንም ስለ እዚህ ነገር ተደሰተ። ምርጦቹንም ኣለበሳቸው።
በማእዱም ላይ በእጥፍ ጨመረ። የቤቱንም ስርኣት ሁሉ ዝግጅት
ኣዘዘ። የንጉሱ የሰሎሞን ቤትም በየቀኑ የተዘጋጀ ነበር። በዚህም
ጊዜ በብዙ ክብር፣ በደስታና በሰላም፣ በጥበብና በምህረት
ከትህትናና ከየዋሃት ጋር ኣዘጋጀው።
5 ከዚህ በህዋላ በመንግስቱ ህግ መሰረት የንጉሱ ማእድ ተሰራ።
በትእይንቱ የተማረከችውም ንግስት በታላቅ ብርሃንና ክብር ገባች።
በትክክል በምትመለከትበትና ሁሉንም በምትረዳበት ከንጉሱ

[30] 1ቆሮ.7 ይመልከቱ።
[31] ?

www.ethiopianorthodox.org

በጥበብ ዘአሠነየ ምንባረ ነጺፎ ሜላተ ወረቢቦ ቢሳጣተ ወገቢሮ
ምስካተ ወአብላቀ ወአፍሪጸ። ነዚሆ ዕፍረታተ ወረቢቦ ሜዓተ ወሰ
ሊካተ መሪጎ ቅንዐተ ወስጊናተ።

6 ወሶበ ይበውእዎ ለውእቱ ማኅደር ፈድፋደ ሠናይ መዐዛሁ።
ወያጸግብ ዘእንበለ ይብልዑ መባልዕተ ጣዕመ ጼናሁ።
7 ወይፌኑ ላቲ መባልዐ መጸምአ በምክር ወበጥበብ ወመሳትየ
መጺጸነ ሰመከ ወፍልፍለ ጥቢቃተ ወዘንተ ይገብር ወይውህባ
ለንግሥት ከመ ትብላዕ እምኔሁ።
8 ወሶበ ተፈጸመ ሥልሰ ወስብዐ ማዕደ ንጉሥ ወአተው መገብት
ወመማክርት ወመሐዛት ወአግብርት። ተንሥአ ንጉሥ ወሖረ ኀበ
ንግሥት ወይቤላ በባሕቲቶሙ ተናዘዚ ዝየ በእንተ ፍቅር እስከ
ነግህ።
9 ወትቤሎ መሐል ሊተ በአምላክከ አምላከ እስራኤል ከመ
ኢትትኀየለኒ እመቦ ለእመ ተስሕትኩ ሕገ ሰብእ ነኣሰ እወርድ
ውስተ ጻማ ወሕማም ወምንዳቤ በፍኖት።

## ፴ በእንተ ዘመሐለ ላቲ ንጉሥ ሰሎሞን

1 አውሥአ ወይቤላ እምሕል ለኪ ከመ ኢይትኄየለኪ። ወባሕቱ አንቲኒ
መሐሊ ከመ ኢትትኄየሊ ኵሎ ዘውስተ ቤትየ።
2 ወሰሐቀት ንግሥት ወትቤሎ እንዘ ጠቢብ አንተ ለምንት ከመ
አብድ ትትናገር። እሰርቅኑ ወሚመ አሀይድ ቤተ ንጉሥ ዘኢወሀበኒ
ንጉሥ። ኢይምሰልከ እግዚእየ በፍቅረ ንዋይ ዘመጻእኩ ዝየ።
ወመንግሥትየኒ ብዕልት በጸጋከ። ወአልቦ ዘይትኀጥአኒ እምዘፈቀድኩ።
አላ ዳእሙ መጻእኩ በኀሢሠ ጥበብከ።
3 ወይቤላ ለእመ አንቲ አምሐልክኒ ሊተ። ወመሐላሰ ይደሉ ለ፪ ከመ
ኢይትዐመፁ። ወለእመ ኢያምሐልክኒ ኢያምሕለኪ አነሂ።
4 ወትቤሎ መሐል ሊተ ከመ ኢትትኀየለኒ። ወአነሂ እምሕል ከመ
ኢይትኀየል ንዋየከ። ወመሐለ ላቲ ወአምሐላ።
5 ወዐርገ ንጉሥ ዲበ ምስካቡ በ፩ ገጽ። ወላቲኒ አስተዳለዊ ላቲ
ምስካበ በ፩ ገጽ።



በስተሁዋላ ተቀመጠች። ባየችውና በሰማችው ፈጽማ ትደነቅና
የእስራኤልንም አምላክ ታመሰግን ነበር። ያየችውንም የቤተ
መንግስቱን ክብር ታደንቅ ነበር። እሷ ሁሉን ታይ ነበር። እሷን
ግን ማንም አያያትም ነበር። የመመልከቻ ስፍራውን በግምጃና
እንዲሁም መጋረጃንም ዘርግቶ በከበሩ ድንጋዮችና በፈርጥ አድርጎ
ሚአትና ስሌክት የተባሉ ሽቶዎችን ረጭቶና ቅንአትና ስሂናት
በተባሉ የሽቱና የእጣን እንጨቶች አስውቦ በጥበብ ሰርቶት
ነበርና።
6 ወደዚህ ቤትም ሲገቡ መአዛው እጅግ ያማረ ነበር። የሽታውም
ጣእም ሳይበሉ የሚያጠግብ ነበር።
7 በብልሃትና በጥበብም የተዘጋጀ ውሃ የሚያስጠሙ ምግቦችና
የኮመጠጡ መጠጦችን፣ የተለያዩ የአሳና የበርበሬ አይነቶችንና
የተሞከቱ ዶሮዎችን ይልክላት ነበር። ይህንን እያደረገ ትመገበው
ዘንድ ለንግስቲቱ ይሰጥ ነበር።
8 ሶስትና ሰባት የንጉስ ማእድ ከተፈፀመ በህዋላ መጋቢዎቹ፣
አማካሪዎቹ፣ አሳላፊዎቹና አገልጋዮቹ ተመለሱ። ንጉሱም ተነሳ።
ወደ ንግስቲቱም ሄደ። ለብቻቸውም ሆነው "እስከ ንጋቱ ድረስ
ስለ ፍቅር እዚሁ ተፅናኚ" አላት።
9 እሷም "ትንሿን የሰው ህግ ብሳሳት በመንገድ ላይ ወደ ድካም፣
ህማምና ችግር ውስጥ እገባለሁና እንዳትደፈረኝ በአምላክህ
በእስራኤል አምላክ ማልልኝ" አለችው።

## ፴ ንጉሱ ሰሎሞን እንደማለላት

1 ንጉሱም መለሰ። "እንዳልደፍርሽ እምልልሻለሁ። ነገር ግን አንቺም
በቤቴ ውስጥ ያለውን ሁሉ እንዳትደፍሪ ማይልኝ" አላት።
2 ንግስቲቱም ሳቀች። "አንተ ብልህ ሳለህ ስለምን እንደ ሰነፍ
ትናገራለህ? እሰርቃለሁ? ወይስ ንጉሱ ያልሰጠኝን የንጉሱን ቤት
እቀማለሁ? ጌታዬ ሆይ! በገንዘብ ፍቅር ምክንያት እዚህ የመጣሁ
አይምሰልህ። መንግስቴም በንብረት ሃብታም ናት። ከምሻው ሁሉ
የሚጎድለኝ አንዳችም የለም። ጥበብክን ብቻ በመሻት መጣሁ
እንጅ" አለችው።
3 እሱም "መሃላ እንዳይከዳዱ በሁለት ሰዎች መካከል ይገባልና
ካማልሺኝ አንቺም ደግሞ ማይልኝ። ካላማልሽኝ ግን እኔም
አላምልሽም" አላት።
4 እሷ ግን "እንዳትደፍረኝ ማልልኝ፤ እኔም ደግሞ ገንዘብህን
ላልደፍር እምላለሁ" አለችው። እሱም ማለላት። እሷንም አማላት።
5 ንጉሱም በአንድ በኩል ወደ መኝታው ወጣ። ለእሷም ደግሞ
በሌላው በኩል መኝታ አዘጋጀላት።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

6 ወይቤሎ ለሕፃን ገብር ሕፅብ መቃልደ ወደይ ፃኅበ ማይ እንዘ
ትሬኢ ንግሥት። ወዕፁ ኀዋኀወ ወኑም። ወዘንተ ዘይቤሎ በካልእ
ልሳን ዘኢታአምር ንግሥት። ወገብረ ከማሁ ወኖመ።
7 ወንጉሥሰ ዓዲሁ ኢኖመ። ወይሬኢ ርእሶ ከመ ንውም።
ወያስተሓይጽ።
8 ወቤቱሰ ለሰሎሞን ንጉሥ ሌሊተኒ ብርህት ከመ መዓልት። እስመ
ገብረ በጥበብ ባሕርያተ ብሩሃተ አምሳለ ፀሐይ ወወርኀ ወከዋክብት
ውስተ ጠፈረ ቤቱ።
9 ወንግሥትኒ ኖመት ንስቲተ። ወሶበ ነቅሐት የብሰ አፉሃ በጽምእ።
እስመ በጥበቡ ዘወሀባ መፃምአ። ወፈድፋደ ጸምአት ወየብሰ አፉሃ።
ወእርመስመሰት አፉሃ። ወኢረከበት ጠለ። ወኀለየት ሰቲየ ማይ
ዘርእየት። ወአስተሐየጸት ወነጸረት ኀበ ንጉሥ ሰሎሞን። ወመሰላ
ዘኖመ ጽኑዐ ንዋመ። ወውእቱሰ ኢኖመ አላ ይጸንሕ እስከ
ትትነሣእ ከመ ትሰርቅ ማየ ለጽምኣ።
10 ወተንሥአት እንዘ ኢታደምፅ በእገሪሃ። ወሖረት ኀበ ውእቱ ማየ
መቅለድ። ወአንሥአት ከመ ትስተይ ማየ። ወአኀዛ እደሃ ዘእንበለ
ትስተይ ማየ። ወይቤላ ለምንት ተዐደውኪ መሐላ ዘመሐልኪ ከመ
ኢትትኀየሊ ኵሎ ዘውስተ ቤትየ።
11 ወአውሥአት በፍርሃት ወትቤ ቦኑ ተዓድዎ መሐላ በሰትየ ማይ።
12 ወይቤላ ንጉሥ ቦኑ ዘርእይኪ ዘይኄይስ እምነ ማይ በታሕተ ሰማይ።
13 ወትቤ አበስኩ ለርእስየ። ወአንተሰ ንጹሕ እምነ መሐላ። ወኅድገኒ
እሰትይ ማየ ለጽምእየ። ወይቤላ ዮጊኬ ኮንኩ ንጹሐ እመሐላኪ
ዘአምሐልክኒ።
14 ወትቤሎ ንግሥት ኩን ንጹሐ እምመሐላ። ወባሕቱ ኅድገኒ እስተይ
ማየ። ወኅደጋ ትሰትይ ማየ። ወእምድኅረ ሰትየት ማየ ገብረ
ፈቃዶ። ወኖሙ ኀቡረ።
15 ወእምድኅረ ኖመ አስተርአዮ ለሰሎሞን ንጉሥ ፀሐይ ብሩህ ወረደት
እምሰማያት። ወአብርሀት ላዕለ እስራኤል ፈድፋደ። ወእምዝ ጕንዲያ
ግብተ ተመሥጠት ወሠረረት እስከ ብሔረ ኢትዮጵያ። ወአብርሀት
በህየኒ ፈድፋደ እስከ ለዓለም። እስመ አፍቀረት ነቢረ ህየ።
ወጕንደይኩ እመ ትገብእ ውስተ እስራኤል ወኢገብአት።
16 ወካዕበ ጕንዲዮ ሠረቀ ብርሃን። ወወረደ ፀሐይ እምሰማያት ውስተ
ብሔረ ይሁዳ። ወአብርሀ ፈድፋደ እምቀዲሙ። ወእስራኤልሰ
አስተአከይዎ ለፀሐይ እምላህቡ። ወኢሖሩ በብርሃኑ።
17 ወውእቱኒ ፀሐይ ተሀየዮሙ ለእስራኤል። ወእሙንቱሂ ቀንዑ ላዕሌሁ።
ወተሰእነ ሰላም ማእከሌሆሙ ወማእከለ ፀሐይ። ወአንሥኡ እደዊሆሙ
ላዕሌሁ ምስለ አብትር ወመጣብሕ። ወፈቀዱ ከመ ያጥፍእዎ
ለፀሐይ። ወአጽለምዎ ለኵሉ ዓለም በድልቅልቅ ወጊሜ። ወመሰሎሙ
ዘኢይሠርቅ ሎሙ ዳግመ። ወአማሰኑ ብርሃኖ ወደበይዎ። ወዐቀቡ
ዓለመ። ወፈድፋደሰ በቀዳሚ ባሕር ወበደኃሪ ባሕር ለኢትዮጵያ
ወለሮም። ወለእስራኤልሰ ተሀየዮሙ ፈድፋደ። ወዐርገ ዲበ መንበሩ
ዘትካት።

- 23 -

6 ወጣቱንም አገልጋይ "ጋን አጥበህ ንግስቲቱ እያየች ማድጋ ውሃ
አስቀምጥበት። በሩንም ዘግተህ ተኛ" አለው። ይህንንም ያለው
ንግስቲቱ በማታውቀው ቋንቋ ነው። እንደ ተባለው አድርጎ ተኛ።
7 ንጉሱ ግን የተኛ ይመስል ነበር። ሆኖም ነገሩን ያወጣና ያወርድ
ነበር እንጅ አልተኛም።
8 በቤቱ ጣራ ላይ በባህርያቸው እንደ ፀሃይ፣ ጨረቃና ከዋክብት
የሚያበሩ እንቁዎችን በጥበብ አድርጎበት ነበርና የሰሎሞን ቤት
እንደ ቀን ያበራ ነበር።
9 ንግስቲቱም ጥቂት ተኛች። በብልሃት የሚያስጠሙ ምግቦችን
አስጋብቷት ነበርና በነቃች ጊዜ አፏ በጥማት ደረቀ። እጅግም
ተጠማች። አፏም ደርቆ ነበርና ልምላሜን አላገኘችም። ካየችውም
ውሃ ልትጠጣ አስባ ታወጣና ታወርድም ነበር። ወደ ንጉሱም
ተመለከተች። ከባድ እንቅልፍ የተኛ መሰላት። እሱ ግን ለጥሟ
ውሃን ለመስረቅ እስክትነሳ ይጠብቅ ነበር እንጂ አልተኛም።
10 በእግሯም ድምፅ ሳታሰማ ተነስታ ወደ ጋኑ ውሃ ሄደች።
ውሃውንም ትጠጣ ዘንድ አነሳች። እሱም ገና ሳትጠጣ እጅዋን ይዞ
"በቤቴ ውስጥ ያለውን ሁሉ ላለመድፈር የማልሽውን መሃላ ለምን
ተላለፍሽ?" አላት።
11 እሷም "ውሃን መጠጣት መሃላን መተላለፍ ነው?" ስትል በፍርሃት
መለሰች።
12 ንጉሱም "ከሰማይ በታች ከውሃ የሚሻል አይተሻልን" አላት።
13 እሷም "ራሴ በድያለሁ። አንተ ግን ከመሃላህ ንፁህ ነህ። ይሁንና
ለጥማቴ ውሃን እጠጣ ዘንድ ተወኝ" አለችው። እሱም "እነሆ
ካማልሽኝ መሃላ ንፁህ ነኝ" አላት።
14 ንግስቲቱም "ከመሃላህ ንፁህ ሁን። ነገር ግን ከውሃው እንድጠጣ
ተወኝ" አለችው። ውሃም ትጠጣ ዘንድ ተዋት። ውሃ ከጠጣችም
በህዋላ ፈቃዱን ፈፀሙ። አብረውም ተኙ።
15 ከተኛም በህዋላ ለንጉሱ የምታበራ ፀሃይ ከሰማይ ወርዳ በእስራኤል
ላይ ስታበራ ታየው። ጥቂት ቆይታም ተነጠቀች። እስከ ምድረ
ኢትዮጵያም በረረች። እዚያም ከበፊቱ የበለጠ ለዘላለሙ አበራች።
ወደ እስራኤል አገር ትመለስ እንድሆን ጠበቀ። እዚያ መቀመጥን
ወዳለችና አልተመለሰችም።
16 ደግሞ ቆይቶ ብርሃን ወጣ። ከሰማያት ወደ ምድረ ይሁዳ ወረደ።
ከፊቱም የበለጠ አበራ። እስራኤልን ግን ከሙቀቱ የተነሳ አጥላሉት።
በብርሃኑም አልሄዱም።
17 ፀሃዩም እስራኤልን ችላ አላቸው። እነርሱም በርእሱ ላይ ቀኑ።
በመካከላቸውና በፀሃዩም መካከል ሰላም ጠፋ። ፀሃዩንም ያጠፉት ዘንድ
ወደዱ። መላውንም አለም በንውፅውፅታ እና በጉም አጨለሙት።
ደግሞም የማይወጣላቸው መሰላቸው። ብርሃኑንም አጠፉት። ከመሬት
ላይም ጣሉት። ከጨመሩበትም ቦታ ጉድጓዱን ጠበቁ። እሱ ግን እነሱ
ባልጠረጠሩበት በኩል ወጣ። በቅድሚያ ለአለሙ ሁሉ፣ በሁለተኛ ጊዜ

www.ethiopianorthodox.org

18 ወዘንተ ራእየ ሶበ ርእየ እንዘ ንውም ሰሎሞን ንጉሠ ደንገፀት
ነፍሱ ። ወተመሥጠት ሕሊናሁ ከመ መብረቅ ወነቅሀ ድንጉፁ።
19 ወካዕበ አንከረ በእንተ ንግሥት። እስመ ጽኑዕ ኀይላ ወሠናይ ላህያ።
ወንጽሕት በድንግልናሃ። ወነግሥት ፮ ዓመተ በብሔራ። ወእንዘ
ከመዝ ተድላሃ ወክብራ አንጽሐት ሥጋሃ።
20 ወትቤሎ ፈንወኒ እሑር ብሔርየ ወቦአ ኀበ ማኀደሩ ወወሀባ ኵሎ
ዘይትፈቀድ ክብረ ወብዕለ ወሠናያተ አልባሰ ዘየሀይድ አዕይንተ
ወኵሎ ክብረ ዘይትፈቀድ ለብሔረ ኢትዮጵያ ወራኵባተ ወሰረገላተ
መጠነ ፮ ሲሕ ዘፅዑን ምስለ ንዋየ ክብር ዘይትፈቀድ ወሰረገላተ
እለ ይዔዐኑ ዲበ ኖፃ ወሰረገላ ዘየሐውር ዲበ ባሕር ወሰረገላ
ዘይረውጽ በነፋሳት ዘገብረ በከመ ጥበብ ዘወሀቦ እግዚአብሔር።

## ፴ወ፩ በእንተ ዘወሀባ ትእምርተ ለንግሥት

1 ወተፈሥሐት ወወፅአት ከመ ትሑር። ወአስተፋነዋ በብዙኀ ግርማ።
2 ወአግኀዛ እንተ ባሕቲቶሙ። ወአውፅአ ሕልቀተ እምአፅባዕቱ እንተ
ትንእስ። ወወሀባ ለንግሥት ወይቤላ ንሥኢ ከመ ኢትርስዕኒ።
ወለእመቦ ዘረከብኩ እምውስቴትኪ ዘርዐ ዝንቱ ይኩኖ ትእምርተ።
ወለእመ ኮነ ተባዕተ ይምጻእ ኀቤየ። ወሰላመ እግዚአብሔር የሀሉ
ምስሌኪ።
3 ወእንዘ እነውም ምስሌኪ ርኢኩ ራእየ ብዙኀ በሕልም ከመ ሠረቃ
ፀሐይ በውስተ እስራኤል ተመሥጠት ወሠረረት ወአብርሀት ለብሔረ
ኢትዮጵያ። እንዳዒ ለእመ ብኪ ትትባረከ ሀገርኪ። እግዚአብሔር
የአምር።
4 ወአንቲሰ ዕቀቢ ዘነገርኩኪ ከመ ታምልኪዮ ለእግዚአብሔር በኵሉ
ልብኪ ወትግበሪ ፈቃዶ። እስመ ውእቱ ይቀሥፎሙ ለዕቡያን።
ወይሣህሎሙ ለትሑታን። ወይነሥት መናብርቲሆሙ ለኃያላን።
ወያከብሮሙ ለነዳያን። እስመ ሞት ወሕይወት እምኀቤሁ። ወብዕል
ወንደት በፈቃዱ ይትወሀብ። እስመ ኵሉ ሎቱ። ወአልቦ ዘየዐብዮ
ለትእዛዙ ወለኵነኔሁ በሰማይ ወበምድር በባሕር ወበቀላያት።
ወእግዚአብሔር የሀሉ ምስሌኪ።
5 ወሖረት በሰላም ወተፋነዉ።

## ፴ወ፪ ዘከመ ወለደት ወበጽሐት ብሔራ

1 ወሖረት ወበጽሐት ውስተ ሀገረ ባላ ዘዲሳርያ በተስዐቱ አውራኀ
ወበኀምስቱ ዕለታት እምዘ ተፈነወት በኀቤሁ። ወአኀዛ ማሕምም
ወወለደት ሕፃነ ተባዕተ ወወሀበቶ ለሐፃኒት። ወአተውት በብዙኀ
ግርማ።

- 24 -

ለኢትዮጵያና ለሮም አበራ። እስራኤላውያንን ግን ፈጽሞ ችላ
አላቸው። በዘላለማዊ ዙፋኑም ተቀመጠ።
18 ንጉስ ሰሎሞንም ተኝቶ ሳለ ይህንን ራእይ ባየ ጊዜ ነፍሱ
ደነገጠች። ሃሳቡም እንደ መብረቅ ተነጠቀች። ደንግጦም ተነሳ።
19 ደግሞም ስለ ንግስቲቱ ተደነቀ። ሃይሏ ብርቱ፤ ለዛዋም ያማረ፤
በድንግልናዋም ንፅህት ነበረችና ስድስት አመት ነገሰች። ተድላዋና
ክብሯም እንዲህ ሆኖ ሳለ ስጋዋን አነፃች።
20 ንጉሱንም "እሄድ ዘንድ ተወኝ" አለችው። ወደ ቤቱም ገባ።
ለሃገረ ኢትዮጵያ የሚገባውን ሃብትና ክብር፤ ለአይን ያማሩ ጥሩ
ጥሩ ልብሶችን ሁሉ ሰጣት። የግመል ባዝራዎችን፤ የክብር እቃ
የተጫኑ ስድስት ሺህ ሰረገላዎችን፤ በአሸዋ ላይ የሚጫኑ
ሰረገላዎችን፤ በባህር ላይ የሚንሳፈፉ ሰረገላዎችን፤ በነፋስ ላይ
የሚበሩ ሰረገላዎችን እግዚአብሄር እንደ ሰጠው ጥበብ መጠን
ሰጣት።

## ፴፩ ለንግስቲቱ ምልክት እንደሰጣት

1 ደስም ተሰኛች። ትሄድም ዘንድ ወጣች። በብዙ ግርማም ሸኛት።
2 ለብቻቸውም ፈቀቅ አድርጎ ከትንሿ ጣቱ ቀለበትን አወጣ።
"ለንግስቲቱም እንዳትረሽኝ እንቺ። ዘርን ብታገኚ ምልክት
ይሆናል። ወንድ ከሆነ ወደ እኔ ይምጣ። የእግዚአብሄር ሰላም
ከአንቺ ጋር ይሁን" ብሎ ሰጣት።
3 "ከአንቺ ጋር ተኝቼ ሳለሁ በእስራኤል አገር ፀሃይ እንደወጣችና
እንደ ተነጠቀች ለኢትዮጵያ አገርም እንዳበራች ብዙ ህልምን
አየሁ። አገርሽ በአንቺ ምክንያት ትባረክ እንድሆነ እንጃ።
እግዚአብሄር ያውቃል።
4 አንቺ ግን በሙሉ ልብሽ እግዚአብሄርን ታመልኪው ዘንድና
ፈቃዱንም ትፈፅሚ ዘንድ የነገርኩሽን ጠብቂ። እሱ ትእቢተኞችን
ይቀስፋቸዋል። የተዋትረዱትንም ይምራቸዋል። ሞትና ህይወት በእሱ
ዘንድ ናቸውና። ብልፅግናና ድህነትም በእሱ ፈቃድ ይሰጣሉ። ሁሉ
በእርሱ ነውና በሰማይም ቢሆን፤ በምድርም ቢሆን፤ በባህርም
ቢሆን፤ በጥልቁም ቢሆን፤ የእሱን ትእዛዝና ፍርድ የሚቃወም
የለም። እግዚአብሄር ከአንቺ ጋር ይሁን። በሰላምም ሂጂ" አላት።
5 በሰላምም ሄደች። ተሰነባበቱም።

## ፴፪ እንደወለደችና አገሯ እንደደረሰች

1 እሷም ሄደች። ከእሱ ከተሰናበተች ከዘጠኝ ወራትና አምስት ቀናት
በሀዋላ ዲሳሪያ ውስጥ ባላ ከተባለ ሃገር ደረሰች። ህመምም ያዛት።
በብዙ ክብርና ተድላም ወንድ ልጅን ወለደች። ለሞግዚትም
ሰጠችው።

www.ethiopianorthodox.org

2 ወይእቲሰ ነበረት እስከ ይትፌጸም መዋዕለ ንጽሓ ወእምዝ አተወት ሀገራ በብዙኀ ግርማ።

3 ወአብኡ መኳንንቲሃ አምኃ ለእግዝእቶሙ እለ ነበሩ ሀየ። ወሰገዱ ወገነዩ ላቲ። ወተፈሥሑ በእትወታ ኵሉ አድያም። ወአልበሰቶሙ ሠናየ አልባሰ ለክቡራኒሆሙ። ወቦ ለዘወሀበት ወርቀ ወብሩረ ወያክንተ ወሜላተ ወኵሎ ንዋየ ወሀበት ዘይትፈቀድ።

4 ወአርትዐት መንግሥታ ወአልቦ ዘተዐደወ እምቃላ እስመ አፍቀረታ ለጥበብ። ወእግዚአብሔር አጽንዐ መንግሥታ።

5 ወልሕቀ ውእቱ ሕፃን። ወሰመየቶ ስሞ በይነ ልሕከም /ኢብነ እልሐኪም/

6 ወኮነ ሎቱ ፲ወ፪ ዓመት። ወየሐትቶሙ ለመሐዛእሁ ሐፃንያኒሁ ወይብሎሙ መኑ አቡየ። ወይብልዎ ሰሎሞን ንጉሥ።

7 ወሖረ ኀበ እሙ ንግሥት ወይቤላ አ ንግሥት ዐይድዕኒ መኑ አቡየ። ወትቤሎ ንግሥት በቁጥዓ እንዘ ታጌርሞ ከመ ኢይፍቅድ ሐዊረ ለምንት ትሴአለኒ በእንተ አብ። አነ ይእቲ አቡከ ወእምከ። ወባዕደ ኢትኅሥሥ።

8 ወወጽአ እምኔሃ ወነበረ ወካዕበ ወሥልሰ ይሴአላ ወያጽሕባ ከመ ትንግሮ ወአሐተ ዕለተ ነገረቶ እንዘ ትብል ርኁቅ ብሔሩ። ወዕፁብ ፍኖቱ። ወኢትፍቅድ ሀየ።

9 ወውእቱሰ ወልድ በይነ ልሕከም ኮነ ላሕየ። ወኵሉ ማኅፈዱ ወአባሉ ወንብረተ ክሣዱ ይመስል ሰሎሞንሃ[31] ንጉሠ አባሁ። ወአዕይንቲሁ ወአቍያጺሁ ወኵሉ ፍኖቱ ይመስል ሰሎሞንሃ ንጉሠ።

10 ወሶበ ኮነ ሎቱ ዕሥራ ወክልኤተ ዓመተ ተምህረ ኵሎ ጸብአ ወፈረሰ ወንዒወ አራዊት ወኵሎ ዘበሕገ ውርዙት።

11 ወይቤላ ለንግሥት አሐውር እነጽር ገጸ አቡየ። ወእገብእ ዝየ በፈቃደ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል።

## ፴ወ፫ ዘከመ ወረደ ንጉሠ ኢትዮጵያ

1 ወጸውዐቶ ለታምሪን ሊቀ ነጋድያኒሃ። ወትቤሎ ተደለዉ ለመንገድከ ወውስዶ ለዝንቱ ወልድየ እስመ አጽሐበኒ ሌሊተ ወመዓልተ ፈድፋደ በሕቁ። ወታበጽሖ ኀበ ንጉሥ። ወታገብኦ በዳኅን ዝየ ለእመ ሠምረ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል።

2 ወአስተዳለወት ሥንቀ በከመ ብዕሎሙ ወክብሮሙ ወኵሎ ንዋየ ዘይትፈቀድ ለፍኖት ወዘይትወሀብ አምኃ ለንጉሥ ወዘይከውን ዕረፍተ ለፍኖት።

[31] ዳዊትሃ የሚልም አለ።



2 የንፅህናዋም ዘመን እስኪፈፀም ቆየች። ከዚህ በሁዋላ በብዙ ግርማ አገሯ ገባች።

3 እዚያው የነበሩት መኳንንቶቿም ለእመቤታቸው እጅ መንሻን አገቡላት። ሰገዱላት። ተገዙላትም። አውራጃዎቹ ሁሉ በመግባቷ ተደሰቱ። ለከበሩትም የተዋቡ ልብሶች አለበሰቻቸው። ወርቅና ብር የሰጠችው አለ። ሰማያዊ ሃርና ግምጃ የሰጠችው አለ። ከገንዘቡ ሁሉ ለእያንዳንዱ እንደሚሻው ሰጠች።

4 መንግስቷንም አፀናች። ከቃሏም የተላለፈ የለም። ጥበብን ወዳታለችና እግዚአብሄርም መንግስቷን አፀናላት።

5 ህፃኑም አደገ። ስሙንም "በይነ ልህለም*" ብላ ጠራችው።

6 አስራ ሁለት አመትም ሆነው። አጫዋቾቹንና አሳዳጊዎቹንም አባቴ ማው ነው? እያለ ይመረምራቸው ነበር። እነሱም ንጉስ ሰሎሞን ነው ይሉት ነበር።

7 ወደ ንግስቲቱም ሄዶ "ንግስት ሆይ! አባቴ ማን እንደሆነ ንገሪኝ" አላት። ንግስቲቱም ልሂድ እንዳይል በቁጣ እያስፈራራች "ለምን ስለ አባት ትጠይቀኛለህ? አባትህም እናትህም እኔ ነኝ። ሌላ አትሻ" አለችው።

8 ከእሷም ወጥቶ ይቀመጣል። ሁለተኛና ሶስተኛም ጊዜ ይጠይቃትና ይመረምራት ነበር። "አንድ ቀንም አገሩ ሩቅ፣ መንገዱም ድንቅ ነውና ወደዚያ አትሻ" አለችው።

9 ይህ ልጅ ልህለም ግን ግርማ ሞገስ ነበረው። ግዝፈቱ፣ አካሉና የአንገቱ አተካከል አባቱን ንጉስ ሰሎሞንን* አይኖቹ፣ ጭኖቹና አካሄዱ ሁሉ ንጉሱን ሰሎሞንን ይመስል ነበር።

10 ሃያ ሁለት አመት ሲሆነውም ውጊያን፣ ፈረስ ግልቢያን፣ አደንና አንድ ጎልማሳ ሊማር የሚያስፈልገውን ሁሉ ተማረ።

11 ንግስቲቱንም "የአባቴን ፊት አይ ዘንድ እሄዳለሁ። በእስራኤል አምላክ፣ በእግዘአብሄር ፈቃድም ወደዚሁ እመለሳለሁ" አላት።

## ፴፫ የኢትዮጵያ ንጉስ እንደ ወረደ

1. የነጋዴዎችን አለቃ ታምሪንን ጠርታ "ለጉዞ ተዘጋጅ። በብዙም፣ በትንሹም ሌትና ቀን አስጨንቆኛልና ይህንን ልጅ ውሰደው። ከንጉሱም ታደርሰዋለህ። የእስራኤል አምላክ እግዚአብሄርም ቢወድ ወደዚህ ትመልሰዋለህ" አለችው።

2. ስንቅንም እንደ ሃብታቸውና ባለፀግነታቸው መጠን አዘጋጀች። ለመንገድ የሚያስፈልገውን ገንዘብ፣ ለንጉሱ የሚሰጠውን ስጦታና በመንገድ ላይ ለእረፍት የሚያስፈልገውን ትልክ ዘንድ ሁሉን

* ኢብን አልሃክምም የሚልም አለ።

* ዳዊትን የሚልም አለ።

www.ethiopianorthodox.org

ወአስተዳለወት ኲሎ ከመ ትፈንዎ ወወሀበት ለመኳንንትኒ እለ
የሐውሩ ምስሌሁ ወወሀበቶሙ ብዙኀ ንዋየ ዘይትፈቀድ ለፍኖት።
3 ወአዘዘቶሙ ከመ ኢይኅድግዎ ህየ ለወልዳ አላ ባሕቱ ያገብርዎ
ለንጉሥ ወያግብእዎ ኀቤሃ ወከመ ይሚም መንግሥተኒ ለብሔራ።
4 እስመ ኮነ ሥርዐታ ለብሔረ ኢትዮጵያ ትነግሥ ብእሲት ድንግል
እንተ ኢያውሰበት ብእሴ ወትቤ እም ይእዜሰአ ይንግሥአ ተባእትአ
እምዘመድከአ ወኢትንግሥአ ብእሲትአ ለዓለምአ ዘእንበለ ዝንቱ
ዘመድከአ ወዘርኡ ለትውልደ ትውልድ ወትለክአ ኀበ መጽሐፈ
ጠማር ውስተ መጽሐፈ ነቢያቲሆሙ ዘብርት ወታነብራ ውስተ ቤተ
እግዚአብሔር ዘተሐንጸ። ለተዝካር ወለትንቢት ለደኃሪ መዋዕል
ወከመ ኢይስግዱ ለፀሐይ ወለሠርጐ ሰማይ ወኢለአድባር ወአዕዋም
ወኢለአዕባን ወለዕፀወ ገዳም ወኢለቀላያት ወለዘውስተ ማይ
ወኢለግልፈዋት ወአምሳለ ወርቅ ወኢለአዕዋፍ ዘይሠርሩ ወኢይጤየሩ
ቦሙ ወኢያምልክዎሙ ወትንበርአ ዛቲ ሥርዐት ለዓለም። ወለእመቦ
ዘተዐደወ እምዛቲ ሥርዐት ለይኩንኖ ዘርዕከ ለዝሉፉ። ወባሕቱ
እምዘፈረ ልብሳ ዘንኤምኃ ለጽዮን ቅድስት ሰማያዊት ታቦተ ሕጉ
ለእግዚአብሔር። ሰላም ለጽንዐ መንግሥትከ ወለጥበብከ ብርሀት
ዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ፈጣሪነ።
5 ወአግኀሡቶ እንተ ባሕቲቱ ወወሀበቶ ይእተ ትእምርተ ዘወሀባ ሰ
ሎሞን ዘውስተ አጽባዕቱ ህልቀተ ከመ ያእምሮ ለወልዱ ወከመ
ይዘከር ነገራ ወኪዳና ዘተካየደት በኲሉ መዋዕለ ሕይወታ ከመ
ታምልኮ ለእግዚአብሔር ይእቲ ወእለ እምታሕተ መንግሥታ በኲሉ
ዘወሀባ እግዚአብሔር።
6 ወእምዝ ፈነወት በሰላም ወአርትዐ ፍኖተ ወሖሩ ወበጽሑ ውስተ
ብሔረ ደወለ ጋዛ ወይእቲ ሀገር ዘወሀባ ሰሎሞን ንጉሥ ለንግሥተ
ኢትዮጵያ።
7 ወበውስተ ግብረ ሐዋርያትሂ ጸሐፈ ሉቃስ ወንጌላዊ እንዘ ይብል
መጋቢሃ ውእቱ ለኲሉ ብሔረ ጋዛ ሕጽዋ ለንግሥተ ሕንደኬ ውእቱ
ዘአምነ በቃለ ሉቃስ ሐዋርያ።[32]

## ፴ወ፩ ዘከመ በጽሐ ብሔረ እሙ

1 ወሶበ በጽሐ ሀገረ እሙ ተፈሥሐ በህየ በክብር ወበአምኃ።
2 ወሶበ ርእይዎ መሰሎሙ ፍጹመ ሰሎሞንሃ ንጉሠ። ወሰገዱ ሎቱ
ወይቤልዎ በሐ ሕየው አበ ነጋሢ። ወያበውኡ ሎቱ አምኃ ወጋዳ

[32] የሃዋ.ስ.8፡26-44



አዘጋጀች። ከእሱ ጋር ለሚሄዱ መኳንንትም ሰጠች። ለመንገድ
የሚያስፈልገውን ብዙ ገንዘብም ሰጠቻቸው።
3. ለንጉሱ እጅ አስነስተው እንዲመልሱትና ለሃገሩም መንግስት
እንዲሾመው እንጂ እዚያ እንዳይተውት አዘዘቻቸው።
4. በኢትዮጵያ ወግ ቀድሞ ወንድ ልጅ ያላወቀች ድንግል ሴት
ትነግስ ነበር። "ከእንግዲህ ግን ከዚህ ከዘመድህና ከዘሩ ወንድ
ይነግሳል እንጅ ሴት ለዘላለም አትነግስም" ስትል ፃፈች።
"ደብዳቤውንም ወደ መፅሃፈ ነቢያት ትገለብጠዋለህ" አለች።
"በሁዋለኛውም ዘመን ለፀሃይ፣ ለሰማይ ሰራዊት፣ ለተራሮች፣ ለዛፎች፣
ለድንጋዮች፣ ለዱር ዛፎችና ለጥልቆችም ቢሆን፣ በውሃ ውስጥ
ላሉት ለጣኦታትም ቢሆን፣ ለወርቅ ምስልና ለሚበሩ አእዋፍ
እንዳይሰግዱ ለመታሰቢያና ለትንቢት እንዲሆን በብረት አስቀርፀህ
በምትሰራው በእግዚአብሄር ቤት ታስቀምጠዋለህ። እያሟረቱ
አያመልኩባቸውም። ይህችም ስርአት ለዘላለም ትኑር። ከዚህች
ስርአት የተላለፈ ቢኖር ዘርህ ለዘላለም ይፍረድበት። ዳሩ ግን ሰ
ላም ከምንላት ከቅድስትና ሰማያዊት ከሆነችው ከእግዚአብሄር ታቦተ
ህግ ከፅዮን ልብስ ጫፍ ስጠን። የእስራኤል አምላክ እግዚአብሄር
ለሰጠህ ብርሀት ለሆነችው ጥበብና ለመንግስትህ ጥናት ሰላም
እንላለን" አለች።
5. ብቻውንም ገለል አደረገችው። ሰሎሞን ልጁን እንዲያውቀው፣
ነገሯን እንዲያስብና በዘመኑ ሁሉ እሷና እግዚአብሄር በሰጣት በእሷ
መንግስት ስር ያሉት ሁሉ እግዚአብሄርን ያመልኩ ዘንድ
የገባችውን ቃል ኪዳን ያስታውስ ዘንድ ለምልክት እንዲሆን የሰ
ጣትን የጣቱን ቀለበት ሰጠችው።
6. ከዚህ በህዋላ በሰላም ላከችው። መንገዳቸውንም አቅንተው ሄዱ።
በጋዛ አውራጃ ካለውም ሃገር ደረሱ። ይህችም ሃገር ንጉስ ሰሎሞን
ለኢትዮጵያ ንግስት የሰጣት ናት።
7. ወንጌላዊው ሉቃስም በሐዋርያት ስራ "የህንደኬ ንግስት ጃንደረባ
ለጋዛ ክፍለ ሀገር ሹም ነው" ሲል ፃፈ። በሃዋርያው በሉቃስ[32]
ቃልም ያመነ እሱ ነው።

## ፴፩ እናቱ አገር እንደደረሰ

1 ከእናቱ አገርም ሲደርስ በተደረገለት ክብርና ስጦታ ተደሰተ።
2 ባዩትም ጊዜ ፍፁም ንጉስ ሰሎሞንን መሰላቸው። ሰገዱለትም።
"የንጉስ አባት ሆይ ። ሰላምና ጤና ላንተ ይሁን ለዘላለም ኑር"
ይሉት ነበር። እንደ ንጉሳቸውም እጅ መንሻዎችን፣ ስጦታን፣

[32] ሉቃስ ሳይሆን ፊሊጶስ መባል ነበረበት። የሃዋ.ስ.8፡26-44

www.ethiopianorthodox.org

ወመጋዝእ ወምሳሐተ ከመ ንጉሦሙ። ወተሀውከት ኵላ ብሔረ ጋዛ
እስከ ደወለ ይሁዳ እንዘ ይብሉ ዝንቱ ውእቱ ንጉሥ ሰሎሞን።
3 ወቦ ዘይቤ ንጉሥሰ ሀለወ በኢየሩሳሌም የሐንጽ ቤቶ እስመ ፈጸመ
ሐኒጸ ቤተ እግዚአብሔር። ወቦ እለ ይቤሉ ዝንቱ ውእቱ ሰሎሞን
ንጉሥ ወልደ ዳዊት። ወተሀውኩ ወተገአዙ።
4 ወፈነዉ መባርዲነ ሰብአ አፍራስ እለ የኀሥሥዎ ለንጉሥ ሰሎሞን
እመ ጥዩቀ ሀየ ሀሎ ወእመ ሀሎ ምስሌሆሙ። ወበጽሑ መባርዲን
ዐቀበተ ሀገረ ኢየሩሳሌም።
5 ወረከብዎ ለሰሎሞን ንጉሥ ሀየ ወሰገዱ ሎቱ ወይቤለዎ ባሕ
ሕየው አበ ነጋሢ። ሀገርሰ ተሀውከት በእንተ ዘመጽአ አሐዱ ነጋዲ
ዘይመስል አርአያከ ወአምሳሊከ ዘእንበለ ሕፀት ወብዕድና። ኪያከ
ይመስል በፀዳል ወበሥን በቆም ወበኀይስና ዘእንበለ ጥልቀት
ወተባዕዶ። ወአዕይንቲሁኒ ፍሡሐት ከመ ዘሰክረ ወይነ። ወአቍያጺሁኒ
ቁጢጣነ ወማኀፈደ ክሳዱኒ ከመ ማኀፈደ ዳዊት አቡከ። ወኪያከ
ይመስል በኵሉ ፍጹም አባል ዘይትማሰለከ።
6 አውሥአ ንጉሥ ወይቤሎሙ አይቴኬ ውእቱ ይፈቅድ ሐዊረ።
አውሥኡ ወይቤልዎ ለሊሁሰ ኢሐተትናሁ እስመ ግሩም ከማከ።
ወእሊአሁሰ ይቤሉ ሶበ ተስእልናሆሙ ወንቤሎሙ እምአይቴ መጻእክሙ
ወአይቴ ተሐውሩ። ወይቤሉነ መጻእነ እምአድያመ ሕንደኬ
ወኢትዮጵያ። ወነሐውር ብሔረ ይሁዳ ኀበ ሰሎሞን ንጉሥ።
7 ወሶበ ሰምዐ ዘንተ ንጉሥ ሰሎሞን ተሀውከ ልቡ። ወተሐሥየ
በመንፈሱ። እስመ አልቦ ውሉደ በውእቱ መዋዕል ዘእንበለ ሕፃን ዘሰ
ብዐቱ ዓም ዘስሙ ኢዮርብአም።
8 በከመ ዘከረ ጳውሎስ ወይቤ እስመ አዕበዳ እግዚአብሔር ለጥበበ ዝ
ዓለም ዘመከረ።[33] በጥበቡ ወይቤ እም፲፻ አንስት እወልድ ፲፻ ተባዕተ
ወእወርስ አህጉረ ፀር ወአመዘብር ጣዖታተ። ወኢወሀቦ ዘእንበለ
ሠለስቱ ደቂቅ። ዘይልህቅ ወልዱ ንጉሠ ኢትዮጵያ ወልዳ ለንግሥተ
ኢትዮጵያ በኵር ውእቱ።
9 ዘይቤ በትንቢት፤ መሐለ እግዚአብሔር ለዳዊት በጽድቅ ወኢይኔሥሕ።
ከመ እምፍሬ ከርሥከ አነብር ዲበ መንበርከ።[34] ወወሀቦ እግዚአብሔር
ሞገሰ በቅድሜሁ ለዳዊት ገብሩ። ወወሀቦ ዘይነብር ዲበ መንበረ
መለኮት እምዘርዑ በሥጋ እምድንግል ወይኳንን ሕያዋነ ወሙታነ።
ወይፈድዮ ለኵሉ በከመ ምግባሩ። ዘሎቱ ይደሉ ስብሐት ለእግዚእነ
ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለመ ዓለም አሜን።

---

[33] 1ቆሮ.1፥20

[34] 2ሳሙ.7፥12፤መዝ.132፥11



3 ፍሪዳዎችንና የምሳ ግብዣ ያደርጉለት ነበር። "ይህ ንጉስ ሰሎሞን
ነው" በማለትም የጋዛ ሃገር እስከ ይሁዳ ድረስ ታወከች። "ንጉሱ
የእግዚአብሄርን ቤት መስራት ስለጨረሰ በኢየሩሳሌም ቤቱን
በመስራት ላይ ይገኛል" ያሉም ነበሩ።" የዳዊት ልጅ ንጉስ ሰሎሞን
ነው" ያሉም ነበሩ። ታወኩ እርስ በርስም ተከራከሩ።
4 ንጉሱ ሰሎሞን በእርግጥ ከዚያ እንዳለ ወይም ከእነሱ ጋር ጋዛ
እንደሆነ የሚያረጋግጡ ፈረስ ጋላቢ ሰላዮችንም ላኩ። ሰላዮችም
የኢየሩሳሌምን አገር ከሚጠብቁት ዘንድ ደረሱ።
5 ሰሎሞንንም ከዚያው አግኝተው ሰገዱለት። "የንጉስ አባት ሆይ!
ሰላምና ጤና ለአንተ ይሁን። ለዘላለምም ኑር። አገሪቱ ያለ
አንዳች ጉድለትና ልዩነት አንተን መስሉ በመጣ በአንድ መንገደኛ
ታወከች። ንጣቱና አካሉ አንተን ይመስላል። ቁመናውና ውበቱም
ያለ ነቀፋና ልዩነት አንተኑ ይመስላል። አይኖቹ በወይን የሰከሩ
ይመስላሉ። ጭኖቹም ቀጫጭኖች ናቸው። የአንገቱ አተካከልም
እንደ አባትህ እንደ ዳዊት አንገት አተካከል ነው። አካሉ ሁሉ
ፍፁም አንተን ይመስላል" አሉት።
6 ንጉሱም መልሶ "ወዴት ሊሄድ ይፈልጋል?" አላቸው። እነሱም
መልሰው "እሱ እንዳንተ አስፈሪ ስለሆነ አልጠየቅነውም። ከእሱ
ጋር ያሉትን ግን 'ከየት መጣችሁ? ወዴትስ ትሄዳላችሁ?' ብለን
በጠየቅናቸው ጊዜ ከህንደኬና ከኢትዮጵያ አውራጃ መጣን። ወደ
ይሁዳ አገር ወደ ሰሎሞንም ዘንድ እንሄዳለን" አሉ።
7 ንጉሱ ሰሎሞንም ይህንን በሰማ ጊዜ ኢዮርብአም ከተባለው የሰባት
አመት ህፃን በቀር ልጅ አልነበረውምና በልቡ ታወከ።
በመንፈሱም ተደሰተ።
8 ቅዱስ ጳውሎስ "እግዚአብሄር የዚህ አለም ጥበበኞችን ጥበብ
ስንፍና አላደረገም?"[33] ብሎ እንደጠቀሰው ሰሎሞን ከሺህ ሴቶች
ሺህ ወንዶችን እወልዳለሁ። የጠላትንም አገር እወርሳለሁ፤
ጣኦታትንም አፈርሳለሁ።" ብሎ እንዲህ አደረገ። ከሶስት ልጆች
በቀር ልጅ አልሰጠውም።
9 ታላቁ ልጁ የኢትዮጵያ ንግስት ልጅ የሆነው የኢትዮጵያ ንጉስ
ነው። "እግዚአብሄር ከሆድህ ፍሬ በዙፋንህ ላይ አስቀምጣለሁ ብሎ
ለዳዊት በእውነት ማለ። አይጸጸትምም።"[34] ተብሎ ስለ እሱ
ትንቢት ተነገረለት። እግዚአብሄር ለባሪያው ለዳዊት በፊቱ ሞገስን
ሰጥቶታል። በመለኮት ዙፋን ላይ የሚቀመጥ በስጋ ከድንግል
የተወለደውንና ከዘሩ የሆነውን ሰጠው። እሱም በህያዋንና በሙታን
ላይ ይፈርዳል። ለእያንዳንዱም እንደስራው ይከፍለዋል። ይሄውም
ለዘላለሙ ምስጋና የሚገባው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

---

[33] 1ቆሮ.1፥20

[34] 2ሳሙ.7፥1፤መዝ.132፥11-12

www.ethiopianorthodox.org

10 ወበምድርኒ ወሀቦ ዘይከውን ንጉሠ ዲበ ታቦተ ሕጉ ጽዮን ቅድስት ሰ
ማያዊት ዘውእቱ ንጉሠ ኢትዮጵያ።
11 ወእለሰ ይነግሡ እለኢኮኑ እስራኤል ተዐድዎ ሕግ ወትእዛዝ ዘኢሠምረ
እግዚአብሔር።

፴ወ፩ በእንተ ዘለአከ ንጉሥ ሰሎሞን መልአከ ኀይሉ ኀበ ወልዱ

1 ወለአከ ሰሎሞን ንጉሥ መልአከ ኀይሉ ዘያሰምክ ዲበ እዴሁ ምስለ
አምኃ ወመባልዕት ወመስቴ ከመ ይትቀበሎ ለውእቱ ነጋዲ። ወሖረ
ምስለ ብዙኃት ሰረገላት ወበጽሐ ኀቤሁ ወአምኆ ወወሀቦ ኵሎ
ዘለአከ ሎቱ ሰሎሞን ንጉሥ ወይቤሎ አፍጥን መጺአ ኀቤየ እስመ
ነደ ልቡ ለንጉሥ በፍቅረ ዚአከ። እንዳዒ ዘየአምር ለሊሁ እመ
ወልዱ አንተ ወኢእመ እኁሁ አንተ። ኢኮንከ ባዕደ እምኔሁ በኵሉ
ራእይከ ወፍኖትከ። ወይእዜኒ ተንሥእ ፍጡነ እስመ ይቤለኒ
እግዚእየ ንጉሥ አፍጥን ወአምጽእ ኀቤየ በክብር ወበዕረፍት
ወበተድላ በፍሥሓ ወበሐሤት።
2 አውሥአ ውእቱ ወልድ ወይቤሎ አእኰቶ ለእግዚአብሔር አምላከ
እስራኤል እስመ ረከብኩ ሞገሰ እምእግዚእየ ንጉሥ ዘእንበለ እርአይ
ገጾ አስተፍሥሐኒ ቃሉ። ወይእዜኒ እሴፎ ለአምላከ እስራኤል ከመ
ያርእየኒ ኪያሁ ወያግብአኒ በዳኅን ኀበ እምየ ንግሥት ወብሔርየ
ኢትዮጵያ።
3 አውሥአ ኢዮአስ ወልደ ዮዳሔ መልአከ ኃይሉ ለንጉሥ ሰሎሞን
ወይቤሎ ለበይነ ልሕከም እግዚእየ ዝሰ ኀዳጥ ወትረክብ ዘየዐቢ
እምዝ ፍሥሓ ወተድላ እምኀበ እግዚእየ ንጉሥ።
4 ወበእንተሰ ዘትብል እምየ ወብሔርየ እምነእምከ ይኄይስ ሰሎሞን
ንጉሥ ወእምሀገርከ /ብሔርከ/ ትኄይስ ሀገርነ ዛቲ። ወሀገርከሰ ሰ
ማዕነ ከመ ምድረ በረድ ወጊሜ ከመ ምድረ ፀዳል ወመርቄ ከመ
ምድረ ደደክ ወአስሐትያ። እስመ ደቂቀ ኖኅ አመ ይትካፈሉ ምድረ
ሴም ወካም ወያፌት ነጸርዋ በጥበብ ለሀገርከ ከመ ስፍሕት ወረሀብ
ወምድረ አውሎ ወመርቄ ይእቲ ወወሀብዎ ለከነአን ወልደ ካም
ክፍሎ ሎቱ ወለዘርው እስከ ለዓለም።
5 ወምድርሰ እንቲአነ ምድረ ርስት ይእቲ ዘወሀበነ እግዚአብሔር በከመ
መሐለ ለአበዊነ ምድር እንተ ታውኅዝ ሀሊበ ወመዐረ እንተ ትከውን
ሲሳየ ዘእንበለ ኀዘን እንተ ትሁብ ፍሬሃ በበጊዜሃ ዘእንበለ ምንዳቤ
እንተ ዘልፈ ይሔውጻ እግዚአብሔር እምዓመት እስከ ርእሰ ዐውደ
ዓመት ኵላ ይእቲ ለከ ወንሕነኒ ለከ ወንከውነከ ርስተ ወትነብር
ውስተ ብሔርነ እስመ አንተ ዘርዐ ለዳዊት እግዚኡ ለእግዚእየ ወለከ
ይእቲ ዛቲ መንበር እንተ እስራኤል።
6 አውሥኡ መኳንንቲሁ ለነጋዲ ወይቤልዎ ትኄይስ ምድርነ እስመ
ሠናይ ነፋሰ ብሔርነ ዘአልቦቱ ላህብ ወሐሩር ወሠናይ ማየ ብሔርነ
ወጥዑም ወይውኅዙ አፍላግ። ወዓዲ አርዕስተ አድባርኒ ያውኅዙ ማየ
ወአኮ ከመ በሀገርከሙ ዘንከረ ዐዘቅተ ነዋኀተ ለማይ።



10 በምድር ደግሞ በታቦተ ህጉ በሰማያዊቷ ጽዮን ላይ ንጉስ
የሚሆንን ሰጠው። እሱም የኢትዮጵያ ንጉስ ነው።
11 እስራኤላውያን ሳይሆኑ የሚነግሱ ግን ህግንና ትእዛዝን ይተላለፋሉ።
ይህም በእግዚአብሄር ዘንድ የተወደደ አይደለም።

፴፩ ንጉስ ሰሎሞን የሃይል አዛዡን ወደ ልጁ እንደ ላከ

1 ንጉስ ሰሎሞን በጎኑ የሚቀመጠውን የሃይል አዛዡን ከስጦታ
ከመብልና ከመጠጥ ጋር ልጁን እንዲቀበል ላከ። ከብዙ ሰረገላዎች
ጋር ሂዶ ከእሱ ዘንድ ሲደርስ ሰላምታ ሰጠው። ንጉስ ሰሎሞን
የሰጠውን ሁሉ አቅርቦ "የንጉሱ የሰሎሞን ልብ ባንተ ፍቅር
ተቃጥሏልና ከእኔ ጋር ለመሄድ ፍጠን። ልጁ ወይም ወንድሙ
እንደሆንክ አውቆ እንደሆነ አላውቅም ። በመልክም በአካሄድህም
ከእሱ አትለይምና። አሁንም ጌታዬ ንጉሱ 'በክብር፣ በእረፍት፣
በተድላና በደስታ ፈጥነህ ወደ እኔ አምጣው' ብሎኛልና ቶሎ
ተነስ" አለው።
2 ልጁም "በጌታዬ በንጉሱ ዘንድ ሞገስን አግኝቻለሁና፣ ፊቱንም
ሳላይ አስደስቶኛልና የእስራኤል አምላክ እግዚአብሄርን አመሰ
ግነዋለሁ። እነሆ አሁንም የእስራኤል አምላክ ፊቱን እንዲያሳየኝና
ወደ እናቴ ንግስቲቱና ወደ አገሬ ኢትዮጵያም በደህና እንዲመልሰ
ኝ ተስፋ አደርጋለሁ" አለው።
3 የንጉሱ የሰሎሞን የሃይል አዛዥ የዮዳሄ ልጅ ኢዮአስም መልሶ
በይነ ልሃኪምን "ጌታዬ ይህ ጥቂት ነው። ከዚህ የሚበልጥ ደስታና
ተድላ ከጌታዬ ታገኛለህ" አለው።
4 "እናቴና አገሬ ስለምትለው ግን ከእናትህ ንጉስ ሰሎሞን፣
ከአገርህም ይህች አገራችን ትበልጣለች። አገርህ የበረዶና የጉም፣
የጨረርና የቆላ፣ የደጋና የውርጭ አገር እንደሆነች ሰምተናልና"
አለው። የኖህ ልጆች ምድርን በተካፈሉ ጊዜ ሴም፣ ካምና ያፌት
አገርህ ሰፊና ዝርግ፣ የአውሎና ቆላ አገር እንደሆነች አይተዋልና
ለካም ልጅ ለከነአን ሰጧት። ለዘለአለምም የእሱና የዘሩ ድርሻ
ሆነች።
5 "የእኛ አገር ግን ለአባቶቻችን እንደማለው እግዚአብሄር የሰጠን የርስት
ምድር ናት። ይህችም ምድር ወተትና ማርን የምታፈስ፣ ያለ ሃዘን
ምግብን የምትሰጥ፣ በየጊዜው ያለ ችግር ፍሬዋን የምትሰጥና እግዚአብሄር
ዘወትር ከአመት እስከ አመት ድረስ የሚጎበኛት አገር ናት። ሁሏም
ያንተ ናት። እኛም ያንተ ነን። ርስትህም እንሆናለን። በአገራችንም
ትቀመጣለህ። አንተ የጌታዬ ጌታ የዳዊት ዘር ነህና። ይህችም የእስራኤል
ዙፋን ያንተ ናትና"አለው።
6 የመንገደኛውም መኳንንት መልሰው "ሙቀትና ሃሩር የሌለው ሀገራችን
ነፋሱ ያማረ፣ ውሃው ጥሩና ጣፋጭ ነው፣ ምንጮቹም ይፈሳሉ፣

www.ethiopianorthodox.org

7 ወእኮ ዘንመውት በሐሩረ ፀሐይ አላ ቀትረኒ ንነው አራዊተ ቶራተ
ወኀየላተ ወአዕዋፈ ወእንስሳ። ወአራዊተነ ቦ ዘይሔውጸነ እግዚአብሔር
እምዓመት እስከ ርዕሰ ዐውደ ዓመት ወቦ በሐጋይኒ ዘይበልዑ እክለ
ከይደሙ በእግር ከመ ምድረ ግብጽ ወዕፀውኒ ይፈርዩ ሠናየ
ወሥርናየኒ ወሰገመ ወኵሉ ፍሬያቲነ ወእንስሳነ ሠናይ ወመንክር።
8 ወባሕቱ አሐተ ብከሙ ጥበብ እንተ ትኄይሱነ እምኔነ ወላቲ
ንነግድ ኀቤክሙ።
9 ወአውሥአ ኢዮአስ መልአከ ኀይሉ ለንጉሥ ምንት ትኄይስ
እምጥበብ እስመ ጥበብ ሣረረታ ለምድር ወአጽንዐቶ ለሰማይ
ወዐፀወት ልጐታተ ባሕር ከመ ኢትክድና ለምድር። ወባሕቱ
ተንሥኡ ንሑር ኀበ እግዚእየ እስመ ተነድፈት ልቡ በፍቅረ ዚኣከ።
ወሊተሰ ፈነወኒ ከመ አምጽእከ አስተፋጢንየ።
10 ወተንሥአ ወልደ ንግሥት ወአልበሶ ለኢዮአስ ወልደ ዮዳሄ ሠናየ
አልባሰ ወለእሊአሁ ሃምሳ ዕደው። ወተንሥኡ ከመ ይሑሩ
ኢየሩሳሌም ኀበ ንጉሥ ሰሎሞን። ወሶበ አልጸቁ ቀሪበ በኀበ ምርዋጸ
አፍራስ ቀደመ ኢዮአስ ወልደ ዮዳሄ ወቦአ ኀበ ንጉሥ ሰሎሞን።
ወነገሮ ከመ ሠናይ ራእዩ ወአዳም ቃሉ ወይመስል ኪያሁ ወፈድፋደ
ሠናይ በኵሉ ፍኖቱ።
11 ወይቤሎ ንጉሥ አይቴ ሀሎ አኮኑ ከመ ታምጽእ ኪያሁ ፍጡነ
ፈነውኩከ። ወይቤ ኢዮአስ ነየ አነ አመጽእ ዝየ ፍጡነ። ወሖረ
ወይቤ ተንሥእ እ ሊቅየ ወነዐ። ወእንዘ ያፈጥንዎ ሖዊረ አብጽሕዎ
ኀበ አንቀጸ ንጉሥ።
12 ወሶበ ርእይዎ ኵሉ ተዐይን ሰገዱ ሎቱ ወይቤሉ ነዋ ንጉሥ ሰ
ሎሞን ወጽአ እማኀደሩ። ወእለሂ ውስጠ ሶበ ይወፅኡ ያነክሩ
ወይገብኡ ድኀሬሆሙ። ወካዕበ ይሬእይዎ ለንጉሥ ዲበ መንበሩ
ወካዕበ ያነክሩ። ይወፅኡ ወይሬእይዎ በህየኒ ወየኀጥኡ ዘይብሉ
ወዘይትናገሩ።ወሶበ ቦአ ካዕበ ኢዮአስ ወልደ ዮዳሄ ከመ ይንግሮ
ለንጉሥ ምጽአተ ዚአሁ አልቦ ዘቆመ ቅድመ ንጉሥ አላ ኵሎሙ
እስራኤል ይጸዐቁ ከመ ይርአዩ ኪያሁ።

## ፴ወ፮ ምስለ ወልዱ ንጉሥ ሰሎሞን

1 ወወፅአ ኢዮአስ ወልደ ዮዳሄ ወአብኦ። ወሶበ ርእዮ ንጉሥ ሰሎሞን
ተንሥአ ወተቀበሎ። ወፈትሐ መዝግሐ ልብሱ እመትከፍቱ ወሐቀፎ
በእደዊሁ ዲበ እንግድዓሁ ወሰዐሞ አፉሁ ወፍጽሞ ወአዕይንቲሁ
ወይቤሎ ናሁ አቡየ ዳዊት ተሐደሰ በውርዙቱ ተንሥአ እምነ ሙታን።

- 29 -

የተራሮችም ጫፎች ውሃ ያፈልቃሉ፤ እንደ አገራችሁም ጥልቅ
የውሃ ጉድጓድ አንቆፍርም። "
7 "በቀትር የዱር አራዊትን፣ ብሆሮችን፣ ዋሊያ የወፍ አይነቶችን፣
(ቆቅ ጅግራ) እናድንበታለን እንጂ በፀሃይ ሃሩር የምንሞት
አይደለንምና አገራችን ትሻላለች አሉት። በክረምትም ከአመት እስከ
ዘመን መለውጫ ድረስ እግዚአብሄር እኛን የሚጎበኝበት ጊዜ አለ።
በበጋም እንደ ግብፅ ሃገር በአገራቸው እህሉን አበራይተው የሚበሉ
አሉ። እፀዋቱም ጥሩ ያፈራሉ። ስንደና ገብስ እንዲሁም
ፍራፍሬዎችና እንስሳዎቻችን ያማሩና የሚያስደንቁ ናቸው።"
8 "እናንተ ግን አንድ ነገር አላችሁ። ይሄውም ከእኛ ጥበብ የምትሻል
ጥበብ ናት። ወደ እናንተም የመጣነው በእሷ ምክንያት ነው" አሏቸው።
9 የንጉሱ የሃይል አዛዥ ኢዮአስም መልሶ "ጥበብ ምድርን
ሰርታታለች። ሰማይንም አጽንታዋለች። ምድርን እንዳታሰጥመው
የባህር ጥልቀትን ዘግታለችና ከጥበብ የተሻለ ምን አለ? ነገር ግን
ተነሱ። ወደ ጌታዩ እንሂድ። ልቡ በፍቅርህ ተነድፋለችና። እኔንም
በቶሎ እንዳመጣህ ልኮኛልና" ሲል መለሰ።
10 የንግስቲቱም ልጅ ተነሳ። የዮዳሄ ልጅ ኢዮአስም ያማሩ ልብሶችን
አለበሰው። ለሃምሳዎቹ ሰዎችም እንዲሁ። ከንጉሱ ሰሎሞን ዘንድም
ወደ ኢየሩሳሌም ሊሄዱ ተነሱ። ከፈረሶች መጋለቢያ ሊደርሱ
በተቃረቡ ጊዜ የዮዳሄ ልጅ ኢዮአስ ቀደመ። ወደ ንጉሱ
ሰሎሞንም ገብቶ መልኩ ሸጋ፣ ቃሉም ያማረ እንደሆነና እሱን
እንደሚመስል፣ ከሁሉም ደግሞ አካሄዱ ያማረ እንደሆነ ነገረው።
11 ንጉሱም "የላኩህ ፈጥነህ እንድታመጣው አይደለምን? ታዲያ የት
አለ?" አለው። ኢዮአስም "እነሆ ፈጥኜ አመጣዋለሁ" አለ። ሄዶም
"ጌታዬ ሆይ ተነስ ና" እያለ ይሄድ ዘንድ ያስቸኩለው ጀመረ።
ከንጉሱም በራፍ አደረሱት።
12 የከተማውም ህዝብ ሁሉ ባየው ጊዜ ሰገደለት። "እነሆ ንጉስ
ሰሎሞን ከቤቱ እየወጣ ነው" ይሉ ነበር። ከውስጥ ያሉትም
ሲወጡ ይደነቁና ወደ ሁዋላቸው ይመለሱ ነበር። ደግሞ ንጉሱን
በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ያዩታል። እንደገናም ያደንቃሉ። በዚያ
ያዩትም መጥተው የሚሉትንና የሚናገሩትን ያጡ ነበር። የዮዳሄ
ልጅ ኢዮአስም መምጣቱን ለንጉሱ ይነግር ዘንድ እንደገና በገባ
ጊዜ በንጉሱ ፊት የቆመ አልነበረም። እስራኤል ሁሉ እሱን ያዩ
ዘንድ ይጨነቁ ነበር ።

## ፴፮ ንጉስ ሰሎሞን ከልጁ ጋር እንደ ተገናኘ

1 የዮዳሄ ልጅ ኢዮአስም ወጥቶ አስገባው። ንጉሱ ሰሎሞን ባየው
ጊዜ ተነስቶና የልብሱን ቁልፍ ከትከሻው ፈትቶ ተቀበለው።
ደረቱንም በእጁ እቅፍ አድርጎ አፉንና ግንባሩን አይኖቹንም

www.ethiopianorthodox.org

ወተመይጠ ኀበ እለ ዜነውዎ ወይቤሎሙ ትቤሉኒ ይመስል ኪያከ ወዘእንተ
እኮ ማኅፈድየ አላ ማኅፈደ ዳዊት አቡየ እመ መዋዕለ ውርዙቱ ወፈድፋደ
ይሤኒ እምኔየ።
2 ወተንሥአ ሶቤሃ ወቦአ ውስተ ማኅደሩ ወአልበሶ ዲባጋተ ዘወርቅ ወቅናተ
ዘወርቅ ወአክሊለ ዲበ ርእሱ ወሕልቀተ ውስተ አጽባዕቱ ወአልበሶ አልባሰ
ክብር ዘየሐይድ አዕይንተ ወአንበሮ ዲበ መንበሩ ዘይትዐረይ ምስሌሁ።
3 ወይቤሎሙ ለመኳንንተ እስራኤል ዘትትሐመዩ በበይናቲክሙ ወትብሉኒ ከመ
አልብየ ውሉድ። ርእዩ ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ፍሬ ዘወፅአ እምከርሥየ
ዘወሀበኒ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል እምዘኢተሐዘብኩ።
4 አውሥእዎ መኳንንቲሁ ወይቤልዎ ትኩን ቡርከተ እም እንተ ወለደቶ
ለዝንቱ ወሬዛ። ወትኩን ቡርከተ ዕለት እንተ ተደመርከ ምስሌሃ
ለእመ ዝንቱ ወሬዛ እስመ ሠረቀ ላዕሌነ* እምሥርወ ዕሤይ ብእሲ
ብሩህ ዘይከውን ንጉሠ ለዘመደ ዘመድነ።
5 እምዘርዑ ዘኢየሐትቱ አቡሁ ወኢይብሉ እምአይቴ ምጽአቱ ዘበአማን
እስራኤላዊ እምዘርዐ ዳዊት በአምሳለ መልክአ ራእዩ ለአቡሁ ተልሕኰ
ፍጹመ ወንሕነኒ አግብርቲሁ ይኩነነ ንጉሠ ወአብኡ ሎቱ አምኃ
በበዕበዮሙ።
6 ወወሰደ ለአቡሁ ይእተ ሕልቀተ እንተ ወሀበቶ እሙ በባሕቲቶሙ።
ወይቤሎ ለአቡሁ ንሣእአ ዘንተ ሕልቀተ ወተዘከር ዘንተ ዘተናገርከ
ምስለ ንግሥት ወሀበነአ* እምዘፈረ ልብሳ ለታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር
ከመ ንስግድ ላቲ በኩሉ መዋዕሊነ ወኩሎሙ እለ እምታሕቴነ ወእለ
እምውስተ መንግሥተ ንግሥት።
7 አውሥአ ንጉሥ ወይቤሎ ለምንት ትሁበኒ ሕልቀተ ትእምርተ ረከብኩ
አምሳለ መልክእየ እስመ አንተ ወልድየ በአማን።
8 ወካዕበ ይቤሎ ነጋዲ ታምሪን ስማዕ አ ንጉሥ ዘለአከተኒ ዓመትከ*
ንግሥት እግዝእትየ ለዝንቱ ሕፃን ቅብዖ ወቀድሶ ወባርኮ ወአንግሦአ
ለብሔርነ ወአዝዝአ ከመ ኢትንግሥአ ብእሲት ለዓለመ ዓለም
ወፈንዎአ በሰላም። ወሰላም ለዕዘዘ መንግሥትከ ወለጥበብከ ብርህት።
ወአንሰአ ኢፈቀድኩ ከመ ይምጻእ ዝየ አላ አጽሐበኒ ፈድፋደ ከመ
ይምጻእ ኀቤከ ወአንሰ ፈራህኩ ሎቱ ከመ እመቦ ኢይድወይ በፍኖት
አው በጽምዐ ማይ አው በሐሩረ ፀሐይ ወኢያውርድ ርሥእንየ ውስተ
መቃብር በኀዘን። ወተማኅፀንኩ በጽዮን ቅድስት ሰማያዊት ታቦተ ሕጉ
ለእግዚአብሔር ከመ ኢትክልእ በጥበብከ። እስመ መኳንንቲከ ኢይክሉ
አቲወ ቤቶሙ ወነጽሮ ውሉዶሙ እምብዝኀ ጥበብ ወመባልዕት
ዘትውህቦሙ ለመፍቅዶሙ እንዘ ይብሉ ይኄይሰነ ማዕደ ሰሎሞን
እምንትፈሣሕ ወንደለው በውስተ አብያቲነ ወበእንተዝ አነ ፈሪህየ

* ለነ የሚልም አለ።
* ወሀበኒአ የሚልም አለ
* ይህ አገላለጽ የኢትዮጵያን ክብር ይነካል።



ሳመው። "እነሆ አሁን አባቴ ዳዊት በጉልምስናው ታደሰ። ከሙታንም
ተነሳ" አለው። ወደሚያነገግሩትም ዞሮ "አንተን ይመስላል ነው
የምትሉኝ? ይህ በጎልማሳነት ዘመን ያባቴ ርዝመት እንጂ የእኔ
ርዝመት አይደለም። ከእኔ ይልቅ ፈጽሞ ያምራልና" አለ።
2 ያኔም ተነስቶ ወደ ቤቱ ገባ። የወርቅ ግምጃንና የወርቅ ዝናርም
አለበሰው። በራሱ ላይም ዘውድ፣ በጣቱ ላይ ቀለበትና ለአይን
የሚያጥበረብር የክብር ልብስ አለበሰው። ከእሱም ጋር በሚታይ
ቦታ በዙፋን ላይ አስቀመጠው።
3 የእስራኤልን መኳንንትም "ልጅ እንደሌለኝ እርስ በእርሳችሁ
ታሙኛላችሁ። የእስራኤል አምላክ እግዚአብሄር የሰጠኝና ከአብራኬ
የወጣው ፍሬ ይህ ነው" አላቸው።
4 መኳንንቱም መልሰው "ይህንን ጎልማሳ የወለደች እናት የተባረከች
ትሁን። አንተም ከዚህ ጎልማሳ እናት ጋር የተገናኘህባት ቀን
የተባረከች ትሁን። ከእሴይ ስር ለልጅ ልጆችህ ንጉስ የሚሆን
ብሩህ ሰው በላያችን ላይ ወጥቷልና" አሉት።
5 "ፍፁም በአባቱ አርአያና አምሳል የተፈጠረ እስራኤላዊ የዳዊት
ዘር ነውና ወገኖቹ አባቱን አይመረምሩም። ከየት መጣም
አይሉም።ለእኛ ለባሪያዎቹም ንጉስ ይሁነን" እያሉ እንደየከፍታቸው
እጅ መንሻን አቀረቡለት።
6 እናቱም ብቻቸውን ሳሉ የሰጠችውን ያችን ቀለበት ወስዶ
"ከንግስት ጋር የተነጋገራችሁበትን ያንን ነገር ታስታውስ ዘንድ
እነሆ። እኛና ከእኛ በታች ያሉት የመንግስቱ ባለስልጣኖች
በዘመናችን ሁሉ እንሰግድላት ዘንድ ከእግዚአብሄር ታቦተ ህግ
ከልብሷ ጫፍ ስጠን" አለው።
7 ንጉሱም መልሶ "አንተ በእውነት ልጄ ነህና፣ የመልኬን አምሳያም
አግኝቻለሁና ስለምን የምልክት ቀለበት ትሰጠኛለህ?" አለው።
8 እንዲሁም ነጋደው ታምሪን "ንጉስ ሆይ! እመቤቴ ባሪያህ ንግስት
የላከችኝን ስማ። ይህንን ህፃን ቅባው። ቀድሰው፤ መርቀው፤
ለአገራችንም አንግሰው። ሴትም ለዘለአለም እንዳትነግስ እዘዝ። በሰ
ላምም ላከው። ለመንግስትህ ብርታትና ለበራችው ጥበብህ መልካም
ምኞቴን እገልፃለሁ። ወደ አንተ እንዲመጣ ግድ አለኝ እንጂ እኔ
እንኳን ወደ እሱ እንዲመጣ አልፈለግሁም ነበር። በጉዞ ላይ በውሃ
ጥም ወይም በፀሃይ ሃሩር እንዳይጎዳና እኔም በስተርጅናዬ በሃዘን
ወደ መቃብር እንዳልወርድ ፈራሁ። መመለስንም ደግሞ
እንዳትከለክለው በቅድስቲቷና ሰማያዊቷ በእግዚአብሄር ታቦተ ህግ
በፅዮን ተማፅኛለሁ። መኳንንቶችህ አንተ ለመፍቅዳቸው ከምትሰ
ጣቸው ብዙ ጥበብና ምግብ የተነሳ "በቤታችን ውስጥ ከምንደሰትና
ከምንዝናና የሰሎሞን ማእድ ይሻለናል" እያሉ ወደቤታቸው መመለስና
ልጆቻቸውን ማየት አይሹምና ይህንን ፈርቼ ነው። ያለ ደዌና

www.ethiopianorthodox.org

ተማኅፀንኩ ከመ ኢታቅሞ ኀቤከ አላ ከመ ትፈንዎ ኀቤየ በሰላም
ዘእንበለ ደዌ ወሕማም በፍቅር ወበሰላም ከመ ይትፈሣሕ ልብየ
በረኪቦቱ።

9 አውሥአ ንጉሥ ወይቤሎ ምንተ ባቲ ላዕለ ውሉድ ለብእሲት ዘእንበለ
ዘተሐምም ወተሐፅን። ወለት ለእም ወወልድ ለአብ። ወእግዚአብሔር
ረገማ ለሔዋን እንዘ ይብል ለዲ በጻዕር ወበኀዘነ ልብ በመሐላ ለዲ።
ወወሊደኪ ምግባእኪ ኀበ ምትኪ።[35] ወዘንተሰ ወልድየ ኢይሁብ
ለንግሥት አላ አነግሦ ላዕለ እስራኤል እስመ ዝንቱ በኩርየ ቀዳሜ
በኩርየ ዘወሀበኒ እግዚአብሔር።
10 ወእምዝ ይልእክ ሎቱ ሠርከ ወነግሀ ሠናያነ መባልዕተ ወአልባሰ
ክቡረ ወርቀ ወብሩረ ወይብሎ እስመ ይኄይስ ዝየ ንብረት ውስተ
ብሔርነ ኀበ ሀለወ ቤተ እግዚአብሔር ወኀበ ሀለወት ታቦተ ሕጉ
ለእግዚአብሔር ወኀበ የኀድር እግዚአብሔር ምስሌነ።

11 ወውእቱኒ ወልዱ ይልእክ ሎቱ እንዘ ይብል ወርቅሰ ወብሩር
ወአልባስ ኢተኀጥአ እምብሔርነ ወባሕቱ አነ መጻእኩ ከመ እስማዕ
ጥበበከ ወእርአይ ገጸከ ወአእምን ኪያከ ወእግነይ ለመንግሥትከ
ወእስግድ ለከ ወሊተኒ ትፈንወኒ ኀበ እምየ ወብሔርየ እስመ አልቦ
ዘይጸልእ ኀበ ተወልደ ወነገረ ብሔሩ ያፈቅር ኩሉ።
12 ወእንስአ ለእመኒ ወሀብከኒ ጥዑመ መባልዕተ ኢያፈቅር ወኢይኤድሞ
ለሥጋየ አላ ይኤድመኒ በዘተመሀርኩ ወልሀቁ መባልዕት ወእመኒ
አደመኒ ብሔር በአምሳለ ገነት ኢይኤድሞ ለልብየ ይኄይሰኒ አድባረ
ምድራ ለእምየ ኀበ ተወለድኩ።
13 ወታቦተ አምላከ እስራኤልሂ ለእመ ገነይኩ ላቲ በኀበ ሀለውኩ
ታከብረኒ ወቤተ እግዚአብሔር ዘሐነጽከ አነጽር ላቲ ወእሠውዕ
ወእትጋነይ በኀበ ሀለውኩ። ወለጽዮንሂ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር
ሀበኒ ዘፈረ ልብሳ ወእሰግድ ላቲ ምስለ እምየ ወኩሉ ዘእምታሕተ
መንግሥትነ።
14 እስመ ቀዲሙኒ እግዝእትየ ንግሥት ሠረወቶሙ ለኩሎሙ እለ
ያመልኩ ጣዖታተ ወእለ ይሰግዱ ለባዕድ ወለአእባን ወለአዕዋም
ወሠረወቶሙ ወአግብአቶሙ ኀበ ጽዮን ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር
እስመ ሰምዐት በኀቤከ ወተምህረት ወገብረት በከመ ነገርከ
ወአምለክናሁ ለእግዚአብሔር።
15 ወበዝ ኩሉ ስእነ እሆ አብህሎቶ ለወልዱ።

[35] ዘፍ.3፥16



ህማም በሰላምና በፍቅር ወደ እኔ እንድትመልሰው እንጂ
እንዳታስቀረው አደራ የምለው። እሱን በማግኘቴ ልቤን ደስ
ይለው ዘንድ ትላለች" አለው።
9 ንጉሱም መልሶ "ለማሰብና ለመጨነቅ ካልሆነ ሴት ከወንድ ልጅ
ምን አላት? ሴት ልጅ ለእናት ወንድ ልጅም ለአባት ነውና።
እግዚአብሄርም 'በፃእርና በልብ ሃዘን ውለጂ። ወልደሽም ፈቃድሽ
ወደ ባልሽ ይሁን[35] ሲል ረገማት። ስለዚህ ይህንን ልጄን
እግዚአብሄር የሰጠኝ የበኩር ልጄና ሃይሌ ነውና በእስራኤል ላይ
አነግሰዋለሁ እንጂ ለንግስት አልሰጣትም" አለው።
10 ከዚህ በህዋላ ጠዋትና ማታ ያማሩ ምግቦችንና የከበሩ ልብሶችን፣
ወርቅና ብርን ይልክለት ነበር። እንዲሁም "የእግዚአብሄር ቤት፣
የእግዘአብሄር ታቦተ ህግና እግዚአብሄር ከእኛ ጋር በሚያድርበት
እዚሁ ከእኛ ጋር መኖር ይሻላል" አለው።
11 ልጁም "እኔ ጥበብህን ልሰማ፣ ፊትህን ላይ፣ ሰላምታ ላቀርብልህ፣
ለመንግስትህ ልገዛና እጅ ልነሳ መጣሁ እንጂ ወርቅ ብርና
ልብስስ በእኛም ዘንድ አልጠፋም። የተወለደበትን የሚጠላ የለምና፣
ሁሉም የአገሩን ወግ ይወዳልና ወደ እናቴ እና ወደ አገሬ
መልሰኝ" እያለ ይልክበት ነበር።
12 "እኔ የለመድኳቸውና ያደግሁባቸው ምግቦች ያምሩኛል። አንተ
ምንም የጣመ ምግብ ብትሰጠኝ አይሻኝም። ለስጋየ አያምረውም።
በገነት አምሳል ያለ አገር ቢሆን እንኳ ልቤን ደስ አያሰኘውም።
የተወለድኩበት የእናቴ አገር ተራሮች ይሻሉኛልና።
13 የእስራኤል አምላክ ታቦትም ብትሆን ባለሁበት ሆኜ ከተገዛሁላት
ታከብረኛለች። ወደ ሰራህው የእግዚአብሄር ቤትም ባለሁበት ፊቴን
መልሼ እሳለማለሁ። ይልቁንስ ከእናቴና ከመንግስታችን በታች
ካሉት ሁሉ ጋር እሰግድላት ዘንድ ከእግዘአብሄር ታቦተ ህግ
ከልብሷ ጫፍ ስጠኝ።
14 ከዚህም በፊት እመቤቴ ንግስት ጣኦትን የሚያመልኩትንና ባእዳን
ለሆኑት ለድንጋዮችና ለእንጨቶች የሚሰግዱትን አጥፍታ የእግዚአብሄር
ታቦት ወደ ሆነችው ወደ ፅዮን መልሳቸዋለች። በአንተ ዘንድ
ሰምታ ተምራለችና እንደ ነገርካት አደረገች። እኛም እግዘአብሄርን
አመለክነው። " አለው።
15 በዚህም ሁሉ ንጉሱ ሰሎሞን ልጁን እሽ ማሰኘት አልቻለም።

[35] ዘፍ.3፥16

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

## ፴ወ፮ ኀበ ተስእሎ ሰሎሞን ለወልዱ፣

1 ወካዕበ ነገሮ እንተ ባሕቲቱ ሰሎሞን ወይቤሎ ለወልዱ ለምንት
ትፈቅድ ከመ ትርኀቅ እምኔየ። ምንተ ኀጣእከ ከመ ትሑር ብሔረ
አረሚ ወምንት አጽሐቀከ ከመ ትኅድግ መንግሥተ እስራኤል።
2 አውሥአ ወልዱ ወይቤሎ ኢይከውነኒ እንበር ዝየ አላ እሑር ኀበ
እምየ እንዘ አንተ ትድኅረኒ እስመ ብከ ወልድ ዘይኄይስ እምኔየ
ኢዮርብአም ዘተወልደ በሕግ እምብእሲትከ ወእምየሰ ኢኮነት
እንቲአከ ብእሲተ ዘበሕግ።
3 አውሥአ ንጉሥ ወይቤሎ ወለእመ ትቤ ከመዝ አነሂ ኢኮንኩ
ዘበሕግ ወልደ ለአቡየ ዳዊት እስመ ነሥአ ብእሲተ ባዕድ
ወአቅተሎ ኪያሁኒ በውስተ ጸብእ።[36] ወወለደ ኪያየ እምኔሃ።[37] እስመ
እግዚአብሔር መሐሪ ሰረየ ሎቱ።[38] ወመኑ ዘየአኪ ወየአብድ እምነ
እጓለ እመሕያው ወመኑ ዘይምሕር ወይጠበብ ከመ እግዚአብሔር፤
ሊተኒአ እምአቡየ ወለከኒ እምኔየ ገብረ እግዚአብሔር በከመ ፈቀደ።
4 ወአንተሰ ኦ ወልድየ ፍርሆ ለእግዚአብሔር አምላክነ ኢትግፋዕ ገጸ
አቡከ ከመ ኢትርከብከ በደኀሪ ግፍዕ እምነ ዘይወፅእ እምነ ሐቋከ
ወከመ ይሠኒ ዘርዕከ በዲበ ምድር።
5 ወውእቱሰ ኢዮርብዓም ሕፃን ዘ፮ ዓመት። ወአንተ ቀዳሚ በኩርየ
ወበጻሕከ ለነጊሥ ወለአንስኦ ኩናቱ ለዘወለደከ።
6 ወአንሰ ነዋ ፳ወ፱ ዓመት እምዘነገሥኩ ወበሳብዕ ዓመተ መንግሥትየ
መጽአት እምከ ኀቤየ።
7 ወለእመ ፈቀደ እግዚአብሔር ያብጽሐኒ ኀበ አምጣነ መዋዕለ አቡየ
ወእምከመ ተወሰኩ ኀበ አቡየ ወአበውየ ወትነብር አንተ ዲበ
መንበርየ ወትነግሥ አንተ ህየንቴየ ወሊቃውንተ እስራኤልኒ ፈድፋደ
ያፈቅሩከ ወእገብር ለከ ከብካበ ወእሁበከ ንግሥታተ ወዕቁባተ
መጠነ ፈቀድከ ወትትባረክ በዛቲ ምድረ ርስት ቡርክት እንተ ወሀበ
እግዚአብሔር ለአበዊነ በከመ ተካየደ ምስለ ኖኅ ገብሩ ወምስለ
አብርሃም ፍቁሩ ወጻድቃን ደቂቆሙ እምድኅሬሆሙ እስከ ዳዊት
አቡየ።
8 ወትሬእየኒ አነ ድኩም ዲበ መንበሮሙ ለአበውየ ወትከውን ከማየ
እምድኅሬየ ወትኴንን አሕዛበ ዘአልቦ ኆልቍ ወአንጋደ ዘአልቦ
መስፈርት።

[36] 2ሳሙ.11፥2-16
[37] 2ሳሙ.12፥24
[38] 2ሳሙ.12፥14



## ፴፮ ሰሎሞን ልጁን እንደ ጠየቀው

1 ሰሎሞን ልጁን "ከእኔ ለመራቅ የምትፈልገው ለምን ነው? ወደ
ኣረመኔ ኣገር ትሄድስ ዘንድ ምን ኣጣህ? የእስራኤልንስ መንግስት
ትተው ዘንድ ያስጨነቀህ ምንድን ነው?" ሲል ለብቻው ጠየቀው።
2 ልጁም መልሶ "ሳታዘገየኝ ወደ እናቴ እሄድ ዘንድ እንጂ እዚህ
እቀመጥ ዘንድ ኣይቻለኝም። ለኣንተ ከህግ ሚስትህ የተወለደ ከእኔ
የሚሻል ልጅ ኢዮርባም ኣለህ። የእኔ እናት ግን የኣንተ የህግ
ሚስትህ ኣይደለችም" ኣለው።
3 ንጉሱም መልሶ "እንዲህ ካልክስ እኔም ደግሞ ለኣባቴ ለዳዊት
ከህግ ሚስቱ የተወለድኩ ኣይደለሁም። የሌላ ሰው ሚስት ወስዶ
እሱን በጦርነት ኣስገድሎታል።[36] እኔንም ከእሷ ወለደ።[37] መሃሪ
እግዚኣብሄር ሃጢያቱን ይቅር ብሎታልና።[38] ከሰው ልጅ የበለጠ
ክፉና ሰነፍ ማነው? እንደ እግዚኣብሄርስ ይቅር ባይና ጠቢብ
ማነው? እኔንም ከኣባቴ ኣንተንም ደግሞ ከእኔ እግዚኣብሄር እንደ
ወደደ ኣደረገ።
4 ልጄ ሆይ ኣንተስ እግዚኣብሄር ኣምላካችንን ፍራው። በሁዋለኛው
ዘመን ከወገብህ በሚወጣው ግፍ እንዳያገኝህ የኣባትህን ፊት
ኣትግፋ። በምድር ላይ የምታየው ሁሉ እንዲያምር።"
5 ይህ ኢዮርብኣም ግን የስድስት ኣመት ህፃን ነው። ኣንተ ግን
መጀመሪያዬ ማለትም የበኩር ልጄ ነህ። ለመንገስና የኣባትህንም
ጦር ለማንሳት ደርሰሃል።
6 እነሆ እኔ ከነገስኩ ሃያ ዘጠኝ ኣመቴ ነው። በሰባተኛው ዘመነ
መንግስቴ እናትህ ከእኔ ዘንድ መጣች።
7 እግዚኣብሄር ከወደደ እስከ ኣባቴ እድሜ ድረስ ያድርሰኝ። ወደ
ኣባቴና ወደ ኣባቶቼ ከተወሰድኩ ኣንተ በዙፋኔ ላይ ትቀመጣለህ።
በእኔ ፋንታም ትነግሳለህ። የእስራኤል ሊቃውንት ፈፅሞ
ይወዱሃል። ሰርግም ኣድርጌ የፈለግሀውን ያህል ንግስታትንና
እቁባትን እሰጥሃለሁ። እግዚኣብሄር ከባሪያው ከኖህ፣ ከወዳጁ
ከኣብርሃምና ከእነሱ በሁዋላ ከነበሩ ፃድቃን ልጆቻቸው ጋር እስከ
ኣባቴ ዳዊት ድረስ ቃል ኪዳን በሰጠው መሰረት ለኣባቶቻችን
በሰጣት በዚህች ቡርክት ምድር ትባረካለህ።
8 እኔን ደካማውን በኣባቶቼ ዙፋን ታየኛለህ። ከእኔም በሁዋላ ኣንተ
እንደ እኔ ትሆናለህ። ብዙ ህዝቦችንና ስፍር ቁጥር የሌላቸውን
ነገዶችንም ትገዛለህ።

[36] 2ሳሙ.11፥2-16 የኦርዮ ሚስት ቤርሳቤህ
[37] 2ሳሙ.12፥24
[38] 2ሳሙ.12፥14

www.ethiopianorthodox.org

9 ወታቦተ አምላከ እስራኤልኒ ለከ ወለዘርዕከ ውእቱ ኀበ ትገብር
ምሥዋዐ ወተዐርግ ጸሎተ ወእግዚአብሔር የኀድር ውስቴታ ለዝሉፉ
ወይሰምዐከ ጸሎተከ በውስቴታ ወትገብር ሥምረቶ ለእግዚአብሔር
በውስቴታ ወዝክርከኒ ለትውልደ ትውልድ በማእከላ።
10 ወአውሥአ ወልዱ ወይቤሎ ኦ እግዚእየ ኢይከውነኒ እኅድግ
ብሔርየ ወእምየ እስመ አምሕሎ አምሐለተኒ እምየ በአጥባቲሃ ከመ
ኢይቁም ዝየ አላ እግባእ ኀቤሃ ፍጡነ። ወበዝየኒ ኢያውሰብ ብእሰ
ተ ወታቦተ አምላከ እስራኤልሂ ትባርከኒ በኀበ ሀለውኩ ወጸሎትከኒ
ትትልወኒ በኀበ ሖርኩ እስመ ፈተውኩ እርእይ ገጸከ ወእስማዕ
ቃለከ ወእንሣእ በረከተከ ወእሑር ኀበ እምየ በዳኅን።

፴ወ፰ ኀበ መከረ ንጉሥ ይፌኑ ወልዶ ምስለ ደቂቆሙ

1 ወእምዝ ገብአ ውስተ ቤቱ ሰሎሞን ንጉሥ ወአስተጋብእሙ
ለመማክርቲሁ ወለመገብቱ ወለመላህቅተ ቤተ መንግሥቱ
ወይቤሎሙ ስእንኩ አሆ አብህሎቶ ለዝንቱ ወልድ ወይእዜኒ
ስምዑኒ ዘእነግረክሙ ሀቡ ናንግሦ ለብሔረ ኢትዮጵያ ምስለ
ደቂቅክሙ እለ ትነብሩ በየማንየ ወበፀጋምየ ከማሁ ይንበሩ ደቅቅክሙ
መላህቅት በየማኑ ወበፀጋሙ ወኩልክሙ መማክርት ወመኳንንት ሀቡ
ነህብ ደቂቀክሙ በኩረ ወይከውን ለነ ክልኤ መንግሥት።
2 ወአንሰ ምስሌክሙ በዝየ እትለአክ ወደቂቅነሂ ይነግሡ በህየ።
ወሣልስኒ እሴፈዎ ለእግዚአብሔር ከመ የሀበኒ ዘርዐ ወይከውን
ሊተ ሣልሰ ንጉሠ።
3 እስመ የኀሥሥ ብልጣሶር ንጉሠ ሮሜ ከመ አህቦ ወልድየ ለወለቱ
ወያንግሦ ሊተ ምስለ ወለቱ ላዕለ ኩሉ ሀገረ ሮሜ እስመ አልቦ
ውሉደ ዘርአ ዘእንበሌሃ ወመሐለ ከመ ኢያንግሥ ዘእንበለ እምዘርዐ
ዳዊት አቡየ።
4 ወለእመ እንገሥነ ሀየኒ ንከውን ሠለስተ ነገሥተ ወኢዮርብአምኒ
ይነግሥ ዝየ ለእስራኤል እስመ ከመዝ ትንቢቱ ለዳዊት አቡየ
ይከውን ዘርዑ ለሰሎሞን ሠለስተ አርእስተ መንግሥት በዲበ
ምድር።
5 ወንፌኑ ሎሙ ካህናተ ወንሥራዕ ሎሙ ሕግጋተ ወያምልኩ
ወይግነዩ ለአምላከ እስራኤል ውስተ አርእስተ መንግሥት። ወይሰ
ባሕ እግዚአብሔር በዘመደ ሕዝቡ እስራኤል። ወይትሌዐል በኩሉ
ምድር።
6 በከመ ጸሐፈ አቡየ ውስተ መጽሐፉ እንዘ ይብል፣ በልዎሙ
ለአሕዛብ ከመ እግዚአብሔር ነግሠ። ወካዕበ ይቤ፣
ወንግርዎሙ ለአሕዛብ ምግባሮ፣
ሰብሕዎ ወዘምሩ ሎቱ።[39] ወካዕበ ይቤ
ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ስብሐተ ሐዲሰ።

[39] መዝ.105፥1-2

- 33 -

9 የእስራኤልም አምላክ ታቦትም መስዋእትን ልታደርግባት፣ ፀሎትን
ልታሳርግባት፣ እግዚአብሄር ሊያድርባት፣ ለፀሎትህም ማሳረጊያና
እግዚአብሄርም ከአንተ ጋር ሊሆን ለአንተና ለዘርህ ለዘላለሙ ተሰ
ጥታለች" አለው።
10 ልጁም መልሶ "ጌታዬ ሆይ እናቴንና አገሬን እተው ዘንድ
አይቻለኝም። እናቴ በቶሎ ወደ እሷ እንድመለስ እንጂ እዚህ
እንዳልቀር በጡቶቿ አምላኛለችና እዚህ አገር ሴት አላገባም።
የእስራኤል አምላክ ታቦትም ባለሁበት ትባርከኝ። ፊትህን ላይ
ቃልህን ልሰማና በረከትህንም ልቀበል ወደ እናቴም በደህና እሄድ
ዘንድ ሽቻለሁና ፀሎትህ በሄድኩበት ትከተለኝ" አለው።

፴፰ ንጉሱ ልጁን ከልጆቻቸው ጋር ለመላክ እንደ ዋከረ

1 ከዚህ በሁዋላ ንጉስ ሰሎሞን ወደ ቤቱ ገብቶ አማካሪዎቹን
ሹማምንቱንና የቤተ መንግስቱን ታላላቆች ሁሉ ሰብስቦ እንዲህ
አላቸው።" ይህን ልጅ እሺ ማሰኘት አልቻልኩም። እነሆ አሁን
የምነግራችሁን ስሙኝ። በቀኜና በግራ የምትቀመጡ ሆይ
ከልጆቻችሁ ጋር ለኢትዮጵያ እንድናነግሰው ፍቀዱ። ልጆቻችሁም
እንዲሁ አለቃ ሆነው በቀኝና በግራው ይቀመጡ። እናንተ ሁላችሁ
አማካሪዎችና መኳንንቶች በኩር ልጃችሁን እንሰጠው ዘንድ
ፍቀዱለት መንግስት ይሆንልናል።
2 እኔ ከእናንተ ጋር በዚሁ እነግሳለሁ። ልጆቻችንም በዚያ ይነግሳሉ።
ሶስተኛም ዘርም እግዚአብሄር እንዲሰጠኝ ተስፋ አደርጋለሁ።
ሶስተኛም ንጉስ ይሆንልኛል።
3 የሮም ንጉስ ብልጣሶር ወንድ ልጁን ለሴት ልጁ እሰጠው ዘንድና
ከሴቱ ልጅ ጋር በሮም ሁሉ ላይ ያነግሰው ዘንድ ይፈልጋል።
ሌላ ወንድ ልጅ የለውምና ከአባቴ ከዳዊት ዘር በቀር ላያነግስ
ምሏል።
4 እዚያም ስናነግስ ሶስት ነገስታት እንሆናለን። ኢዮርብኣም እዚሁ
እስራኤል ውስጥ ይነግሳል። ለአባቴ ለዳዊት የተነገረው ትንቢት
የሰሎሞን ዘር በምድር ላይ ሶስት መንግስታት ይሆናል ተብሎ
ነውና።
5 ካህናትን እንልክላቸዋለን። ህግጋትንም ደግሞ እንሰራላቸዋለን።
የየመንግስታቱ ርእሶችም የእስራኤልን አምላክ ያመልካሉ።
ለእግዚአብሄርም ይገዛሉ ። እግዚአብሄርም በእስራኤል ህዝብ ወገን
ይመሰገናል።
6 አባቴም በመፅሃፉ እግዚአብሄር እንደ ነገሰ ለአህዛብ ንገሯቸው።
ደግሞም ለአህዛብ ስራውን አውሩ። ተቀኙለት። ዘምሩለት።[39]

[39] መዝ.105፥1-2

www.ethiopianorthodox.org

ስብሐቲሁ በማኅበረ ጻድቃኑ።
ይትፌሣሕ እስራኤል በፈጣሪሁ።[40] ለነ ይእቲ ክብረ መንግሥት።
7 ወንሴብሖ ለፈጣሪነ ወይርአዩ ኪያነ አሕዛብ እለ ያመልኩ ጣዖተ
ወይፈርሁነ ወያነግሡነ ወይሴብሕዎ ለእግዚአብሔር ወይፈርህዎ።
8 ወይእዜኒ ሀቡ ናንግሥ ወንፈንዎ ምስለ ደቂቅክሙ እለብክሙ
ምርካበ ወሢመተ በከመ ሢመትክሙ። ወምርካብክሙ በዝየ ይኩን
ከማሁ ለደቂቅክሙ በህየ። ወይርአዩ ሕገ መንግሥት ወንረስዮሙ
በከመ ሕግነ። ወነአዝዞሙ ሕገ ወትእዛዛተ ወንፈንዎሙ ይንግሡ
በህየ።
9 ወአውሥኡ ወይቤሉ ካህናት ወመኳንንት ወመማክርት ለንጉሥ
አንተ ትፌንዎ ለበኩርከ። ወንሕነ ንፌኑ ደቂቀነ እለ ብነ በከመ
ፈቀድከ። መኑ የዐቢ ትእዛዞ ለእግዚአብሔር ወለንጉሥ። እስመ
አግብርቲከ እሙንቱ ለከ ወለዘርዕከ በከመ ነበብከ። ለእመ ፈቀድከ
እምሄጥኮሙ ከመ ይኩኑ አግብርተ ምስለ እማቲሆሙ። ወአልቦ
ዘንትዐደው እምትእዛዝከ ወእምትእዛዘ እግዚአብሔር አምላክከ።
10 ወእምዝ አስተዳዉ ከመ ይግበሩ ሎሙ ዘበሕግ ወይፈንዎሙ ውስተ
ብሔረ ኢትዮጵያ ወይንግሡ በህየ ወይንበሩ እስከ ለዓለም
እሙንቱ። ወዘርዖሙ ለትውልደ ትውልድ።

### ፴ወ፱ ኀበ አንገሥዎ ለወልደ ሰሎሞን

1 ወአስተዳለዉ ዕፍረተ ወቅብዐ መንግሥት። ወተነፍሐ ቃለ ቀርን
ወብዕንዛ ወእንዚራ ወመሰንቆ ወከበሮ። ወጸርሐት ሀገር በውውዓ
በትፍሥሕት ወበይባቤ።
2 ወአብእዎ ውስተ ቅድስተ ቅዱሳን። ወተእኀዘ በአቅርንተ ምሥዋዕ።
ወተውህቦ መንግሥት በአፈ ሳዶቅ ካህን ወበአፈ ኢዮአስ ካህን
መልአከ ኃይሉ ለንጉሥ ሰሎሞን። ወቀበዖ እምነ ቅዱስ ቅብዐ
ዕፍረት ለመንግሥት።
3 ወወጽአ እምነ ቤተ እግዚአብሔር። ወሰመይዎ ስሞ ዳዊት እስመ
በሕግ ረከበ ስመ ንጉሥ።
4 ወአፅዐንዎ ዲበ በቅለ ንጉሥ ሰሎሞን። ወአየድዎ ሀገረ እንዘ ይብሉ
ሜምናከ እምዝየ። ወእምዝ ይቤልዎ ባሕ ሕየው አበ ነጋሢ። ወቦ
እለ ይብሉ ርቱዕ ይደልዎ እምፈለገ ግብፅ እስከ ምዕራብ ፀሐይ
ይኩን ሢመትከ ኢትዮጵያ። ቡሩክ ዘርዕከ በዲበ ምድር እምሴዋ
ደቡባዊ እስከ ሠርቀ ሕንድ ዘታሠምሮን።

[0] መዝ.149፡1-2



እንደገናም ለእግዚኣብሄር ኣዲሱን ቅኔ ተቀኙለት። ምስጋና
በቅዱሳኑ ጉባኤ ነው። እስራኤል በፈጣሪው ደስ ይበለው[40] ኣለ።
7 የመንግስት ክብር ለእኛ ነው። ኣምላካችንን እናመሰግነዋለን። ይህም
ጣኦትን የሚያመልኩ ኣህዛብ እኛን ኣይተው ይፈሩንና ያነግሱን
ዘንድ ነው። እግዚኣብሄርን ያመሰግኑታል። ይፈሩታልም። "
8 "እነሆ ኣሁንም እናንተ ደመወዝና ሹመት ያላችሁ ከልጆቻችሁ ጋር
እናነግሰውና እንልከው ዘንድ ፍቀዱ። የልጆቻችሁም ሹመትና
ደመወዝ እናንተ እዚህ እንዳላችሁ ሹመትና ደመወዝ ይሁን። ህገ
መንግስቱንም ይጠብቁ ዘንድ እንደ ህጋችን እናደርግላቸዋለን።
ህግንና ትእዛዝን እናዝላቸዋለን።በዚያም ይነግሱ ዘንድ እንልካቸዋለን።"
9 ካህናቱ፣ መኳንንቱና መማክርቱም "ኣንተ የበኩር ልጅህን ትልካለህ።
እኛም ደግሞ ያለንን እንደ ፈቃድህ እንልካለን" ሲሉ ለንጉሱ
መለሱ። "የእግዚኣብሄርንና የንጉሱን ትእዛዝ እንቢ የሚል ማነው?
ኣንተ እንዳልከው እነሱ የኣንተ እና የዘርህ ባሪያዎች ናቸውና
ብትፈልግ ከእናቶቻቸው ጋር ባሪያዎች ሊሆኑ ልትሰጣቸው
ትችላለህ። ከትእዛዝህና ከኣምላክህ ከእግዚኣብሄር ትእዛዝ የሚወጣ
የለም" ሲሉ መለሱ።
10 በህጉ መሰረት ሊያደርጉላቸው፣ ወደ ኢትዮጵያ ሊልኳቸውና
እነሱና ዘሮቻቸው ለዘላለሙና ለትውልደ ትውልድ በዚያ
ሊነግሱና ሊኖሩ ይዘጋጁ ጀመር።

### ፴፱ የሰሎሞንን ልጅ እንዳነገሱት

1 ቅብኣ መንግስቱንና የሚጣፍጥ ሽቶዎችን ኣዘጋጁ። ነጋሪት፣
እምቢልታ፣ እንዚራ፣ መሰንቆና ከበሮም ተመታ። ኣገሪቱም
በውካታ፣ በደስታና በልልታ ድምፅ ተመላች።
2 ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑም ውስጥ ኣስገቡት። በመሰዊያው ቀንዶችም
ተይዞ በካህኑ በሳዶቅና የንጉስ ሰሎሞን የሃይል ኣዛዥና ካህን
በሆነው በኢዮኣስ ኣፍ መንግስት ተሰጠው። ለንግስና ከሆነው
ከቅዱሱ ጣፋጭ ሽቱ ቀባው።
3 ከእግዚኣብሄር ቤትም ወጣ። ስሙንም ዳዊት ብለው ሰየሙት።
የንግስ ስም በህግ ኣግኝቷልና።
4 በንጉሱ በሰሎሞን በቅሎም ኣስቀመጡት። ከኣሁን ጀምሮ ሾምንህ
እያሉ ኣገሩን ኣዞሩት። "ከዚህም በሁዋላ ንጉስ ሆይ! ሺህ ኣመት
ያንግስህ" ኣሉት። "ከግብጽ ምንጭ እስከ ፀሃይ መግቢያ ድረስ
ሹመትህ በኢትዮጵያ ይሁን። ዘርህ በምድር ላይ የተባረከ ይሁን።
ከሸዋ ደቡባዊ እስከ ምስራቅ ህንድ ድረስ የምትገዛ ሁን" የሚሉም
ነበሩ።

[40] መዝ.149፡1-2

www.ethiopianorthodox.org

5 ወእግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ይኩንከ መርሐ። ወታቦተ ሕጉ
ለእግዚአብሔር ኀበ ኵሉ ዘአንጸርከ። ወይኩኑከ ግሩራነ ኵሎሙ ፀርከ
ወጸላእትከ በቅድሜከ። ወይኩንከ ፍጽመ ወከዋላ ለከ ወለዘርዕከ
እምድኅሬከ። ወትኳነን ብዙኃነ አሕዛበ። ወለከሰ አልቦ ዘይኳንነከ።
6 ወካዕበ ባረኮ አቡሁ ወይቤሎ በረከተ ሰማይ ወምድር ይኩን
በረከትከ። ወይቤሉ ማኅበረ እስራኤል አሜን።
7 ወካዕበ አቡሁኒ ይቤሎ ለሳዶቅ ካህን አይድዖኬ ወንግሮ ፍትሐ
ወኵነኔሁ ለእግዚአብሔር ከመ ይዕቀብ በህየ።

## ፺ ኀበ አዘዞ ሳዶቅ ካህን ለዳዊት ንጉሥ[41]

1 ወአውሥአ ሳዶቅ ካህን ወይቤሎ ስማዕ ዘእነግረከ ወለእመ ገበርከ
ተሐዩ ለእግዚአብሔር። ወለእመሰ ኢገበርከ ይቀሥፈከ
እግዚአብሔር።
2 ወትከውን ሕጹጸ እምነ ኵሉ አሕዛብ። ወትትመዋእ በፀርከ።
ወይመይጥ ገጸ አምኔከ። ወትከውን ድንጉፀ ወኀዙነ ወሕሙመ
በልብከ። ወንዋምከኒ ዘእንበለ ኀድኣት ወጥዒና።
3 ወስማዕ ቃለ እግዚአብሔር ወግበር። ወኢትትገሐሥ ኢለየማን
ወኢለፀጋም እምዘ ንኤዝዘከ ዮም። ወኢታምልክ አማልክተ ባዕድ።
4 ወለእመ ኢሰማዕከ ቃለ እግዚአብሔር ስማዕ ዘይረከበከ ዝንቱ ኵሉ
መርገም።
5 ርጉመ ትከውን በሐቅል።
6 ርጉመ ትከውን በሀገር።
7 ርጉመ ይከውን ፍሬ ምድርከ፤
8 ርጉመ ይከውን ፍሬ ከርሥከ።
9 ወይፌኑ ላዕሌከ እግዚአብሔር ረኀበ ወብድብደ።
10 ርጉመ ይከውን ፍሬ ከርሥከ ወአዕጻደ ላህምከ ወመርዕየ አባግዒከ።
ወይጠፍእ ኵሉ ዘወደይከ እደከ እስከ ያጠፍአከ እስመ ኢሰማዕከ
ቃሎ ወይከውነከ ሰማይ በመልዕልተ ርእስከ ብርተ ወምድር
በታሕቴከ ኀፂነ።
11 ወይሬስዮ እግዚአብሔር ለዝናመ ምድርከ ቆባረ። ወመሬት ይወርድ
እምሰማይ ላዕሌከ እስከ ይደፍነከ ወእስከ ያጠፍአከ ወትትቀተል
በቅድመ ፀርከ።
12 በአሐቲ ፍናው ትወፅእ ኀቤሆሙ። ወበሳብዕ ፍናው ትነትዕ
እምቅድመ ገጾሙ። ወትከውን ዝርወ። ወአብድንቲከኒ መብልዐ
ለአዕዋፈ ሰማይ። ወአልቦ ዘይቀብረከ።
13 ወይቀሥፈከ በዐበቅ በደዌ ሲሕ ወበፈፀንት ወበመቅሠፍተ ግብጽ
ወበዐዊር ወበድንጋፄ ልብ።
14 ወታረመስስ መዐልተ ከመ ዕውር በውስተ ጽልመት። ወኢትረክብ
ዘይረድአከ በግፍዕ።

[41] ዘዳግ.27 ይመልከቱ።

- 35 -

5 "የእስራኤል አምላክ እግዚአብሄር መሪ ይሁንህ። የእግዚአብሄር
ታቦተ ህግም ፊትህን ወደ አዞርክበት ሁሉ ትከተልህ። ጠላቶችህ
በፊትና በሁዋላ ለአንተና ከአንተም በሁዋላ ለዘርህ በፊትህ
ወድቀው ይስገዱልህ። አንተን ግን የሚገዛህ አይኑር።"
6 ደግሞም አባቱ "በረከትህ የሰማይና የምድር በርከት ይሁን" ሲል
መረቀው። ማህበረ እስራኤልም "አሜን" አሉ።
7 ደግሞም አባቱ ካህኑን ሳዶቅን "በዚያ ይጠብቀው ዘንድ
የእግዘአብሄርን ፍርድና ግዛት አፅንተህ ንገረው" አለው።

## ፺ ካህኑ ሳዶቅ ንጉስ ዳዊትን* እንዳዘዘው[41]

1 ካህኑ ሳዶቅም መልሶ "የምነግርህን ስማ። ብታደርገው
ለእግዚአብሄር በህይወት ትኖራለህ።
2 ካላደረግከው እግዚአብሄር ይቀስፍሃል" አለው። "ከአህዛብም ሁሉ
የጎደልክ ትሆናለህ። በጠላትህ ድል ትነሳለህ። ፊቱን ከአንተ
ይመልሳል። ደንጋጣ፣ አዘንተኛና በልብህም ታማሚ ትሆናለህ።
መኝታህም ያለ ፀጥታና ጤና ይሆናል።
3 የእግዚአብሄርን ቃል ስማ፤ አድርገውም። ዛሬ ከምናዝዝህም ወደ
ቀኝም ወደ ግራም አትበል። ባእድ አማልክትን አታምልክ።
4 የእግዚአብሄርን ቃል ካልሰማህ ግን የሚያገኝህን ርግማን ሁሉ ስማ።
5 በዱር የተረገምክ ትሆናለህ።
6 በቤት የተረገምክ ትሆናለህ።
7 የምድርህ ፍሬ የተረገመ ይሆናል።
8 የሆድህ ፍሬ የከብትህና የበግህ መንጋ የተረገመ ይሆናል።
9 እግዚአብሔር ረሃብና በሽታ ይልክብሃል።
10 እስኪያጠፋህ ድረስ እጅህን ያሳረፍክበት ሁሉ ይጠፋል። ቃሉን
አልሰማህምና ሰማይ በራስህ ላይ መደብ በበታችህ ብረት
ይሆንብሃል።
11 እግዚአብሄርም የምድርህን ዝናም ጭጋግ ያደርግብሃል። ከሰማይም
እስኪደፍንህ፣ በጠላትህ ፊት እስኪገድልህና እስኪያጠፋህ ድረስ ናዳ
ይወርድብሃል።
12 በአንድ መንገድ ወደ እነሱ ትወጣለህ። በሰባት መንገድም ከእነሱ
ትሸሻለህ። የተበታትንክ ትሆናለህ። ስጋህንም የሰማይ ወፎች
ይቀራመቱታል። የሚቀብርህም የለም።
13 በእከክና ሺ በሚሆን ልዩ ልዩ ደዌና የወባ በሽታ በግብፅ መቅሰ
ፍቶች በእውርነት በልብ ድንጋጤም ይቀስፍሃል።
14 እውር በጨለማ እንደሚያደርገው በቀን እንደ እውር ትዳብሳለህ።
በግፍ ጊዜ የሚረዳህ የለም።

* ምኒልክን ለማለት።

[41] ዘዳግ.27 ይመልከቱ።

www.ethiopianorthodox.org

15 ወታወስብ ብእሲተ ወየሐይደከ ካልእ ብእሲ።
16 ወትነድቅ ቤተ ወኢትነብር ውስቴቱ።
17 ወትተክል ወይነ ወኢትቀስም እስካሉ።
18 ወይጠብሑ ላህመከ ስቡሐ በቅድሜከ። ወኢትበልዕ እምኔሁ።
19 ወየሀይዱ አድገከ ወኢያገብኡ ለከ። ወይገብኡ አባግዒከ ለአግብርት
ወለፀርከ ወኢትረክብ ዘይረድአከ።
20 ወይገብኡ ደቂቅከ ወአዋልዲከ ለካልእ ሕዝብ። ትሬኢ በአዕይንቲከ
እንዘ ይኩርዕዎሙ ወአልቦ ዘትክል ገቢረ።
21 ወይበልዑ ፀር እለ ኢተአምር እክለ ምድርከ ወፃማከ። ወኢትክል
ከሊአ።
22 ወትከውን ዕውረ ወድንጉፀ። ሶበ ጸብሐ ትብል እፎ ይመሲ።
ወሶበ መስየ እፎ ይጸብሕ እምብዝኀተ ፍርሀት ለእመ ኢሰማዕከ
ቃለ እግዚአብሔር።
23 ወለእመ ሰሚዐ ሰማዕከ ቃለ እግዚአብሔር ስማዕ ዘይረክበከ ሠናይ
እምኀበ እግዚአብሔር። ወትኤነን አህጉረ ፀር። ወትወርስ ክብረ
ዘለዓለም እምኀበ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ዘኩሎ ይመልክ።
እስመ ያከብሮ ለዘአከበሮ ወያፈቅሮ ለዘአፍቀሮ። እስመ መልአኬ
ሕይወት ውእቱ ይኤዝዝ ወይመልክ ኩሎ ዓለመ በጥበቡ
ወበከሂሎቱ ወበመዝራዕቱ።

### ፵ወ፩ በእንተ በረከተ ነገሥት[42]

1 ወስማዕሂ ዘይረክበከ ቡራኬ።
2 ለእመ ገበርከ ፈቃደ ለእግዚአብሔር ቡሩክ ትከውን በኩሉ ፍናዊከ።
3 ቡሩክ ትከውን በሀገር።
4 ቡሩክ ትከውን በሐቅል።
5 ቡሩክ ትከውን በቤትከ።
6 ቡሩክ ትከውን በአፍአከ።
7 ቡሩክ ይከውን ፍሬ ከርሥከ። ይቤሉ ጉቡኣን አሜን።
8 ቡሩክ ይከውን ፍሬ ምድርከ አሜን።
9 ቡሩክ ይከውን አንቅዕተ ማያቲከ። አሜን።
10 ቡሩክ ይከውን ፍሬ አትክልቲከ። አሜን።
11 ቡሩክ ይከውን ዐፀደ ላህምከ ወመራዕየ አባግዒከ። አሜን።
12 ቡሩክ ይከውን መዛግብቲከ ወትሩፋቲከ። አሜን።
13 ቡሩክ ትከውን በበአትከ። አሜን።
14 ቡሩክ ትከውን በፀአትከ። አሜን።
15 ወያገብኦሙ እግዚአብሔር ለፀርከ ለእለ ይትቃወሙከ። ይትቀጠቀጡ
በታሕተ እገሪከ። አሜን።

[42] ዘዳግ.28 ይመልከቱ።



15 ምሽት ታገባለህ። ሌላ ወንድም ይቀማሃል።
16 ቤትን ትሰራለህ። በውስጡ ግን አትኖርም።
17 ወይን ትተክላለህ። ፍሬውን ግን አትለቅምም።
18 የሰባውን በሬህን በፊትህ ያርዱታል። ከእሱም አትበላም።
19 አህያህንም ይቀማሉ። አይመልሱልህምም። በጎችህም ለባሮችና
ለጠላቶችህ ይሆናሉ። የሚረዳህም አታገኝም።
20 ወንዶችና ሴቶች ልጆችህ ለሌላ ህዝብ ይሆናሉ። ሲደበድቧቸው
በአይኖችህ ታያለህ። የምታደርገው የለም።
21 የማታውቀው ጠላት የምድርህንና የድካምህን አዝመራ ይበላል።
መከልከልም አትችልም።
22 የተጨነቀና የደነገጠ ትሆናለህ። በየጠዋቱ እንዴት ይመሻል?
ሲመሽም ከፍርሃት ብዛት የተነሳ እንዴት ይጠባል? ትላለህ
ይሄውም የእግዚአብሄርን ቃል ያልሰማህ እንደሆነ ነው።
23 የእግዚአብሄርን ቃል ከሰማህ ደግሞ ከእግዚአብሄር ዘንድ
የሚያገኝህን መልካም ነገር ስማ። የጠላትክን አገሮች ትገዛለህ።
ሁሉን ከሚገዛ ከእስራኤል አምላክ ከእግዚአብሄር ዘንድም የዘላለም
ክብርን ትወርሳለህ። እሱ ያከበረውን ያከብራል። የወደደውንም
ይወዳልና። የህይወት መልአክም ነውና። በጥበቡ በችሎታውና
በክንዱ አለሙን ሁሉ ያዝዛል፤ ይገዛልም። "

### ፵፩ ስለ ነገስታት በረከት[42]

1 "የሚያገኝህን በረከት ስማ።
2 የእግዚአብሄርን ፈቃድ ብታደርግ በመንገድህ ሁሉ የተባረክህ ትሆናለህ።
3 በአገርህ የተባረክህ ትሆናለህ።
4 በዱር የተባረክ ትሆናለህ።
5 በቤትህ የተባረክህ ትሆናለህ።
6 በውጭም የተባረክህ ትሆናለህ።
7 የሆድህ ፍሬ የተባረከ ይሆናል። " የተሰበሰቡት "አሜን" ይላሉ።
8 "የምድርህ ፍሬ የተባረከ ይሆናል"። "አሜን። "
9 "የወንዝህ ምንጮች የተባረኩ ይሆናሉ።" "አሜን። "
10 "የተክሎችህ ፍሬ የተባረከ ይሆናል። " "አሜን። "
11 "የከብትህ በረትና የበጎችህ መንጋ የተባረከ ይሆናል። " "አሜን። "
12 "ያከማቸህውና ያተረፍከው የተባረከ ይሆናል። " "አሜን። "
13 "ስትገባ የተባረክህ ትሆናለህ። ""አሜን። "
14 "ስትወጣ የተባረክህ ትሆናለህ። " "አሜን። "
15 "እግዚአብሄር የሚቃወሙህን ጠላቶችህን ከእግርህ በታች እንዲቀጠቀጡ
ያደርጋቸዋል። " "አሜን። "

[42] ዘዳግ.28 ይመልከቱ።

www.ethiopianorthodox.org

16 ወይፌኑ እግዚአብሔር ውስተ አብያቲከ በረከቶ ወውስተ ኩሉ
ዘወደይከ እዴከ። አሜን።
17 ወያበዝኀከ እግዚአብሔር ውስተ ሠናይት በውሉደ ከርሥከ ወበእክለ
ምድርከ ወበተዋልዶ እንስሳከ። አሜን።
18 ወበምድር እንተ መሐለ ለአበዊከ ይሁበከ ከመ መዋዕለ ሰማይ።
አሜን። ወይፈትሕ ለከ እግዚአብሔር መዝገበከ በረከተ ሰማያት
ወይሁበከ ዝናመ ቡሩከ ወይባርክ ለከ ፍሬ ተግባርከ። አሜን።
19 ወትሌቅሕ አንተ ለብዙኃን አሕዛብ ወአንተሰ ኢትትሌቃሕ። አሜን።
20 ወትኴንን አንተ ለብዙኃን አሕዛብ ወለከሰ ኢይኴንኑከ። አሜን።
21 ወይሠይመከ እግዚአብሔር ውስተ ርእስ ወአኮ ውስተ ዘነብ።
ወትከውን መልዕልተ ወአኮ መትሕተ። አሜን።
22 ወታስተጋብእ እምነ ኩሉ በረከተ ምድር ለእንስሳከ ወትነሥእ በርበረ
አሕዛብ ለትዕይንትከ። ወይሰግዱ ለከ ውስተ ገጸ ምድር
ለመንግሥትከ በእንተ ዕበየ ክብርከ። ወይትሌዐል ክብርከ ከመ ዐርዝ
ወከመ ኮከበ ጽባሕ ብርሃነ ክብርከ በቅድመ ኩሉ አሕዛበ ምድር
ወበቅድመ ኩሉ ነገደ ሕዝብከ እስራኤል እስመ እግዚአብሔርኒ
ይሄሉ ምስሌከ በኩሉ ፍናትከ ወይገብር ፈቃደከ በኩሉ ዘኀለይከ።
23 ወትወርስ አህጉረ ፀርከ ወይትዌደስ ዕበየ ሕዝብከ በብዝኀ ግርማከ
ወበብዝኀ ሠራዊትከ። ወይፈርሁከ ኩሉ እለ ኢይገብሩ ፈቃዶ
ለእግዚአብሔር። እስመ አንተ ትገብር ፈቃዶ ወትትለአክ ሎቱ።
ወበእንተ ይሁብከ ግርማ ዐቢየ በቅድመ እለ ይሬእዩከ በአልጕሞ
አፍራሲከ ወበምጕንጳ ቀስትከ ወበአንጸብርቆ ወልታከ ይርዕድ
ልቦሙ። ወይሰግዱ ለከ ውስተ ገጸ ምድር እስመ ይደነግፅ ልቦሙ
በርእየ ግርማከ። ወሶበ ይሬእዩከ እምርጕቅ እለ ውስተ አድባር
ይወርዱ ምድረ ወእለ ውስተ አብሕርት ወቈላት ይወጽኡ አፍአ
ከመ ያግብእሙ እግዚአብሔር ውስተ እዴከ በእንተ ዘዐለዉ ትእዛዘ
እግዚአብሔር።
24 ወአንተሰ ሶበ ትገብር ፈቃዶ ኩሎ ዘሰአለከ ትነሥእ በኀቤሁ እስመ
ለእመ አፍቀርከ ያፈቅረከ ወለእመ ዐቀብከ ትእዛዞ ይሁበከ ስእለተ
ልብከ ወኩሎ ዘኀሠሥከ ትነሥእ በኀቤሁ። እስመ ኄር ለኄራን
ወየዋህ ለየዋሀን ውእቱ ወይገብር ፈቃዶሙ ለእለ ይፈርህዎ
ወይሁቦሙ ዐስበ ለእለ ይትዔገሥዎ። ተዐገሣ ለመዐት ወድኅረ
ታስፌሥሐከ። አፍቅራ ለጽድቅ ወትፈሪ ለከ ሕይወተ። ኩን ኄረ
ለኄራን ወመገሥጸ ለመአብሳን።
25 ወአኅድጎ እኪተ ለእኩይ በገሥፆ ወበአርትዖ ወበአርስሖ ወበአኅሥሮ
ለዘይዔምፅ ቢጸ በእኩይ በውስተ ዐውደ ቅስት።
26 ወፍታሕ ለነዳይ ወለእጓለ ማውታ ወአንግፎ እምእደ ዘይትዔገሉ።
27 ወኢትፍታሕ በአድልዎ ወበነቢአ ገጽ አላ በጽድቅ ፍታሕ
ወኢታፍቅር ሕልያነ በነቢአ ፍትሕ በአድልዎ ለገጽ።
28 ወለመኳንንቲከኒ ገሥጾሙ ከመ ይኩኑ ንጹሐነ እምሕልያን
ወኢያድልው ፍትሐ ለገጸ ፍቁራኒሆሙ ወኢለጸላኢሆሙ
ወኢለአብዕልቲሆሙ ወኢለነዳያኒሆሙ አላ በጽድቅ ኩነኔ ይኰንኑ
ቢጾሙ በርቱዕ ፍትሕ።



16 "እግዚኣብሄር እጅህን በጨመርክበትና በቤትህ ውስጥ በረከቱን ይልካል።
" ኣሜን። "
17 "እግዚኣብሄር በሆድህ ፍሬዎች በምድር እህል በከብቶቹ መራባት
በመልካም ያበዛልሃል። " "ኣሜን። "
18 "ለኣባቶች በማለው ምድር የሰማይን ዘመን ያህል ይሰጥሃል። " "ኣሜን።
" "እግዚኣብሄር የሰማይን በርከት መዝገብ ይከፍትና የተባረከ ዝናብ
ይሰጥሃል። " "ኣሜን። "
19 "ለብዙ ህዝቦች ታበድራለህ።ኣንተ ግን ኣትበደርም። " "ኣሜን። "
20 "ኣንተ በብዙ ህዝቦች ላይ ትፈርዳለህ። " "በኣንተ ግን ኣይፈርዱብህም። "
"ኣሜን። "
21 "እግዚኣብሄር ራስ ኣድርጎ ይሾምሃል እንጂ ጅራት ኣያደርግህም። "
"በላይ እንጂ በታች ኣትሆንም። " "ኣሜን። "
22 "ከሁሉ የምድር በረከትን ለእንስሶች ትሰበስባለህ። ለከተማው ከኣህዛብ
ወገን የሆኑ ኣረመኔዎችን ትወስዳለህ። ስለ ክብርህ ከፍታ በምድር ላይ
ያሉ ሁሉ ይሰግዱልሃል። ክብርህ እንደ ዝግባ ከፍ ከፍ ይላል።
የክብርህ ብርሃንም በምድር ላይ በሚኖሩ ህዝቦችና ወገንህ በሆነው
በእስራኤል ህዝብ ዘንድ እንደ ንጋት ኮከብ ያበራልሃል። እግዚኣብሄር
በመንገድህ ሁሉ ካንተ ጋር ይሆናል። ባሰብከውም ሁሉ ፈቃድህን
ያደርግልሃል።
23 የጠላትህን ኣገር ትወርሳለህ። በግርማህ ብዛትና በሰራዊትህ የህዝብ ከፍታ
ይመሰገናል። የእግዚኣብሄርን ፈቃድ የማያደርጉ ሁሉ ይፈሩሃል። ኣንተ
ፈቃዱን ታደርጋለህና። ትላከዋለህምና። ስለዚህ በፈረስህ ኣሰላለፍና
በቀስትህ ሰገባ ነፀብራቅ ልባቸው ይንቀጠቀጣል። ከምድር ላይ ይሰ
ግዱልሃል። ግርማህን በማየት ልባቸው ይደነግጣል። በተራራ ላይ ያሉም
ሲያዩህ ወደ ምድር ይወርዳሉ በባህሮችና በቆላዎች ያሉትም
የእግዚኣብሄርን ትእዛዝ ስላፈረሱ እግዚኣብሄር በእጅህ ይጥላቸው ዘንድ
ወደ ውጭ ይወጣሉ።
24 ኣንተ ግን ፈቃዱን በምታደርግ ጊዜ ከእሱ የለመንከውን ሁሉ
ትቀበላለህ። ከወደድክ ይወድሃል። ትእዛዙንም ከጠበቅህ የልብህን ልመና
ሁሉ ይሰጥሃል። የፈለግከውን ሁሉ ከእሱ ትቀበላለህ። ለቸሮች ቸር
ለቅኖችም ቅን ነውና። ለሚፈሩት ፈቃዳቸውን ያደርጋልና። ለሚታገሰ
-ትም ዋጋቸውን ይሰጣቸዋልና። መኣትን ታገሳት። በሁዋላም
ታስደስትሃለች። እውነትንም ውደዳት። ህይወትንም ታፈራልሃለች። ለቸሮች
ቸር ለበዳዮችም ገሳጭ ነው።
25 በሰፊ ኣደባባይ ወንድሙን በክፉ የሚበድልን በመቆጣት፣ በማስተካከል
በማስነወርና በማጎሳቆል ክፉውን ከክፋት ኣስወግደው።
26 ለደሃና ለሙት ልጅ ፍረድ። ከሚበድለውም እጅ ኣድነው።
27 በእውነት ፍረድ እንጂ በኣድልዎና ፊትን በማየት ኣትፍረድ። ለሰው
ፊት ስትል በፍርድ ፈንታ ማማለጃን ኣትውደድ።
28 መኳንንቶችህ ከማማለጃ ንፁህ ይሆኑ፣ ወንድሞቻቸውን በቅን ፍርድና
በእውነተኛ ኣገዛዝ ይገዟቸው ዘንድ እንጂ ዘንድ ለወዳጆቻቸውም፣
ለጠላቶቻቸውም፣ ለባለፀጎቻቸውም፣ ለደሃዎቻቸውም ፊት ቢሆን ፍርድን
እንዳያደሉ ገስፃቸው። "

www.ethiopianorthodox.org

## ፵ወ፪ በእንተ ዐሠርቱ ቃላት[43]

1 ወስምዑ እስራኤል ዘተአዘዘ እም እግዚአብሔር ከመ ትዕቀቡ ኪያሁ።
2 ወይቤ አነ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክከ ዘአውፃእኩከ እምነ ምድረ
ግብጽ ወእምነ ቤተ ቅኔ።
3 ወኢይኩንከ ባዕደ አምላከ ዘእንበሌየ።
4 ወኢትግበር አምላከ ዘግልፎ ወኢበኵሉ አምሳል ዘውስተ ሰማይ
ዘላዕሉ ወኢበኵሉ ዘበምድር በታሕቱ ወኢዘውስተ ማይ ዘመትሕተ
ምድር።
5 ወኢትስግድ ሎሙ ወኢታምልኮሙ።
6 እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክከ አምላክ ቀናኢ ዘእትፈደይ
ኀጢአተ ወላዲ ላዕለ ውሉድ ፲ስከ ሣልስ ወራብዕ ትውልድ ለእለ
ይጸልኡኒ ወእገብር ምሕረተ ፲ስከ እልፍ ትውልድ ለእለ ያፈቅሩኒ
ወየዐቅቡ ትእዛዝየ።
7 ወኢትምሐል በስመ እግዚአብሔር አምላክከ በሐሰት። እስመ ኢያነጽሕ
እግዚአብሔር ለዘይምህል በስመ ዚኣሁ በሐሰት። ወዕቀብ ዕለተ ሰ
ንበት ከመ ትቀድሳ በከመ አዘዘ እግዚአብሔር አምላክከ።
8 ሰዱስ መዋዕለ ግበር ግብረከ ወበሳብዕት ዕለት ሰንበቱ
ለእግዚአብሔር አምላክከ። ኢትግበር ባቲ ግብረ ቅኔ። ኢአንተ
ወኢወልድከ ወኢወለትከ ወኢገብርከ ወኢአድግከ ወኢኵሉ እንስሳከ
ወኢፈላሲ ዘይነብር ኀቤከ።
9 እስመ በሰዱስ መዋዕል ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ ወባሕረ
ወኵሎ ዘውስቴታ ወአዕረፈ አመ ዕለተ ሳብእት ወበይነዝ ባረካ
እግዚአብሔር። ለሳብዕት ዕለት ወአጽደቃ።
10 አክብር አባከ ወእመከ ከመ ይኩንከ ጽድቀ ብዙኀ ዕለተ ትረክብ
በውስተ ምድር ዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ።
11 ኢትሑር ብእሲተ ብእሲ።
12 ኢትቅትል ነፍሰ።
13 ኢትዘሙ።
14 ኢትስርቅ።
15 ስምዐ በሐሰት ኢትስማዕ ላዕለ ቢጽከ።
16 ወኢትፍቱ ብእሲተ ካልእከ ኢቤቶ ወኢገራህቶ ወኢገብሮ ወኢአመቶ
ወኢላህሞ ወኢብዕራዮ ወኢአድጎ ወኢእምኵሉ እንስሳሁ ዘአጥረየ
አጥርዮ ካልእከ።
17 ዝ ነገር ዘነገረ እግዚአብሔር ሕጎ ወሥርዓቶ።
18 ወለእለኒ ይኤብሱ ገሥጸሙ ከመ ኢይጽንዑ ውስተ ስሒት
ወይትዐገሡ እምርኩሰ ዘኢሠምረ እግዚአብሔር። ወዝንቱ ውእቱ ነገር
ዘኢሠምረ እግዚአብሔር።

[43]ዘፀ.20 ይመልከቱ።



## ፵፪ ስለ አስሩ ቃላት[43]

1 "እስራኤል ሆይ! ትጠብቁት ዘንድ ከእግዚኣብሄር የታዘዘውን
ስሙ።
2 ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣሁህ እግዚኣብሄር ኣምላክህ እኔ
ነኝ።
3 ከእኔ በቀር ሌላ ኣምላክ ኣይሁንልህ።
4 በላይ በሰማይ፣ በታችም በምድር ካለው ከምድርም በታች በውሃ
ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ የተቀረፀውንም ምስል ለኣንተ
ኣታድርግ።
5 ኣትስገድላቸው። ኣታምልካቸውም።
6 በሚጠሉኝ እስከ ሶስተኛና አራተኛ ትውልድ የኣባቶችን ሃጢያት
በልጆች ላይ የማመጣ፣ ለሚወዱኝ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ
ኣስር ሺ ትውልድ* ድረስ ምህረትን የማደርግ እኔ እግዘኣብሄር
ነኝ።
7 በኣምላክህ በእግዚኣብሔር ስም በሃሰት አትማል። እግዚኣብሄር
በስሙ በሃሰት የሚምለውን ኣያነፃውምና እግዚኣብሄር ኣምላክህ
እንዳዘዘው የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ ጠብቅ። ስድስት ቀን
ስራህን ትሰራለህ። ሰባተኛው ቀን ግን ለኣምላክህ ለእግዚኣብሄር ሰ
ንበት ነው።
8 ኣንተ ወንድ ልጅህ፣ ሴት ልጅህ፣ ሎሌህም ኣህያህም ከብትህም
ሁሉ በኣንተም ዘንድ ያለ እንግዳ በእርሷ ምንም ስራ ኣይስሩባት።
9 እግዚኣብሄር በስድስት ቀን ሰማይና ምድርን ባህርንም ያለባቸውን
ሁሉ ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን ኣርፏልና፤ ስለዚህ እግዚኣብሄር የሰ
ንበትን ቀን ባርኮታል። ቀድሶታልም።
10 ኣባትህንና እናትህን ኣክብር። እግዚኣብሄር ኣምላክህ በሚሰጥህ
ምድር እድሜህ እንዲረዝም።
11 ወደ ወንድ ምሽት ኣትግባ።
12 ኣትግደል።
13 ኣታመንዝር።
14 ኣትስረቅ።
15 በባልንጀራህ ላይ በሃሰት ኣትመስክር።
16 የባልንጀራህን ሚስት ኣትመኝ። ቤቱንም፣ እርሻውንም፣ ሎሌውንም፣
ገረዱንም፣ በሬውንም፣ ኣህያውንም፣ ከባልንጀራህ ገንዘብ ማናቸውንም
ኣትመኝ።
17 ይህ ነገር እግዚኣብሄር ህጉንና ስርኣቱን የተናገረበት ነው።
18 የሚበድሉትም በስህተታቸው እንዳይፀኑና እግዚኣብሄር ካልወደደው
ርኩሰትም እንዲታገሱ ገስፃቸው። ይህ እግዚኣብሄር ያልወደደው
ነገር ነውና።

[43]ዘፀ.20፥1-8

*አንዳንድ የውጭ ትርጉሞች ለሚወዱኝ ብዙ ሺ ምህረቶችን የማደርግ ሲሉ ተገኝተዋል።

www.ethiopianorthodox.org

19 ወርቱዕ ይትገሐሡ እምኔሁ ብእሲ ብእሲ ኀበ ይከውኖ ዘመዱ
ኢይባእ ይክሥት ኀፍረቶ እስመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር
አምላክክሙ።
20 ኀፍረተ አቡከ ወእምከ ኢትክሥት እስመ እምከ ይእቲ።
21 ኢትክሥት ኀፍረተ ብእሲተ አቡከ እስመ ኀፍረተ እምከ ይእቲ።
22 ኀፍረተ እኅትከ እንተ እምነ አቡከ አው እንተ እምነ እምከ
ኢትክሥት እመኒ እንተ እምነ አፍአ ተወልደት ሎቱ ወእመኒ እንተ
እምአዝማዲከ ይእቲ ኢትክሥት ኀፍረታ።
23 ኀፍረተ ወለተ ወልድከ ኢትክሥት አው ኀፍረተ ወለተ ወለትከ
ኢትክሥት እስመ ኀፍረትከ ይእቲ።
24 ኀፍረተ ወለተ ብእሲተ አቡከ ኢትክሥት እስመ እኅትከ ወለተ
እምከ ይእቲ። ወኢትክሥት ኀፍረታ።
25 ኀፍረተ እኅተ አቡከ ኢትክሥት እስመ ቤተ አቡከ ይእቲ።
26 ኀፍረተ እኅተ እምከ ኢትክሥት እስመ ቤተ እምከ ይእቲ።
27 ኀፍረተ ብእሲተ እኅሁ ለአቡከ ኢትክሥት። እስመ ዘመድከ ይእቲ።
28 ኀፍረተ ብእሲተ ወልድከ ኢትክሥት። እስመ ብእሲተ ወልድከ
ይእቲ።
29 ኀፍረተ ወለትከ ወብእሲተ ወልደ እኁከ ኢትክሥት። እስመ
ኀፍረትከ ውእቱ።
30 ኀፍረተ ብእሲተ እኁከ ኢትክሥት እስመ ኀፍረተ እኁከ ይእቲ።
31 አምጣነ ሀሎ ሕያው እኁከ ኀፍረተ ብእሲቱ ምስለ ወለታ
ኢትክሥት። ወኢዘወለተ ወልዳ ወኢዘወለተ ወለታ ኢትግበር ከመ
ትክሥት ኀፍረቶን ቤትከ ውእቱ ወኃጢአት ውእቱ።
32 ወብእሲተ ምስለ እኅታ ኢታውስብ ከመ ታስተቃንዮን ወከመ
ትክሥት ኀፍረቶን ለዛቲኒ ወዘእንታክቲኒ እንዘ ዓዲሃ ቀዳሚት
ሕያውት ይእቲ።
33 ወኀበ ብእሲት ትክት ኢትባእ እንበለ ትንጻሕ ከመ ትክሥት
ኀፍረታ እንዘ ዓዲ ርኩስት ይእቲ።
34 ወኢትባእ ኀበ ብእሲተ ካልእከ ከመ ትስክብ ምስሌሃ። ወኢትዝራዕ
ዘርእከ ውስቴታ። ወኢታስተፃምድ ኀበ መልአከ ውሉድከ ከመ
ኢታርኩስ ስሞ ለቅዱስ ስመ እግዚአብሔር።
35 ወምስለ ተባዕት ኢትስክብ ከመ ምስለ አንስት እስመ ርኩስ ውእቱ።
36 ወኢትሑር ኀበ እንስሳ ከመ ታውፅእ ዘርዐከ ላዕሌሁ ከመ ኢትርኩስ
ቦቱ።
37 ወብእሲትኒ ኢትሑር ኀበ እንስሳ ከመ ይስከባ እስመ ርኩስ ውእቱ።
38 ኢታርኩሱ ርእሰክሙ በኩሉ ዝንቱ። እስመ ቦቱ ረኩሱ አሕዛብ እለ
አነ አውፃእክዎሙ እምቅድሜክሙ።
39 ወበዝንቱ ኢታርኩሱ ሥጋክሙ ወቀድሱ ነፍሰክሙ ወሥጋክሙ
ለእግዚአብሔር። እስመ ቅዱስ ውእቱ ወያፈቅሮሙ ለእለ ይቄድሱ
ነፍሶሙ ወሥጋሆሙ ሎቱ። እስመ ቅዱስ ወግሩም ወልዑል ውእቱ።
ወመሓሪ ወመስተሣህል ውእቱ። ወሎቱ ይደሉ ስብሐት ለዓለመ
ዓለም አሜን።

- 39 -

19 ቀጥሎ ካለው ሊታገሱ ይገባል። ከእናንተ ማንም ሰው ሃፍረተ
ስጋውን ይገልጥ ዘንድ ወደ ዘመዱ ሁሉ አይቅረብ። እኔ
እግዚአብሄር አምላካችሁ ነኝ።
20 የአባትህን ሃፍረተ ስጋና የእናትህን ሃፍረተ ስጋ አትግለጥ።
እናትህ ናት።
21 የአባትህን ሚስት ሃፍረተ ስጋ አትግለጥ። የአባትህ ሃፍረተ ስጋ
ነውና።
22 የእህትህን፣ የአባትህን፣ ወይም የእናትህን ልጅ፣ በቤት ወይም
በውጭ የተወለደች ብትሆን ሃፍረተ ስጋዋን አትግለጥ።
23 የወንድ ልጅህን ሴት ልጅ ሃፈረተ ስጋዋን ወይም የሴት ልጅህን
ሴት ልጅ ሃፍረተ ስጋ አትግለጥ። የአንተ ሃፍረተ ስጋ ነውና።
24 የአባትህን ሚስት ልጅ ሃፍረተ ስጋ አትግለጥ። የእናትህ ልጅ
እህትህ ናትና። ሃፍረተ ስጋዋን አትግለጥ።
25 የአባትህን እህት ሃፍረተ ስጋ አትግለጥ። የአባትህ ዘመድ ናትና።
26 የእናትህን እህት ሃፍረተ ስጋ አትግለጥ። የእናትህ ዘመድ ናትና።
27 የአባትህን ወንድም ሚስት ሃፍረተ ስጋ አትግለጥ። ዘመድህ ናትና።
28 የምራትህን ሃፍረተ ስጋ አትግለጥ። የልጅህ ሚስት ናትና።
29 የሴት ልጅህንና የወንድ ልጅህን ልጅ ሚስት ሃፍረተ ስጋ
አትግለጥ። የአንተ ሃፍረተ ስጋ ነውና።
30 የወንድምህን ሚስት ሃፍረተ ስጋ አትግለጥ። የውንድምህ ሃፍረተ
ስጋ ነውና።
31 ወንድምህ በህይወት ሳለ የሚስቱንና የሴት ልጁን ሃፍረተ ስጋ፣
የወንድ ልጁንም የሴት ልጁንም ሴት ልጅ ሃፍረተ ስጋቸውን
አትግለጥ። ዘመዶችህ ናቸውና። ሃጢአት ነው።
32 ሚስትህ በህይወት ሳለች እህቷ ጣውንቷ እንዳትሆን ሃፍረተ
ስጋዋን ትገልጥ ዘንድ ከእርስዋ ጋር እህትዋን አታግባ።
33 እርስዋም በመርገሟ ርኩሰት ሳለች ሃፍረተ ስጋዋን ትገልጥ ዘንድ
ወደ ሴት አትቅረብ።
34 እንዳትረክስባት ከባልንጀራህ ሚስት ጋር አትተኛ። የተቀደሰውን
የእግዚአብሄር ስም እንዳታረክስና ከልጅህ ጠባቂ መልአክ ጋር
እንዳታጣምድህ ዘርህን በውስጧ አትዝራ።
35 ከሴትም ጋር እንደምትተኛ ከወንድ ጋር አትተኛ። ርኩስ ነገር
ነውና።
36 እንዳትረክስባት ወደ እንስሳ አትቅረብ። ዘርህንም ታስወጣ ዘንድ
ከእርሷ ጋር አትተኛ።
37 ሴትም ከእርሱ ጋር ትተኛ ዘንድ ወደ እንስሳ አትቅረብ።ርኩስ ነውና።
38 ከፊታችሁ የማሳድዳቸው አህዛብ በእነዚህ ሁሉ ረክሰዋልና በእነዚህ
ነገሮች አትርከሱ።
39 በዚህ ሁሉ ሰውነታችሁን አታርክሱ። ስጋችሁንና ነፍሳችሁን
ለእግዚአብሄር ቀድሱ። በእውነት እርሱ ቅዱስ፣ የሚያስፈራ፣ ከፍ
ያለ፣ መሃሪና ይቅር ባይ ነው። ለእሱ እስከ ዘላለሙ ምስጋና
ይገባል። "

www.ethiopianorthodox.org

## ፵ወ፫ ኀበ ተአዘዙ ደቂቀ ኀይለ እስራኤል

1 ሀገርሰ ተፈሥሐት በእንተ ዘአንገሠ ወልደ ንጉሥ ወረሰዮ ንጉሠ
እምደወሉ እስከ ደወለ ባዕድ። ወዓዲ ኀዘነት ሀገር እስመ አዘዘ
ንጉሥ ከመ የሀቡ ደቂቆሙ እለ ተሰምዩ በኵረ።
2 ወእለኒ እምየማን ከማሁ ይንበሩ በከመ አበዊሆሙ ይነብሩ ምስለ
ንጉሥ ሰሎሞን ከማሁ ይንበሩ በየማነ ወልዱ ዳዊት ንጉሠ
ኢትዮጵያ። ወእለኒ እምፀጋም ከማሁይነብሩ በከመ አበዊሆሙ
ይነብሩምስለ ንጉሥ ሰሎሞን በፀጋሙለወልዱ ዳዊት ንጉሠ
ወሢመቶሙኒ በከመ አበዊሆሙ ወአስማቲሆሙኒ በከመ ኢትዮጵያ። አበዊሆሙ።
3 ወኵሉ በበሥርዓቱ ወበከመ ዕበዩ ወበከመ ምልክናሁ ወበከመ
ምርካቡ ወበከመ ምኩናኑ ከማሁ ይኩኑ።
4 ከማሁ ይኩኑ በከመ ገብረ ሰሎሞን ለመኳንንቲሁ ከማሁ ይግበር
ሎሙ ዳዊትሂ ለመኳንንቲሁ።
5 ወበከመ ሠርዖሙ ሰሎሞን ለመገብቱ ወከማሁ ዳዊትሂ ይሥራዕ
ሥርዓተ ቤቱ።
6 ወከመዝ አስማቲሆሙ ለእለ ተሠይሙ ይትፈነዉ።
7 አዛርያስ ወልደ ሳዶቅ ካህን ዘ ውእቱ ሊቀ ካህናት።
8 ወኤልያስ ወልደ አርኒ ሊቀ ዲያቆናት። ወአቡሁሰ ለአርኒ ሊቀ
ዲያቆናት።
9 ናታን ነቢይ።
10 ወአድራም ወልደ አርድሮንስ መልአከ አሕዛብ።
11 ወፈንቄራ ወልደ ሰባ ጸሓፌ ላህም።
12 ወአኮንሔል ወልደ ጦፌል እንዘ ሕፃን።
13 ወሳምንያስ ወልደ አኪታሌም መዘክር።
14 ወፊቃሮስ ወልደ ንያ መልአከ ሠርዌ ዘ ውእቱ ሊቀ ሐራ።
15 ወሌዋንዶስ ወልደ አኪሬ መልአከ አንገቦት።
16 ወፋቂጤን ወልደ አድራይ መልአካዊ ለባሕር።
17 ወማታን ወልደ ብንያስ መልሀቀ ቤት።
18 ወአዳርዝ ወልደ ኬሬም ደቀ ሰርጉ።
19 ወደስከም ወልደ ማትሬም ሊቀ ሐራ ለአፍራስ።
20 ወአደርዮስ ወልደ ኔድሮስ ሊቀ ሐራ ለአጋር።
21 ወአውስጥራን ወልደ ዮዳድ ጸዋሬ ክብር።
22 ወአስተርአዮን ወልደ አሳ ቃለ ታዕካ።
23 ወኢሚ ወልደ መታትያስ ሊቀ መጻብእት ወማካሪ ወልደ አቢሳ
ፈታሔ ታዕካ።
24 ወአቢስ ወልደ ካርዮስ
25 ወአስሪ ሊቀ ውንድዮስ ወልደ ኔልትዮስ መስፍነ ዐውድ።
26 ወካርሚ ወልደ ሐፃንያስ ሊቀ ገባር ዘቤተ ንጉሥ።
27 ወሰራንያስ ወልደ አካዝኤል መጋቢ ዘቤተ ንጉሥ።



## ፵፫ የእስራኤል ሃይል ልጆች እንደታዘዙ

1 ሀገሪቱም ንጉሱ ልጁን ስላነገሰና እስከ ባእድ አውራጃ ድረስ
ንጉስ ስላደረገው ተደሰተች። ደግሞም ንጉሱ በኩር የሆኑ
ልጆቻቸውን እንዲሰጡ ስላዘዘ አገሪቱ አዘነች።
2 በቀኝ የሚቀመጡት ልጆች አባቶቻቸው በንጉሱ በሰሎሞን ቀኝ
እንደሚቀመጡ እንዲሁ ይቀመጡ። በግራ ያሉትም አባቶቻቸው
በንጉሱ በሰሎሞን ግራ እንደሚቀመጡ እንደዚሁ በኢትዮጵያ ንጉስ
በልጁ በዳዊት ግራ ይቀመጡ። ሹመታቸውም እንደ አባቶቻቸው
ሹመቶች ስሞቻቸውም እንደ አባቶቻቸው ስሞች ይሁኑ።
3 ሁሉም እንደ ስራቱ፣ እንደ ከፍታው፣ እንደ ግዛቱ፣ እንደ ሃብቱና
እንደ ዳኝነቱ እንደዚሁ ይሁን።
4 ሰሎሞን ለመኳንንቶቹ እንዳደረገው ዳዊትም ለመኳንንቶቹ እንደዚሁ
ያድርግ።
5 ሰሎሞን ሹማምንቱን በስርዓት እንዳደረጋቸው፣ ዳዊትም ሹማምንቱን
እንዲሁ በስርአት ያድርጋቸው።
6 ይላኩ ዘንድ የተሾሙት ስም ይህ ነበር።
7 የካህኑ የሳዶቅ ልጅ አዛርያስ ሊቀ ካህናት፣
8 የአርኒ ልጅ ኤልያስም የዲያቆናት አለቃ፣
9 ናታንም ነቢይ፣
10 የደሮንሳም ልጅ አድራም የአህዛብ አለቃ፣
11 የሶባ ልጅ ፊንቂራ ርሀሰ ላህም፣
12 የጦፌል ልጅ አኮንሄል ብላቴን ጌታ፣
13 የአኬታለም ልጅ ሳሞንያስ አቃቤ ሰአት፣
14 የንያ ልጅ ፊቃሮስም የጦር አበጋዝና ፊታውራሪ፣
15 የአኩሬ ልጅ ሌዎንዶስም የአገንቦት ገዥ፣
16 የአፅራይ ልጅ ፋቂጤን የባህር ገዥ
17 የበንያስ ልጅ ማታን ሞግዚት፣
18 የኩሬም ልጅ አዳሪዝ ሰላሚ አልባሃ፣
19 የማትሬም ልጅ ደለከም የፈረሰኞች አለቃ፣
20 የኔድሮስ ልጅ አፃርዮስ የእግረኛ አለቃ፣
21 የዮዳድ ልጅ አውስጥረን የክብር ተሸካሚ፣
22 የአሳ ልጅ አስተርአዮን የከተማው አዋጅ ነጋሪ፣
23 የመታትያስ ልጅ ኢሚም የአጥቂው ጦር አለቃ፣
24 የካርዮስ ልጅ አቢስም የንጉሱ አልባሽ፣
25 የኔልትዮስ ልጅ ሊቀ ውንድዮስም የአደባባይ ሹም፣
26 የህፃንያስ ልጅ ከርሜም የቤተ መንግስት የግብር ሰብሳቢዎች አለቃ፣
27 የአካዝኤል ልጅ ሰራውያስም የቤተ መንግስት ሹም፣

www.ethiopianorthodox.org

28 እሉ ኵሎሙ እለ ተውህቡ ለዳዊት ንጉሠ ኢትዮጵያ ወልደ ሰሎሞን
ንጉሠ እስራኤል።
29 ወዓዲ ወሀቦ አፍራሰ ወሰረገላተ ራኩባተ ወአብቅልተ ወጽዑነ ሰ
ረገላተ ወርቀ ወብሩረ ወአልባሰ ክቡረ ቢሶሰ ወሜላተ ዕንቈ
ባሕርያተ ወአፍራጸ ወኵሎ ዘይትፈቀድ ለብሔረ ኢትዮጵያ ወሀቦ
ለወልዱ።
30 ወእምዝ ተደለዉ ከመ ይሑሩ። ወኮነ ፍሥሓ ለመኳንንተ ንጉሠ
ኢትዮጵያ ወኮነ ኀዘን ለመኳንንተ ንጉሠ እስራኤል እስመ በእንተ
በኵሩ ለሰሎሞን ንጉሠ እስራኤል ዝውእቱ ንጉሠ ኢትዮጵያ ተውህበ
በኵሮሙ ለመኳንንተ እስራኤል ከመ ይንግሡ ለብሔረ ኢትዮጵያ
ምስለ ወልደ ሰሎሞን ንጉሥ። ወእምዝ ተጋብኡ ወበከዩ ምስለ
አበዊሆሙ ወእማቲሆሙ ወአዝማዲሆሙ ወአንጋዲሆሙ ምስለ
ሕዘቢሆሙ ወበሐውርቲሆሙ ወይረግምዎ በኅቡእ ለንጉሥ ወየሐምይዎ
በእንተ ዘሄደ ደቂቆሙ ዘእንበለ ፈቃዶሙ።
31 ወለንጉሥሰ ይብልዎ ሠናየ ገበርከ። በእንተዝ እስመ ኀየሰ ጥበብከ
ከመ መንግሥተ እስራኤል ኮነት ለብሔረ ኢትዮጵያ በፈቃደ
እግዚአብሔር ወበጥበበ ዚአከ።
32 ወለካልኣንኒ መንግሥታት ያገብኦን እግዚአብሔር ውስተ እደከ እስመ
ሠናየ ትሔሊ ለእግዚአብሔር ወትፈቅድ ከመ ያምልክዎ ለአምላከ
እስራኤል ወከመ ይሠረዉ ጣዖታት እምዓለም።
33 ወይዌድስዎ ወይብልዎ ይእዜ አእመርነ ከመ በእንቲአከ ይቤሎ
እግዚአብሔር ለአቡነ አብርሃም በዘርዕከ ይትባረኩ ኵሎሙ አሕዛበ
ምድር ወያሜንዩ ገጾሙ ወይሥሕቁ በቅድሜሁ ወይዌድስዎ ፈድፋደ
በእንተ ጥበቡ።
34 ወሶበ ዘንተ ይብልዎ የአምሮሙ በጥበብ ወይትዔገሦሙ እስመ
እግዚአብሔር ይትዔገሠነ እንዘ የአምር ኵሎ ኃጢአተነ።
35 ወመንግሥትሰ ለእግዚአብሔር ኵላ ምድር ወሰማያትኒ ወአጽናፈ
ዓለም ወባሕር ወየብስ ውእቱ ይኴንን ወለንጉሠ ምድርሂ ወሀቦ
እምታሕቲሁ ከመ ይኰንን ከማሁ ለእለ ይገብርዋ ለሠናይት ከመ
ይዕሥዮሙ ሠናየ እስመ መንፈሰ እግዚአብሔር የዐርፍ ውስተ ልቡ
ለንጉሥ ወእደዊሁ ውስተ ሕሊናሁ ወአእምሮቱ ውስተ ልቡናሁ።

## ፴ወ፬ ከመ ኢምፍትው ሐምዮ ንጉሥ

1 ወኢመፍትው ይሕምይዎ ለንጉሥ እስመ መሢሑ ለእግዚአብሔር
ውእቱ።
2 ኢመፍትው ወኢኮነ ሠናየ ሐሚዮቱ ለንጉሥ።
3 ለእመ ገብረ ሠናየ ኢይትኀጐል እምሠለስቱ መንግሥት። ፩ ያገርር
ሎቱ ፀሮ ወኢያገብኦ ውስተ እደ ጸላኢሁ። ፪ ወበሰማያትኒ ያነግሦ
ምስሌሁ ምስለ ጻድቃኒሁ ወያነብሮ በየማኑ። ፫ በዲበ ምድርኒ

- 41 -

28 እነዚህ ሁሉ ለሰሎሞን ልጅ ለኢትዮጵያዊው ንጉስ ለዳዊት የተሰ
ጡት ናቸው።
29 ከዚህም በቀር ፈረሶችን፣ ሰረገላዎችን4 የግመል ባዝራዎችን፣
በቅሎዎችን፣ የተጫኑ ሰረገላዎችን፣ ወርቅን፣ ብርን፣ የከበሩ
ልብሶችን፣ ጥሩ ሃሮችን፣ ግምጃዎችን፣ እንቁዎችን፣ የሚያበሩ
እንቁዎችንና ፈርጦችንና ለኢትዮጵያ የሚገባውን ሁሉ ለልጁ ሰጠው።
30 ከዚህ በሁዋላ ይሄዱ ዘንድ ተዘጋጁ። ለኢትዮጵያ ንጉስ መኳንንት
ደስታ፣ ለእስራኤል ንጉስ መኳንንትም ሃዘን ሆነ። በእስራኤል ንጉስ
በሰሎሞን በኩር ልጅ ማለትም በኢትዮጵያው ንጉስ ምክንያት
የበኩር ልጆቻቸው ከንጉሱ ከሰሎሞን ልጅ ጋር በኢትዮጵያ ይነግሡ
ዘንድ ተሰጥተዋልና። ተሰብስበው ከኣባቶቻቸውና ከእናቶቻቸው
ከዘመዶቻቸው፣ ከእንግዶቻቸው፣ ከህዝቦቻችውና ከኣገራቸው ጋር
ኣለቀሱ። ንጉሱንም ልጆቻቸውን ያለፈቃዳቸው ስለቀማቸው በስውር
ያሙትና ይረግሙት ነበር።
31 በግልጽ ግን ንጉሱን "በእግዚኣብሄር ፈቃድና በኣንተ ጥበብ
የእስራኤል መንግስት ለኢትዮጵያ ሆናለችና ጥበብህም ደግሞ
የበለጠች ናትና መልካም ኣደረግህ" ይሉት ነበር።
32 "የእስራኤልንም ኣምላክ ያመልኩትና ጣኦታትንም ከኣለም ይነቀሉ
ዘንድ ለእግዚኣብሄር መልካምን ታስባለህና እግዚኣብሄር ሌሎችንም
መንግስታት በእጅህ ያስገባቸዋል።"
33 እያመሰገኑም "እግዚኣብሄር ኣባታችን ኣብርሃምን የምድር ኣህዛብ
በዘርህ ይባረካሉ ያለው ስለ ኣንተ እንደሆነ ዛሬ ኣወቅን" ይሉት
ነበር። መልካቸውን ያሳምሩ፣ በፊቱም ይስቁና ስለ ጥበቡም
ፈጽመው ያመሰግኑት ነበር።
34 ይህንን ሲሉት በብልሃቱ ያውቅባቸውና ይታገሳቸውም ነበር፤
እግዚኣብሄር ሃጢኣታችንን ሁሉ እያወቀ ይታገሰናልና።
35 መንግስት የእግዚኣብሄር ናት። ምድርን ሁሉ፣ ሰማያትንም ሁሉ፣
የኣለምን ዳርቻና የብስንም እሱ ይገዛል። የምድር ንጉስም ከእሱ
በታች እንደ እሱ እንዲገዛና ክፉ ለሚሰሩ፣ ፍዳቸውን መልካም
ለሚያደርጉ ዋጋቸውን እንዲከፍላቸው ሰጠው።
የእግዚኣብሄር መንፈስ በንጉሱ ልብ ያርፋልና። እጆቹ በህሊናው፣
እውቀቱም በልቡናው ነውና።

## ፴፬ ንጉስን ማማት እንዳይገባ

1 ከእግዚኣብሄር የተሾመ ነውና ንጉስን ያሙት ዘንድ ኣይገባም።
2 ንጉስን ማማት መልካም ኣይደለም። ኣይገባም።
3 መልካም ከሰራ ከሶስት መንግስት ኣይጎድልም። ጠላቱን ያስገዛለታል።
በጠላቶቹም እጅ ኣያስገባውም። በሰማያትም ከእሱና ከፃድቃኑ ጋር
ያነግሰዋል። በቀኙም ያስቀምጠዋል። በምድር ላይም በክብርና

www.ethiopianorthodox.org

ያነግሦ በክብር ወበፍሥሓ ወያረትዕ ሎቱ መንግሥቶ ወያገርር
አሕዛበ ታሕተ እገሪሁ።
4 ወእመሰ ተዐወሮ ለእግዚአብሔር ወኢገብረ ሠናየ ወኢሖረ በፍኖት
ርትዕት ለሊሁ እግዚአብሔር ይገብር በከመ ፈቀደ ላዕሌሁ ወበዲበ
ምድርኒ የሐጽጽ መዋዕሊሁ ወበሰማያትኒ ውስተ ማኅደረ ሲኦል ምስለ
ዲያብሎስ ማኅደሩ ወበዲበ ምድርኒ ዘእንበለ ጥዒና ወፍሥሓ ልብ
ምስለ ድንጋፄ ወፍርሃት ዘእንበለ ሰላም በሁከት።
5 ኢኮነ ሠናየ ሐሚዮቱ ለንጉሥ እምሕዝብ እለ እምታሕቴሁ እስመ
ፍዳ ለእግዚአብሔር ውእቱ።
6 ወባሕቱ ካህናትሰ አምሳለ ነቢያት እሙንቱ። ወባሕቱ ፈድፋደ
ይኄይሱ እምነቢያት እስመ ተውህቦሙ ምሥጢራት ከመ የአኀዙ
ፀሐየ ጽድቅ ሱ ራፌል እለ ተፈጥሩ እምእሳት ዘኢይክሉ እኂዘ
ምሥጢራት ዘእንበለ በጉጠት።
7 ለካህናትሰ ሰመዮሙ ጼወ። ወዓዲ ለካህናት ሰመዮሙ ማኅቶተ። ካዕበ
ሰመዮሙ ብርሃና ለዓለም።[44] ወካዕበ ሠመዮሙ ፀሐየ ዘያበርህ
ጽልመተ እንዘ ክርስቶስ ፀሐየ ጽድቅ ውስተ አልባቢሆሙ።
8 ወካህንሰ ዘቦቱ ልቡና ይገሥጽ ለንጉሥ በእንተ ምግባራት ዘርእየ
ወዘኢርእየሰ እግዚአብሔር ይፈትን ወአልቦ ዘይወቅሶ።
9 ወዓዲ ኢይሕምይዎሙ አሕዛብ ለጳጳሳት ወለካህናት እስመ ደቂቀ
እግዚአብሔር ወሰብአ ቤቱ እሙንቱ በእንተ ዘገሠጾሙ በእንተ
ኃጢአቶሙ ወጌጋዮሙ።
10 ወአንተኒ እ ካህን ለእመ ርኢከ ዕውቀ ኃጢአቶ ለብእሲ ኢትኅፈር
ገሥጾቶ ኢያፍራህከ ሰይፍ ወኢስደት።
11 ወስማዕ ዘከመ ተምዖ እግዚአብሔር ለኢሳይያስ በእንተ ዖዝያን ንጉሥ
እስመ ኢገሠጾ።
12 ወካዕበ ስማዕ በእንተ ሳሙኤል ነቢይ ዘከመ ገሠጾ ለሳኦል ንጉሥ
እንዘ ኢየኀፍሮ።[45] ወሠጠጠ መንግሥቶ በነገሩ ወኤልያስኒ ለአክዓብ[46]
ወአንተኒ ኢትኅፈር። ገሥጽ ወመሐሮ ለዘይኤብስ።
13 ወእስራኤል እምትካት የሐምዩ ንጉሦሙ። ወያምዕዑ ነቢያቲሆሙ።
ወድኅረሰ ሰቀሉ መድኃኒቶሙ።
14 ወሕዝበ ክርስቲያንሰ መሃይምናን ይነብሩ በሰላም ዘእንበለ ደዌ
ወሕማም ዘእንበለ ጽልአ ወማዕቀፍ ምስለ ንጉሥነ ዕገሌ መፍቀሬ
እግዚአብሔር እንዘ ኢየአትት እምልቡ ነገረ ጽድቅ ወሃይማኖት
በእንተ አብያተ ክርስቲያናት ወመሃይምናን ወፀሩኒ ግሩራን በኀይለ
መስቀሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ።

[44] ማቴ.5፥14፡ማር.9፥50፡ሉቃ.14፥34-35
[45] 1ሳሙ. 15፥19-20
[46] 1ነገ.18፥18-19

- 42 -

በደስታ ያነግሰዋል። መንግስቱን ያቀናለታል። ኣህዛብን ከእግሩ
በታች ያስገዛለታል።
4 እግዚኣብሄር ቸል ቢለውና መልካም ባያደርግ፣ በቀና መንገድ
ባይሄድ ግን እግዚኣብሄር በላዩ ላይ እንደወደደ ያደርጋል።
በምድር ዘመኑ ያጥራል። በሰማያት ቤቱ በሲኦል ውስጥ
ከዲያቢሎስ ጋር ነው። በምድርም ያለጤናና ያለ ልብ ደስታ
በድንጋጤ በፍርሃትና ያለ ሰላምም በሁከት ይሆናል።
5 ከበታቹ ከሆኑት ህዝቦች ንጉስን ማማት መልካም ኣይደለም። ዋጋን
መክፈል የእግዘኣብሄር ፈንታ ነውና።
6 ካህናቱ ግን እንደ ነቢያት ናቸው። ከነቢያትም ደግሞ ይበልጣሉ።
ምክንያቱም ከእሳት የተፈጠሩ ሱራፌል በጉጠት ካልሆነ በቀር
መያዝ የማይቻላቸውን ምስጢር ማለትም የእውነት ፀሃይን ይይዙ
ዘንድ ምስጢራት ተሰጥተዋቸዋልና።
7 ደግሞም ካህናትን "ጨው" ኣላቸው። "መብራት" ኣላቸው።
"የኣለም ብርሃንም"[44] ኣላቸው። እውነተኛ ፀሃይ ክርስቶስ በልባቸው
ውስጥ ስላለ ጨለማን የሚያበራ ፀሃይ ኣላቸው።
8 ልቡና ያለው ካህን ስለሚያያቸው ስራዎች ንጉሱን ይገስፀዋል።
ስለማያያው ግን እግዚኣብሄር ይመረምራል። የሚወቅሰውም የለም።
9 ደግሞም ስለ ሃጢያታቸውና ስለ በደላቸው፣ ስለ ገሰፃቸው
የእግዚኣብሄር ልጆችና ቤተሰቦች ናቸው። ህዝቡ ጳጳሳቱንና
ካህናቱን ኣይሟቸው።
10 ካህን ሆይ ኣንተ ደግሞ የሰውን የታወቀ ሃጢኣት ስታይ መገሰፅን
ኣትፍራ። ሰይፍም ስደትም ኣያስፈራህ።
11 እግዚኣብሄር ስለ ንጉሱ ኦዝያን ኢሳያስን እንደተቆጣው ስማ።
ኣልገሰፀውም ነበርና።
12 ደግሞም ሳሙኤል ንጉሱን ሳኦልን ሳያፍር እንደገሰፀው ስማ።
መንግስቱንም ደግሞ ቀደደ።[45] ኤልያስም ኣክኣብን እንዲሁ።[46]
ኣንተ ግን መገሰፅን ኣትፍራ። የሚበድለውንም ኣስተምረው።
13 እስራኤል ግን ከመጀመሪያው ጀምሮ ንጉሳቸውን ያሙና
ነቢያቶቻቸውንም ያስቆጡ ነበር። በሁዋላ ግን ነቢያቶቻቸውንም ሰ
ቀሉ።
14 ኣማኞች የክርስቲያን ወገኖች ግን የእውነትንና የሃይማኖት ነገርን
እንዲሁም ስለ ኣብያተ ክርስቲያናትና ስለ መሃይምናን ማሰብን
ከልቡ ሳያስወግድ ጠላቶቹን በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ሃይል
ከሚገዙለትና እግዘኣብሄርን ከሚወደው ከንጉሳቸው ጋር ያለ ደዌና
ህማም፣ ያለ ጠብና እንቅፋት በሰላም ኖሩ።

[44] ማቴ.5፥13፡ማር.9፥50፡ ሉቃ.14፥34-35
[45] 1ሳሙ.15 ፥19-20
[46] 1ነገ.18፥18-19

www.ethiopianorthodox.org

## ፺ወ፭ በእንተ ዘበከዩ ወመከሩ እለ ተፈነዉ

1 ወደቂቀ መኳንንተ እስራኤልሰ እለ ተአዘዙ ከመ ይሑሩ ምስለ
ወልደ ንጉሥ መከሩ ኅቡረ እንዘ ይብሉ ምንተ ንሬሲ እስመ ኀደግነ
ብሔረነ ወሙላደነ ወአዝማዲነ ወሰብአ ሀገርነ።
2 ወይእዜኒ ሀቡ ከመ ናቅም ኪዳነ በባሕቲትነ ዘኢየአምሩ አዝማዲነ
ከመ ንትፋቀር በህየ ወአልቦ ዘይጌጉእ ወይጕነዲ በዝየ። ወኢንፍራህ
ወኢንናፍቅ እስመ በዝየኒ እግዚአብሔር። ወበህየኒ እግዚአብሔር።
ወይኩን ሥምረቱ ለእግዚአብሔር። ወሎቱ ስብሐት እስከ ለዓለመ
ዓለም አሜን።
3 አውሥኡ አዛርያስ ወአልሚያስ ደቂቀ ካህናት ባዕድሰ ኢያኀዝነነ
በእንተ ዘጸልኡነ አዝማዲነ።
4 ወባሕቱ ነኀዝን በእንተ ጽዮን እግዝእትነ እስመ የኀድጉነ ኪያሃ።
እስመ ባቲ አወፈዩነ ለእግዚአብሔር ወተልእክነ ላቲ እስከ ዮም።
ወባሕቱ ነኀዝን በእንቲአሃ። እስመ የኀድጉነ ኪያሃ። በእንተዝኬ
ፈድፋደ ያበክየነ በእንቲአሃ።
5 ወአውሥኡ እሙንቱ ባዕዳን ወይቤልዎሙ በአማን ዛቲ ይእቲ
እግዝእትነ ተስፋነ ወምክሕነ ወልህቅነ በብፅዐቲሃ። ወበአይቴ ንክል
ኀዲጎታ ለጽዮን እግዝእትነ። እስመ ላቲ ተውህብነ። ወምንተ ንሬሲ
ሶበ አበይነ ትእዛዞ ይቀትለነ ንጉሥ። ወኢንክል ተዓድዎ እምቃለ
አበዊነ ወእምትእዛዘ ንጉሥ። ወምንተ ንገብር በእንተ ጽዮን
እግዝእትነ።
6 ወአውሥአ አዛርያስ ወልደ ሳዶቅ ካህን ወይቤ አነ እመክረክሙ
ዘንገብር። ሀቡኒ ኪዳነ እስከ ፀአተ ነፍስክሙ። ወመሐሉ ሊተ ከመ
ኢትንግሩ እመኒ ሞትነ ወእመኒ ሐየውነ ወእመኒ ተእኅዝነ ወእመኒ
ወፃእነ።
7 ወመሐሉ ሎቱ በስመ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ወበጽዮን ሰ
ማያዊት ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ወበዘአሰፈዎ ለአብርሃም
ወበንጽሑ ወበኂሩቱ ለይስሐቅ ወበአስተባዝኆ ለያዕቆብ ወአውረሶ
ምድረ ነኪረ ሎቱ ወለዘርዑ እምድኅሬሁ።
8 ወዘንተ ሶበ መሐሉ ሎቱ አውሥአሙ ወይቤሎሙ ሀቡኬ ንንሥአ
ለጽዮን እግዝእትነ ወዘከመ ንነሥኣ አየድዐክሙ። ወግበሩ ምክርየ።
ለእመ እግዚአብሔር ፈቀደ ንክል ነሢአታ ለእግዝእትነ ምስሌነ።
ወለእመኒ አእመሩነ ወቀተሉነ ኢየኀዝነነ። እስመ በእንተ እግዝእትነ
ጽዮን ንመውት።

9 ወተንሥኡ ኵሎሙ ወሰዐምዎ ርእሶ ወገጾ ወዐይኖ። ወይቤልዎ
ንገብር ኵሎ ዘአምከርከነ። ንመውትሂ ወነሐዩሂ ምስሌከ በእንተ
እግዝእትነ ጽዮን። እመኒ ሞትነ እየኀዝነነ። ወለእመ ሐየውነ ዘፈቀደ
እግዚአብሔር ይከውን።



## ፺፭ የተላኩት እንዳለቀሱና እንደ መከሩ

1 ከንጉሡ ልጅ ጋር እንዲሄዱ የታዘዙት የእስራኤል መኳንንት ልጆች
ግን "ሃገራችንን፣ ትውልዳችንን፣ ዘመዶቻችንና የኣገራችንን ሰዎች
ትተናልና ምን እናድር?" ሲሉ በኣንድነት መከሩ።
2 "ኣሁንም በእዚህ እርስ በርሳችን ልንዋደድ፣ እዚያም እግዚኣብሄር
ነውና የሚቸኩልም የሚዘገይም ሳይኖር፣ እዚህም ሳንፈራና
ሳንጠራጠር፣ ዘመዶቻችንም ሳያውቁ ቃል ኪዳን እንግባ። የእግዚኣብሄር
ፈቃድ ይሁን። ለእሱም ለዘላለሙ ምስጋና ይገባል።" ኣሉ።
3 የካህናት ልጆች ኣዛርያስና ኣልሚያስም "ዘመዶቻችን ስለጠሉን ነው
እንጂ ሌላውስ ኣያሳዝነንም" ሲሉ መለሱ።
4 "ይልቁንም ደግሞ ስለእመቤታችን ፅዮን እናዝናለን። እሷን
ኣስቀርተውብናል፣ በእሷም ምክንያት ለእግዚኣብሄር ሰጥተውናል፣
እስከ ዛሬም ተልከንላታልና ስለ እሷ እናዝናለን። እሷን
ያስቀሩብናልና በእሷ ምክንያት ፈጽሞ እናለቅሳለን" ኣሉ።
5 ሌሎችም መልሰው "በእውነት እሷ እመቤታችን፣ ተስፋችንንና
መመኪያችን ናት። በእሷም ብፅኣት ኣደረገን። እንዴትስ
እመቤታችንን ጽዮንን ልንተዋት እንችላለን? ለእሷም ተሰጥተናልና
ምን እናድርግ? ትእዛዙን እንቢ ብንል ንጉሡ ይገድለናል።
ከኣባቶቻችን ቃልና ከንጉሡ ትእዛዝ መተላለፍ ኣንችልም።
ስለእመቤታችን ጽዮን ምን እናድርግ?" ኣሉ።
6 የካህኑ የሳዶቅ ልጅ ኣዛርያስም መልሶ "የምናደርገውን እኔ
እመክራችሁዋለሁ። ብንሞትም፣ በህይወት ብንኖርም፣ ብንያዝም፣
ብንወጣም እስከ ሞት ድረስ ላትናገሩ ቃል ኪዳን ግቡልኝ፣
ማሉልኝም" ኣለ።
7 እነሱም በእስራኤል ኣምላክ በእግዚኣብሄር ስም፣ የእግዚኣብሄር
ታቦተ ህግ በሆነችው በሰማያዊቷ ጽዮንና ለኣብርሃም በሰጠው
ተስፋ፣ በይስሃቅ ቸርነትና ብርታት፣ ያእቆብን ባዘዘውና ከእሱም
በሁዋላ ለዘሩ የባእድ ኣገርን ባወረሰው ማሉለት።
8 በማሉለትም ጊዜ መልሶ "እመቤታችን ጽዮንን እንወስዳት ዘንድ
ፍቀዱ። እንዴት እንደምንወስዳት እነግራችሁዋለሁ። በምክሬ
ተስማሙ። እግዚኣብሄር ከፈቀደ እመቤታችንን ከእኛ ጋር መውሰድ
እንችላለን። ቢያውቁብንና ቢገድሉንም ኣያሳዝነንም። ስለ
እመቤታችን ጽዮን እንሞታለንና" ኣላቸው።
9 ሁሉም ተነስተው ራሱን፣ ፊቱንና ኣይኑንም ሳሙት። "የመከርከንንን
ሁሉ እናደርጋለን። ከኣንተ ጋር እንሞታለን።
ከኣንተም ጋር እንድናለን። ስለ እመቤታችን ብንሞትም ኣናዝንም
ብንድንም እግዚኣብሄር የወደደው ይሁን" ኣሉ።

www.ethiopianorthodox.org

10 ወይቤ አሐዱ እምኔሆሙ ወልደ ዮአስ ዘስሙ ዘካርያስ አንሰ ስእንኩ
ነቢረ እምብዝኀ ፍሥሓ ዘውስተ ልብየ። ንግረኒኬ አንተሰ ትክል
ነሚአታ በአማን። ወኢኮነ ሐሰት እስመ አንተ ታንሶሱ ውስተ ቤተ
እግዚአብሔር ህየንተ አቡከ። ወመራትትኒ ውስተ እደከ። ኵሎ ጊዜ
ወዘእንበለ ይንሥኡ መራትተ እምእደከ ጠይቅ በዘንመክር
ወመሳክዋተኒ ኀቡኣተ ዘገብረ ንጉሥ ሰሎሞን። አንተ ተአምር
ወካህናትሂ አልቦሙ ዘይበውኡ ህየ ዘእንበለ አቡከ ምዕረ በበዓመት
ፍቅድ ወኀሊ ወኢትኑም በእንተዝ ግብር ከመ ትፍቅድ ነሚአታ
ወንሑር ምስሌሃ በከመ አወፈየነ ወትኩን ለነ ፍሥሓ ወለአበዊነ
ኀዘን በምጽአተ ዚኣሃ ምስሌነ ውስተ ሀገረ ኢትዮጵያ።
11 ወእምዝ ይቤሎሙ አዛርያስ ግበሩ ዘአነ እቤለክሙ ወንረክብ ሀቡኒ
በበዐሠርቱ ዲድርክም ወእሁቦ ለፀራቢ ከመ ያፍጥን ሊተ ገቢረ
አልዋሐ ሠናያነ ወያስተጣግዖን ሊተ ፍጡነ በእንተ ፍቅረ ብሩር
በቆማ ወግድማ ወኑኃ ወሥፍራ ለእግዝእትየ ወእሁቦ ሠፈርየ ላቲ
ዲበ ባሕር እመቦ ለእመ ተጕድዐት ሐመር ከመ እዕርግ ውስተ
ረመስ ወንድኀን እምባሕር። ወአነ እወስዳ በበአሐዱ ዘእንበለ
አስተጣግዖ ወበህየ አስተላጽቆን ለእሙንቱ ዕፀው ወአነብሮሙ ውስተ
ምንባሪሃ ለጽዮን ወአለብሶን አልባሲሃ ለጽዮን። ወእነሥኣ ለጽዮን
ወእከሪ ምድረ። ወአነብራ ህየ እስከ ነሐውር ወንነሥኣ ምስሌነ።
ወለእግዚእየሰ ንጉሥ ኢይነግሮ እስከ ነሐውር ርኁቀ።
12 ወወሀብዎ ኵሎሙ በበዐሠርቱ ዲድርክም። ወነሥኦ ወወሀቦ ለጸራቢ።
13 ወእሠነየ ሎቱ በአሐቲ ጊዜ እምነ ትሩፋተ ዕፀው ዘቤተ መቅደስ።
14 ወተፈሥሐ ወአርአዮሙ ለአኀዊሁ።

## ፴ወ፮ ዘከመ መከሩ በእንተ ጽዮን

1 ወእንዘ ይነውም በሌሊት አስተርአዮ መልአከ እግዚአብሔር ለአዛርያስ
ወይቤሎ ንሣእ ለከ አርባዕተ ጠሊተ ዘዘዓመት ዘበእንተ ኀጢአትክሙ
ወለከ ወለኤርምያስ ወለአቢሳ ወለማክሪ። ወአርባዕተ አባግዐ ንጹሐ
ዘዘዓመት ወአሐተ ላህመ እንተ ኢሰሐበት አርዑተ ወትሠውዓ
እምሥራቃ ወአባግዐኒ ወአጣሌ በየማና ወበፀጋማ ወበዐረቢሃ እንተ
ኀበ ሙፃኣ። ወይንግሮ እግዚእከሙ ዳዊት ለሰሎሞን ንጉሥ ወይበሉ
አሐተ እስእል በኀቤከ አ አባ ከመ እሡዕ ለቅድስት ሀገር
ኢየሩሳሌም ወለእግዝእትየ ጽዮን ቅድስት ሰማያዊት ታቦተ ሕጉ
ለእግዚአብሔር። ወይበሉ ግበር ወካዕበ ይበሉ ይሡዕ ሊተ ወልደ
ካህን በከመ የአምር። ወይኤዝዝከ ለከ።



10 ከእነሱ አንዱ ስሙ ዘካርያስ የተባለ የዮአስ ልጅ በልቡ ውስጥ
ካለው የደስታ ብዛት የተነሳ "መቀመጥ ተሳነኝ። በእውነት አንተ
ጽዮንን መውሰድ ትችላለህ፤ ሃሰት አይደለም። ስለ አባትህ ወደ
እግዚአብሄር ቤት ትመላለሳለህና። ቁልፉም ሁልጊዜ በእጅህ ነውና።
ቁልፉንም ከእጅህ ሳይወስዱ የምንሞክርበትን አፈላልግ። ንጉሱ ሰ
ሎሞን ያደረጋቸውን የተሰወሩ መስኮቶችንም አንተ ታውቃለህ።
አባትህ በቅድስተ ቅዱሳን ስለ ራሱና ስለ ህዝቡ ለመስዋት
በያመቱ ከመግባቱ በቀር ካህናቱም ወደ እዚህ የሚገቡበት
ምክንያት የለም። ስለዚህ ፈቃድህ ይሁን። አስብ። እሷን ትወስድና
ከእሷ ጋር እንድንሄድ ትፈቅድ ዘንድ ቸል አትበል።። እኛን
አሳልፈው እንደሰጡን ለእኛ ደስታና ለአባቶቻችን የእሷ ከእኛ ጋር
ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ሃዘን ይሁን" አለ።
11 ከዚህ በሁዋላ አዛርያስ አላቸው። "የምላችሁን አድርጉ። የሻነውንም
እናገኛለን። እያንዳንዳችሁ አስር አስር ብር ስጡኝና በገንዘቡ
ያማሩ ጽላቶቹ ስራ እንዲያፋጥንልኝና ስለ ገንዘቡም ፍቅር
በእመቤታችን በቁመቷ፤ በወርዷ፤ በርዝመቷና በልኳ ያጠጋጋልኝ
ዘንድ ለጠራቢው እሰጠዋለሁ። ሰፍሩንም ሰፍሬ እሰጠውና
ታንኳዎችን አደርግ ዘንድ ችንካር አድርግልኝ እለዋለሁ። በባህር
ላይ እንሄዳለንና መርከቧ ብትጎዳ ወደ ታንኳ እንድንገባና ከባህር
እንድን ዘንድ ይረዳል። እኔም ሳላጠጋጋ እያንዳንዱን ነጣጥዬ
እወስዳለሁ። ከዚያም እንጨቶችን አጠጋጋቸዋለሁ። በፅዮን
መቀመጫ አስቀምጣቸዋለሁ። የፅዮንን ልብስም አለብሳቸዋለሁ።
ፅዮንንም እወስዳታለሁ። ምድርም ቆፍሬ እስክንሄድ ድረስ ከዚያ
አስቀምጣታለሁ። ከእኛ ጋርም እንወስዳታለን። ለጌታዬ ለንጉሱ ግን
ርቀን እስክንሄድ ድረስ አልነግረውም። "
12 ሁሉም አስር አስር ብር ሰጡት። እሱም ተቀበለና ለእንጨት
ጠራቢው ሰጠው።
13 በአንድ ጊዜ ከቤተ መቅደሱ እንጨት ትርፍራፊ አሳምሮ ሰራለት።
14 ደስም ተሰኘና ለወንድሞቹ አሳያቸው።

## ፴፮ ስለ ፅዮን እንደ መከሩ

1 አዛርያስም ሌሊት ተኝቶ ሳለ የእግዚአብሄር መልአክ ተገለፀለትና "በየአመቱ
ለሃጢአታችሁ የሚቀርቡትን አራት ፍየሎች ለአንተ፣ ለኤርምያስ፣ ለአቢስና
ለማክሪ ውሰድ። እንዲሁም የአመቱን አራት ንፁህ በጎች ትወስዳለህ። አንድ
ቀንበር ያላረፈባት ላም ትወስድና በምስራቅ በኩል ትሰዋታለህ። በቀኝዋና
በግራዋ በምእራቧና በመውጫዋ በኩል ትሰዋቸዋለህ። ጌታችሁ ዳዊትም ለንጉሱ
ሰሎሞን አባቴ ሆይ! ከአንተ ዘንድ አንድ ነገርን እለምናለሁ። ለተቀደሰ
ችው አገር ለኢየሩሳሌም፣ ለተቀደሰችውና የእግዚአብሄር ታቦተ ህግ ለሆነችው
ለእመቤታችን ለሰማያዊቷ ፅዮን እሰዋ ዘንድ ነው' ብሎ ይንገረው። ደግሞም
እንደሚያውቅ የካህን ልጅ ይሰዋልኝ ይለዋል። አንተንም ያዝዝሃል።

www.ethiopianorthodox.org

ወአንተ ትሠውዕ ወታወፅእ ለታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር እምድኅረ
ሦዕከ። ወካዕበ አስተርአየከ ዘከመ ትገብር ላቲ እንዘ ታወፅኣ እስመ
እምኀበ እግዚአብሔር ኮነት ዛቲ እስመ አምዕዕዎ እስራኤል
ለእግዚአብሔር ወበእንተዝ ያፈልሳ ለታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር
እምኔሆሙ።
ወሶበ ነቅሐ እምንዋሙ አዛርያስ ተፍሥሐ ፈድፋደ ወበርሀ ልቡ
ወሕሊናሁ ወተዘከረ ኵሎ ዘአስተርአዮ በሌሊት መልአከ እግዚአብሔር
ወዘከመ ዐተቦ ወአጽንዖ ወአለበዎ።
3 ወሖረ ኀበ እሙንቱ አበዊሁ ወተጋብኡ አሐተኔ ወነገሮሙ ኵሎ
ዘከመ አስተርአዮ መልአከ እግዚአብሔር ወዘከመ ተውህበት ሎሙ
ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር። ወዘከመ ይትዔወራ እግዚአብሔር
ለመንግሥተ እስራኤል ወዘከመ ይሁባ ለባዕዳን ለክብሮሙ ወዘከመ
ንነሥእ ንሕነ ለታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ወዘከመ ተሀይደት ኀበኒ
መንግሥተ ሰሎሞን ወኢተርፈት ኀበ ኢዮርብዓም ወልዱ ዘእንበለ ፪
በትር ወዘከመ ትትከፈል መንግሥተ እስራኤል።
4 ወይእዜኒ ተፈሥሑ ሊተ እስመ አንሰ እትፌሣሕ በእንተ ዘአስተርአየኒ
ከመዝ እስመ ምስሌነ ትፈልስ ጸጋ ክህነቶሙ ወመንግሥቶሙ እስመ
በፈቃደ እግዚአብሔር ይከውን ከመዝ ይቤለኒ።
5 ወይእዜኒ ንዑ ንሑር ወንንግሮ ለዳዊት እግዚእነ ከመ ይበሎ ለአቡሁ
እሠውዕ።
6 ወሖሩ ወነገርዎ ወውእቱ ተፈሥሐ ወለአከ ኀበ ኢዮአስ ወልደ
ዮዳሔ ከመ ይምጻእ ኀቤሁ ወይልአኮ ኀበ አቡሁ።
7 ወመጽአ ወለአኮ ዳዊት ኀበ አቡሁ ሰሎሞን ወይቤሎ ፈንወኒአ
እሑርአ ውስተ ብሔርየ በኵሉ ዘአሠነይከ ሊተ ወጸሎትከ ትትልወኒ
ኀበ ሖርኩ በኵሉ ጊዜ።
8 ወባሕቱአ ይእዜኒአ እስእልአ በኀቤከአ ዕለተአ አሐተአ ለእመአ
ረከብኩአ ሞገሰአ በኀቤከአ ወኢትሚጥአ ገጸከአ እምኔየአ እስመ አነአ
ገብርከአ አሐውርአ ወእፈቅድአ እሠዕአ መሥዋዕተአ ወመድኀኒተአ
ለእንተ ኀጢአትየአ ውስተ ዛቲ ሀገርአ ቅድስትአ ኢየሩሳሌምአ
ወጽዮንአ ታቦተ ሕጉአ ለእግዚአብሔርአ ወሰላም ለዕዘዝከ።

## ፵ወ፮ በእንተ መሥዋዕተ አዛርያስ ወንጉሥ

1 ወሖረ ኢዮአስ ወልደ ዮዳሔ ወነገሮ ለንጉሥ ሰሎሞን።
2 ወተፈሥሐ ንጉሥ በእንተዝ። ወአዘዘ ከመ ያስተዳልዉ መሣውዐ
ወመሥዋዕተ ከመ ይሠዕ ወልዱ ወአምጽአ ወወሀቦ ዘይበፅዕ
ለእግዚአብሔር ፻ አሥዋረ ወ፻ መግዝአ ላህም ወ፼ አባግዐ ወ፼
አጣሌ ወእምነ ዘይትበላዕ አራዊት በበ፲ ወእም አዕዋፍ ዘንጹሕ
በበ፲ በዘያወጽሕ ወይሠውዕ ለአምላከ እስራኤል። ወመሥዋዕተ
ስንዳሌ ፳ ጸሕለ ዘብሩር ለለአሐቲ ዘበበ፲ወ፪ ድልወተ ሰቅሎን



አንተም ትሰዋለህ። ከሰዋህም በሁዋላ የእግዚአብሄርን ታቦተ ህግ
ታወጣታለህ" አለው። "ደግሞም ስታወጣት እንዴት እንደምታደርጋት
አሳይሃለሁ። ይህ ከእግዚአብሄር ዘንድ ሆኗልና። እስራኤል
እግዚአብሄርን አስቆጥተውታልና ስላገርህ የእግዚአብሄርን ታቦተ ህግ
ከእነሱ ይወስዳታል።"
2 አዛርያስም ከእንቅልፉ በነቃ ጊዜ ፈጽሞ ደስ አለው። ልቡም
ህሊናውም በራ። የእግዚአብሄር መልአክ በሌሊት በአሳየው ሁሉ፣ እንደ
ባረከውና እንዳፀናው እንዳስገነዘበውም አሰበ።
3 ወደ አባቶቹም ሄደ። በአንድነትም ተሰበሰቡ። የእግዚአብሄር መልአክ
እንደተገለፀለት፣ የእግዚአብሄር ታቦተ ህግም እንደ ተሰጠቻቸው
እግዚአብሄር የእስራኤልን መንግስት ቸል እንዳላትና ክብራቸውን ለሌላ
አሳልፎ እንደሚሰጣት፣ የእግዚአብሄርን ታቦተ ህግ እኛ እንደምንወስዳት
የሰሎሞን መንግስት ወደ እኛ እንደ ተወሰደችና ለልጁ ለኢዮርብአም
ከሁለት ነገድ በቀር እንዳልቀረችልትና የእስራኤልም መንግስት
እንደምትከፈል ሁሉ ነገራቸው።
4 አሁንም "እንደዚህ ያለ ስላሳየኝ ደስ ብሎኛልና ደስ ይበላችሁ።
የክህነታቸውና የመንግስታቸው እድል ከእኛ ጋር ትሄዳለች። ይህ
በእግዚአብሄር ፈቃድ ሆኗልና" አለኝ።
5 "አሁንም ኑ። ጌታችን ዳዊት አባቱን ልሰዋ እንዲለው እንነግረው
ዘንድ እንሂድ" አላቸው።
6 ሄደውም ነገሩት። እሱም ተደስቶ ወደ እሱ እንዲመጣና ወደ አባቱ
እንዲልከው፣ ወደ ዮዳሄ ልጅ ወደ ኢዮአስ ላከ።
7 እሱም መጣ። ዳዊትም ወደ አባቱ ወደ ሰሎሞን "ወደ አገሬ እሄድ
ዘንድ ፍቀድልኝ፤ ባደረግህልኝ መልካም ነገር ሁሉ አመሰግናለሁ፤
ጸሎትክም በሄድኩበት ሁሉ ሁልጊዜ ትከተለኝ" ሲል ላከ።
8 "እነሆ አሁንም አንዲት ልመና አቀርባለሁ። ሞገስንም አግኝቼ ቢሆን
ፊትህን ከእኔ አትመልስ። እኔ ሎሌህ እሄዳለሁና ስለ ሃጢአቴ በዚህች
ቅድስት አገር ኢየሩሳሌም የደህንነት መስዋትን ለእግዚአብሄር ታቦተ
ህግ ለጽዮን እሰዋ ዘንድ እሻለሁ፤ ለመንግስትህ ሰላም ይሁን።"

## ፵፮ ስለ አዛርያስና ስለ ንጉሱ መስዋእት

1 የዮዳሄ ልጅ ኢዮአስም ሄደና ለንጉሱ ሰሎሞን ነገረው። ንጉሱም በዚህ
ነገር ተደሰተ።
2 ልጁም መስዋቱን ይሰዋ ዘንድ መሰዊያውን እዲያዘጋጁ አዘዘ።
ለእግዚአብሄር የተሳለውንም መቶ በሬዎች፣ መቶ የላም ፍሪዳዎች፣ አስር
ሺ በጎች፣ አስር ሺ ፍየሎችና ደሙን አፍሶ ይሰዋ ዘንድ ለመስዋእት
የሚቀርቡ ከያይነቱ አስር አስር ከሚበሉ የዱር አራዊት፣ በየአስራ ሁለቱ

www.ethiopianorthodox.org

ወእብወ ፴ መዛርዐ ኀባውዝ ወዘንተ ኩሎ ወሀቦ ለዳዊት ወልዱ
ሰሎሞን ንጉሥ።
3 ወካዕበ ለአከ እንዘ ይብል ይሡዕአ ሊተ አዛርያስ ወልደ ካህን ሀየንቴየ
ወይቤሎ ግበርአ ዘፈቀድከ።
4 ወተፈሥሐ አዛርያስ በእንተዝ ነገር። ወሖረ ወአምጽአ እመራዕየ አቡሁ
አሐተ ላህመ እንተ ኢሰሐበት አርዑተ ወ፩ ጠሊተ ዘ ዓመት ወ፩ በግዐ
ንጹሐነ ዘዓመት።
5 ወሖረ ንጉሥ ከመ ይሡዕ። ወተደለዉ ካህናት። ወተጋብኡ ነዳያን።
ወተፈሥሑ አዕዋፈ ሰማይ። ወገብሩ ፍሥሓ ዐቢየ በይእቲ ዕለት።
6 ወአዛርያስኒ ደመረ ምስለ መሥዋዕተ ንጉሥ ወሦዐ ንዋዮ በከመ አዘዞ
መልአከ እግዚአብሔር ለአዛርያስ በሌሊት።
7 ወእምዝ እምድኅረ ሦዑ ገብኡ ውስተ አብያቲሆሙ ወኖሙ።

## ፴ወ፰ ኀበ አንሥእዋ ለጽዮን

1 ወናሁ ካዕበ አስተርአዮ መልአከ እግዚአብሔር ለአዛርያስ ወሠረቀ ላዕሌሁ
ከመ ዐምደ እሳት ወመልአ ቤተ በብርሃኑ።
2 ወአንሥኦ ለአዛርያስ ወይቤሎ ቁም ወጽናዕ። ወአንቅሖ ለኤልምያኖስ
እትኩ ወለአብሳ ወለማክሪ። ወንሥኡ እሉንተ ዕፀወ አልዋህ። ወአነ አርኅ
ለከ አናቅጺሃ ለቤተ መቅደስ። ወንሥአ ለታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር።
ወትወስዳ ዘእንበለ ደዌ ወሕማም። ወአነሂ እስመ ተአዘዝኩ እምኀበ
እግዚአብሔር ከመ እህሉ ዘልፈ ምስሌሃ ወእኩንከ መርሐ በነሢእታ።
ወተንሥአ ሶቤሃ ወአንቅሆሙ ለሠለስቲሆሙ አኀዊሁ። ወነሥኡ እሙንቱ
አልዋሐ። ወሖሩ ውስተ ቤተ እግዚአብሔር።
3 ወረከቡ ርኅወ ኩሎ አናቅጸ እምአፍአ እስከ ውስጥ ርኅዋተ አናቅጸ እስከ
ውእደ ይበጽሕ ኀበ ጽዮን ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር።
4 ወተንሥአት ሶቤሃ ከመ ቅጽበተ ዐይን። እስመ መልአከ እግዚአብሔር
ይሜግባ። ወሶበሰ ኢፈቀደ እግዚአብሔር እመ ኢተንሥአት ሶቤሃ።
5 ወነሥእዋ አርባዕቲሆሙ ወአእተውዋ ውስተ ቤተ አዛርያስ።
6 ወገብኡ ውስተ ቤተ እግዚአብሔር። ወአስተሳጸቁ ውስተ ምንባሪሃ ለጽዮን
ወከደንዎን ለዕፀው በአልባሲሃ ለጽዮን።
7 ወአጸዉ አናቅጸ። ወገብኡ ውስተ ቤቶሙ። ወነሥኡ መኀትወ። ወአንበርዋ
ውስተ ምንባኢሃ።
8 ወሦዑ ላቲ በግዐ። ወአጸንሕሑ ስሂነ። ወነጸፉ ላቲ ሜላተ። ወአንበርዋ
ውስተ ምስዋር ፯ ዕለተ ወ፯ ሌሊተ።

## ፴ወ፱ ኀበ ባረኮ አቡሁ ለወልዱ

1 ወእምዝ ተንሥአ ንጉሠ ኢትዮጵያ ከመ ይሑር ብሔሮ። ወቦአ ኀበ አቡሁ
ከመ ይጸሊ ሎቱ። ወይቤሎ ባርከኒ አባ። ወሰገደ ሎቱ።



3 ደግሞም የካህኑን ልጅ ኣዛርያስን ስለ እኔ ሆኖ ይሰዋልኝ ብሎ
ላከ። እሱም "የወደድከውን አድርግ" ኣለ።
4 ስለዚህም ነገር ኣዛርያስ ደስ ተሰኘ። ሄዶም ከኣባቱ መንጋ ቀንበር
ያላረገባት ኣንዲት ላምና ንፁህ የሆኑ ኣንድ ዓመት የሆናቸው
ኣራት በጎች ኣመጣ።
5 ንጉሱም ይሰዋ ዘንድ ሄደ። ካህናቱም ተዘጋጁ። ድሆችም ተሰበሰቡ።
የሰማይ ወፎችም ተደሰቱ። በዚህችም እለት ታላቅ ደስታን ኣደረጉ።
6 ኣዛርያስም የእግዚኣብሄር መልኣክ በሌሊት እንዳዘዘው ከንጉሱ
መስዋእት ጋር ጨምሮ የራሱን መስዋእት ሰዋ።
7 መስዋቱንም ከሰው በሁዋላ ወደ ቤታቸው ገቡ። ተኙም።

## ፴፰ ፅዮንን እንዳነሷት

1 እነሆ የእግዚኣብሄር መልኣክ ለኣዛርያስ ደግሞ ታየው። በላዩም
ላይ እንደ እሳት ምሰሶ ወጣ። በብርሃኑም ቤቱ መላ።
2 ኣዛርያስንም ኣስነስቶ "ቁም፤ ፅና፤ ወንድምህን ኤልምያኖስንና
ኣብሳን ማክሪንም ኣንቃ። እነዚህን የፅላት እንጨቶች ውሰዱ።
እኔም የቤተ መቅደሷን በሮች እከፍትልሃለሁ። የእግዚኣብሄርንም
ታቦተ ህግ ውሰዳት። ያለደዌና ህማም ትወስዳታለህ። እኔም
ለዘላለም ከእሷ ጋር እንድኖርና በኣያያዟም መሪ እንድሆንልህ
ከእግዚኣብሄር ታዝዣለሁ" ኣለው ።
3 እነዚያንም ፅላቶች ያዙ። ወደ እግዚኣብሄር ቤትም ሄዱ። ከውጭ
እስከ ውስጥ በሮቹ ሁሉ ክፍት ሆነው ኣገኙ። የበሮቹም መከፈት
የእግዚኣብሄር ታቦተ ህግ እስካለችበት ድረስ ነበር።
4 ያንጊዜም የእግዚኣብሄር መልኣክ ይጠብቃት ነበርና እንደ ቅፅበተ
ኣይን ተነሳች። እግዚኣብሄር ባይፈቅድ ግን ባልተነሳች ነበር።
5 ኣራቱም ኣነሷትና ወደ ኣዛርያስ ቤት ኣስገቧት።
6 ወደ እግዚኣብሄር ቤትም ገቡ። በፅዮንም ማስቀመጫ እንጨቶችን
ኣገጣጠሙ። እንጨቶቹንም በፅዮን ልብሶች ሸፈኗቸው።
7 በሮቿንም ዘግተው ወደ ቤታቸው ተመለሱ። ማብሪያንም ይዘው
በመሸሸጊያው ኣስቀመጧት።
8 በግንም ሰውላት። ነጭ እጣንንም ኣጠኑላት። ቀይ ግምጃንም
ኣነጠፉላት። በመሰወሪያም ውስጥ ሰባት ቀንና ሰባት ሌሊት
ኣስቀመጧት።

## ፴፱ ኣባት ልጁን እንደመረቀው

1 ከዚህ በሁዋላ የኢትዮጵያ ንጉስ ወደ ኣገሩ ይሄድ ዘንድ ተነሳ።
ይመርቀውም ዘንድ ወደ ኣባቱ ገባና "ኣባቴ ሆይ ባርከኝ"
ኣለው። ሰገደለትም።

www.ethiopianorthodox.org

2 ወአንሥአ ወባረኮ። ወአኀዘ ርእሰ ወይቤ ቡሩክ እግዚአብሔር
አምላኪየ ዘባረኮ ለዳዊት አቡየ ወዘባረኮ ለአቡነ አብርሃም የሀሉ
ምስሌከ በኲሉ ጊዜ። ወይባርክ ዘርዐከ በከመ ባረኮ ለያዕቆብ
ወአብዝኀ ዘርዖ ከመ ኮከበ ሰማይ ወከመ ኆፃ ባሕር ወበከመ ባረኮ
አብርሃም ለይስሐቅ አቡየ። ከማሁ ይኩን በረከትከ እምጠሉ ለሰማይ
ወእምስፍሓ ለምድር ወይትአዘዝ ለከ ኲሉ እንስሳ ወአዕዋፈ ሰማይ
ወአራዊተ ገዳም ወዓሣተ ባሕር።
3 ኩን ምሉአ ወአኮ ንቱገ።
4 ኩን ፍጹመ ወአኮ ሕፁፀ።
5 ኩን የዋሀ ወአኮ ነቢረ።
6 ኩን ጥዑየ ወአኮ ሕሙመ።
7 ኩን ኄረ ወአኮ መስተቀይመ።
8 ኩን ንጹሐ ወአኮ ርሱሐ።
9 ኩን ጻድቀ ወአኮ ኀጥአ።
10 ኩን መሓሬ ወአኮ ዐማፄ።
11 ኩን ብሩሀ ወአኮ ጸዋገ።
12 ኩን መስተዓግሠ ወአኮ ምዑዐ።
13 ወይፍርሁከ ፀር። ወይግርሩ ለከ ጸላእትከ ታሕተ መከየደ እገሪከ።
14 ወትኩን ለከ መርሐ እግዝእትየ ጽዮን ቅድስት ሰማያዊት ታቦተ ሕጉ
ለእግዚአብሔር በኲሉ ጊዜ። ኀበ ኀለይከ በልብከ ወአንጸርከ
በአጻብዒከ።
15 ዘርኁቅ ወዘቅሩብ ለከ።
16 ኀበ ዘትሑት ወዘልዑል ለከ።
17 ኀበ ዘጽኑዕ ወዘድኩም ለከ።
18 ኀበ ዘአፍአ ወዘውስጥ ለከ።
19 ኀበ ዘቤት ወዘገዳም ለከ።
20 ኀበ ዘያስተርኢ ወዘኢያስተርኢ ለከ።
21 ኀበ ዘእቱት ወልጹቅ ለከ።
22 ኀበ ዘኀቡእ ወክሡት ለከ።
23 ኀበ ዘከቡት ወግሁድ ለከ።
24 ትኩንከ መርሐ እግዝእትነ ጽዮን ቅድስት ሰማያዊት ታቦተ ሕጉ
ለእግዚአብሔር ንጽሕት።
25 ወተባረከ ወሰገደ ወሖረ።

## ፱ ኀበ ተፋነዉ ምስለ አቡሁ ወለሐወት ሀገር

1 ወተፋነዉ ወሖሩ ወአቅደሙ ዕኢኖታ ለጽዮን በሌሊት ውስተ ሠረገላ
በኀሡራት ንዋያት ወርሱሐት አልባስ ምስለ ንዋየ ቈሳቍሳት።
2 ወተፅዕኑ ኲሉ ሠረገላት ወተንሥኡ ሊቃናት። ወተነፍሐ ቀርን
ወደምፀት ሀገር ወወውኡ መሐዛት ወከለላ ግርማ ወያዳ ጸጋ
አውየዉ ርሱዓን ወከልሑ ሕፃናት ወበከያ ዕቤራት ወለሓዋ ደናግል
በእንተ ዘተንሥኡ ደቂቀ መኳንንቲሆሙ ለኀያላነ እስራኤል።

- 47 -

2 አንስቶም ባረከው። ራሱንም አንስቶ "አባቴን ዳዊትን፣ አባታችንን
አብርሃምንም የባረከው ብሩክ አምላኬ ሁልጊዜ ከአንተ ጋር
ይሁን። ያእቆብን እንደ ባረከውና ዘሩንም እንደ ሰማይ ኮከብና
እንደ ባህር አሸዋ እንዳበዛው፣ አብርሃምም አባቴን ይስሃቅን
እንደባረከው ዘርህን ይባርከው። በረከትህ እንደ ሰማይ ካፊያና
እንደ ምድር ስፋት ይሁን። እንስሳ ሁሉ የሰማይ ወፎች፣ የዱር
አራዊትና የባህር አሶች ይታዘዙልህ።
3 ሙሉ እንጂ ጎዶሎ አትሁን።
4 ፍፁም እንጂ ከፊል አትሁን።
5 የዋህ እንጂ ክፉ አትሁን።
6 ጤናማ እንጂ ታማሚ አትሁን።
7 ቸር እንጂ ተበቃይ አትሁን።
8 ንፁህ እንጂ ጎስቋላ አትሁን።
9 ፃድቅ እንጂ ሃጥእ አትሁን።
10 ይቅር ባይ እንጂ አመፀኛ አትሁን።
11 መልከ ቀን እንጂ መልከ ክፉ አትሁን።
12 ታጋሽ እንጂ ቁጡ አትሁን።
13 ጠላቶችህ ይፈሩህ። ከእግርህ በታች ይስገዱልህ።
14 ቅድስቲቷና ሰማያዊቷ የእግዚአብሄር ታቦተ ህግ እመቤቴ ፅዮን
በልብህ ባሰብከው በእጅህ በተመለከትከው ሁሉ መሪ ትሁንህ።
15 የሩቁና የቅርቡ የአንተ ይሁን።
16 ዝቅተኛውና ከፍተኛው ያንተ ይሁን።
17 ደካማውና ብርቱው የአንተ ይሁን።
18 የውስጡና የውጬ የአንተ ይሁን።
19 የቤቱና የዱሩ የአንተ ይሁን።
20 የሚታየውና የማይታየው ለአንተ ይሁን።
21 የተወገደውና አንድ የሆነው ለአንተ ይሁን።
22 የተሰወረውና የተከሰተው ለአንተ ይሁን።
23 የተሸሸገውና የተገለፀው ለአንተ ይሁን።
24 ቅድስት ሰማያዊትና ንፅህት የምትሆነው የእግዚአብሄር ታቦተ ህግ
እመቤቴ ፅዮን መሪ ትሁንህ" አለው።
25 ተባረከ፣ ሰግዶም ወጣ።

## ፱ ከአባቱ ጋር እንደተሰነባበቱና አገሪቱ እንዳለቀሰች፣

1 ተሰነባብተውም ሄዱ። ፅዮንንም ከአልባሌ እቃዎች ጋር በቆሻሻ ልብሶች
በሰረገላ ላይ በሌሊት መጫንን አስቀደመ።
2 ሰረገላዎች ሁሉ ተጫኑ። አለቆች ሁሉ ተነሱ። ነጋሪት ተመታ። አገሪቱም
ጮሀች። ጎልማሶችም ደነፉ። ግርማም ጋረዳት። ፀጋም ከበባት።
የእስራኤል ጀግኖችና የመኳንንት ልጆች ስለ ተነሱ ሽማግሎች ዋይ
ዋይ አሉ። ህፃናት ጮሁ። ባልቴቶች አለቀሱ። ደናግሉም አለቀሱ።

www.ethiopianorthodox.org

3 ወአኮ ባሕቲቶሙ በእንቲአሆሙ ዘትበኪ ሀገር አላ እስመ ተሀይደ
ግርማሃ ለሀገር ምስሌሆሙ። ወሶበኒ ኢያእመሩ ገሃደ ከመ ተንሥእት
ጽዮን እምኔሆሙ በልቦሙሰ ኢስሕቱ ወይበክዩ መሪረ ከመ አመ
ቀተለ እግዚአብሔር በኵሮሙ ለግብጽ ከማሁ ኮኑ። ወአልቦ ቤት
ኀበ አልቦ አውያተ እምሰብእ እስከ እንስሳ ከለባትኒ የአወይዉ
ወአእዱግኒ ይነቅዉ ወኵሎሙ ኀቡረ ያውኀዙ አንብዖሙ እለ ተርፉ
ሀየ ከመ ዘዐገትዋ መላእክተ ፀር ጽኑዓን ለዐባይ ሀገር ወሮድዋ
ወማኅረክዋ ወዔውዋ ወቀተልዋ በአፈ ኀፂን ከማሁ ኮነት ሀገረ ጽዮን
ይእቲ ኢየሩሳሌም።
4 ወደንገፀ ንጉሥኒ ሰሎሞን በእንተ ብካይ ወጽርሐ ሀገር ወሐወጸ
እንተ ታዕካ ቤተ መንግሥት ቀልዐ ዘቤተ ንጉሥ። ወርእየ ኵላ
ሀገር እንዘ ትበኪ ትተልዎሙ ከመ ሕፃን ዘአኅደገቶ ጥበ እሙ
ወጉየት እምኔሁ ወይተሉ አሠረ እሙ እንዘ ይጸርሕ ወይበኪ።
ከማሁ ኮኑ ይጸርሑ ወይበክዩ ወይወድዩ ሐመደ ዲበ ርእሶሙ።
ወያውኀዙ አንብዐ እምአዕይንቲሆሙ።
5 ወሰሎሞንሂ ተሀውከ ወርዕደ ሶበ ርእየ ግርማሆሙ ለእለ ሖሩ።
ወተሀውኩ አማዑቲሁ ወአንብዑ ታንጠበጥብ ዲበ ልብሱ። ወይቤ
ሰይ ልየ እስመ ኀለፈት ክብርየ ወወድቀት አክሊለ ምክሕየ።
ወውዕየት ከርሥየ በእንተ ዘሖረ ዝንቱ ወልድየ ወነሠተ ግርማሃ
ለሀገርየ ወግዕዙ ደቂቀ ኀይልየ።
6 ወእምይእዜሰ ኀለፈት ክብርነ ወተሀይደት መንግሥትነ ውስተ ሕዝብ
ነኪር እለ ኢየአምርዎ ለእግዚአብሔር። በከመ ይቤ ነቢይ ሕዝብ
እለ ኢኀሠሡኒ ረከቡኒ።[47]
7 እምይእዜሰ ይትወሀቦሙ ሕግ ወጥበብ ወአእምሮ። ወአቡየኒ ተነበየ
በእንቲአሆሙ እንዘ ይብል
ይገንዩ ቅድሜሁ ኢትዮጵያ
ወጸላእቱሂ ሐመደ ይቀምሑ።[48]
8 ወበካልእኒ ይብል፣
ኢትዮጵያ ትሜጥዎ እደዊሃ ለእግዚአብሔር
ወውእቱኒ ይትሜጠዋ በክብር።
ወነገሥተ ምድርኒ ይሴብሕዎ ለእግዚአብሔር።[49] ወበሣልስኒ ይቤ፣
ወናሁ ኢሎፍሊ ወጤሮስ ወሕዝበ ኢትዮጵያ።[50] እለ ተወልዱ
ዘእንበለ ሕግ ይትወሀቦሙ ሕግ።
ወይብልዋ ለጽዮን እምነ[51] በእንተ ብእሲ ዘተወልደ
በእንተ ዝንቱኑ ወልድየ እንጋ ዘተወልደ እምኔየ።

---

[47] ኢሳ.65፡1
[48] መዝ.72፡9
[49] መዝ. 87፡5
[50] መዝ.87፡4
[51] መዝ.87፡5፡51፡16

- 48 -

3 በእነሱ ምክንያት ግርማዋ ስለተወሰደባት እንጂ አገሪቱም
የምትላቀሰው ስለ እነሱ ብቻ አይደለም። ፅዮን ከእነሱ እንደ
ተወሰደች በግልፅ ባያውቁም በልባቸው አልሳቱትም ነበርና
እግዚአብሄር የግብፅን የበኩር ልጆች በገደለ ጊዜ እንደ ነበረው
አይነት መሪር ልቅሶ አለቀሱ። ከሰው እስከ እንስሳት ልቅሶ
ያልነበረበት አልነበረም። ውሾች ተፋጁ። አህዮችም ጮሁ። እዚያ
የቀሩት ብርቱዎች ሁሉ እንባቸውን አፈሰሱ። የጠላት ሰራዊቶች
እንደ ከበቧትና አደጋ እንደጣሉባት፣ ፈፅመውም እንደማረኳት፣
በጦር መሳሪያም እንዳጠፏት አንዲት ታላቅ አገር ፅዮን
ኢየሩሳሌምም እንደዚሁ ሆነች ።
4 ንጉሱም ሰሎሞን ስለ ልቅሶውና ስለ አገሪቱ ጩሀት ደነገጠ።
የታላቁን ቤተ መንግስተት አዳራሽ የንጉሱን ክፍል መጋረጃ ከፍቶ
አገሩ በሙሉ እነሱን እየተከተለ የእናቱን ጡት እንዳስተውትና
ከእሱ የሄደችውን እናቱን ተከትሎ እንደ ሚጮህና እንደሚያለቅስ
ህፃን ሲያለቅስ ተመለከተ። ሲያለቅሱም በራሳቸው ላይ አመድ
ይነሰንሱና ከአይኖቻቸውም እንባቸውን ያፈሱ ነበር።
5 ሰሎሞንም የሄዱትን ግርማቸውን ባየ ጊዜ ደንግጦ ተንቀጠቀጠ።
አንጀቶቹ ታወኩ። እንባውም በልብሱ ላይ ትንጠባጠብ ነበር።
እሱም ይህ ልጅ በመሄዱ የአገሩን ግርማ ስላፈረሰ፣ የበኩር
ልጆቹን ይዞ ስለ ተንቀሳቀሰ፣ " ክብሬ አልፋለች፣ የመመኪያ
ዘውደም ወድቃለች፣ ሆደም ተቃጥላለችና ወዮልኝ።" አለ።
6 "እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ክብራችን አለፈች። ነቢዩ እንዳለው
መንግስታችን እግዚአብሄርን ለማያውቅ ለሌላ ህዝብ ተሰጠች።[47]
7 ከእንግዲህ ጥበብና እውቀት ይሰጣቸዋል። አባቴም 'በፊቱ
ኢትዮጵያውያን ይሰግዳሉ ጠላቶቹም አመድ ይቅማሉ'[48] ሲል ስለ
እነሱ ተናገረ።
8 በሌላ ቦታም 'ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሄር ትዘረጋለች።
እሱም በክብር ይቀበላታል። የምድር ነገስታትም እግዚአብሄርን
ያመሰግኑታል።'[49] ይላል። በሦስተኛውም 'እነሆ ያለ ሕግ የተወለዱ
ኢሎፍሊ፣ ጢሮስና የኢትዮጵያ ህዝብም።[50] ሕግም ይሰጣቸዋል'"
አለ። ደግሞም 'ስለ ተወለደው ሰው ፅዮንን እናታችን'[51] ይሏታል
ይላል። ይህስ ከእኔ ስለ ተወለደው ስለዚህ ልጅ ይሆን? እንጃ"
አለ።

---

[47] ኢሳ.65፡1
[48] መዝ.72፡9
[49] መዝ.87፡5
[50] መዝ.87፡4
[51] መዝ.87፡5፡51፡16

www.ethiopianorthodox.org

## ፶ወ፩ ኀበ ዘይቤሎ ለሳዶቅ ካህን ሑር ወአምጽእ ውእተ ልብሰ ዘላዕሌሃ።

1 ወይቤሎ ለሳዶቅ ካህን ሑር አምጽእ ውእተ ልብሰ ዘላዕሌሃ ለጽዮን
ወንሣእ ለከ ዘንተ ልብሰ ዘይኄይስ እምኔሁ ወአልብሳ መልዕልተ ፪
ዘታሕቴሃ።
2 ወውእቱ ልብሳ ዘዐስቅ ወርቀ ቈፋዝ። ዝብጠ ወእኑም በስሕቦ።
ወአኮ ዘፍትሎ ዘሜላት ወ፭ እሞፃሃ[52] ለጽዮን አናጹት ወ፲ አምሳለ
ንፍስቶሙ ዘገብሩ ቤዛሆሙ መኳንንተ ኢሎፍሊ። ወእምጸናጽል
አምሳለ ወርቅ ዘወፅአ እምድረ ቃዴስ ዘተአዘዘ ለሙሴ በሲና ከመ
ይግበር ጸናጽለ ውስተ ልብሰ አሮን እኁሁ። ወአስተጋብአን ውስተ
ልብሳ ለጽዮን። ወሰድ ሎቱ ለወልድየ ዳዊት እስመ ትቤ እሙ
በመልእክተ ታምሪን ገብራ ሀበነአ እምዘፈረ ልብሳ ለጽዮን ከመ
ናምልክ ኪያሃ ንሕነ ወእለ እምታሕቴነ ወኵሉ መንግሥትነ።
ወይእዜኒ ሀቦ ወበሎ አምልካ ለዛቲ ልብሰ ጽዮን። እስመ ለአከት
እምከ በእንተዝ። ወለሊከኒ ትቤ ሀበነ ዘናመልክ እምዘፈረ ልብሳ
ከመ ኢናምልክ ባዕደ ከመ አሕዛብ። ወጽዮንሂ ታቦተ ሕጉ
ለእግዚአብሔር ትኩንከ መርሐ በኀበ ሀለውከ።
3 ወለነሰ ሀለወት ወትረ ኀቤነ። ወኢናስተጠናቅቅ አክብሮታ። ወአንትሙሰ
እንዘ ኢሀለወት ኀቤክሙ ታከብርዋ በአስተጠናቅቆ።
4 እስመ ይቤሎ እግዚአብሔር ለዔሊ ካህን በአፈ ሳሙኤል ነቢይ አነ
ፈቀድኩ ከመ ትንበሩ አንተ ወቤተ አቡከ ከመ ትዕጥኑ ታቦተ
ሕግየ ወትንበሩ ቅድሜሃ እስከ ለዓለም።
5 ወይእዜሰ ተነሳሕኩ እመይጥ ገጽየ እምኔከ። እስመ ተዐውሮ
ተዐወርከ ላዕለ መሥዋዕትየ። ወአፍቀርከ ደቂቀከ እምኔየ። ወይእዜሰ
ለዘአክበረኒ አከብሮ ወለዘአስተሐቀረኒ አስተሐቅሮ ወእስዕር ኵሎ
ዘርዐከ።[53] ወዘንተ ዘይቤ በእንተ ዘአስተሐቀርዎ ሌዋውያን።
6 ወበሎ ንሣእ ዘንተ ልብሳ ለጽዮን ወዘንተኒ ሞፃ ይኩኖ ህየንቴሃ
ለጽዮን። ወአንብሮ ውስተ ደብተራከ።
7 ወሶበኒ ትምሕል ወታምሕል መሐላ አምሕል ባቲ ከመ ኢትዝክር
አስማተ ባዕድ አማልክተ አሕዛብ።
8 ወሶበኒ ትሠውዕ አንጺረከ ለኀቤነ ሠውዕ ለኢየሩሳሌም ወለጽዮን
ቅድስት።
9 ወሶበኒ ትጼሊ አንጺረከ ለኢየሩሳሌም ለኀቤነ ጸሊ።

1ሳሙ.6፥4
1ሳሙ.2፥29-34

- 49 -

## ፶፩ ካህኑን ሳዶቅን ሂድና በላዩዋ ላይ ያለውን ልብስ አምጣ እንዳለው

1 ካህኑ ሳዶቅን "ሂድና በፅዮን ላይ ያለውን ልብስ አምጣ። ከዚህም
የተሻለ ልብስ ውሰድና ደራርበህ አልብሳት" አለው።
2 ይህም ልብስ የተዥጎረጎረ ቈፋዝና ዝብጦ ከተባለ ወርቅ ተጠልፎ
የተሰራ እንጂ ከሃር የተፈተለ አይደለም። ለፅዮን ካሳ እንዲሆኑ
የኢሎፍሊ መኳንንት አለቆች በአምስት አይጦችና[52] በሌሎችም
አስር ነፍሳት አምሳል ያሰሩአቸው ሙሴ በወንድሙ በአሮን ልብስ
ፀናፅል እንዲያደርግ በሲና በታዘዘው መሰረት ከምድረ ቃዴስ
በወጣ ወርቅ አምሳል ተዘምዝሞ የተሰራ ልብስ ነው። በፅዮን
ልብስ ውስጥ ሰብስባቸው። እናቱ በአገልጋይዋ በታምሪን መላክተኛ
ነት 'እኛና ከእኛ በታች ያሉት፣ እንዲሁም መንግስታችን
እናመልክባት ዘንድ ከፅዮን ልብስ ጫፍ ስጠን' ባለችው መሰረት
ለልጄ ለዳዊት ውሰድለት። ስጥተህም ይህችን የፅዮንን ልብስ
አምልክበት። እናትህ ስለዚህ ልካለችና።
3 አንተም ደግሞ 'የምናመልክበት ከልብሷ ጫፍ ስጠን ብለሃልና'
በለው። ለአንተ የእግዚአብሐር ታቦተ ሕግ ባለህበት መሪ ትሁንህ።
ለእኛ ግን ሁልጊዜ ከእኛ ዘንድ አለች። ማክበሯንም አንጠነቀቅም።
እናንተስ በውስጣችሁ ሳትኖር በጥንቃቄ ታከብሯታላችሁ።
4 'እግዚአብሄር ካህኑ ኤሊን በነቢዩ በሳሙኤል አፍ አንተና የአባትህ
ቤት የህጌን ታቦት ታጥኑ ዘንድ በፊቱ ለዘላለም እንድትኖሩ
ፈቀድኩ" አለው።
5 "በመስዋእቴ ላይ መታወርን ታውረሃልና ከእኔም ይልቅ ልጆችህን
ወደሃልና እነሆ ፊቴን ከአንተ እመልስ ዘንድ ተፀፀትኩ። አሁንም
ያከበረኝን አከብረዋለሁ። ያቃለለኝንም አቃልለዋለሁና ዘርህን ሁሉ
እሽረዋለሁ።'[53] አለ። ይህንም ያለ ሌዋውያን ስለ አቃለሉት ነው።
6 "እነሆ የፅዮንን ልብስና ሞጣህት ውሰድ። በፅዮንም ፈንታ
ይሁንልህ። በድንኳንህ አስቀምጠው።
7 ስትምልና ስታስምል የአህዛብን አማልክት ስም እንዳትጠራ
አስምልባት ።
8 ስትሰዋም ወደ እኛ ዙረህ ወደ ቅድስት ፅዮን ኢየሩሳሌም አንፃር
ሰዋ።
9 ስትፀልይም ወደ ኢየሩሳሌም ዙረህ ፀልይ። ለእኛም ፀልይ። "

[52]1 ሳሙ.6፥4
[53] 1 ሳሙ.2፥29-30

www.ethiopianorthodox.org

## ፶ወ፪ ኀበ ዘሖረ ሳዶቅ ካህን

1 ወሖረ ሳዶቅ ካህን ወወሀቦ ልብሳ ለጽዮን ወአዘዘ ኵሉ ዘነገሮ ሰሎሞን።
2 ወተፈሥሐ ዳዊት ወልደ ሰሎሞን በእንተዝ። ወአንከረ ወአስተብዕዐ ፈድፋደ ወይቤ ዛቲ ትኩነኒ እግዝእትየ በተአምኖታ ለታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር።
3 ወአውሥአ አዛርያስ ወይቤ በቅድመ አቡሁ ተፈሣሕከ በልብስ? ወእፎ ፈድፋደ እምተፈሣሕከ በእግዝእተ ልብስ?።
4 ወይቤሎ አቡሁ በአማን እምተፈሥሐ በእግዝእተ ልብስ ወእምቀነየነ ለኵልነ ሶበ ኢየሐውር ብሔሮ።
5 ወይቤሎ ለንጉሥ ሀበኒኬ ኪዳነ ከመ ተሀቦ ለዝንቱ ወልድየ ዘንተ ንዋየ እግዝእቱ ለትሕቢቱ* ወምዕቅብናሁ ከመ ይትመሐፀን ኵሉ መዋዕለ ሕይወቱ ሎቱ ወለዘርዑ እምድኅሬሆሙ። ወዐሥራትኒ ከመ ተሀቦ ወሀገረ ምስካይኒ ከመ የሀቦ በውስተ መንግሥትከ ወለዐሥራተ አህጉርኒ በኵሉ መንግሥቱ።ወውእቱኒ ከመ ይኩንከ ካህነ ወራእየ ወነቢየ ወመሃሬ ለከ ወለዘርዕከ እምድኅሬከ ወቀባዔ ቅብዐ መንግሥትኒ ለደቂቅከ ወለደቂቀ ደቂቅከ።
6 ወይቤ እሆ። ወተካየዱ ወነሥአ እምኀበ አቡሁ ሞፃ ወልብሳ ለጽዮን ወቃማ ዘወርቅ።
7 ወፀዐኑ ከመ ይሑሩ ሰረገላተ ወአፍራሰ ወአብቅልተ ወተሠርሐ ፍኖቶሙ።
8 ወእምዝ አርትዑ ሐዊረ እንዘ ሚካኤል መልአክ የሐውር ቅድመ። በባሕርኒ ሰፊሖ አኬዶሙ ከመ የብስ። ወበየብስኒ ሠጢቆ ደመና አንጦሊዖ ሰወሮሙ ላህበ ፀሐይ።
9 ሰረገላቲሆሙ አልቦ ዘይስሕቦ አላ የሐውር ለሊሁ በሠረገላ ተልዒሎ እምድር መጠነ እመት። እመሂ ሰብእ ወእመሂ አፍራስ ወእመሂ አብቅልት ወእመሂ ራኩባት ወኵሎሙ እለ ፅዑናን ይትሌዐል እምዘባናቲሆሙ መጠነ ስዝረ ብእሲ ኵሉ ንዋየ ቀሳቀሶሙ ዘፅዑን።
10 ወእለ ይጼዐኑ ይትሌዐሉ መጠነ ስዝረ ብእሲ። ወእንስሳኒ ይትሌዐሉ መጠነ ስዝረ ብእሲ። ወኵሉ ይረውጹ በሰረገላ ከመ ሖመር በውስተ ባሕር ሶበ ያነውኃ ነፋስ ወከመ ጥንግ በውስተ አየር ሶበ ያሠርሖ ፍትወተ ክርሡ ለበሊዕ እምአብያጺሁ ወከመ ንስር ሶበ ያቀልል ሥጋሁ በመልዕልተ ነፋስ ከማሁ ይረውጹ በሰረገላ ዘአልቦ ቅድመ ወድኅረ ዘእንበለ ተሀውኮ ይምነ ወጸግመ።

## ፶ወ፫ ኀበ ተውህባ ሰረገላ ለኢትዮጵያ

ወበኀበ ኀደሩስ ጋዛ ይእቲ ሀገረ እሙ ለንጉሥ ዘወሀባ ሶበ ትመጽእ ኀቤሁ ንጉሥ ሰሎሞን ለንግሥተ ኢትዮጵያ። ወእምሀየ

---

ለትንቢቱም ይላል።

## ፶፪ ካህኑ ሳዶቅ እንደ ሄደ

1 ካሁኑ ሳዶቅም ሄደ። የፅዮንንም ልብስ ሰጠው። ሰሎሞን የነገረውን ሁሉ አዘዘው።
2 የሰሎሞን ልጅ ዳዊት ስለዚህ ተደሰተ። እጅግም አደነቀ። የእግዚአብሄርን ታቦተ ሕግ በማመን "ይህች እመቤቴ ትሁን" አለ።
3 አዛርያስም በአባቱ ፊት "በልብሱ ተደሰትክ? ይልቁንስ በልብሱ እመቤት እንዴት በተደሰትክ?" አለው።
4 አባቱም "በእውነት በልብሱ እመቤት ይበልጥ በተደሰተ፤ ለሁላችንም በተገዛ፤ አገሩም ባልሄደ" አለው።
5 እንደገናም ንጉሱን "ለዚህ ለልጄ ለትንቢቱና ለአደራው በዘመኑ ሁሉ ለእሱና ከእሱ በሁዋላም ለዘሩ ይማፀንባት ዘንድ ይህንን የእመቤቴን እቃ ትሰጠው ዘንድና አስራትና በመንግስትህም ውስጥ ጉልት ትሰጠው ዘንድ ቃል ኪዳን ግባልኝ" አለው። "ለአንተና ከአንተም በሁዋላ ለዘርህ ካህን፣ ባለራእይ፣ ነቢይ፣ መምህርና ለልጅህና ለልጅ ልጆችህም ቅብአ መንግስት የሚቀባ ይሆን ዘንድ።
6 እሱም "እሺ" አለ። ቃል ኪዳንም ገቡ። ከአባቱም ሞጣህቷንና የፅዮንን ልብስ፣ የወርቅ ሽልማቱንና የአንገት ዶቃን ተቀበለ።"
7 ይሄዱም ዘንድ ሰረገላዎችን፣ ፈረሶችንና በቅሎዎችን ጫኑ። መንገዳቸውም ተዘጋጀ።
8 ከዚህም በሁዋላ መላኩ ሚካኤል በፊታቸው እየሄደ መንገዳቸውን ጀመሩ።በባህሩም ላይ ክንፉን ዘርግቶ እንደ የብስ አድርጎ አስኬዳቸው። በየብሱም ደመናውን ሰንጥቆና ከፀሃይ ትኩሳት ጋርዶ ሰወራቸው።
9 ሰረገላቸውንም የሚስበው አልነበረም። እራሱ ከምድር አንድ ክንድ ያህል ከፍ ብሎ በሰረገላ ይሄዳል እንጂ። ሰዎችም ቢሆኑ፣ ፈረሶችም ቢሆኑ፣ በቅሎዎችም ቢሆኑ፣ የግመል ባዝራዎችም ቢሆኑ፣ ከተጫኑትም ሁሉ አንድ ስንዝር ያህል ከፍ ይሉ ነበር።
10 የተጫነው ማናቸውም ቁሳቁስና የሚጫነውም ሁሉ የሰው ስንዝር ያህል ከፍ ይሉ ነበር። እንስሳትም የሰው ስንዝር ያህል ከፍ ይሉ ነበር። ሁሉም በባህር ውስጥ ነፋስ እንደሚያናውጣት ጀልባና ከጓደኞቹ ይልቅ የሆዱ ፍላጎት ወደ መብል እንደሚያጣድፈው ወፍና ስጋውን በነፋስ ላይ እንደሚያቀል ንስር እንደዚሁ ፊትና ሁዋላ እና ግራና ቀኝ በማይሉ ሰረገላዎች ባለመታወክ ይሮጡ ነበር።

## ፶፫ ለኢትዮጵያ ሰረገላ እንደ ተሰጠ፣

1 ያደሩባት ጋዛ ንጉሱ ሰሎሞን ወደ እሱ ስትመጣ ለኢትዮጵያ ንግስት የሰጣት የንጉሱ እናት አገር ነበር። ከዚያም ምስሪን ከተባለው የግብፅ አገር በአንድ ቀን ደረሱ። የእስራኤል ሃያላንም ልጆች የአስራ ሶስት ቀናትን መንገድ በአንድ ቀን እንደ ደረሱ

www.ethiopianorthodox.org

በጽሑ በአሐቲ ዕለት ውስተ ደወለ ግብጽ እንተ ስማ ምስሪን።
ወሶበ ርእዩ ደቂቀ ኀያላነ እስራኤል ከመ በአሐቲ ዕለት በጽሑ
ምሕዋረ ፲ወ፫ ዕለት ወኢደከሙ ወኢርኀቡ ወኢጸምኡ ኢሰብእ
ወኢእንስሳ ወኵሎሙ ከመ ዘሶቤ ጸግቡ ወሰትዩ አእመሩ ወአምኑ
እሙንቱ ደቂቀ ኃይል ከመ እምኀበ እግዚአብሔር ኮነት ዛቲ።
2 ወይቤልዎ ለንጉሦሙ ናወርድ ሰረገላተ እስመ በጸሕነ ማየ
ኢትዮጵያ። ዛቲ ይእቲ ተከዚ እንተ ትወርድ እምኢትዮጵያ ወትሰቅ
ፈለገ ግብጽ።
3 ወአውረዱ ሠረገላቲሆሙ ህየ። ወተከሉ ደባትሪሆሙ። ወሖሩ ኀቡረ
ደቂቀ ኀይል። ወሰደዱ ኵሎ አሕዛበ።
4 ወይቤልዎ ለንጉሦሙ ንንግርከኑ ነገረ ለእመ ትክል ተዐግሦ።
5 ወይቤሎሙ እወ እክል። ወለእመ ትቤሉኒ እስከ ዕለተ ሞትየ
ኢያወፅእ ወኢያወሥእ።
6 ወይቤልዎ ወረደት ፀሐይ እምሰማይ። ወተውህበት በሲና
ለእስራኤል። ወኮነት መድኀኒት ለዘመደ አዳም እምነ ሙሴ እስከ
ዘርዐ ዕሤይ። ወነዋ ኀቤከ በፈቃደ እግዚአብሔር። ወአኮ እምኀቤነ
ዘተገብረ ዝንቱ አላ በፈቃደ ኬንያሃ ወገባሪሃ ኮነ ከመዝ። ንሕነ
ፈቅድነ ወእግዚአብሔር ፈጸመ። ንሕነ ተሰነዐውነ ወእግዚአብሔር
አሠነየ። ንሕነ ተናገርነ ወእግዚአብሔር ገብረ። ንሕነ ኀለይነ
ወእግዚአብሔር መከረ። ንሕነ ንቤ ወእግዚአብሔር ሠምረ። ንሕነ
አንፀርነ ወእግዚአብሔር አርትዐ። ንሕነ ኀለይነ ወእግዚአብሔር
አጽደቀ።
7 ወይእዜኒ ኪያከ ኀረየ እግዚአብሔር ወሀገረከ። ሠምረ ከመ ትኩን
ላእከ ለጽዮን ቅድስት ሰማያዊት ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር።
8 ወይእቲ ትኩንከ መርሐ እስከ ለዓለም ለከ ወለዘርዕከ እምድኅሬከ
ለእመ ዐቀብከ ትእዛዞ ወገበርከ ፈቃዶ ለእግዚአብሔር አምላክከ።
እስመ ኢትክል አንተ አግብእታ ለእመ ፈቀድከ ወአቡከ ነሢኦታ
ለእመ ፈቀደ።
9 እስመ ለሊሃ ተሐውር ኀበ ፈቀደት። ወኢትትነሣእ እመንበራ ለእመ
ኢፈቀደት ለሊሃ። ወነያ ይእቲ እግዝእትነ እምነ ወመድኀኒትነ
ፀወንነ ወምስካይነ ክብርነ ወመርሶ መድኀኒትነ ለእለ ናሰምክ ባቲ።
10 ወቀጸቦ አዛርያስ ለኤልምያስ ወይቤሎ ሑር አሠንያ ወአልብሳ
ለእግዝእትነ ከመ ይርአያ ንጉሥነ።
11 ወዘንተ ሶበ ተናገረ አዛርያስ ደንገፀ ንጉሥ ዳዊት ወአንበረ
ክልኤሆን እደዊሁ ውስተ ልቡ። ወአስተንፈሰ ሠለስተ እስትንፋሰ።
ወይቤ አማንኑ እግዚኦ ትዜከረነ በሣህልከ ለግዱፋን እለ መነንከ
ሕዝብ ከመ እርአያ ለማኅደርከ ንጽሕት እንተ በሰማያት ጽዮን
ቅድስት ሰማያዊት። ወምንትኑ ነዐሥዮ ለእግዚአብሔር በእንተ ኵሉ
ዘገብረ ለነ ሠናያተ ከመ ወኢምንትኒ በኀቤሁ ክብረ ወስብሐተ
ከለለነ በጸጋሁ ከመ ናእምር በምድር ስብሐቲሁ ወንግነይ ኵልነ
ለዕበየ ዚአሁ።

- 51 -

እንዳልደከሙና እንዳልተጠሙ፣ ሰዎቹም ቢሆኑ፣ እንስሳቱም ቢሆኑ፣
ሁሉም እንደጠገቡና እንደ ጠጡ ሆነው ባዩ ጊዜ እነዚህ የሃይል
ልጆች እንደሆኑና ይህች ከእግዚአብሄር ዘንድ እንድሆነች አወቁ።
ንጉሳቸውንም "ሰረገላችንን እናውርድ። ከኢትዮጵያ ወንዝ ደርሰ
2 ናልና። ይህች ከኢትዮጵያ እየወረደች የግብጽን ወንዝ የምታጠጣ
ተከዜ ናት" አሉት።
ሰረገላቸውንም አወረዱ። ድንኳኖቻቸውንም ተከሉ። ወታደሮችም
3 በህብረት አህዛብንም ሁሉ ሰደዱ።
ንጉሳቸውንም "መታገስ ትችል እንደሁን ምስጢር እንንገርህ?" አሉት።
4 እሱም "አዎ እችላለሁ። እስከ እለተ ሞቴም አላወጣም።
5 አልናገርምም" አላቸው።
እነሱም "ፀሃይ ከሰማይ ወረደች። በሲናም ለእስራኤል ተሰጠች።
6 ከሙሴ እስከ እሴይ ዘር ድረስ ለአዳም ዘር ሁሉ መድሃኒት
ሆነች። እነሆ በእግዚአብሄር ፈቃድ በአንተ ዘንድ ናት። ይህም
በእግዚአብሄር ፈቃድ እንጂ ከእኛ የተደረገ አይደለም። በጥበበኛዋና
በሰሪዋ ፈቃድ እንደዚህ ሆነ እንጂ ከእኛ የተደረገ አይደለም። እኛ
ፈቀድን። እግዚአብሄር ፈፀመ። እኛ ተስማማን። ግዚአብሄር
አሳመረልን። እኛ ተናገርን። እግዚአብሄር ሰራ። እኛ አሰብን
እግዚአብሄር መከረ። እኛ አልን። እግዚአብሄር ወደደ። እኛ
አመለከትን። እግዚአብሄር አቀናው። እኛ አሰብን እግዚአብሄር ግን
እውነት አደረገው።
እነሆ ዛሬም እግዚአብሄር አንተን መረጠ። አገርህንም ወደደ።
7 ይሄውም ለእግዚአብሄር ታቦተ ሕግ ለቅድስቲቱና ለሰማያዊቷ ፅዮን
አገልጋይ ትሆን ዘንድ ነው።
የአምላክህን የእግዚአብሄርን ፈቃዱን ብታደርግ፣ ትእዛዙን
8 ብትጠብቅ እሷ እስከ ዘላለም ለአንተና ከአንተም በህዋላ ለዘርህ
መሪ ትሁንህ። አንተም ብትሻ እሷ ለመመለስ አትችልም።
አባትህም ቢሻ ሊወስዳት አይችልም።
እሷ እራሷ ወደምትሻበት ትሄዳለችና። ካልወደደችም ከመንበሯ
9 አትነሳም። እነሆ እሷ የምንማጠንባት እናታችንና መድሃኒታችን፣
መጠጊያችንና መማጠኛችን፣ ክብራችንና የመድሃኒታችን መልህቅ
ናት" አሉት።
አዛርያስም ኤልምያኖስን ጠቀሰውና "ንጉሳችን ያያት ዘንድ
10 እመቤታችንን አሳምራት፣ አልብሳትም" አለው።
አዛርያስም ይህን በተናገረ ጊዜ ንጉስ ዳዊት ደነገጠ። ሁለቱን
11 እጆቹን በልቡ ላይ አስቀመጠ። ሶስት ጊዜም ተነፈሰ። "በሰማይ
የምትኖር ንፅህት ቤት ማለትም ቅድስቲቱና ሰማያዊቷ ፅዮንን አይ
ዘንድ እኛን የተጠላንና የተናቅን ሕዝቦችህን በውነት በቸርነትህ
ታስበናለህ? እግዚአብሄር ስለ ሰራልን መልካም ስራ ሁሉ ምን
እንከፍለዋለን? በምድር ምስጋናውን እናውቅና ለልእልናውም እንሰ
ግድ ዘንድ በእሱ ዘንድ ኢምንት ሳለን በፀጋው ክብርና ምስጋናን

www.ethiopianorthodox.org

እስመ ኄር ውእቱ ለኀሩያኒሁ። ወሎቱ ስብሐት እስከ ለዓለም።
12 ወተንሥአ ንጉሥ እንዘ ያንፈርዕፅ ከመ
ሐርጌ ጽጉበ ሐሊበ እሙ በከመ ፍሥሓ ዳዊት አበ አቡሁ በቅድመ
ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር። አጽሐሰ በእገሪሁ። ወተሐሥየ በልቡ።
ወተሀለለ በአፉሁ።
13 ወምንተ እብል ሚ መጠን ፍሥሓ ወሐሤት በውስተ ትዕይንተ
ንጉሠ ኢትዮጵያ። ይነግሮ ፩ ለካልኡ። ወያንፈርዕፁ ኵሎሙ ከመ
ጣዕዋ ላህም። ወይጠፍሑ እደዊሆሙ ወያነክሩ። ወይሰፍሑ
እደዊሆሙ ውስተ ሰማይ። ወይሰግዱ በገጾሙ ውስተ ምድር።
ወየአኵትዎ ለእግዚአብሔር በአልባቢሆሙ።

## ፶ወ፩ ኀበ ተነበየ ዳዊት ወተሳለማ ለጽዮን

1 ወቦአ ንጉሥ ወቆመ ቅድሜሃ ወተሳለማ ወሰገደ ላቲ ወይቤ እግዚአ
አምላከ እስራኤል ለከ ስብሐት እስመ ትገብር ፈቃደከ ወአኮ
ፈቃደ ሰብእ ታረስዮ ጥበቦ ለጠቢብ ወተኀብጾ ምክረ ለመካሪ
ወትሜጥቆ ለነዳይ እምነ ሠርም ወታቃውሞ ውስተ ኵኵሕ ጽኑዕ
ለሰኰናሁ እስመ ጽዋዐ ክብር ምሉዕ ውስተ እዴከ ለእለ ያፈቅሩከ
ወጽዋዐ ኀሣርኒ ምሉእ ለእለ ይጸልኡ ኪያከ።
2 ወለነሰ መድኀኒትነ ይወጽእ እምጽዮን ወየአትት ኀጢአተ እምሕዝቡ
ወይትከዐው ሠናይት ወምሕረት ውስተ ኵሉ ዓለም እስመ ንሕነሂ
ተግባረ እደዊሁ ንሕነ። መኑ ይትዔየሮ ለእመ አፍቀረነ ከመ
እስራኤል ሕዝቡ ወመኑ ይገዕዞ ለእመ አዕረገነ ውስተ ሰማያት
መንበሩ እስመ ሞት ወሕይወት እምኀቤሁ። ክብር ወኀሣር ውስተ
እዴሁ። ይክል ቀሢፈ ወያበዝኀ ተሣህሎ ይትመዐዕ ወያበዝኀ
ምሕረቶ እስመ ፈታኄ ልብ ወኵልያት ውእቱ። ይሁብ ወይነሥእ።
ይተክል ወይምሕዉ። የሐንጽ ወይነሥት። ያሜኒ ወይመቀኵ እስመ
ኵሉ ሎቱ ወኵሉ እምኀቤሁ ወኵሉ ቦቱ ኮነ።[54]
3 ወአንቲኒ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር መድኃኒተ ኩኒ።
4 ኀበ ተሐውሪ ወእምኀበኒ ወፃእኪ መድኀኒተ ኩኒ።
5 በቤትኒ ወበገዳምኒ መድኀኒተ ኩኒ።
6 በዝየኒ ወበከሐከኒ መድኀኒተ ኩኒ።
7 በታዕካኒ ወበፅሙናኒ መድኀኒተ ኩኒ።
8 በባሕርኒ ወበየብስኒ መድኀኒተ ኩኒ።
9 በአድባርኒ ወበአውግርኒ መድኀኒተ ኩኒ።
10 በሰማያትኒ ወበምድርኒ መድኀኒተ ኩኒ።
11 በምድናዓትኒ ወበቀላያት መድኀኒተ ኩኒ።
12 በሞትኒ ወበሕይወትኒ መድኀኒተ ኩኒ።
13 በበአትኪ ወበፀአትኪ መድኀኒተ ኩኒ።

[54] ዮሃ.1፥1



ኣለበሰን። ለምርጦቹ ቸር ነውና። እስከ ዘላለሙ ምስጋና ለእሱ
ይሁን" አለ።
12 ንጉሱም ኣያቱ ዳዊት በእግዚኣብሄር ታቦተ ሕግ ፊት እንደ
ተደሰተ፤ እንደ በግ ግልገልና የእናቱን ጡት እንደ ጠገበ ጥጃ
እየዘለለ ተነሳ። በእግሩ ኣሸበሸበ፤ በልቡ ተደሰተ፤ በአፉም እልል ኣለ።
13 በኢትዮጵያ ንጉስ ከተማ ምን ያህል ደስታ እንደ ነበር ምን
እላለሁ? ኣንዱ ለሌላው ይነግረዋል። ሁሉም እንደ ላም ጥጃ
ይዘላሉ። እጃቸውን ያጨበጭባሉ። ያደንቃሉ። እጃቸውንም ወደ ሰ
ማይ ይዘረጋሉ። በፊታቸውም ተደፍተው ይሰግዳሉ። በልባቸውም
እግዚኣብሄርን ያመሰግኑታል።

## ፶፩ ዳዊት ትንቢት እንደ ተናገረና ፅዮንን እንደተሳለማት

1 ንጉሱም ገብቶ ከፊቷ ቆሞ ተሳለማት፤ ሰገደላትም። "ኣቤቱ
የእስራኤል ኣምላክ ሆይ! የራስክን ፈቃድ እንጂ የሰውን ፈቃድ
ኣታደርግምና ለኣንተ ምስጋና ይገባል። ጥበበኛውን ጥበቡን
ታስረሳዋለህ። መካሪውንም ምክር ትሸሽግበታለህ። ችግረኛውን ከማጥ
ታወጣዋለህ። የእግሩንም ሰኮናዎች በፀና ኣለት ላይ ታቆማቸዋለህ።
ኣንተን ለሚወዱህ የክብር ፅዋ፤ ለሚጠሉህም የሃሳር ፅዋ በእጅህ ምሉ
ነውና።
2 ለእኛስ መድሃኒታችን ከፅዮን ይወጣል። ሃጢያትንም ከህዝቡ
ያስወግዳል። በዓለም ሁሉ በጎነት ይፈሳል። እኛም ደግሞ የእጁ
ስራዎች ነንና እንደ ህዝቡ እንደ እስራኤልም ከወደደን ማን
ይነቅፈዋል? ወደ ሰማያት ማለትም መቀመጫው ቢያወጣንስ ማን
ይከለክለዋል? ሞትና ህይወት ከእሱ ዘንድ ናቸው። ክብርና ሃሳርም
በእጁ ናቸው። መቅሰፍን ይችላል። ይቅርታውንም ያበዛል።
ይቆጣል። ምህረቱንም ያበዛል። ኩላሊትን ይመረምራል። ይሰጣል፤
ይነሳል። ይተክላል፤ ይነቅላል። ይሠራል፤ ያፈርሳል። ያሳምራል፤
ያበላሻል። ሁሉ የእሱ ነው፤ ሁሉም በእሱና ከእሱ ሆነ።[54]
3 ኣንቺ የእግዚኣብሄር ታቦተ ሕግ ሆይ መድሃኒት ሁኚ።
4 ለምትሄጅበትና ለወጣሽበት መድሃኒት ሁኚ ።
5 በቤትም በዱርም መድሃኒት ሁኚ።
6 በዚህም በዚያም መድሃኒት ሁኚ።
7 በቤተ መንግስትም በገዳምም መድሃኒት ሁኚ።
8 በየብስም በባህርም መድሃኒት ሁኚ።
9 በተራራና በኮረብታም መድሃኒት ሁኚ።
10 በሰማይም በምድርም መድሃኒት ሁኚ።
11 በታላቁ ምንጮችም በወንዞችም መድሃኒት ሁኚ።
12 በሞትም በህይወትም መድሃኒት ሁኚ።
13 በመግባትሽ በመውጣትሽ መድሃኒት ሁኚ።

[54] ዮሃ.1፥1

www.ethiopianorthodox.org

14 ለደቂቅነሂ ወለነገደ ሕዝብኪ መድኀኒተ ኩኒ።
15 ለበሐውርትኪ ወለአህጉርኒ መድኒተ ኩኒ።
16 ለነገሥት ወለመኳንንት መድኀኒተ ኩኒ።
17 ለአትክልት ወለፍሬያት መድኀኒተ ኩኒ።
18 ለሰብእኒ ወለእንስሳ መድኀኒተ ኩኒ።
19 ለአዕዋፍኒ ወለአራዊት መድኀኒተ ኩኒ።
20 ለሐመልማልኒ ወለጽጌያት መድኀኒተ ኩኒ።
21 ጸልዩ ወመሐሪ መሐኪ ሕዝበኪ።
22 ኩንነ ጥቅመ ወንከውነኪ ሐጹረ። ንገሢ ለነ ወንከውነኪ ሕዝበ።ኩንነ
መርሐ ወንተሉ ድኅሬኪ። ኢትትአንትሊ ኢትትሐየዩ ወኢትትቆጥዒ
በብዝኀ አበሳነ እስመ ንሕነ ሕዝብ ዘአልቦ ሕገ ዘኢተምህረ
ስብሐተኪ። ወእምይእዜሰ ምርሂነ ወመሀሪነ ወአለብዊነ ወአጥብቢነ
ከመ ንትመሀር ስብሕተኪ ወከመ ይሰባሕ ስምኪ በላዕሌነ በኩሉ
ጊዜ ወበኩሉ መዋዕል በኩሉ መዐልት ወበኩሉ ሌሊት በኩሉ
ሰዓት ወበኩሉ ኑኀ አዝማን።
23 ሀብነ ኀይለ ንትቀነይ ለኪ። ተንሥኢ ጽዮን ወልበሲ ኀይለኪ።
ወሙኢዮሙ ለጸላእትኪ ወሀብነ ጽንዐ ለነገሥትኪ። ወአስተኃፍሪዮሙ
ለእለ ይጸልኡ ኪያኪ። ወአስተፍሥሒዮሙ ለእለ ያፈቅሩኪ።
24 ወእምዝ የዳ ወይቤ። ነያ ጽዮን። ነያ መድኀኒት። ነያ
መስተፍሥሒት። ነያ ብርሀት ከመ ፀሐይ። ነያ ሥርጉት በስብሓት
ከመ መርዓት። አኮ በአልባሰ ክብር ኀላፊ አላ ሥርጉት በክብር
ወበስብሐት እምኀበ እግዚአብሔር።
25 እንተ ይኔጽሩ መፍትው ወአኮ እንተ የኀድጉ። እንተ ያበድሩ
መፍትው ወአኮ እንተ ይሜንኑ። እንተ ያፈቅሩ መፍትው ወአኮ
እንተ ይጸልኡ። እንተ ይቀርቡ መፍትው ወአኮ እንተ ይርኅቁ።
ነቀርበኪ ወኢትርሐቅነ። ንትመረጉዘኪ ወኢታድኀፅነ። ንስእለኪ
ወኢትጸመምነ። ንጸርኀ ኀቤኪ ወስምዒ ገዐረነ። በኩሉ ዘሰአልነ
ኀቤኪ ወኢትፍቅዲ ተግሕሦ እምኔነ እስከ ይመጽእ እግዚእኪ
ወይነግሥ ላዕሌኪ እስመ ማኀደሩ አንቲ ለአምላከ ሰማይ።
26 ዘንተ ተናገረ ዳዊት ንጉሥ ወልደ ሰሎሞን ንጉሠ እስራኤል እስመ
ወረደ ላዕሌሁ መንፈሰ ትንቢት በእንተ ፍሥሓሁ ወኢየአምር
ዘይነብብ በከመ ጴጥሮስ ወዮሐንስ በርእሰ ደብረ ታቦር[55] ወአንከርዎ
ኩሎሙ ወይቤሉ ዝንቱ ወልደ ነቢይ ውስተ ነቢያትኒ ኀሉቀ።

[55] ማቴ.7፥11፡ሉቃ.19፥33



14 ለልጆቻችንና ለህዝቦችሽ ነገዶች ሁሉ መድሃኒት ሁኚ።
15 ለአገሮችና ለአህዛብ መድሃኒት ሁኚ።
16 ለነገስታቱና ለመኳንንቱ መድሃኒት ሁኚ።
17 ለአትክልትና ለፍራፍሬዎች መድሃኒት ሁኚ።
18 ለሰውና ለእንስሳ መድሃኒት ሁኚ።
19 ለወፎችና ለአራዊት መድሃኒት ሁኚ።
20 ለልምላሜዎችና ለአበቦች መድሃኒት ሁኚ።
21 ፀልይ፤ ማሪ፤ ለህዝብሽ ራሪ።
22 ቤት ሁኚን፤ አጥር እንሆንልሻለን። ንገሽልን፤ ህዝብ እንሆንሻለን።
መሪ ሁኚን። በሁዋላሽ እንከተልሻለን። አትሰልችን፤ ቸል አትበይን።
በአሳባችን ብዛት አትቆጭን። እኛ ህግ የሌለን ምስጋናሽንም
ያልተማርን ህዝቦች ነንና። ከዛሬ ጀምሮ ምስጋናሽን እንማር ዘንድ
ምሪን። አስተምሪን። አስታውሽን። ጥበብኛ አድርጊን። ስምሽ
በላያችን ላይ ሁል ጊዜና በዘመናት ሁሉ፤ በቀንና በሌሊት፤ በሰ
አትና በዘመን ርዝመት ሁሉ ይመስገን።
23 እንገዛልሽ ዘንድ ሃይልን ስጭን። ፅዮን ሆይ ተነሽ። ሃይልሃንም
ልበሺ። ጠላቶችሽንም ድል ንሻቸው። ለነገስታቶችሽም ፅናትን
ስጭን። አንችን የሚጠሉሽን አሳፍሪያቸው። የሚወዱሽንም
አስደስቻቸው።"
24 ከዚህ በሁዋላ ዞራት። "እነሆ ፅዮን፤ እነሆ መድሃኒት፤ እነሆ
አስደሳች፤ እነሆ እንደ ፀሃይ የበራች፤ እነሆ በምስጋና እንደ
ሙሽራ የተሸለመች፤ ከእግዚአብሄር ዘንድ በሆነ ክብርና ምስጋና
እንጂ በሚታይና በሃላፊ ልብስ የተሸለመች ያይደለች" አለ።
25 "የሚያስተውሉ መልካም አደረጉ። የማያስተውሉ ደግ አላደረጉም።
የሚያከብሩ መልካም አደረጉ። የሚንቁ ግን ደግ አላደረጉም።
የሚወዱ መልካም አደረጉ። የሚጠሉ ግን ደግ አላደረጉም።
የሚቀርቡ መልካም አደረጉ። የሚርቁ ግን ደግ አላደረጉም።
እንቀርብሻለን። አትራቂ። እንመረኮዝሻለን። አታድጭን። ወደ አንቺ
እንጮሃለን። ወደ አንቺ በለመነው ሁሉ ነገራችን ስሚ። ጌታሽ
እስኪመጣና በላይሽ ላይ እስኪነግስ ድረስ ከእኛ መሸሽን
አትፍቀጂ። አንቺ የሰማይ አምላክ ማደሪያ ነሽና።"
26 ይህን ሁሉ የእስራኤል ንጉስ የሰሎሞን ልጅ ንጉስ ዳዊት ተናገረ።
የትንቢት መንፈስ ወርዶበታልና። በደብረ ታቦር ጴጥሮስና ዮሃንስ[55]
ይናገሩት የነበረን እንደ አላወቁ ሁሉ የሚናገረውን አያውቅም
ነበር። ሁሉም አድንቀው "ይህ የነቢይ ልጅ ቁጥሩ ከነቢያት
ውስጥ ነው?" አሉ።

[55] ማቴ.7፥11፡ሉቃ.11፥33

www.ethiopianorthodox.org

## ፶ወ፩ በእንተ ዘተፈሥሑ ሰብአ ኢትዮጵያ

1 ወአኀዙ ዕንዚራተ ወነፍሑ ቀርነ ወከበሮ ወብዕንዛ ወበቃለ
ማኀሌቶሙ ወፍሥሓሆሙ ተሀውከት ወደምፀት ፈለገ ግብጽ
ወኀብሩ ምስሌሆሙ ውውዓ ወማኀሌት።
2 ወወድቁ ጣዖታቲሆሙ ዘገብሩ በእደዊሆሙ አምሳለ ሰብእ ወከልብ
ወድመት። ወዓዲ ማኅፈድ ነዋኀት ወእለ ምስሌሆሙ አምሳለ
አንሥርት ዘወርቅ ወብሩር። ወድቁ ወተቀጥቀጡ። እስመ ከመ
ፀሐይ ታበርህ። ወእምግርማሃ ይደነግፁ።
3 ወአልበስዋ አልባሲሃ። ወያሩ ሞፃሃ ቅድሜሃ። ወአንበርዋ ዲበ
ሰረገላ ነጺፎሙ ሜላተ ታሕቲሃ ወፀፈሮሙ ሜላተ በመልዕልቴሃ።
ወየኀልፉ ማኀሌተ በቅድሜሃ ወበድኅሬሃ ወተንሥኡ ሰረገላትኒ ከመ
ቀዲሙ ወጌሠ በጽባሕ እንዞ የኀልፉ ላቲ።
4 ወተለዐሉ ኵሎሙ መጠነ እመት እንዘ ያስተፋንውዎሙ ሰብአ
ብሔረ ግብፅ። ኀለፉ በቅድሜሆሙ ከመ ጽላሎት። ወሰገዱ ሎሙ
ሰብአ ብሔረ ግብጽ። እስመ ርእይዋ እንዘ ትረውጽ ከመ ፀሐይ
በውስተ ሰማይ። ወኵሎሙ ይረውጹ በሠረገላ እንዘ ይረውጹ
በቅድሜሃ ወበድኅሬሃ።
5 ወበጽሑ ባሕረ እልኀመር እንተ ይእቲ ባሕረ ኤርትራ እንተ ተሰ
ጥቀት በእደ ሙሴ። ወኬዱ ደቂቀ እስራኤል ውስተ ማዕምቅቲሃ
ዐቀበ ወቈልቋላ። እስመ ኢተውህበት አሜሃ ለሙሴ ታቦተ ሕጉ
ለእግዚአብሔር። ወበእንተዝ ጠግዐ ማይ አረፍት በፀግም። ወአረፍት በይምን
ወአኀለፎሙ ለእስራኤል ምስለ እንስሳሆሙ
ወደቂቆሙ ወአንስቲያሆሙ።
6 ወእምድኅረ ዐደዉ ባሕረ ተናገሮ እግዚአብሔር ወወሀቦ ታቦተ
ኪዳን ምስለ መጽሐፈ ሕግ። ወሶበ ተዐዱ ጽዮን ቅድስት ምስለ
እሊኣሃ አሜሃ እንተ ኀቤሃ እንዘ የኀልፉ ማኀሌተ በመሰንቆ
ወበዕንዚራት። ባሕርኒ ተቀበለቶሙ እንዘ ታንፈርዕፅ መዋግዲሃ ከመ
ሶበ ይትበተኩ አድባር ነዋኃት ወከመ ድምፀ አንበሳ ዘይጥሕር
ከማሁ በገንሀ ትደምፅ። ወከመ ነጎድጓደ ክረምተ ደማስቆ
ወኢትዮጵያ ሶበ ይዘብጠን መብርቅ ለደመናት ከማሁ ታንጎደጕድ።
7 ወኀብረ ነጐድጓድ ምስለ እንዚራት። ወሰገደት ላቲ። ባሕርኒ እንዘ
ይትሀወከ መዋግዲሃ ከመ አድባር ተለዐለ ሰረገላቲሆሙ መልዕልተ
መዋግድ መጠነ ሠለስቱ እመት።
8 ወበዜማ ማኀሌቶሙ መንክር ተላህያ ለባሕር። ግሩም ፈድፋደ።
ወመድምም ተላህያ ለባህር።[56] ዐዚዝ ጥቀ። ወእዕጹብ ተላህያ
ለባሕር። ወእለ ውስቴታኒ አራዊት እለ ይትዐወቁ ወእለ
ኢያስተርእዩ ይወፅኡ ወይሰግዱ ላቲ ወአዕዋፍኒ እለ ውስቴታ
ይጠፍሑ በክነፊሆሙ ወይጼልልዋ። ወኮነ ፍሥሓ ለባሕረ ኤርትራ
ወለሰብአ ኢትዮጵያ።

መዝ.93፥4

- 54 -

## ፶፩ የኢትዮጵያ ሰዎች እንደተደሰቱ

1 እንዚራንም አነሱ። ከበሮዎችና ነጋሪቶች ተመቱ። መለከቶችም
ተነፉ። በዘፈናቸውና በደስታቸው ቃል የግብፅ አገር ፈፅማ
ታወከች። ከእነሱም ጋር ውካታውና እልልታው አስተጋባ።
2 በሰው፣ በውሻና በድመት አምሳል በእጆቻቸው የሰሩአቸው
ጣኦቶቻቸውና ፎቆቻቸው ወደቁ። ከእነሱም ጋር በወርቅና በብር
በአሞራ ምስል የተሰሩ ጣአታቶቻቸው ተቀጠቀጡ። እንደ ፀሃይ
ታበራና ከግርማዋም ይቀልጡ ነበርና።
3 ልብሷንም አለበሷት። ሞጣህቷንም በፊቷ ተሸከሙ። በታችም በላይም
ጥሩ ሃርን አንጥፈውና አልብሰው በሰረገላ ላይ አስቀመጧት።
በፊትና በሁዋላዋም መዝሙር ይዘምሩ ነበር። ሰረገላዎችም እንደ
በፊቱ ተነሱ። እየዘመሩላትም በጠዋት ገሰገሱ።
4 የግብፅ አገር ሰዎችም ሲሸኙአቸው ሳለ ሁሉም አንድ ክንድ ያህል
ከፍ ብለው በፊታቸው እንደ ጥላ አለፉ። የግብፅ ሰዎችም በሰ
ማይ ላይ እንደ ፀሃይ ስትሮጥ አይተዋት ነበርና ሰገዱላቸው።
ሁሉም ደግሞ በፊትና በሁዋላ እየሆኑ በሰረገላ ይሮጡ ነበር።
5 የአልአህመር ባህር ከሆነችው ከባህረ ኤርትራም ደረሱ። ይህችውም
በሙሴ እጅ የተከፈለችውና የእስራኤል ልጆችም በጥልቅ ወደ
ላይና ወደ ታች የተሻገሩባት ናት። ያኔ የእግዚአብሄር ታቦተ ህግ
ለሙሴ አልተሰጠችም ነበርና በዚሁ ምክንያት ውሃው በግራም
በቀኝም እንደ ግድግዳ ሆነ። እስራኤል ከእንስሳቶቻቸውና
ከልጆቻቸው ከሴቶቻቸውም ጋር አሳለፉአቸው። ባህርንም ከተሻገሩ
በሁዋላ እግዚአብሄር ተናገረው። የቃል ኪዳኑንም ታቦት ከህጉ
መፅሃፍ ጋር ሰጠው።
6 ቅድስት ፅዮን ከእሷ ከሆኑትና ከእሷ ጋር ካሉት በመሰንቆና በእንዚራ
መዝሙር በተሻገረች ጊዜ፣ ባህር ማእበሎቿን እያዘለለች፣ ረጃጅም
ተራሮች ሲፈነቀሉ እንዲናወጡ እንደሚያገሳ አንበሳና እንደበገና
እንዲሁም እንደ ደማስቆና እንደ ኢትዮጵያ ክረምት ነጎድጓድ
መብረቅ ደመናቱን ሲመታ እንዲያንጎደጉድ እንደዚሁ ታንጎደጉድ
ነበር።
7 ነጎድጓዱም ከእንዚራዎቹ ጋር ተስማማ። ባህርም ማእበሎቿ እንደ
ተራሮች እየታወኩ ሰገደችላት። ሰረገላዎቻቸውም በሞገዱ ላይ ሶስት
ክንድ ያህል ከፍ ከፍ አሉ። ከባህርም ታላቅ ሞገድ ይልቅ
እግዚአብሄር በከፍታው ድንቅ ነው።[56] ይህም የሚገርም ነው።
8 በዘፈን ዜማም ከባህርም ታላቅ ሞገድ ይልቅ እግዚአብሄር በከፍታው
ድንቅ ነው። ይህም ፈፅሞ ብርቱ ነው። ከባህር ታላቅ ሞገድ ይልቅ
እግዚአብሄር በከፍታው ድንቅ ነው ከሚለው መዝሙራቸው ጋር በውስጧ
ያሉት የሚታወቁትና የማይታዩት እየወጡ ይሰግዱላት ነበር። በውስጧ
ያሉ ወፎችም በክንፋቸው ያጨበጭባሉ። ይጋርዷታልም። ለኤርትራ
ባህርና ለኢትዮጵያ ሰዎች ደስታ ሆነ።

[56] መዝ.93፥4

www.ethiopianorthodox.org

9 ወወጽኡ ባሕረ ወተፈሥሑ ፈድፋደ እምነ እስራኤል ሶበ ይወፅኡ
እምግብጽ ወበጽሑ አንፃረ ደብረ ሲና። ወኀደሩ ውስተ ቃደስ።
ወበህየኒ እንዘ ይሴብሑ መላእክት ወየኀብሩ ስብሐቲሆሙ መንፈሳውያን
ምስለ ደቂቀ መሬታውያን በማኅሌት ወበመዝሙር በክበሮ
ወበትፍሥሕት። ወእምህየሂ ፀዐኑ ሰረገላቲሆሙ። ወተንሥኡ ወሖሩ።
ወኀለፍዋ ለብሔረ ምድያም። ወበጽሑ ሀገረ ቤሉንቶስ እንተ ሀገረ
ኢትዮጵያ። ወተፈሥሑ በህየኒ። ወአዕረፉ እስመ ደወለ ብሔሮሙ በጽሑ
በክብር ወበፍሥሓ ዘእንበለ ጻማ በፍኖት በሠረገላ ነፋስ ምስለ ኀይለ ሰ
ማይ ወሚካኤል ሊቀ መላእክት። ወተፈሥሑ ኲሎሙ አድያመ
ኢትዮጵያ። እስመ ታበርህ ጽዮን ኀበ በጽሐት ከመ ፀሐይ በውስተ
ጽልመት።

## ፶ወ፮ በእንተ ግብአተ ሳዶቅ ካህን ውሂቦ ሞፃ

1 ወሶበ ገብአ ሳዶቅ ካህን ኀበ ሰሎሞን ንጉሥ ወረከቦ እንዘ ይቴክዝ
አውሥአ ንጉሥ ለሳዶቅ ካህን ወይቤሎ አመ ትመጽእ ንግሥት
አስተርአየኒ ከመዝ በሌሊት ከመ ዘእቀውም ውስተ ቀመራ
ለኢየሩሳሌም ወረደት ፀሐይ እምሰማይ ውስተ ብሔረ ይሁዳ
ወአብርሀት ፈድፋደ ወጕንድያ ዐረበት ወአብርሀት ለብሔረ ኢትዮጵያ
ወኢገብአት ዳግመ ውስተ ብሔረ ይሁዳ።
2 ወካዕበ ወረደት ፀሐይ እምሰማይ ውስተ ብሔረ ይሁዳ።
ወአብርሀት ፈድፋደ እምቀዲሙ። ወተሀየይዋ እስራኤል።
ወፈቀዱ ይድፍኑ ብርሃና። ወሠረቀ እንተ መትሕተ ምድር
እንተ እምኀበ ኢተኀዘብዎ። ወአብርሀ ለብሔረ ሮሜ ወለብሔረ
ኢትዮጵያ። ወእምድኅሬሁ ለኲሎሙ እለ አምኑ ቦቱ።
3 ወአውሥአ ሳዶቅ ካህን ወይቤ እግዚእየ ለምንት ዘኢነገርከኒ
ቀዲሙ ዘከመዝ አርአያ ዘርኢከ። አርዐድከኒ ለብረክየ። አሌ ለነ
ደቂቅነ ለእመ ነሥእዋ ለእግዝእትነ ጽዮን ቅድስት ሰማያዊት
ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር።
4 ወአውሥአ ንጉሥ ወይቤሎ ተረስዐ ጥበብነ። ወተደፍነ ኀሊናነ።
በአማን አምሳሊሃ ለፀሐይ ጽዮን ቅድስት ዘአስተርአየኒ አሜሃ
እንዘ ሀሎኩ ንውምየ ምስለ ንግሥተ ኢትዮጵያ።ወባሕቱ ንግረኒ
እስኩ ትማልም ሶበ ትነሥእ ልብሰ ተወንያ ዘቃማ እምላዕሌሃ
ለጽዮን ኢጠየቀኑ ህላዌሃ።
5 አውሥአ ሳዶቅ ወይቤ አልቦ እግዚአ እስመ ሠለስቱ ልብስ
በኀቤሃ። ነሣእኩ እንተ ላዕሌሃ ወአልበስክዋ እንተ ወሀብከኒ
ወአምጻእኩ ኀቤከ።
6 ወይቤሎ ሑርኬ አፍጥን ነጽሮታ ለእግዝእትነ ወርአያ ጥዩቀ።
7 ወነሥአ መራኁተ ሳዶቅ ካህን። ወሖረ ወፈትሐ ኆኅተ ቤተ
መቅደስ። ወአፍጠነ ነጽሮ ወኀሢሠ። ወአልቦ ዘረከበ ዘእንበለ
ዕፀወ ለውሕ ጥጕዓን በአረፍተ ምንባሪሃ ለጽዮን ዘአስተማሰለ
አዛርያስ።



9 ከባህርም ወጡ። ከእስራኤል ከወጡበት ጊዜ ይልቅ በግብፅ
ፈፅመው ተደሰቱ። በደብረ ሲና ትክክልም ደረሱ። በምስጋናም
በቃደስ አደሩ። የሰማያውያንም ምስጋና ከመሬታውያን ልጆች
ምስጋና ጋር በማህሌት በመዝሙርና በክበሮ እንዲሁም በደስታ
አንድ እየሆኑ አደሩ።
10 ከዚያም ሰረገላዎቻቸውን ጫኑና ተነሱ። የምድያምንም አገር
አልፈው ኢትዮጵያ ውስጥ ቤሉንቶስ ከተባለው አገር ደረሱ።
በነፋስ ሰረገላ ሆነው ከሰማይ ሰራዊትና ከሊቀ መላእክቱ ሚካኤል
ጋር በመንገድ ያለ ድካም ከአገራቸው አውራጃ ደርሰዋልና ተደሰቱ
አረፉም። ፅዮንም በደረሰችበት ሁሉ ፀሃይ በጨለማ እንድታበራ
ታበራ ነበርና የኢትዮጵያ አውራጃዎች ሁሉ ተደሰቱ።

## ፶፮ ካህኑ ሳዶቅ የበደል መሰዋእት አቅርቦ ስለ መመለሱ

1 ካህኑ ሳዶቅም ወደ ንጉስ ሰሎሞን በተመለሰ ጊዜ ሲተክዝ
አገኘው። ንጉሱም ለካህኑ ለሳዶቅ መለሰለት፤ አለውም። "ንግስቲቱ
በመጣችበት ወቅት በሌሊት እንዲህ አሳየኝ። በኢየሩሳሌም ዋልታ
እንደቆምኩ በይሁዳ አገር ከሰማይ ፀሃይ ወረደች። እጅግም
አበራች። ቆይታም ጠፋች። ለሃገረ ኢትዮጵያም አበራች። ሁለተኛም
ወደ ይሁዳ ምድር አልተመለሰችም።
2 ደግሞም ፀሃይ ከሰማይ ወደ ምድረ ይሁዳ ወረደ። ከበፊቱም
የበለጠ አበራ። እስራኤል ቻል አሉት። ብርሃኑንም ሊያጠፉ
ወደዱ። ካልጠበቁት ዝቅተኛ ቦታም ወጣ። ለሮምና ለኢትዮጵይያ
አገሮችም አበራ። ከዚህም በሁዋላ ለአመኑበት ሁሉ።
3 ሳዶቅም መልሶ "ጌታዬ ሆይ! ስለምንድን ነው እንደዚህ ያለ
ራእይ እንዳየህ አስቀድመህ ያልነገርከኝ? ጉልበቴን አንቀጠቀጥከው።
እመቤታችን ፅዮንን፤ ቅድስቷንና ሰማያዊቷን የእግዚአብሄር ታቦተ
ህግን ልጆቻችን ወስደዋት እንደሆነ ወዮልን" አለ።
4 ንጉሱም መልሶ "ጥበባችን ተረሳ። ህሊናችን ታወረ። ያኔ
ከኢትዮጵያ ንግስት ጋር ተኝቼ ሳለሁ የታየችኝ ፀሃይ ምሳሌ
በእውነት ቅድስቷ ፅዮን ናት" አለው። "ነገር ግን እስኪ አሁን
ንገረኝ። ከፅዮን ላይ ልብሷንና የወርቅ ማርዳዋን በወሰድክ ጊዜ
መኖሯን አልጠየቅም?" አለው።
5 ሳዶቅም መለሰ፤ አለም። "ጌታዬ ሆይ! የለም። ከእሷ ዘንድ ሶስት
ልብሶች አሉና። የእሷን ወስጄ የሰጠህኝን በላይ አለብሳታለሁ። የወሰ
ድኩትንም ወደ አንተ አመጣለሁ" አለው።
6 ንጉሱም መልሶ "ሂድ። እመቤቴን ማየት አፍጥን። አረጋግጠህም እያት"
አለው።
7 ካህኑ ሳዶቅም መብራትን ይዞ ሄደ። የቤተ መቅደሱንም በር ከፈተ።
መመልከትና መፈለግንም አፋጠነ። አዛርያስ በፅዮን ልክ ከመሰለው
ከጠርብ እንጭት በቀር ምንም አላገኘም።

www.ethiopianorthodox.org

## ፶ወ፮ በእንተ ውድቀተ ሳዶቅ ካህን

1 ወርእዮ ዘንተ ወድቀ በገጹ ውስተ ምድር። ወተከዕወት ነፍሱ በላዕሌሁ።
እስመ ደንገፀ ወኮነ ከመ በድን።ወሶበ ጕንደየ ወጊአ ለእከ ሎቱ ኢዮአስ
ወልደ ዮዳሔ። ወረከቦ ውዱቀ ከመ በድን። ወአንሥአ ርእሶ ወገሠሠ
ልቦ ወእንፎ እመ ይረክብ ምውቀ እስትንፋስ በላዕሌሁ። ወነፍሐ
ወአንሥአ ወነገፎ ወአፅገዮ ውስተ ጠረጴዛ። ወተንሥአ ወነጸረ ውስተ
ምንባሪሃ ለጽዮን። ወኢረከባ ወወድቀ። ወወደየ ሐመደ ውስተ ርእሱ።
ወተንሥአ ወሖረ። ወከልሐ በእናቅጺሃ ለቤተ እግዚአብሔር። ወተሰምዐ
ድምፅ እስከ ቤተ ንጉሥ። ወተንሥአ ንጉሥ። ወአዘዘ ይዑድ ዐዋዲ።
ወይንፍሑ ቀርነ ፀባዒት ከመ ይሑር ወይስድዶሙ ለሰብአ ብሔረ
ኢትዮጵያ ወለእመ ረከቦሙ ከመ የአኀዞ ለወልዱ ወያግብእ ምስለ ጽዮን
ወይቅትሎሙ ለከሎሙ በአፈ ኀፂን።
2 እስመ በአፉሁ ነበበ ወይቤ ሕያው እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ከመ
ሰብአ ሞት እሙንቱ። ወኢኮኑ ለሕይወት። እስመ በአማን ይደልዎሙ
ሞት በእንተ ዘሰረቁ ቤተ መቅደሱ ለእግዚአብሔር ወፈቀዱ ያርኵሱ
ማኅደረ ስሙ ውስተ ምድር ዘአልቦ ሕግ።

## ፶ወ፯ ኀበ ተንሥአ ሰሎሞን ይቅትሎሙ

1 ከመዝ ተናገረ ንጉሥ ሰሎሞን ወተንሥአ በመዓት ወሖረ ከመ
ይኅሥሦሙ። ወሶበ ተንሥኡ ንጉሥ ወመኳንንቲሁ ወኃያላቲሁ ተጋብኡ
እዕሩገ እስራኤል ውስተ ቤተ እግዚአብሔር ምስለ እቤራት ወደናግል።
ወበከዩ በእንተ ጽዮን። እስመ ተነሥአት እምኔሆሙ ታቦተ ሕገ
ለእግዚአብሔር። ወለሳዶቅኒ እስመ ገብአ ልቡ እምድኅረ ጉንዱይ ሰዓት።
ወእምዝ አዘዘ ንጉሥ ከመ ይሑሩ ይምነ ወጸግመ ከመ እመቦ ከመ
ይትገሐሡ እምፍርሃተ ሰርቅ። ወለሊሁሰ ንጉሥ ተንሥአ በአሠረ ፍኖቶሙ
ለሰብአ ኢትዮጵያ። ወፈነወ መባርዲነ ሰብአ አፍራስ ከመ ያእምሩ ኀበ
ሀለዉ ወይግብኡ ወይንግርዎ።
2 ወሖሩ ወበጽሑ ሀገረ ምስር ኀበ ተዐየኑ ህየ ሰብአ ኢትዮጵያ ምስለ
ንጉሦሙ ወኀበሂ ተሳለምዋ ለጽዮን ወተፈሥሑ። ወሐተቱ ኪያሆሙ ሐራ
ንጉሥ ወይቤልዎሙ ሰብአ ብሔረ ግብጽ እምርጉቅ መዋዕል በዝየ ኀለፉ
ሰብአ ኢትዮጵያ እንዘ ይረውጹ በሰረገላ ከመ መላእክት። ወይቀልሉ እምነ
አንስርት በውስተ ሰማይ።
ወይቤልዎሙ ማዕዜ ዕለተ ኀለፉ እምኔከሙ።ወይቤልዎሙ ዮም ተሱዕ
መዋዕል በዘኀለፉ እምኔነ። ወቦ እምኔሆሙ እለ ገብኡ ወነገርዎ ለንጉሥ ሰ
ሎሞን ከመ ኀለፉ ተሱዐ መዋዕለ እምዝ ኀለፉ እምስር። ወአብያጺነሰ ሖሩ
ከመ ይኅሥሡ እስከ ባሕረ ኤርትራ ወንሕነሰ ገባእነ ከመ ንንግርከ ዘንተ።
እስኩ ኀሊ ለሊከ ንጉሥ በዕለተ ሠኑይ እምከመ ወፅኡ እምኀቤከ በጽሑ
በሠሉስ ኀበ ፈለገ ተከዚ ሀገረ ምስር። ወለነኒ ሶበ ፈነውከነ
እምኢየሩሳሌም በጸሕነ በዕለተ ሰንበት። ወገባእነ ኀቤከ ዮም በዕለተ ረቡዕ።
ኀሊኬ በጥበብ መጠነ ይበጽሑ እሙንቱ ሰብእ።

- 56 -

## ፶፮ ስለ ካህኑ ሳዶቅ ውድቀት

1 ይህንን አይቶ በፊቱ በምድር ላይ ወደቀ። ነፍሱም ፈሰሰች። በድንጋጤ
እንደ በድን ሆኖ ነበርና። ከመምጣትም በዘገየ ጊዜ የዮዳሄ ልጅ
ኢዮአስን ላከበት። እንደ በድንም ሆኖ ወድቆ አገኘው። ከራሱም
አነሳው። በላዩም ላይ የሞቀ ትንፋሽን ያገኝ እንደሆነ ልቡንና
አፍንጫውን ዳሰሰው። ተነፈሰ፤ አንስቶም አርገፈገፈው፤ ወደ ጠረጴዛም
አስጠጋው። ተነስቶም በፅዮን ማስቀመጫ ተመለከተ። አላገኛትምና
ወደቀ። በራሱም ላይ አመድ ነሰነሰ። ተነሳና ወደ እግዚአብሄር ቤት
ደጃፍ ሄዶ ጮሀ። ድምፁም እስከ ቤተ መንግስት ተሰማ። ንጉሱም
ተነሳ። የኢትዮጵያን ሰዎች ያሳድዷቸው ዘንድ እንደሚሄድና ካገኛቸው
ልጁን ከፅዮን ጋር እንደሚመልሰው፤ የቀሩትን ግን ሁሉንም በጦር
መሳሪያ እንደሚገድላቸው፤ አዋጅ ነጋሪም እንዲዘምርና የጦርነት ነጋሪትም
እንዲመታ አዘዘ።
2 የስሙን ማደሪያ ያረክሱ ዘንድ ስለ ወደዱ የእስራኤል አምላክ "ህያው
እግዚአብሄርን እነሱ የሞት እንጂ የምህረት ሰዎች አይደሉም። በእውነት
ሞት ይገባቸውዋል" ሲል በቃሉ ተናግሯልና።

## ፶፯ ሰሎሞን ይገድላቸው ዘንድ እንደተነሳ

1 ንጉሱ ሰሎሞን እንደዚህ ተናገረ። በቁጣም ተነሳ። ሊፈልጋቸው
ሄደ። ንጉሱ፤ መኳንንቱና ሃያላኑ በተነሱ ጊዜ የእስራኤል
ሽማግሌዎች ከባልቴቶችና ከደናግል ጋር ተሰበሰቡ። የእግዚአብሄር
ታቦተ ህግ ከእነሱ ተወስዳለችና ስለ ፅዮን አለቀሱ። ሳዶቅም
ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ ልቡ ተመልሶ ነበር። ከዚህ በሁዋላ ንጉሱ
ለምናልባት ከሌብነት አደጋ እንዲጠነቀቁና ቀኝና ግራ ሆነው
እንዲሄዱ አዘዘ። ራሱ ግን የኢትዮጵያን ሰዎች ዱካ ተከትሎ ሄደ።
ያሉበትን ያጠኑና ተመልሰውም ይነግሩት ዘንድ ፈረሰኛ
መርማሪዎችን ላከ።
2 ሄደውም የኢትዮጵያ ሰዎች ከንጉሳቸው ጋር ወደ ሰፈሩበትና
ፅዮንንም ተሳልመው ከተደሰቱበት ከግብፅ አገር ደረሱ። የንጉሱ
ወታደሮችም እነሱን መረመሩ። የግብፅ ሰዎችም "የኢትዮጵያ ሰዎች
ከሩቅ ጊዜ ጀምሮ እንደ መላእክት በሰረገላ እየሮጡ በሰማይ ላይ
ከአሞራዎች ይልቅ ቀለው በዚህ አለፉ?
3 እነሱም መቸ ከእናንተ ዘንድ አለፉ? አሏቸው። እነዚያም በዚህ
ካለፉ ዘጠኝ ቀናቸው ነው" አሏቸው። ከወታደሮቹም ግብፅን ካለፉ
ዘጠኝ ቀናቸው እንደሆነ ለንጉሱ ሰሎሞን ተመልሰው የነገሩት
ነበሩ። ጓደኞቻቸው ግን ይፈልጉ ዘንድ እስከ ባህረ ኤርትራ ድረስ
ሄዱ። "እኛ ግን ይህንን እንነግርህ ዘንድ ተመለስን። ንጉስ ሆይ
እስኪ አስብ። ማክሰኞ እለት ከአንተ ወጡ። በሦስተኛው ቀን
ግብፅ ውስጥ ከተከዜ ወንዝ ደረሱ። እኛንም ከኢየሩሳሌም በላክህን
ጊዜ ቅዳሜ ቀን እነዚህ ሰዎች የሚደርሱበትን አስብ" አሉት።

www.ethiopianorthodox.org

4 ወተምዐ ንጉሥ ወይቤ አኀዝዎሙ ለአምስቲሆሙ እስከ ንረክብ ጽድቀ ቃሎሙ። ወአፍጠኑ ሐዊረ ንጉሥ ወሠራዊቱ። ወበጽሑ ጋዛ። ወተስእሎሙ ወይቤሎሙ ማዕዜ ኀለፈ ወልድየ እምኔክሙ።

5 አውሥኡ ወይቤሉ ኀለፈ ይእቲ ሠሉስ ዕለት። ወሶበ ፀዐኑ ሰረገላቲሆሙ አልቦ ዘየሐውር መልዕልተ ምድር አላ በሰረገላ ስቁላን መልዕልተ ነፋስ። ወይቀልሉ እምነ አንስርት ዘውስተ ሰማይ ወኵሉ ንዋዮሙ የሐውር ምስሌሆሙ መልዕልተ ነፋስ በሰረገላ። ወለነሰ መሰለነ ዘአንተ ረሰይከ ሎሙ በጥበብከ ከመ ይሑሩ በሰረገላ መልዕልተ ነፋስ።

6 ወይቤሎሙ ቦኑ ዘሀለወት ጽዮን ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ምስሌሆሙ።

7 ወይቤልዎ አልቦ ዘርኢነ።

## ፶ወ፱ ጎበ ሐተቶ ለግብጻዊ ገብረ ፈርዖን

1 ወኀለፈ እምህየ ወረከበ አሐደ መኰንነ እመኳንንተ ግብጽ ዘንጉሥ ፈርዖን ዘለአኮ ኀቤሁ ምስለ አምኃ ወምሉዕ ንዋይ ምስሌሁ ወበጽሐ ወሰገደ ለንጉሥ።

2 ወአፍጠነ ሐቲተ ሰሎሞን ንጉሥ ዘእንበለ የሀብ አምኃሁ ወመልእክቶ። ወይቤሎ ቦኑ ዘርኢከ ሰብአ ኢትዮጵያ እንዘ ይግዕዙ እምህየ።

3 ወአውሥአ ወይቤሎ መልአከ ፈርዖን ለንጉሥ ሕያው አንተ ንጉሥ ለዓለም። ለአከኒ እግዚእየ ንጉሥ ፈርዖን እምእስክንድርያ ኀቤከ። ወነዋ አየድዐከ ወሶበ መጻእኩ እም እስክንድርያ። ቦእኩ ቃህራ ውስተ ሀገሩ ለንጉሥ። ወበብጽሐትየ በጽሑ ህየ እሉ ሰብአ ኢትዮጵያ ዘትብል። በጽሑ እንተ ኀለፈት ሠሉስ ውስተ ተከዚ ፈለገ ምስር እንዘ ይነፍሑ በእንዚራት ወይረውጹ በሰረገላት ከመ ኀይለ ሰማያውያን።

4 ወእለ ርእይዎሙ ይቤልዎሙ እሉሰ እንዘ መሬታውያን ኮኑ ሰማያውያነ። መኑኬ ይጠበብ እም ሰሎሞን ንጉሠ ይሁዳ። ወውእቱኒ ኢሖረ በሰረገላ ነፋስ ከመዝ።

5 ወእለ ሀለው ውስተ አህጉር ወማኀፈድ ስምዐ ኮኑ ከመ ሶበ ቦኡ እሉ ውስተ ብሔረ ግብጽ። ወድቁ ወተሰብሩ አማልክቲነ ወአማልክተ ንጉሥ። ወማኀፈደ ጣዖታትኒ ከማሁ ተቀጥቀጡ። ወሐተቱ ገነውተ አማልክት ማርያነ ግብጽ በእንተ ዘወድቁ አማልክቲነ። ወይቤሉነ ታቦተ አምላከ እስራኤል እንተ ወረደት እምሰማይ። ሀለወት ምስሌሆሙ ወትነብር ውስተ ሀገሮሙ እስከ ለዓለም። ወበእንተዝኬ ሶበ ትበውእ ብሔረ ግብጽ ተቀጥቀጡ አማልክቲነ።

- 57 -

4 ንጉሱም ተቆጥቶ "የቃላቸውን ትክክለኛነት እስክናገኝ ድረስ አምስቱንም ያዟቸው" አለ። ንጉሱና ሰራዊቱም መሄድን አፈጠኑ። ጋዛም ደረሱ። "ልጄ ከእናንተ ዘንድ መቼ ነው የሄደው" ሲል ጠየቃቸው።

5 እነሱም መልሰው "ዛሬ ሰኞ ሶስተኛ ቀኑ ነው። ሰረገላቸውንም በጫኑ ጊዜ ሁሉም በነፋስ ላይ በሰረገላ ይሄዱ ነበር እንጂ በምድር ላይ የሚሄድ አልነበረም። ከምናውቃቸው ከሰማይ አእዋፍም ይቀሉ ነበር። ሃብታቸውም ሁሉ ከእነሱ ጋር በነፋስ ላይ በሰረገላ ይጓዝ ነበር። እኛ ግን አንተ በነፋስ ላይ በሰረገላ ይሄዱ ዘንድ በጥበብህ ያደረከው መስሎን ነበር" አሉት።

6 እሱም "የእግዚአብሄር ታቦተ ህግ ፅዮን ከእነሱ ጋር ነበረች? " አላቸው።

7 እነሱም "ያየነው የለም" አሉት።

## ፶፱ ግብፃዊውን የፈርኦንን አገልጋይ እንደ መረመረው

1 ከዚያም ሲያልፍ ፈርኦን ከእጅ መንሻና ከብዙ ገንዘብ ጋር የላከውና ከግብፅ ንጉስ መኳንንት የሆነ አንድ መኮንን አገኘ። እንደደረሰም ለንጉሱ ሰገደ።

2 እጅ መንሻንውንና መልእክቱንም ሳያቀርብ ንጉሱ ሰሎሞን ምርመራውን አፋጠነ። "የኢትዮጵያ ሰዎች በዚህ ሲጓዙ አላየህምን?" አለው።

3 የፈርኦንም መልእክተኛ ለንጉሱ መልሶ "ንጉስ ሆይ! ለዘላለም ኑር። ጌታየ ንጉስ ፈርኦን ከእስክንድርያ ወደ አንተ ላከኝ። እነሆ እንዴትም እንደመጣሁ እነግርሃለሁ። ከእስክንድርያ በመጣሁ ጊዜ ከንጉሱ አገር ውስጥ ቃህራ ውስጥ ገባሁ። ወዲያው ስደርስም እነዚህ የኢትዮጵያ ሰዎች የምትላቸው እዚህ ደረሱ። ባለፈው ማክሰኞ እንዚራ እየነፉና እንደ ሰማያውያን ሃይሎች በሰረገላ እየሮጡ ከግብፅ ወንዝ ማለትም ተከዜ ደረሱ።

4 የሚያዩአቸውም "እነዚህ መሬታውያን ሲሆኑ ሰማያውያን ሆኑ። ከይሁዳ ንጉስ ከሰሎሞን የበለጠ ጥበበኛ ማነው? እሱም ቢሆን እንደዚህ በነፋስ ሰረገላ አልሄደም። " ይሉ ነበር።

5 "ወደ ምድረ ግብፅ ሲገቡ አማልክቶቻችንና የንጉሱም አማልክቶች እንደ ወደቁና እንደ ተሰባበሩ ምስክሮች ናቸው። የጣኦታቱ ቤተ መቅደሶችም እንዲሁ ነኳኩቱ። የግብፅ ነቢያት ሃሰትና ካህናተ ጣኦቶቻችን የወደቁበት ነገር መርምረው ከሰማይ የወረደችው የእስራኤል አምላክ ታቦት ከእነሱ ጋር አለች። በአገራቸውም ለዘላለም ትኖራለች። በዚህም ምክንያት እሷ አገራችን ስትገባ ጣኦቶቻችን ተቀጠቀጡ" አሉን።

www.ethiopianorthodox.org

6 ወአንተሰ እ ንጉሥ አልቦ ዘይመስላ ለጥበብከ እምታሕተ ሰማይ።
ወለምንት ወሀብከ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር አምላክከ ዘአጽንሑ
ለከ አበዊከ። እስመ ንሰምዕ ከመ ይእቲ ታድኅነክሙ እምእደ
ፀርክሙ። ወመንፈሰ ትንቢትኒ ባቲ ይትናገረክሙ። ወአምላከ ሰማይኒ
የኀድር ውስቴታ በመንፈሱ ቅዱስ። ወትሰመዩ ሰብአ ቤቱ
ለእግዚአብሔር። ወለምንት ዘወሀብክሙ ክብረክሙ ለባዕድ።
7 አውሥአ በጥበብ ሰሎሞን ወይቤ በአይቴ ይክሉ ነሚኦታ
ለእዝግእትነ። እስመ ሀለወት ኀቤነ።

## ፳ ኀበ ለሐዋ ሰሎሞን ለጽዮን

1 ወቦአ ውስተ ኀይመቱ። ወበከየ ብካየ መሪረ እንዘ ይብል እግዚኦ
በመዋዕልየኑ ትነሥእ ለታቦተ ኪዳንከ እምኔነ። ባሕቱ እምቀደምከ
ነሚአ ነፍስየ እምኔሃ ዘበመዋዕልየ ትነሥእ። እስመ አንተሰ ኢትሔሱ
ቃለከ ወኢትዔምፅ ኪዳነከ ዘተካየድከ ምስለ አበዊነ ምስለ ኖኅ
ገብርከ ዘአቀባ ለጽድቅ ወምስለ አብርሃም ዘኢተዐደወ ትእዛዘከ
ወምስለ ይስሐቅ ቁልዔከ ዘአንጽሐ ሥጋሁ እምርሥሐተ ኃጢአት
ወምስለ እስራኤል ቅዱስከ ዘአስተባዛኅከ በመንፈስ ቅዱስ። ወሰመይኮ
አሠረ ዚአከ እስራኤል። ወምስለ ሙሴ ወአሮን ካህናቲከ እለ
በመዋዕሌሆሙ አውረድካ ለታቦተ ሕግ እምሰማይ ዲበ ምድር
ለደቂቀ ያዕቆብ ርስትከ ምስለ ሕግከ ወትእዛዝከ በአርአያ ሥርዓተ
መላእክት።
2 እስመ አቅደምከ ሣርሮታ ለጽዮን ለማኅደረ ስብሐቲከ ውስተ ደብረ
መቅደስከ። ወበዳግምስ ወሀብኮ ለሙሴ ከመ ያሠኒ ገቢሮታ በዲበ
ምድር ወያንብራ ውስተ ደብተራ ዘስምዕ ከመ አንተኒ ትምጻእ ህየ
እምደብረ መቅደስከ ወታሰምኦሙ ቃለከ ከመ ይሑሩ በትእዛዝከ።
3 አእመርኩ ይእዜ ከመ ተሐየይከ ርስተከ እምነ እስራኤል ሕዝብከ።
ወእስከ ይእዜ ሀለወት ምስሌነ። ወኢያሠነይነ ተግባራ። ወበእንተዝ
ተማዕከነ። ወሜጥከ ገጸከ እምኔነ።
4 እግዚኦ ኢትነጽር ምግባረነ እኩየ። አላ ነጽር ኂሩቶሙ ለአበዊነ
ቀደምት። አቡየ ዳዊት ገብርከ ፈቀደ ይሕንጽ ቤተ ለስምከ። ሰሚዖ
ቃለ ነቢይከ ዘይቤ አይኑ ቤት ለማኅደርየ ወአይኑ መካን
ለምዕራፍየ አኮኑ እደውየ ዘገብራ ዘኩሎ ይቤ እግዚአብሔር[57]
ዘኩሎ ይመልክ። ወዘንተ ሶበ ኀለየ ትቤሎ ኢይትከሀለከ ዘዘንተ
ሐነጽከ አላ ዘወፅአ እምሐቋከ የሐንጽ ሊተ።[58]

[57] ኢሳ.66፥1፡
[58] 1ዜ.መ.22፥8-9

- 58 -

6 "ንጉስ ሆይ! አንተ ግን ከሰማይ በታች ጥበብህን የሚመስላት
የለም። ስለዚህ አባቶችህ ያቆዩህን የአምላክህን የእግዚአብሄርን
ታቦተ ህግ ስለምን ሰጠህ? እሷ ከጠላቶቻችሁ እጅ እንድታድናችሁ
ሰምተናልና። በእሷ ያለ የትንቢት መንፈስም ይናገራችሁዋል። የሰ
ማይ አምላክም ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ በውስጧ ያድራል።
ስለዚህም የእግዚአብሄር ቤተ ሰቦች ትባላላችሁ። ታዲያ ክብራችሁን
ለባእድ የሰጣችሁ ለምንድን ነው? " አሉ።
7 ንጉሱም በጥበብ አነጋገር "እመቤታችንን እንዴት ሊውስዷት
ይችላሉ? በእኛ ዘንድ ናትና" ሲል መለሰ።

## ፳ ሰሎሞን ለፅዮን እንደ አለቀሰላት

1 ወደ ድንኳኑም ገባ። "አቤቱ! የቃል ኪዳንህ ታቦት በዘመኔ ከእኛ
ትወስዳታለህ? " ሲል የመረረ ልቅሶ አለቀሰ። "እሷን በዘመኔ
ከምትወስዳት ይልቅ ነፍሴን መውሰድ ባስቀደምህ በተሻለ ነበር።
አንተ ከአባቶቻችን ማለትም እውነትን ከጠበቃት ከባሪያህ ከኖህ
ጋር፣ ትእዛዝህን ካልተላለፈው ከአብርሃም ጋር፣ ከሃጢያት
ጉስቁልና ስጋውን ካነፃ ከወዳጅህ ከይስሃቅ ጋር፣ በመንፈስ ቅዱስ
ካበዛህውና በአንተም እግር እስራኤል ብለህ ከጠራህው ከቅዱስህ
ጋር፣ በመላእክት ስርአት ምሳሌ ከህግህና ከትእዛዝህ ጋር ለርስትህ
ለያእቆብ ልጆች ታቦተ ህግን ከሰማይ ወደ ምድር ባወረድክላቸው
ከካህናቶችህ ከሙሴና ከአሮን ጋር በገባህው ቃል ኪዳን
አትበድልምና። በቃልህም አትዋሽምና።
2 በመቅደስህ ውስጥ ለምስጋናህ ማደሪያ ትሆን ዘንድ ፅዮንን
አስቀድመህ ሰርተሃታልና። ዳግመኛም ከመቅደስህ ቦታ እዚህ
ትመጣ ዘንድና በትእዛዝህም እንዲሄዱ ቃልህን ታሰማቸው ዘንድ፣
ለሙሴም በምድር ላይ አሠራሯን ያሳምር ዘንድና በምስክሯ
ድንኳንም ውስጥ ያስቀምጣት ዘንድ ሰጠህው።
3 እነሆ ዛሬ ርስትህን ከህዝብህ እስራኤል ችላ እንዳልከው አወቅሁ።
እስከ ዛሬ ከእኛ ጋር ነበረች። ስራችንን አላሳመርንም ነበር።
ስለዚህም ተቆጣህን። ፊትህንም ከእኛ መለስክ።
4 አቤቱ! የቀደሙ አባቶቻችንን ቸርነት እንጂ የእኛን ክፉ ስራ
አትመልከት። አባቴ ባሪያህ ዳዊት 'ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሄር
የሚያድርበት ቤት የት አለ? የሚያርፍበትስ ምን ቦታ አለ? ይህንን
ሁሉ እጆቼ አልሰሩትምን'[57] ያለውን የነቢይህን ቃል ሰምቶ ለስምህ
ቤትን ሊሰራ ወደደ። ይህንንም ባሰበ ጊዜ 'ከአብራክህ የወጣው ይሰ
ራልኛል እንጂ አንተ ይህን መስራት አይቻልህም' አልከው።[58]

[57] ኢሳ.66፥1
[58] ዜ.መ.22፥8-9

www.ethiopianorthodox.org

5 ወይእዜኒ እግዚኦ ኢተሐሰወ ቃልከ። ወሐነጽኩ ቤተከ እንዘ አንተ
ረዳእየ። ወሶበ ፈጸምኩ ሐኒጸ ቤትከ አባእክዋ ለታቦተ ኪዳን
ውስቴታ። ወሦዕኩ መሥዋዕተ ለሥላሴ ስምከ ቅዱስ። ወሐወጽከ
ውስቴታ። ወመልአ ቤተ ስብሐቲከ እንዘ ኩሎ ዓለመ ምሉእ
መለኮትከ። ወተፈሣሕነ ሕዝብከ በነጽሮ ስብሐቲከ ውስቴታ።
6 ወእምአሜሃሰ ዮም ሣልሲት ዓመታ። ወመሠጥካ ለብርሃንነ እምኔነ
ከመ ታበርህ ለእለ ውስተ ጽልመት። ነሰትካ ለክብርነ ከመ ታክብሮ
ሙ ለኀሡራን። አጥፋእከ ግርማነ ከመ ታግርሞ ለዘኢኮነ ግሩመ።
ነሠትካ ለሕይወትነ ከመ ትሕንጸ ለዘርኀቀ ሕይወቱ እምኔከ።
7 አሌ ሊተ አሌ ሊተ እበኪ በእንተ ርእስየ። ተንሥእ ዳዊት አቡየ
ወብኪ ምስሌየ በእንተ እግዝእትነ። እስመ ተሀየየነ እግዚአብሔር
ወነሥአ ለእግዝእትነ እምደቂቅከ። አሌ ሊተ አሌ ሊተ እመ
ተሀየየኒ ፀሐየ ጽድቅ። አሌ ሌተ በእንተ ዘተሀየይነ ትእዛዘ
አምላክነ። ኮነ ኀሡራነ በዲበ ምድር። ካህናትኒ ኢያሠነይነ።
ወነገሥትኒ ኢያርታዕነ ፍትሐ ለእጓለ ማውታ። አሌ ለነ አሌ ለነ
እስመ ኀለፈት ርትዕ እምኔነ። ወተገሠጽነ። አሌ ለነ ፈሥሐነ
ተመይጠት ኀበ ጸላእትነ። ወሞገስነ ተረስዐት እምላዕሌነ። አሌ ለነ
አሌ ለነ ተመጠወ ዘባንነ ለኩናተ ፀርነ። አሌ ለነ ኮኑ ሕብልያ
ድቂቅነ ወዔዋ ለእለ ይእዜ ነሐ በልዮሙ ወንዔውዎሙ አሌ ለነ
በከያ ዕቤራቲነ ወለሐዋ ደናግሊነ አሌ ለነ አሌ ለነ አውየዉ
ርሡእኒነ ወከልሑ ሕፃናቲነ። አሌ ለነ አሌ ለነ አንብዓ አንስቲያነ።
ወማሰነት ሀገርነ። አሌ ለነ አሌ ለነ እምዮም እስከ ተፍጻሜተ
መዋዕሊነ ምስለ ደቂቅነ። አሌ ለነ አሌ ለነ እስመ ተነሥተ ክብራ
ለወለተ ጽዮን ክብርት። ወዐብየ ክብራ ለወለተ ኢትዮጵያ ኀሰርት።
8 ተምዕዐ እግዚአብሔር ወመኑ ይሣህል። አስተራኩሶ እግዚአብሔር
ወመኑ ያነጽሕ። መከረ እግዚአብሔር ወመኑ ይትቃወማ ለምክሩ።
ፈቀደ እግዚአብሔር ወመኑ የአብዮ ለሕሊናሁ። ይቤ እግዚአብሔር
ወኩሎ ይከውን። አኅሰረ እግዚአብሔር ወአልቦ ዘያከብር። ነሥአ
እግዚአብሔር ወአልቦ ዘያገብእ። ጸልአ እግዚአብሔር ወአልቦ
ዘያፈቅር።
9 አሌ ለነ እንዘ ክቡር ስምነ። ዮምሰ ተመነነ ስምነ። አሌ ለነ እንዘ ሰብ
እ ቤት ንሕነ ኮነ ሰብአ አፍኣ። እንዘ ሰብአ ውስጥ ንሕነ ተሰደድነ
በኀጢአትነ። እስመ እግዚአብሔር ያፈቅር ንጽሐ። ካህናትኒ አበይዋ
ለንጽሕ ወአፍቀርዋ ለርኩስ። ወነቢያትኒ ገሠጹነ ወኢተገሠጽነ። ወአስምዑነ
ወኢሰማዕነ። አሌ ለነ በኃጢአትነ ተመነነ። በኀሣርነ ተቀሠፍነ።
10 መንግሥትኒ ኢይበቍዕ ዘእንበለ ንጽሕ። ወፍትሕኒ ኢይበቍዕ ዘእንበለ
ርትዕ። ወብዕልኒ ኢይበቍዕ ዘእንበለ ፍርሀተ እግዚአብሔር።
11 ካህናትኒ አፍቀሩ ነገረ ዛውዕ እምነገረ መጻሕፍት። ወአፍቀሩ ቃለ መሰ
ንቆ እምቃለ መዝሙር። ወአፍቀሩ ግብረ ዓለም እምጸሎት። ወአፍቀሩ
ቅስተ ዓለም እምቃለ መለኮት። ወአፍቀሩ ሰሐቀ ወዝሙተ እምብካየ
ሕይወት። ወአፍቀሩ መብልዐ ኀላፊተ እምጸዊም ለእግዚአብሔር። ወአፍቀሩ
መስቴ ወስካረ እምሠዊዕ ለእግዚአብሔር።

- 59 -

5 ኣቤቱ! እነሆ ዛሬም ቃልህ ኣልተዋሸም። ቤትህንም ኣንተ እየረዳህኝ ሰ
ራሁ። ቤትህንም መስራት በጨረስኩ ጊዜ የቃል ኪዳንህን ታቦት ወደ
ውስጥ ኣስገባሁዋት። ለቅዱሱ ስምህ ስላሴም መስዋእትን ሰዋሁ።
ውስጧንም መረመርከ። መለኮትህ በኣለሙ ምሉ ሲሆን ምስጋናህም ቤትን
መላ። በውስጧም ምስልህን በማየት ህዝቦችህ ተደሰትን።
6 ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እነሆ ዛሬ ሦስተኛ ኣመት ናት። በጨለማ
ላሉት ታበራ ዘንድ ብርሃንህን ከእኛ ነጠቅሃት። የተዋረዱትንም
ታከብር ዘንድ ክብራችንን ኣፈለስካት። የማያስፈራውን ኣስፈሪ
ታደርገው ዘንድ ግርማችንን ኣጠፋሃት። ህይወቱ ካንተ የራቀውን
ትሰራው ዘንድ ህይወታችንን ኣፈረስካት።
7 ወዮልኝ፤ ስለራሴ ኣለቅሳለሁ። ኣባቴ ዳዊት ሆይ! ከሙታን ተነሳ።
ስለ እመቤታችን ከእኔ ጋር ኣልቅስ። እግዚኣብሄር ቸላ ብሎናልና።
እመቤታችንን ከልጆችህ ወስዷታልና። እውነተኛ ፀሃይ ቸላ ስላለን
ወዮልን። በምድር ላይ ጎስቋሎች ሆንን። ካህናት መልካም
ኣላደረግንም። ነገስታቱም ለሙት ልጆች ፍትህ ኣላስተካከልንም።
ርትእ ከእኛ ተወስዳለች፤ ተገስፀናልምና። ወዮልን፤ ወዮታ
ይገባናል። ደስታችን ወደ ጠላቶቻችን ተመለሰች። ሞገሳችንም
ከላያችን ላይ ተረሳች። ወዮልን፤ ወዮታ ይገባናል። ጀርባችን
ለጠላቶቻችን ጦር ተሰጠ። ወዮልን፤ ወዮታ ይገባናል። ልጆቻችንም
ሽንጋዮች ሆኑብን። ለምናታልላቸውና ለምንማርካቸው ምርኮ ሆንን።
ወዮልን፤ ወዮታ ይገባናል። ባልቴቶቻችን ኣለቀሱ። ደናግሎቻችን
ተንሰቀሰቁ። ወዮልን ወዮታ ይጋባናል። ሽማግሎች ተንሰቀሰቁ፤
ህፃናቶቻችንም ኣለቀሱ። ወዮልን፤ ወዮታ ይጋባናል። የሴቶቻችን
እንባ ፈሰሰ። ኣገራችን ጠፋች። ከዛሬ እስከ ዘመናችን ፍፃሜ
ድረስ ከልጆቻችን ጋር። ወዮልን፤ ወዮታ ይገባናል። የከበረችው
የፅዮን ልጅ ክብር ተነስቷልና። የጎስቋላዋ የኢትዮጵያ ልጅ ክብር
ከፍ ብሏልና። ወዮልን፤ ወዮታ ይገባልናል።
8 እግዚኣብሄር ተቆጣ። ማንስ ይቅር ይላል? እግዚኣብሄር ኣረከሰ።
ማንስ ያነፃል? እግዚኣብሄር መከረ። ምክሩንስ ማን ይቃወማል?
እግዚኣብሄር ወደደ። ሃሳቡንስ ማን ይቃወማል? እግዚኣብሄር ኣለ።
ሁሉም ይሆናል። እግዚኣብሄር ካዋረደ ማን ያከብራል? እግዚኣብሄር
ወሰደ። የሚመልስም የለም። እግዚኣብሄር ጠላ። የሚወድም የለም።
9 የከበረ ሳለ ስማችን ተንቋልና ወዮልን። ቤተሰቦች ሳለን የውጭ ሰዎች
ሆነናልና ወዮልን። የውስጥ ሰዎች ሳለን በሃጢኣታችን ተሰደድን።
እግዚኣብሄር ንፅህናን ይወዳል። ካህናቶቻችን ግን ንፅህናን እንቢ
ኣሏት። ርኩሰትንም ወደዷት። ነቢያቶቻችን ገሰፁን። እኛ ግን ኣልተገሰ
ፅንም። ነገሩን፤ እኛ ግን ኣልሰማንም። በሃጢኣታችን ተንቀናል፤
በጥፋታችን ተገርፈናልና ወዮልን።
10 መንግስት ያለ ንፅህና፣ ፍርድም ያለ ርትእ፣ ሃብትም ያለ ፈሪሃ
እግዚኣብሄር ኣይጠቅምም።
11 ካህናት ከመፃህፍት ይልቅ ዋዛ ፈዛዛን ወደዱ። ከማህሌትም ይልቅ
የኣዝማሪን ቃል፣ ከፀሎትም ይልቅ የኣለምን ስራ ወደዱ። ከመለኮት
ቃል የከርከርን ነገር ወደዱ። ከህይወትም ልቅሶ ሳቅና ዝሙትን

www.ethiopianorthodox.org

ወአፍቀሩ ሐኬተ እምስእለት ወንዋየ እምጽዋት።
እምስብሐት። ወአፍቀሩ ንዋመ ንዝህላለ እምንቃሕ።
12 አሌ ለነ አሌ ለነ። ነገሥትኒ ተሀከይነ እምነ ትእዛዝ
ዘእግዚአብሔር። ወአፍቀርነ ነገረ መስተዛውዓን እምቃለ ካህናት።
ወገጸ አንስቲያነ ንፈቅድ ነጽሮ እምነሚሠ ገጸ እግዚአብሔር
በንስሓ። ወአፍቀርነ ነጽሮ ሕፃናቲነ እም ሰሚአ ቃለ እግዚአብሔር።
ወአፍቀርነ ተናዝዞ በእብነ ሰርድዮን እም አርትዖ ፍትሕ ለእጓለ
ማውታ። ወአፍቀርነ ነጽሮ ክብርነ እም ሰሚዐ ቃለ እግዚአብሔር።
ወአፍቀርነ ነገረ በከ እም ቃለ ማእምራን። ወአፍቀርነ ነገረ አብዳን
እምነ ሰሚዐ ነገረ ነቢያት አሌ ለነ በፈቃድነ አርኰስና ለሕይወትነ።
አሌ ለነ እስመ ዘያፈቅር እግዚአብሔር ንሥሓ ወምሕረተ ኢገበርነ።
አሌ ለነ ወሀበነ ክብረ ወበእበድነ ገደፍነ። አጥበበነ ፈድፋደ።
ወበፈቃድነ አበድነ እምነ እንስሳ ወሀበነ ብዕለ ወአንደይነ ርእስነ
እምጽዋት። ነጸርነ አፍራሲነ። ወረሳዕነ ምግባኢነ። አፍቀርነ ኀላፊተ
ወኢያእመርና ለነባሪት። ረሰይነ መዋዕሊነ ተቀጽቦ ለሕይወትነ።
ወአብደርነ ተድላ ሲሲትነ ዘይከውን ዕፅፈ እመብልዐ ሕይወት
ዘይነብር ለዓለም። ወቀጠንተ አልባስ ዘኢይበቍዕ ለነፍስ ወአእተትነ
ልብሰ ግርማ ዘለዓለም።
13 ወመኳንንቲነኒ ወአሕዛብ ይገብሩ ዘይጸልእ እግዚአብሔር ወኢያፍቀሩ
ዘያፈቅር እግዚአብሔር። ፍቅረ ቢጸሙ ወትሕትና ወየውሀት
ወምሒረ ነዳይ ወትዕግሥተ ወአፍቅሮ ቤተ እግዚአብሔር ወሰጊድ
ለወልድ። ወዘይጸልእሰ እግዚአብሔር ተጠይሮ ወአጣዕዎ ወሐቲተ
ማሪት ወመቃስም ወሰገል ወጽንጽንያ ወአቀሪኖ ወብትክ ወማውታ
ወሰርቅ ወዐመፃ ወዝሙት ወተቃንዖ ወሐቢል ወስታይ ወስካር
ወመሐላ በሐሰት ለቢጸሙ ወስምዐ ሐሰት ላዕለ ቢጸሙ ዘንተ ኵሎ
ይገብሩ ዘይጸልእ እግዚአብሔር።
14 ወበእንተ ዝንቱኬ ዘነሥአ እግዚአብሔር ለታቦተ ኪዳኑ እምኔነ
ወወሀባ ለሕዝብ እለ ይገብሩ ፈቃዶ ወሕጎ ወሥርዐቶ። ሜጠ ገጸ
እምኔነ። ወአብርሀ ገጸ ላዕሌሆሙ። ተሀየየ ኪያነ። ወአፍቀረ
ኪያሆሙ። መሐረ ኪያሆሙ። ወአጥፍአ ኪያነ በእንተ ዘነሥአ
ለታቦተ ኪዳኑ እምኔነ።
5 እስመ መሐለ መሐላ በርእሱ ከመ ኢይከልእ ክረምተ ወሐጋየ ዘርዐ
ወማእረረ ፍሬ ወተግባረ ፀሐየ ወወርኀ እንዘ ሀለወት ጽዮን ዲበ
ምድር። ወከመ ኢይትመዐዕ ለሰማይ ወምድር ኢበአይኑ ወኢበእሳት
ወከመ ኢያጥፍእ ሰብ አ ወእንስሳ ወአራዊተ አላ ዳእሙ ከመ
ይምሐር ተግባረ እደዊሁ ወከመ ያብዝኅ ምሕረቶ ላዕለ ልሕኵቱ
ወአመ ይነሥእ እግዚአብሔር ለታቦተ ኪዳኑ አሜሃ ያጠፍኦሙ ለሰ
ማያት ወምድር ወለኵሉ ተግባሩ። ወዮምኒ እስመ ተሀየየነ
እግዚአብሔር ወነሥአ እምኔነ ለታቦተ ሕጉ።
ወዘንተ እንዘ ይብል ኢየዐርፍ ብካየ ወአንብዐ እምአዕይንቲሁ።
ወአውሥአ መንፈሰ ትንቢት እንዘ ይብሎ ለምንት ከመዝ ተኀዝን
እስመ በፈቃደ እግዚአብሔር ኮነ ዝንቱ። ወይእቲኒ አኮ ለባዕድ

- 60 -

ለእግዚአብሄር ከመፆምም ሃላፊ መብልን ወደዱ። ለእግዚአብሄር ከመሰዋት
መጠጥና ስካርን ከልመና ከፋትን ወደዱ። ከምስጋና እንቅልፍን
ከጥንቃቄ ይልቅ ንዝህላልነትን ወደዋልና ወዮልን፤ ወዮታ ይገባናል።
12 ነገስታቱም በእግዚአብሄር ትእዛዝ ሰነፍን። ከካህናቱ ነገር ይልቅ
የፌዘኞችን ነገር ወደድን። እግዚአብሄርንም በንስሃ ከመፈለግ ይልቅ
የሴቶቻችን መልክ ማየትን እንወዳለን። የእግዚአብሄርን ቃል
ከመስማት ክብራችንን ወደድን። ከአዋቂዎች ቃል ይልቅ ከንቱ
ነገርን ወደድን። የነቢያትን ነገር ከመስማት የሰነፎችን ነገር
ወደናልና ወዮልን። ህይወታችንን በፈቃዳችን አርክሰናታልና
ወዮልን። እግዚአብሄር የሚወደውን ንስሃና ምህረት አላደረግንምና
ወዮልን። ክብርን ሰጠን። እኛም በስንፍናችንም ጣልነው። እጅግ
ብልሆች አደረገን። በፈቃዳችንም ከእንስሳት ይልቅ ሰነፍን።
ባለፀግነትን ሰጠን። ራሳችንንም ከምፅዋት አደሀየን። ፈረሶቻችን
አየን። ምግባራችንንም ረሳን። ሃላፊውን ወደድን። ዘላለማዊቱንም
አላወቅናትም። የህይወታችንን ዘመን እጅግ ጥቂት አደረግነው።
ከዘላለም የህይወት ምግብ ይልቅ ተድላና ደስታን፤ ምግባችንንና
ለነፍስ የማይጠቅሙ ቀጭንና ዘላለማዊ ልብስን አስበለጥን።
13 መኳንንቶቻችንና አህዛብም እግዚአብሄር የሚጠላውን ያደርጋሉ።
እግዚአብሄር የሚወደውን ወንድምን መውደድንና ትህትናን፤
ፍቅርንና ለችግረኛ መራራትን፤ ትእግስትን ሁሉ፤ ቤተ
እግዚአብሄርን መውደድንና ለእሱ መስገድን ጠሉ። እግዚአብሄር
የሚጠላውን ማስጠንቆልን፤ አምልኮ ጣኦትንና ጥንቆላን
መመርመርን፤ ሟርትን፤ ጨሌ መጣልን፤ ኮከብ ማስቆጠርን፤
ማነብነብን፤ ማጣላትንም፤ የጠነባን፤ የሞተን፤ ሌብነትን፤ አመፃን፤
ዝሙትን፤ ቅናትን፤ ሽንገላን፤ መጠጥን፤ ስካርንና ለጓደኞቻቸው
በሃሰት መማልን፤ በወንድሞቻቸው ላይ በሃሰት መመስከርን፤
እግዚአብሄር የሚጠላውን ይህን ሁሉ ያደርጋሉ።
14 እግዚአብሄር የቃል ኪዳኑን ታቦት ከእኛ የወሰዳት በዚህ ምክንያት
ነው። ፈቃዱን፤ ህጉንንና ስርአቱን ለሚያደርጉ ህዝቦች ሰጣት።
ከእኛም ፊቱን መለሰ። ፊቱንም በላያቸው አበራ። እነሱንም ይቅር
አለ። የቃል ኪዳኑንም ታቦት ከእኛ በመውሰድ እኛን አጠፋ።
15 ፅዮን በምድር ላይ እስካለች ድረስ ክረምትና በጋን፤ ዘርንና
አዝመራን፤ ፍሬንና ስራን፤ ፀሃይና ጨረቃን፤ ላይከለክል በራሱ
ምሏልና። ፅዮን በምድር ላይ እስካለች ድረስ የእጁን ስራ ሊምርና
በስራውም ላይ ምህረቱን ሊያበዛ እንጂ ሰማይና ምድርን በጥፋት
ውሃም ቢሆን፤ በእሳትም ቢሆን፤ ሰውንና እንስሳንም፤ አራዊትንም
ላይቀጣ በራሱ ምሏልና። እግዚአብሄር የቃል ኪዳኑን ታቦት
በወሰደ ጊዜ ያን ጊዜ ሰማይንና ምድርን፤ የእጁን ስራ ሁሉ
ያጠፋቸዋል። እነሆ ዛሬም እግዚአብሄር ቸል ብሎናል። ከእኛ
የቃል ኪዳኑን ታቦት ወስዷታልና።"
16 ይህንንም ሲል ልቅሶና ከአይኑም እንባ አያቋርጥም ነበር።
የትንቢት መንፈስም መልሶ "ይህ በእግዚአብሄር ፈቃድ ሆኗልና

www.ethiopianorthodox.org

ዘተውህበት አላ ለወልድከ ቀዳሜ በከ'ርከ ዘይነብር ዲበ መንበረ ዳዊት
አቡከ።
እስመ መሐለ እግዚአብሔር ለዳዊት በጽድቅ ወኢይኔሥሕ።
ከመ እምፍሬ ከርሡ ያነብር ዲበ መንበሩ እስከ ለዓለም በውስተ ታቦተ
ኪዳኑ ጽዮን ቅድስት
ወእሬስዮ ልዑለ እምነገሥተ ምድር።
ወመንበሮሂ ከመ መዋዕለ ሰማይ።
ወከመ ሥርዓተ ወርኅ እስከ ለዓለም።[59]
17 ወበሰማያትኒ ዘይነብር ዲበ መንበረ መለኮት በሥጋ ይኴንን ሕያዋነ
ወሙታነ እስከ ለዓለም ወይገንዩ ሎቱ መላእክት ወሰብእ።ወይሴብሐ
ኩሉ ልሳን ወይሰግዱ ሎቱ ኩሉ ብርክ በቀላያት ወበአፍላግ
ወበዝንቱ ተናዘዝ ወግባእ ቤተከ ወኢታኅዝን ልበከ ፍጹመ።
18 ወበዝንቱ ተናዝዞ ይቤ ይኩን ፈቃዱ ለእግዚአብሔር ወአኮ ፈቃደ
ሰብእ።
19 ወካዕበ አስተርአዮ መልአክ ገሃደ ወይቤሎ ወአንተሰ ሐነጽከ ቤተ
እግዚአብሔር ወትከውነከ ምክሐ ይእቲ ወምስማከ ለእመ ዐቀብከ
ትእዛዞ ወኢያምለከ ባዕደ አማልክተ። ትትፈቀር በኀበ እግዚአብሔር
ከመ ዳዊት አቡከ።

## ፳ወ፩ በእንተ ግብአተ ሰሎሞን ኢየሩሳሌም

1 ወእምዝ አተወ ሀገረ ኢየሩሳሌም ወበከየ በህየኒ ምስለ አእሩገ
ኢየሩሳሌም ብካየ ዐቢየ በውስተ ቤተ እግዚአብሔር። ወእምድኅረዝ
ተአኀዙ ንጉሥ ምስለ ሳዶቅ ካህን በከዋውዲሆሙ ወበከዩ መሪረ
በውስተ ምንባሪሃ ለጽዮን።
2 ወአርመሙ እምድኅረ ጉንዱይ ሰዓት። ወተንሥኡ መኳንንት
ወተናገርዎ ለንጉሥ እንዘ ይብሉ ኢትኅዝን እግዚእነ በእንተዝ ነገር።
እስመ ንሕነ አእመርነ ዘእንበለ ኀበ ፈቀደ እግዚአብሔር ኢትነብር
ጽዮን እምቀዳሚ እስከ ደኃሪ። ወአልቦ ዘይከውን ዘእንበለ በፈቃደ
እግዚአብሔር።
3 ወዘበእንተ ጽዮንሂ ቀዲሙ በመዋዕለ ኤሊ ካህን ዘእንበለ ይስአሉ
አበዊነ ንጉሠ ዔወውዋ ኢሎፍሊ በውስተ ትዕይንት ሶበ ተሀየዮሙ
እግዚአብሔር ለእስራኤል በውስተ ጸብእ። ወወድቁ ካህናቲሃ አፍኒን
ወፊንሐስ በአፈ ኀፂን። ወነሥእዋ ኢሎፍሊ ለታቦተ ሕጉ
ለእግዚአብሔር። ወአእተውዋ ውስተ ሀገሮሙ። ወወደይዋ ውስተ ቤተ
አምላኮሙ ዳጎን።
4 ወተሰብረ ወተንኰለ ዳጎን ወኮነ ከመ ፀበል። ወምድሮሙ ኮነት
በድወ በአናጹት። ወበልዐ ኵሎ ፍሬ ምድሮሙ ወነፍስቶሙኒ ኮነ
ጸልአ ወሕበጠ።
5 ወአስተጋብኡ ማርያኒሆሙ ወመሰንግላኒሆሙ ወረአይተ ከዋክብቲሆሙ
ወተሰእልዎሙ ወይቤልዎሙ እፎ ንድኅን እምዝ ጸልዕ ወምንዳቤ
ዘረከበነ ለነ ወለሀገርነ።

[59] መዝ.72፥22 ፥89፥3፤132፥1

- 61 -

በአባትህ በዳዊት ዙፋን ላይ ለሚቀመጠው ለበኩር ልጅህ ነው
እንጂ ለባእድ የተሰጠች አይደለችምና ለምን እንደዚህ ታዝናለህ?
እግዚአብሄር ለዳዊት 'በቃል ኪዳኑ ታቦት በቅድስት ፅዮን ውስጥ
በዙፋኑ ላይ ከሆዱ ፍሬ ለዘላለም እንደሚያስቀምጥ ከምድር
ነገስታት ሁሉ ከፍ ከፍ አደርገዋለሁ። በእውነት ዙፋኑንም እንደ
ሰማይ ከፍታና እንደ ጨረቃ ስርአት አደርገዋለሁ'[59] ሲል ምሏልና።
17 በሰማያትም በመለኮት ዙፋን ላይ የሚቀመጠው በስጋ ህያዋንና
ሙታንንም ይገዛል። መላእክትና ሰዎችንም ይገዙለታል። አንደበትም
ሁሉ ያመሰግነዋል። በወንዞችና በምንጮችም ጉልበት ሁሉ
ይንበረከክለታል። በዚህ ተፅናና። ወደ ቤትህም ተመለስ። ልብህንም
ፈፅመህ አታሳዝነው" አለው።
18 በዚህም ተፅናንቶ "የእግዚአብሄር እንጂ የሰው ፈቃድ አይሁን" አለ።
19 ደግሞም የእግዚአብሄር መልአክ በገሃድ ተገለፀለት። "አንተ ቤትን
ሰርተሃል። ትእዛዝን ከጠበቅህና ባእድ የሆኑ አማልክትን ካላመለክህ
ይህች መመኪያ ትሆንልሃለች። በእግዚአብሄር ዘንድም እንደ አባትህ
እንደ ዳዊት ትወደዳለህ" አለው።

## ፳፩ ሰሎሞን ወደ ኢየሩሳሌም ስለ መመለሱ፤

1 ከዚህ በሁዋላ ኢየሩሳሌም ገባ። ከዚያም ከኢየሩሳሌም ሽማግሎች
ጋር በእግዚአብሄር ቤት ውስጥ መራራ ልቅሶን አለቀሱ። ንጉሱና
ካህኑ ሳዶቅም አንገት ለአንገት ተያይዘው በፅዮን መኖሪያ ውስጥ
መራራ ልቅሶ አለቀሱ። ከጥቂት ጊዜ በሁዋላም ዝም አሉ።
2 ሽማግሎችም ተነሱ። ንጉሱንም "ጌታችን ሆይ! ስለዚህ ነገር
አትዘን። እግዚአብሄር የፈቀደው ቦታ ካልሆነ በቀር ፅዮን
እንዳትቀመጥ አውቀናልና። ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻውም
ቢሆን ያለፈቃደ እግዚአብሄር የሚሆን የለም።
3 ስለ ፅዮን አስቀድሞ በካህኑ በኤሊ ዘመን ገና አባቶቻችን ንጉስን
ሳይጠይቁ፤ እግዚአብሄር እስራኤላውያንን በጦርነት ውስጥ ችላ
ባላቸው ጊዜ ኢሎፍላውያን የእግዚአብሄርን ታቦተ ህግ ወሰዷት።
ወደ አገሮቻቸውም አስገቧት። በአምላካቸውም በዳጎን ቤት
ጨመሯት።
4 ዳጎንም ተሰበረ። ጠፋም እንደ አፈርም ሆነ። ምድራቸውም
በአይጦች ምድረ በዳ ሆነች። የምድራቸውን ፍሬ ሁሉ በሉ።
ሰውነታቸውም ቁስልና እበጥ ሆነ።
5 ማርተኞቻቸውንና ጠንቋዮቻቸውን፤ ኮከብ ቆጣሪዎቻቸውንም ሰበሰቡ።
'እኛንና አገራችንን ካገኘው ከዚህ ቁስልና ችግር እንዴት ልንድን
እንችላለን' ሲሉም ጠየቁአቸው።

[59] መዝ. 72፥2፤ 89፥31፤32፥1

www.ethiopianorthodox.org

6 ኀለዩ እሙንቱ መሰግላን ተግሒሶሙ እንተ ባሕቲቶሙ።
ሰገላቲሆሙ። ወኀለዩ ወሐሰቡ ወመከሩ ዘከመ እፎ ይድኀኑ እምንዳቤ
ሀገሮሙ ወነፍስቶሙ። ወረከቡ ዘንተ ከመ በእንተ ጽዮን ዘረከቦሙ
ዝንቱ መቅሠፍት ሎሙ ወለሀገሮሙ።
7 ወሖሩ ኀበ ነገሥቶሙ ወመኳንንቲሆሙ። ወይቤልዎሙ ዝንቱ ኵሉ
ዘረከበክሙ በእንተ ጽዮን ሰማያዊት ታቦተ ሕግ ለእግዚአብሔር።
ወይእዜኒ አእምሩ ዘከመ ታገብእዋ ውስተ ሀገራ ወብሔራ ወቤታ
ወአኮ ዕራቃ ዘንፌንዋ አላ ሀብዋ ሞፃ ከመ ትሠረይ ዛቲ
ኀጢአትክሙ ወታሰስል ምንዳቤክሙ ሶበ ገብአት ጽዮን ውስተ
ሀገራ። ወሶበሰ ኢፈነውክምዋ ውስተ ሀገራ ኢኮነ ሠናየ አንብሮታ
ኀቤክሙ። አላ ትትቀሠፉ ኵልክሙ እስከ ተኀልቁ።
8 ወይቤልዎሙ ነገሥቶሙ ወመኳንንቲሆሙ ለማርያኒሆሙ። ምንተኬ
ዘትብሉ ዘንሁባ ሞፃ ወከመ እፎ ንፌንዋ ጠይቀክሙ ንግሩነ ዘከመ
ንረሲ።
9 ወመከሩ ካዕበ ማርያነ ኢሎፍሊ ወይቤልዎሙ ለነገሥቶሙ
ወለመኳንንቲሆሙ ግበሩ ላቲ በርእሰ አብያቲክሙ ወርቀ ሞፃ ፭
አምሳሉ በከመ አጥፍኡ ሀገረክሙ ወአምሳለ ነፍስተ ብእሲ ፭ በከመ
ሐመምክሙ ነፍስተክሙ በጸልዕ ወሕበጥ እንተ ኀበ ቀኅልፈትክሙ።
10 ወገብሩ በከመ አዘዝዎሙ ኢሎፍሊ ፻፳ ሞጻ ዘወርቅ። ወወሀብዋ
ለጽዮን። ወካዕበ ይቤልዎሙ ዘከመ እፎ ንፌንዋ ወመኑ ትብሉ
ዘይወስዳ ውስተ ሀገራ።
11 ወይቤልዎሙ ካዕበ መሰንግላነ ኢሎፍሊ ያምጽኡ ክልኤ ናቃት እለ
ተበኵራ በእሐቲ ጊዜ። ወይርሐኑ ሰረገላተ ዲቤሆሙ። ወይክልኡ
እጐላቲሆሙ። ወይዕጽው ውስተ ቤት ወይፅምድዎን። ይኅድግዎን
ይሑራ ኀበ ፈቀዳ። ወለእመ አርትዓ ለኢየሩሳሌም ዮጊ ነአምር ከመ
ተሣህላ እግዚአብሔር ለምድርነ። ወለእመሰ አውከካ ወአንጌገያ
ወፈቀዳ ገቢአ ድኅሬሆን ነአምር ከመ ተምዕዐነ እግዚአብሔር
ወኢያእተተ መቅሠፍቶ እስከ ያጠፍአነ ኪያነሂ ወሀገረነ።
12 ወገብሩ በከመ አዘዝዎሙ ማርያነ ኢሎፍሊ ለመኳንንቲሆሙ
ወአስተፋነውዋ ወገነዩ ላቲ።
13 ወእምዝ አርትዓ እማንቱ አግማል ለፍኖተ ብሔረ ይሁዳ። ወበጽሓ
ውስተ ዐውደ እክል። ወተቀበልዋ ቤተ ዘመድከ። ወእለሰ ኢተቀበልዋ
ሰብአ ቤተ ዳን እለ ኢገነዩ ላቲ እንዘ ይሬእይዋ አኅለቆሙ
እግዚአብሔር በመዐት። ወለእሙንቱሰ ዕፀወ ሰረገላ ሠፀርዎን።
ወለእማንቱኒ አግማል ረሰይዎን መሥዋዕተ ወገብአት ጽዮን ውስተ
መካና።

- 62 -

እነዚያ ጠንቋዮችም ለብቻቸው ፈቀቅ ብለው አሰቡ።
6 ማረተኞቻቸውንም አመጡ። ከአገራቸውና ከሰውነታቸውም' መከራ
እንዴት እንደሚድኑ መላልሰው አሰቡ። መከሩም። ይህም መቅሰፍት
እነሱንና አገራቸውን በፅዮን ምክንያት እንዳገኛቸው ደረሱበት።
ወደ ነገስታቶቻቸውና መኳንንቶቻቸውም ሄዱ። ይህ ሁሉ ያገኛቸው
7 በእግዚአብሄር ታቦተ ህግ ማለትም በሰማያዊቷ ፅዮን ምክንያት
እንደሆነ ነገሯቸው፣ አሏቸውም። 'እነሆ አሁንም እንዴት ወደ አገሯና
ወደ ቤቷ እንደምትመልሷት አስቡ። የምትመልሷት እንዲሁ
አይደለምና። ፅዮን ወደ አገሯ በተመለሰች ጊዜ ይህች ሃጢያታችሁ
እንድትሰረይላችሁና መከራችሁንም እንድታስወግድላችሁ የበደልን
መስዋእት አቅርቡላት። ወደ አገሯ ካልመለሳችሁዋትና በእናንተ
ዘንድ ካስቀመጣችሁዋት መልካም አይሆንም። ሁላችሁም እስክታልቁ
ድረስ ትቀሰፋላችሁና' አሉዋቸው።
ነገስታቶቻቸውና መኳንንቶቻቸውም ጠንቋዮቻቸውን 'የምናቀርብላት
8 የበደል መስዋእት ምን መሆን አለበት ነው የምትሉት? ስለ
አላላኩም እንዴት እንደምናደርግ ጠይቃችሁ ንገሩን' አሏቸው።
9 የኤሎፍሊ ማርተኞችም እንደገና መከሩ። ለነገስታቱና ለመኳንንቱም
'አገራችሁን ባጠፉት አይጦችና በስልሳ ሰዎችም አምሳል ስልሳ
የወርቅ የበደል መስዋእትንና ባልተገረዘው ሃፍረተ ስጋችሁ
አጠገብም ባመሟችሁ አምሳል ስልሳ የወርቅ እባጮችን አድርጉ።
በሰረገላውም ላይ አኑሩት' አሏቸው።
ኤሎፍላውያንም ማርተኞቻቸው እንዳዘዟቸው መቶ ሃያ የወርቅ
10 የበደል መስዋእትን አደረጉ። ለፅዮንም አቀረቡላት። ደግመውም
'እንዴት እንደምንልካትና ወደ አገሯስ የሚወስዳት ማን ነው
የምትሉት' አሏቸው።
የኢሎፍሊ ጠንቋዮችም 'በአንድ ጊዜ የእናታቸውን ማህፀን የከፈቱ
11 ሁለት ላሞችን አምጡ። በላያቸውም ላይ ሰረገላ ይጫኑአቸው።
እንቦሶቻቸውንም ለይተው ወደ ቤት ይመልሷቸው። ጠምደውም
ወደ ፈቀዱበት ይሄዱ ዘንድ ይተዋቸው። ወደ ኢየሩሌም ከአቀኑ
እነሆ እግዚአብሄር ምድራችንን ይቅር እንዳላት እናውቃለን።
ቢደክሙና ቢቅበዘበዙ ወደ ሁዋላቸውም መመለስን ቢወዱ ግን
እግዚአብሄር እንደ ተቆጣንና እኛንና አገራችንን እስኪያጠፋን
ድረስ መቅሰፍቱን እንዳላስወገደ እናውቃለን' አሏቸው።
እነሱም የኢሎፍሊ ማርተኞች መኳንንንቶቻቸውን እንዳዘዟቸው
12 አደረጉ። ላኳት፤ ሰገዱላትም።
13 ከዚያ በሁዋላ እነዚያ ላሞች ወደ አገረ ይሁዳ አቀኑ። ከአውድማ
ቦታም ደረሱ። ቤተሰቦችም ተቀበሏት። እያዩ ያልተቀበሏትንና
ያልሰገዱላትን የዳን አገር ሰዎችን ግን እግዚአብሄር በመአቱ
ጨረሳቸው። እነዚያን የሰረገላ እንጨቶች ግን ሰንጥቀው ላሞቹን
አቃጠሉባቸው። ፅዮንም ወደ ቦታዋ ተመለሰች።

www.ethiopianorthodox.org

14 ወአሜሃ እንዘ ሀለወት ውስተ ቤት ተልእከ ሳሙኤል ነቢይ
ወተከሥተ ሎቱ ራእይ ወትንቢት። ወኮነ ዘያሠምሮ ለእግዚአብሔር
በኵሉ ግብሩ። ወኰነኖሙ ለእስራኤል ፵ወ፰ ዓመተ።
15 ወእምድኅሬሁ ሰአሉ ሕዝብነ ያንግሥ ሎሙ እግዚአብሔር ከመ
አሕዛብ እለ ዐውዶሙ። ወቀበዖ ሳሙኤል ነቢይ ለሳኦል ንጉሥ።
ወውእቱኒ ነግሠ ፵ ዓመተ። ወለሊሁሰ እምሕዝበ ብንያሚ እንተ
ትንዕስ በበትር እምሕዝበ እስራኤል። ወቀበዖ ካዕበ ሳሙኤል ነቢይ
ለአቡከ ዳዊት።
16 ወሶበ ተአኀዙ ቀትለ ኢሎፍሊ ምስለ ሳኦል ንጉሥ ተመውዐ ሳኦል
ወሞተ ምስለ ዮናታን ወልዱ። ወዘተርፉ ደቂቀ ፈቀዱ ከመ
ይንሥእዋ ለጽዮን ሶበ አእመሩ ሞተ አቡሆሙ ወእኁሆሙ።
17 ወእምዝ ሶበ ፈቀዱ ኀቢእታ ወአግዕዞታ እስከ ቁላተ ጌላቡሄ ከመ
ኢይንሥእሙ አቡከ ዳዊት። ወዐበየቶሙ ተንሥእ እስከ ይመጽእ
አቡከ ዳዊት ወይንሥአ እምሀገሮሙ ኢበመሥዋዕት ወኢበዕጣን
ወአጸንሕሖ እስመ ኢይትከሀል ነሢእታ ለጽዮን ዘእንበለ ፈቃዳ
ወፈቃደ እግዚአብሔር።
18 ወካዕበ አቡከ ሶበ አርትዐ ወነግሠ ላዕለ እስራኤል ነሥአ እምሀገረ
ሰማርያ ወአብአ ዝየ ኢየሩሳሌም እንዘ ያፅሕስ በእገሪሁ በቅድሜሃ
ወይጠፍሕ በእደዊሁ በእንተ ፍሥሓሃ እስመ ተንሥአት ሎቱ ከመ
ትምጻእ ሀገረ ዳዊት አቡከ።
19 ወዝንቱሰ ዘትብል በእንተ ዘሖረት ጽዮን ሀገሮሙ ለብሔረ
ኢትዮጵያ። ለእመ ፈቀደ እግዚአብሔር ወፈቀደት ለሊሃ ኢይክል
ከሊእታ ወኢአሐዱ። እስመ በፈቃዳ ተሐውር ወበፈቃዳ ትገብእ።
ለእመ ሠምረ እግዚአብሔር ወለእመሰ ኢገብአት ይኩን ሥምረቱ
ለእግዚአብሔር። ወለነሰ ለእመ ፈቀደ እግዚአብሔር ሀለወት ኀቤነ
ኢየሩሳሌም ዘሐነጽከ ለነ ቤተ እግዚአብሔር።
20 ወይእዜኒ ኢታኀዝን ልበከ ወተናዘዝ በዘንነግረከ። ወጥበብሰ
እምኀቤከ ይእቲ ዘሠረፀት ዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል።
እስመ ነኪር ለጥበብ ከመ ማኅቶት። ለፀሐይ ዘኢይበቍዕ ወከመ
ብሒዕ ወዕጉስታር ለመዐር ኢይበቍዕ። ከማሁ ነገሮሙ ለአብዳን
በላዕለ ጠቢብ ኢይበቍዕ። ከመ ጢስ ለዐይን ወከመ ቆዕ ለስነን
ከማሁ ኢይበቍዕ በላዕለ ጠቢብ ነገረ አብዳን።

## ፷ወ፪ በእንተ ዘአውሥኦሙ ሰሎሞን

ወአውሥኦሙ ሰሎሞን ንጉሥ ወይቤሎሙ ስምዑኒ ዘእነግረክሙ ኪያየ
ሶበ ወሰደኒ እንዘ እጸውር ኪያሃ ምንት እምተሰእኖ ለእግዚአብሔር።
ወኪያክሙኒ ሶበ ይወስደክሙ ጸዊረክሙ ኪያሃ ምንት እምተሰእኖ
ለእግዚአብሔር። ወሶበሂ ያወርሶሙ ሀገረነ ወይሜርወነ ኪያነ ምንት
እምተሰእኖ ለእግዚአብሔር። እስመ ኵሉ ሎቱ ወአልቦ ዘየአብያ
ለፈቃዱ። ወአልቦ ዘይትዐደው እምትእዛዙ በሰማይ በላዕሉ ወበምድር
በታሕቱ። ንጉሥ ውእቱ ዘኢይሰዐር መንግሥቱ ለዓለመ ዓለም
አሜን።

- 63 -

14 በቤትም እያለች ነቢዩ ሳመኤል ተላከላት። ራእይና ትንቢትም
ተገለፀለት። እግዚኣብሄርንም በስራው ሁሉ የሚያስደስተው ሆነ።
እስራኤልንም ኣርባ ስምንት ኣመታት ገዛቸው።
15 ከዚህ በሁዋላ ህዝባችን እግዚኣብሄር ከፊቱ እንዳስወጣቸው ኣህዛብ
ንጉስን ያነግስላቸው ዘንድ ለመኑ። ነቢዩ ሳሙኤልም ንጉስ ሳኦልን
ቀባው። እሱም ኣርባ ኣመት ነገሰ። ከእስራኤል ህዝብ በሃይል
ከምታንሰው ከብንያም ወገን ነበር። ሁለተኛም ነቢዩ ሳሙኤል
ኣባትክን ዳዊትን ቀባው።
16 ኢሎፍላውያንም ከሳኦል ጋር ጦርነት በተጋጠሙ ጊዜ ሳኦል ተሸነፈ።
ከልጁ ከዮናታንም ጋር ሞተ። የቀሩትም ልጆችህ የኣባታቸውንና
የወንድማቸውን ሞት ባወቁ ጊዜ ፅዮንን ይወስዱ ዘንድ ወደዱ።
17 ከዚህ በሁዋላ እነሱ ኣባትህ እንዳይዛቸው ታቦተ ፅዮንን መሸከምንና
እስከ ጌላቡሄ ቆላ ድረስ መጓዝን በወደዱ ጊዜ ኣባትህ ዳዊት
እስኪመጣና ከኣገራቸው እስኪወስዳት ድረስ መነሳትን እንቢ
ኣለቻቸው። በመስዋእትም ቢሆን፣ በእጣንም ቢሆ፣ን በሚቃጠል
መስዋእትም ቢሆን እንቢ ኣለቻቸው። ፅዮንን ያለፈቃዷ መውሰድ
ኣይቻልምና።
18 ደግሞም ኣባትህ ባሸነፈና በእስራኤል ላይ በነገሰ ጊዜ በደስታው
ምክንያት በፊቷ በእግሩ እያሸበሸበና በእጁ እያጨበጨበ ከሰማርያ
ኣገር ወደዚሁ ወደ ኢየሩሳሌም ኣመጣት። ወደ ኣባትህ ወደ
ዳዊት ኣገር ለመምጣት ተነስታለታለችና።
19 ወደ ኢትዮጵያውያን ኣገር ሄደች ስለምትለው እግዚኣብሄር
ከፈቀደና እሷም ከወደደች ኣንድም የሚከለክላት የለም። በፈቃዷ
ትሄዳለች፤ በፈቃዷም ትመለሳለችና እግዚኣብሄር ከወደደና
ካልተመለሰች የእግዚኣብሄር ፈቃድ ይሁን። ለእኛ ግን እግዚኣብሄር
ከወደደ በእኛ ዘንድ ኢየሩሳሌም ውስጥ ኣንተ የሰራህልን
የእግዚኣብሄር ቤት ኣለች።
20 ዛሬም ልብህን ኣታሳዝነው። በምነግርህም ተፅናና። የእስራኤል
ኣምላክ እግዚኣብሄር የሰጠህ ጥበብ ግን ከኣንተ ሰረፀች። ማድነቅ
ለጥበብ፣ መብራት ለፀሃይ፣ መራራ፣ ሆምጣጤና እሬት ለማር
እንዳይጠቅመው የሰነፎችም ነገር በጥበበኞች ላይ እንዲሁ ነው።
ጢስ ለኣይን፣ ጮርቃም ለጥርስ እንደሆነ የሰነፎችም ነገር በጠቢባን
ላይ እንዲሁ ኣይጠቅምም" ኣለው።

## ፷፪ ሰሎሞን እንደ መለሳቸው

1 ንጉስ ሰሎሞን መልሶ "የምነግራችሁን ስሙን። እሷን ኣሸክሞ እኔን
ቢወስደኝ ኖሮ ለእግዚኣብሄር ምን በተሳነው ነበር? እናንተስ እሷን
ኣሸክሞ ቢወስዳችሁ ኑሮ ለእግዚኣብሄር ምን በተሳነው ነበር።
ኣገራችንንስ ቢያወርሳቸውና እኛንስ በነቀለን ለእግዚኣብሄር ምን
በተሳነው ነበር? ሁሉ የእሱ ነውና ፈቃዱንስ የሚቃወማት ማነው?
በላይ በሰማይ፣ በታችም በምድር ትእዛዝን የሚተላለፍ ማነው?

www.ethiopianorthodox.org

2 ወባሕቱ ንሑር ንትጋነይ በውስተ ቤተ እግዚአብሔር። ወሖሩ
ሊቃውንተ እስራኤል ምስለ ንጉሦሙ ውስተ ቤተ እግዚአብሔር።
ወቦኡ ውስተ ቅድስተ ቅዱሳን ወሰአሉ ወተጋነዩ ወበፅዑ
ለእግዚአብሔር። ወሰሎሞንሂ በከየ በውስተ ምንባሪሃ ለጽዮን ሰ
ማያዊት ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር። ወበከዩ ኵሎሙ ምስሌሁ
ወእምድኅረ ሕቅ አርመሙ።
3 አውሥአ ሰሎሞን ወይቤሎሙ ኀድጉኬ ከመ ኢይትመከሑ ቈላፋን
ሕዝብ ላዕሌነ ወኢይበሉነ ተነስተ ክብርሙ። ወኀደጎሙ
እግዚአብሔር። ኢትክሥቱ እምዝ ዳግመ ለባዕዳን ሕዝብ።
4 ወለእሉሂ አልዋሕ እለ ስሙካን ወልጹቃን ዝየ ንሢሞን ወንልብጦን
በወርቅ። ወናሠርግዎን በአምሳለ እግዝእትነ ጽዮን። ወመጽሐፈ ሕግሂ
ናንብር ውስቴታ።
5 ወሀለወት ኀቤነ ኢየሩሳሌም እግዓዚት እንተ በሰማያት መልዕልቴነ
ዘርእየ ያዕቆብ አቡነ። ወእምታሕቴሃ ዛቲ ይእቲ አንቀጸ ሰማይ
እንተ በምድር ኢየሩሳሌም።
6 ለእመ ገበርነ ፈቃዶ ለእግዚአብሔር ወሥምረቶ ይሄሉ እግዚአብሔርኒ
ምስሌነ። ወያነግፈነ እምእደ ፀርነ ወእምእደ ኵሎሙ እለ ይጸልኡነ።
ወይኩን ፈቃዱ ለእግዚአብሔር ወአኮ ፈቃደ ዚአነ። ወይኩን
ሥምረተ እግዚአብሔር ወአኮ ሥምረተ ዚአነ።
7 ወበይእቲሰ አሕዘዘነ። ወባሕቱ እምይእዜሰ ያቈርር መዐቶ እምኔነ።
ወኢየኀድገነ ለጸላእትነ። ወኢያርኅቅ ሣህሎ እምኔነ። ተዘኪሮ ኪዳነ
ዘምስለ አበዊነ አብርሃም ወይስሐቅ ወያዕቆብ። ኢይሔሱ ቃሎ።
ወኢይዔምፅ ኪዳኖ ከመ ኢያማስን ዘርዖሙ ለአበዊነ።

## ፳ወ፫ ኀበ ኀብሩ ዐበይተ እስራኤል

1 ወእምዝ አውሥእዎ መላህቅተ እስራኤል ወይቤልዎ ትኩን ሥምረትከ
ወሥምረተ እግዚአብሔር አምላክከ። ወንሕነሰ አልቦ ዘንትዐደው
እምቃልከ ወኢናየድዖሙ ለባዕድ አሕዛብ ከመ ተነሥአት ጽዮን
እምኔነ። ወዐቀሙ ዘንተ ኪዳነ በውስተ ቤተ እግዚአብሔር መላህቅተ
እስራኤል ምስለ ንጉሦሙ ሰሎሞን እስከ ይእዜ።
2 ወሰሎሞንሰ ነበረ እምድኅረ ተነሥአት ጽዮን እምኔሁ ፲ወ፩
ዓመተ። ወእምዝ አእተተ ልቦ እምፍቅረ እግዚአብሔር ወረስዐ ጥበቦ
እምብዝኀ ፍቅረ አንስት። ወአፍቀራ ፈድፋደ ለወለተ ፈርዖን ንጉሠ
ግብጽ እንተ ስማ ማቅሟራ። ወአእተዋ ውስተ ቤቱ ዘገብረ አምሳለ
ፀሐይ ወወርኅ ወከዋክብት ውስተ ጠፈራ ዘያበርህ ሌሊተ ከመ
መዐልት። ወሥረዊሁ ብርት ወተድባቡ ብሩር ወጸፍጸፉ አረር
ወመንደቀ እብኑ አፍራጽ። በአሥዋር አሕማር በአብያጽ አክዶር
ወጸፍጸፉኒ አብላቀ ሶፎር ወእብነ ሰርድዮን።

- 64 -

መንግስቱ የማይሻር ንጉስ ነው። ለዘላለሙ በእውነት። ኣሜን። ነገር
ግን እንሂድና በእግዚኣብሄር ቤት ምስጋና እናቅርብ" ኣላቸው።
2 የእስራኤል ሊቃውንትም ከንጉሳቸው ጋር ወደ ቤተ እግዚኣብሄር
ሄዱ። ከቅድስተ ቅዱሳንም ውስጥ ገቡ። ለመኑ፤ ኣመሰገኑ።
ለእግዚኣብሄርም ተሳሉ። ሰሎሞንም በሰማያዊቷ ፅዮን ማለትም
በእግዚኣብሄር ታቦተ ህግ መኖሪያ ውስጥ ኣለቀሰ። ሁሉም ከእሱ
ጋር ኣለቀሱ። ከጥቂት ጊዜ በሁዋላም ዝም ኣሉ።
3 ሰሎሞንም መልሶ ኣላቸው። "ክብራቸው ፈረሰ። እግዚኣብሄርም
ተዋቸው ብለው ያልተገረዙት ወገኖች በላያችን ላይ እንዳይመኩ
ተውት፤ ከእንግዲህ በሁዋላ ለሌሎች ወገኖች ኣትግለፁ።
4 እነዚህን የተጠጋጉና የተያያዙ ጠፍጣፋ ገበታዎች ግን ኣሁኑኑ
እንቀድሳቸው። በወርቅም እንለብጣቸው። በእመቤታችን በፅዮን
ምሳሌም እንሸልማቸው። በውስጧም የህጉን መፅሃፍ እናስቀምጥ።
5 ኣባታችን ያእቆብ ያያትና በላያችን ማለትም በሰማያት ያለችው
እመቤቲቱ ኢየሩሳሌምም በእኛ ዘንድ ኣለች። ይህችውም ከበታቹ
ማለትም በምድር ያለችውንና የሰማይ ደጅ የሆነችው ኢየሩሳሌም ናት።
6 እግዚኣብሄር የሚወደውንና ፈቃዱንም ብናደርግ እግዚኣብሄርም
ከእኛ ጋር ይሆናል። ከጠላቶቻችንና ከሚጠሉን ሁሉ እጅ
ይታደገናል። የእግዚኣብሄር ፈቃድ እንጂ የእኛ ፈቃድ ኣይሁን።
እግዚኣብሄር የወደደው እንጂ እኛ የወደድነው ኣይሁን።
7 በዚህች ግን ኣሳልፎ ሰጠን። ዳሩ ግን ከእግዲህ መኣቱን ከእኛ
ያቀዝቅዝልን። ለጠላቶቻችንም ኣይተወን። ይቅርታውንም ከእኛ
ኣያርቅ። ከኣባታችን ከኣብርሃምና ከይስሃቅ ከያእቆብም ጋር
ያደረገውን ቃል ኪዳን ኣስቦ ይቅርታውን ከእኛ ኣያርቅ። ቃሉን
ኣይዋሽም። የኣባቶቻችንን ዘራቸውን ላያጠፋ በገባው ቃል ኪዳን
ላይም ኣይበድልም። "

## ፳፫ የእስራኤል ታላላቆች እንደ ተባበሩ፣

1 ከዚህ በሁዋላ የእስራኤል ሽማግሎች መልሰው ኣሉት። "የኣምላክህ
የእግዚኣብሄር ፈቃድ ይሁን። እኛም ከቃልህ የምንተላለፈው ነገር
የለም። ፅዮንም ከእኛ እንደ ተወሰደች ለሌላ ህዝብ ኣንነግርም። "
የእስራኤል ሽማግሎችም ይህንን ቃል ኪዳን ከንጉሳቸው ጋር እስከ
ዛሬ ድረስ ጠብቀዋል።
2 ሰሎሞንም ፅዮን ከእሱ ከተወሰደች በሁዋላ ኣስራ ኣንድ ኣመት
ቆየ። ከዚህ በሁዋላ ልቡን ከእግዚኣብሄር ፍቅር መለሰ። በሴ
ቶችም ፍቅር ብዛት ጥበቡን ረሳው። ይልቁንም ስሟ ማቅሳራ
የተባለችውን የግብፁን ንጉስ የፈሮንን ልጅ ፈፅሞ ወደዳት።
እሷንም ጠፈሩን ሌሊት በሚያበሩት በፀሃይ፣ በጨረቃና በከዋክብት
ኣምሳል፣ ጣራውን በብር፣ መሰረቱን ከእርሳስ ማእድን፣ የህንፃውን
ኣሰራር ኣስዋፅ በተባሉ የከበሩ ድንጋዮችና በኣህማር፣ በኣረንጓዴና
በኣብያጽ፣ ምንጣፉም ሶፎርና ሰርድዮን በተባሉ የከበሩ ድንጋዮች

www.ethiopianorthodox.org

ወየሐውር ወይነብር ሀየ በእንተ ፍቅረ ቤቱ ወብእሲቱ ማቅሣራ ወለተ ፈርዖን ንጉሠ ግብጽ።
ወይእቲሰ ባቲ ጣዖታተ ዘወሀባ አቡሃ ከመ ትስግድ ሎሙ። ወበእንተዝ እንዘ ይሬእያ ትሠውዕ ወትሰግድ ሎሙ። ወኢገሠጻ ወኢኀደጋ ሰሎሞን። ወበእንተዝ ተምዕዖ እግዚአብሔር ወአርስዮ ጥበቢሁ።
ወይእቲሰ አፈድፈደት ሠዊዐ ወሰጊደ ወተውኔተ በከመ እበዱሙ ለግብጻውያን። ወይሰግዱ ለጣዖት ወተምህሩ ኵሉ ሰብአ ቤታ ተውኔተ ጣዖታት። ወበአስተአድሞ ሐውዘ ተውኔቶሙ ይሰግዱ ምስሌሃ ለወለተ ፈርዖን። ወኀብሩ ደቂቀ እስራኤል ምስሌሃ። ወአንስት ወአእማቲሃ ኀብራ ምስሌሃ በሰጊድ ወበተዋንዮ ለጣዖታ። ወለሊሁኒ ያስተአድም ሰሚዖ ተውኔታ ወእበዳ።
ወሶበ ርእየት ከመ ያፈቅር ላቲ ወይሰምዕ ወያረምም ወየሐትት ተውኔተ አማልክቲሆሙ ለግብጻውያን ፈድፋደ ታስተጥዕም ሎቱ። ወትነግሮ በጥዑም ቃል ወበድኵም ነገረ አንስት ወበአክሞስሶ ዘምስለ አርእዮ ምግባረ እኩይ በተመይጦ ገጽ ወበአሠንዮ ወበአትሕቶ ርእስ። ወበዘከመዝ ታፈርስ ልቦ እምሠናይ ኀሊናሁ። ወትቀጽቦ ውስተ እከየ ምግባራ። ወትፈቅድ ታውርዶ ውስተ እበዳ ተውኔተ ጣዖት በንዝህላል ወከመ ባሕር ዕሙቅ ዘይስሕብ ውስተ ልጎት ለዘኢይክል ጸቢተ እስከ የኀነዝዞ ማይ ወየሀጕል ነፍሶ ከማሁ ትፈቅድ አስጥሞቶ ይእቲ ብእሲት ለሰሎሞን ንጉሥ።

## ፳ወ፬ ኀበ አስሐተቶ ለሰሎሞን ወለተ ፈርዖን

ወእምዝ ተግህደት በቅድሜሁ ወትቤሎ ይኄይስ ሰጊድ ለአማልክት ከመ አቡየ ወኵሎሙ ነገሥተ ግብጽ እለ እምቅድሜሁ ለአቡየ።
ወአውሥአ ወይቤላ ሎሙሰ ይብሉ አማልክቲሆሙ ዘገብሩ በእደዊሆሙ በነሓቢ ወበጸራቢ በለሓኵ ወበሰዓሊ በወቃሪ ወበገባፊ እለ ኢኮኑ አማልክተ ግብረ እደ ሰብእ ወርቅ ወብሩር ብርት ወአረር ኀፂን ወልሕኵት ወእብን። ወትብልዎሙ አማልክቲነ ለእለ ኢኮኑ አማልክቲክሙ። ወንሕነሰ ኢንሰግድ ለባዕድ ዘእንበለ ለአምላክ ቅዱስ እስራኤል ወለእግዝእትነ ጽዮን ቅድስት ሰማያዊት ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ዘወሀበነ ከመ ንስግድ ላቲ ንሕነ ወዘርዕነ እምድኅሬነ።
አውሥአቶ ወትቤሎ ለእግዝእትከሰ ነሥአ ወልድከ ዘወለድኮ ዘእምነኪር ሕዝብ ዘኢአዘዘክሙ እግዚአብሔር ከመ ታውስቡ ኢትዮጵያዊተ እንተ ኢኮነት ኀብረከ ወቅርብተ ሀገርከ ጸሊማን ሕዝብ ባዕድ።



በሰራው ቤት አስገባት። በቤቱና በምሽቱ በግብፅ ንጉስ በፈርኦን
ልጅ በመቅሳራ ፍቅር ወደዚሁ ቤት እየሄደ ኣዘውትሮ እዚያ
ይቀመጥ ነበር።
3 እስዋም ትሰግድላቸው ዘንድ ኣባቷ የሰጣት ጣኦቶች ነበሯት። ሰ
ሎሞንም ስትሰዋና ስትሰግድላቸው እያያት ኣልተቆጣትም።
ኣልተዋትምም። ስለዚህ እግዚኣብሄር ተቆጣው። ጥበቡንም
ኣስረሳው።
4 እሷ ግን እንደ ግብፃውያን እብደት መሰዋትን፣ መስገድንና
ጭዋታንም ኣበዛች። ለጣኦትም ይሰግዱ ነበር። ቤተሰቦቹም ሁሉ
ኣምልኮ ጣኦትን ጭዋታን የጭዋታቸውንም ማማር በማድነቅ
ከፈርኦን ልጅ ጋር ኣብረዋት ይሰግዱ ነበር። የእስራኤል ልጆች
ሁሉ ከእሷ ጋር ኣንድ ሆኑ። ወይዛዝርትና ባሪያዎችም ከእሷ ጋር
ለጣኦት በመስገድና በመጫወት ኣንድ ሆኑ። እሱ ደግሞ
ጭዋታውንና እብደቱንም ሰምቶ ያደንቅ ነበር።
5 እሷም የግብፃውያንን ኣማልክቶች ጭዋታ እንደሚሰማላትና ዝም
ብሎም እንደሚመረምር፣ እንደወደደላትም ባየች ጊዜ የበለጠውን
ታጣፍጠው ጀመር። በተሰበረ ድምፅና በደካማ የሴቶች ኣነጋገር፣
ክፉ ስራን ከማሳየት ጋር በጥቂቱ ጥርሷን በመግለጥ፣ ፊቷንም
በማሽኮርመም፣ በማስዋብና በትህትና፣ ይህንና ይህን በመሳሰለው
ሁሉ ልቡን ትሸረሽር ነበር። ከመልካሙም ኣስተሳሰቡ ወደ ክፉ
ስራ ትጠቅሰውና በንዝህላልነትም ወደ እብደቷ የኣማልክት ጭዋታ
ልትስበው ትሻ ነበር። ባሕር ዋና የማይችለውን ወደ ጥልቁ
እንደሚስብና ውሃውም ትን እንዲለው፣ እንዲያጠፋውም እንደዚሁ
ሁሉ ይህች ሴት ንጉሱን ሰሎሞንን ልታሰጥመው ትሻ ነበር።

## ፳፬ የፈርኦን ልጅ ሰሎሞንን እንዳሳተችው

1 ከዚህ በሁዋላ በፊቱ ተገልፃ "እንደ ኣባቴና ከኣባቴም በፊት እንደ
ነበሩት የግብፅ ነገስታት ሁሉ ለጣኦት መስገድ ይሻላል" ኣለችው።
2 መልሶም በእጃቸው የሰሩኣቸውን በኣንጥረኛ፣ በጠራቢ፣ በሸክላ
ሠሪ፣ በሰኣሊ፣ በድንጋይ ጠራቢና በጣኦት ሰራተኛ የተሰሩትንና
ኣምላክ ያልሁኑትን የሰው እጅ ስራ ከወርቅ፣ ብር፣ መዳብ፣
እርሳስ፣ ብረትና ሸክላ ድንጋይም የሆኑትን ኣማልክት ይሏቸዋል።
ኣማልክት ያልሆኑትንም ኣማልክቶቻችን ትሏቸዋላችሁ። እኛ ግን
ለእስራኤል ቅዱስ ኣምላክና እኛና ከእኛም በሁዋላ ዘራችን እንሰግድላት
ዘንድ ለሰጠን ለሰማያዊቷ ለእግዚኣብሄር ታቦተ ህግ ለቅድስት
ፅዮን ካልሆነ በቀር ለሌላ ባእድ ኣምላክ ኣንሰግድም" ኣላት።
3 እሷም መልሳ "እመቤትክንስ ከልዩ ህዝብ ከሆነችው፣ ኣምሳያህና
ጎረቤትህ ካልሆነችው፣ እግዚኣብሄርም እንድታገባት ካላዘዘህ፣
ከጥቁር ባእድ ህዝቦችም ከሆነችው ኢትዮጵያዊት የወለድከው ልጅህ
ወሰዳት" ኣለችው።

www.ethiopianorthodox.org

አውሥአ ወይቤላ ለእመ ከመዝ ትቤሊ አንቲኒ ኢኮንኪ እምዘ አዘዘነ እግዚአብሔር ከመ ንትዋሰብ። ወዘመድከሙ ምስለ ዘመደ ዚአሃ ደቂቀ ካም ኵልክሙ። ወሠሪዎ ዘርአ ካም ሰብዐተ ነገሥተ ከነዓን አውረሰነ እግዚአብሔር ሀገረ ኀበ ንነብር ውስቴታ ለዓለም ንሕነ ወዘርዕነ እምድኅሬነ።

ወበእንተ ጽዮንኒ ፈቃደ እግዚአብሔር ኮነ። ወወሀቦሙ ከመ ያምልኩ ኪያሃ። ወአንሰ ኢይሠውዕሂ ወኢይሰግድሂ ለጣዖትኪ ወኢይገብር ፈቃደኪ።

ወዘንተ እንዘ ትብሎ እንዘ ታስተጥዕሞ ሎቱ ሠርከ ወነግሀ ሌሊተ ወመዓልተ ወውእቱኒ እንዘ የዐብያ አሐተ ዕለተ ተሠነየት ወተምዕዘት ሎቱ ወተከብረት ሎቱ ወተዐበየት ሎቱ።

ወይቤላ ምንተ እገብር እስመ አሕሰምኪ ገጸኪ ላዕሌየ ወነጽሮትኪ አኮ ከመ ዘትካት። ወላህይኪኒ ኢኮነ አዳመ። ወሰአልኒ ዘእሁበኪ ዘትፈቅዲ ወዘእገብር ለኪ ከመ ታሠንዪ ገጸኪ ኀቤየ ከመ ዘትካት። ወአርመመት ወኢያውሥአቶ።

ወደገመ ላቲ ቃለ ከመ ይግበር ላቲ ዘፈቀደት። ወትቤሎ መሐል ሊተ በአምላከ እስራኤል ከመ ኢትሐስወኒ። ወመሐለ ላቲ ከመ የሀባ ዘሰአለቶ ወከመ ይግበር ላቲ ኵሎ ዘትቤሎ።

ወአሰረት ፈትለ ለይ በመንፈቀ ኖኅታ ለቤተ አማልክቲሃ። ወአምጽአት ሠለስተ አንበጣ። ወነበረት ውስተ ቤተ አማልክቲሃ። ወትቤሎ ባእ ኀቤየ ዘእንበለ ትብክ ፈትለ ለይ ደኒክ። ወቅትሎሙ ለእሉ አንበጣ በቅድሜየ። ወከላእ ከማውዲሆሙ። ወገብረ ከማሁ። ወትቤሎ አነ እገብር እምይእዜሰ ፈቃደከ። እስመ ሦዕከሂ ወሰገድከሂ ለአማልክትየ።

ወውእቱሰ በእንተ መሐላሁ ገብረ ከመዝ ከመ ኢይብላዕ መሐላሁ ዘአምሐለቶ እንዘ የአምር ከመ ጌጋይ ውእቱ በዊእ ውስተ ቤተ አማልክቲሃ።

ወእግዚአብሔርኒ አዘዞሙ ለደቂቀ እስራኤል እንዘ ይብል ኢታውስቡ እምአንስተ ባዕድ ከመ ኢትስሐቱ ቦቶን በአማልክቲሆን በእከየ ምግባሪሆን ወበጣዕመ ቃሎን። እስመ ያደክማ ልበ ወራዙት የዋሃን በጣዕመ ቃሎን ድኵማት። ወበስነ ላህዮን ይዘርዎ ጥበበ ብእሲ አብድ።

መኑ ይጠበብ እምሰሎሞን ወስህተ በብእሲት። ወመኑ ይጸድቅ እምነ ዳዊት ወስህተ በብእሲት። ወመኑ ይጸንዕ እምነ ሶምሶን ወስህተ በብእሲት። ወመኑ ይሜኒ በላህይ እምነ አምኖን ወስህተ በእኅቱ ትዕማር ወለተ ዳዊት አቡሁ። ወአዳምኒ ቀዳሜ ልሕኵቱ ለእግዚአብሔር ስሕተ በሔዋን ብእሲቱ። ወበይእቲ ስሕተት ተፈጥረት ሞት ላዕለ ኵሉ ፍጥረት።

- 66 -

4 እሱም መልሶ "እንደዚህስ ካልሽ አንችም እግዚአብሄር
እንድናገባቸው ካዘዘው ወገን አይደለሽም። ወገንሽም ከእሷ ወገን
ነው። ሁለታችሁም የካም ልጆች ናችሁ። እግዚአብሄር እኛና ከእኛ
ም በሁዋላ ልጆቻችን ለዘላለም ልንኖርባት የካም ዘር የሆኑ ሰባት
ነገስታትን ነቅሎ ምድርን አወረሰን።
5 ስለ ፅዮንም የእግዚአብሄር ፈቃድ ሆነ። እሷንም ያመልኩ ዘንድ ሰ
ጣቸው እንጅ እኔ ለጣኦቶችሽ አልሰዋም፤ አልሰግድምም፤
ፈቃድሽንም አላደርግም" አላት።
6 እንደዚህም እያደረገች ጠዋትና ማታ እያጣፈጠች ስትነግረው እሱም
እንቢ ሲላት አንድ ቀን ተውባና ተኳኩላ ኮራችበት። ጠመመችበትም።
7 እሱም "ፊትሽን አክፍተሽብኛልና ምን ላድርግልሽ። አስተያየትሽ
እንደ ሁልጊዜው አይደለም። ውበትሽም ጥሩ አልሆነም።
እንደሁልጊዜው መልክሽን በፊቴ ታሳምሪ ዘንድ የምትሽውን
ልስጥሽ። የምችለውንና የማደርግልሽን ለምኝኝ" አላት። እሷ ግን
ዝም አለች። አልመለሰችለትም።
8 እሱ ግን የምትሻውን ሁሉ ሊያደርግላት ደጋግሞ ቃል ገባላት።
እሷም "እንዳትዋሸኝ በእስራኤል አምላክ ማልልኝ" አለችው።
የለመነችውን እንዲሰጣትና የምትለውንም ሁሉ እንዲያደርግላት
ማለላት።
9 በጣኦቶቿ ቤት በበሩ ዝቅ አድርጋ የሃር ፈትል አሰረች። ሦስት
አንበጣዎችንም አመጣች። በጣኦቷ ቤትም ውስጥ ተቀመጠች። እሱ
ንም የሃሩን ፈትል ስትቆርጥ "አጎንብሰህ ወደ እኔ ግባ።
እነዚህንም አንበጣዎች በፊቴ ግደላቸው። አንገታቸውንም ቁረጥ"
አለችው። እንደዚሁም አደረገ።
10 እሷም "እኔም ደግሞ ከእንግዲህ ፈቃድህን አደርጋለሁ"
ለአማልክቶቼ ሰውተሃል፤ ሰግደሃልምና" አለችው።
11 እሱ ግን ወደ ጣኦት ቤት መግባት ሃጢኣት እንደሆነ ባለማወቅ
ያማለችውን መሃላ እንዳይበላ እንዲህ አደረገ።
12 እግዚኣብሄር ግን የእስራኤልን ልጆች "በአማልክቶቻቸው
እንዳትስቱባቸው ከባእድ ሴቶች አታግቡ" ሲል አዘዛቸው።
"በምግባራቸው ክፋትና በቃላቸው ጣእም የየዋሆችን ጎበዛዝት ልብ
ያደክማሉና። የሰነፍም ሰው ጥበብ በመልካቸው ደም ግባት
ይበተናል። "
13 ከሰሎሞን ማን ጥበበኛ ይሆናል? እሱም በሴት ተሳሳተ። ከዳዊትስ
ማን ፃድቅ ይሆናል? እሱም በሴት ተሳሳተ። ከሶምሶንስ ማን
ይበረታል? እሱም በሴት ተሳሳተ። ከአምኖንስ በደም ግባት ማን
ይበልጣል? እሱም የአባቱ የዳዊት ልጅ በሆነችው በእህቱ ትእማር
ተሳሳተ። የእግዚኣብሄር የመጀመሪያ ስራ የሆነው አዳም በሄዋን
ተሳሳተ። በዚህችም ስህተት ሞት በፍጥረት ሁሉ ላይ መጣ።

www.ethiopianorthodox.org

ወይእቲ ስሕተተ ተባዕት እምአንስት ተፈጥረት እምሔዋን እስመ
አዋልደ ሔዋን ኵሎን።

## ፳ወ፭ በእንተ ኀጢአተ ሰሎሞን

1 ወለሰሎሞንሰ ኮኖ ጌጋየ በእንተ ሰጊድ ለጣዖት ፈድፋደ። እስመ
እንዘ ጠቢብ ኮነ አብደ። ወተጽሕፈ ኀጢአቱ ውስተ መጽሐፈ
ነቢያቲሆሙ። ወአውሥኡ እለ ህየ ሊቃነ ጳጳሳት ወይቤሉ ይምሕሮኑ
እግዚአብሔር ለሰሎሞን በእንተዝ ጌጋይ ዘተጽሕፈ ኀጢአቱ።
2 እወ መሐሮ እግዚአብሔር። ወኈለቈ ስሞ ምስለ አብርሃም ይስሐቅ
ወያዕቆብ ወዳዊት አቡሁ ውስተ መጽሐፈ ሕይወት በሰማያት።
እስመ ሰራዪ እግዚአብሔር ለእለ አበሱ።
3 ሀቡኬ ወበይኑ ለአቡሁኑ የዐቢ ኀጢአቱ ወሚመ ለወልዱ ሰሎሞን።
ወዘአቅተሎ ለዖርዮን በውስተ ጸብእ በምክረ ጕሕሉቱ ከመ ይንሥአ
ለብእሲቱ ቤርሳቤሕ እሙ ለሰሎሞን።
4 ወነስሐ ወመሐሮ እግዚአብሔር። ወእንዘ ይመውትኒ አምከሮ ለወልዱ
ሰሎሞን እንዘ ይብል ቅትሎ ለኢዮአብ በከመ ቀተሎ ለአሚር።
ወቅትሎ ለሳሚ በእንተ ዘረገመኒ።[60]
5 ወገብረ ፈቃደ አቡሁ። ወቀተሎሙ እምድኅረ ሞተ ዳዊት አቡሁ።
6 ወሰሎሞንሰ አልቦ ዘቀተለ ዘእንበለ እኁሁ ሶበ ፈቀደ ያውስብ
ብእሲተ አቡሁ ዳዊት ሱናማዊተ እንተ ስማ አቢሳ።[61] ወበእንተሰ
ዘተጽሕፈ ጌጋዩ ለሰሎሞን አነ እከሥት ለክሙ በዘከሠተ ሊተ
እግዚአብሔር።

## ፳ወ፮ በእንተ ትንቢተ ክርስቶስ

1 እስመ ሰሎሞን ብሂል በስውር ነገር ወበፍካሬ ትንቢት ክርስቶስ ብሂል።
ወበከመ ሰሎሞን ሐነጸ ቤተ እግዚአብሔር ከማሁ ክርስቶስኒ አንሥአ
ወረሰየ ሥጋሁ ቤተ ክርስቲያን።
2 ወበከመ ይቤሎሙ ለአይሁድ ንሥትዎ ለዝንቱ ቤት ወበሠሉስ ዕለት
አሐንጾ።[62] እስመ ይቤሎሙ በእንተ ቤተ ሥጋሁ።
3 ወበከመ ሰሎሞን አብዝኀ አንስተ እምሕዝብ በእንተ ሰኖን ወላህዮን
ወበአምስሎን አፍቅሮ ፍትወታት ከማሁ ክርስቶስኒ አስተጋብአ እምሕዝበ
ነኪር እለ አልቦሙ ሕግ እለ አምኑ ቦቱ ዘአልቦ ቈላፈ።
ወአልቦ አረማዊ ወአልቦ ገብረ ወአይሁዳዊ ወአልቦ ነባሬ ወዐግዓዜ።[63]
ኵሎሙ አስተጋብአ ውስተ መንግሥተ ሰማያት በሥጋሁ ወደሙ።

[60] 1ነገ.2፥5
[61] 1ነገ.1፥3
[62] ዮሐ.2፥19-21
[63] ገላ.3፥28

- 67 -

ይህችም ከወንድም ከሴትም የሆነችው ስህተት ከሄዋን ተፈጠረች።
ሁሉም የሄዋን ልጆች ናቸውና።

## ፳፭ ስለ ሰሎሞን ሃጢኣት

1 ሰሎሞንም ለጣኦት መስገዱ ፈፅሞ ሃጢያት ሆነበት። ብልህ ሳለ ሰ
ነፍ ሆኗልና። ሃጢያቱም በነቢያቶቻቸው መፅሃፍ ተፅፏልና። በዚያ
ያሉ ሊቃነ ጳጳሳትም ስለዚህ ስለተፃፈው ሃጢኣት በደል
"እግዚኣብሄር ሰሎሞንን ይቅር ይለዋልን?" ኣሉ።
2 ኣዎ፤ እግዚኣብሄር ይቅር ብሎታል። ስሙንም ከኣብርሃም፣
ከይስሃቅ፣ ከያእቆብና ከኣባቱም ከዳዊት ጋር በሰማያት ባለው
የህይወት መፅሃፍ ፃፈ። እግዚኣብሄር የበደሉትን ይቅር ባይ ነውና።
3 እስኪ ፍረዱ። የኣባቱ ወይንስ የልጁ የሰሎሞን ሃጢኣት
ይበልጣል? በሸንጋዮች ምክር ሚስቱን ቤርሳቤህን ማለትም ሚስቱን
የሰሎሞንን እናት ይወስድ ዘንድ ባሏን ኦርዮን በጦርነት
ኣስገድሎታል።
4 እሱም መልሶ ተፀፀተ። እግዚኣብሄርም ይቅር ኣለው። ሲሞትም
"ልጁን ሰሎሞንን ኣሜርን እንደገደለው ኢዮኣብን ግደለው።
ሳሚንም ስለረገመኝ ግደለው"[60] ሲል መከረው።
5 የኣባቱንም ፈቃድ ኣደረገ። ኣባቱም ዳዊት ከሞተ በሁዋላ
ገደላቸው።
6 ሰሎሞን ግን የኣባቱን የዳዊትን ሚስት ማለትም ኣቢስ
የተባለችውን ሱናማዊት ሊያገባ ከወደደ[61] ከወንድሙ በቀር ሌላ
ኣልገደለም። ስለተፃፈው የሰሎሞን በደል ግን እግዚኣብሄር
እንደገለፀልኝ እኔ እገልፅለታለሁ።

## ፳፮ ስለ ክርስቶስ ትንቢት

1 ሰሎሞን ማለት በስውር ቋንቋ፣ በትንቢትም ኣተረጓጎም ክርስቶስ
ማለት ነው። ሰሎሞን የእግዚኣብሄርን ቤት እንደ ሠራ፣ ክርስቶስም
እንዲሁ ስጋውን ኣነሳ። ቤተ ክርስቲያንም ኣደረገ።
2 ኣይሁድንም "ይህን ቤተ መቅደስ ኣፍርሱት። በሦስት ቀንም
ኣነሳዋለሁ" ኣላቸው። ይህንም ስለ ሰውነቱ ቤተ መቅደስ ይል
ነበር።[62]
3 ሰሎሞንም ህግ ከሌላቸው ከባእድ ህዝቦች ሴቶችን እንዳበዛ፣
ያልተገረዘ፣ ኣረማዊ፣ ባሪያ፣ ኣሽከርና ነፃም እንዳላለ ሁሉንም
በመንግስተ ሰማያት ውስጥ በስጋውና በደሙ ሰበሰባቸው።[63]

[60] 1ነገ.2፥5
[61] 1ነገ.1፥3
[62] ዮሃ.2፥19-21

www.ethiopianorthodox.org

4 ወበመሐልየ መሐልይሂ ለሊሁ ሰሎሞን ኀለየ እንዘ ይብል
ዐራቱ ለሰሎሞን ፷ ኃያላን።
ዐውዳ ኵሎሙ ምሁራነ ቀትል እንዛነ አስይፍት።
ብእሲ ብእሲ ዲበ መንቅዕቱ።[64] ሰይፉ ያነብር። ፷ ብሂል በኀልቈ
፬ አበው ጻድቃን ወነቢያት ወሐዋርያት ወሰማዕት ወመሃይምናን
ወቅዱሳን መነኮሳት እለ የዐብይዎ ለኀሊና እኩይ ጸብአ ሰይጣን።
5 ወሰይፍሂ ይተረጐም ቃለ መጻሕፍት ከመ መላጺ በሊኅ ዘርቱዐ
ይመትር ቃለ እግዚአብሔር ከማሁ ይመትሩ እምልቦሙ ድንጋፄ
ለያልይ ዘሕልመ ሐሰት።
6 ወዐራተ ሰሎሞንሰ ምስካቡ ይተረጐም በቤተ ክርስቲያኑ ለክርስቶስ።
ወካዕበ ኀለየ እንዘ ይብል መጸረ ገብረ ለርእሱ ንጉሥ ሰሎሞን።[65]
ወዝንተ ተርጐመ ከመ ክርስቶስ ለብሰ ሥጋነ።
7 ሰሎሞን ብሂል በነገረ ዕብራውያን ክርስቶስ ብሂል።
8 ወአብዳንሰ አይሁድ ይመስልዎ ለቃለ ዳዊት ዘተብህለ በእንተ ሰ
ሎሞን ወልደ እግዚአብሔር፤
ይቤለኒ ወልድየ አንተ
ወአነ ዮም ወለድኩከ።[66]
እግዚኦ ኵነኔከ ሀቦ ለንጉሥ።
ወጽድቀከኒ ለወልደ ንጉሥ።
ከመ ይኰንኖሙ ለሕዝብከ በጽድቅ።
ወለነዳያኒከኒ በፍትሕ።[67]
የሐዩ ወይሁብዎ እምወርቀ ዐረብ።
ወዘልፈ ይጼልዩ በእንቲአሁ።
ወኵሉ አሚረ ይድኀርዎ።
ወይከውን ምስማከ ለኵሉ ምድር።
ውስተ አርእስተ አድባር።
ወይነውኅ እምዐርዝ ፍሬሁ።
ወይበቍል ውስተ ሀገር ከመ ሣዕረ ምድር።
ወይከውን ቡሩከ ስሙ ለዓለም።
እምቅድመ ፀሐይ ሀሉ ስሙ
ወለድኩከ እምከርሥ እምቅድመ ኮከበ ጽባሕ።[68]
መሐለ እግዚአብሔር ወኢይኔስሕ።
አንተ ካህኑ ለዓለም በከመ ሚመቱ ለመልከ ጼዴቅ።[69]

መኀ.3፥7
ምሳ.3፥9
መዝ.2፥7
መዝ.72፥1-2
መዝ.72፥15-17
መዝ72፥1፥110፥4



4 ከመዝሙር ሁሉ በሚበልጥ የሰሎሞን መዝሙር "እነሆ የሰሎሞን
አልጋ ናት። ከእስራኤል ሃያላን ስድሳ ሃያላን በዙሪያው ናቸው።
ሁሉም ሰይፍ የያዙ ሰልፈኞች ናቸው። ሰው ሁሉ ሰይፍ በወገቡ
አለ"[64] ሲል እራሱ ሰሎሞን እንደ ዘመረ ስድሳ ያለው ክፉ ሃሳብ
ማለትም የሰይጣን ጦርነት የሚቃወሙ ፃድቃን አባቶች፣ ነቢያት፣
ሃዋርያት፣ ሰማእታት፣ ምእመናንና ቅዱሳን መነኮሳት ናቸው።
5 ሰይፍ በመፃህፍት ቃል ይተረጎማል። በእውነት የእግዚአብሄር ቃል
እንደ ተሳለ ምላጭ ይቆጠራል። የሰሎሞን መተኛ አልጋዎች
የተባሉ በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ይተረጎማሉ።
6 ንጉስ ሰሎሞን "መሸከሚያውን ለራሱ አሰራ"[65] ብሎ ዘመረ። ይህም
ክርስቶስ ስጋችንን እንደ ለበሰ ይተረጎማል።
7 ሰሎሞን ማለት በእብራውያን ቋንቋ ክርስቶስ ማለት ነው።
8 ሰነፎች አይሁድ ግን ስለ ልጁ ሰሎሞን የተነገረውን፣
እግዚአብሄር አለኝ አንተ ልጄ ነህ
እኔ ዛሬ ወለድኩህ።[66]
አቤቱ ፍርድህን ለንጉስ ስጥ
ፅድቅህንም ለንጉስ ልጅ
ህዝብህን በፅድቅ
ችግረኞችህንም በፍርድ ይዳኝ ዘንድ።[67]
እርሱ ይኖራል።
ከአረብ ወርቅ ይሰጡታል፤
ሁልጊዜ ወደ እርሱ ይፀልያሉ፤
ዘወትርም ይባርኩታል።
በምድር ውስጥ በተራሮች ላይ መጠጊያ ይሆናል፤ ፍሬውም
ከሊባኖስ ይልቅ ከፍ ከፍ ይላል።
እንደ ምድር ሳር በከተማ ይበቅላል፤
ስሙ ለዘላለም ቡሩክ ይሆናል፤
ከፀሃይም አስቀድሞ ስሙ ይኖራል።[68]
ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ ከሆድ ወለድኩህ።
እንደ መልከ ጼዴቅ ስርአት አንተ ለዘላለም ካህን ነህ
ብሎ እግዚአብሄር ማለ። አይፀፀትም።[69]
ይህንንና የመሰለውን ስለ ክርስቶስ የተነገረውን ትንቢት ሰነፎችና
የልብ እውሮች አይሁድ ዳዊት በመፅሃፉ ውስጥ ይህንን ስለ ልጁ

[63] ገላ.3፥28
[64] መሃ.3፥7
[65] ምሳ.3፥9
[66] መዝ.2፥7
[67] መዝ.72፥1-2
[68] መዝ.72፥15-17
[69] መዝ.72፥1፥110፥3-4

www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

ወዘንተ ወዘይመስሉ ትንቢተ ዘበእንተ ክርስቶስ ዘተነበየ ዳዊት
ይብሉ አብዳን ዕውራነ ልብ አይሁድ። ይቤ ዳዊት ውስተ ርእሰ
መጽሐፉ በእንተ ሰሎሞን ወልዱ ዘተናገረ ዘንተ ይብሉ አይሁድ
ወይመስልዎ ለክርስቶስ በሰሎሞን በመክሌ ስም በጥበብ ወለወልደ
ዳዊት በሥጋ።
10 ወዘንተ እምድኅረ አእመሩ እለ እምድኅረ ዳዊት ወሰሎሞን ኤልያስ
ወኤልሣዕ ጸሐፉ ኀጢአቶ ለሰሎሞን ውስተ መጽሐፈ ነገሥት ከመ
ያስተኃፍርዎሙ ለአይሁድ ዕውራነ ልብ ፀራ ለጽድቅ።
11 ወሰሎሞንስ ንጉሥ ወልደ ዳዊት ንጉሥ ወነቢይ ወለሊሁኒ ንጉሥ
ወነቢይ ውእቱ። ወበጥበብ ተነበየ ዘበእንተ ክርስቶስ ብዙኀ አምሳለ።
ወበእንተ ቤተ ክርስቲያን ጸሐፈ አርባዕተ መጽሐፈ ትንቢቱ።
ወተኈለቈ ምስለ አብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ ወዳዊት አቡሁ
በመንግሥተ ሰማያት።

## ፳ወ፮ በእንተ ብካየ ሰሎሞን

1 ወዘከመሂ አዕረፈ እነግረክሙ። ኮኑ መዋዕሊሁ ፳። ወአኀዞ ሕማም።
ወበከመ መዋዕለ አቡሁሰ ዳዊት ኢኮነ። አላ ፷ ሐጸ እምኔሁ በእንተ
ዘተአዘዘ ለአንስት ወሰገደ ለጣዖታት።
2 ወመጽአ መልአከ ሞት ወዘበጦ እግሮ። ወበከየ ወይቤ እግዚኦ
አምላከ እስራኤል እስመ ሕገ መሬታዊ ተመዋእኩ። እስመ አልቦ
ንጹሐ እምርስሐት በቅድሜከ። እግዚኦ ወአልቦ ዘይጸድቅ ወይጠብብ
በቅድሜከ። እግዚኦ እስመ አንተ ትሬኢ ወትፈትን ልበ። ወአልቦ
ዘይሴወር እምኔከ። ኅቡአተ ትሬኢ በክሡታት። ወልበ ተሐትት።
መሐረኒ እግዚኦ ልበ ሰብእ ተኀሥሥ ወኵልያተ ትፈትን መሐረኒ
እግዚኦ ዘለሐሳሰ ወዘረዓም ትሰምዕ። መሐረኒ እግዚኦ።
3 ወእመሰ መሐርኮሙ ለጻድቃን እለ ኢተዐደዉ እምትእዛዝከ ምንተ
መንክር ምሕረትከ። መሐረኒ እግዚኦ አላ ሶበ ትምሕር ኪያየ ኀጥአ
ወእቱኬ መንክር። ወአዳም ምሕረትከ። መሐረኒ እግዚኦ።
4 ሶበ አነ አበስኩ ተዘከር አብርሃምሃ ወይስሐቅሃ ወያዕቆብሃ አበውየ እለ
ኢተዐደዉ እምትእዛዝከ። መሐረኒ እግዚኦ እስመ መሐሪ ወሰራዪ አንተ።
እግዚኦ በእንተ ዳዊት ገብርከ መሐረኒ። እግዚኦ አኀዜ ዓለም ወነገሥት
ወመኳንንት። መሐረኒ እግዚኦ መጥበቤ አብዳን ወማዕበደ ጠቢባን
መሐረኒ እግዚኦ መያጤ ኀጥአን ወዐሳዬ ጻድቃን። መሐረኒ እግዚኦ።
5 ወዘንተ እንዘ ይብል ይውኅዝ አንብዑ ውስተ ገጹ። ወየኀሥሥ በሰበኑ።
ወወረደ ኀቤሁ መልአከ እግዚአብሔር። ወይቤሎ ስማዕ ዘእነግረከ ዘለአከኒ
እግዚአብሔር። እንዘ ጠቢብ አብደ ረሰይከ ርእሰከ። ወእንዘ ባዕል
አንደይከ ርእሰከ። ወእንዘ ንጉሥ አኅሠርከ ርእሰከ በተዐድዎ ትእዛዘ
እግዚአብሔር። ወርእሳ ለእከይ በእንተ ዘአብዛኅከ አንስተ ተዐዲወከ ሕጎ
ወፍትሖ ወሥርዐቶ ለእግዚአብሔር ዘጸሐፈ ሙሴ ወወሀበክሙ ለእስራኤል
ከመ ኢታውስቡ እምባዕድ ፍጥረት ዘእንበለ እምዘመድክሙ ወቤተ



ሰሎሞን ተናገረ ይላሉ። አይሁድ በስም ሞክሼነት፣ በጥበቡና በስጋም
የዳዊት ልጅ በመሆኑ ክርስቶስን በሰሎሞን ይመስሉታል።
የዳዊት ልጅ በመሆኑ ክርስቶስን በሰሎሞን ይመስሉታል። ኤልያስና ኤልሳእ ግን ይህን ካወቁ
9 ከዳዊትና ከሰሎሞን በሁዋላ የነበሩት ኤልያስና ኤልሳእ ግን ይህን ካወቁ
በሁዋላ የሰሎሞን ሃጢአት በመፅሃፈ ነገስት ፃፉ። ይሄውም የልብ እውሮ
ችና የፅድቅ ጠላት የሆኑትን አይሁድን ያሳፍሩአቸው ዘንድ ነው።
10 ንጉሱ ሰሎሞን ግን የንጉሱና የነቢዩ የዳዊት ልጅ ከመሆኑም ጋር
እራሱም ንጉስና ነቢይ ነበር። ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን
በጥበቡ በብዙ አርአያና ምሳሌ ተናገረ። አራት የትንቢት መፅሃፎችንም
ፃፈ። በመንግስተ ሰማያትም ከአብርሃም፣ ከይስሃቅና ከያእቆብ፣ ከአባቱም
ከዳዊት ጋር ተቆጠረ።

## ፳፮ ስለ ሰሎሞን ልቅሶ

1 እንደት እንደሞተም እነግራችሁዋለሁ። ስሳ አመት ሲሆነው
ታመመ። ለሴቶች ስለታዘዘና ለጣኦታትንም ስለ ሰገደ ሃያ አመት
ጎደለው። እድሜው እንደ አባቱ እንደ ዳዊት እድሜ አልሆነም።
2 መልአከ ሞትም መጥቶ እግሩን መታው። "አቤቱ የእስራኤል
አምላክ ሆይ! ለመሬታዊ ህጎች ተሸንፌአለሁና ወዮልኝ" ብሎ
አለቀሰ። "አሁንም በፊትህ ከሃጢአት የነፃ እውነተኛና ጥበበኛ
የለም። አቤቱ አንተ ልብን ትመረምራለህ። ከአንተም የሚሰወር
የለም። የተሰወሩትን ታያለህ። ልብንም ትመረምራለህና አቤቱ
ይቅር በለኝ። ሹክሹክታንና የከፍታውን ድምፅ የምትሰማ ሆይ!
አቤቱ ማረኝ።
3 ከትእዛዝህ ያልተላለፉትን ፃድቃንን ብትምራቸው ምህረትህ ምን
ይደንቃል? ስለዚህ አቤቱ እኔን ማረኝ። እኔን ሃጥኡን ብትምረኝ
ግን ምህረትህ ድንቅ፣ መልካምም ይሆናልና አቤቱ እኔን ሃጥኡን
ባሪያህን ማረኝ።
4 እኔ ብበድል እንኳን ከትእዛዝህ ያልተላለፉትን አብርሃምን፣
ይስሃቅንና ያእቆብን አስብና አቤቱ ማረኝ። አንተ ቸርና
ሃጢአትንም ይቅር ባይ ነህና አቤቱ ማረኝ። ስለባሪያህ ስለ ዳዊት
አቤቱ ይቅር በለኝ። የአለም ነገስታትና የመኳንንት ገዥ ሆይ!
አቤቱ ይቅር በለኝ። ሰነፎችን ጥበበኞች፣ ጥበበኞችን ሰነፎች
የምታደርግ ሆይ! አቤቱ ይቅር በለኝ። ሃጥአንን ከክፉ ስራቸው
የምትመልስ፣ ለፃድቃንም ዋጋቸውን የምትከፍል ሆይ! አቤቱ
ይቅር በለኝ።"
5 ይህንንም እያለ እንባው በፊቱ ላይ ይፈስና በመሃረምም ይጠርግ ነበር።
የእግዚአብሄር መልአክም ወደ እሱ ወርዶ አለው። "እግዚአብሄር
የላከኝንና የምነግርህን ስማኝ። ብልህ ሳለህ ራስክን ሰነፍ አደረግህ።
ባለፀጋ ሳለህ ራስክን አደሀየህ። ንጉስ ሳለህ የእግዚአብሄርን ትእዛዝ
በመተላለፍ ራስህን አዋረድህ። የስንፍናውም ዋና ምክንያት ዘሮቻችሁ
በሙሉ ንፁሃንና ቅዱሳን እንዲሆኑና እግዚአብሄርንም ከእናንተ ጋር
እንዲያድር ከወገኖቻችሁ ካልሆነ በቀር ከባእድ ህዝቦች እንዳታገቡ

www.ethiopianorthodox.org

አቡክሙ ከመ ይኩኑ ንጹሓነ ወቅዱሳነ ዘርዕክሙ ከመ ይኅድር
እግዚአብሔር ምስሌክሙ።
6 ወአንተሰ አስተሐቀርከ ሕገ እግዚአብሔር እንዘ ይመስለከ ዘትጠበብ
እም እግዚአብሐር ወትረክብ ብዙኀ ደቂቀ ተባዕተ። ወእበዱ
ለእግዚአብሔር ይጠበብ እምጥበቢሁ ለእጓለ እመሕያው ወኢወሀበከ
ዘእንበለ ፲ ደቂቅ።
፩ ዘነሥአ ክብረከ ለባዕድ። ወረሰየ ማኅደሮ ለእግዚአብሔር ውስተ
ብሔረ ኢትዮጵያ።
ወ፩ ፅውሰ እግር ዘይከውን በዲበ መንበርከ ለነገደ እስራኤል ወልደ
ዘመደ ዘመድከ ተርባን እምቤተ ይሁዳ።
ወ፩ ወልደ ሮማዊት አመት ዘበደኃሪ መዋዕል ይሜርዎ ለኢዮርብዓም
ወለኵሉ ዘመድከ እስራኤል ወትከውን ሎቱ ዛቲ ምድር እስመ
ለሊሁ የአምን በዘይመጽእ መ.ኆኅን።
ወነገደ ዮርብዓምሰ ወእለ ተርፉ እስራኤል ይሰቅልዎ ለዘይመጽእ
መድኅን ወይጠፍእ ዝክርከሙ እምነ ምድር እስመ ይጌልዩ ምክረ
እንተ ኢይክሉ አቅሞ ወውእቱኒ ይትመዐየሙ ወያጠፍእ ዝክሮሙ።
ወለከሰ ይኩንከ ትእምርተ ዮሴፍ ወልደ ያዕቆብ እስመ ሜጥዎ
አኀዊሁ ብሔረ ግብጽ እምሶርያ ሀገረ ላባ። ወበርደቱ ብሔረ ግብጽ
ኮነ ረኀብ ውስተ ሶርያ ወውስተ ኵሉ ዓለም።
ወበርደቱ ጸውዖሙ ለአዝማዲሁ ወአድኅኖሙ እምርኀብ። ወወሀቦሙ
ማኅደረ በምድረ ግብጽ እንተ ስማ ጌሤም። እስመ ለሊሁ ንጉሥ
እምታሕተ ፈርዖን ንጉሠ ግብጽ። ወከማሁ ዘይመጽእ መድኅን
እምዘመድከ ይሰሪ ለከ በምጽአቱ ወያወጽአከ እምሲኦል።
ወእስከ ይመጽእ መድኅን ትሣቀይ በሀየ ምስለ አበዊከ ወያወጽአከ።
እስመ እምዘርዕከ ይመጽእ መድኅን ዘያድኅነከሙ ለከ ወለእለ
እምቅድሜከ ወለእለ እምድኅሬከ እምአዳም እስከ ምጽአቱ ለዘመደ
ዘመድከሙ።
ወያውፅአከሙ እምሲኦል በከመ አውፅኦሙ ዮሴፍ ለአዝማዲሁ
እምረኀብ። እስመ ቀዳሚት ሲኦል በምድረ ረኀብ። ወከማሁ
ያወፅአከሙ መድኅን እምሲኦል ለአዝማዲሁ።
ወበከመ ቀነይዎሙ ድኅረ ግብጻውያን ከማሁ ቀነዩከሙ አጋንንት
በስሕተተ ጣዖት።
ወበከመ አውፅኦሙ ሙሴ ለአዝማዲሁ እምግብርናት ከማሁ
ያወፅአከሙ መድኅን እምግብርናተ ሲኦል።
ወበከመ ገብረ ሙሴ ፲ ተአምራተ ወመቅሠፍታተ በቅድመ ፈርዖን
ንጉሥ ከማሁ ዘይመፅእ መድኅን እምዘመድከ ይገብር ፲ ተአምራተ
ለሕይወት በቅድመ ሕዝብከ።
ወገቢሮ ትእምርታተ ሙሴ በከመ ዘበጠ ባሕረ ወአንለፎሙ እንተ
የብስ ከማሁ ዘይመጽእ መድኅን ይነስት አረፋቲሃ ለሲኦል
ወያውፅአከሙ።
ወበከመ አስጠሞ ሙሴ ለፈርዖን ምስለ ግብጻውያን ውስተ ባሕረ
ኤርትራ ከማሁ ያሰጥሞሙ ለሰይጣን ወለአጋንንቲሁ መድኅን ውስተ

- 70 -

ሙሴ የፃፈውንና ለእስራኤል የሰጠውን የእግዚኣብሄርን ህጉን፣
ፍርዱንና ስርኣቱን በመተላለፍ ሴቶችን ስላበዛህ ነው።
6 ኣንተ ግን ከእግዚኣብሄር የምትጠበብና ብዙ ወንዶች ልጆችን
የምታገኝ እየመሰለህ የእግዚኣብሄርን ህግ ኣቃለልክ። የእግዚኣብሄርም
ስንፍና ግን ከሰው ልጅ ጥበብ ይልቅ ይጠበባል። ከሶስት
ልጆችም በቀር ኣልሰጠህም።
7 ከእነሱም ኣንዱ ክብርህን ወስዶ ለባእድ የሰጠውና በኢትዮጵያም
የእግዚኣብሄርን ማደሪያ ያደረገው ነው።
8 ሌላውም እግረ ሰባራውና በዙፋንህ ላይ ለእስራኤል ህዝብ
የሚቀመጠው የዘመድህ ዘመድ ከይሁዳ ቤት ኣለቃ የሆነው ነው።
9 ሌላውም የባሪያዋ ሮማዊቷ ልጅ የሆነውና በሁዋለኛው ዘመን ኢዮር
ብኣምንና ዘመዳችሁ እስራኤላውያንም ሁሉ የሚነቅል ነው።
ይህችም ምድር ለእርሱ ትሆናለች። በሚመጣው ኣዳኝ ያምናልና።
10 የዮርብኣም ነገዶችና የቀሩት እስራኤላውያን ግን የሚመጣውን
ኣዳኝ ይሰቅሉታል። መታሰቢያው ከምድር ላይ ይጠፋል።
ኣቅማቸው የማይችለውን ምክር ያስባሉና። እሱም ይቆጣቸዋል።
መታሰቢያቸውንም ያጠፋል።
11 ለኣንተ ግን የያእቆብ ልጅ ዮሴፍ ትምህርት ይሆንሃል። ከላባ
ኣገር፣ ከሶርያ ወንድሞቹ ወደ ምድረ ግብፅ ሸጠውታልና። ወደ
ግብፅ ምድር በመውረዱም በሶርያ ኣገርና በኣለም ሁሉ ረሃብ ሆነ።
12 በመውረዱም ዘመዶቹን ጠራቸው። ከረሃብም ኣዳናቸው። ስሟ ጌሴ
ን በተባለችው በግብፅ ምድርም ማደሪያን ሰጣቸው። ከግብፅ ንጉስ
ከፈርኦን በታች እሱ ራሱ ንጉስ ነበርና።
13 ኣዳኝም እስኪመጣ ድረስ ከኣባቶችህ ጋር በዚህ ትሰቃያለህ።
ኣንተንና ከኣንተም በፊትና ከኣንተም በሁዋላ ከኣዳም እስከ
ምፅኣት ድረስ ያሉትን የዘመዶቻችሁን ዘመዶች ሁሉ የሚያድናችሁ
ከዘርህ ይወጣልና። ያድናችሁዋልም።
14 ዮሴፍ ዘመዶቹን ከረሃብ እንዳወጣቸው ከሲኦል ያወጣችሁዋል።
የመጀመሪያዋ ሲኦል የረሃብ ምድር ናት። እንደዚሁም ኣዳኙ
ዘመዶቹን ከሲኦል ያወጣቸዋል።
15 ግብፃውያን እስራኤላወያን እንደገዟቸው ኣጋንንትም በጣኦት ስህተት
ገዟችሁ።
16 ሙሴ ዘመዶቹን ከባርነት እንዳወጣቸው እንዲሁም ኣዳኙ ከሲኦል
ባርነት ያወጣችህዋል።
17 ሙሴ በንጉሱ በፈርኦን ፊት ኣስር መቅሰፍትንና ተኣምራቶችን
እንዳደረገ እንዲሁም ከወገንህ የሚመጣው በህዝብህ ፊት ኣስር
የድህነትን ተኣምራቶችን ያደርጋል።
18 ሙሴ ትእምርተ መስቀል ኣድርጎ ባህሩን እንደመታውና በደረቅ
እንዳሳለፋቸው እንዲሁም የሚመጣው የሲኦልን ኣጥሮች ኣፍርሶ
ያወጣችሁዋል።
19 ሙሴ በኤርትራ ባህር ውስጥ ፈርኦንን ከግብፃውያን ጋር እንዳሰ
ጠመው ኣዳኙ ሰይጣንና ኣጋንንቶችን በሲኦል ውስጥ

www.ethiopianorthodox.org

ሲኦል እስመ ባሕር ትተረጐም በሲኦል ወፈርዖን ይተረጐም በሰይጣን ወሰራዊቱ ግብጻውያን ይተረጐሙ በአጋንንት። ወበከመ ሴሰዮሙ መና በገዳም ዘእንበለ ጻማ ከማሁ ይሴሰየክሙ መድኅን መብልዐ ገነት ዘለዓለም እምድኅረ አውጽአክሙ እምሲኦል። ወበከመ አንበሮሙ በገዳም ፵ ዓመተ እንዘ ኢይበሊ አልባሲሆሙ ወኢነቅዐ ሰኰናሆሙ ከማሁ መድኅን ያነብረክሙ ዘእንበለ ጻማ እምድኅረ ትንሣኤ። ወበከመ አብኦሙ ኢያሱ ምድረ ርስት ከማሁ ያበውአክሙ መድኅን ውስተ ገነተ ትፍሥሕት። ወበከመ ቀተሎሙ ኢያሱ ለ፯ ነገሥተ ከነአን ከማሁ ይቀትሎሙ መድኅን ለ፯ አርእስተ አብሊስ።[1] ወከመ ሠረዎሙ ኢያሱ ለሕዝበ ከነአን ከማሁ ይሤርዎሙ መድኅን ለኀጥአን ወየኀትሞሙ ውስተ ማኀተመ ሲኦል። ወበከመ አንተ ሐነጽከ ቤተ እግዚአብሔር ከማሁ ይትሐነጻ አብያተ እግዚአብሔር ውስተ አርእስተ አድባር።

## ፳ወ፳ በእንተ መድኅኒትነ ማርያም

ወካዕበ ይኩንከ ትእምርተ ከመ ይመጽእ መድኅን እምዘርዕከ ወከመ ያድኅንከ ምስለ አበዊከ ወዘርዕከ እምድኅሬከ።
በምጽአቱ ተፈጥረት መድኅኒትክሙ ውስተ ከርሠ አዳም ከመ ዕንቊ ባሕርይ እምቅድመ ሔዋን።
ወሶበ ፈጠራ ለሔዋን እምዐፅመ ገቦሁ ለአዳም ወይቤሎሙ ብዝኁ እምከርሠ አዳም ኢወፅአት ኀበ ቃየን ወአቤል አላ ኀበ ሣልስ ወፅአት እምከርሠ አዳም ወገብአት ውስተ ከርሠ ለሴት።
ወእምኔሁ እንዘ ተሐውር ይእቲ ባሕርይ ኀበ እለ ኮኑ በኲረ በጽሐት እስከ አብርሃም። ወእምነ አብርሃም ኢወፅአት ውስተ በኲሩ ይስማኤል አላ ጸንሐት ወቦአት ኀበ ይስሐቅ ንጹሕ።
ወእምይስሐቅኒ ኢሖረት ኀበ በኲሩ ዕቡይ ኤሳው አላ ቦአት ኀበ ያዕቆብ ትሑት።
ወእምያዕቆብ ኢቦአት ኀበ ሮቤል በኵር ስሑት አላ ቦአት ኀበ ይሁዳ የዋህ።
ወእምይሁዳኒ ኢወጽአት እስከ ይትወለዱ ፬ መአብሳን አላ ቦአት ኀበ ፋሬስ መስተአግሥ።
ወእምኔሁ ይእቲ ባሕርይ ሖረት ኀበ በኵር እስከነ በጽሐት ውስተ ከርሠ ዕሤይ አበ አቡከ። ወእምዝ ጸንሐት እስከ ይትወለዱ ፯ ኀርቡዳን።
ወእምዝ ቦአት ኀበ ሳብዓይ ዳዊት አቡከ የዋህ ወትሑት እስመ እግዚአብሔር ይጸልእ ዕቡያነ ወዝኁራነ ወያፈቅር የዋሀነ ወትሑታነ።
ወእምዝ ጸንሐት ውስተ ሐቌ አቡከ እስከ ይትወለዱ ፭ ስሑታን ወእብዳን። ወቦአት ውስተ ሐቌ ዚአከ በእንተ ጥበብከ ወልቡናከ።
ወእምዝ ጸንሐት ባሕርይ ወኢሖረት ኀበ በኵርከ። እስመ ሠናያን እሙንቱ ሰብአ ሀገሩ። እመ ኢክሕድዎ ወእመ ኢሰቀልዎ ከመ

[1]ሊስም ይላል።



ያስጥማቸዋል። ባህር በሲኦል ትተረጎማለች። ፈርኦንም በሰይጣን ይተረጎማል። ሰራዊቱ ግብፃውያንም በኣጋንንት ይተረጎማሉና።
20 ያለ ድካም በዱር መና እንደመገባቸው እንዲሁም ኣዳኙ ከሲኦል ከወጣችሁ በሁዋላ የዘላለም የገነት መብልን ይመግባቸዋል። ልብሳቸው ሳያረጅ፣ ሽኮናቸው ሳይነቃ፣ ኣርባ ኣመት በዱር እንዳስቀመጣቸው እንዲሁ ኣዳኙ ከትንሳኤ በሁዋላ ያለ ድካም ያስቀምጣችሁዋል። ኢያሱ ወደ ምድረ ርስት እንዳስገባችሁ እንደዚሁም ኣዳኙ ወደ ደስታ ገነት ያገባችሁዋል። ኢያሱ ሰባቱን የከነኣን ነገስታት እንደገደላቸው እንዲሁም ኣዳኙ ሰባቱን የኣጥፊዎች ኣለቆች ይገድላቸዋል። ኢያሱ የከነኣንን ሕዝቦች እንደ ነቀላቸው እንዲሁም ጌታ ሃጥኣንን ይነቅላቸዋል። በሲኦል ማህተምም ያትማቸዋል። ኣንተ የእግዚኣብሄርን ቤት እንደ ሰራህ እንደዚሁም በተራሮች ራሶች ላይ የእግዚኣብሄር ቤቶች ይሰራሉ።"

## ፳፳ ስለ መድሃኒታችን ማርያም

1 "ደግሞ ኣዳኙ ከዚህ እንደሚመጣና ከኣባቶችሁ ከኣንተና ከዘርህም ጋር እንደሚያድንህ ምልክት ይሆንልሃል።
2 በመምጣቱም ከሄዋን በፊት መድሃኒታችሁ እንደ ባህር እንቁ ከኣዳም ሆድ ውስጥ ተፈጠረች።
3 ሄዋንንም ከኣዳም ከጎኑ ኣጥንት በፈጠራት ጊዜ ወደ ቃየንና ወደ ኣቤል ኣልወጣችም። ከኣዳም ሆድ ወጥታ ወደ ሶስተኛው፣ ወደ ሴት ሆድ ገባች እንጂ።
4 ከእሱም ይህች እንቁ በኩር ወደ ሆኑት ስትሄድ እስከ ኣብርሃም ደረሰች። ከኣብርሃም ወደ ንፁህ ይስሃቅ ገባች እንጂ ወደ በኩሩ ወደ እስማኤል ኣልወጣችም።
5 ከይስሃቅም ወደ ትሁቱ ያእቆብ ገባች እንጂ ወደ ትእቢተኛው ልጁ ወደ ኤሳው ኣልሄደችም።
6 ከያእቆብም ወደ የዋሁ ይሁዳ ገባች እንጂ ወደ በኩር ልጁ ወደ ሮቤል ኣልገባችም።
7 ከይሁዳም ወደ ትእግስተኛው ወደ ፋሬስ ገባች እንጂ ኣራቱ ሃጢኣተኞች እስከሚወለዱ ድረስ ኣልወጣችም።
8 ከእሱም በሁዋላ ይህች እንቁ እስከ ኣያትህ እሴይ ድረስ በየበኩሩ ሄደች። ስድስቱም እብዶች እስከሚወለዱ ድረስ ቆየች።
9 ከዚህ በሁዋላ ወደ የዋሁና ወደ ትሁቱ፣ ወደ ሰባተኛው ኣባትህ፣ ወደ ዳዊት ገባች። እግዚኣብሄር ትእቢተኞችንና ኩራተኞችን ይጠላል። የዋሃንንና ትሁቶችንም ይወዳልና።
10 ከዚህ በሁዋላ ኣምስቱ ስሁቶችና ሰነፎች እስከሚወለዱ ድረስ በኣባትህ ወገብ ቆይታ ስለ ጥበብህና ማስተዋልህ ወደ ኣንተ ወገብ ገባች።
11 ከዚህ በሁዋላ እንቁዋ ቆየች። ወደ በኩርህም ኣልሄደችም። የኣገሩ ሰዎች ደጋጎች ነበሩና ከእንቁዋ የሚወለደው ታምራትን ሲያደርግ

www.ethiopianorthodox.org

እስራኤል ሕዝብከ ሶበ ይሬእዩ ዘይገብር ተአምረ ዘይትወለድ እምባሕርይ። እሙንቱሰ የአምኑ ቦቱ በሰሚዐ ዜናሁ።

ወኀበ ዘይንእስኒ ወልድከ አድራሚ ኢሖረት እስመ እሙንቱ ሠናያን እመ ኢሰቀልዎ ወእመ ኢክህዱ ሶበ ርእዩ ዘይገብር ተአምረ ወመንክረ ዘይትወለድ እምባሕርይ። ወበደኃሪ የአምኑ ቦቱ በአርድእቱ።

አላ ባሕቱ ወፅአት ባሕርይ እምከርሥከ እንተ ትከውን መድኀኒትክሙ ወቦአት ውስተ ከርሠ ኢዮርብዐም ወልድከ በእንተ እከዮሙ ለእስራኤል ሕዝብከ እስመ በክህደቶሙ ወበእከዮሙ ይሰቅልዎ።

ወሶበሰ ኢተሰቅለ እመ ኢኮነ መድኀኒትክሙ እስመ ይሰቀል ዘእንበለ ኀጢአት። ወይትነሣእ ዘእንበለ ሙስና።

ወበእንተዝ ይወርድ ኀቤክሙ ውስተ ሲኦል። ወይነሥት አረፋቲሃ ከመ ያድኅንክሙ ወያውፅእክሙ ወይምሐርክሙ ለኩልክሙ እለ ተጸውረት ባሕርይ ውስተ ከርሥክሙ። ትድኅኑ ምስለ አንስቲያክሙ።

ወአልቦ ዘይትኀጐል እምኔክሙ። እምአቡከ አዳም እስከ ዘይመጽእ ዘመድከ ኢያቄም ወእምሔዋን እምከ ብእሲቱ ለአዳም እስከ ኖኅ ወብእሲቱ ተርሚዛ፣ እስከ ታራ ወብእሲቱ አሚንያ ወእስከ አብርሃም ወብእሲቱ ሣራ፣ ወእስከ ይስሐቅ ወብእሲቱ ርብቃ፣ ወእስከ ያዕቆብ ወብእሲቱ ልያ፣ ወእስከ ይሁዳ ወመርዓቱ ትዕማር፣ ወእስከ አቡከ ወብእሲቱ ቤርሳቤህ፣ ወእስከ ለሊከ ወተርባና ብእሲትከ፣ ወእስከ ኢዮርብአም ወልድከ ወአሚሳ ብእሲቱ፣ ወእስከ ኢዮአቄም ዘይመጽእ ዘመድከ ወብእሲቱ ሐና። ኵልክሙ እለ ጾርክምዋ ለባሕርይ አልቦ ዘይትህጐል እምኔክሙ፣ እምተባዕትክሙ ወእስከ አንስቲያክሙ ኢትትህጐሉ። እለ ጾርክምዋ ለባሕርይ። እስመ ትጸወር ባሕርይ በተባዕት እለ ትከውኑ ጻድቃነ።

ወአንስትኒ እለ ጸራ ምጽዋረ ባሕርይ ኢይትኀጐላ እስመ ንጹሐተ ይከውና በይእቲ ባሕርይ። እስመ ቅድስት ወንጽሕት ይእቲ። ወባቲ ትትቄደሱ ወትነጽሑ እስመ በእንቲአሃ ወበእንተ ጽዮን ፈጠሮ ለኵሉ ዓለም። ጽዮንሰ ነበረት ኀበ በኵርከ ወትከውን መድኀኒቶሙ ለሕዝበ ኢትዮጵያ እስከ ለዓለም።

ወባሕርይኒ ተጸውረት ውስተ ከርሠ ኢዮርብዓም ወልድከ። ወትከውን መድኃኒተ ለኵሉ ዓለም። እስመ አመ በጽሐ እድሜሁ ትትወለድ እምዘርዕከ ይእቲ ባሕርይ። እስመ ንጽሕት ፈድፋደ ምስብዒተ እምነ ፀሐይ።

ወይመጽእ መድኅን እመንበረ መለኮቱ ወየኀድር ላዕሌሃ ወይለብስ ሥጋሃ።

ወአሚሃኒ ለሊከ ትዜንዋ ይቤለኒ እግዚእነ ወእግዚእከ።

አነ ገብርኤል መልአክ ዐቃቢክሙ ለእለ ትጸውርዋ ለባሕርይ እምከርሠ አዳም ወእስከ ከርሠ ሐና ከመ እክላእክሙ እምግብርናት ወርኩስ ኀበ ተኀድር ባሕርይ።

ወሚካኤልኒ ተአዘዘ ኀበ ጽዮን ከመ ይመግባ በኵሉ ኀበ ሖረት።

ወዑርያልኒ ይሜግብ ዕፀ ሳቤቅ እንተ ትከውን መስቀሉ ለመድኅን።

ወአመ ሰቀልዎ በቅንዐቶሙ ሕዝብከ ሀለዎሙ ይድብይዎ ለመስቀሉ እምብዝኀ ተአምራት ዘይከውን ቦቱ ወየኀፍሩ ርእዮሙ መንክራቲሁ።

- 72 -

ቢያዩ እንደ ሕዝብህ እስራኤል ባልካዱትና ባልሰቀሉትም ነበር።
እነሱስ ዜናውን በመስማት ያምኑበታል።
12 ወደ ትንሹ ልጅህ ወደ አድራሚም አልሄደችም። እነሱ ደጎች
ነበሩና ከእንቁ የሚወለደው የሚያደርጋቸውን ተአምራቶችን ድንቅ
ነገሮችን ባዩ ጊዜ ባልሰቀሉትና ባልካዱትም ነበርና። በሁዋላም
በደቀ መዛሙርቱ የሚያምኑ ናቸውና።
13 እንቁ መድሃኒት እየሆነች፣ ከሆድ ወጥታ፣ በህዝቦችህ በእስራኤል
ክፋት ምክንያት ወደ ልጅህ ወደ ሮብኣም ሆድ ገባች። እነሱ
በክህደታቸውና በክፋታቸው ይሰቅሉታልና።
14 ባይሰቀል ኑሮ መድሃኒታችሁ ባልሆነ ነበር። ያለ ሃጢኣት ይሰ
ቀላል። ያለጥፋትም ይነሳልና።
15 ስለዚህ ሁላችሁም ማለት የባህሯ እንቁ በሆዳችሁ ያደረችባችሁንና
ሴቶቻችሁንም ሊያድናችሁ፣ ሊያወጣችሁና ይቅር ሊላችሁ፣ ስለዚህ
ነገር ወደ እናንተ ወደ ሲኦል ይወርዳል። ቅፅሮቹንም ያፈርሳል።
ከኣባትህ ከኣዳም እስከሚመጣው ዘመድህ ኢያቄም፣ ከእናትህ
ከኣዳም ሚስት ከሄዋን እስከ ኖህና እስከ ተርሚዛ፣ እስከ ታራና
እስከ ሚስቱ ኣሚንያ፣ እስከ ኣብርሃምና እስከ ሚስቱ ሳራ፣ እስከ
ይስሃቅና እስከ ሚስቱ ርብቃ፣ እስከ ያእቆብና እስከ ሚስቱ ልያ፣
እስከ ይሁዳና እስከ ሚስቱ ትእማር፣ እስከ ኣባትህና እስከ ሚስቱ
ቤርሳቤህ፣ እስከ ኣንተና እስከ ሚስትህ ተርባና፣ እስከ ልጅህ
ኢዮርብኣምና እስከ ሚስቱ ኣቢሳ፣ እስከ መጣው ዘመድህ እስከ
ኢያቄምና እስከ ሚስቱ ሃና፣ እንቁውን ከተሸከማችሁት ከሁላችሁ
ወንዶች እስከ ሴቶቻችሁ ሁሉ ኣትጠፉም። የባህሯ እንቁ ፃድቃን
በሆናችሁት በወንዶች ትተላለፋለች።
16 የባህሯን እንቁ መሸከሚያ የተሸከሙ ሴቶች ኣይጠፉም። በዚህችው
እንቁ የነፁ ይሆናሉና። እሷ የተቀደሰችና የነፃች ናትና በእሷ
ትቀደሳላችሁ። ትነፃላችሁም። ኣለሙን ሁሉ ስለ እሷና ስለ ፅዮን
ፈጥሯታልና። ፅዮን ግን በበኩርህ ነበረች። ለኢትዮጵያ ህዝቦችም
እስከ ዘላለም መድሃኒታቸው ትሆናለች።
17 እንቁዋም በልጅህ በኢዮርብኣም ሆድ ኣደረች። ለኣለሙ ሁሉ
መድሃኒት ትሆናለች። ዘመኑም በደረሰ ጊዜ ይህችው እንቁ ከዘርህ
ትወለዳለች። ከፀሃይ ሰባት እጅ የነፃች ናትና።
18 ኣዳኙም ከመንበረ መለኮቱ ይመጣል። በላዮም ላይ ያድራል።
ስጋዋንም ይለብሳል።
19 ያንጊዜም ኣንተ ትነግረዋለህ ኣለኝ ጌታዬና ጌታህ።
20 እኔ መልኣኩ ገብርኤል ከኣዳም ጀምሮ እስከ ሃና ድረስ እንቁዋን
ለምትሸከሟት ሁሉ ከባርነትና ከርኩሰት እከለክላችሁ ዘንድ እንቁዋ
በምታድርበት ሁሉ ጠባቂያችሁ ነኝ።
21 ሚካኤል ደግሞ በሄደችበት ሁሉ ያገለግላት ዘንድ ወደ ፅዮን ታዘዘ።
22 ኡራኤል የኣዳኙ መስቀል የምትሆን እፀ ሳቤቅን ይጠብቃል።
23 ህዝቦችህ በቅናታቸው በሰቀሉት ጊዜ በሚፈፅሙት ተኣምራት ልክ
መስቀሉ ከመሬት ላይ ሊጥሉት ኣላቸው። ተኣምራቱንም ኣይተው
ያፍራሉ።

www.ethiopianorthodox.org

24 ወበደኃሪ ይነሥእ ለዕፀ መስቀል ዘርዐ አድራሚስ ወልድከ ፫
መድኀኒተ ዘተፈነዋ ዲበ ምድር።
25 ሚካኤል መልአክ ኀበ ጽዮን ምስለ ዳዊት ወልድከ በኩርከ ዘነሥአ
መንበረ ዳዊት አቡከ።
26 ወአነ ኀበ ባሕርይ ንጽሕት ለዘይነግሥ እስከ ለዓለም ኀበ
ኢዮርብዓም ወልድከ ማእከላዊ።
27 ወዑርኤል መልአክ ኀበ አድራሚ ወልድከ ዘይንእስ።
28 ዘንተ ነገርኩከ ወኢታኅዝን ልበከ በእንተ መድኀኒትከ ወበእንተ
መድኀኒተ ደቂቅከ።
29 ወዘንተ ሶበ ሰምዐ ተኀየለ በውስተ ምስካቡ ወሰገደ ለመልአከ
እግዚአብሔር ወይቤ አእኵቶ ለእግዚአብሔር ለእግዚእየ ወለእግዚእከ አ
ብርሃናዊ መንፈሳዊ ዘአስማዕከኒ ቃለ ዘያስተፌሥሐኒ ዘኢሜቁሳ ለነፍስየ
በእንተ አበዋየ እምርስተ አበውየ ዘተወከፈ ንስሐየ እምድኅረ ምንዳቤየ
ዘነጸረ አንብዕየ ወሰምዐ ገዐርየ ዘርእየ ምንዳቤየ ወኢኀደገኒ ትትኩዝየ
እሞት አላ አስተፍሥሐኒ ዘእንበለ ትፃዕ ነፍስየ እምሥጋየ።
30 እምይእዜሰ ኢየኀዝነኒ መዊት። ወአፈቅሮ ከመ ሕይወት እምይእዜሰ
እሰርዖ ለጽዋዐ ሞት መሪር ከመ መዐር እምይእዜሰ አፈቅራ
ለመቃብር ከመ ማኅደር ዘበአፍራጽ።
ወእመኒ ወረድኩ ወተወረውኩ ውስተ ሲኦል በእንተ አበሳየ
ኢየኀዝነኒ እስመ ሰማዕኩ ቃለ ዘያስተፌሥሐኒ። ወእመኒ ወረድኩ
ውስተ መትሕተ ታሕቲት ማዕምቅተ ሲኦል ዘበእንተ አበሳየ ሚ
ላዕሌየ። ወእመኒ ጠየሰኒ ውስተ እደሁ ወዘረወኒ እስከ አጽናፈ
ምድር ወውስተ ነፋሳት በእንተ አበሳየ ኢየኀዝነኒ። እስመ ሰማዕኩ
ቃለ ዘያስተፌሥሐኒ ዘኢመቁሳ ለነፍስየ እምርስተ አበውየ።
ወትከውን ነፍስየ ምስለ ነፍሰ ዳዊት አቡየ ወምስለ ነፍሰ አብርሃም
ወይስሐቅ ወያዕቆብ አበውየ። ወይመጽእ መድኀን ወያውጽአኒ እምሲ
ኦል ምስለ ኵሎሙ አበውየ ወአዝማድየ ቀደምት ወደኀርት።
ወለደቂቅየኒ በዲበ ምድር ሠለስቱ መላእክት ኀያላን እለ
የዐቅብዎሙ። ረከብኩ መንግሥተ ሰማያት። ወረከብኩ መንግሥተ
ምድር።
መኑ ከመ እግዚአብሔር መሐሪ ዘይምሕር ወይምሕክ ተግባሮ
ዘይሠሪ አበሳ ለመአብሳን ወኢያጠፍእ ዝክረ ነሳሕያን። እስመ
ኵለንታሁ ሥርየት ወኵለንታሁ ምሕረት። ወሎቱ ይደሉ ስብሐት
አሜን።

## ፳ወ፱ በእንተ ስእለተ ሰሎሞን

ወተመይጠ ወአንቃዕደወ ኀበ መልአክ። ወሰፍሐ ክልኤሆን እደዊሁ።
ወይቤ እግዚኦ ቀርበኑ ምጽአቱ ለመድኅን ዘትቤ ወሚመ ርኁቅኑ።
አውሥአ መልአክ ወይቤሎ በ፹ወ፫ ትውልድ እምዘመድከ
ወእምዘርዕከ ይመጽእ ወያድኀነክሙ።
ወእስራኤልሰ ይጸልእ መድኀኒቶሙ። ወይቀንኡ ላዕሌሁ በዘገብረ
ተአምረ ወመንክረ በቅድሜሆሙ። ወይሰቅልዎ ወይቀትልዎ።



24 በመጨረሻም የልጅህ የአድራሚስ ዘር እፀ መስቀሉን ይወስደዋል።
ወደ ምድርም ሶስት መድሃኒቶች ተልከዋል።
25 መልአኩ ሚካኤል ወደ ፅዮንና የአባትህ የዳዊትን ዙፋን ወደ
ወረሰው ወደ በኩር ልጅህ ወደ ዳዊት።
26 እኔ እስከ ዘላለሙ ለሚነግሰው እናት ወደ ሆነችው፣ ወደ ንፅህቷና
እንቁዋና ወደ መካከለኛው ልጅህ ወደ ኢዮርብአም።
27 መልአኩ ኡራኤል ዳግም ወደ ትንሹ ልጅህ ወደ አድራሚስ
ተልኳል።
28 ስለ መድሃኒትህና ስለ ልጆችህ መድሃኒት ልብህን እንዳታሳዝን
ይህንን ነገርኩህ። "
29 ይህንንም በሰማ ጊዜ በመኝታው ውስጥ ተበረታታ። ለእግዚአብሄርም
መልአክ ሰገደ። "የሚያስደስተኝን ቃል ላሰማኝ፣ ስለ በደሌ ነፍሴን
ከአባቶች ርስት ላልነቀላት፣ ከችግሬ በሁዋላ ንስሃየን የተቀበለውን፣
እንባዬን ያየውንና ጩሀቴን የሰማውን፣ ችግሬንም የተመለከተውን፣
ጌታዬንና የብርሃንን ጌታ አመሰግነዋለሁ። ነፍሴ ከስጋዬ ሳትለይ
አስደሰተኝ እንጂ አዝኜ እሞት ዘንድ አልተወኝም።
30 እንግዲህስ ሞት አያሳዝነኝም። እንደ ህይወትም እወደዋለሁ።
ከእንግዲህስ መራራውን የሞት ፅዋ እንደ መአር እሸመጥጠዋለሁ።
ከእንግዲህስ መቃብርን ከፈርጥ እንደ ተሰራ ቤት እወደዋለሁ።
31 ስለ በደሌ ወደ ሲኦል ብወርድና ብወረወር እንኳን አያሳዝነኝም።
ደስ የሚያሰኘኝን ቃል ሰምቻለሁና። በበደሌ ምክንያት ወደ ጥልቁ
የሲኦል ክፍል ብወርድ ምን ቸገረኝ? በእጁም ውስጥ ቢያጠፋኝና
እስከ ምድር ዳርቻ ሁሉ በነፋሳትም ቢዘራኝ አያሳዝነኝም።
የሚያስደስተኝ ቃል ሰምቻለሁና። ነፍሴ ከአባቴ ከዳዊት ነፍስ፣
ከአባቶቼ ከአብርሃም፣ ከይስሃቅና ከያእቆብ ነፍሳት ጋር
ትሆናለችና። መድሃኒትም ይመጣል። ከፊተኞቹና ከሁዋለኞቹ
ዘመዶቼና አባቶቼ ሁሉ ጋር ከሲኦል ያወጣኛል።
32 በምድርም ላይ ልጆቼን ሶስቱ ብርቱዎች መላእክት ይጠብቋቸዋል።
የሰማይን መንግስት አገኘሁ። የምድርንም መንግስት አገኘሁ።
33 እንደ እግዚአብሄር ፈፅሞ የሚምር ቸር ማነው? ለበደለኞች
በደላቸውን የሚፍቅ፣ ሁለንተናው ይቅርታ፣ ሁለንተናው ምህረት
ነውና። ለእሱ ምስጋና ይገባዋል፣ አሜን።"

## ፳፱ ስለ ሰሎሞን ልመና

1 ተመልሶ ወደ መልአኩ አንጋጠ፣ ሁለቱን እጆቹን ዘረጋና "አቤቱ
ያልከኝ ያዳኙ መምጫ ቅርብ ነው ወይንስ ገና ሩቅ?" አለ።
2 መልአኩም መልሶና "በአርባ ሶስተኛው ትውልድ ከዘመድህና
ከወገንህ መጥቶ ያድናችሁዋል።
3 እስራኤል ግን መድሃኒታቸውን ይጠላሉ። በፊታቸውም ተአምራትንና
ድንቅ ነገር ስላደረገ በእሱ ላይ ይቀናሉ። ይሰቅሉታል። ይገድሉታልም።

www.ethiopianorthodox.org

ወይትነሣእ ወያድኅነክሙ እስመ መሐሪ ውእቱ ለነሳሕያን ወኄር ለኀሩያኒሁ። ወናሁ ነገርኩክሙ ጥዩቀ ከመ ኢያኀድገክሙ ውስተ ሲኦል ለዘመዱ እስራኤል እለ ተጸውረት ባሕርይ ኀቤክሙ። ወዘንተ ብሂሎ መልአከ እግዚአብሔር ይቤሎ ሰላም ለከ።

ወአውሥአ ሰሎሞን ወይቤሎ ብቍዕኒ እግዚእየ። አሐተ እስእለከ ወኢትትሐየየኒ ገዓርየ። ወይቤሎ በል ተሰአለኒ። ወአነ አየድዐከ ዘሰ ማዕኩ ወዘርኢኩ።

ወይቤሎ ሰሎሞን ባሕቱ አኀዝን በእንተ እስራኤል ሕዝቡ እለ ኀረየ እምኩሉ በትረ ርስቱ። ቀዳሚ በኩሩ ትቤለኒ ይጠፍኡ እምድኅረ መጽአ መድኅን።

ወካዕበ አውሥአ መልአከ እግዚአብሔር ወይቤሎ እወ ነገርኩከ ከመ ይሰቅልዎ ለመድኅን። ወሶበ ከዐዉ ደሞ በዲበ ዕፀ መስቀል ይከውኑ ዝርዋነ ውስተ ኩሉ ዓለም።

ወይቤ ሰሎሞን እበክዮሙ ለሕዝብየ። አሌ ሎሙ ለሕዝብየ እለ ዘልፈ ያምዕዑ ፈጣሪሆሙ እምቀዳሚ ወእስከ ደኃሪ አነ ወእለ እምቅድሜየ። ወኢይደሉ ከመ ይምሐሩነ በእንተ እከየ ምግባሪነ። እስመ ትውልድ ዘአልብነ አሚነ አሌ ሎሙ እለ ይከዕዉ ደመ ንጹሐ ወእለ ይቀትሉ ጻድቀ ወይትካፈሉ በርበራቲሁ ወኢየአምኑ በቃሉ ወኢየሐውሩ በትእዛዙ ጽኑሕ ደይኖሙ ወንቡር ጌጋዮሙ። ዐቢይ መቅሠፍቶሙ ወጽኑሕ ኀጢአቶሙ። ወኢይሰሪ ሎሙ። ወያዜክሩ ኀጢአተ አበዊሆሙ እስመ ምግባሮሙ ኀጢአት። ወይትሀጕሉ በዘመከሩ ለሊሆሙ።

ወባሕቱሰ አሌ ላ ለነፍስየ እስመ ከበርኩ አኀሥር በሞትየ ወተጠበብኩ በዲበ ምድር። ወእከውን ሐመደ። ምንት ኀይስናሁ ለንጉሥ ለእመ ኢገብረ ሠናየ በዲበ ምድር ምስለ ነዳያን። አሐቲ ድቀቶሙ ውስተ መቃብር ወአሐቲ ፍኖቶሙ ውስተ ማዕምቅት። ምንት በቍዔትነ ለሰብእ እስመ በከ ተፈጠርነ። ወእምድኅረ ንስቲት ንከውን ከመዘኢተፈጠርነ። እስመ ጢስ እስትንፋስነ ለእመ አርመመት ሕቀ ተኀልፍ ነፍስነ። ወቃለ ቀለምጺጽ ልብነ ዘይትሐወሳ ውስተ ሕሊናነ እምከመ ኀለፈት ንከውን ሐመደ። ወያስቈርሩን ፍቁራኒነ ወማኅፈርነ ወአእምሮ ሕሊናነ ዘመልዕልተ ርእስነ እምከመ ተከዕወት ነፍስነ ንከውን ዕፄ ወጺአተ። ወሙቀተ ሥጋነ እምከመ ኀለፈት ከመ ወኢምንትኒ ንከውን ወከመ ሳሕወ ደመና ንኀልፍ። ምንተኬ አብዝኖ ነቢብኒ ኢይበቍዕ። ወሥነ ላህይኒ ይትኀጕል። ወጽንዐ ነገሥትኒ ይጠፍእ። ወኀይለ መኳንንትኒ ይትሀጕል ወኢይትረከብ። ወኩልነ ከመ ጽላሎት ንኀልፍ። ወእምድኅረ ኀለፍነ በሞት ይትረሳዕ ስምነ። ወኢይትረከብ አሠርነ እምድኅረ ሠለስቱ ትውልደ ደቂቅነ። አልቦ ዘይዜክር ስመነ።



4 ለተፀፃቾች ይቅር ባይ፣ ለምርጦች ቸር ነው። ይነሳና ያድናቸዋል።
እንቁዋን የተሸከሙትን የእስራኤል ወገኖች ሁሉ በሲኦል ውስጥም
እንዳይተዋችሁ እነሆ አስረድቼ ነገርኳችሁ። የእግዚአብሄር መልአክም
ይህንን ብሎ ሰላም ለአንተ ይሁን" አለው።
5 ሰሎሞንም መልሶ "ጌታዩ ሆይ! አንዲት ነገርን እለምንሃለሁና
ፍቀድልኝ፣ ጩሄቴንም ቸል አትበልብኝ።" አለው። እሱም "በል
ለምነኝ። እኔም ያየሁትንና የሰማሁትን እነግርሃለሁ" አለው።
6 ሰሎሞንም "ከርስቱ አለቃዎች ሁሉ ስለ መረጣችሁ ስለ ህዝቡ ስለ
እስራኤል አዝናለሁ። አዳኙ ከመጣ በሁዋላ ይጠፋሉ ትለኛለህና"
አለው።
7 የእግዚአብሄር መልአክም እንደገና መልሶ "አዳኙን እንዲሰቅሉት
ነገርኩህ። ደሙንም በምድር ላይ በእፀ መስቀል ላይ ባፈሰሱት
ጊዜ በዓለሙ ሁሉ የተበተኑ ይሆናሉ" አለው።
8 ሰሎሞንም "ለህዝቤ አለቅስላቸዋለሁ። ከፊት እስከ ሁዋላ ዘወትር
ፈጣሪአቸውን የሚያስቆጡ ህዝቦች ናቸውና ወዮላቸው። እኔና
ከእኔም በፊት የነበሩ ስለ ስራችን ክፋት ይቅር ሊለን የማንገባ
ነን። ንፁህ ደምን ለሚያፈሱ ወዮላቸው። ፃድቃንን የሚገድሉ፣
ዘረፋቸውን የሚያካፍሉ፣ በቃሉም የማያምኑ፣ በትእዛዙም የማይሄዱ
ወዮላቸው። መከራቸው ይጠብቃቸዋል። በደላቸው ተቀምጦላቸዋል።
ቅጣታቸው ብዙ ነው። ሃጢአታቸው ይቆያቸዋል። አይፋቅላቸውም።
የአባቶቻቸውንም ሃጢአት ያስታውሳል። ስራቸው ሃጢአት ነው።
ራሳቸው በመከሩበት ይጠፋሉ።
9 ይልቁንም ለነፍሴ ወዮላት። በሃሳር በሞቴ መከሬአለሁና በምድር
ላይ ጥበበኛ ሆንኩ። አመድም እሆናለሁ። በምድር ላይ ከድሆች
ጋር መልካም ነገርን ካላደረገ ንጉስ የሚባለው ከምኑ ላይ ነው?
በመቃብር ውስጥ አወዳደቃቸው አንድ ነው። ወደ ጥልቁም
መንገዳቸው አንዲት ናት።
10 የሰዎች ጥቅማችን ምንድን ነው? በከንቱ ተፈጥረናልና። ከጥቂት
ጊዜ በሁዋላ እንዳልተፈጠርን እንሆናለን። ትንፋሻችን እንደጢስ
ናትና። ጥቂትም ከቆመች ነፍሳችን ትወጣለች። በህሊናችን ውስጥ
የሚንቀሳቀሰው ልባችን የእሳት ፍንጣሪ ነው። ነፍሳችንም ካለፈች
አመድ እንሆናለን። ወዳጆቻችንና ጎረቤቶቻችን እንዲሁም የራሳችን
ህሊና ይፀየፉናል። ነፍሳችንም ከፈሰሰች ትልና ግማት እንሆናለን።
የስጋችንም ሙቀት ካለፈ ባዶ ነው። እንደ ደመናም በንነን እናልፋለን።
11 ምንድን ነው? ነገር ማብዛት አይጠቅምም። የመልክም ደም ግባት
ይጠፋል። የነገስታትም ብርታት ይጠፋል። የመኳንንትም ሃይል
እንዳልነበር ይሆናል። አይገኝምም። ሁላችንም እንደጥላ እናልፋለን።
ከአለፍንም በሁዋላ ስማችን በሞት ይረሳል። ዱካችንም አይገኝም።
ከሶስት የልጆቻችንም ትውልድ በሁዋላ ስማችንን የሚያስታውስ የለም።"

www.ethiopianorthodox.org

ወሶቤሃ አንጸረ ገጸ ኀበ ኢዮርብዓም ወልዱ። ወይቤሎ ወልድየ
ተፀገሣ ለእኪት። ወግበራ ለሠናይት ከመ ትርከብ ብዙኀ መዋዕለ
በዲበ ምድር። ወኢትስግድ ለአማልክት ባዕዳን ወኢታምልኮሙ። አላ
ባሕቱ እግዚአብሔር ፍራህ ወአክብሮ ከመ ትማእ ፀረከ ወጸላእተከ።
ወበሰማያትኒ ከመ ትረስ ማኅደረ አበዊከ ወትረስ ሕይወተ ዘለዓለም።
ወይቤ ጸሐፋ ሊተ ውስተ መጽሐፈ ጦማር ወአንብራ ውስተ
ቀማጥር።
.ወይቤሎ ለሳዶቅ ካህን ቅብዖ ወአንግሦ ለወልድየ በከመ አንገሠኒ
አቡየ ዳዊት እግዚእየ። እንዘ ሕያው አነሂ አነግሦ ለወልድየ
ኢዮርብዓም። ወይኩን ዘርዑ መድኀኒትየ ሊተ ወለአበውየ እስከ
ለዓለም በከመ ነገረኒ መልአከ እግዚአብሔር።

## ፩ በእንተ ዘነግሠ ሮብዓም

ወእምዝ ነሥአ ሳዶቅ ካህን። ወአንገሦ ወቀብዖ። ወገብረ ሎቱ
ዘበሕቱ ወአንበረ ዕፀ ዲበ ደብተራ።. ወረከቦ በስመ አቡሁ ሰሎሞን።
ወአጽዐንዎ ዲበ በቅለ ንጉሥ። ወይቤልዎ በሐ ሕየው አበ ነጋሢ
ወደምፀት ሀገር ወተነፍሐ ቀርን።
ወዘእንበለ ይግባእ ኀበ አቡሁ አዕረፈ ሰሎሞን። ወወሰክዎ ኀበ
መቃብረ አቡሁ ዳዊት። ወለሐውዎ ለሰሎሞን ዐቢየ ላሐ። እስመ
አልቦ ዘተረከበ ዘከማሁ በጥበብ በውእቱ መዋዕል።
ወእምድኅረ ኀለፈ ሰቡዐ መዋዕለ አንገፍዎ ላሐ አቡሁ ለኢዮርብኣም።
ወተጋብኡ ሕዝበ እስራኤል ኀበ ኢዮርብኣም። ወይቤልዎ አቅልል
ለነ ግብረ እስመ አቡከ አክበደ ለነ በኀጢበ ዕፅ ወበውቅረተ እብን
ወበአቅሞ ሰረገላ ለአውርዶ ዕፀ ቄድሮስ።
ወመከረ ምስለ መማክርት ወመላህቅት ዘቤተ ንጉሥ። ወይቤልዎ
አውሥእሙ ሠናየ እስመ አንተ ይእዜ ከመ ሕፃን ዘኢያጽንዐ ሐቋሁ
ለሐዊር። ወይእዜሰ ተናገሮሙ ሠናየ ወበሎሙ እገብር ለኵልክሙ
ኵሎ ዘትፈቅዱ። ወእምከመ ጸንዐት እዴከ ላዕሌሆሙ ትገብር ሕዝበከ
ዘፈቀድከ።
ወአውፅኦሙ ለመላህቅቲሁ ወአብኦሙ ለዕደው ዕንቡዛን እለ ተሐፅኑ
ምስሌሁ። ወመከረ ምስሌሆሙ ወነገሮሙ ዘለአኩ ሎቱ ቤተ እስራኤል
ወዘከመሂ አምከርዎ መላህቅተ ቤተ ንጉሥ።
ወይቤልዎ እሙንቱ ዕንቡዛን አረጋዊ ይገብር ምክረ አእሩግ። ወልሂቅ
ይገብር ምክረ ልሂቃን። ወርሡእሂ ይገብር ምክረ ርሡኣን። ወወሬዛሰ
ዘከማከ ይገብር ምክረ ወራዙት ዘከማሁ። ወእለኒ ርሡኣን ደከሙ ሐቋሆሙ
ከመ ሕፃን ዘኢይክል ሐዊረ። ወበዝንቱሰ ነገር ዘትብል መኑ የዐቢ ትእዛዘ
እግዚእነ ንጉሥ።

- 75 -

12 ፊቱንም ወደ ሮብኣም አዙሮ "ልጄ ሆይ! ክፉ ነገርን ታገሳት።
መልካሙንም አድርግ። በምድር ላይ እድሜህ እንዲበዛ። ለባእድ
ኣማልክት ኣትስገድ። ኣታምልካቸውም። ጠላቶችህን ታሸንፍ ዘንድና
በሰማያት የኣባቶችህን ቤትና የዘላለምን ህይወት ትወርስ ዘንድ
እግዚኣብሄርን ፍራ፣ ኣክብረውም" ኣለው።
13 ሮብኣምም ኣለ። "በክታብ ፃፍልኝ። በሳጥንም ኣስቀምጥልኝ" ኣለው።
14 ካህኑን ሳዶቅንም "ጌታዬና ኣባቴ ዳዊት እንዳነገሰኝ እኔም
በህይወት ሳለሁ ልጄን ሮብኣምን ቅባው። ኣንግሰውም።
የእግዚኣብሄር መልኣክ እንደነገረኝ ለእኔና ለኣባቶቼ እስከ ዘላለም
መድሃኒት ይሁነን" ኣለው።

## ፩ ሮብኣም ስለ መንገሱ

1 ከዚህ በሁዋላ ካህኑ ሳዶቅ ኣነገሰው፣ ቀባውም። እንደ ህጉም
ኣደረገለት። በድንኳኑም ላይ እንጨትን ኣስቀመጠ። በኣባቱም በሰ
ሎሞን ስም ሰየመው። በንጉሱ በቅሎ ላይም ኣስቀመጠው። "ሽህ
ኣመት ንገስ" ኣሉት። ኣገሪቱም ተናወፀች። ነጋሪት ተመታ።
2 ወደ ኣባቱም ሳይገባ ሰሎሞን ሞተ። ወደ ኣባቱ ወደ ዳዊት
መቃብር ጨመሩት። ለሰሎሞንም ታላቅ ልቅሶ ኣለቀሱለት።
በዚያው ዘመን በጥበብ እንደ እሱ ያለ ሰው ኣልነበርም።
3 ከሰባት ቀናት በሁዋላ ሮብኣምን የኣባቱን ልቅሶ ኣስተውት።
የእስራኤል ህዝቦችም ወደ ሮብኣም ተሰብስበው "እንጨት
በመቁረጥና በመፍለጥ፣ ድንጋይ በመጥረብ፣ የቄድሮስን እንጨት
ለማጋዝ ሰረገላ በማቆም ኣባትህ ቀንበርን ኣክብዶብን ነበርና
ኣቅልልን" ኣሉት።
4 እሱም ከቤተ መንግስቱ ኣማካሪዎችና ሽማግሌዎች ጋር መከረ።
እነሱም "ዛሬ ኣንተ በእግሩ ለመሄድ እንዳልፀና ብላቴና ነህና
ለህዝቡ መልካም ነገር ተናገራቸው። የምትሹትን ሁሉ
ኣደርግላችሁዋለሁ በላቸው። እጅህ በላያቸው ላይ ከበረታች በሁዋላ
ህዝብህን እንደ ወደድህ ታደርገዋለህ" ኣሉት።
5 ሽማግሌዎችንም ኣስወጥቶ ከእሱ ጋር ያደጉትን በሃሳብ ያልበሰሉ
ጎልማሶችን ኣስገባቸው። ከእነሱም ጋር መከረ። የእስራኤል ቤተ-
ሰቦች የላኩበትንና የቤተ መንግስቱ ሽማግሌዎች ያማከሩትን
ነገራቸው።
6 እነዚያ ልበ ቢሶች ግን "ያረጀን ምክር የሚያደርግ ያረጀ ነው።
የሽማግሌን ምክር የሚያደርግ ሽማግሌ ነው። የረሱትን ምክር
የሚያደርግ የረሳ ነው። እንዳንተ ያለ ጎልማሳ ግን እሱን የመሰሉ
ጎልማሶችን ምክር ያደርጋል። የረሱት መሄድ እንደማይችል ህፃን
ወገባቸው ደክሟል። ማን ይበልጣል ስለምትለው ግን የጌታችን
የንጉሱ ትእዛዝ ይበልጣል" ኣሉት።

www.ethiopianorthodox.org

ወቦ እምኔሆሙ ዘይሠርር በቅድመ ኢዮርብዓም። ወቦ እምኔሆሙ ዘይመልግ
ሰይፎ። ወቦ እምኔሆሙ ዘይቀልብ ረምሐ። ወቦ ዘይእኅዝ ቀስቶ
ወምጕንጳሁ። ወሶበ ፈጸሙ ተውኔቶሙ አምከርዎ ወይቤልዎ እግዚእነ እንዘ
ንሕነ ምስሌከ ወአንተ ምስሌነ ወአቡከኒ በጥበብ ወሀበከ ኪያነ። ደቂቀ
ምሁራነ ፀብእ እስራኤል ከመ ንልሀቅ ምስሌከ ወከመ ትጽናዕ መንግሥትከ
እምድኅሬሁ።
ወአንተሰ እግዚእነ ኢታርእዮሙ ገጸ ሕመቅ ለእሙንቱ ሕዝብ ከመ
ኢያምስሉከ ድኩመ ወዘኢትክል ገቢረ ጸብእ ላዕሌሆሙ ወላዕለ ፀርከ።
ወእመሰ ርእዩ ለነ ገጸ ድካም በቃል ወበምግባር ንከውን ሕቁራነ
እምኔሆሙ ወኢይሁቡነ አምኃ ወጋዳ ወኢግብረ ወኢጸባሕተ ወትማስን
መንግሥትከ።አላ በሎሙ በጽኑዕ ቃል ወበገንሖ ተናገሮሙ እንዘ
ትብል አቡየሰ ትቤልዎ በዕፅ ወበእብን ወአንሰ እቀንየክሙ በጋጋት
ወበዐቃርብት። እስመ እምግዘፈ አቡየ ይጸንዕ ቍጠጠ ዚአየ።
ወእምክሩ ለአቡየ ዘወለደኒ የዐቢ ምክረ ዚአየ። አልቦ ዘአነትግ
ለክሙ ግብረ ወገብጋበ ዘእንበለ ዘአፈድፍድ ለክሙ በኵሉ።
ወለእመኒ ኢሰማዕክሙ ቃልየ ወኢገበርክሙ ትእዛዝየ እገብር
እንስሳክሙ ሕብልያ። ወደቂቅክሙ ይከውኑ ዔዋ። ወለክሙኒ
መጥባሕት ትበልዐክሙ። ወእነሥእ አህጉሪክሙ ወአዕጻዲክሙ፣
ወአትክልቲክሙ ወዐዘቃቲክሙ ወገራውሂክሙ ወአዕፃዳተ ወፍርክሙ።
ወለክቡራኒክሙ በእደ ሰናስለ ኀፂን። ወለአብዕልቲክሙኒ ሲሳየ
አግብርትየ። ወአንስቲያክሙ ሠርጕ ለቤተ ክቡራንየ። ወዘንተ ቃልየ
ኢያፀርዓ ወኢያሐፅፃ ወኢይመቀሓ ወኢያበጥላ ወእገብራ ፍጡነ።
ወእከትባ ለዓለም።
ስመ ኵሉ ዘይእቲ ምድር ተውህበት መንግሥት ለአበ አቡየ ዳዊት
ወለአቡየ ሰሎሞን። እምድኅሬሁ ወሊተኒ እምድኅረ አቡየ ወሀበኒ
ከማሆሙ። ወእቀንየክሙ አነኒ ከማሆሙ። ወይእዜኒ ምክሩ ወተአዘዙ
ሊተ። ወነገሮሙ ከመዝ ለሊቃውንተ እስራኤል።
ወተንሥኡ ኵሎሙ ኅቡረ በምልእሙ ወይቤሉ። እቱ ቤተከ
እስራኤል። አልብነኑ ዘናነግሥ ዘእንበለ በቤተ ይሁዳ ወቤተ
ብንያሚ። ዐበይናሆሙ ለቤቶሙ ወለሕዝብ ክልኤሆሙ። ወናነግሥ
ዘፈቀድነ ለርእስነ ወለዘሠምረት ነፍስነ።
ወጸሩ ንዋየ ሐቅሎሙ ወጐዩ በምልእሙ ወበጽሑ ሀገረ ሰማርያ
ዘቤተ ኤፍራታ። ወበህየ መከሩ ወአንገለጉ ወተዓፀዉ ቤተ እስራኤል
ነመ ያንግሡ ዘኀረዩ እምኔሆሙ ለዘረከቡ ዕፃ በውስተ ቤተ አቡሁ።
ዐበጽሐ ዕፃ ኀበ ቤተ ኤፍሬም ወልደ ናባጥ ወኀረዩ በውስተ ቤተ
ነቡሁ። ወአንገሥዎ ለኢዮርብዓም ወከመዝ ተከፍለት መንግሥት
ምንበ ኢዮርብዓም ወልደ ሰሎሞን ወኢተርፎ ዘእንበለ ቤተ ብንያሚ
ዐቤተ ይሁዳ አቡሁ።

- 76 -

7 ከመካከላቸውም በሮብአም ፊት የሚወረወሩ፣ ሰይፋቸውን የሚመዙና
ጦርንም የሚቀልቡ ነበሩ፤ ፍላፃዎችንና ሰገባቸውንም የሚይዙ ነበሩ።
ፉከራቸውንም በጨረሱ ጊዜ "ጌታችን እኛ ካንተ ጋር ሳለን፣
አንተንም ከእኛ ጋር ሳለህ፣ አባትህ በጥበቡ እኛን የእስራኤልን
ጦርነት የተማርነውን ልጆች ከአንተ ጋር እናድግ ዘንድና
መንግስትህም ትፀና ዘንድ ሰጥቶሃል።
8 ጌታችን ሆይ! አንተ ግን ደካማና በእነሱና በጠላቶችህ ላይ
ጦርነት ማድረግ የማትችል እንዳትመስላቸው ለህዝቡ የደካማነት
ፊት አታሳያቸው።
9 በቃልም በተግባርም የድካም ሁኔታ ካዩብን ግን በእነሱ ዘንድ
የተናቅን እንሆናለን። እጅ መንሻንም፣ ገፀ በረከቱንም፣ ግብሩንም፣
ቀረጡንም ቢሆን ይከለክሉናል። መንግስትህም ትጠፋለች። ስለዚህ
በብርቱ ቃልና በገናና አነጋገር አባቴ በእንጨትና በድንጋይ
ቀንበር እንዳከበደባችሁ ትናገራላችሁ። እኔ ግን በከባድና በጊንጥ
እገዛችሁዋለሁ። ታናሽቱ ጣቴ ከአባቴ ወገብ ትወፍራለች። ከወለደኝ
ከአባቴ ምክርም የእኔ ምክር ይበልጣል። በሁሉ ነገር
ከምጨምርባችሁ በቀር የምቀንስላችሁ ግብርና ፍርድ የለም።
10 ቃሌን ባትሰሙኝ፣ ትእዛዜን ባታደርጉ ግን ከብቶቻችሁን ለዘረፋ
አደርጋለሁ። ልጆቻችሁም ለምርኮ ይሆናሉ። እናንተንም ሰይፌ
ትበላችሁዋለች። አገራችሁንና ባድማችሁን፣ ተክሎቻችሁንና የውሃ
ጉድጓዶቻችሁን እወስዳለሁ። ክቡራኖቻችሁን በእግር ብረት፣
ሃብታችሁን የባሮች ቀለብ፣ ሴቶቻችሁንም ለክቡራኖች ሽልማት
አደርጋለሁ። ይህችንም ቃሌን አልቀንስም፤ አላጎድላትምም።
አልለውጣትምም። አልሽራትም። በቶሎም አደርጋታለሁ።
11 የዚህች ምድር መንግስት ለአባቴ ዳዊትና ከእሱም በሁዋላ ለአባቴ
ሰሎሞን ተሰጥታለችና። ከአባቴም በሁዋላ ደግሞ ለእኔም ተሰ
ጠችኝ። እኔም ደግሞ እንደ እነሱ እገዛችሁዋለሁ። አሁንም ምክሩና
ታዘዙልኝ በላቸው" አሉት። እንዲሁም ለእስራኤል ሽማግሌዎች
ነገራቸው።
12 ሁሉም በአንድነት ተነስተው "እስራኤል ሆይ ወደ ቤትህ ግባ።
ከይሁዳምና ከብንያም ቤት ሌላ የምናነግሰው የለንም? የሁለቱንም
ህዝቦችና ወገናቸውን እንቢ ብለናቸዋል። ለራሳችን የምንፈልገውንና
ነፍሳችን የሻችውንም እናነግሳለን" አሉ።
13 የጦር መሳሪያዎቻቸውንም ተሸከሙ፤ ሁሉም ሸሹ። በኤፍራታ
ካለችው ከሰማርያ አገርም ደረሱ። በዚያም መከሩ። እጣ የደረሰ
በትንም ለማንገስ በየአባቱ እጣ ተጣጣሉ።
14 እጣውም ከኤፍራታ ቤት ለሆነው ለናባጥ ልጅ ወጣ። ከአባቱም
ቤት መረጡ። ኢዮርብአምንም አነገሱት። እንደዚሁም ከሰሎሞን
ልጅ ከሮብአም ጀምሮ መንግስት ተከፈለች። ለሮብአምም ከብንያምና
ከይሁዳ ቤት በቀር ምንም አልቀረለትም።

www.ethiopianorthodox.org

ወቃለ እግዚአብሔር ኢተሐሰወ ዘይቤሎ ለዳዊት ገብሩ እምፍሬ ክርሥከ አነብር ዲበ መንበርከ።[70] ወካዕበ ይቤ ሥሩዕ ከመ ወርኀ ለዓለም።[71] ወካዕበ ይቤ መሐለ እግዚአብሔር ለዳዊት በጽድቅ ወኢይኔሥሕ።[72]

ዘነግሠ ዲበ መንበረ ዳዊት አቡሁ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘመዱ በሥጋ እምድንግል ዘነበረ ዲበ መንበረ መለኮቱ።

ወበምድርኒ ወሀቦ ዘይነግሥ ዲበ መንበሩ ንጉሠ ኢትዮጵያ በኩሩ ለሰሎሞን ወለዮርብዓም ኢወሀቦ እግዚአብሔር ዘእንበለ ክልኤቱ በትር።

ወንጉሠ ሮምሂ ወልዱ ለሰሎሞን ዘይንእስ ወዘንተ ዘገብረ እግዚአብሔር ከመ ኢይበሉነ አብዳን ሕዝበ አይሁድ በእንተ ሰሎሞን ወበእንተ ሮብዓም ወልዱ እስመ ማእምረ ልብ እግዚአብሔር ከመ ኢያምስሉ ዘንተ ገብረ።

ወለኢዮርብዓምኒ ሰመይዎ ንጉሠ እስራኤል ወእምትውልደ ኢዮርብዓም ኮነት ትውልድ እስከ ኢያቄም ፵ወ፩። ወአሜሃ ተወልዱ ለመልኪ ፪ ደቂቀ ሌዊ ወሴም ወለደ ምናሴሃ ወምናሴ ወለደ ቀለምዮስሃ። ወቀለምዮስኒ ወለደ ኢያቄምሃ። ወኢያቄምኒ ወለዳ ለማርያም ወለተ ዳዊት።

ወካዕበ ኤሊ ወለደ መልኪሃ። ወሜልኪ ወለዶ ለማቲ። ወማቲ ወለዶሙ ለኤሊ ወለያዕቆብ ወለሐና ብእሲተ ኢያቄም።

ወአውሰበ ኤሊ ብእሲተ ወሞተ እንዘ አልቦ ውሉድ። ወአውሰባ ያዕቆብ ለብእሲተ ኤሊ ዮሐዳ ወወለደ ላቲ ዮሴፍሃ ጸራቤ ዘፈኀራ ለማርያም።

ወዮሴፍሰ ወልደ ያዕቆብ በሥጋ ወወልደ ኤሊ በሕገ ኦሪት በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ ከመ ይትዋሰቡ ምስለ ዘመዶሙ በበአብያተ አበዊሆሙ ወኢይትዋሰቡ እምባዕድ ዘመድ።

## ፳ወ፩ በእንተ ማርያም ወለተ ዳዊት

ወበእንተዝኬ ተዐውቀ ከመ ማርያም ወለተ ዳዊት ይእቲ። ወዮሴፍኒ ወልደ ዳዊት ውእቱ።

ወበእንተዝ ተፍኀረት ማርያም ለዮሴፍ ዘመዳ በከመ ተብህለ በወንጌል አ ዮሴፍ ወልደ ዳዊት ኢትፍራህ ነሚኦታ ለማርያም ፍኅርትከ። እስመ ዘይትወለድ እምኔሃ እመንፈስ ቅዱስ ቃለ እግዚአብሔር ውእቱ።[73]

ወተወልደ እምኔሃ እግዚአብሔር ቃል፣ ብርሃን ዘእምብርሃን፣ አምላክ ዘእምአምላክ፣ ወልድ እምአብ ዘመጽአ ወአድኀነ ፍጥረቶ እምእደ ሲኦል ወእምሰይጣን ወእሞት። ባልሐነ ለኵልነ እለ አመነ ቦቱ።

ዑ.7፥12፥መዝ.132፥2
.89፥37
.89፥35
.1፥20

- 77 -

15 ሆኖም ለዳዊት "በዙፋንህ ላይ ከሆድህ ፍሬ አስቀምጣለሁ"[70] ያለው የእግዚአብሄር ቃል አልተዋሸም። ደግሞም እንደ "ጨረቃ ለዘላለም ያበራል"[71] አለ። እንደገና "እግዚአብሄር በእውነት ማለ፤ አይፀፀትም"[72] አለ።

16 በአባቱ በዳዊት ዙፋን የነገሰ እሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እሱም በድንግል በኩል በስጋ ዘመዱ የሆነውና በመንበረ መለኮቱ ላይ የተቀመጠው ነው።

17 በምድርም ደግሞ በዙፋኑ ላይ የሚቀመጥ የኢትዮጲያ ንጉስን ማለትም የሰሎሞንን የበኩር ልጅ ሰጠው። ለሮብኣም ግን ያለ ሁለት ነገድ አልሰጠውም።

18 የሰሎሞን ታናሹ ልጅ የሮም ንጉስ ነው። ይሄውም ሰነፎች የአይሁድ ህዝቦች እግዚአብሄር ይህንን ያደረገው ስለ ንጉስ ሰ ሎሞንና ስለ ልጁ ስለ ሮብኣም ነው እንዳይሉ ነው። ይህንን እንዲሉ እግዚአብሄር ልብን አዋቂ ነውና።

19 ሮብኣምንም የእስራኤል ንጉስ አሉት። ከሮብኣም ትውልድ እስከ ኢያቄም አርባ አንድ ትውልድ ሆነ። ያንጊዜም ለመልኪ ሁለት ልጆች ተወለዱለት። ሌዊና ምናሴ። ምናሴም ቀለምዮስን ወለደ። ቀለምዮስም ኢያቄምን ወለደ። ኢያቄምም የዳዊትን ልጅ ማርያምን ወለዳት።

20 ደግሞም ኤሊ መልኪን ወለደ። መልኪም ማቴን ወለደ። ማቴም ኤሊንና ያእቆብን የኢያቄምን ሚስት ሐናንም ወለዳቸው።

21 ኤሊም ሚስት አገባ። ልጅም ሳይወልድ ሞተ። ያእቆብም የኤሊን ሚስት ዮሃዳን አገባ። የማርያምን እጮኛ ጠራቢውን ዮሴፍንም ወለደ።

22 እግዚአብሄር በየትውልዳቸው ከዘመዶቻቸው ጋር እንዲጋቡና ከባእድ ጋር እንዳይጋቡ ሙሴን ባዘዘው መሰረት ዮሴፍ በስጋ የያእቆብ፣ በኦሪት ህግ ግን የኤሊ ልጅ ነው።

## ፳፩ ስለ ዳዊት ልጅ ስለማርያም

1 በዚህም ምክንያት ማርያም የዳዊት ልጅ እንደ ሆነች ታወቀ። ዮሴ ፍም የዳዊት ልጅ እንደ ሆነ ታወቀ።

2 ስለዚህም ማርያም ለዘመዷ ለዮሴፍ ታጨች። በወንጌል "የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ! እጮኛህን ማርያምን መውሰድ አትፍራ። ከእሷ የሚወለደው የእግዚአብሄር ቃል በመንፈስ ቅዱስ ነውና"[73] እንደ ተባለ።

3 ከእሷም ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ከአምላክ የተገኘ አምላክ የእግዚአብሄር ቃል ይሄውም ከአብ የመጣው ወልድ ተወለደ።

[70] 2ሳሙ.7፥12 መዝ.132፥2
[71] መዝ.89፥37
[72] መዝ.89፥35
[73] ማቴ.1፥20

www.ethiopianorthodox.org

ሰሐበነ ኀበ አቡሁ። ወአዕረገነ ውስተ ሰማያት መንበሩ ከመ ንኩን መዋርስቲሁ። እስመ ውእቱ መፍቀሬ ሰብእ ውእቱ። ወሎቱ ይደሉ ስብሐት እስከ ለዓለም። አሜን።

## ፳ወ፪ በእንተ ንጉሠ ሮም

ወበእንተ ንጉሠ ሮምሂ ንዌጥን ንንግርክሙ ዘሰማዕነ ወዘረከብነ ጽሑፈ ዘርኢነ። መንግሥተ ሮምስ ለያፌት ወልደ ኖኅ ኮነት ክፍሉ ወመንግሥቱ።

ወእንዘ ይነብሩ ገብሩ አህጉረ ዐበይተ ፲ወ፪ ወእለ የአብያ አህጉረ መንግሥቶሙ። ዳርዮስ ሐነጸ እንጦክያ ወጺርስያ ወባርቶንያ ወሮምያ። ወይነብሩ ህየ እለ ነግሡ።

ወቁስጥንጥንያ እምድኅረ ክርስቶስ ሐነጸ ቆስጠንጢኖስ ንጉሥ በስሙ ሶበ አስተርአዮ ትእምርተ መስቀል በውስተ ጸብእ በአምሳለ ከዋክብት ጽሑፋን ውስተ ሰማይ። ወድኅነሂ እምእደ ፀሩ። ወእምአሜሃ ረሰዩ ማኅደሮሙ ህየ ነገሥተ ሮም። ወውእቱ ዳርዮስ ኮነ ዘርዑ ብዙኀ። ወእምዳርዮስ እስከ መዋዕለ ሰሎሞን ኮኑ ፲ወ፰ ትውልድ።

ወእምዘርዐ ዚአሁ ተወልደ ብእሲ ዘስሙ ዘንበሬስ። ወገብረ በጥበብ መጽሐፈ አስጠሉባ። ወረሰየ ከዋክብተ ወመዳልወ ፀሐይ። ወርእየ በደኃሪ ከመ ኢትነብር መንግሥት ኀቤሆሙ ለደቂቀ ያፌት አላ ትፈልስ ኀበ ዘርዐ ዳዊት ነገደ ሴም።

ወሶበ ርእየ ከመዝ ለአከ ኀበ ዳዊት ንጉሥ። ወይቤ ንሣእአ ወለትየ ለወልድከ።

ወነሥአ ዳዊት ንጉሥ ወወሀቦ ለሰሎሞን ወልዱ። ወወለደ እምኔሃ ወሰመዮ አድራሚ።

ወሞተ ውእቱ ቀዳሚ። ወነግሠ ብልጣሶር ዘእምአዝማዲሁ። ወኀጥአ ተባዕተ ውሉደ ዘይነግሥ ድኅሬሁ ዲበ መንበሩ። ወይቀንዕ ከመ ኢይንግሡ ድኅሬሁ ደቂቀ አቡሁ።

ወለአከ ኀበ ሰሎሞን ንጉሥ ጽሒፎ እንዘ ይብል ሰላምእ ለዕበየ መንግሥትከ ወለጥበብከ ክብርት። ወይእዜኒአ ሀበኒአ ወልደከአ ዘእነግሥአ ላዕለ ሀገረ ሮምያአ። እስመ አንሰ ስእንኩአ ወሊደ ተባዕተ ዘእንበለ ፫ አዋልድ። ወእሁቦ እምአዋልድየ ዘፈቀደ። ወእሁቦ መንበርየ። ወይከውን ንጉሠ ውእቱ ወዘርዑ እምድኅሬሁ ውስተ ሀገረ ሮምያ እስከ ለዓለም።

ወሶበ አንበባ ለይእቲ ክርስታስ ንጉሥ ሰሎሞን ኀ ለየ እንዘ ይብል ለእመ ከላእክዎ ወልድየ ይልእክ ኀበ ንጉሠ ሠርቅ። ወይሁቦ ወልዶ ወትበጥል እንተ መከርኩ። ወይእዜሰ እሁቦ።



ፍጥረቱንም ከሲኦልና ከሰይጣን እጅ ከሞትም አዳነን። ያመነውንም ሁላችንንም ወደ አባቱ ሳበን። ወራሾቹ እንሆን ዘንድ ወደ ሰማያዊው ዙፋን ሳበን። እሱ ሰውን ወዳጅ ነውና። ለእሱም ለዘላለሙ ምስጋና ይገባል።

## ፳፪ ስለ ሮም ንጉስ

1 ስለ ሮም ንጉስም የሰማነውን፣ ተፅፎ ያገኘነውንና ያየነውን
ልንነግራችሁ እንጀምራለን። የሮም መንግስት የኖህ ልጅ። የያፌት
እጣ መንግስቱ ናት።
2 እዚያም ሲኖሩ አስራ ሁለት ታላላቅ አገሮችንና ከዚህም የሚበልጡ
የመንግስታቶቻቸውን አገሮችን አደረጉ። ዳርዮስም አንጦኪያንና
ዲሳርያን በርቶንያን ሮምያን ሰራ። የሚነግሱትም ከእዚህ ይቀመጣሉ።
3 ንጉስ ቆስጠንጢኖስም ከክርስቶስ ልደት በሁዋላ በጦርነት ውስጥ
በከዋክብት አምሳያ በሰማይ ላይ የመስቀል ምልክት ተፅፎ በታየው
ጊዜ በስሙ ቁስጥንጥንያን ሰራ። ከጠላቶቹም እጅ ዳነ። ከዚያን
ጊዜ ጀምሮ የሮም ነገስታት ቤተ መንግስታቸውን ከዚህ አደረጉ።
የዳርዮስም ዘሩ ብዙ ሆነ። ከዳርዮስም እስከ ሰሎሞን ዘመን አስራ
ስምንት ትውልዶች ሆኑ ።
4 ከእሱም ዘር ስሙ ዘንበሬስ የተባለ ሰው ተወለደ። በጥበብም
የእስጠሉባን መፅሃፍ አደረገ። የከዋክብትንና የፀሃይን መለኪያ
አደረገ። እሱም ወደ ሴም ነገድ ወደ ዳዊት ዘር ይተላለፋል
እንጂ በያፌት ልጆች ዘንድ መንግስት እንደማትኖር የሁዋላውን
ነገር አየ።
5 ይህንንም ባየ ጊዜ ወደ ንጉስ ዳዊት ዘንድ "ሴት ልጄን ለወንድ
ልጅህ ውሰድ" ሲል ላከበት። ንጉሱ ዳዊትም ወሰዳት። ለልጁ ለሰ
ሎሞንም ሰጣት።
6 ከእሷም ወለደላት። ስሙንም አድራሚስ ብሎ ጠራው።
7 እሱም አስቀድሞ ሞተ። ከዘመዶቹም ውስጥ ብልጣሶር ነገሰ።
ከእሱም በሁዋላ በዙፋኑ የሚቀመጡ ወንዶች ልጆች አልነበሩትም።
ከእሱም በሁዋላ የአባቱ ልጆች እንዳይነግሱ ይቀና ነበር።
8 ለንጉሱ ለሰሎሞንም "ለመንግስትህ ግርማና ለከበረችው ጥበብህ ሰ
ላም ይሁን። አሁንም በሮም አገር ላይ የሚነግስ ወንድ ልጅህን
ስጠኝ። እኔ ከሶስት ሴቶች ልጆች በቀር ወንድ መውለድ ተስኖኛ
ልና። ከሴቶችም ልጆቼ የወደደውን እሰጠዋለሁ። ዙፋኔንም እሰ
ጠዋለሁ፤ እሱና ከእሱም በሁዋላ ዘሩ በሮም አገር ለዘላለም
ይነግሳል" ሲል ፅፎ ላከ።
9 ንጉሱ ሰሎሞንም ይህችን ደብዳቤ ባነበባት ጊዜ በልቡ
"ብከለክለው ወደ ምስራቅ አገር ንጉስ ይልካል። ልጁንም ይሰ
ጠዋል። የመከርኳትም ምክር ትፈርሳለች። ስለዚህ እሰጠዋለሁ" ሲል
አሰበ።

www.ethiopianorthodox.org

10 ወመከረ ምስለ መማክርቲሁ ዘቤተ እስራኤል። ወይቤሎሙ እስመ
ወሀብነ ወልደነ ወደቂቀነ ለብሔረ ኢትዮጵያ። ወኮነ በህየ መንግሥት
ለእስራኤል።
11 ወይእዜኒ ከመ ይኩን ለነ ሣልስ መንግሥት በሀገረ ሮሜ አነሂ
እፌንዎ ለአርዳሚስ ወልድየ ዘይንእስ። ወአንትሙኒ ኢታስተአክዩኒ
በእንተ ዘቀዲሙ ዘነሣእክዎሙ ለደቂቅክሙ። እስመ ይከውን ብፅዐ
ለእግዚአብሔር በእንተ ዘአእመሩ ስሞ ሰብአ ኢትዮጵያ። ወኮንዎ
ሕዝበ። ወከማሁ ሰብአ ሮምኒ ለእመ ወሀብኖሙ ደቂቀነ ይከውኑ
ሕዝበ እግዚአብሔር። ወለነኒ ይትወሀብ ለነ ስም በተብህሎ ወበተሰ
ምዮ ሕዝበ እግዚአብሔር። ነሥኡ መንግሥተ ኢትዮጵያ ወመንግሥተ
ሮምያ። ሕዝበ እስራኤል ወሀቡ ከመ ቀዳሚ ደቂቀክሙ መንእሳን።
ወማእከላውያንሰ ይቁሙ ውስተ ሀገርነ።
2 ወተንሥኡ ወመከሩ ወገብኡ። ወይቤልዎ ንንግሮ ለእግዚእነ ንጉሥ
ዘንተ ነገረ ወይግበር ፈቃዶ።
3 ወይቤሎሙ አስምዑኒ ዘትብሉ።
4 ወይቤልዎ ነሣእከ መላህቅተ ቤትነ። ወይእዜኒ ንሣእ እምእለ
ይቴሐቱ ደቂቀሙ መንእስአን።
5 ወሠምረ በዝንቱ ምክር። ወገብረ ሎሙ በከመ ፈቀዱ። ወሤሞ
ለአድራሚ ወልዱ። ወነሥአ እምእለ ይቴሐቱ መኳንንተ ቤተ
እስራኤል። ወረከበ ዕፀ በስመ አቡሁ ሰሎሞን።
6 ወወሀብዎ ካህነ እምነገደ ሌዋውያን ዘስሙ አኪሚሔል። ወአጽዐንዎ
ዲበ በቅለ ንጉሥ። ወይቤልዎ በሐ ሕየው አበ ነጋሢ። ወይቤሉ
ኵሉ ሕዝብ ርቱዕ ይደልዎ።
7 ወቀብዕዎ ቅብዐ መንግሥት ዕፍረተ ወአዘዝዎ ይዕቀብ ኵሎ ሕገ
መንግሥት። ወአምሐልዎ ከመ ኢያምልክ ባዕደ አማልክተ ዘእንበለ
አምላከ እስራኤል። ወባረክዎ በከመ ባረክዎ ለዳዊት እጉሁ።
ወትእዛዘኒ በከመ አዘዝዎ ከማሁ አዘዝዎ ለአድራሚ። ወአስተፋነውዎ
እስከ ሐይቀ ባሕር።
ወጸሐፈ ወለአከ እንዘ ይብል ንጉሥ ሰሎሞን። ሰላምአ ለብልጣሶር
ንጉሠ ሮሜ ንሣእአ ወልድየ አድራሚ ወሀቦ ወለተከ። ወአንግሦ
ውስተ ሀገረ ሮምያ። እስመ አፍቀርከ ንጉሠ እምዘርአ ዳዊት አቡየ።
ወአነሂ ገበርኩ ፈቃደከ ወለአኩ ለከ ፲ወ፩ መኳንንቲሁ በየማኑ
ወበፀጋሙ እለ የዐቅቡ ሕገ ምስሌሁ። ወይትኤዘዙ ለከ በከመ
ፈቀድከ።
ወበጽሑ ህየ ምስለ ልኡካነ ንጉሠ ሮሜ ምስለ ብዙኅ ክብር ወኵሉ
ንዋይ ዘይትፈቀድ ለብሔረ ሮሜ። ወበጽሑ ሀገረ ሮሜ ኀበ
ብልጣሶር ንጉሥ። ወነገርዎ ኵሎ ዘለአኮሙ። ወአወፈይዎ ለወልዱ።
ወተፈሥሐ ፈድፋደ ብልጣሶር። ወወሀቦ ወለቶ እንተ ትልህቅ እንተ
ስማ አድሎንያ። ወገብረ ዐቢየ ከብካበ በከመ ዕበየ መንግሥቱ።



10 ከአማካሪዎቹ ከእስራኤል ቤት ጋርም መከረ። "ወንዶችና ሴቶች
ልጆቻችንን ለኢትዮጵያ ሰጠን። በዚያም ለእስራኤል መንግስት
ሆነች። እነሆ ዛሬም በሮሜ ሶስተኛ መንግስት እንዲሆንልን እኔም
ትንሹን ልጄን አድራሚስን እልከዋለሁ። እናንተም የኢትዮጵያ
ሰዎች ስሙን ስላወቁና ህዝቦችም ስለሆኑለት እንደ ስእለት
ይሆናልና ስለ ቀደመው ማለትም ልጆቻችሁን ስለ ወሰድኩባችሁ
ነገር ቅር አትሰኙብኝ።
11 እንዲሁም ለሮም ሰዎች ልጆቻችንን ብንሰጣቸው የእግዚአብሄር
ህዝቦች ይሆናሉ። ለእኛም ደግሞ የእግዚአብሄር ህዝቦች
የኢትዮጵያንና የሮምን መንግስት ያዙ ተብሎ ስም ይሰጠናል።
ስለዚህ የእስራኤል ህዝብ ሆይ! እንደ መጀመሪያው ሁሉ ትንሾች
ልጆቻችሁን ስጡ። መካከለኞች ግን በአገራችን ይቁሙ" አላቸው።
12 ተነስተውም መከሩ። ተመልሰውም "ጌታችንን ንጉሱን ይህንን ነገር
እንንገረው። ፈቃዱንም ያድርግ" አሉት።
13 እሱም "የምትሉትን አሰሙኝ" አላቸው።
14 እነሱም አሉት። "ልጆቻችንን ወሰድክ። አሁንም ደግሞ ከእነሱ
ዝቅ ብለው ያሉትን ታናናሾችን ልጆቻችንን ውሰድ። መካከለኞቹ
ግን በአገራቸው ይቁሙ።"
15 እሱም በዚህ ምክር ተስማማ። እንደ ወደዱትም አደረገላቸው።
ልጁን አድራሚንም ሾመው። የበታቶችንና ትንንሾች ልጆቻቸውንም
ወሰደ። ከታናናሾችም የእስራኤል መኳንንት ወሰደ። በአባቱ በሰ
ሎሞንም ስም እንጨትን አደረገ።
16 ከሌዋውያንም ወገን ስሙ አኪሚሄል የተባለ ካህንን ሰጡት።
በንጉሱም በቅሎ አስቀመጡት። "ንጉስ ሆይ ሽህ አመት ንገስ" አሉት።
17 ህዝቡም ሁሉ "ይገባዋል" አሉ። የመንግስት ቅባት የሆነ ሽቶን
ቀቡት። ህገ መንግስቱን ሁሉ እንዲጠብቅ አዘዙት። ከእስራኤልም
አምላክ በቀር ባእድ አማልክትን እንዳያመልክ አማሉት።
ወንድሙንም እንደ መረቁት አድርገው እሱንም መረቁት። እሱንም
እንዳዘዙት አይነት ትእዛዝ አድራሚንም አዘዙት። እስከ ጥልቁ
ባህርም ድረስ ሸኙት።
18 ንጉሱ ሰሎሞንም "ንጉስ ብልጣሶር ሆይ! ሰላም ለአንተ ይሁን።
ልጄን አድራሚን ተቀበለው። ሴት ልጅህንም ስጠው። በሮም
አገርም አንግሰው። ከአባቴ ከዳዊት ዘር ንጉስን ወደሃልና
ፈቃድህን አደረግሁ። በግራና በቀኝ ሆነው ከእሱ ጋር ህግን
የሚጠብቁና እንደ ወደድከው የሚታዘዙልህ አስራ አራት
መኳንንትን ላኩልህ" አለው።
19 ከዚያም ከሮም ንጉስ መልክተኞች ጋር በብዙ . ክብርና ለሮም
ከሚያስፈልገው እቃ ጋር ደረሱ። ሮምም ከንጉሱ ከብላጣሶር ዘንድ
ቀረቡ። የነገራቸውንም ሁሉ ነገሩት። ልጁንም ሰጡት።
20 ብልጣሶርም እጅግ ደስ አለው። ታላቂቱንና ስሟ አድሎንያ
የተባለችውንም ልጁን ሰጠው። እንደ መንግስቱም ታላቅነት ታላቅ

www.ethiopianorthodox.org

ወሤሞ ውስተ ኵሉ ሀገረ ሮምያ። ወባረኮ ላዕሌሁ ወተፈሥሐ ቦቱ።
እስመ ሠናይ ላህዩ ወመንክር ጥበቢሁ። ወጽኑዕ ፈድፋደ በኀይሉ።
21 ወእምዝ እሐተ ዕለተ ፈቀደ ያመክሮ ውስተ ፍትሕ ሶበ መጽአ
ኀቤሁ በዐለ ዐጸደ ወይን።
22 ወከልሐ ሎቱ እንዘ ይብል እግዚእየ ተዐደወኒ ቃልከ። ወአኅለቀ
ዐፀደ ወይንየ አርሳኒ ወልደ ዮዳድ በአባግዒሁ። ወነዋ ውስተ ቤትየ
አንገዝኩ አባግዒሁ። ምንተ ትፈትሕ ላዕሌነ።
23 ወመጽአ በዐለ አባግዕኒ ኀበ ንጉሥ። ወከልሐ እንዘ ይብል አግብአ
ሊተ አባግዕየ እስመ ይነሥአን በእንተ ዘቦአ ውስተ ዐፀደ ወይኑ።
24 ወይቤሎሙ ንጉሥ ሑሩ ተዋቀሱ ኀበ ንጉሥክሙ አድራሚ።
ወዘይቤለክሙ ግበሩ። ወሖሩ ወተዋቀሱ በቅድሜሁ። ሐተቶ ለቀዳማዊ
እንዘ ይብል እፎ በልዓ አባግዕ ዐፀደ ወይንከ። ቈጽለኑ ወሚመ
አዕጹቀ ወሚመ ቆዐ ወሚመ ሥርወ እምጕንዱ።
25 አውሥአ ወይቤሉ በዐለ ዐፀደ ወይን በልዓ አዕጹቂሁ ምስለ አዕጹቀ
ቆዑ። ወኢያትረፋ አሕሩጊሁ ምስለ ጕንዱ።
26 ወካዕበ ሐተቶ ለበዐለ አባግዕ። ወይቤሎ አማንኑ ከመዝ ወአውሥአ
ወይቤሉ በዐለ አባግዕ እግዚእየ በልዓ አዕጹቀ ምስለ ቈጺሊሁ።
27 ወአውሥአ አድራሚ ወይቤ ወዘንቱሰ ይብል በልዓ ቆዐ አማንኑ
ከመዝ።
28 አውሥአ ወይቤ በዐለ አባግዕ አልቦ እግዚእየ ዘእንበለ ይኩን ቆዐ
ሠርፀ ጽጌ በልዓ።

## ፲ወ፫ በእንተ ቀዳሚ ፍትሑ ለአድራሚ ንጉሠ ሮም

ወይቤሎሙ ስምዑኒ ዘእፈትሕ ለክሙ። ለእመ ሠረዋ አሕሩገ ጕንዱ
ሥርዎን ወኵሎን ለከ። ወለእመ በልዓ ቈጽለ አዕጹቅ ወጽጌ ቆዕ
ንሣእ ወቅርፅ ፀምሮን ወደቂቆን እለ ኢተበኵራ። ወእለሰ ተበኵራ
ወወለዳ ኀድግ ሎቱ ለበዐለ አባግዕ።
ወአንከርዎ ኵሎሙ እለ ሰምዑ አውሥኦተ ፍትሑ። ወይቤ
ብልጣሶር በአማን ዝንቱ ፍትሕ ፍትሐ ሕዝበ አምላከ እስራኤል።
ወእምይእዜሰ ለዘሂ ይትዋቀስ ፍታሕ። ወለዘሂ ይጸብእ ጽባእ።
ወለዘሂ ይትኳነን ኰንን። ወለዘሂ የሐዩ አሕዩ። ወለኵሉ በከመ
ፍትሑ ፍታሕ። ወንሥአ ለዛቲ ሀገር ለከ ወለዘርእከ እምድኅሬከ።
ወሠምሩ ኵሎሙ ሰብአ ሀገረ ሮሜ። ወአንገሥዎ ላዕሌሆሙ።
ወተፈሥሑ ቦቱ ዐቢየ ፍሥሓ። እስመ በፈቃዶሙ ወበፈቃደ
እግዚአብሔር ኮነ ከመዝ።

- 80 -

ስርግን አደረገ። በሮም አገር ሁሉ ላይም ሾመው። መረቀውም።
ተደሰተበትም። ደም ግባቱ ያማረ ጥበቡም ድንቅ ሃይሉም የበረታ
ነውና።
21 ከዚህ በሁዋላ አንድ ቀን አንድ የወይን ቦታ ባለቤት ወደ እሱ
በመጣ ጊዜ በፍርድ ሊፈትነው ወደደ።
22 እሱም "ጌታዬ ሆይ ቃልህን አስተላልፍልኝ፤ የዮዳድ ልጅ አርሳኒ
በበጎቹ የወይን ቦታዬን አስጨረሰው። እነሆ በጎቹን በቤቴ ውስጥ
አግኝቻቸውለሁና ስለዚህ ምን ትፈርዳለህ?" ሲል ጠየቀው።
23 ባለበጉም ወደ ንጉሱ መጣ። በወይን ቦታ ስለገቡ "በጎቼን
ያግዱብኛልና በጎቼን አስመልስልኝ" ሲል ጮሀ።
24 ንጉሱም "ሂዱና በንጉሳችሁ በአድራሚስ ዘንድ ተከራከሩ።
የሚላችሁንም አድርጉ" ሲል መለሰላቸው። በፊቱ ተከራከሩ።
25 እሱም "በጎቹ የወይኑን አትክልት እንደት በሉ? ቅጠሉን?
አፅቁን? ጮርቃውን? ወይንስ ከግንዱ ስሩን? ነው" ሲል
የመጀመሪያውን መረመረው።
26 ባለወይን ተከሉም "አፅቁን ከነጮርቃው ከአረጉና ከግንዱ በቀር
ምንም አላስተረፈም" አለው። እንደ ገናም ባለበጉን "ነገሩ እንዲህ
ነው?" ሲል መረመረው። ባለበጉም "ጌታዮ ሆይ አፅቁን ከቅጠሉ
ጋር በሉ" አለው።
27 አድራሚም መልሶ "እሱ ጮርቃ በሉ ይላልና እውነት ነው?" አለው።
28 ባለበጉም "ጌታዮ ሆይ አይደለም። ገና ሳያፈራ የአበባውን ፍንዳቂ
በሉ እንጂ" አለው።

## ፲፫ ስለሮሙ ንጉስ ስለ አድራሚ መጀመሪያ ፍርድ

1 እሱም "የምፈርድላችሁን ስሙኝ" አላቸው። "የግንዱን አረጎች
ነቅለው ከሆነ በጎቹ ሁሉ የአንተ ናቸው። የአፅቁን ቅጠሎችና
የፍሬውን አበባ በልተው ከሆነ ግን ውሰድና ጠጉራቸውን ሸልት።
የቁቦችንም ልጆች ውሰድ። የመጀመሪያ ግልገሎቻቸውን የወለዱትን
ግን ለባለበጉ ተውለት።"
2 ይህንንም የፍርዱን መልስ የሰሙት ሁሉ አደነቁት። ንጉሱ
ብልጣሶርም "በእውነት ይህ ፍርድ የእስራኤል አምላክ ህዝብ
ፍርድ ነው። ከእግዲህ ለሚከራከር ፍረድ። ለሚዋጋም ተዋጋ።
ለሚፈርድበትም ፍረድበት። ለእያንዳንዱም እንደ ፍርዱ ፍረድ።
ይህችንም አገር ለአንተና ከአንተም በሁዋላ ለዘርህ ውሰድ አለ" አለ።
3 የሮም አገር ሰዎች ሁሉ ይህንን ወደዱ። በላያቸውም ላይ አነገሱ
ት። በፈቃዳቸውና በእግዚአብሄር ፈቃድ እንዲህ ሆኗልና ታላቅ
ደስታን አደረጉ።

www.ethiopianorthodox.org

4 ወአኀዞ ፈፀንት ለብልጣሶር። ወእምአሜሃ ይልእኮ ኀበ ጸብእ
ወውስተ ኩሉ ዘፈቀደ። ወውእቱሰ ይነብር ሀገረ።
5 ወእምድኅረዝ ሞተ ብልጣሶር ወአርትዐ መንግሥተ። ወኮነት ሀገረ
ሮሜ ለአድራሚ ለትውልደ ትውልድ። እስመ በፈቃደ እግዚአብሔር
ተውህበ ኩሉ መንግሥተ ዓለም ለዘርአ ሴም። ወግብርናት ለዘርዐ
ካም። ወኀቅትያ ለዘርዐ ያፌት።

## ፰ወ፩ በእንተ ንጉሠ ምድያም

ንጉሠ ምድያምኒ ዘርዐ ሴም ውእቱ። እስመ ዘርዐ ይስሐቅ ኤሳው
ውእቱ ዘወፅአ እምከርሠ እሙ እንዘ ይእኀዝ ያዕቆብ በሰኰናሁ
ወሄደ ብኵርናቲ ለዔሳው በእንተ ተብሲለ ብርስን።
ወበስመ ጽዕለቱ ተሰምየ ስመ መንግሥቱ። እስመ ኤዶም
ትርጕምናሁ ብርስን ብሂል። ወበእንተኬ ተሰምዩ ዘርአ ዔሳው
ኤዶማውያነ። እስመ በስጥመተ ከርሡ ኀደገ ወተሠዕረ እምብኵርናተ
ዘርዐ ሴም።
እስመ ለእመ ኢተአሥረት ነፍስ በትዕግሥት ያወርዶ ለኵሉ ዘሥጋ
ፍትወተ ከርሥ ውስተ መሥገርት። እስመ ሥጋሰ ሥሥዕት ወነፍስሰ
እስርት በትዕግሥት።
ወበእንተዝ ይቤ ጳውሎስ ዘኢትፈቱ ነፍስ ትፈቱ ሥጋ። ወዘኢትፈቱ
ሥጋ ትፈቱ ነፍስ። ወክልኤሆን ይትዐበያ በበይናቲሆን።[74]
ለእመ አጥብዐ ብእሲ ወኀብረት ነፍሱ ምስለ ፍትወተ ሥጋሁ
ይከውን ከመ ዲያብሎስ። ወለእመሰ አሰረ ሥጋሁ ወኀብረ ምስለ
ፍትወተ ነፍሱ ይከውን ከመ ክርስቶስ። እስመ ኩሉ ብእሲ
ዘየሐውር በፍኖት ርትዕት ርእሱ ክርስቶስ ይቤሉ ሐዋርያት።
ወእግዚእነኒ ይቤሎሙ ለአርዳኢሁ በመንፈስ ሑሩ። ወፍትወተ
ሥጋክሙ ኢትግበሩ።[75] ወዘንተ ሰሚዖሙ ኀደጉ ኩሎ ፍትወተ ሥጋ።
ወይቤልዎ ለእግዚእነ ናሁኬ ኀደግነ ኩሎ ወተለውናከ። ምንት
አስብነ።
ወይቤሎሙ መድኀኒነ እስመ ተመሰልክሙ በሥጋ ከመ መላእክት።
ወትገብሩ ኀይለ ከማየ። ወናሁ አባሕኩክሙ ታንሥኡ ምውታነ።
ወወሀብኩክሙ ሥልጣነ ትፈውሱ ድውያነ። ወትኪዱ ኩሎ ኀይለ
ጸላኢ። ወበዳግም ምጽአትየ ትኴንንዎሙ ወታስተኀፍርዎሙ ለ፲ወ፪
ነገደ እስራኤል በእንተ ዘኢአምኑ ኪያየ። ወአስተሐቀሩ ስብሐትየ።
ወለእለሰ የአምኑ ብየ ታዐብይዎሙ ወታስተፌሥሕዎሙ ምስሌክሙ
በመንግሥትየ።[76]

ላ.4፥17
ላ.4፥16
ቴ.10፥8፥19፥28፥ሉቃ.10፥19



4 ብልጣሶርንም ንዳድ አመመው። እሱንም ከዚያው ጊዜ ጀምሮ ወደ
ጦርነትና ወደ ሚሻው ሁሉ ይልከዋል። እሱ ግን አገር ውስጥ
ይቀመጥ ነበር።
5 ከዚህ በሁዋላ ብልጣሶር ሞተ። መንግስቱንም አፀና። የሮምም አገር
ለአድራሚና ለልጅ ልጁም ሆነች። በእግዚአብሄር ፈቃድ የአለም
መንግስት ሁሉ ለሴም ዘር፣ ባርነት ላካም ዘር፣ ሽንገላም ለያፌት
ዘር ተሰጥቷልና።

## ፹፩ ስለ ምድያም ንጉስ

1 የምድያምም ንጉስ የሴም ዘር ነው። የይስሃቅ ዘርም ያእቆብ
ከእናቱ ማህፀን ሽኮናውን ይዞት የወጣው ኤሳው ነው። በምስር
ንፍሮ ምክንያት የኤሳውን በኩርነትም የቀማውም እሱ ነው።
2 የመንግስቱም ስም በስድብ ስሙ ተሰየመ። የኤዶም ትርጉሙ ምስር
ማለት ነውና። በሆዱ ምክንያት ከሴም ዘር በኩርነት ተሸሮአልና።
ስለዚህ የኤሳው ዘሮች ኤዶማውያን ተባሉ።
3 ነፍስ በትእግስት ካልታሰረች የሆድ ፍላጎት ስጋ ለባሹን ሁሉ ወደ
ወጥመድ ያወርደዋል። ስጋ ስሱ፣ ነፍስ ግን በትእግስት የታሰረች ናትና።
4 ስለዚህ ጳውሎስ "ነፍስ የማትወደውን ስጋ ትወዳለች። ስጋ
የማትወደውንም ነፍስ ትወዳለች። ሁለቱም እርስ በርሳቸው
ይገፋፋሉ"[74] አለ።
5 ሰው ቢጨክንና ነፍሱ ከስጋው ፍላጎት ጋር ብትተባበር እንደ
ዲያብሎስ ይሆናል። ስጋውን ቢገታና ከነፍሱ ፍላጎት ጋር
ቢተባበር ግን እንደ ክርስቶስ ይሆናል። በቀና መንገድ ለሚሄድ
ሰው ሁሉ ራሱ ክርስቶስ ነውና።
6 ሃዋርያትም "ጌታ ደቀ መዛሙርቱን በመንፈስ ተመላለሱ።
የስጋችሁን ምኞት አታድርጉ"[75] አላቸው አሉ። እነሱም ሰምተው
ሁሉም የስጋ ምኞታቸውን ተው። ጌታንም "እነሆ እኛ ሁሉን
ትተን ተከተልንህ ዋጋችን ምንድን ነው?" አሉት።
7 መድሃኒታችንም "ስጋ ለባሾች ሁናችሁ በመላእክት ተመስላችሁዋልና
እንደ እኔ ሃይልን ታደርጋላችሁ። እነሆ ሙታንን ታነሱ ዘንድ
አሰለጠንኳችሁ። ድውያንን ትፈውሱ ዘንድና የሰይጣንን ሃይል ሁሉ
ትረግጡ ዘንድ ስልጣንን ሰጠሁዋችሁ። በዳግም ምፅአቴም በአስራ
ሁለቱ ነገደ እስራኤል ትፈርዳላችሁ። ታሳፍሯቸዋላችሁም። ይሄውም
በእኔ ስለ አላመኑና ምስጋናየንም ስለ አቃለሉ ነው።
የሚያምኑብኝን ግን ከፍ ከፍ ታደርጓቸዋላችሁ፤ ከእናንተም ጋር
በመንግስቴ ታስደስቷቸዋላችሁ"[76] አላቸው።

[74] ገላ.4፥17
[75] ገላ.4፥16
[76] ማቴ.10፥8፥19፥28፥ሉቃ.10፥19

www.ethiopianorthodox.org

## ፳ወ፭ በእንተ ንጉሠ ባቢሎን

ወንጉሠ ባቢሎንሂ ዘርዐ ሴም ውእቱ። ወንነግረክሙ ጥዩቀ ከመ ዘርዐ ሴም ንጉሠ ባቢሎን።
ወሀሎ በውእቱ መዋዕል በመንግሥተ ምናሴ ንጉሠ እስራኤል ወሀሎ ፩ ብእሲ ዘስሙ ከርሚን ፈራሄ እግዚአብሔር። ወይገብር ብዙኀ ምጽዋተ ለነዳያነ እስራኤል።
ወሶበሂ ይሠውዕ ለቤተ እግዚአብሔር ይገብር በንጹሕ። ወዓሥራተሂ ይሁብ አመክዒቦ። ወበኩሉ ፍኖቱ ሠናይ። ወአልቦ ወኢምንተኒ እኩየ በቅድሜሁ።
ወሰይጣንሰ ጸላኤ ሠናያት ይቀንዕ ላዕሌሁ በዘርእየ ሠናየ ፍኖቶ። ወውእቱሰ ብእሲ ባዕል ጥቀ አግማለ ወአፍራሰ ወመራዕየ እንስሳ ወአልህምተ ወርቀ ወብሩረ ወአልባሰ ክቡረ።
ወይሴሲ በቅለ ንጉሥ በአርማቴም ሀገረ እስራኤል። እስመ ደወሉሰ ብሔረ ይሁዳ ክፍለ አበዊሁ። ወበእንተ ፍቅረ ንዋይ ሖረ ውስተ አርማቴም ከመ ይንበር። ወአንበርዎ እስራኤል በእንተ ብዕሉ እስመ ቦ ብዙኀ ንዋይ ወይፈርህ መኳንንተ።

## ፳ወ፮ በእንተ ሰማዕተ ሐሰት

ወሀሎ አሐዱ ጸዋግ እምዘርዐ ብንያም ዘስሙ ብንያስ ዘይስሕብ በቅለ ንጉሠ እስራኤል። ወይሴስዮ ከርሚን ምስለ በቅለ ንጉሥ ምናሴ።
ወእምኀሩ ለከርሚን ሀለዉ እለ ይቀንዑ ላዕሌሁ በእንተ ማዕር ወዐዘቅት ወበእንተ ብዝኀ እንስሳ ወአግብርት። እስመ ይእቲ ምድር ርስተ አበዊሆሙ ይእቲ። ወበእንተ ዝንቱ ይፈቅዱ ያርኅቅዎ እምሀገሮሙ ወይዋሕይዎ በእኪት ለብንያስ ሰሐቤ በቅለ ንጉሥ።
ወሐመይዎ ወይቤልዎ ይፀርፍ ዝንቱ ከርሚን ፀሬፈ ላዕለ ንጉሠ እሥራኤል መሲሑ ለእግዚአብሔር እንዘ ይብል ዝንቱ ንጉሥ ኢኮነ ወልደ አግዓዚት አላ ወልደ አመት አረጋዊት እንተ ተሳየጥዋ በክልኤ መሥፈርተ ቆሮስ ለገብረ ማኀፈድ ወግንፋል።
ወአንተ ተዋቀሶ በኀበ ንጉሥ ወዝልፎ እስመ ንከውነከ ስምዐ በቅድመ ንጉሥ ወኢናኀፍረከ።
ወአቀሙ ኪዳነ። ወመሐሉ ሎቱ ከመ ይኩኑ ስምዐ ላዕሌሁ ለከርሚን በሐሰት ዘኢተናገረ በልሳኑ። ወውስተ ሕሊናሁኒ ጥቀ ኢዐርገ ውእቱ ነገር።
ወሖረ ብንያስ ኀበ እግዚኡ ንጉሥ። ወነገሮ ዘንተ ኵሎ።
ወይቤሎ ቦኑ ዘሰምዐ ምስሌከ። ወአውሥአ ወይቤ እወ ሀለዉ እለ ሰምዑ ክልኤቱ ዐበይተ እስራኤል ዘእምአርማቴም።

## ፳፭ ስለ ባቢሎን ንጉስ

1 የባቢሎን ንጉስም የሴም ዘር ነው። የባቢሎን ንጉስ የሴም ዘር እንደሆነ እናስረዳችሁአለን።
2 በእስራኤል ንጉስ በምናሴ መንግስት ዘመን ስሙ ከርሚን የተባለ እግዚአብሄርን የሚፈራ ሰው ነበር። ብዙ ምፅዋትን ለእስራኤል ድሆች ያደርግ ነበር።
3 ለቤተ እግዚአብሄርም በሚሰዋበት ጊዜ በንፁህ ያደርገው ነበር። አስራቱንም እጥፍ ድርብ አድርጎ ይሰጥ ነበር። በአካሄዱ ሁሉም የአማረ ነበር። በፊቱም አንዳች ክፉ ነገር አልነበረም።
4 የበጎ ስራዎች ጠላት የሆነ ሰይጣን ግን በእሱና ባየው መልካም አካሄድ ሁሉ ይቀና ነበር። ሰውየው በግመሎች፣ በፈረሶች፣ በቤት እንስሳትና በከብት በወርቅ፣ በብርና በከበሩ ልብሶችም የበለፀገ ነበርና።
5 በእስራኤል አገር በአርማቴም የንጉስ በቅሎዎችን ይመግብ ነበር። የአባቶቹ ትውልድና አውራጃው ግን የይሁዳ አውራጃ ነበር። በገንዘብም ምክንያት በዚያ ይቀመጥ ዘንድ ወደ አርማቴም ሄደ። እስራኤልም በሃብቱ ምክንያት አስቀመጡት። ሃብቱ ብዙ ነበርና መኳንንቱንም ይፈራ ነበርና።

## ፳፮ ስለ ሃሰት ምስክር

1 ከብንያም ወገን የሆነና ስሙ ብንያስ የተባለ አንድ የእስራኤልን ንጉስ በቅሎ የሚስብ ክፉ ሰው ነበር። ከርሜንም ከንጉሡ ከምናሴ በቅሎ ጋር ይመግበው ነበር።
2 የከርሜን ጎረቤቶችም ስለ ሳሩ፣ ስለውሃው ጉድጓድ፣ ስለ እንስሳቱ ብዛትና ስለ ባሪያዎቹ የሚቀኑበት ነበሩ። ያች ምድር የአባቶቻቸው ርስት ነበረችና ከአገራቸው ሊያስወግዱት ይሹ ነበር። የንጉሱን በቅሎ ሳቢ ብንያስንም በክፉ ሊያሞኙት ፈለጉ።
3 "ይህ ከርሜን በእግዚአብሄር ሹም በንጉሱ ላይ ይህ ንጉስ ለወፍጮና ለቡኮ ስራ በሁለት መስፈሪያ እህል የተገዛች የአሮጊት ባሪያ ልጅ ነው እንጂ የባላባት ልጅ አይደለም እያለ ይሳደባል" ሲሉ ነገር ሰሩበት።
4 "ስለዚህ አንተ በንጉሱ ዘንድ ክሰሰው። አዋርደውም። እኛም በንጉሱ ዘንድ ምስክር እንሆንሃለን። አናሳፍርልሃለንም" አሉት።
5 እነሱም በቃሉ ባልተናገረው በሃሳቡም ፈፅሞ ባልነበረ በዚሁ ነገር በከርሜን ላይ በሃሰት ሊመሰክሩ ተማማሉ። ቃል ኪዳንንም አቆሙ።
6 ብንያስም ወደ ጌታው ወደ ንጉሱ ሄዶ ይህንን ነገረው።
7 እሱም "ይህንን የሰማ አለን? " አለው። መልሶም "አዎ! ከአርማቴም የሆኑ ሁለት የእስራኤል ታላላቅ ሰዎች አሉ" አለው።

www.ethiopianorthodox.org

ወይቤ ንጉሥ ሑርኬ አምጽእሙ በኅቡእ ከመ ንጠይቆሙ ለእመ
የኀብሩ ምስለ ቃልከ ወንምትሮ ርእሶ።
8 ወሖረ ወአምጽእሙ ለዘርዮስ ወከርሜሎስ ነገደ ምናሴ። እስመ
ምስሌሆሙ ተካየደ ከመ ኢያፍርኆ በቅድመ ንጉሥ በእንተ ስምዐ
ሐሰቶሙ።
9 ወበባሕቲቶሙ መከሩ በፍኖት እንዘ ይብሉ። ሶበ ነገርናሁ ለንጉሥ
ለእመ ተጠየቅነ በበባሕቲትነ ከመ ያእምር ጽድቀ ቃልነ ወይብለነ
በአይቴ ሰማዕክሙ ዘንተ ቃለ። ንብሎ በበባሕቲትነ እንዘ ንሰቲ
ወይነ ምስሌሁ። ወሶበ ይቤለነ ምንት ዕለቱ ንብሎ እመ ሠርቀ
ወርኀ እንተ ኀለፈት ኀሙስ። ወሶበ ይቤለነ አየ ጊዜ ንብሎ በ፱
ሰዓት እንዘ ይነብር ማዕከሌነ ወንሰቲ ወይነ ኀቡረ። ወሶበ ተስእለነ
እንዘ ይብል በምንት ሰተይክምዎ ወአይቴ ነበርክሙ ንብሎ
በቀናዲል ዘወርቅ ወምንባሪነሂ ውስተ ጽርሕ ኅቡረ ውስተ
ምፅንጋዕ።
10 ወበዛቲ እኪት ምክር ኀብሩ በውስተ ፍኖት። ወሶበ በጽሑ ኀበ
ንጉሥ አብጽሖሙ ብንያስ። ወሐተቶሙ ንጉሥ ወነገርዎ ኩሎ
ምክረ ሐሰቶሙ። ወተስእሎሙ በከመ መከሩ በፍኖት ጊዜሁ፣
ወዕለቶ፣ ወሰዓቶ፣ ወመስቴሆሙ፣ ወመናብርቲሆሙ። ወነገርዎ በከመ
አዘዘ እግዚአብሔር ይጠይቁ ፍትሐ ነገሥት ወመኳንንት። ወኩሎሙ
እለ ይነብሩ በልዑል መንበር በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ።
11 ወዘንተ ሶበ ተጠየቀ ንጉሥ ጸውዖ ለሊቀ ሐራሁ ዘይቀውም
ቅድሜሁ ወይቤሎ ሑር ንግሀ በጽባሕ ወዕግታ ለቤተ ካርሚን
ወኢያምስጥከ ፩ እምእሊኣሁ ኢተባዕት ወኢአንስት። ቅትል በአፈ
ኀፂን። ወለሊሁኒ ምትር ርእሶ። ወአምጽእ ኩሎ ንዋዮ ወበርበሮ
እንስሳሁ ወወርቆ ወብሩሮ።
12 ወተፈሥሑ ወገብኡ እሙንቱ ሐሳውያን ውስተ ሀገሮሙ። ወሖሩ
ውስተ ቤተ ካርሚን። ወተናገርዎ በነገረ ሰላም። ወይዌድስዎ
ወይስሕቁ በቅድሜሁ እንዘ ውስተ ልቦሙ እኪት።
13 አሚሃኬ ተፈጸመ ላዕሌሆሙ ትንቢተ ዳዊት ዘይቤ
እለ ይትናገሩ ሰላመ ምስለ ቢጾሙ።
ወእኩይ ውስተ ልቦሙ።
ሀቦሙ በከመ እከየ ምግባሮሙ።
ወበከመ እከየ ኀሊናሆሙ።[77] ወእሙንቱሰ ሰከሩ በውስተ ቤተ
ከርሚን። ወኖሙ ኅቡረ ምስሌሁ።
14 ወሶበ ኖሙ ናሁ ተፈነወ መልአከ እግዚአብሔር ኀበ ካርሚን።
ወአንቅሖ ወይቤሎ ኅድግ ኩሎ ንዋየከ። ወአድኅን ርእሰከ እስመ
ተአዘዘ እምኀበ ምናሴ ንጉሥ ከመ ይምትሩ ርእሰከ። ወንሣእ
እምንዋይከ መጠነ ትክል ዘፈቀድከ። ወጕየይ ውስተ ብሔረ ባዕድ
እስመ ቀታሌ ነቢያት ወንሣዔ ደመ ንጹሐን ውእቱ ምናሴ።

[7] መዝ28፡3-4



ንጉሱም "ቃላቸው ከቃልህ ጋር አንድ ከሆነ እራሱን እንቆርጠው
ዘንድ እንጠይቃቸዋለንና ሂድና በስውር አምጣቸው" አለው።
8 በሃሰት ምስክርነት በንጉሱ ፊት ሊያሳፍሩት ከእነሱ ጋር ቃል
ኪዳን ገብቷልና ዘርዮስና ከርሜሎስ የተባሉ የምናሴ ነገዶችን አመጣ።
9 እነሱም ለብቻቸው በመንገድ እንዲህ ሲሉ መከሩ። "ለንጉሱ
ስንናገር የነገሩን እውነተኛነት ሊያውቅ ለየብቻችን ይህን ቃል የት
ሰማችሁት ያለን እንደሆን ከእሱ ጋር ወይን ጠጅ እየጠጣን ሳለን
ለየራሳችን ነው የሰማነው እንለዋለን። ቀኑ መቼ ነው? ካለን
ያለፈው ሃሙስ የመባቻለት ነው እንለዋለን። በስንት ሰአት ነው?
ካለን በዘጠኝ ሰአት በመካከላችን ተቀምጦ የወይን ጠጅ በአንድነት
እየጠጣን ሳለን ነው እንለዋለን። በምን ጠጣችሁ? የትስ ተቀምጣችሁ
ነበር? ካለን የጠጣነው በወርቅ ዋንጫ ነው። የሰማነውም በቤት
ውስጥ በማረፊያ ክፍል ተቀምጠን ነው እንለዋለን" ሲሉ መከሩ።
10 በዚህችም ክፉ ምክር በመንገድ ተስማሙ። ከንጉሱ ዘንድም በደረሱ
ጊዜ ብንያስ ወደ ንጉሱ አስገባቸው። ንጉሱም መረመራቸው። የሃሰ
ቱንም ምክር ሁሉ ነገሩት። በመንገድ እንደተማከሩትም ጊዜውን፣
ቀኑን፣ ሰአቱን፣ የመጠጡን አይነትና አቀማመጣቸውንም ሁሉ
ጠየቃቸው። ነገስታት፣ መኳንንትና በታላላቅ የፍርድ ወንበር
የሚቀመጡ ሁሉ ፍርዱን ይረዱ እግዚአብሄር ሙሴን ባዘዘው መሰረትም
ነገሩት።
11 ንጉሱም ይህንን በተረዳ ጊዜ በፊቱ የሚቆመውን የሰራዊቱን አለቃ
ጠራውና "ነገ ጠዋት ገስግሰህ የከርሜንን ቤት ከበባት። ከእነሱ
ወንድም ቢሆን፣ ሴትም ቢሆን፣ አንድም እንዳያመልጥህ። በጦር
መሳሪያ ግደል፤ እሱንም ራሱን ቁረጥ፤ ሃብቱንም ሁሉ አምጣ፤
እንስሳውንም ወርቁንም ብሩንም ዝረፍ።" አለው።
12 እነዚያም ቀጣፊዎች እየተደሰቱ ወደ አገራቸው ተመለሱ። ወደ
ካርሚንም ቤት ሄደው በሰላም አነጋገር ተናገሩት። በልባቸውም
ክፋት ሳለ እሱን እያሞካሹ ይስቁበት ነበር።
13 ያንጊዜም "ከባልንጀሮቻቸው ጋር የሰላም ቃልን የሚናገሩ፣
በልባቸውም ክፋት ያለ፣ እንደ ልባቸውም ክፋት ሰጣቸው"[77]
የሚለው የዳዊት ትንቢት በእነሱ ላይ ተፈፀመ። እነሱ ግን
በከርሚን ቤት ሰከሩ። ከእሱም ጋር በአንድነት ተኙ።
14 በተኙም ጊዜ የእግዚአብሄር መልአክ ወደ ከርሚን ተላከ።
ቀስቅሶም "ሃብትህን ሁሉ ተው። ራስክንም አድን።ከንጉሱ ከምናሴ
ዘንድ ራስክን ይቆርጡ ዘንድ ታዝዟልና የምትሻውንና የምትችለውን
ያህል ከሃብትህ ውሰድ። ወደ ባእድ አገርም ሽሽ። ምናሴ
የነቢያት ገዳይና የንፁሃንን ደም ፈሳሺ ነውና" አለው።

[77] መዝ.28፡3-4

15 ወእምዝ ተንሥአ ሶቤሃ ወኀሠሠ ወርቀ አስከሬነ። ወነሥአ ወአንቅሃ
ለብእሲቱ ምስለ ክልኤ ደቂቁ። ወካዕበ አንቅሐ አግብርቲሁ እለ
ኀረየ። ወአጸርሙ ንዋየ ክብር ወወፅአ በሌሊት። ወፈነዎሙ
ለብእሲቱ ወለደቂቁ ምስለ ክልኤ አግብርቲሁ ይባኡ ኢየሩሳሌም።
16 ውእቱሰ ሖረ ምስለ ክልኤ አግብርቲሁ ርኁቀ ብሔረ መጠነ
ምሕዋረ ፫ አውራኀ። ወበጽሐ ብሔረ ባቢሎን ወቦአ ኀበ በላዖን
ንጉሠ ባቢሎን። ወአብአ አምኃ ሎቱ። ወነገሮ ዘከመ መጽአ
ኀቤሁ።
17 ወአፍቀሮ በላዖን ለከርሚን። ወወሀቦ ማኅደረ በአግዋረ ቤተ
ነጋዲሁ።
18 ወነጋዲሁሰ ሖረ ርኁቀ ብሔረ መጠነ ፫ ዓመት።
19 ወለእሉሰ እለ ሐሰዉ ስምዐ ቀተልዎሙ በውስተ ምስካብ በቤት።
20 ወአፍቀረቶ ለከርሚን ብእሲተ ነጋዲ። ወተስሕተት ቦቱ። ወፀንሰት
እስመ እኩይ ምግባሪሆን ለአንስት። እስመ ኀደጋ ብእሲሃ እንዘ
ፅንስት ይእቲ። ወወለደት ወወሀበት ለሐፃኒት ወአልሀቀት።
ወበካልእ ዓመት ተስሕተት ወፀንሰት እም ኀበ ከርሚን። እስመ
ሠናይ ላህዩ ለከርሚን ፈድፋደ በውስተ እስራኤል።
21 ወይእቲሰ ፈቀደት ለዘፀንሰቶ ወልዳ ትግድፎ ውስተ ባሕር
ወትጽንሖ ለነጋዲ ብእሲሃ ከመ ዘኢተስሕተት ወኢገብረት ምንተኒ።
22 በከመ ይቤ ሰሎሞን ጠቢብ ፫ የዐጽበኒ በሕሊናየ። ወራብዮሙሰ
ስእንኩ ጠይቆቶ። አሠረ ንስር በውስተ ሰማይ፣ ወፍኖተ አርዌ
ምድር በዲበ ኩኩሕ፣ ወፍኖተ ሐመር በዲበ ባሕር።[78] ወራብዮሙሰ
ስእንኩ ጠይቆ ዘይቤ በእንተ ብእሲት እኪት እንተ ትዔምፅ ምታ
ወተኀፂባ ትነብር ከመ ዘኢገብረት ወትምሕል እንዘ ትሔሱ።
23 ወአሜሃ ብእሲተ በላዖን ንጉሠ ባቢሎን ፀንሰት። ወወለደት አምሳለ
ንስር ዘአልቦ ክንፈ ኩለንታሁ ያፍ ፍጹም።
24 ወጸውዐታ ለአመታ እንተ ኀርየት ወፈነወቶ ውስተ ምቅላደ መሶብ
ወአዘዘታ ዘእንበለ ያእምር አሐዱ ትገሮ ውስተ ባሕር።
25 ወይእቲኒ ብእሲተ ነጋዲ በጽሐ ወሊዶታ። ወወለደት ሕፃነ ተባዕተ
መምሕረ ዘሠናይ ላህዩ። ወዘእንበለ ታጥብዎ ጸውዐታ ለአመታ
እንተ ኀረየት። ወፈነወት ውስተ ቀማጥረ ሳጥን። ወአዘዘታ ዘእንበለ
ያእምር አሐዱ ትገሮ ውስተ ባሕር። እስመ ፈርሀት ብእሲሃ።
26 ወበአሐቲ ሌሊት ወለዳ ምስለ ብእሲተ ንጉሥ። ወበአፈ ጽባሕ
ፈነዋ አእማቲሆን ከመ ይውግራሆሙ ውስተ ባሕር ለደቂቆን።
ወበፈቃደ እግዚአብሔር ተራከባ እላ አእማት ዘእንበለ ይውግራሆሙ
ውስተ ባሕር። ወተናገራ በበይናቲሆን።
27 ወሐተተታ አመተ ንጉሥ ለአመተ ነጋዲ ወትቤላ ምንት ዘውስተ
ሣጹንኪ። ወአርአየታ ሕፃነ ሠናየ። ወትቤላ ለምንት አምጻእኪዮ
ዝየ።

78 ምሳ.30፥18

- 84 -

15 ከዚህ በሁዋላ ወዲያውኑ ተነሳ። የተቀበረውንም ወርቅ ፈለገና
ወሰደ። ሚስቱንም ከሁለት ልጆቹ ጋር ቀሰቀሳት። ደግሞም
የመረጣቸውን ባሪያዎቹን ቀሰቀሰ። የክብር እቃዎችንም
አሸከማቸው። በሌሊትም ወጣ። ኢየሩሳሌምም ይገቡ ዘንድ
ሚስቱንና ልጆቹን ከሁለት ባሪያዎቹ ጋር ላካቸው።
16 እሱ ግን ከሁለት ባሪያዎቹ ጋር የሶስት ወር መንገድ ያህል ሩቅ
አገር ሄደ። ወደ ባቢሎንም አገር ደረሰ። በላኦን ወደተባለ
የባቢሎን ንጉስ ዘንድም ገባ። እጅ መንሻንም ሰጠው። ወደ እሱ
የመጣበትንም ነገር ነገረው።
17 በላኦንም ከርሚንን ወደደው። በአንድ ነጋዴ ቤት አጠገብም ቤትን
ሰጠው።
18 ነጋደው ግን የሶስት አመት ያህል ሩቅ መንገድን ሄዶ ነበር።
19 እነዚህን ፀምስክርነት የዋሹትን በቤት ውስጥ በመኝታ ሳሉ
ገደሏቸው።
20 የነጋደው ሚስት ግን ከርሜንን ወደደችው። የሴቶች ባህርይ ክፉ
ነውና ሳተችበት። ፀነሰችም። ባሏ ፀንሳ ሳለች ትቷት ሄዶ ነበርና
ወልዳ ለአሳዳጊ ሰጥታው ነበር። ከከርሜንም ፀንሰች። የከርሜንም
መልክ ከእስራኤል ሁሉ እጅግ የተዋበ ነበር።
21 ነግር ግን የፀነሰችውን ወልዳ በባህር ልትጥለውና ነጋደውንም ባሏን
እንዳልተሳሳተችና ምንም እንዳላደረገች ሆና ልትቆየው ወደደች።
22 ጠቢቡ ሰሎሞን፣ "ሶስት ነገር ይገርመኛል። አራተኛውን ከቶ
አላስተውለውም። ይሄውም የንስር መንገድ በሰማይ ላይ የእባብ
መንገድ በድንጋይ ላይ፣ የመርከብ መንገድ በባህር ላይ፣ በልታ
አፍዋን የምታብስና አንዳች ነገር አላደረግሁም የምትል የአመንዝራ
ሴት መንገድ"[78] እንዳለው ነው።
23 የዚህን ጊዜ የንጉሱ የባላኦን ሚስት ደግሞ ፀነሰች። ክንፍ የሌለው
ነገር ግን ሁለመናው ፍፁም ወፍን የመሰለ አሞራን ወለደች።
24 የመረጠቻትንም አገልጋይዋን ጠራቻት። በመሶብ ውስጥ አድርጋ
አንድም ሰው ሳያውቅ በባህር ውስጥ ትጥለው ዘንድ አዘዘቻት።
25 ይህችም የነጋደው ሚስት የመውለጃዋ ጊዜ ደረሰ። መልኩ ያማረና
የተዋበ ወንድ ልጅን ወለደች። ሳታጠባውም የመረጠቻትን
አገልጋይዋን ጠራቻት። በሳጥን ውስጥ አድርጋ ላከቻት። ማንም
ሳያውቅ በባህር ውስጥ እንድትጥለው አዘዘቻት። ባሏን ፈርታ ነበርና።
26 በአንዲት ሌሊትም ከንጉሱ ሚስት ጋር ወለዱ። ጎህ ሲቀድም
ልጆቻቸውን ከባህር እንዲጥሉ ባሪያዎቻቸውን ላኩ። በእግዚአብሄር
ፈቃድ እነዚያ ባሪያዎች ህፃናቱን ከባህር ውስጥ ሳይጥሏቸው
ተገናኙ። እርስ በርሳቸውም ተነጋገሩ።
27 የንጉሱም ባሪያ የነጋደውን ባሪያ "በሳጥንሽ ውስጥ ያለው ምንድን
ነው? ስትል መረመረቻት" መልኩ የተዋበንም ልጅ አሳየቻት።

78 ምሳ.30፥18

28 ወትቤላ እስመ ብእሲተ እግዚእየ ስሕተት በኀበ አሐዱ እስራኤላዊ።
ወፀንሰት ወወለደት ወልደ። ወአዘዘተኒ ከመ እገሮ ውስተ ባሕር።
29 ወትቤላ አመተ ንጉሥ ለምንት ኢያልሀቀት ዘመጠነዝ ሠናይ ሕፃን።
30 ወትቤላ እንዘ ፅንስት ይእቲ ኀደጋ ብእሲሃ። ወወለደት
ወአልሀቀት። ወዝንቱ በአይቴ ተሐፅን ዘባዕድ ነኪር ዘርዕ።
31 ወይእቲኒ ሐተተታ ወትቤላ ምንት ውእቱ ዘውስተ መሶብ።
32 ወትቤላ ዘንተ እግዝእትየ ወለደት ዘአልቦ አርኣያ ሰብእ ባዕሌሁ
አላ ይመስል ንስረ ዘአልቦ ክንፈ። ወአዘዘተኒ ከመ እገሮ ውስተ
ባሕር።
33 ወይእዜኒ ሀበንዮ ለዝንቱ ወልድኪ ከመ እሰዶ ኀበ እግዝእትየ።
ወአንቲኒ ንሥኢ ወገሪዮ ለዝንቱ ዖፍ ውስተ ባሕር። ወገብረት
ከማሁ። ወወሰደት አመተ ንጉሥ ውእተ ሕፃነ ኀበ እግዝእታ።
34 ወተፈሥሐት ንግሥት ወአርድእዎ ለንጉሥ ከመ ወለደት ይእቲ
ንግሥት ወልደ። ወወሀብዎ ለሐፃንያን ወልሀቀ በቤተ ንጉሥ። ወሰ
መየቶ ስሞ ናቡከደነፆር። ቦ ገጸ ዖፍ ብሂል። ወበእንተዝ ተዐውቀ
ከመ ዘርዐ ሴም ውእቱ ንጉሠ ባቢሎን።
35 ወመጽአ ወነሠታ ለኢየሩሳሌም በፈቃደ እግዚአብሔር። ወዔወዎሙ
ለደቂቀ እስራኤል ወአግዐዞሙ ውስተ ሀገረ ባቢሎን ምስለ ደቂቀ
ደቂቀ ለምናሴ። ወኮነ ባዕለ ጥቀ እስከ ያቀውም ሐውልተ ወርቅ
በሐቅለ ባቢሎን ዘ፷ እመት ኑኁ ወ፮ እመት ግድሙ። ወኮነ ዕቡየ
ልብ ወይቤ አሠርቅ ፀሐየ በላዕለ ሰማይ። ወሰገደ ለጣዖት።
36 ወሠረዎ እግዚአብሔር ከመ ያእምር ኪያሁ። ወመክፈልተሂ ምስለ
አራዊተ ገዳም ረሰየ። ወሶበ አእመረ ስመ እግዚአብሔር እምድኅረ
ዓመት ፯ ምሕሮ ወአግብኦ ውስተ ንሥሓ። ወኮነት መንግሥተ
ባቢሎን ሎቱ ለዘርዑ እስከ ለዓለም።

## ፰ወ፮ በእንተ ንጉሠ ፋርስ

ወንጉሠ ፋርስኒ ዘርዐ ሴም ውእቱ። ወዘበእንቲኣሁ ናየድዐክሙ።
ወለደ ይሁዳ ክልኤ ደቂቀ። ወአእተወ ሎቱ ትዕማርሃ ለዘይልህቅ
ወልዱ ወሞተ።
ወፈነዎ ለዘይንእስ ወልዱ ኀቤሃ ከመ ያቅም ለእኁሁ ዘርዐ ኀበ
ብእሲተ እኁሁ።
ወውእቱኒ ገብረ ዘይጸልእ እግዚአብሔር ወኢፈቀደ ከመ ያቅም ዘርዐ
ለእኁሁ በከመ አዘዞ አቡሁ ይሁዳ።

- 85 -

28 ያችኛዋም "የጌታየ ሚስት በአንድ እስራኤላዊ ተሳሳተችና ፀነሰች።
ወንድ ልጅን ወለደች። ከባህርም ውስጥ እንድጥለው አዘዘችኝ"
አለቻት።
29 የንጉስም ባሪያ "እንደዚህ ያለውን መልከ መልካም ልጅ
ያላሳደገችው ለምንድን ነው?" አለቻት።
30 ሌላዋም መልሳ ፀንሳ ሳለ ባሏ ተዋት። ወልዳም አሳደገች። ይህንን
"የሌላ ሰው ዘር ግን እንዴት ታሳድጋለች" አለቻት።
31 ይህችኛዋም ደግሞ "በመሶብ ውስጥ ያለው ምንድን ነው" ስትል ጠየቀች።
32 "ይህንን ክንፍ የሌለው አሞራ የሚመስልና የሰው አርኣያ
የሌለውን ልጅ እመቤቴ ወለደች። በባህር ውስጥም እንድጥለው
አዘዘችኝ" አለቻት።
33 "አሁንም ወደ እመቤቴ እወስደው ዘንድ ይህንን ልጅሽን ስጭኝ።
አንችም ይህንን ወፍ ውሰጅና ከባህር ውስጥ ጣይው" አለቻት።
እንደዚሁም አደረገች። የንጉሱም ባሪያ ህፃኑን ወደ እመቤቷ ወሰደችው።
34 ንግስቲቱም ተደሰተች። ለንጉሱም ንግስቲቱ ወንድ ልጅን
እንደወለደች ነገሩት። ለሞግዚትም ሰጡት። በቤተ መንግስትም
አደገ። ስሙንም ናቡከደነፆር አለችው። የወፍ ልዋጭ ማለት ነው።
ስለዚህም የባቢሎን ንጉስ የሴም ዘር እንደሆነ ታወቀ።
35 ኢየሩሳሌም ደርሶ በፈቃደ እግዚኣብሄር አፈረሳት። የእስራኤልንም
ልጆች ማረካቸው፤ ከምናሴ የልጅ ልጆችም ጋር ነፃ አወጣቸው።
ርዝመቱ ስልሳ ክንድ፣ ስፋቱ ስድስት ክንድ የሆነ የወርቅ
ሃውልትን በባቢሎን ዱር እስኪያቆም ድረስ ፈፅሞ ሃብታም ሆነ።
ልበ ከፉም ሆነ።
36 "በሰማይ ላይ ፀሃይን አወጣለሁ" አለ። ለጣኦትም ሰገደ። እሱንም
ያውቀው ዘንድ እግዚኣብሄር ነቀለው። እጣውንም ከዱር እራዊት
ጋር አደረገ። የእግዚኣብሄርን ስም ከኣወቀ ከሰባት አመታት
በሁዋላ ማረው። ወደ ንስሃም መለሰው። የባቢሎንም መንግስት
ለእሱና ለዘሩ ለዘላለም ሆነች።

## ፸፮ ስለ ፋርስ ንጉስ

1 የፋርስም ንጉስ የሴም ዘር ነው። ስለ እሱም እንነግራችሁዋለን።
2 ይሁዳ ሁለት ልጆችን ወለደ። ለትልቁም ልጁ ትእማርን አጋባው።
ሞተም።
3 ትንሹን ልጁንም ለውንድሙ ከዋርሳው ዘርን ያቆም ዘንድ ወደ እሷ
ላከው። እሱ ግን እግዚኣብሄር የሚጠላውን አደረገ። አባቱ ይሁዳም
እንዳዘዘው ለወንድሙ ዘርን ያቆም ዘንድ አልወደደም። ነገር ግን ከራሱ
ሚስት በራሱ ስም ዘርን ያቆም ዘንድ ስለ ወደደ የወንድሙ ዘር
እንዳይባልና ዘሩ በማህፀኗ እንዳይቋጠር ከትእማር ጋር ሲገናኝ ዘሩን

www.ethiopianorthodox.org

ወውእቱሰ ሶበ ይሰክብ ምስለ ትዕማር ያወፅእ ዘርዖ ውስተ ምድር
ከመ ኢይትወቈር ውስተ ከርሠ ዚአሃ ወኢይሰመይ ዘርዐ እጉሁ አላ
ይፈቅድ ከመ ያቅም ዘርዐ እም ብእሲቱ በስመ ዚአሁ። ወርእዮ
እግዚአብሔር እከየ ምግባሪሁ ሜጠ ገጾ እምኔሁ ወቀተሎ።
4 ወአግብአ ይሁዳ ሐሙሃ ለትዕማር ወአእተዋ ውስተ ቤተ አቡሃ
ወይቤሎሙ ለአዝማዲሃ ዕቀብዋ ለዛቲ እስራኤላዊት ወኢታርክስዋ
ኀበ ባዕድ እስመ ብየ ንኡሰ ሕፃነ ለእመ አልሀቆ እግዚአብሔር
እውህብ ኪያሃ።
5 ወእንዘ ትነብር ምዕስብት ውስተ ቤተ አቡሃ ናሁ መጽአ ይሁዳ
ሐሙሃ ውስተ መራዕየ አዕፃዳተ አባግዒሁ ከመ ይቅርፅ ፀምረ ምስለ
ብዙኀ ፍግዓ ወተድላ። ወትዕማርሰ ሶበ ሰምዐት ከመ መጽአ ሐሙሃ
ገደፈት እምላዕሌሃ አልባሰ ምዕስብና። ወተረሰየት በአልባሰ ክብር
ወተገልበበት በአምሳለ ዘማት። ወሖረት እንተ ድኅሬሁ ወነበረት።
6 ወለአከ ኀቤሃ እንዘ ይብል ለፈቅድ እባእ ኀቤኪ። ወትቤሎ ምንተ
ትሁበኒ ዐስብየ። ወይቤላ እፌኑ ለኪ ነግሀ በጽባሕ መሐስአ ጠሊ።
ወትቤሎ ሀበኒ አኀዘ እስከ ተሁበኒ ጠሊተ። ወወሀባ በትረ ወሕልቀተ
ወቆብዐ እንተ መትሕተ አክሊሉ። ወቦአ ኀቤሃ። ወነሥአት ወሖረት
ውስተ ቤታ።
7 ወፈነወ ላቲ በጽባሕ ጠሌ። ወተስእሉ አግብርቲሁ ወይቤሉ አይቴ
ውእቱ ቤተ ዘማት። ወይቤልዎሙ አልቦ ውስተ ሀገርነ ዘማት።
ወገብኡ ውስተ ሀገሮሙ። ወነገርዎ ከመ አልቦ ውስተ ሀገሮሙ
ዘማት። ወይቤ ይሁዳ ኀድጉአ ፈቃደ እግዚአብሔር ለይኩን።
8 ወእምዝ ፀንሰት ትዕማር። ወነገርዎ ለሐሙሃ ከመ ፀንሰት።
9 ወሖረ ወነሥአ መላህቅተ እስራኤል ኀበ አቡሃ ለትዕማር። ወይቤሉ
አቅርብ ሊተ ወለተከ ፅንስተ ከመ ንውግራ በእእባን በከመ አዘዘ
ሙሴ። እስመ አኀሰረት ቤተ እስራኤል።
10 ወነገርዋ ለትእማር አቡሃ ወአዝማዲሃ ከመ ከመዝ ይቤ አሙሃ።
11 ወአውፅአት ሕልቀተ ወበትረ ወቆብዐ። ወወሀበት ለአቡሃ ወለአዝማዲሃ
ወትቤሎሙ በዐለ ዝንቱአ ዘአስሐተኒ ወይውግሩኒ ምስሌሁ በአእባን።
12 ወሶበ ርእየ ይሁዳ ንዋዮ አእመረ። ወይቤ ጸድቀት ትዕማር እምኔየ።
ወኀደጋ ወአተወ ቤቶ።
13 ወወለደት ትዕማር መንታ ክልኤተ ሕዝበ ፋሬስ ወዛራ። ወተሐንጸት ፋርስ
በስመ ፋሬስ። ወነግሠ ላዕሌሃ ውእቱ ወዘርዑ እምድኅሬሆሙ። ወተሰምዩ
ፈረሳውያን። ናሁኪ ተዐውቀ ንጉሠ ፋርስ ከመ ዘርዐ ሴም ውእቱ።

## ፴ወ፳ በእንተ ንጉሠ ሞአብ

ወንጉሠ ሞአብሂ ዘርዐ ሴም ውእቱ። ወናየድዐክሙ ዘከመሂ ኮነ።

- 86 -

በምድር ላይ ያፈሰው ነበር። እግዚአብሄርም የምግባሩን ክፋት ባየ
ጊዜ ፊቱን ከእሱ መለሰ፤ ገደለውም።
4 ይሁዳም ትእማርን መለሳት። ወደ አባቷ ቤትም አገባት፤
ዘመዶቿንም "ይህችን እስራኤላዊት ጠብቋት፤ በባእድም አታርክሷት።
ህፃን ልጅ አለኝ። እግዚአብሄር ቢያሳድገው እሷን እሰጠዋለሁ" አላቸው።
5 መበለትም ሁና በአባቷ ቤት ስትኖር አማቷ የበጎቹን ጠጉር
ሊሸልት በብዙ ተድላና ደስታ ወደ በጎቹ መንጋ ማሰማሪያ መጣ።
ትእማር ግን አማቷ እንደ መጣ በሰማች ጊዜ የመበለትነት ልብሷን
አወለቀች። በክብር ልብስም ተሸለመች። እንደ ሴት አዳሪዎችም
ሁና ተከናነበች። በሁዋላውም ሄደች። ተቀመጠችም።
6 እሱም "ወደ አንች ልገባ እሻለሁ" ሲል ላከባት። እሷም "ዋጋየን
ስንት ትሰጠኛለህ" ስትል ጠየቀችው። እሱም "ጠዋት የፍየል
ጠቦቶች እልክልሻለሁ" አላት። እሷም "ፍየሉን እስከምትሰጠኝ
መያዣ ስጠኝ" አለችው። ብትሩን፤ ቀለበቱንና ከባርኔጣው ስር
ያለውን ኮፍያውን ሰጣት።
7 ጠዋትም ፍየሉን ላከላት። ባሪያዎቹም "የሴት አዳሪዎች ቤት የት
ነው?" እያሉ ጠየቁ። እነዚያም በአገራችን "ሴት አዳሪዎች
የሉም" አሏቸው። ወደ አገራቸው ተመልሰው በአገሩ ሴት
አዳሪዎች እንደሌሉ ነገሩት። ይሁዳም "ተዋት የእግዚአብሄር ፈቃድ
ይሁን" አለ።
8 ከዚህ በሁዋላ ትእማር ፀነሰች። ለአማቷም እንደ ፀነሰች ነገሩት።
9 ሄዶም የእስራኤል ሽማግሌዎችን ወደ ትእማር አባት ወሰደ።
"የእስራኤልን ቤት አርክሳለችና ሙሴ እንዳዘዘው በድንጋይ
እንወግራት ዘንድ በአመፅ የፀነሰችውን ልጅህን አቅርብ" አለው።
10 አባቷና ዘመዶቿ አማቷ እንደዚህ እንዳለ ነገሯት።
11 እሷም ቀለበቱን ብትሩንና ኮፍያውን አወጣች። ለአባቷና
ለዘመዶቿም ሰጠች። "ያሳተኝ ባለዚህ ነውና ከእሱ ጋር በድንጋይ
ይውገሩኝ" አለቻቸው።
12 ይሁዳም እቃዎቹን ባየ ጊዜ አወቀ። "ከእኔ ይልቅ ትእማር
እውነተኛ ሆነች" አለ። ተዋት፤ ከቤቱም አስገባት።
13 ትእማርም መንታይ የሆኑ ሁለቱን የፋሬስ ህዝቦች ዘሮች ወለደች።
ፋርስም በፋሬስ ስም ተሰራች። በእሱም ላይ እሱና ከእሱም
በሁዋላ ዘሩ ነገሰ። ፈረሳውያንም ተባሉ። እነሆ የፋርስ ንጉስ የሴም
ዘር እንደሆነ ታወቀ።

## ፴፰ ስለ ሞአብ ንጉስ

1 የሞአብም ንጉስ የሴም ዘር ነው። እንዴትም እንደሆነ እንነግራችሁዋለን።

www.ethiopianorthodox.org

2 ወሶበ አፍለሶ እግዚአብሔር ለአብርሃም እምሀገረ አቡሁ ውስተ
ምድረ ካራን ወሎጥኒ አዕደዎ እግዚአብሔር ውስተ
ወገሞራ። ወሶበ ፈቀደ እግዚአብሔር ከመ ያጥፍኦሙ ለሰብአ ሰዶም
ወገሞራ ፈነወ እግዚአብሔር መላእክቲሁ ሚካኤልሃ ወገብርኤልሃ ከመ
ያውፅእዎ ለሎጥ ወያውፅይዎን ለሀገረ ሰዶም ወገሞራ።
3 ወአማሰኑ ኪያሃ ወአውፅእዎ ለሎጥ ምስለ ደቂቁ።
4 ወብእሲቱሰ ሶበ ተመይጠት ድኅሬሃ ከመ ትርአይ ሀገረ አቡሃ ወእማ
እስመ ወረደ መዓተ እግዚአብሔር ላዕለ ሀገረ ሰዶም ወዝናመ እሳት
እምሰማይ ዘያነድድ አድባረ ወአውግረ አእባነ ወመሬተ። ወይወርድ
መባርቅት ወፀዓዓት ወነጐድጓድ ምስለ ድምፀ መዐተ እግዚአብሔር
ወደመና እሳትኒ ዘያጠይስ ለመርቆ።
5 ወዝንቱ ኩሉ ሶበ ተሰምዐ ድምፅ ይቤልዎ መላእክት ለሎጥ
ኢትትመየጡ ድኅረ እምከመ ወፃእክሙ እምሀገርክሙ። ኢትትመየጡ
ድኅሬክሙ ከመ ሞተ ኢትሙቱ። ወሶበ ሰምዐት ይእቲ ብእሲተ ሎጥ
አቅማባ ተመይጠት ድኅሬሃ። ወኮነት ሐውልተ ፄው። ወሀለወት
እስከ ዮም ወእስከ ዛቲ ዕለት።
6 ወለሎጥሰ እኅሁ ለአብርሃም አንበሮ እግዚአብሔር ውስተ አድባረ
አራራት። ወተከለ ወይነ ሐዲሰ።
7 ወአስተያሁ ወይነ ለአቡሆን አዋልዲሁ። እስመ መከራ ምክረ እኪተ
ወይቤላ ዝንቱ ንዋየ አቡነ በአይቴ ይጠፍእ እምኔኪ ተንገሥት
በፍኖት ወለነኒ አልቦ ዘያወስበነ በዝየ።
8 ወአስከራሁ ለአቡሆን። ወሰከበት እንተ ትልህቅ ወለቱ ምስሌሁ ኀበ
ጸልመ ልቡ በወይን። ወሎጥሰ ጻድቅ ኢያእመረ በሰኪቦታ ለወለቱ።
9 ወኖኅኒ በስካር ኮነ ዕሩቀ እምብእሲቱ ወደቂቁ እስከ ይረግም ውሉዶ
ለዘሰሐቆ። እስመ ስካር ያጸልም ልቦ።
10 ወለሎጥሰ ኢተኈለቈ ኃጢአተ እስመ በኢያእምሮ ገብረ።
11 ወፀንሰት ወወለደት እንተ ትልህቅ። ወሰመየቶ ስመ ሞአብ። እምኀበ
አቡየ በብርክየ ብሂል። ወውእቱኬ አቡሆሙ ለሞአባውያን
ወለአጋራውያን። ናሁኬ ተዐውቀ ንጉሠ ሞአብሂ ከመ ዘርዐ ሴም
ውእቱ።

## ፳ወ፱ በእንተ ንጉሠ አማሌቅ

ወሶበ ወለደት እንተ ትልህቅ ትቤላ ለእንተ ትንእስ ሀቢኬ ናስትዮ
ወይነ ለአቡነ ወአንቲኒ ከመ ትባኢ ኀቤሁ እመ ትረክቢ ውሉደ።
ወካዕበ ገብራ ወይነ። ወደገማ ቃለ ዕበድ እንዘ ይብላ ስተይ ወይነ
ኦአቡነ ከመ ይትናዘዝ ልብከ።
ወውእቱሰ የዋህ ሰትየ ወሰከረ።
ወካዕበ ሶበ ሰትየ ወጸልመ ልቡ ቦአት እንተ ትንእስ ወሰከበት
ምስሌሁ።

- 87 -

2 እግዚአብሄር አብርሃምን ከአባቱ አገር ወደ ካራን ምድር ባወጣው
ጊዜ፣ ሎጥንም ወደ ሰዶምና ገሞራ ምድር ባሻገረው ጊዜ፣ የሰ
ዶምና የገሞራን ምድር ያጠፋቸው ዘንድ በወደደ ጊዜ፣ ሎጥን
ያወጡት ዘንድና የሰዶምንና የገሞራን አገር ያቃጥሏት ዘንድ
መላእክቱን ሚካኤልንና ገብርኤልን ላከ።
3 እሷንም አጠፏት። ሎጥንም ከልጆቹ ጋር አወጡት።
4 ሚስቱ ግን የአባቷንና የእናቷን አገር ለማየት ወደ ሁዋላዋ በዞረች
ጊዜ፣ በሰዶም ላይ የእግዚአብሄር መአት ወርዷልና፣ ተራራውንና
ኮረብታውን ድንጋዮችንና መሬቱን የሚያቃጥል የእሳት ዝናም ከሰ
ማይ ወርዷልና፣ መብረቅ ድብልቅልቅና ነጎድጓድ ከእግዚአብሄር
መአት ድምፅ ጋር በረሃን የሚያቃጥል የእሳት ደመናም ወርዷልና፣
5 ይህ ሁሉ ድምፅ በተሰማ ጊዜ መላእክት ሎጥን "ከአገራችሁ
ከወጣችሁ በሁዋላ ሞትን እንዳትሞቱ ወደ ሁዋላችሁ አትዩ። ወደ
መጣችሁበትም አትመለሱ" ብለውት ነበር። ይህች አቅማባ የተባለች
የሎጥ ሚስት ግን ይህን በሰማች ጊዜ ወደ ሁዋላዋ ተመለሰች።
የጨው ሃውልትም ሆነች። እስከዚም ቀን አለች።
6 የአብርሃምን ወንድም ሎጥን ግን እግዚአብሄር በአራራት ተራሮች
ላይ አስቀመጠው። አዲስ ወይንንም ተከለ።
7 "ይህ የአባታችን ገንዘብ በምን ይጠፋል? በመንገድ ከጠፋም
እኛን የሚያገባን አይኖርም" ሲሉ ክፉ ምክርን መክረው ነበርና
ሴቶች ልጆቹ ለአባታቸው ወይንን አጠጡት።
8 አባታቸውንም አሰከሩት። ታላቂቱም ልጁ ልቡ በወይን እንደ ጠፋ
ከእርሱ ጋር ተኛች። ፃድቅ ሎጥ ግን ስካር ልብን ያጠፋልና
ከእርሱ ጋር መተኛቷንና መነሳቷንም አላወቀም ነበር።
9 ኖህም ደግሞ የሳቀበትን ልጁን እስኪረግም ድረስ በሚስቱና
በልጆቹ ፊት ራቁቱን ሆነ።
10 ሎጥ ግን ባለማወቅ አድርጎታልና ሃጢአት ሆኖ አልተቆጠረበትም።
11 ታላቂቱም ፀነሰች። ወንድ ልጅም ወለደች። ስሙንም ሞአብ
አለችው። ይህም ከአባቴ በጉልበቴ አገኘሁት ማለት ነው። እሱም
የሞአባውያውና የአጋራውያን አባት ነው። እነሆ የሞአብ ንጉስ
የሴም ዘር እንደሆነ ታወቀ።

## ፳፱ ስለ አማሌቅ ንጉስ

1 ታላቋ በወለደች ጊዜ ታናሿን "አንች ደግሞ ልጅን ታገኚ ዘንድ
አባታችንን ወይን እናጠጣው" አለቻት።
2 ደግሞም ወይንን አደረጉ። እንዲሁም "አባታችን ሆይ! ልብህ ይረጋጋ
ዘንድ ውይንን ጠጣ" ሲሉ የተለመደውን የእብደት ቃል ደገሙ።
3 እሱም ቀና ነውና ጠጣ። ሰከረ። ልቡም ጠፋ።
4 ዳግመኛም በሰከረና ልቡ በጠፋ ጊዜ ታናሽቱ ገባችና ከእሱ ጋር
ተኛች።

www.ethiopianorthodox.org

5 ወውእቱሰ ካዕበ ኢያእመረ በሰኪቦታ ወበተንሥኦታ።
6 ወካዕበ ይእቲኒ ፀንሰት ወወለደት ወልደ። ወሰመየቶ ስሞ አሞን።
7 ወውእቱ ንጉሦሙ ለአማሌቃውያን። ወናሁኬ ተዐውቀ ከመ ንጉሠ
አማሌቅ ከመ ዘርዐ ሴም ውእቱ።

## ፲ በእንተ ንጉሠ ኢሎፍሊ

1 ወናሁ ኢሎፍሊ ዘርዐ ሶምሶን ይነግሡ ላዕሌሆሙ።
2 ወሶምሶንሰ እም ፲ወ፪ ደቂቀ ያዕቆብ ዘርዐ ዳን ውእቱ። ወልደ
ዓመት እምያዕቆብ ውእቱ ሶምሶን ናየድዐከሙ ዘከመ ኮነ።
3 አስተርአያ መልአከ እግዚአብሔር ለእሙ ለሶምሶን። ወይቤላ ተዐቀቢ
እምኩሉ ርኩስ። ወኢትቅረቢ ዘእንበለ ኀበ ምትኪ። እስመ
ዘይትወለድ እምኔኪ ናዝራዊ ቅዱሱ ለእግዚአብሔር። ወይከውን
መድኀኒቶሙ ለእስራኤል እምእደ ኢሎፍሊ። ወእምዝ ወለደቶ።
4 ወካዕበ አስተርአያ ወይቤላ ኢታዕርጊ መላጼ ዲበ ርዕሱ። ወኢይብላዕ
ሥጋ ወኢወይነ ኢያውስብ እምባዕድ ፍጥረት ዘእንበለ እምዘመዱ
ወቤተ አቡሁ።[79]
5 ወዘከመ ወሀቦ እግዚአብሔር ኀይለ ሰማዕከሙ በውስተ መጽሐፈ
መሳፍንት። ወተዐደወ ትእዛዘ እግዚአብሔር። ወቦአ ወአውሰበ ውስተ
አዋልደ ኢሎፍሊ ቄላፋን።
6 ወበእንተዝ ተምዐ እግዚአብሔር። ወመጠዎ ውስተ አዋልደ ኢሎፍሊ
ቄላፋን። ወአየርዎ አዕይንቲሁ። ወረሰይዎ መስተዛውዐ ወበውስተ ቤተ
ንጉሦሙ ወአፍረሰ መልዕልቶሙ።
7 ወቀተሎሙ ለ፫፻። ወበህይወቱሰ ቀተሎሙ ለ፫፻ወለ፪፻ በኀይን
ወበእብን ወበበትር ወመንሰከ አድግ። እስመ ብዝኖሙ ከመ አንበጣ
እስከ አኅደጎሙ ለእስራኤል እምግብርናተ ኢሎፍሊ።
8 ወእምዝ ፀንሰት ደሊላ እምሶምሶን። ወእንዘ ፅንስት ይእቲ ሞተ
ሶምሶን ምስለ ሰብአ ኢሎፍሊ።
9 ወወለደት ወልደ ደሊላ። ወሰመየቶ ስሞ ምናሂም*። ዘርዐ ኀያል
ብሂል። ወደሊላሰ እኅታ ይእቲ ለመክሰባ ብእሲተ ንጉሠ ኢሎፍሊ።
ወሶበ ቀተሎ ሶምሶን ለንጉሠ ኢሎፍሊ በውስተ ቤት ምስለ ሕዝቡ
ወለሊሁኒ ሞተ ምስሌሁ።
10 ወገብአት ደሊላ ኀበ እኅታ ንግሥተ ኢሎፍሊ መክሳባ። እስመ
ክልኤሆን ላህያት እማንቱ። ወአልቦን ውሉደ ወባሕቱ ፅኑሳት ሀየ።
፮ አውራኀ መክሳባ እምዘፀንሰት እም ኀበ ቄላፈን* ንጉሠ ኢሎፍሊ
ወደሊላ ፬ አውራኀ እሙንቱ እምዘፀንሰት እምሶምሶን።
11 ወሞቱ እምታቲሆን። ወይትፋቀራ ፈድፋደ። ወፍቅሮንሂ አኮ ከመ
አኀት አላ ከመ እም ወሕፃን፤

[79] መሳ.13፥5

* ምናሄም ይላል።

* ቆላፋንም ይላል።

- 88 -

5 እሱ ግን ስትተኛም ስትነሳም ኣላወቀም።
6 ይህችም ደግሞ ፀነሰች። ወንድ ልጅም ወለደች። ስሙንም ኣሞን
ኣለችው።
7 እሱም የኣማሌቃውያን ንጉስ የሴም ዘር እንደሆነ ታወቀ።

## ፲ ስለ ኢሎፍላውያን ንጉስ

1 እነሆ በኢሎፍላውያን ላይ የሶምሶን ዘሮች ይነግሱባቸዋል።
2 ሶምሶን ከኣስራ ሁለቱ የያእቆብ ልጆች የዳን ዘር ነው። ደግሞም
የያእቆብ የሴት ባሪያው ልጅ ነው። ይህም ሶምሶን እንዴት
እንድሆነ እንነግራችሁዋለን።
3 የእግዚኣብሄር መልኣክ ለሶምሶን እናት ተገለፀና "ከርኩስ ነገር
ሁሉ ተጠበቂ። ከባልሽ በቀር ሌላ ወንድ ኣትቅረቢ። ከኣንቺ
የሚወለደው የእግዚኣብሄር ቅዱስ ነውና እስራኤላውያንም
ከኤሎፍላውያን እጅ የሚታደጋቸው ይሆናል" ኣላት። ከዚህ በሁዋላ
ወለደችው።
4 እንደገናም ተገለፀላትና "ምላጭ በራሱ ላይ ኣታሳርፊበት፤ ስጋ
ኣይብላ፤ ወይን ኣይጠጣ። ከኣባቱና ከወገኑ ቤት በቀር ከልዩ
ወገን ኣያግባ" ኣላት።
5 እግዚኣብሄር የሰጠውንም ሃይል በመፅሃፈ መሳፍንት ሰማችሁ። ነገር
ግን የእግዚኣብሄርን ትእዛዝ ተላለፈ። ገብቶም ካልተገረዙት
ከኢሎፍላውያን ልጆች ኣገባ።[79]
6 ስለዚህ እግዚኣብሄር ተቆጣው። ባልተገረዙት በኢሎፍላውያን ሰዎች እጅ
ኣሳልፎ ሰጠው። ኣይኑንም ኣጠፉት። በንጉሳቸውም ቤት መዘባበቻ
ኣደረጉት። በላያቸውም ላይ ግንብን ኣፈረሰ።
7 ብዛታቸው እንደ ኣንበጣ ነበርና እስራኤላወያንን ከኢሎፍላውያው ባርነት
እስካወጣቸው ድረስ ነው። ሰባት መቶ ሽዎችን በህይወቱ ገደለ። ሁለት
መቶ ሽዎችንም በብረት፤ በድንጋይ፤ በዱላና በኣህያ መንጋጋ ገደላቸው።
8 ከዚህ በሁዋላ ደሊላ ከሶምሶን ፀነሰች። ፀንሳም ሳለች ሶምሶን ከኢሎፍሊ
ሰዎች ጋር ሲፋለም ሞተ።
9 ደሊላም ልጅን ወለደች። ስሙንም ምናሄም ኣለችው። ትርጓሜውም
"የሃያል ልጅ" ማለት ነው። ደሊላ ለኢሎፍሊ ንጉስ ሚስት ለመክሳባ
እህቷ ነበረች። ሶምሶንም የኢሎፍሊ ንጉስ በቤት ውስጥ ከህዝቡ ጋር
በገደለው ጊዜ እሱም ኣብሮ ሞተ።
10 ደሊላም ወደ እህቷ ወደ ኢሎፍሊ ንግስት ወደ መክሳባ ተመለሰች።
ሁለቱም መልከኞች ነበሩ። ፀንሰውም ነበር እንጅ ልጆች ኣልነበራቸውም።
መክሳባ ከኢሎፍሊ ንጉስ ከቅላሶን ከፀነሰች ስድስት ወሯ ነበር። ደሊላም
ከሶምሶን ከፀነሰች ኣራት ወሯ ነበር።
11 ባሎቻቸውም ሞቱ። ፈፅመውም ይዋደዱ ነበር። ፍቅራቸውም እንደ
እህቶች ፍቅር ኣልነበረም። ነገር ግን እናት ለልጅዋ ልጅ ለእናቷ

[79] ምሳ.13፥5

www.ethiopianorthodox.org

ወከመ ሕፃን ለእም ከማሁ ፍቅሮን። ወነበራ ክልኤሆን ኅቤሁ።
12 ወመንግሥትሰ ውስተ እደሃ ለመከሰባ እምእለ ተርፉ እምቀትለ
ሶምሶን በውስተ ቤተ ንትሥ። እስመ አልቦ ዘተርፈ እምደቂቀ ኀይለ
መንግሥተ ኢሉፍሊ። ወበእንተዝ ነግሠት ላዕለ እለ ተርፉ መከሰባ።
13 ወይብልዋ ነግሀ ወሠርከ አልብነ ንጉሠ ዘእንበሌኪ ካልአ ወዘእንበለ
ዘወፅአ እም ከርሥኪ። ለእመ አሠነየ ለነ እግዚእነ ዳጎን ይከውን
ወልደ ዘውስተ ከርስኪ ዘያነሥእ ለአምላክነ ዳጎን ወዘይነግሥ
ላዕሌነ ወእመሂ ኮነት ወለተ ፍነግሣ ላዕሌነ ከመ ይኩን ስምኪ
ወስመ ቈላሶን እግዚእነ ላዕሌነ ዝክርክሙ።
14 ወእምዝ ወለደት ተባዕተ። ወተፈሥሑ ኵሎሙ ሰብአ ኢሉፍሊ።
ወገነዩ ላቲ። ወኀለዩ እንዘ ዳጎን ወቤል አክበርዋ ወአፍቀርዋ
ለመከሳባ። ወተረክበ ዘርዐ ቈላሶን እምኔሃ ለመከሳባ።
15 ወደሊላኒ ወለደት ወልደ። ወሐፀናሆሙ በብዙኅ ክብር ለደቂቆን።
16 ወሶበ ኮነ ሎሙ ፭ ዓመተ ይበልዑ ወይትዋነዩ በቅድሜሆን። ወገብረ
ሎሙ ዐስቀ ዘዲባጋት ወሰዋትለ ውስተ ሐቍያቲሆሙ ወአዕኑገ ውስተ
ከሣውዲሆሙ። ወረሰይዎ ንጉሠ ለወልደ መከሳባ ውስተ መንበረ
አቡሁ ላዕለ ኢሉፍሊ።

፴ወ፩ ዘከመ ቀተሎ ወልደ ሶምሶን ለወልደ ንጉሠ ኢሉፍሊ

1 ወውእቱሰ ወልድ አከምሔል ወልደ ሶምሶን ይቤላ ለእሙ ደሊላ
ለምንት አነ ኢይነግሥ ወኢይነብር ላዕለ ዝንቱ መንበር።
2 ወትቤሎ እሙ ኅድግ ወልድየ። ኢኮነት ዛቲ መንበር ዘአቡከ።
ወኢኮነ ዝየ ሀገሩ ለአቡከ። ወአንተሰ ለእመ አልሀቀከ አምላከ
አበዊከ ተሐውር ኀበ መንበረ አቡከ።
3 ወይቤላ ወልዳ አልቦ። ኢየኀድግ ኪያኪ እምየ ወመከሳባ እምየ።
ወእነግሥ በዝየ።
4 ወእሐተ ዕለተ ሰከሩ ክልኤሆሙ እምድኅረ ኀለፈ ምሳሕ። ወተዐደወ
ኆዋኀው። ወሀለዋ ይነብራ ክልኤሆን ከመ ይብልዓ ሥጋ።
ወእሙንቱኒ ደቂቅ ይትዋነዩ ቅድሜሆን። ወይበልዑ ምስሌሆን።
ወአሐቲ አመት ትእኀዝ መጽብኀ በማዕከሌሆን።
5 ወነሥአ አከምሔል ወልደ ደሊላ ሥጋ ምሉዐ ክልኤሆን እደዊሁ
እምኑ መጽብኀ ወተፍእመ። ወዘአትረፈ እምአፉሁ ጠለፎ ወልደ
መከሳባ ጥብሬሌስ ንጉሠ ኢሉፍሊ።
6 ወአውፅአ ሰይፎ አከምሔል ወአውቀዮ ርእሶ ወወድቀት ውስተ
መጽብኀ ዘእንበለ የኀጥ እንተ ሄዶ። ወሥጋሁኒ ወድቀ ውስተ
ጸፍጸፈ ቤት። ወአንቀጥቀጠ እደዊሁ ወእገሪሁ። ወተፈጸመ ሶቤሃ።
ወለእማንቱሰ እማቲሆሙ አኀዞን ፍርሃት ወድንጋፄ።

- 89 -

እንዳላት ፍቅር እንዲሁ ይዋደዱ ነበር። ሁለቱም በአንድነት ይኖሩ
ነበር።
12 በቤተ መንግስት ውስጥ ከኢሉፍሌ መንግስት ሃያላን የተረፈ
አልነበረምና ከሶምሶን በተረፉት ላይ መንግስት በመክስባ እጅ
ነበር። በቀሩት ላይ ነገሰች።
13 "ጠዋትና ማታም ከአንቺ ከሆድሽ ከሚወጣው በቀር ንጉስ የለንም።
ጌታችን ዳጎን ፈቃዱ ቢሆን ከሆድሽ የሚወጣው ልጅሽ ይነግሳል።
ስምሽና የጌታችን የቆላሶን ስም ለምንጊዜውም በመካከላችን
ሲታወስ እንዲኖር አምላካችን ዳጎን የሚያነሳው ከማህፀንሽ የወጣው
ልጅሽ በላያችን ላይ ይነግሳል" ይሏት ነበር።
14 ከዚህ በሁዋላ ወንድ ልጅን ወለደች። ሁሉም የኢሉፍሊ ሰዎች
ተደሰቱ። ተገዙላት። ዳጎንና ቤል መክሰባን ወደዷት። አከበሯትም።
የቆላሶንም ዘር ከእርሷ ተገኘ ሲሉ ዘመሩላት።
15 ደሊላም ወንድ ልጅ ወለደች። ልጆቻቸውንም በብዙ ክብር አሳደጓቸው።
16 አምስት ዓመትም ሲሆናቸው በፊታቸው ይበሉና ይጠጡ ነበር።
በተለይም ሀብር የተጠለፉ ድርቦችንና ዝናሮችን ለወገባቸው፣
የወርቅ ማርዳዎችን ለአንገታቸው አደረጉላቸው። የመክሰባንም ልጅ
በኢሉፍላውያን ላይ በአባቱ ዙፋን ንጉስ አደረጉት።

፴፩ የሶምሶን ልጅ የኢሉፍሊን ንጉስ ልጅ እንደ ገደለው

1 ይህ አከምሄል የተባለው የሶምሶን ልጅ እናቱን ደሊላን "ለምን
እኔ አልነግስም? ለምንስ በዚህ ዙፋን ላይ አልቀመጥም?" አላት።
2 እናቱም "ልጄ ሆይ! ተው። ይህች ዙፋን የአባትህ ዙፋን
አይደለችም። የአባትህም አገር ከዚህ አይደለም። አንተ ግን
የአባትህ አምላክ ቢያሳድግህ ወደ አባትህ ዙፋን ትሄዳለህ" አለችው።
3 ልጅዋም "የለም፤ አንችንና እናቴን መክሳባን አልተውም። በዚህም
እነግሳለሁ" አላት።
4 አንድ ቀንም ምሳ ካለፈ በሁዋላ ሁሉቱም ሰከሩ። በሮችንም
ቆለፉ። ሁለቱም ሴቶች ስጋ ሊበሉ በዚያ ነበሩ። ልጆች በፊታቸው
ይጫወቱና ከእነሱም ጋር ይበሉ ነበር። በመካከላቸውም አንዲት
ሴት ባሪያ ወጥ ታሳልፍ ነበር።
5 የደሊላ ልጅ አኬምሄል ሁለት እጆቹን ስጋ መልቶ ከወጡ ወሰደና
ጎረሰ። ከአፉ የተረፈውንም የመክሰባ ልጅና የኢሉፍሊ ንጉስ
ጥብሬለስ ከአፉ ጠለፈው።
6 አኬምሄል ሰይፉን አወጣ። ራሱንም ቆረጠው። የቀማውንም
ሳይበላው ራሱ በወጡ ላይ ወደቀች። ስጋውም በቤቱ ንጣፍ ላይ
ወደቀ። እጆቹንና እግሮቹንም አንቀጥቅጦ ወዲያው ሞተ።
እናቶቻቸውንም ፍርሃትና ድንጋጤ ያዛቸው። ፈርተዋልና ለማንም

www.ethiopianorthodox.org

ወኢነገራ ወኢለመኒሂ እስመ ፈርሃ ወውኅጣ ዘውስተ አፉሆን።
ወተናጸራ እስመ ኢያእመራ ዘይገብራ።
7 ወይእቲሰ አመት ተንሥአት እምኔሆን። ወነሥአት ርእሶ እምነ
መጽብኅ። ወአስተጣግዐት ዲበ ክሣዱ። ወከደነቶ ልብሳ።
8 ወተንሥአት ደሊላ። ወመልኀት ሰይፈ ምውት ወልደ እኅታ።
ወሖረት ከመ ትቅትሎ ለአኪሚሔል።
9 ወውእቱሰ ተጸወነ ኀበ ምስዋረ ዐምድ። ወተደለወ ለቀትለ እሙ።
10 ወተንሥአት እኅታ። ወአኀዘታ እንዘ ትብል ለምንት ተሀጕልነ
እምካልኢኒሆሙ። ወዝንቱሰ ዘጕንዱ እኩይ ኢይክል ፈርየ ሠናየ።
ንዒ እኅትየ ኪያኪኒ ኢያሀጕልኪ። ወነሥአት እምእደሃ ሰይፈ።
ወአንሥአት እምትርአሲሃ ልብሰ ሠናየ ዘሜላት ዘይለብሱ ነገሥት።
ወወሀበቶ ወየውሀቶ በጥዑም ቃል እንዘ ትብል ንሣእ ወልድየ
ልብሰ ወትነብር አንተ ዲበ መንበረ መንግሥተ ኢሎፍሊ።
11 ወውእቱሰ ኮነ ፀዋገ ከመ ድብ። እስመ ፈቀደ ይቅትሎን ለክልኤሆን
እስከ የኀድጋ ቤተ ወወፅአ።
12 ወእምዝ ሶበ የኀድጋሁ ነሥአ ወለብሰ ሜላተ። ወወፅአ አፍአ።
ወእማንቱኒ ቦአ። ወገነዛ በድኖ። ወቀበራሁ በጽምሚት።ወሶበ ኮነ
ጊዜ ድራር ኀሠሥዎ ወኢረከብዎ።
13 ወተስእልዎ መሐዛት ወመገብት። ወትቤሎሙ እሙ እስመ ሐመ
ውእቱ ንትሥከሙ። ወዝንቱ ይነብር ህየንቴሁ።
14 ወነሥእዎ ወአንበርዎ ወሠርዑ ማዕደ ወተፈሥሑ።
15 ወእምአሜሃ ነግሠ ወልደ ሶምሶን ላዕሌሆሙ። ወአልቦ ዘተዐደወ
እምትእዛዙ እምዝ ፭* ክረምት ዘተወልደ ዘንተ ገብረ። ወኮነት
መንግሥተ ኢሎፍሊኒ ሎቱ ወለዘርዑ እምድኅሬሁ። ናሁኬ ተዐውቀ
ከመ መንግሥተ ኢሎፍሌ ዘርዐ ሴም ውእቱ።

## ፹ወ፪ በእንተ ርደተ አብርሃም ግብጽ

1 ወካዕበ ናየድዐክሙ ከመ ሶበ ወሀቦ እግዚአብሔር ለአብርሃም ክብረ
ወብዕለ። ኀጥአ ውሉደ። በውስተ ምስካቢሆሙ ይትናገሩ ሳራ
ወአብርሃም። ወይቤላ ኮንኪ መካነ። ወይእቲኒ ትቤሎ አኮ አነ
መካን አላ አንተ። ወበእንተዝ ነበሩ ይትማከሩ ይትገአዙ
በበይናቲሆሙ።
2 ወቦአ ረኃብ ውስተ ምድረ ከነአን። ወሰምዐ አብርሃም ከመ ቦ
እክል በብሔረ ግብጽ ሀገረ ፈርዖን። ወሶበ አኅለቀ ኵሎ ንዋዮ
በምሒረ ነዳይ በመዋዕለ ረኃብ እንዘ ኢይናፍቅ ለጌሠም ወጸንዐ
ረኃብ በብሔረ ከናአን። ወኀጥአ ዘይሴሰይ። ወይቤ አእኵቶ
ለእግዚአብሔር ዘወሀበኒ ዘአኅለቀ ምስለ አግብርትየ። ወባሕቱ አንቲ
እኅትየ ሳራ ንዒ ንሑር ውስተ ብሔረ ግብጽ ከመ ናድኅን ርእሰነ
እሞተ ረኃብ።

---

* ፲ወ፭ የሚልም አለ።



አልነገሩም። የአፋቸውንም ዋጡ። የሚያደርጉትንም አላውቁምና
እርስ በርሳቸው ተያዩ።
7 ያች ባሪያ ግን ከእነሱ ተነሳች። ራሱንም ከወጡ ወሰደችና
በአንገቱ ላይ አጣጋችው። ልብስንም አለበሰችው።
8 ደሊላም የሟቹን የእህቷን ልጅ ሰይፍ መዛ ተነሳች። አኪምሄልንም
ትገድለው ዘንድ ሄደች።
9 እሱ ግን በምሶሶው መሸሸጊያ ተጠጋ። እናቱንም ለመግደል ተዘጋጀ።
10 እህቷም ተነሳች። "ለምን ሁሉቱንም እናጣለን" ስትል ያዘቻት።
"ከመሰረቱ ክፉ የሆነ መልካም ፍሬ ሊያፈራ አይችልም። እህቴ
ሆይ! ነይ። አንችም አላጠፋሽም" ስትል ከእጅዋ ሰይፉን ወሰደች።
ከትራሷም ነገስታት የሚለብሱትን የሃር ልብስ ወሰደችና ሰጠችው።
በአማረም ቃል "ልጄ! እነሆ አንተም በኢሉፍሊ መንግስት ላይ
ትቀመጣለህ" ስትል ሸነገለችው።
11 እሱ ግን እንደ ድብ ጨካኝ ነበር፤ ቤታቸውንም እስኪተው ድረስ
ሁለቱን ሊገድላቸው ሽቶ ነበርና ወጡ።
12 ቤቱንም ሲተውለት ሃሩን ወሰደ። ወደ ውጪም ወጣ። እነሱም
ገቡ። በድኑንም ገነዙ። በፅሞናም ቀበሩት። የራት ጊዜም ሲሆን
ፈለጉት አላገኙትምም።
13 አለቆችና ሹማምንቱም ጠየቁ። እናቱም "ይህ ንጉሳችሁ ታሟልና
ይሃኛው በእሱ ፈንታ ይሆናል" አለቻቸው።
14 ወሰደውም አስቀመጡት። ማእድንም ሰሩ። ተደሰቱም።
15 ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሶምሶን ልጅ በላያቸው ላይ ነገሰ።
ከትእዛዙም የተላለፈ የለም። በተወለደ በአምስት ዓመቱ ይህንን
አደረገ። የኢሉፍሊ መንግስትም ከዚያው ጊዜ ጀምሮ ለእሱና
ከእሱ በሁዋላ ለዘሩ ሆነች። እነሆ የኢሉፍሊ መንግስትም የሴም
ዘር እንደሆነ ታወቀ።

## ፹፪ አብርሃም ግብፅ ስለ መውረዱ

1 ደግሞም እግዚአብሄር ለአብርሃም ክብርና ብልፅግናን በሰጠው ጊዜ
በመኝታቸው ልጆችን እንደ አጣ እንነግራችሁዋለን። አብርሃምና ሳራ
"አንች መካን ሆንሽ። አንተ እንጂ እኔ አይደለሁም" እየተባባሉ ይነጋገሩ
ነበር። በዚህም ምክንያት አንዱ አንዱን ባለእዳ ያደርግና ይወቃቀሱ
ነበር።
2 በከነአን ምድር ረሃብ ገባ። አብርሃምም በፈርኦን አገር በግብፅ ምድር
እህል እንዳለ ሰማ። ሃብቱን ሁሉ ለነገ ሳይል በርሃቡ ዘመን ለድሆች
በመራራት በጨረሰ ጊዜና የሚመገበውም ባጣ ጊዜ፣ ረሃብም በከነአን
አገር በበረታ ጊዜ፣ "የሰጠህኝን ከባሪያዎቼ ጋር ጨረስኩ። ስለዚህም
እግዚአብሄርን አመሰግነዋለሁ። ነገር ግን አንች እህቴ ሳራ ሆይ ራሳችንን
ከረሃብ ሞት እናድን ዘንድ ነይ። ወደ ግብፅ አገር እንሂድ" አለ።

www.ethiopianorthodox.org

3 ወትቤሎ ይኩን ሥምረትከ እግዚእየ። ወእመኒ ሞትከ እመውት ምስሌከ። ወእመኒ ሐየውከ አሐዩ ምስሌከ። ወአልብየ ዘእትዐደው እምቃልከ እስከ ለዓለም።

4 ወእምዝ ተንሥኡ ወአኀዙ ይሑሩ። ወሶበ ቀርቡ ይቤላ አብርሃም ለሳራ አሐተ እሴአለኪ ወግበሪ ዘእቤለኪ። ወትቤ ሳራ በል እግዚእየ።

5 ወይቤላ አነ ሰማዕኩ ዘእንበለ ሕግ ንብረቶሙ በጣዖት ወበዝሙት። ወሶበ ርእዩኪ ላዕሌየ ይመክሩ እኩየ ይቅትሉኒ በእንተ ሥነ ላህይኪ። እስመ አልቦ ዘይትማሰለኪ በኀቤሆሙ። ወይእዜኒ ከመ ታሕይዊ ነፍስየ በሊ አንቲ ለእመ ተስእሉኪ በእንቲአየ እኅቱ አነ ከመ ታድኅኒያ ለነፍስየ እሞት በእደ ነኪራን።

6 ወትቤ ሳራ ይኩን ፈቃድከ በሊ ዘትቤለኒ እብል። ወግበሪ ዘትቤለኒ እገብር።

7 ወበከዩ ወሰገዱ ለእግዚአብሔር። ወቦኡ ውስተ ዐባይ ሀገረ ንጉሠ ምስር።

8 ወሶበ ርእይዎ ግብጽ ለአብርሃም ወለሳራ አንከሩ በእንተ ሥነ ራእዮሙ። እስመ ይመስሉ ከመ ዘተወልዱ እምአሐቲ እም፤ ወይቤልዎ ለአብርሃም ምንትከ ይእቲ ዛቲ። ወይቤሎሙ እኅትየ፤ ወካዕበ ተስእልዋ ለሳራ ወይቤልዋ ምንትኪ ውእቱ ዝ። ወትቤሎመ እኅዩ ውእቱ። ወበእንተዝ አርድእዎ ለፈርዖን ከመ መጽኡ ክልኤቱ አኀው ሠናያን ላህይ አሐቲ ብእሲት ወአሐዱ ወሬዛ። ወአልቦ ዘይመስሎሙ በውስተ ኵሉ ምድር።

9 ወተፈሥሐ ፈርዖን። ወለአከ ሎቱ ለአብርሃም እንዘ ይብል ሀበኒአ እኅተከ ከመ እሕፀያ።

10 ወሐለየ አብርሃም እንዘ ይብል ለእመ ከላእኩ ይቀትለኒ ወይነሥእ። ወይቤሎ ግበርአ ዘፈቀድከ*።

11 ወወሀቦ ጠፍልሐ ብሩር እልፈ። ወነሥአ ለሳራ ከመ ይረስያ ብእሲቶ። ወአእተዋ ውስተ ቤቱ። ወአንበራ ውስተ አራቱ። ወቦአ ኀቤሃ ፈርዖን ንጉሠ ግብጽ።

12 ወአስተርአዮ መልአከ እግዚአብሔር በሌሊት እንዘ ይጸውር ሰይፈ እሳት። ወቀርበ ኀቤሁ። ወአብርሀ ቤተ እም ነበልባሉ። ወፈቀደ ይቅትሎ። ወጐየ ፈርዖን እም አረፍተ ቤት እስከ አረፍተ ቤት። ወማዕዘንተ ቤት እስከ ማዕዘንተ ቤት። ወኀበ ሖረ ይተልዎ። ወኀጥአ ኀበ ይትገመር ወኀበ ይትኀባእ።

13 ወእምዝ ሰፍሐ እደዊሁ ወይቤሎ ለመልአክ ኅድግ ሊተ ዛተ አበሳየ እግዚእ።

14 ወይቤሎ ለምንት ትገፍዕ ብእሲቶ ለብእሲ።

15 ወይቤሎ እግዚእ ኢትቅትል ደመ ንጹሐ። እስመ ይቤለኒ እኅትየ ወበእንተዝ አነ ሐፀይክዋ በንጹሕ። ወምንተ እግበር ከመ እድኅን እምእደከ።

* ለእመ አሥመረከ የሚልም አለ።

- 91 -

3 እሷም "ጌታዬ ሆይ! እንደ ፈቃድህ ይሁን፤ ብትሞትም ከአንተ ጋር እሞታለሁ። ከዳንክም ከአንተ ጋር እድናለሁ። ለዘላለምም ከቃልህ የምተላለፈው የለኝም" አለችው።

4 ከዚህ በሁዋላ ተነሱ። ሊሄዱም ጀመሩ። ሲቀርቡም አብርሃም ሳራን "አንድ ነገር እለምንሻለሁ። የምልሽንም አድርጊ አላት። ሳራም ጌታዬ ሆይ! እሺ" አለች።

5 እሱም "እኔ የዚህ አገር ሰዎች ኑሮአቸው በጣኦትና በዝሙት እንደሆነ ሰምቻለሁና፣ አንችን ባዩች ጊዜ በመልክሽ ደም ግባት ይገድሉኝ ዘንድ በእኔ ላይ ክፉ ይመክራሉ። በእነሱ ዘንድ አንችን የሚመስል የለምና። አሁንም ከክፉዎች እጅ ነፍሴን ታድኝኝ ዘንድ ሲጠይቁሽ እህቱ ነኝ በይ" አላት።

6 ሳራም "ፈቃድህ ይሁን፤ በይ የምትለኝንም እላለሁ። አድርጊ የምትለኝንም አደርጋለሁ" አለች።

7 አለቀሱ። ለእግዚአብሄርም ሰገዱ። ወደ ታላቁም የግብፅ ንጉስ አገር ገቡ።

8 ግብፃውያንም አብርሃምንና ሳራን ባዩ ጊዜ ስለ ደም ግባታቸው አደነቁ። ከአንድ እናት የተወለዱ ይመስላሉና። አብርሃምንም "ይህ ምንሽ ነው?" ሲሉ ጠየቋት። "ወንድሜ ነው" አለቻቸው። ስለዚህ ለፈርኦን ሁለት መልከ መልካሞች ወንድምና እህት፣ ማለትም አንዲት ቆንጆና አንድ ጎልማሳ እንደ መጡ ነገሩት። በምድር ሁሉንም የሚመስላቸው የለም አሉት።

9 ፈርኦንም ተደሰተ። ለአብርሃምም "እህትህን አገባት ዘንድ ፍቀድልኝ" ሲል ላከበት።

10 አብርሃምም "ብከለክለው ይገድለኛል፤ እሷንም ይወስዳታል" ሲል አሰበ። ስለዚህ "የምትሻውን አድርግ" አለው።

11 ፈርኦንም ለአብርሃም አስር ሺ ብር ሰጠው። ሳራንም ሚስቱ ያደርጋት ዘንድ ወሰዳት። ወደ ቤቱም አስገባት። በአልጋውም አስቀመጣት። የግብፅ ንጉስ ፈርኦንም ወደ እሷ ገባ።

12 በሌሊትም የእግዚአብሄር መልአክ የእሳት ሰይፉን ይዞ ታየው። ወደ እሱም ቀረበ። ከእሱ የወጣው ነበልባልም ቤቱን አበራ። ይገድለውም ዘንድ ወደደ። ፈርኦንም በቤቱ ውስጥ ከደረጃ ወደ ደረጃ፣ ከማእዘን ወደ ማእዘን ሸሸ። በሄደበትም ይከተለው ነበርና የሚሄድበትና የሚሸሸግበት አጣ።

13 ከዚህ በሁዋላ እጁን ዘረጋና መላኩን "አቤቱ! ይህችን በደሌን ይቅር በለኝ" አለው።

14 መልአኩም "ለምን የሰውየውን ሚስት ትቀማለህ?" አለው።

15 ፈርኦንም "አቤቱ! ንፁህ ደምን አታፍስ። እህቴ ናት ብሎኛልና። ስለዚህ ያጨሁዋትም በንፁህ ነው። አሁንም ከእጅህ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?" አለው።

www.ethiopianorthodox.org

16 ወይቤሎ አግብእ ሎቱ ለአብርሃም ብእሲቶ ወሀቦ አስቦ ወፈንዎ
በሰላም ይእቲ ብሔሮ።
17 ወሶቤሃ ጸውዖ ለአብርሃም። ወወሀቦ ሳራሃ ብእሲቶ ምስለ አመት
እንተ ስማ አጋር። ወወሀቦ ወርቀ ወብሩረ ወአልባሰ ክቡረ
ለአብርሃም። ወፈነዎ በሰላም ወገብኡ ውስተ ሀገሮሙ።
18 ወትቤሎ ሳራ ለአብርሃም አእመርኩ አነ ከመ መካን አነ። ወባሕቱ
ባእ ኀበ ዛቲ አመትየ እንተ ወሀበኒ ፈርዖን እመ ይሁበከ
እግዚአብሔር ዘርዐ በውስቴታ። ወአንሰ ቀበጽኩ ርእስየ ወተነግፈ
ወየብሰ ጽጌ ከርሥየ።
19 ወወሀበቶ አጋርሃ። ወቦአ ኀቤሃ ወፀንሰት ሎቱ ወወለደት። ወሰ
መየቶ ስሞ እስማኤል። ሰምዐኒ እግዚአብሔር ብሂል።
20 ወእምድኅሬሁ ወሀቦ ዘርዐ እግዚአብሔር እምነ ሳራ ብእሲቱ።
ወወለደ ይስሐቅሃ።
21 ወእምድኅሬሁ ቀንዐት ሳራ በእንተ ይስማኤል ወልደ አመታ። እስመ
ልህቀ እምቅድመ ወልዳ ትቤ ዮጊ ይቀትሎ ለወልድየ ወይወርስ
ቤተ አቡሁ።
22 ወሦዐ መሥዋዕተ አብርሃም ለእግዚአብሔር። ወይቤ እግዚኦ ምንተ
እግበር በእንተ ይስማኤል ወልድየ ቀዳሚ በኵርየ። አነ እፈቅድ
ይሕይወኒ ቅድሜከ። ወሳራ እኅትየ ትቀንእ በንተ ዘወሀብከኒ ዘርዐ
በርስአንየ። እስመ ኮና ለይስማኤል ፲ወ፬ ዓመተ ዘእንበለ ይትወለድ
ይስሐቅ።
23 ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአብርሃም አማን ዘትቤ ሳራ ስድዳ ለአመት
ምስለ ወልዳ ይስማኤል። ወለይስማኤልሰ ኅድጎ ይሕየው ቅድሜየ።
ወአነ እሬስዮ ሕዝበ ዐቢየ ወይወልድ ፲ወ፪ ሕዝበ ወይነግሥ
ላዕሌሆሙ ። ወኪዳንየሰ አቀውም ምስለ ይስሐቅ ገብርየ ወልደ ሳራ
ወእባርከ በዘርዑ ኵሎሙ አሕዛበ ምድር። ወእገብሮ ዐቢየ ንጉሠ
ላዕለ ኵሉ አሕዛበ ምድር። ወበሰማያትኒ እሬስዮ ንጉሠ።[80]

## ፲ወ፫ በእንተ ንጉሠ እስማኤላውያን

1 ወበእንተዝ ኮኑ ነገሥተ ደቂቀ ይስማኤል ላዕለ ትርብ ወላዕለ ቅብጥ
ወላዕለ ኖባ ወሳባ ወኩርጕ ወሪፌ ወማካ ወሞርና ወፈልቃናወደርሲ
ባና ወሊባ ወመስዕ እስመ ዘርአ ሴም ውእቱ።
2 ወዘርዐ ይስሐቅኒ ነግሠ ላዕለ ይሁዳ ወላዕለ አሞሬዎን ወላዕለ
ኬጤዎን ወኢያቡሴዎን ወፌርዜዎን ወኤዌዎን ወኬልቄደዎን ወሮምያ
ወአንጾኪያ ወሶርያ ወአርማንያ ወፍልስጥኤም ወኢትዮጵያ ወኤዶም
ወኢሎፍሊ ወኢዮአብ ወአማሌቅ ወአፍርንግያ ወባቢሎን ወዮናንስጥ
ወዕብራይስጥ።

[80] ዘፍጥ.17፥19-20



16 መልአኩም "የአብርሃምን ሚስቱን መልስለት። ካሳውንም ስጠው።
ወደ አገሩም ይሄድ ዘንድ በሰላም አሰናብተው" አለው።
17 ያንጊዜም አብርሃምን ጠራው። ሚስቱን ሳራንም አጋር ከተባለች
ባሪያ ጋር ሰጠው። ብር ወርቅና የከበረ ልብስንም ሰጠው። በሰ
ላምም ላከው። ወደ አገራቸውም ገቡ።
18 ሳራም አብርሃምን "እኔ መካን እንድሆንኩ አወቅሁ። ስለዚህ
እግዚአብሄር ከእሷ ዘርን ቢሰጥህ ፈርኦን ወደ ሰጠኝ ወደዚህች
ባሪያየ ግባ። እኔ ተስፋ ቆርጫለሁና። የወር አበባዬም አቋርጧል፤
ደርቋልምና" አለችው።
19 አጋርንም ሰጠችው። ወደ እሷም ገባ። ፀነሰች፤ ወለደችም፤ ስሙንም
እስማኤል አለችው። "እግዚአብሄር ሰማኝ" ማለት ነው።
20 ከዚህ በሁዋላ እግዚአብሄር ከሚስቱ ከሳራ ዘርን ሰጠው።
ይስሃቅንም ወለደ።
21 በሁዋላም ሳራ በባሪያይቱ ልጅ በእስማኤል ቀናች። ከልጅዋ
አስቀድሞ አድጓልና። "ልጄን ይገድለዋል። የአባቱንም ቤት
ይወርሳል" ብላ።
22 አብርሃምም ለእግዚአብሄር መስዋእትን አቀረበና "አቤቱ! ስለ በኩር
ልጄ ስለ እስማኤል ምን ላድርግ? እኔ በፊትህ እንዲኖርልኝ
እሻለሁ። እህቴ ሳራ ደግሞ በስተርጅና ስለሰጠህኝ ዘር ትቀናለች"
አለ። ይስሃቅ ሳይወለድ እስማኤል አስራ አራት አመቱ ሆኖ ነበር።
23 እግዚአብሄርም አብርሃምን "ሳራ ያለችው እውነት ነው። ባሪያይቱን
ከልጅዋ ከእስማኤል ጋር ስደዳት። እስማኤል ግን በፊቴ በህይወት
ይኖር ዘንድ ተወው። እኔም ታላቅ ህዝብን አደርገዋለሁ። አስራ
ሁለት ነገዶችንም ይወልዳል። በላያቸውም ላይ ይነግሳል። ቃል
ኪዳኔንም ከሳራ ልጅ ከይስሃቅ ጋር አቆማለሁ። በዘሩም የአለምን
ህዝቦች እባርካለሁ። በምድር ህዝቦች ሁሉ ላይ ታላቅ ንጉስን
አደርገዋለሁ፤[80] በሰማይም ንጉስ አደርገዋለሁ" አለው።

## ፲ወ፫ ስለ እስማኤላውያን ንጉስ

1 ስለዚህ የይስማኤል ልጆች ነገሰታት በትርብ፣ በግብፅ፣ ኖባ፣ በሳባ፣
በኩርጎ፣ በሪፌ፣ በማካ፣ በምርና፣ በፊንቃና፣ በአርሳባ፣ በሊባና
በመስአ ላይ ንጉሶች ሆኑ። እስማኤል የሴም ዘር ነው።
2 የይስሃቅ ዘርም በይሁዳ፣ በአሞሬዎን፣ በኬጤዎን፣ በኢያቡሴ ዎን፣
በፌርዜዎን፣ በኤዊዎን፣ በኬልቄዲዎን፣ በሮምያ፣ በአንፆኪያ፣ በሶርያ፣
በአርማንያ፣ በፍልስጤም፣ በኢትዮጵያ፣ በኢዶም፣ በኢዮሎፍሊ፣
በኢዩአብ፣ በአማሌቅ፣ በአፍርንግያ፣ በባቢሎንና በዮናንስጥና ላይ
ነገሰ።

[80] ዘፍጥ.17፥19-20

www.ethiopianorthodox.org

3 እስመ ኵላ መንግሥት በከመ መሐለ እግዚአብሔር ወወሀቦሙ
ለዘርዐ ሴም ልዑለ መንበር ወምኵናን ለዘርዐ ሴም በከመ ባረኮ
አቡሁ ኖኅ በቃለ እግዚአብሔር ለሴም ወልዱ እንዘ ይብል ኩን
እግዚአ ለአኀዊከ ወንገሥ ላዕሌሆሙ።
4 ወዘንተ ዘይቤ በእንተ መድኅን ዘለኵልነ ንጉሠ ኢየሱስ ክርስቶስ
ንጉሠ ሰማያት ወምድር። ዘውእቱ የዐቢ ነገሥተ። ወለእለ ፈቀደ
ካዕበ ይስዕር ሥልጣኖሙ። እስመ ሎቱ ክሂል ወሥልጣን ላዕለ ኵሉ
ፍጥረት። ለዓለመ ዓለም አሜን።

## ፲ወ፬ በእንተ ንጉሠ ኢትዮጵያ ዘከመ ገብአ ሀገሮ

1 ወንጉሠ ኢትዮጵያሰ ቦአ ውስተ ሀገሩ በዐቢይ ፍስሓ ወተድላ ምስለ
ኵሉ ቃለ ማኅሌቶሙ ወእንዚራቲሆሙ ወሠረገላቲሆሙ ከመ ኀይለ ሰ
ማያውያን። እንዘ ይረውጹ በጽሑ ደወሎሙ እምኢየሩሳሌም በዕለት
ሀገረ ወቁሮም።
2 ወለእኩ ላቲ በአሕማር ከመ ይንግርዋ ለማክዳ ንግሥተ ኢትዮጵያ።
ወአርድእዋ ዘከመ ረከቡ ኵሎ ሠናያተ ወዘከመ ነግሠ ወልዳ ወዘከመ
አምጽእዋ ለጽዮን ሰማያዊት። ተዜነወት ዘንተ ኵሎ ክብረ።
3 ወአየደት ዐዋደ ውስተ ኵሉ መንግሥት ዘእምታቴሃ ከመ ትትቀበሎ
ለወልዳ። ወፈድፋደሰ ዘበእንተ ጽዮን ሰማያዊት ታቦት አምላከ
እስራኤል።
4 ወነፍሑ ቀርነ በቅድሜሃ። ወተፈሥሑ ኵሎሙ ሰብአ ኢትዮጵያ
እምንኡስ እስከ ዐቢይ ወእምተባዕት እስከ አንስት። ወተንሥኡ ሰቤሃ
ምስሌሃ ከመ ይትቀበልዎ ለንጉሦሙ።
5 ወበጽሐት ሀገረ ምስፍና እንተ ይእቲ ርእሰ መንግሥተ ኢትዮጵያ
ዘበደኃሪ መዋዕል ኮነ ርእሰ ክርስቲያን ኢትዮጵያ።
6 ወውስቴታ አስተዳለወት ዕፍረተ ዘአልቦ ኍልቈ እምነ ህንድ ወእምነ
በልቲ እስከ ጋልቴት ወእምነ አልሳፋ እስከ አዘዘት ወአስተጋብአት።
7 ወመጽአ ወልዳ እንተ ፍኖተ አዝያባ ወቂሮ። ወወፅአ እንተ መስዕ።
ወዐርገ ቡር። ወመጽአ ሀገረ ምስፍና ርዕሰ ኢትዮጵያ ዘለሊሃ
አሕነጸታ በስማ ወተብህለት ደብረ ማክዳ።

## ፲ወ፭ ኀበ ተፈሥሐት ማክዳ ንግሥት

1 ወበጽሐ ዳዊት ንጉሥ በዐቢይ ግርማ ውስተ ሀገረ እሙ።
2 ወእምዝ ርእየታ በመልዕልት ለጽዮን ቅድስት እንዘ ታበርህ ከመ
እንተ ፀሐይ።
3 ወሶበ ርእየታ አእኰተቶ ወሰብሐቶ ለአምላከ እስራኤል። ወሰገደት
ወጐድአት እንግድዓሃ። ወአልዐለት ርእሳ። ወነጸረት ውስተ ሰማያት።
ወአእኰተቶ ለፈጣሪሃ። ወጠፍሐት በእደዊሃ። ወየበበት በአፉሃ።

- 93 -

3 እግዚአብሄር እንደ ማለ መንግስትን ሁሉ ለሴም ዘር
ሰጥቷቸዋልና። አባቱ ኖህ በእግዚአብሄር ቃል ልጁን ሴምን
"ለወንድሞችህ ጌታ ሁን። በላያቸው ላይ ንገስ" ብሎ እንደ
መረቀው የሴም ዘር ዙፋንና ግዛቱ ታላቅ ነው።
4 ይህንንም ያለው ለሁላችን ንጉስ ስለሆነው፣ ስለ ሰማያትና ምድር
ንጉስ፣ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እሱ ከነገስታት ሁሉ
ይበልጣል። ደግሞም ስልጣናቸውን ይሽራል። እሱ በፍጥረታት ሁሉ
ላይ ስልጣንና ችሎታ አለው። ለዘላለሙ አሜን።

## ፲፬ የኢትዮጵያ ንጉስ ወደ አገሩ እንደ ተመለሰ

1 የኢትዮጵያ ንጉስ ግን በብዙ ደስታና ተድላ ወደ አገሩ ገባ።
እንደ ሰማይ ሃይላትም ከብዙ የዘፈንና የእንዚራ ድምፅ ጋር በሰ
ረገሎቻቸው እየወጡ ከኢየሩሳሌም በአንድ ቀን ወቂሮም ከተባለ
አገር ገቡ።
2 ለኢትዮጵያ ንግስት ማክዳም ይነግሯት ዘንድ በጀልባዎች
መልእክተኞችን ላኩ። መልካሙን ሁሉ እንዳገኙና ልጅዋም እንደ
ነገሰ ሰማያዊቷ ፅዮንንም እንደ አመጧት ነገሯት። ይህንን ሁሉ
ክብር የምስራች ተባለች።
3 ልጅዋንና ይልቁንም ሰማያዊቷን የእስራኤልን አምላክ ታቦት ትቀበል
ዘንድ በበታቹ ባለች መንግስት ሁሉ አዋጅ ነጋሪን አዞረች።
4 በፊቷም ነጋሪትን መቱ። ሁሉም የኢትዮጵያ ሰዎች ከትልቅ እስከ
ትንሽ ከወንድ እስከ ሴት ድረስ ተደሰቱ። ያንጊዜም ንጉሳቸውን
ሊቀበሉት ከእሷ ጋር ወጡ።
5 የምስፍና አገር ከተባለችውና በሁዋለኛው ዘመን ክርስቲያን የሆነው
የኢትዮጵያ መንግስት ርእሰ መዲና ከሆነችው ቦታ ደረሱ።
6 በውስጧም ቁጥር የሌለው ከህንድ፣ ከባልቴ እስከ ጋልቴት፣
ከአሳፋም እስከ አዘዘችበት ድረስ ሽቶን አዘጋጀች ሰበሰበችም።
7 ልጅዋም በአዝያባና በቂሮ መንገድ መጣ። በመስእ በኩልም መጣ።
ወደ ቡርም መጣ።የኢትዮጵያ ርእሰ መዲና ከሆነችው ሃገር ደረሰ።
ይሄውም እሷ ያሰራችው የማክዳ ደብር የተባለው ነው።

## ፲፭ ንግስት ማክዳ እንደ ተደሰተች

1 ንጉስ ዳዊትም በታላቅ ግርማ ከእናቱ አገር ደረሰ።
2 ከዚህ በሁዋላ ንግስት ማክዳ ከፍ ካለ ቦታ ሁና ቅድስት ፅዮንን
እንደ ፀሃይ ስታበራ አየቻት።
3 ባየቻትም ጊዜ የእስራኤልን አምላክ ፈፅማ አመሰገነች፣ ሰገደችም።
ደረቷንም ደቃች። ራሷንም አቅንታ ወደ ሰማያት ተመለከተች።
ፈጣሪዋንም አመሰገነች። በእጅዋ አጨበጨበች። በአፏም እልል
አለች። በእግሯ አሸበሸበች። ሰውነቷን ሁሉ በደስታ አስጌጠች።
በውስጧ መንፈሷ ሁሉ ተደሰተች።

www.ethiopianorthodox.org

ወአጽሐሰት በእገሪሃ። ወአሠርገወት ኵሎ ሥጋሃ በፍሥሓ።
ወተሐሥየት በመንፈስ ኵሉ ውሳጥያቲሃ።
4 ወምንተ እብል ዘኮነ አሜሃ ፍሥሓ ለብሔረ ኢትዮጵያ እምሰብእ
እስከ እንስሳ እምንኡስ እስከ ዐቢይ ወእምአንስት እስከ ተባዕት።
5 ወተከለት ደብተራ [illegible]መታተ መትሕተ ደብረ ማክዳ ውስተ ስፉሕ
ምድር ኀበ ሠናይ [illegible]ይ። ወጠብሐት መጋዝአ ላህም ወአሥዋረ
መጠነ ፲፻፸ወ፷፻።
6 ወአንበርዋ ለጽዮን ውስተ ሕጽነ ደብረ ማክዳ ወአግበረት ላቲ
ዐቀብተ ፫፻ እንዛነ አስይፍት ለጽዮን እም የዐቅቡ ደባትሪሃ ለጽዮን
ምስለ እሊኣሃ ወመኳንንቲሃ ኀያላነ እስራኤል ወእሊኣሃ ፫፻ እንዛነ
አስይፍት ወለወልዳሂ ንጉሥ ዳዊት ከማሁ፮፻።
7 ወይትፌሥሑ ፈድፋደ በብዙኀ ክብር ወተድላ በሠናይ አልባስ።
እስመ አርትዐት መንግሥተ እምባሕረ ኢሊባ እስከ ባሕረ አሴካ
ወኵሉ ይትኤዘዝ በቃላ። ወባቲ ክብረ ወብዕለ ፈድፋደ ዘአልቦ ዘኮነ
እምቅድሜሃ ወኢይከውንሂ እምድኅሬሃ።
8 እስመ በውእቱ መዋዕል በኢየሩሳሌም ሰሎሞን ንጉሥ ወበኢትዮጵያ
ማክዳ ንግሥት። ለክልኤሆሙ ተውህበ ጥበብ፣ ወብዕል፣ ወሞገስ፣
ወአእምሮ፣ ወሥነ ቃል፣ ወልቡና። ወወርቅ ወብሩር ኀሠረ ከመ
ብርት ወዲባጋት ዘወርቅ ኮነ ከመ ዐግያት ዘፈትል ወእንስሳ
ወአፍራስ ዘአልቦ ኍልቍ።

## ፹ወ፮ ኀበ አንገሠቶ ማክዳ ለወልዳ

ወአመ ሣልስት ዕለት አወፈየቶ ለወልዳ አፍራስ ኅሩያነ እለ የዐቅቡ ተዓይነ ፀር ወያመዘብሩ ካዕበ አህጉረ ፀር ፲፻ወ፹ ወ፫፻ ምእተ። ወበቅለ እንስተ ዐሠርተ ምእተ። ወበቅለ ተባዕተ ኅሩያነ ሰብዐተ ምእተ። ወአልባሰ ክብር፣ ወርቀ፣ ወብሩረ ስፉረ በጎሞር ወመጠነ መሥፈርተ ቆሮስ በበሳድስ ወሳብዕ። ወአወፈየቶ ኵሎ ዘበሕጉ ወመንበረ መንግሥታኒ ኵሎ አወፈየቶ ለወልዳ።

## ፹ወ፯ ኀበ መሐሉ መኳንንተ ኢትዮጵያ

1 ወትቤሎሙ ለመኳንንቲሃ በሉኬ መሐሉ በጽዮን ሰማያዊት ከመ
ኢታንግሡ አንስተ ውስተ መንበረ መንግሥተ ኢትዮጵያ ዘእንበለ
ዘርዑ ለዳዊት ወልደ ሰሎሞን ንጉሥ ተባዕተ እስከ ለዓለም
ወኢታንግሡ አንስተ እስከ ለዓለመ ለዓለም።
2 ወመሐሉ ኵሎሙ ዐበይተ ቤተ ንጉሥ ወመኳንንት ወመማክርት
ወመገብት። ወአምሐልዎሙ ኤልምያስ ወአዛርያስ ሊቀ ካህናት ወሊቀ
ዲያቆናት። ወሐደሱ መንግሥተ። ወገብሩ ሕገ ደቂቀ ኀይለ
እስራኤል ምስለ ንጉሦሙ ዳዊት በውስተ ደብተራ ስምዕ።

- 94 -

4 ያን ጊዜ ለኢትዮጵያ ከሰው እስከ እንስሳ፣ ከትንሽ እስከ ትልቅ፣
ከሴት እስከ ወንድ ስለሆነው ደስታ ምን እላለሁ?።
5 ድንኳኖችንና መጠለያዎችን ከደብረ ማክዳ በታች በሰፊ ምድር
በጥሩ ወንዝ ተከለች። ቁጥራቸው ሰላሳ ሁለት ሺ ያህሉ
ፍሪዳዎችንና በሬዎችን አረደች።
6 ፅዮንንም ከደብረ ማክዳ ውስጥ አስቀመጧት። ሶስት መቶ ሰይፍ
የያዙ ጠባቂዎችንም አደረገችላት። እንዲሁም የፅዮንን ድንኳንኖች
ከእሷና ከእስራኤል ሃያላን ከመኳንንቶቹ ጋር የሚጠብቁ ሶስት
መቶ ሰይፍ የያዙ ነበሩ። ልጅዋን ንጉስ ዳዊትንም የሚጠብቁ
እንደዚሁ ስድስት መቶ ነበሩ።
7 በብዙ ክብርና ተድላ በአማሩ ልብሶችም ፈዕመው ደስ ኣላቸው።
ከኣሌላ ባህር ጀምሮ እስከ ኣሴካ ባህር ድረስ መንግስቷን ኣፀናች።
ሁሉም በቃሏ ይታዘዝላት ነበር። ከእሷ በፊት ያልነበርና ከእሷም
በሁዋላ የማይሆን ብዙ ክብርና ሃብት ነበራት።
8 በዚያን ዘመን በኢየሩሳሌም ንጉስ ሰሎሞን፣ በኢትዮጵያም ንግስት
ማክዳ ነበሩ። ለሁለቱም ጥበብ፣ ክብር፣ ሃብትና ሞገስ ኣእምሮም
የአነጋገር ማማርና ማስተዋል ተሰጥቷቸው ነበር። ወርቅና ብር
እንደ ብረት ርካሽ የወርቅ ማርዳም እንደ ተልባ እግር ፈትል
ሆነ። እንስሳትና ፈረሶችም ቁጥር አልነበራቸውም።

## ፹፮ ማክዳ ልጅዋን እንዳነገሰች

በሶስተኛው ቀን የጠላትን ሰፈር የሚጠብቁና የጠላትን ኣገሮች የሚያፈራርሱ ኣስራ ሰባት ሺ ሰባት መቶ የተመረጡ ፈረሶችን፣ አንድ ሺ እንስት በቅሎዎችን፣ ሰባት መቶ ተባእት በቅሎዎችንና የክብር ልብሶችን ወርቅና ብርን በጎመር* እና በቆሮስ* በስድስትና በሰባት ተሰፍሮ ሰጠችው። ሁሉንም በህጉ መሰረት ሰጠችው። የመንግስቷንም ዙፋን ሰጠችው።

## ፹፯ የኢትዮጵያ መኳንንት እንደ ማሉ

1 መኳንንቶቹንም "በኢትዮጵያ መንግስት ዙፋን ላይ የዳዊት ዘር
ከሆነው ከንጉስ ሰሎሞን ወንድ ልጅ ካልሆነ በቀር ለዘላለሙ
ሴቶችን እንዳታነግሱ ማሉ" ኣለቻቸው።
2 ሁሉም የቤተ መንግስቱ ታላላቆችና መኳንንቱ ኣማካሪዎችና
ሹማምንቱ ሁሉ ማሉ። መንግስቱንም ኣደሱ። በምስክሩ ድንኳን
ውስጥ ከንጉሳቸው ከዳዊት ጋር ሆነው የእስራኤል ሃያላን ልጆች
ህግን ሰሩ።

---

*አራት ሊትር ያህል የሚይዝ መስፈሪያ

*ዝኒ ከማሁ።

www.ethiopianorthodox.org

3 ወተሐደሰት መንግሥት። ወበርሃ አልባበ ሰብእ በርእየተ ጽዮን ታቦተ
ሕጉ ለእግዚአብሔር። ወገደፉ ጣዖቶሙ ሕዝበ ኢትዮጵያ። ወአምለኩ
ፈጣሪሆሙ ለዘገብሮሙ እግዚአብሔር።
4 ኀደጉ ምግባራቲሆሙ ሰብአ ኢትዮጵያ። ወአፍቀሩ ጽድቀ ወርትዐ
ዘያፈቅር እግዚአብሔር።
5 ኀደጉ ዝሙቶሙ ዘትካት። ወአፍቀሩ ንጽሐ በውስተ ትዕይንት
-በርእየተ ጽዮን ሰማያዊት።
6 ኀደጉ ማሪተ ወሰገለ። ወአፍቀሩ ንሥሓ ወአንብዐ ለእግዚአብሔር።
7 ኀደጉ ተጠይሮ ወአማዕም። ወገብኡ ለሰሚዐ ወለሠዊዐ
ለእግዚአብሔር።
8 ኀደጉ ተውኔተ አማልክት ዘአጋንንት። ወአፍቀሩ ተቀንዮ ወሰብሖ
ለእግዚአብሔር። ተኀሥራ አዋልደ ኢየሩሳሌም። ወከብራ አዋልደ
ኢትዮጵያ።
9 ተከዘት ወለተ ይሁዳ። ወተፈሥሐት ወለተ ኢትዮጵያ።
10 ተፈሥሓ አድባረ ኢትዮጵያ። ወተከዛ አድባረ ሊባኖስ በጣዖት
ወግልፈዋት።
11 ተኀርዩ ሕዝበ ኢትዮጵያ። ወተመነኑ ሕዝበ እስራኤል ተመነና
አዋልደ ጽዮን። ወከብራ አዋልደ ኢትዮጵያ።
12 ኀሥሩ አእሩገ እስራኤል። ወከብሩ አእሩገ ኢትዮጵያ። እስመ
እግዚአብሔር ተወክፎሙ ለግዱፋን ሕዝብ። ወመነኖሙ ለእስራኤል
በእንተ ዘተንሥአት ጽዮን እምኔሆሙ ወወፅአት ውስተ ብሔረ
ኢትዮጵያ።
13 እስመ ኀበ ሠምረ እግዚአብሔር ተኀድር ጽዮን። ወኀበሰ ኢሠምረ
ኢተኀድር። እስመ ለሊሁ ኬንያሃ፣ ገባሪሃ፣ ወሐናጺሃ እግዚአብሔር።
14 እግዚአብሔር ኄር በውስተ ጽርሐ መቅደሱ ለማኀደረ ስብሐቲሁ
ምስለ ወልዱ ወመንፈሱ ቅዱስ እስከ ለዓለመ ዓለም። አሜን።
15 ወወሀበት ንግሥተ ኢትዮጵያ ማክዳ መንግሥተ ለወልዳ ዳዊት
ወወልደ ሰሎሞን ንጉሠ እስራኤል። ወትቤሎ ንሣእ ወሀብኩከ።
ወአንገሥኩ ዘእግዚአብሔር አንገሠ። ወኀረይኩ ዘእግዚአብሔር ኀረየ
ቀዋሚሃ ለደብተራሁ። ወሠመርኩ ዘእግዚአብሔር ሠምረ ላእከ ታቦተ
ኪዳኑ ወሕጉ። ወአዕበይኩ ዘእግዚአብሔር አዕበየ መጋቤ ለእቤራቲሁ።
ወአክበርኩ ዘእግዚአብሔር አክበረ ወሀቤ ሲሳይ ለእጓለ ማውታ።
6 ወተንሥአ ንጉሥ ወቀነተ ዘይትዐጸፍ። ወሰገደ ለእሙ። ወይቤላ ንግሥትሰ
አንቲ እግዝእትየ። ወአነ እትለአክ በኀበ ኵሉ ዘአዘዝክኒ እመሂ ለሞት
ወእመሂ ለሕይወት። ኀበ ፈነውክኒ እትፌነው። ወኀበ ለአክኒ እትለአክ።
ወኵሉ ዘአዘዝክኒ እገብር። እስመ አንቲ ርእስ። ወአነ እግር። ወአንቲ
እግዝእት። ወአነ ገብር ለኪ። ወኵሉ ይትገበር በቃልኪ። ወአልቦ
ዘይትዐደው እምትእዛዝኪ። ወእገብር ኵሉ ዘፈቀድኪ።
ወባሕቱ ጸልዪ ላዕሌየ ከመ ያድኅነኒ እምመዐቱ አምላከ እስራኤል እስመ
ይትመዐዕ። ይቤሉነ ለእመ ኢያርታዕነ ልበነ ለገቢረ ፈቃዱ ወኢያሠነይነ
በኵሉ ትእዛዛ ለጽዮን ማኀደረ ስብሐቲሁ ለእግዚአብሔር። እስመ መልአከ
ኀይሉ ምስሌነ ዘመገበነ ወአብጽሐነ ዝየ። ወኢይትፈለጥ ወኢይትአተት
እምኔነ።

- 95 -

3 መንግስቲቱ ታደሰች። የእግዚአብሄር ታቦተ ህግ ማለት ፅዮንን
በማየት የሰዎች ልብ በራ። የኢትዮጵያ ሰዎችም ጣኦታቸውን
ጣሉ። የፈጠራቸውን አምላካቸው እግዚአብሄርን አመለኩ።
4 የኢትዮጵያ ሰዎችም ምግባራቸውን ተው። እግዚአብሄር የወደደውን
እውነትንና ቅንነትን ወደዱ።
5 የዘወትር ዝሙታቸውንም ተው። ሰማያዊቷ ፅዮን ባለችበት
ከተማቸው ውስጥ ንፅህናን ወደዱ።
6 ሟርትንና ጥንቆላን ተው። ንስሃንና ወደ እግዚአብሄር ማልቀስን ወደዱ።
7 ማሟረትንና አምልኮ ጣኦትን ተው። እግዚአብሄርን ለመስማትና
ለእግዚአብሄር ወደ መሰዋትም ተመለሱ።
8 የአጋንንትንና የአምልኮ ጣኦት ጨዋታን ተው። እግዚአብሄርን
ማመስገንና ለእግዚአብሄር መገዛትን ወደዱ። የኢየሩሳሌም ልጆች
ተኀሳቀሉ። የኢትዮጵያ ልጆችም ከበሩ።
9 የይሁዳ ልጅ ተከዘች። የኢትዮጵያ ልጅ ተደሰተች።
10 የኢትዮጵያ ተራሮች ተደሰቱ። የሊባኖስ ተራሮችም በጣኦትና
በተቀረፁ ምስሎች አዘኑ።
11 የኢትዮጵያ ህዝቦች ተመረጡ። የፅዮን ሴቶች ልጆችም መናቅን ተናቁ።
12 የእስራኤል ሽማግሎች ተኀሳቀሉ። የኢትዮጵያ ሽማግሎች ከበሩ።
ከእግዚአብሄር የተጣሉትን ህዝቦች ተቀብሏቸዋልና። ፅዮን ከእነሱ
ዘንድ ስለ ተወሰደችና ወደ ኢትዮጵያ ስለ መጣች እስራኤልን ናቃቸው።
13 እግዚአብሄር በወደደበት ፅዮን ታድራለች። ባልወደደበት ግን
አታድርም። እሱ እራሱ መስራቿ፣ ሰሪዋና አናፂዋ ነውና።
14 እግዚአብሄር በመቅደሱ ውስጥ ለምስጋናው ከልጁና ከመንፈስ
ቅዱስ ጋር ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ቸር ነውና።
15 የኢትዮጵያ ንግስት ማክዳ ለልጅዋና ለእስራኤል ንጉስ ለሰሎሞን
ልጅ ለዳዊት መንግስትን ሰጠችው። አለችውም። "እነሆ መንግስትን
ሰጠሁህ። እግዚአብሄር ያነገሰውን አነገስኩ። እግዚአብሄር
የመረጠውንና ለድንኳኑ ቋሚ የሆነውን መረጥኩ። እግዚአብሄር
የወደደውን ወደድኩ። የቃል ኪዳኑን ታቦትና የህጉ መልእክተኛ
የሆነውን ወደድኩ። እግዚአብሄር ለሽመገሉት ሹም ይሆን ዘንድ
እንቢ ያለውን እንቢ አልኩ። ለሙት ልጆች መጋቢ የሆነውንና
እግዚአብሄር ያከበረውን አከበርኩ።"
16 ንጉሱም ተነሳ። የለበሰውንም ታጠቀ። ለእናቱም "ንግስት ሆይ
አንች እመቤቴ ነሽ። እኔም ለሞትም ቢሆን አንች ባዘዝሽኝ ሁሉ
እላካለሁ። ያዘዝሽኝን ሁሉ እሰራለሁ። አንች ራስ፣ እኔም እግር
ነንና። አንች እመቤቴ እኔም የአንች ባሪያ ነኝና። ሁሉ በቃልሽ
ይደረጋል። ከትእዛዝሽም የሚተላለፍ የለም። የፈቀድሽውንም ሁሉ
አደርጋለሁ" አላት።
17 "ነገር ግን የእስራኤል አምላክ ከመአቱ ያድነኝ ዘንድ ፀልዩ።
ፈቃዱን ለማድረግ ልባችንን ካላቀናው፣ በእግዚአብሄር የምስጋናው

www.ethiopianorthodox.org

18 ወይእዜኒ ስምዒ ኦ እግዝእትየ ለእመ አሠነይነ ወገበርነ ፈቃዶ አነ
ወእለ እምድኅሬየ ይነብር እግዚአብሔር ምስሌነ ወየዐቅበነ እምነ
ኵሉ እኩይ ወእምእደ ፀርነ።
19 ወእመሰ ኢያርታዕነ ልበነ ኀቤሁ ይትመዐዐነ ወይመይጥ ገጾ እምኔነ።
ወይቀሥፈነ። ወይትሐበለዩነ ጸላእትነ። ወይመጽአነ ፍርሃት ወረዓድ
እምኀበ ኢተሐዘብነ። ወይትነሥኡ ላዕሌነ ወይጸብኡነ ጸብአ።
ወያጠፍኡነ።
20 ወለእመሰ ገበርነ ፈቃደ እግዚአብሔር ወአሠነይነ ግብረ ለጽዮን
ንከውን ኄራነ። ወአልቦ ዘይክል አሕስሞ ላዕሌነ በደብረ መቅደሱ
እንዘ ሀለወት ማኅደሩ ምስሌነ።
21 ወነዋ ዘአምጻእነ ጽሑፍ ምስሌነ ኵሉ ሕገ መንግሥት ወትእዛዙ
ለእግዚአብሔር ዘነገረነ ሳዶቅ ሊቀ ካህናት አመ ይቀብዐኒ ቅብዐ
መንግሥት በውስተ ቤተ መቅደሱ ለእግዚአብሔር እንዘ ውስተ እደሁ
ቀርነ ቅብዐ ዕፍረት ዘክህነት ወዘመንግሥት። ወገብሩ ለነ ዘበሕጉ
ወተቀባዕነ አዛርያስ ለክህነት፣ ወአነ ለመንግሥት፣ ወኤልምያስ አፈ
እግዚአብሔር ዐቃቤ ሕግ። ዘውእቱ ዐቃቢሃ ለጽዮን ወእዘኒሁ
ለንጉሥ በኵሉ ፍኖተ ጽድቅ።
22 ወአዘዙኒ ከመ አልቦ ዘእገብር ዘእንበለ በምክሮሙ። ወአቀሙነ
ቅድመ ንጉሥ ወቅድመ ሊቃውንተ እስራኤል። ወኵሉ ሕዝብ ይሰ
ምዕ እንዘ ይኤዝዘነ ሳዶቅ ካህን።
23 ወተነፍሐ ኢዮብልዮስ ወአርጋኖን ወቃለ እንዚራቲሆሙ ወብእዛቲሆሙ
ወድምፀ ጽራሐቲሆሙ ዘተገብረ አሜሃ በአናቅጺሃ ለኢየሩሳሌም።
ምንተ እነግረክሙ ለእለ ሀለውክሙ ዝየ። እስመ መሰለነ ምድር
ዘታድለቀልቅ እስከ መሠረታቲሃ፣ ወሰማይኒ ዘያንጐደጕድ
በመልዕልቴነ፣ ወልብኒ ትርዕድ ምስለ ብረኪሃ።

## ፹ወ፭ ኀበ ዜነዋ ለእሙ ዘከመ አንገሥዎ

1 ወሶበ አርመሙ እሉ ተንሥአ ካህን ዘይኤዝዘነ ዘምስለ ፍርሀተ
እግዚአብሔር ወአንብዕ እንዘ ትርዕድ ከርሥነ ወትውኅዝ አንብዕ
ውስተ ልብነ።
2 በአማንኬ ኢኮነ ሐሰተ። ህልው እግዚአብሔር ወይነብር ውስተ
ትእዛዙ። ወነገረ ትእዛዙ ኢያአትት እምእለ ያፈቅርዎ ወየዐቅቡ
ትእዛዞ። ይሄሉ ወትረ ምስሌሆሙ።
3 ወይእዜኒአ ስምዕዮሙአ ለእሉ መላህቅት ወደቂቀ ኀያላነ እስራኤል
ዘአምጽኡ ኵነኔ ወፍትሐ። ዘጸሐፉ በቅድመ ንጉሥ ሰሎሞን
ወወሀቡነ ከመ ኢንትገሐሥ ኢለየማን ወኢለፀጋም እምዘ አዘዙነ።
ወካዕበ ይቤሉነ ወአለበዉነ ከመ ነሣእነ ሞተ ወሕይወተ ወከመ
ንእሲ ዘቦቱ ውስተ ፀጋሙ እሳት ወውስተ የማኑ ማይ። ወኀበ
ይፈቅድ ይወዲ እደሁ እስመ መቅሠፍት ወሕይወት ጽሑፍ



ማደሪያ በሆነችው በፅዮን ትእዛዝ አካሄዳችንን ካላሳመርን ይቆጣል
ብለውናልና። የጠበቀንና እዚህ ያደረሰንን መልአክ ሃይሉ እዚህ
ነውና። ከእኛም አይለይም አይወገድም።
18 እነሆ ዛሬም እመቤቴ ሆይ ስሚኝ። እኔና ከእኔ በሁዋላ ያሉት
አካሄዳችንን ካሳመርንና ፈቃዱን ካደረግን እግዚአብሄር ከእኛ ጋር
ይሆናል። ከክፉ ነገርና ከጠላቶቻችንም ይጠብቀናል።
19 ልባችንን ወደ እሱ ካላቀናው ግን ይቆጣናል። ፊቱንም ከእኛ
ይመልስብናል፣ ይቆጣናል፣ ጠላቶቻችንም ይሸነግሉናል፣ ፍርሃትና
እንቅጥቃጤ ከወደ ኣላሰብነው ይመጡብናል፣ በላያችን ላይ
ይነሳሉ፣ ጠብንም ይጣሉናል፣ ያጠፉናልም።
20 የእግዚኣብሄርን ፈቃድ ካደረግንና የፅዮንንም ስራ ካሳመርን ቸሮች
እንሆናለን። ማደሪያው ከእኛ ጋር እስካለች ድረስ በቤተ መቅደሱ
በእኛ ላይ ክፉ ማድረግ የሚቻለው የለም።
21 ከእኛ ጋር የመጣው ፅሁፍ፣ ህገ መንግስቱና ሊቀ ካህናቱ ሳዶቅ፣
በእግዚኣብሄር ቤተ መቅደስ ውስጥ የክህነቱና የመንግስቱ ቅብኣ
እፍረት በእጁ ሳለ ቅብኣ መንግስት ሲቀባኝ የነገረን የእግዚኣብሄር
ትእዛዝ ይህ ነው።
22 ኣዛርያስ ለክህነት፣ እኔ ለመንግስት፣ ኣልምያስም የእግዚኣብሄር
አፍና ኣቃቤ ህግ፣ የፅዮን ጠባቂና በሁሉም ነገር የንጉሱ ጆሮ
ጠቢ ሁነን ተቀባን። ያለ እነሱም ምክር እንዳላደርግ ኣዘዘኝ።
ከንጉሱና ከእስራኤል ሊቃውንት ፊት ኣቆሙው ካህኑ ሳዶቅም
ሲያዝዘው ህዝቡ ሁሉ ይሰማ ነበር።
23 ቀንደ መለከት፣ የዘፈንና የማህሌት መሳሪያ፣ የእንዚራ መሳሪያዎች፣
መላከተኞችና ያኔ በኢየሩሳሌም ደጃፍ ላይ የተደረገው የድምፃቸው
ቃና ሁሉ ተሰማ። እዚህ ላላችሁት ምን እነግራችሁዋለሁ? ምድር
እስከ መሰረቷ ድረስ የምትነዋወጥ፣ ሰማይም በላያችን ላይ
የሚያንጎደጉድ፣ ልብም ደግሞ ከጉልበቷ ጋር የምትንቀጠቀጥ
ይመስለን ነበር።

## ፹፭ እንደ ኣነገሱት ለእናቱ እንደ ነገሯት

1 "እነሱ ዝም ባሉ ጊዜ እግዚኣብሄርን በመፍራትና በእንባ ሆዳችን
እየንቀጠቀጠች፣ እንባችንም በልባችን ውስጥ እየፈሰሰች የሚያዝዘው
ካህን ተነሳ።
2 በሃሰት ያይደለ በእውነት እግዚኣብሄር ኣለ። በትእዛዙም ውስጥ
ይኖራል። ከሚወዱትና ትእዛዙን ከሚጠብቁት ትእዛዙን መንገር
ኣያስወግድም። ከእነሱም ጋር ለዘወትር ይኖራል።
3 ኣሁንም እነዚህን ኣገዛዝንና ፍርድን ያመጡና ወደ ቀኝም ወደ
ግራም እንዳንል በንጉሱ በሰሎሞን ፊት የፃፉና የሰጡንን እነዚህን
ኣለቆችና የእስራኤል ሃያላንን ሽማግሌዎች ስሚያቸው። እነሱም
በግራው እሳት፣ በቀኙ ውሃ እንዳለውና እጁንም ወደ ወደደው
እንደሚጨምር ሰው ሞትና ህይወትን እንደወሰድን ኣሳሰቡን።

www.ethiopianorthodox.org

ውስቴቱ ለእለ ገብርዋ ለእኪት መቅሠፍት ወለእለ ገብርዋ
ለሠናይት ሕይወት።
4 ወአውፅኡ ኤልምያስ ወአዛርያስ ይእተ መጽሐፈ እንተ ተጽሕፈት
በቅድመ እግዚአብሔር ወበቅድመ ንጉሠ እስራኤል። ወአንበብዋ
በቅድመ ማከዳ ወበቅድመ ዐበይተ እስራኤል።
5 ወሶበ ሰምዑ ዘንተ ቃላተ ሰገዱ ለእግዚአብሔር ኵሎሙ እለ
ውስተ ዐውድ ንኡሶሙ ወዐቢዮሙ። ወገነዩ ወሰብሑ ለእግዚአብሔር
ለዘአስምዖሙ ዘንተ ቃለ ወወሀቦሙ ዘንተ ትእዛዘ ከመ ይግበሩ
ፍትሐ ወኵነኔሁ ለእግዚአብሔር።
6 ወዓዲ ረሰዮሙ ሰብአ ቤቱ። እስመ ሀለወት ጽዮን ማእከሌሆሙ
ወማኅደረ ስብሐቲሁ ለእግዚአብሔር እንተ ታድኅኖሙ እምኵሉ
እኩይ። ወትባርክ ፍሬ ምድሮሙ። ወታበዝኅ እንስሳሆሙ። ወትባርክ
አንቅዕተ ማያቲሆሙ። ወትባርክ ተግባሮሙ ወፍሬ አትክልቲሆሙ።
ወታልህቅ ውሉዶሙ። ወተዐቅብ ርስዐኒሆሙ። ወትከውኖሙ ፍጽመ
ወከዋላ ኀበ ኵሉ ዘኀደሩ። ወይመውኡ ፀሮሙ በኵሉ ኀበ ሐሩ።
ወተፈሥሑ ኵሎሙ ሰብአ ኢትዮጵያ።
7 ወንግሥትኒ ትቤሎ ለወልዳ ወልድየ። ወሀበከ እግዚአብሔር ርትዐ።
ወሑር ባቲ። ወኢትትገሐሥ ኢለየማን ወኢለፀጋም። ወአፍቅር
እግዚአብሔርሃ አምላክከ። እስመ መሓሪ ውእቱ ለየዋሃን። እስመ
እምትእዛዙ ይትዐወቅ ፍኖቱ። ወእምአምሕርተ ነገሩ ይትአመር
ኂሩቱ።
8 ወተመይጠት ኀቤሆሙ ለኤልምያስ ወአዛርያ ወለኵሎሙ ኀያላነ
እስራኤል አንትሙ ዕቀብዎ ወመሀርዎ ፍኖተ ለመንግሥተ
እግዚአብሔር ወአክብሮታ ለጽዮን እግዝእትነ። ወለኵሉ ዘኢታፈቅር
እግዝእትነ ኢንግበር። ንግሩነ በአስተጠናቅቆ ለዓለም ለትውልደ
ትውልድ ከመ ኢትትመዐነ ለእመ ኢያሠነይነ ግብራ ወእግዚአብሔርኒ
ከመ ይኅድር ምስሌነ።
9 ወአንተኒ ኦወልድየ ስማዕ ቃለ አበዊከ። ወሑር በምክሮሙ።
ኢያዕብድከ ስታይ ወኢአንስት ወኢአስተምክሖ አልባስ ወአልጕም
አፍራስ። ኢነጽሮ ንዋየ ሐቅል ዘቅድም ወዘድኅር። አላ ይኩን
ትውክልትከ በእግዚአብሔር ወበጽዮን ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር
ፈጣሪከ ከመ ትማዕ ፀረከ ወይብዛኅ ዘርዕከ በዲበ ምድር ወይግርሩ
ጸላእትከ ወፀርከ ዘቅሩብ ወዘርጉቅ።
10 ወእሙንቱኒ ደቂቀ ኀይል አውሥኡ በአሐዱ ቃል ወይቤሉ ንሕነሰ
እግዝእትነ ምስሌክሙ ኵሉ ጊዜ። ወንዜክሮ ለእግዚእ ንጉሥ። ናሁ
እሙ ይሰምዕ። ወንነግሮ ፍኖታ ለምግባረ ሠናይ። እስመ አልቦ
ዘይትረከብ በዝ መዋዕል በጥበብ ዘእንበለ እግዚእነ ንጉሥ ዘከማኪ።
11 ሰሐብክነ ዝየ ከመ አግብርትኪ ምስለ እግዝእትነ ጽዮን ሰማያዊት
ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር አምላክነ በከመ ይስሕብዎ ለገመል
ዘጽዑን ንዋየ ክብር በንስቲቅ ቀጢን ፈትል ኢዊጥ እንተ
ኢትትበተክ ዲበ አንፉ ዝማማት።

- 97 -

ከፋትን ላደረጓት መቅሰፍት፣ መልካምን ላደረጓት ደህንነት
እንዲሆን በውስጧ መቅሰፍትና ደህንነት ተፅፏል ሲሉ ነገሩን።
4 ኣልምያስና ኣዛርያስም በእግዚብሄር ፊትና በንጉሱ ሰሎሞን
የተፃፈችውን መፅሃፍ ኣወጡ። በማክዳና በእስራኤል ታላላቆች ፊት
ኣነበቧት።
5 እነዚህንም ቃላት በሰሙ ጊዜ፣ በኣደባባይ ያሉት ታላላቆቹና
ታናናሾቹ ሁሉ ለእግዚኣብሄር ሰገዱ። ይህንንም ቃል ላሰማቸውና
የእግዚኣብሄርን ፈቃዱንና ግዛቱን ያደርጉ ዘንድ ይህንን ትእዛዝ
ለሰጣቸው ለእግዚኣብሄር ተገዙ። ኣመሰገኑም።
6 ደግሞም ቤተ ሰቦቹ ኣደረጋቸው። ከክፉ ሁሉ የምታድናቸው
የእግዚኣብሄር ማደሪያ ፅዮን በመካከላቸው ስላለች የምድራቸውን
ፍሬ ትባርካለች። እንስሳዎቻቸውን ታበዛለች። የወንዞቻቸውን
ምንጮች ትባርካለች። ስራዎቻቸውንና የኣትክልቶቻቸውን ፍሬ
ትባርካለች። ልጆቻቸውን ታሳድጋለች። ሽማግሌዎቻቸውን ትጠብቃለች።
በኣደሩበት ሁሉ ፊትና ሁዋላ ትሆንላቸዋለች። በሄዱበት ሁሉ
ጠላቶቻቸውን ሁሉ ያሸንፋሉ። የኢትዮጵያም ሰዎች ሁሉ ተደሰቱ።"
7 ንግስቲቱም ልጇዋን "ልጄ ሆይ! እግዚኣብሄር ቅን ነገርን ሰጠህ።
ሂድበት። ወደ ቀኝም ወደ ግራም ኣትበል። ኣምላክህን ውደድ።
ለየዋሆች መሃሪ ነውና። መንገዱም ከትእዛዙ ይታወቃልና። ከነገሩ
መሃሪነትም ቸርነቱ ይታወቃል" ኣለችው።
8 ወደ ኤልምያስና ኣዛርያስ ወደ እስራኤል ሃያላንም ሁሉ ተመለሰ
ችና ኣለቻቸው። "እናንተም ጠብቁት። የእግዚኣብሄርንም መንግስት፣
መንገዱንና የእመቤታችንን የፅዮንን ኣከባበሯን ኣስተምሩት።
ስራዋንም ያሳመርን እንደሆነ፣ እንዳትቆጣ እግዚኣብሄርም ከእኛ ጋር
ያድር ዘንድ፣ ለዘላለሙ ለልጅ ልጅ በጥንቃቄ እናደርገው ዘንድ
የምትወደውን ሁሉ ንገሩን። ኣንተም ልጄ ሆይ! የኣባቶችህን ቃል
ስማ። በምክራቸውም ሂድ። መጠጥና ዝሙት፣ በልብስ መመካት
ቢሆን፣ ፈረስ መጫንም ቢሆን፣ የጦር መሳሪያም ቢሆን፣ የፊቱም
ቢሆን የሁዋላው ኣያስክርህ።
9 ነገር ግን ጠላትህን ታሸንፍ፣ በምድርም ላይ ዘርህ ይበዛ ዘንድ፣
የቅርብና የሩቅ ጠላትህን ታሸንፍና በምድርም ላይ ዘርህ ይበዛ
ዘንድ፣ የቅርብና የሩቅ ጠላቶችህና የሚጠሉህ ይገዙልህ ዘንድ
እምነትህ በእግዚኣብሄርና በፈጣሪህ በእግዚኣብሄር ታቦተ ህግ
በፅዮንም ይሁን" ኣለችው።
10 እነዚያም ወታደሮች በኣንድ ቃል ኣሏት። "እመቤታችን ሆይ! እኛ
ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነን። ኣሁንም የተፃፈውን ለጌታችን ለንጉሱ
እናሳስበዋለን። የእስራኤል ኣምላክ ረዳት እየሆነው የእናቱን ነገር
ይሰማል። መልካሙን መንገድ እንነግረዋለን። በዚህ ዘመን ኣንዳች
ከሆነው ከጌታችን ንጉሱ በቀር ጥበበኛ የለምና።
11 የክብር እቃ የተጫነውን ግመል በማትበጠስ በቀጭን ፈትልና
በኣፍንጫው ቀለበት እንዲሰቡት፣ እንዲሁም ኣንች ከእመቤታችንና

www.ethiopianorthodox.org

12 ወይእዜኒ ኢትትሀየዩነ ወኢትረስዩነ ከመ ነግድ ለባዕድ አላ ረስዩነ
ከመ አግብርቲክሙ እለ የሐፅቡ እገሪክሙ። እስመ ንሕነሰ እመኒ
ሞትነ ወእመኒ ሐየውነ ምስሌክሙ ወአልብነ ተስፋ ውስተ ብሔረ
ሙላድነ ዘእንበለ ኀቤክሙ ወእግዝእትነ ጽዮን ቅድስት ሰማያዊት
ማኀደረ ስብሐቲሁ ለእግዚአብሔር።

## ፳ወ፱ ኀበ ነገረቶሙ ንግሥት ለደቂቀ እስራኤል

1 ወአውሥአት ንግሥት ወትቤሎሙ። አኮ ከመ አግብርት ዘትብሉ አላ
ንሬስየክሙ ከመ አብ ወከመ መምህር። እስመ አንትሙ ዐቃብያነ
ሕጉ ለእግዚአብሔር፣ ወመራሕያነ ትእዛዙ ለአምላከ እስራኤል፣ ወሰ
ብአ ቤቱ ለእግዚአብሔር፣ ወዐቃብያኒሃ ለጽዮን ታቦተ ሕጉ
ለእግዚአብሔር።
2 ወአልቦ ዘንትዐደው እምትእዛዝክሙ። እስመ አንትሙ ትከውኑነ
መርሐ በኀበ ፍኖተ እግዚአብሔር። እምኵሉ እኩይ ንትገሐሥ
በቃልክሙ እምዘኢይሠምር እግዚአብሔር ወንቅረብ ኀበ ኵሉ ሠናይ
ዘሠምረ እግዚአብሔር በትእዛዝ ዚኣክሙ።
3 ወባሕቱ አይድዑ ለዝንቱ ኵሉ ሕዝብ ወመሀርዎሙ ቃላተ አእምሮ
እስመ አልቦ አመ ሰምዑ ዘእንበለ ዮም ዘከመዝ። ወባሕቱ ጥበብሰ
ወአእምሮ ታበርህ ከመ ብርሃነ ፀሐይ ለእለ ቦሙ አእምሮ።
4 ወአንሰ እስከ ይእዜሂ ኢረወይክዎ ለማየ አእምሮ። እስመ ይጥዕም
እምነ መዐር፣ ወያረዊ እምነ ወይን፣ ወያጸግብ ወያጕሥዕ ጥበበ፣
ያስየዝዝ ልቡና፣ ወያልሕስ ከመ ዘሰክረ፣ ወያለደልድ ከመ ዘጕየ፣
ወየሐፋ ከመ ዘጸረ ክቡደ በፍኖተ ዐቀብ በብሔረ ሐሩር ወላህበ
ፀሐይ።
5 ሰበ ተከሥተ አልባቢሆሙ ወጠቢባን ለትንቢት ወለምህር። ኢይፈርህዎ
ለንጉሥ በእንተ ዕበየ ክብሩ ለእመ ተግሕሠ እምፍኖተ እግዚአብሔር።
6 ነዋኬዝ ዘተነግረ ቃለ ሕግ ዘበአማን አእምሮ ለእለ ይፈቅድዎ ወይሰ
ትይዎ ወይረውይዎ።
7 አንሰ እጼሊ እግዚአ አምላከ እስራኤል ቅዱሰ ቅዱሳን። ሀበኒ ከመ
እትልዋ ለጥበብ ወኢይትገደፍ። ሀበኒ ከመ እጠቀም ባቲ
ወኢይንኀል። ሀበኒ ከመ እሣረር ባቲ ወኢያንቀልቅል። ሀበኒ ከመ
አትዐመድ ባቲ ወኢይጸነን። ሀበኒ ከመ እስግድ ባቲ ወኢይትቀላዕ
ሀበኒ ከመ እትሐነጽ ባቲ ወኢይንሐጽ ባቲ።ሀበኒ ከመ እትወርዘው
ባቲ ወኢይድከም። ሀበኒ ከመ እቁም ባቲ ወኢይደቅ፣ ሀበኒ ከመ
እትመርጕዝ ባቲ ወኢይተንትን፣ ሀበኒ ከመ እሠአን ባቲ ወኢይድኀፅ፣

- 98 -

የአምላካችን የእግዚአብሄር· ታቦተ ህግ ከሆነችው ከቅድስቷና
ሰማያዊቷ ፅዮን ጋር እንደባሮችህ ወደዚህ ሳብሽን።
12 እነሆ አሁንም ቸል አትበሉን። እግሮቻችሁን እንደሚያጥቡ
ባሪያዎቻችሁ አድርጉን እንጂ እንደ እንግዳና እንደ ባእድም
አታድርጉን። እኛ ብንሞት ከእናንተ ጋር እንጂ በትውልድ
አገራችን ተስፋ የለንም። ከእናንተና የእግዚአብሄር ማደሪያ
ከሆነችው ከቅድስቲቷና ሰማያዊቷ ፅዮን በቀር ተስፋ የለንም።"

## ፳፱ ንግስቲቱ ለእስራኤል ልጆች እንደነገረቻቸው

1 ንግስቲቱም መልሳ አለቻቸው። "እንደ አባትና እንደ መምህር
እናደርጋችሁዋለን እንጅ እናንተ እንደምትሉት እንደ ባሪያዎች
አይደለም። እናንተ የእግዚአብሄር ህግ ጠባቂዎችና የእስራኤል
አምላክ ትእዛዝ መሪዎች ናችሁ። የእግዚአብሄር ቤተ ሰቦችና
የእግዚአብሄር ታቦተ ህግ የፅዮን ጠባቂዎች ናችሁ።
2 ከትእዛዛችሁ የምንተላለፈው የለም። እናንተም በእግዚአብሄር
መንገድ ትሆናላችሁ። በቃላችሁ እግዚአብሄር ከማይወደው ከክፉ
እንታገሳለን። በናንተ ትእዛዝ እግዚአብሄር ወደ ሚወደው ወደ
መልካም ነገር ሁሉ እንቀርባለን።
3 ነገር ግን ለዚህ ህዝብ ሁሉ ንገሩ። የእውቀትንም ነገር
አስተምሩአቸው። ከዛሬ በቀር የሰሙት የለምና። ጥበብና እውቀትም
አእምሮ ባላቸው ዘንድ እንደ ፀሃይ ብርሃን ታበራለች።
4 እኔ እስከ ዛሬ ድረስ የእውቀትን ውሃ አልጠገብኳትም። ከማር
ይጣፍጣል፤ ከወይንም የበለጠ ያረካል፤ ያጠግባልም፤ ጥበብንም
ያናግራል። ልብንም ያፈዛል። እንደ ሰካራምም ያደርጋል። እንደ
ኮበለለም ያቅበዘብዛል። በሞቃት አገር በፀሃይ ሃሩር በአቀበት
መንገድ ከባድ ሸክምን እንደ ተሸከመ ያስልባል።
5 የጥበበኞች ልብ ለትንቢትና ለማስተማር በተገለፀ ጊዜ
ከእግዚአብሄር መንገድ ፈቀቅ ካለ ንጉሱን በክብሩ ታላቅነት
አይፈሩትም።
6 በእውቀት ለሚሹት፣ ለሚጠብቁትና ለሚረኩበት አሁን የተነገረው
በእውነት የእግዚአብሄር ቃል ነው።
7 አቤቱ የቅዱሳን ቅዱስ፣ የእስራኤል አምላክ ሆይ፣ ጥበብን
እንድከተላት ታድለን ዘንድ እፀልያለሁ። እታነፅባት ዘንድ እንጂ
እንዳልፈርስባት አድለኝ። እሸንፍባት ዘንድ እንጂ እንዳልሸነፍባት
አድለኝ። እሰወርባት ዘንድ እንጂ እንዳልናድባት አድለኝ።
እጎለምስባት ዘንድ እንጂ እንዳልደክምባት አድለኝ።
እቆምባት ዘንድ እንጂ እንዳልወድቅባት አድለኝ። እመረኮዝባት
ዘንድ እንጂ እንዳልፍገመገምባት አድለኝ። እጫመትባት ዘንድ
እንጂ እንዳልንሸራተትባት አድለኝ። እንሳፈፍባት ዘንድ እንጂ
እንዳልሰጥምባት አድለኝ። እፀናባት ዘንድ እንጂ እንዳልነቀልባት
አድለኝ። እሰራባት ዘንድ አድለኝ። በውበቷ እኖር ዘንድ አድለኝ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ሀበኒ ከመ እትኣኅዝ ባቲ ወኢይሰጠም፣ ሀበኒ ከመ እጽናዕ ባቲ
ወኢይሠረው፣ ሀበኒ ከመ እንበር ባቲ በስንእሃ፣ እጽገብ በማዕዳ፣
ወኢይሜጽራ እሰትያ ወኢይረውያ እጸግባ ወኢይተፍኣ።
8 ሰከርኩ ባቲ ወኢተንተንኩ። ተንተንኩ በእንቲሃ ወኢወደቁ። ወደቁ
በእንቲኣሃ ወኢተሀኰልኩ ባቲ። ተሰጠምኩ በእንቲሃ ውስተ ዐቢይ
ባሕር። ወአኀዝኩ ባሕርየ በውስተ ልኀተ መዓምቅቲሃ። በዘባቲ
እብዕል ወረድኩ ከመ ዐቢይ መልሕቀ ኀፂን በዘይበይታ አሕማር
ውስተ ዕመቀ ባሕር። ወነሣእኩ ማኅቶተ እንተ ታበርህ ሊተ።
ወዐረጉ በአሕባለ ራግናቲሃ ለልቡና። ኖምኩ ውስተ መዓምቅቲሃ
ለባሕር። ወዘእንበለ እትኣዘዝ በማይ ሐለምኩ ባቲ እንዘ ኮከብ
ውስተ ሕፅንየ።
9 ወአንከርኩ ባቲ በእጊዞታ። ወአጽናዕክዋ ምስለ ፀዳለ ፀሐይ።
አኀዝክዋ ወኢየኀድጋ እስከ ለዓለም። ቦእኩ ውስተ አናቅጸ
መዛግብቲሃ ለጥበብ ወሐብኩ ሊተ ማየ አእምሮ።
10 ቦእኩ ውስተ ዋዕየ ነበልባለ ፀሐይ። ወአብርሀተኒ በፀዳላ።
ወተወልተውኩ ባቲ። ወድኅንኩ በተወክሎታ። አኮ ሊተ ባሕቲትየ።
አላ ለኲሎሙ እለ ሖሩ በአሠራ ለጥበብ። አኮ ሊተ ለባሕቲትየ አላ
ለኲሎሙ ሰብአ ሀገርየ መንግሥተ ኢትዮጵያ። ወአኮ ሎሙ
ለባሕቲቶሙ። አላ ለእለ የሐውሩ በፍኖቶሙ አሕዛብ እለ
ዐውዶሙ።
11 እስመ እግዚአብሔር ወሀበነ ዘርዐ በጽዮን ወማኅደረ በኢየሩሳሌም።
ወዓዲ ኮነ ክፍለ ምስለ እለ ኀረየ ዘርዐ ያዕቆብ። እስመ ረሰያ
ለማኅደሩ ትኅድር ምስሌነ።
12 እሙንቱሰ እምይእዜ ተዐቅጹ። ወንሕነሰ እምይእዜ ረታዕነ። እሙንቱ
እምይእዜ ኀሰሩ ወተመነኑ። ወንሕነሰ እምይእዜ ከበርነ። ወተፈቀርነ። እስከ
ለዓለመ ዓለም ወለትውልደ ትውልድ ዘይመጽእ።
13 ወአንትሙኒ መኳንንት ስምዑኒ ወጠይቅዋ ለመክሥተ አፉየ ወቃልየ።
አፍቅርዋ ለርትዕ። ወጽልእዋ ለሐሰት። ርትዕሰ ጽድቅ። ወሐሰትሰ ርእሰ
ዓመፃ። ወኢትትዐመፁ በበይናቲክሙ። እስመ እግዚአብሔር የኀድር
ምስሌክሙ። ወማኅደረ ሰብሐቲሁ ማእከሌክሙ። እስመ ሰብአ ቤቱ
ኮንክሙ።
14 ወኀድጉ እምይእዜ ዘትካት ልማደክሙ፣ ተጠይሮ፣ ወአማዕዎ ሰገለ ወሥራየ
ወቀስመ ወሐረሰ።
15 ወለእመቦ ዘተረክበ እምዮም በውስተ ዘትካት ልማድ ይትበርበር ቤቱ።
ወይትኴነን ምስለ ብእሲቱ ወውሉዱ ወንዋዩ።
16 ወትቤሎ ለአዛርያስ በል ንግር ዘከመ ታፈቅር እግዝእትነ ምስለ ንጉሣ ሰ
ማያዊ።

## ፺ ኀበ ወደሳ አዛርያስ ለንግሥት ወለሀገራ

1 ወተንሥአ አዛርያስ ወይቤላ ለንግሥት እእግዝእትነ በአማን አልቦ ዘይትማሰ
ለኪ በጥበብ ወበአእምሮ ወተውህበ ለኪ እምኀበ እግዚአብሔር ዘእንበለ
እግዚእየ ንጉሥ ዘአብጽሐነ ውስተ ዛቲ ምድር ምስለ እግዝእትነ ጽዮን
ቅድስት ሰማያዊት ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር።



በማእዷ እጠገብ ዘንድ አድለኝ። እጠጣላታሁ፤ ነገር ግን
አልረካም፤ አልተፋትምም።
8 ሰከርኩባት፤ ግን አልተፍገመገምኩም። ስለ እሷ ተፍገመገምኩ። ግን
አልወደቅሁም። በእሷ ምክንያት ወደቅሁ። ግን አልጠፋሁባትም።
በእሷ ምክንያት በከባድ ባህር ውስጥ ሰጠምኩ። ግን በባህርም
ጥልቅ ውስጥ የምከብርበትን እንቁ አገኘሁ። መርከቦች
የሚቀዝፉበት በጥልቅ ባህር ውስጥ እንዳሉ መርከቦች ቅልቅ
የብረት መልህቅ ወረድኩ። በባህሩም ጥልቅ ውስጥ ተኛሁ።
በውሃም ሳልጠፋ ኮከብ በጭኔ እንዳለ አለምኩ።
9 በመያዟም አደነቅሁዋት። በፀሃይ ብርሃንም አጠናሁዋት። ያዝኳት፤
ለዘላለሙም አልተዋትም። በጥበብ መዛግብት በሮች ገባሁ።
የእውቀት ውሃንም ቀዳሁ።
10 በፀሃይ ሙቀት ውስጥ ገባሁ። በብርሃኑ አበራችልኝ። አጌጥኩባት።
በእሷም በመታመን ዳንኩ። በጥበብ ዱካ ከሄዱ ሁሉ ጋር እንጂ
እኔም ብቻ አይደለሁም። በኢትዮጵያ መንግስት ላሉት ለአገሬ
ለኢትዮጵያ ሰዎች ጭምር እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም።
በአካባቢያቸው ባሉት በእነሱ መንገድ የሚሄዱ ከአህዛብ ሁሉ ጋር
እንጂ እነሱም ብቻ አይደሉም።
11 እግዚአብሄር በፅዮን ዘርን በኢየሩሳሌምም ማደሪያን ሰጥቶናልና።
ደግሞም ከመረጣቸው ከያእቆብ ዘር ጋር ክፍል ሆንን
ማደሪያውንም ከእኛ ጋር ታድር ዘንድ አድርጓልና።
12 እነሱ ተሰነካከሉ። እኛ ግን ከዛሬ ጀምሮ ቀጥ አልን። እነሱ
ተዋረዱ። እኛ ግን ከዛሬ ጀምሮ ከበርን። ለዘላለሙና ለሚመጣው
ለልጅ ልጅም ተወደድን።
13 እናንተም መኳንንት ሆይ ስሙኝ። የአፌንና የቃሌን መከፈት
ተረዱት። ቅንነትን ውደዷት። ሃሰትን ጥሏት። ቅንነት እውነት
ናት። ሃሰት ግን የበደል ሁሉ ርእስ ናት። እርስ በእርሳችሁ
አትበዳደሉ። እግዚአብሄር ከእናንተ ጋር ያድራልና፤ የምስጋናውም
ቤት በመካከላችሁ ናትና ቤተ ሰቦቹ ሁናችሁዋል።
14 ከዛሬ ጀምሮ የቀደመውን ልምዳችሁን ተውት። ማሟረትን፣ አምልኮ
ባእድን፣ ጥንቆላን፣ ስራይን ሟርትንና አስማተኝነትን ተው።
15 ከዛሬ ጀምሮ በቀደመው ልማዱ የተገኘ ቢኖር ቤቱ ይበርበር።
ከሚስቱ፣ ከልጆቹና ከሃብቱ ጋር ይፈረድበት።"
16 አዛርያስንም "እመቤታችን ከሰማያዊው ንጉሷ ጋር የምትወደውን
በል፤ ተናገር።" አለችው።

## ፺ አዛርያስ ንግስቲቱንና አገሯን እንደ አመሰገናት

1 አዛርያስም ተነስቶ ንግስቲቱን አላት። "እመቤታችን ሆይ! ከእመቤታችን
ማለትም ቅድስትና ሰማያዊት ከሆነችው ከእግዚአብሄር ታቦተ ህግ ከፅዮን
ጋር እዚሁ ከመጣው ከጌታችን ከንጉሱ በቀር ከእግዚአብሄር ዘንድ በተሰ
ጠሽ ጥበብና እውቀት በእውነት የሚመስልሽ የለም።

www.ethiopianorthodox.org

2 ንሕነሰ ወአበዊነ ቀደምት ንቤ አልቦ ዘኀረየ እግዚአብሔር ዘእንበለ
ቤተ ያዕቆብ። ኪያነ ኀረየ ወኪያነ አብዝኀ። ወኪያነ ሠምረ።
ወእንገሠነ ወረሰየነ ሰብአ ቤቱ ወመማክርቲሁ ለስብሐቲሁ ወለታቦተ
ኪዳኑ።
3 ወሀገርኒ ንብል አልቦ ዘኀረየ ዘእንበለ ሀገርነ። ወይእዜሰ ርኢነ እንተ
ትኄይስ ሀገረ ኢትዮጵያ እምብሔረ ይሁዳ። ወእምከመ በጻሕነ
ውስተ ብሔርክሙ ሠናያነ ኵሎ ዘርኢነ። ማይክሙኒ ሠናይ። ወትሁቡ
ዘእንበለ ሤጥ። ወነፋስ ዘእንበለ መረዋሕት ወጸቃውዕ ከመ ጽንጕነ
መርኀብ ወእንስሳ ከመ ኆፃ ባሕር።
4 ወእምዘርኢነ አልቦ ሕሡመ ወአልቦ ፀዋገ እምዘንሰምዕ፣
ወእምዘንከይድ፣ ወእምዘንገሥሥ፣ ወእምዘንጥዕም በአፉነ። ወባሕቱ
እምእንተ ንኄጽር አሐቲ ሀለወት። ኮንክሙ ጸሊማነ በገጽ። ወዘንተ
ዘእቤ በዘርኢኩ። ወባሕቱ ለእመ አብርሀ እግዚአብሔር አልባቢክሙ
አልቦ ዘይነክየክሙ።
5 ወባሕቱ ተገሐሡ እማውታ፣ ወደም ወብትክ ወዝሙት[81] ወእምኵሉ
ዘይጸልእ እግዚአብሔር። ከመ ንትፈሣሕ ብክሙ ሶበ ንሬእየክሙ
እንዘ ትፈርሁ እግዚአብሔር ወእንዘ ትርዕዱ እምቃሉ በከመ አዘዞሙ
እግዚአብሔር ለአበዊነ። ወይቤሎ ለሙሴ አዝዞሙ በኵሉ ወንግሮሙ
ከመ ይዕቀቡ ሕግየ ወሥርዐትየ። ወኢትትገሐሡ ኢለየማን ወኢለፀጋም
እምዘ ንኤዝዘክሙ ዮም።
6 ወይእዜኒ ከመ ታምልክዎ ለእግዚአብሔር ቅዱስ እስራኤል ወትግበሩ
ሥምረቶ እስመ መነኖሙ ለሕዝብነ በከመ ተነበዩ ነቢያቲነ። ወኀረየ
ኪያክሙ አኮኑ ለኵልክሙ እግዚአብሔር ፈጣሪክሙ። ምንት ይሠአኖ
ለእግዚአብሔር ለእመ አፍቀረ ኪያነ ወጸልአ ኪያሆሙ። እስመ ኵሉ
ሎቱ ወኵሉ ተገባሩ።ወአልቦ ዘይሰእኖ ለእግዚአብሔር አምላከ
እስራኤል።
7 ወስምዑ እንግርክሙ ትእዛዘ። አሐዱ ኢይትኀየል ካልኦ። ወኢትሂዱ
ንዋየ ቢጽክሙ። ወኢትትሐመዩ ወኢትትዓመፁ ወኢትትላኰዩ።
8 ወለእመቦ ዘአተወ እንስሳ ምስለ ንዋይክሙ እምንዋየ ቢጽክሙ
ኢትትዐወርዎ አላ አግብኡ ሎቱ። ወለእመሰ ኢያእመርክሙ በዐለ
ንዋይ አጽንዑ ሎቱ ወእምከመ ረከቦ አግብኡ ሎቱ ንዋዮ።
9 ወእመቦ ዘወድቀ ንዋየ ቢጽክሙ ውስተ ግብ፣ አው ውስተ ዓዘቅት፣
አው ውስተ ቀላይ፣ አው ውስተ ጸድፍ፣ ኢትትዐደው ወኢትትኀለፉ
እስከ ትነግርዎ ወታስተላዕልዎ።
10 ወእመኒቦ ዘከረየ ዐዘቅተ ወዘሐነጸ ማኅፈደ ኢይኅድግ ዘእንበለ
መከድን ወተድባብ።
11 ወለእመኒቦ ዘጸረ ጾረ ክቡደ፣ አው ለእመኒ ቦ ዘፀዐነ ዘወድቆ
ኢትኅልፉ ዘእንበለ ታስተላዕልዎ ወታቅልሉ ሎቱ እስመ እኁክሙ
ውእቱ።
12 ወኢታብስሉ እጕልተ በሐሊበ እሙ።

[1]ሐዋ. ሥ.15፡27

- 100 -

2 እኛና የቀደሙት አባቶቻችን ግን እግዚአብሄር ከያእቆብ ቤት
በቀር የመረጠው የለም። እኛን መረጠ። እኛን አበዛ። እኛንም
ወደደ። አነገሰን። ለክብሩና ለቃል ኪዳኑ ታቦት ቤተ ሰቦቹና
አማካሪዎቹ አደረገን እንል ነበር።
3 ስለ አገርም ከአገራችን በቀር የመረጠው የለም እንል ነበር። እነሆ
ዛሬ ከይሁዳ አገር የተሻለች የኢትዮጵያን አገር አየን። ወደ
አገራችሁ ከደረስን በሁዋላ ያየነው ሁሉ አስደሰተን። ውሃችሁ ጥሩ
ነው። ያለ ዋጋም ትሰጣላችሁ። ነፋሱ ያለ ማራገቢያ ነው። የግጦሽ
ወለላ እንደ ሜዳ ጭቃ፣ እንስሳቱም እንደ ባህር አሸዋ ናቸው።
4 ካየነው ሁሉ መጥፎ ነገር የለም። ከምንሰማው፣ ከምንረግጠውና
ከምናስሰው በአፋችንም ከምንቀምሰው ሁሉ ከፉና መጥፎ ነገር
የለም። ነገር ግን አንዲት የምናያት ነገር አለች። በመልክ ጥቁሮች
ናችሁ። ይህንንም የምለው ባየሁት ነው። ነገር ግን እግዚአብሄር
ልቡናችሁን ካበራ የሚጎዳችሁ የለም።
5 ሆኖም ከሞተ፣ ከደም፣ ከታነቀ፣ ከዝሙትና[81] እግዚአብሄር
ከሚጠላው ሁሉ ተወገዱ። እግዚአብሄርን ስትፈሩ አባቶቻችንን
እንዳዘዘው ለእግዚአብሄርም በቃሉ ስትንቀጠቀጡ ስናያችሁ ደስ
እንዲለን ነው። ሙሴን 'በሁሉ ነገር ህጌንና ስርአቴን ይጠብቁ
ዘንድ እዘዛቸው' አለው። ዛሬ ከምናዝዛችሁም ወደቀኝም ወደግራም
አትበሉ።
6 እነሆ አሁንም የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሄርን ታመልኩ ዘንድና
ፈቃዱን ታደርጉ ዘንድ ነቢያቶቻችን እንደ ተናገሩት ህዝቦቻችንን
ንቆ እናንተንም መርጧልና። የሁላችሁስ ፈጣሪ እግዚአብሄር
አይደለምን? እግዚአብሄር እኛን ቢወድና እነሱን ቢጠላ
ለእግዚአብሄር ምን ይሳነዋል? ሁሉም የእሱ ስራ ነውና ለእስራኤል
አምላክ ለእግዚአብሄር የሚሳነው የለም።
7 እነግራችሁ ዘንድ ስሙኝ። የአንዱን ትእዛዝ ሌላው እንቢ አይበል።
የባልንጀሮቻችሁን ገንዘብ አትቀሙ። አትተማሙ። አትበድሉ። እንዱ
ሌላውን አያንጓጠው።
8 ከሃብታችሁ ጋር ከባልንጀሮቻችሁ የገባ ሃብት ቢኖር እንስሳም
ቢሆን መልሱለት እንጂ ቸል አትበሉ። ባለቤቱንም ካላወቃችሁት
መርምሩት። ከተገኘ ሃብቱን መልሱለት።
9 በጉድጓድ ወይም በአዘቅት፣ ወይም በባህር፣ ወይም በዋሻ፣ የወደቀ
የባልንጀሮቻችሁ ንብረት ቢኖር አትዝለሉት። አትለፉት።
ሳታናግሩትና ሳታገኙት አትለፉ።
10 አዘቅትን ቆፍሮ ቤትን የሰራ ቢኖር ያለ ክዳንና ያለጣራ አይተወው።
11 ከባድ ሸክምን የተሸከመ ወይም የጫነው የወደቀበት ቢኖር
ሳታናሳውና ሳታቀልለት አትለፈው። ውንድማችሁ ነውና።
12 ጥጃውን በእናቱ ወተት አትቀቅሉት።

[81] የሃዋ.ስ.15፡27

www.ethiopianorthodox.org

13 ወኢትግምጹ ፍትሐ ምስኪን ወእጓለ ማውታ ወኢታድልዉ ለገጽ
ወኢትንሥኡ ሕልያነ ለገሚጸ ፍትሕ ወለስምዐ ሐሰት።
14 ወሶበ ትረክቡ ዖፈ በውስተ ምድርክሙ ምስለ እፍኅርቲሃ ታሐይው
ኪያሃ። ወኢትንሥኡ ደቂቃ ከመ ይኑኅ መዋዕሊክሙ በዲበ ምድር።
ወይትባረኩ ዘርዕክሙ ለነዋኅ መዋዕል።
15 ወሶበ ተአጽዱ ማእረረ እክልክሙ ኢትጠናቀቁ አጺደ። ወዘወድቀሂ
ኢትእርዩ። ወዘረሳዕክሙ ከላስስተ ኀድጉ። ተመይጠክሙ ኢትንሥኡ።
አላ ኀድጉ ለግዩረ ሀገርክሙ ከመ ይባርክ እግዚአብሔር ፍሬ
ምድርክሙ።
16 ወኢትግበሩ ርኩሰ። ወኢትፍትሑ በአድልዎ። ወኢትግበሩ ዐመፃ
በኩሉ ዘትትናገሩ ከመ ትትባረኩ፤ ወከመ ይብዛኅ ፍሬ ምድርክሙ፤
ወከመ ትድኅኑ እምመርገመ ሕግ ዘአዘዘ እግዚአብሔር ከመ
ይርግምዎ ለገባሬ እኪት።
17 ወጸሐፈ እንዘ ይብል፤
18 ዘያስሕቶ ፍኖቶ ለዕውር ርጉም ውእቱ።
19 ወዘይነግሮ ሕሡመ ለጽሙም ርጉም ውእቱ።
20 ወዘአርከኩሰ ምስካበ አቡሁ ርጉም ውእቱ።
21 ወዘይዘብጥ ቢጸ በጕሕሉት ርጉም ውእቱ።
22 ወዘይገምጽ ፍትሐ ግዩር ከመ ይቅትል ደመ ንጹሐ ርጉም ውእቱ።
23 ዘያስተአኪ አባሁ ወእሞ ርጉም ውእቱ።
24 ወኵሉ ዘይገብር ግልፎ ወስብኮ ዘርኩስ ግብረ እደ ሰብእ
ወይሠይሞ ወየኀብእ ውስተ ቤቱ ወይሰግድ ሎቱ ከመ አምላክ
ኢአሚኖ ከመ እግዚአብሔር ፈጣሬ ሰማያት ወምድር ዘገብሮ ለአዳም
በዘዚአሁ አርአያ ወእምሳል ወሤሞ ላዕለ ኵሉ ዘፈጠረ። ወኵልነ
ተግባሩ ንሕነ። ዘንተ ዘኢየአምን ርጉመ ለይኩን። አሜን።
25 ወዘይሰክብ ምስለ እንስሳ ርጉመ ለይኩን።
26 ወዘይሰክብ ምስለ ተባዕት ከመ ዘምስለ አንስት ርጉመ ለይኩን።
27 ዘይቀትል ነፍሰ ደመ ንጹሐ በዐመፃ ወበጕሕሉት ርጉመ ለይኩን።
28 ወእምኵሉሰ ኢታምልኩ ባዕደ አማልክተ እስመ ቀናኢ እግዚአብሔር
ለእለ ይትኤወርዎ ወይገብሩ ከመዝ ወያቀውም ገጸ ላዕሌሆሙ እስከ
ይሤርዎሙ እምድር ሕይወቶሙ። ወያጠፍእ ዝክሮሙ እስከ ለዓለም።
29 ብፁዓን እለ ይሰምዑ ቃለ እግዚአብሔር ወይገብሩ ወየዐቅቡ።
ወብፁዓን እለ ይትገሐሡ እምእለ ይገብር እኩየ ከመ ኢትርከቦሙ
እምእንተ ትመጽእ መቅሠፍት ለኀጥኣን።
30 ወለእመሰ ኮንከ ዘተዐቀብ ቃለ እግዚአብሔር ተገሐሥ እምፍኖተ ኀጥኣን
ከመ ኢትዘበጥ በእንተ ዘተዘብጡ በበትር። በከመ ይቤ ዳዊት አበ አቡሁ
ለእግዚእነ ዳዊት እስመ ኢየኀድግ እግዚአብሔር በትረ ኀጥኣን ዲበ
መክፈልተ ጻድቃን። ከመ ኢያንሥኡ እደዊሆሙ ጻድቃን በዐመፃ።
31 ለእመ ተክህሉ ለብእሲ ይግበር ሠናየ ለሊሁኒ ይዕቀብ። ወለቢጹኒ ይንግር
ከመ ይኩን በዐለ ፪ መካልይ ወይትዌሰኮ ፪ መካልይ።[82]

[82] ማቴ.25፥22

13 የድሃውንና የሙት ልጁን ፍርድ አትገምድሉ። ለሰው ፊት
አታድሉ። ፍርድን ለመገምደልና ለሃሰት ምስክርነት መማለጃ አትቀበሉ።
14 በምድራችሁ ውስጥ ወፍን ከጫጩቶቿ ጋር በምታገኙበት ጊዜ
እሷን ታድኗታላችሁ። ልጆቿንም አትውሰዱም። ዘመናችሁ በምድር
ላይ ይረዝም ዘንድና ዘሮቻችሁም በምድር ላይ ለረጅም ዘመን
ይባረኩ ዘንድ።
15 የእህላችሁን አዝመራ በምታጭዱበት ጊዜ አጣርታችሁ አትጨዱ።
የወደቀውንም አትልቀሙ። የረሳችሁትንም ነዶ ተው። እግዚአብሄር
የምድራችሁን ፍሬ ይባርክ ዘንድ። ለሃገራችሁ መፃተኛ ተው እንጂ
ተመልሳችሁ አታንሱ።
16 ትባረኩና የምድራችሁ ፍሬ ይበዛ ዘንድ፤ እግዚአብሄርም ክፉ ሰ
ሪውን ይረግሙት ዘንድ ካዘዘው የህግ መርገም ትድኑ ዘንድ ርኩስ
ነገርን አታድርጉ። በአድልዎ አትፍረዱ። በምትናገሩት ሁሉ በደልን
አታድርጉ። እንዲህ ሲልም ፃፈ።
17 እውሩን መንገድ የሚያስተው የተረገመ ነው።
18 ለደንቆሮው ክፉ ነገር የሚነግረው የተረገመ ነው።
19 የአባቱን መኝታ ያረከሰ የተረገመ ነው።
20 ወንድሙን በሸንገላ የሚመታ የተረገመ ነው።
21 ንፁህ ደም ያፈስ ዘንድ የመፃተኛውን ፍርድ የሚያጣምም የተረገመ ነው።
22 አባቱንና እናቱን የሚያክፋፋ የተረገመ ነው።
23 ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ እግዚአብሄር በፈጠረው ሁሉና በእኛም
ላይ እንደሾመው የእጁም ስራ እንደሆነ አምኖ የረከሰውንና
የሰው እጅ ስራ የሆነውን ምስልንና ጣኦትን የሚያደርግ
የሚያከብረውና በቤቱ ውስጥ ሸሽጎ እንድ አምላክ የሚሰግድለት
ርጉም ይሁን፤ አሜን።
24 ከእንስሳ ጋር የሚተኛ ርጉም ይሁን።
25 እንደ ሴት ከወንድ ጋር የሚተኛ ርጉም ይሁን።
26 ነፍስ የሚገድል ርጉም ይሁን።
27 በበደልና በሸንገላ የንፅሁን ነፍስ የሚገድል ርጉም ይሁን።
28 ይልቁንም ባእድ አማልክትን አታምልክ። እግዚአብሄርን
በሚፈታተኑት ላይ ቀናተኛ አምላክ ነውና። እንደዚህ በሚያደርጉት
ላይ ከምድር ህይወታቸውን እስከ ሚነቅላቸውና መታሰቢያቸውንም
ለዘላለም እስከ ሚያጠፋቸው ድረስ እግዚአብሄር በሚፈታተኑት
ቀናተኛ ነውና።
29 የእግዚአብሄርን ቃል የሚሰሙ፤ የሚያደርጉና የሚጠብቁ ብፁአንና
ክቡራን ናቸው። ለሃጥአን የመጣች መቅሰፍት እንዳታገኛቸው ክፉ
ከሚሰሩ ሰዎች የሚርቁ ብፁአን ናቸው።
30 የእግዚአብሄርን ቃል የምትጠብቅ ከሆንክ ከሃጥአን መንገድ ራቅ።
31 መልካም ነገርን ማድረግ የሚቻለው ሰው ለራሱ ይጠብቅ። ለጓደኛ
ውም ይንገር።ባለ ሁለት ዋጋ[82] ይሆን ዘንድ። ዋጋው በእግዚአብሄር

[82] ማቴ.25፥22

www.ethiopianorthodox.org

ወይከውን ትርብዕተ አስቡ በኀበ እግዚአብሔር። እስመ ገብረ ለሊሁ
ወመሐረ ለቢጹ። ወበእንተዝ ይፈደፍድ አስቡ።
32 ወካዕበ ብፁዓን ትከውኑ ለእመ ወሀብክሙ ንዋየክሙ ዘእንበለ ርደ
ወልቃሕ።

## ፺ወ፩ በእንተ ዘይትበልዕ ወዘኢይትበልዕ ንጹሕ ወርኩስ[83]

1 ወዝንቱ ዘትበልዑ ንጹሕ ወዘኢኮነ ንጹሐ፣ ላህም፣ በግዕ ወጠሊ፣
ሐርጌ ሀየል፣ ወይጠል፣ ቶራ፣ ድስከን፣ ወውዕላ፣ ዓርጋ፣ ወዝራት፣
ወኵሉ እንስሳ ዘንፉቅ ሰኰናሁ ወጽፈሪሁ ብልዑ። ወዘይትመሰኳዕ
ብልዑ።
2 ወዝንቱሰ ዘኢትበልዑ እምዉስተ ዘይትመሰኳዕ ዘንፉቅ ሰኰናሁ
ገመል ወዳሲጳዳ፣ ወካርገልዮን፣ እስመ ይትመሰኰዑ ወኢኮነ ንፉቀ
ጽፈሪሆሙ። ወዝእብ ወሐራውያ ኢትብልዑ። እስመ ንፉቅ
ሰኰናሆሙ ወኢይትመሰኰዑ ርኩሳን።
3 ኢትብልዑ በውስተ ማይ ዘቦ ክንፈ ወቅሥረ ብልዑ ወእምኔሁ
ርኩሰ ኢትብልዑ። ወእምነ ውስተ አዕዋፍ ኩሉ ዘንጹሕ ብልዑ።
ወዘኢትበልዑ ዝንቱ ንስር ጊጳ፣ ኤልያጣን፣ ግሪጳ፣ ሆባይ
ኢብን፣ ቀጣራቃጤን፣ ጉዛ፣ ሂጳጳ፣ ጉን፣ ወአባ፣ ጉባሕ፣
ወከራድዮን፣ ጳርፍርዮና፣ ድግነት። ዝንቱ ዘርኩስ ወዘኢትበልዑ
ደጎብያ ወዘአምሳሉ። አቃጠን ወዘአምሳሉ። አፍዮማክን ወዘአምሳሉ።
አንበጣ ወዘአምሳሉ። እምነ ዘይሰርር በበ፪ ወበበ፬ ወበበ፮ እግሩ።
ውእቱ ርኩስ ሥጋሆሙ ኢትብልዑ። ወበድኖሙ ኢትግሥሡ።
ወዘገሠሠ በድኖሙ እስከ ሠርክ ርኩስ ውእቱ።
4 ዘንተኬ ነገርናክሙ ከመ ትዕቀቡ ወትግበሩ ፍርሀተ እግዚአብሔርከመ
ትትባረኩ በዛቲ ምድርክሙ እንተ ወሀበክሙ እግዚአብሔር በእንተ
ጽዮን ሰማያዊት ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር እስመ ተኀረይክሙ
በእንቲኣሃ።
5 ወአበዊነሰ ተመነኑ በእንተ ዘነሥኦሙ እግዚአብሔር ለጽዮን ታቦተ
ሕጉ ለእግዚአብሔር ትዕቀብክሙ ለክሙ ወለዘርዕክሙ እስከ
ለዓለም። ወይባርክ ፍሬ ምድርክሙ ወያብዝኀ እንስሳክሙ ወይዕቀብ
ደቂቀክሙ በኵሉ ዘትትመኀፀኑ።
6 ወአንቲኒ እግዝእትየ ጥበብኪ ሠናይ ዘተዐደወ እምጥበበ ሰብእ።
ዘከማኪ አልቦ ዘይትማሰላ ለሕሊናኪ። አኮ ምክረ አንስት ባሕቱ
ዘተፈጥረ እስከ ይእዜ አላ እምክረ ተባዕትኒ ፈድፋደ አእምሮ
ልብኪ። ወአልቦ ዘይትማሰለኪ በብዝኀ አእምሮትኪ ዘእንበለ ሰሎሞን
እግዚእየ። ወእምሰሎሞንኒ ተዐደወ ጥበብኪ እስከ ትስሕቢ ደቂቀ
ኀይለ እስራኤል ወታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር በአሕባለ አእምሮ
ትኪ።

ዘዳግ.14፥3-21፥ ዘሌ.11፥1-47

- 102 -

ዘንድ እጥፍ ድርብ ይሆናል። ለራሱ አድርጓልና። ለባለንጀራውም
አስተምርዋልና። ስለዚህ ዋጋው ይበዛል።
32 ደግሞም ገንዘባችሁን ያለ አራጣና ያለብድር ብትሰጡ ንኡዳን
ክቡራን ትሆናላችሁ።"

## ፺፩ ስለ ሚበሉትና ስለማይበሉት[83]

1 "ንፁህ የሆነውና የምትበሉት ይህ ነው። ላም፣ በግ፣ ፍየል፣ የበግና
የፍየል ወጠጤ፣ ፌቆ፣ ዋልያ፣ ጎሽ፣ ሚዳቋ፣ የሜዳ ፍየል፣
ብሆር፣ ጅራተ ቀጭን የሆነውንና ሸኮናውና ጥፍሩ የተሰነጠቀውን
ብሉ። የሚያመሰኳውን ብሉ።
2 ከሚያመሰኳውና ሸኮናው ከተከፈለው የማትበሉት ግመል፣ ጥንቸልና
አሳማ ናቸው። ያመሰኳሉ። ነገር ግን ሸኮናቸው የተከፈለ
አይደለም። እንዲሁም ጅብና እሪያ አትብሉ። ሸኮናቸው የተከፈለ
ነው። ነገር ግን አያመሰኩምና አትብሉ። ርኩሳን ናቸው። በውሃ
ውስጥ ካለው ክንፍና ቅርፊት ያለውን ብሉ። ከእነሱ ውስጥ ግን
ርኩስ የሆነውን አትብሉ። ከወፍ ውስጥ ንፁህ የሆነውን ሁሉ
ብሉ። የማትበሉት ንስር፣ አገዳ ሰበር አሞራ፣ እባብ ዋጭ አሞራ፣
ዘማች አሞራ፣ እንጭት (ግልገል አንሳ) እንቆራ፣ ቁራ፣ ሰጎን፣
አራት እራስ አሞራ፣ ይብራ፣ አፈ ያሬድ፣ እርኩም፣ የመስቀል
ወፍ፣ ድንቢጥ፣ ጥንብ አንሳ አሞራ፣ ጉጉት፣ እርኩም፣ አፍ ፀአዳ፣
ሳቢሳና የሌሊት ወፍ ናቸው። እነዚህ የረከሱና የማትበሏቸው ናቸው።
3 እንደዚሁም ፌንጣና የመሳሰለውን፣ ኩብኩባና የመሳሰለውን፣ አሸንና
የመሳሰለውን፣ አንበጣና የመሳሰለውን ሁሉ አትብሉ። ከሚበረው
ሁለት ሁለት፣ አራት አራትና ስድስት ስድስት እግር የሆነው ሁሉ
ርኩስ ነው። ስጋቸውን አትብሉ። በድናቸውን አትዳሱ።
በድናቸውን የዳሰሰ እስከ ሰርክ ድረስ ርኩስ ነው።
4 እግዚአብሄር የእግዚአብሄር ታቦተ ህግ ስለ ሆነችው ስለ ሰማያዊቷ
ፅዮን፣ በሰጣችሁ በዚህች ምድራችሁ ትባረኩ ዘንድና ትእዛዙንም
ትጠብቁት ዘንድ፣ ፈሪሃ እግዚአብሄርንም ታደርጉ ዘንድ ይህንን
ነገርሁዋችሁ። ስለ እሷ ተመርጣችሁዋልና።
5 እናንተንና ዘራችሁን ለዘላለም ትጠብቃችሁና የምድራችሁን ፍሬ
ትባርክ ዘንድ፣ ልጆቻችሁን በምትለምኑት ሁሉ ይጠብቅ ዘንድ
እግዚአብሄር የእግዚአብሄርን ታቦተ ህግ ፅዮንን ስለ ወሰደባቸው
አባቶቻችን ተናቁ።
6 እመቤቴ ሆይ! አንች ግን ጥበብሽ ከሰው ሁሉ ጥበብ የላቀ
ነው። ሃሳብሽን የሚመስላት የለም። ምክርሽ የሴት ምክር
አይደለም። እስከዛሬ እንዳለው እንደ ሴቶች ምክር አይደለም።
ከወንዶችም ምክር ይልቅ አብዝቶ በለጠ። በእውቀትሽም ብዛት
ከጌታዬ ከንጉሱ ከሰሎሞን በቀር የሚመስልሽ የለም። ጥበብሽም

83 ዘዳግ.14፥3-21 ፥ዘሌ.11፥1-47

www.ethiopianorthodox.org

7 ወነሠትኪ ቤተ ጣዖቶሙ። ወደምሰስኪ አምሳሊሆሙ። ወአንጻሕኪ
ርኩሰ እምሕዝብኪ። እስመ አሰሰልኪ ዘጸልአ እግዚአብሔር
እምላዕሌሆሙ። ወለስምኪኒ እግዚአብሔር አስተዳለዋ ዘሰመየኪ ማክዳ
ወትርጓሜሁ አኮ ከመዝ ብሂል።
8 ነጸርኪ በውስተ ሕዝብኪ ዘኢይሠምሮ እግዚአብሔር። ወትቤሊ አኮ
ከመዝ ሠናይ አላ ይረትዕ ንስግድ ለእግዚአብሔር። አኮ ከመዝ
ሠናይ ሰጊድ ለፀሐይ አላ ሰጊድ ለእግዚአብሔር ይረትዕ ትቤሊ።
አኮ ከመዝ ሠናይ ሐቲተ ማሪት አላ ተወክሎ በእግዚአብሔር
ይኄይስ ትቤሊ። አኮ ከመዝ ሠናይ አስተቃስሞ ሰገል አላ እስምኮ
በቅዱሰ እስራኤል ይኄይስ ትበሊ አኮ ከመዝ ሠናይ ሠዊዕ
ለአእባን ወለአዕዋም አላ ሠዊዕ ለእግዚአብሔር ይረትዕ ትቤሊ። አኮ
ከመዝ ሠናይ ተጠይሮ በአዕዋፍ አላ ተአምኖ በፈጣሪ ይረትዕ
ትበሊ።
9 ወእምዝ ኀረይኪያ ለጥበብ። ወኮነተኪ እመ። ኀሠሥኪያ ወኮነተኪ
መዝገበ። ተጸወንኪያ ወኮነተኪ ጥቅመ። ጸሀቂያ ወአፍቀረተኪ።
እምኵሉ ተወከልኪያ ወሐቀፈተኪ ከመ ሕፃና። አፍቀርኪያ ወኮነተኪ
በከመ ፈቀድኪ። አኀዝኪያ ወኢተኀድገኪ እስከ ዕለተ ሞትኪ። አንቲ
ኀዘንኪ በእንቲአሃ ወአስተፍሥሐተኪ እስከ ለዓለም። ጻመውኪ
በእንቲአሃ ወአጥዐየተኪ እስከ ለዓለም። ርኅብኪ በእንቲአሃ
ወአጽገበተኪ እስከ ለዓለም። ጸማእኪ ለጥበብ ወአርወየተኪ እስከ
ለዓለም። ተመንደብኪ በእንቲአሃ ለጥበብ ወኮነተኪ ፈውሰ እስከ
ለዓለም። ጸመምኪ በእንቲአሃ ለጥበብ ወአስምዐተኪ እስከ ለዓለም።
ያርኪ በእንቲአሃ ለጥበብ ወአብርሀተኪ ፈድፋደ እምነ ፀሐይ እስከ
ለዓለም።
10 ወዝንቱ ኵሉ ዘኮነ እምኀበ እግዚአብሔር በእንተ ዘአፍቀርኪያ
ለጥበብ። እስመ ጥበብ ወአእምሮ ወልቡና እምኀበ እግዚአብሔር
ውእቱ። ልቡና ወአእምሮ ወቀዳሚ ጥበብሰ ፈሪሀ እግዚአብሔር፣
ወአእምሮ፣ ወመኪረ ሠናይኒ፣ ምጽዋት፣ ወምሕረት እስከ ለዓለም
እንተ ትጌሊ ዘንተ ኵሎ ረከብኪ እግዝእትየ ኀበ አምላከ
እስራኤል ቅዱሰ ቅዱሳን ማእምረ አልባብ ዘየሐትት ዘውስተ ልበ
ሰብእ ዘእምኀቤሁ ኵሉ ኮነ።
11 ወዝኒ ኮነ በፈቃደ እግዚአብሔር ኮነ ከመ ትምጻእ ጽዮን ውስተ
ዛቲ ብሔረ ኢትዮጵያ ወከመ ትኩኖ መርሐ ለንጉሥነ ዳዊት
መፍቀሬ እግዚአብሔር ቀዳሚሃ ለደብተራሁ መጋቢሃ ለማኅደረ
ስብሐቲሁ።

## ፯ወ፪ ኀበ ሐደሱ መንግሥቶ ለዳዊት

1 ወይቤ አዛርያስ አምጽኡ ኢዮቤል ወንሑር ኀበ ጽዮን ወበህየ
ነሐድስ መንግሥቶ ለእግዚእነ ዳዊት።



የእስራኤልን ሃያላን ልጆችንና የእግዚአብሄርን ታቦተ ህግ
በእውቀትሽ ሃብል እስክትሰቢ ድረስ ከሰሎሞን ጥበብ ይልቅ በዛ።
7 የጣኦቶቻቸውን ቤት አፈረስሽ። ምሳያቸውንም አጠፋሽ።
ከህዝብሽም ርኩሰትን አጠፋሽ። እግዚአብሄር የጠላውን ከላያቸው
ላይ አጠፋሽ። ከአህዛብም ርኩሰትን አጠፋሽ። ስምሽንም
እግዚአብሄር ማክዳ ብሎ አዘጋጀው። ትርጓሜውም እንደዚህ
አይደለም ማለት ነው።
8 በህዝብሽ ውስጥ እግዚአብሄር የማይወደውን አየሽ። እንደዚህ
መልካም አይደለም። ለእግዚአብሄር መስገድ እንጂ ለፀሃይ መስገድ
መልካም አይደለም አልሽ። በእግዚአብሄር ማመን እንጂ ሟርትን
መመርመር መልካም አይደለም አልሽ። ለእግዚአብሄር መሰዋት
እንጂ ለድንጋይና ለዛፎች መሰዋት መልካም አይደለም አልሽ።
በፈጣሪ መታመን ይሻላል እንጂ በወፎች ማሟረት መልካም
አይደለም አልሽ።
9 ከዚህ ሁዋላ ጥበብን መረጥሻት። እናትም ሆነችሽ። ተጠጋሻት።
ቤትም ሆነችሽ። ተጨነቅሽላት። ከሁሉም ወደደችሽ። ታመንሽባት
እንደ ልጅም አቀፈችሽ። ወደድሻት። እንደ ወደደሽውም
ሆነችልሽ። ያዝሻት። እስከ እለተ ሞትሽም አትተውሽም። አንቺ
ስለ እሷ አዘንሽ። እሷም አንችን ለዘላለሙ አስደሰተችሽ። ስለ
እሷ ደከምሽ። ለዘላለሙ አዳነችሽ። ስለ እሷ ተራብሽ። እሷም
አንችን ለዘላለሙ አጠገበችሽ። ጥበብን ተጠማሻት። እሷም አንችን
ለዘላለሙ ከጥምሽ አረካችሽ። በጥበብ ምክንያት ተጨነቅሽ።
ለዘላለሙ መድሃኒት ሆነችልሽ። በእሷ ማለትም በጥበብ ደነቆርሽ።
ለዘላለሙም እንድትሰሚ አደረገችሽ። በእሷ ምክንያት ታወርሽ።
ከፀሃይም ይልቅ ፊፅሞ ለዘላለሙ አበራችሽ።
10 ይህ ሁሉ የሆነው ከእግዚአብሄር ዘንድ ነው። ጥበብን ስለ
ወደድሻት። ጥበብ፣ አእምሮና ማስተዋል ከእግዚአብሄር ዘንድ
ነውና። እመቤቴ ሆይ ልቡና፣ አእምሮ፣ የጥበብ መጀመሪያ የሆነው
እግዚአብሄርን መፍራት፣ እውቀትና መልካም ምክር፣ ለዘላለሙ
የምትኖር ምፅዋት፣ ምህረትና የምታስቢውን ይህን ሁሉ የቅዱሳን
ቅዱስ የልብን የሚያውቅና በሰው ልብ ውስጥ ያለውን
የሚመረምር ሁሉ ከእሱ ከሆነ ከእስራኤል አምላክ ዘንድ አገኘሽ።
ይህም ሁሉ በእግዚአብሄር ፈቃድ ሆነ።
11 ፅዮንም ወደ ዚህች ወደ ሃገረ ኢትዮጵያ ትመጣ ዘንድና
የእግዚአብሄር ወዳጅ፣ የካህናቷ ቋሚና የምስጋና ቤት ሹም ለሆነው
ለንጉሳችን ለዳዊት መሪ ትሆነው ዘንድ ይህ ሁሉ በእግዚአብሄር
ፈቃድ ሆነ።"

## ፯፪ የዳዊትን መንግስት እንደ አደሱት

1 አዛርያስም "ኢዮቤልን አምጡ። ወደ ፅዮንም እንሂድ።
የጌታችንንም የዳዊትን መንግስት እናድስ" አለ።

www.ethiopianorthodox.org

2 ወነሥአ ቅብዐ መንግሥትኒ ምሉዐ ቀርን ወቀብእዎ ዕፍረተ
ዘውእቱ ቅብዐ መንግሥት።
3 ወነፍሑ ቀርነ፣ ወብዕንዛ፣ ወከበሮ፣ ወመሰንቆ፣ ወእንዚራ፣ ወኵሎ
ተውኔተ ወማኀሌተ ዘምስለ ፈረስ ወልታ ወቀስት።
4 ወኵሉ ተባዕት ወአንስት ሰብአ ብሔረ ኢትዮጵያ ንኡሶሙ
ወዐቢዮሙ ወንኡሳን ጸሊማን በበ፰፻ ወአዋልድ ደናግል እለ ኀረየ
አዛርያስ ለአዋልደ ጽዮን ዘበሕግ እለ ይከይድ ንጉሥ ዳዊት ሶበ
የዐርግ ውስተ ቄፋዝ ለምሳሕ ወለድራር በውስተ ታዕካ መንግሥት።
5 ወከመዝ ተሐደሰ መንግሥቱ ለዳዊት ወልደ ሰሎሞን ንጉሠ
እስራኤል በሀገረ ምስፍና በደብረ ማክዳ በቤተ ጽዮን ኀበ ተገብረ
ቀዳሚ ሕግ ለንጉሠ ኢትዮጵያ።
6 ወእምዝ ሶበ ተፈጸመ ዘተገብረ ሕግ ወበከመ ርእዩ በኢየሩሳሌም
ገብሩ በቤተ ጽዮን ሕገ ለኀሩያነ መንግሥት ወለእለ ውስጥ ወለእለ
አፍአ። ወለሕዝብ ወለአላዳስ ወለአህጉር ወለበሐውርት ወለኵሉ
ሕዘቢሆሙ ወአንጋዲሆሙ ከመዝ ሠርዑ።
7 ወከመዝ ሞፃእተ ሀገረ መንግሥቱ ለንጉሠ ኢትዮጵያ ሠረቃዊ ጥንተ
ሀገረ ጋዛ በምድረ ይሁዳ ዘውእቱ ኢየሩሳሌም ወሞፃእቱ ባሕረ
ኢያሪኮ። ወትትኀለፍ በሐይቀ ባሕሩ እስከ ሊባ ወሳባ። ወትወርድ
ሞፃእቱ እስከ ቢሲስ ወአስኔት። ወሞጻእቱ ብሔረ ጸሊማን ወዕሩቃን
ወተዐርግ ደብረ ኬቤሬንዮን ውስተ ባሕረ ጽልመት። ዝውእቱ
ምዕራበ ፀሐይ ወተዐዱ ሞጻእቱ እስከ ፌኔኤል ወለሲፋላ ወሞፃእቱ
አግዋረ ገነት። ወሥመረ እክል ወብዝኀተ እንስሳ ወፌኒቂኒሃ።
ወሞጻእቱ እስከ ዛውል ወትኀለፍ ባሕረ ህንድ። ወሞጻእቱ እስከ
ባሕረ ተርሴስ ወበቅሥፊቱ ብሔረ ምድያም እስከ ይበጽሕ ብሔረ
ጋዛ። ወሞጻእቱ ኀበ ቀዳሚ ተወጥነ። ወከመዝ ሢመቱ ለንጉሠ
ኢትዮጵያ ሎቱ ወለዘርዑ እስከ ለዓለም።

## ፺ወ፫ በእንተ ዘአማሰኑ ሃይማኖተ ሮም

1 ወእምድኅረ ነበሩ ፫ አውራኀ እስመ መጽአት ውስተ ብሔረ
ኢትዮጵያ አመ ሠርቀ ቀዳሚ ወርኀ በነገረ ዕብራውያን ወበጽርዕ
ታርሞን ወበግእዝ ሚያዝያ አመ ፮ ወጸሐፍዎን ለእሉ ሕግ
ወአስማት። ወአንበርዎን ለተዝካር ለደኃሪ መዋዕል በዘይትገበር ሕግ
ለደብተራ ወበዘይትዐወቅ ክብረ ነገሥተ ኢትዮጵያ ወክብረ ነገሥተ
ሮምያ እስመ አኀው እሙንቱ።
2 ወበአሚነ ክርስቶስኒ ቀዳሚሰ ርቱዐ አምነ በስብከተ ሐዋርያት እስከ
ቆስጠንጢኖስ ወእሌኒ ንግሥት ዘአውፅአት ዕፀ መስቀል። ወነበሩ ፻ወ፴
ዓመተ።
3 ወእምድኅሬሁ ተንሥአ ሰይጣን ዘእምትካት ዕድዉ ለሰብእ ወአስሐቶሙ ለሰ
ብአ ብሔረ ሮሜ። ወአሕሠምዎ ለሃይማኖተ ክርስቶስ።
4 ወእምጽኡ ኑፋቄ ላዕለ ቤተ ክርስቲያን ዘእግዚአብሔር በአፈ ንስጥሮ
ስ ወአርዮስ ወይባስ እለ ወደየ ውስተ ልቦሙ ዘወደየ ቅንዐተ

2 በቀንዱ የመላውንም ቅብአ መንግስት ወሰደ። የመንግስት ቅባት
የሆነውንም ሽቶ ቀቡት። ከፈረስ፣ ከጋሻና ከቀስት ጋር የሆነውን
ጨዋታውንና ዘፈኑን ሁሉ ተጫወተ።
3 ነጋሪትና እንቢልታ፣ ከበሮና መሰንቆ፣ እንዚራም ተመታ።
4 የኢትዮጵያ ሰዎችም ትልቁና ትንሹ፣ ሴትና ወንዱ፣ ታናናሾችና
ታላላቆቹ፣ ትንሾቹ ሻንቅሎች ሁሉ፣ ስድስት ስድስት ሺህ እየሆኑ
ጭዋታን ተጫወቱ። ንጉስ ዳዊት በቤተ መንግስቱ ውስጥ ለምሳና ለራት
ወደ ኣዳራሹ ሲገባ የሚያሸበሽቡና በሕጉ መሠረት አዛርያስ ለፅዮን
ልጆች ይሆኑ ዘንድ የመረጣቸው ወጣት ልጃገረዶች ሁሉ ይጫወቱ
ነበር።
5 ለኢትዮጵያ ንጉስ የመጀመሪያው ሕግ በተሠራባት በፅዮን ቤት፣ የሹመት
ኣገሩ በሆነው በማክዳ ደብር፣ የእስራኤል ንጉስ የሰሎሞን ልጅ የዳዊት
መንግስት እንደዚህ ታደሰች።
6 ስርዓቱም ካለቀ በሁዋላ ለመንግስቱ ባለስልጣኖች በውስጥና በውጭ
ላሉት፣ ለዜጎችና ለባእዳን፣ ለኣህጉርና ለበሃውርት፣ እንዲሁም ለሕዝባቸው
በኢየሩሳሌም እንዳዩት ኣድርገው ስርአትን ሰሩ።
7 ኣገሩ በፀሃይ መውጫ የሆነው የኢትዮጵያ መንግስት ወሰን እንዲህ ነው።
ጥንት ኣገሩ በይሁዳ ምድር ማለትም በኢየሩሳሌም ያለው ጋዛ ነው።
ወሰኑ የኢያሪኮ ባህር ሆኖ፣ በወንዝ ሃይቆችና እስከ ሊባና ሳባ እያለፈች
ቢሲስና ኣሰኔት ትደርሳለች። ድንበሩም የጥቁሮችና እራቁታቸውን የሚሄዱ
ሰዎች ኣገር ነው። ወደ ኬቤሬኒየን ተራራ ወጥቶ እስከ ጨለማው ባህር፣
እስከ ፀሃይ መግቢያ። እስከ ፌኒኤል እስከ ለሲፋላና እስከ ገነት
በርም ትደርሳለች። ኣዝመራዋም እህል፣ ብዙ እንስሳና ተምር ነው። ወሰ
ኗም ዛውል ነው። ህንድ ውቅያኖስም ታልፋለች። በሌላም በኩል
ከተርሴስ ባህር ጀምሮ በምድያም ኣገር በኩል እስከ ጋዛ ማለትም
ሹመቱ እስከ ተጀመረበት ኣገር ይደርሳል። የኢትዮጵያ ንጉስ፣ የእሱና
የዘሩ ሹመት ለምንጊዜውም እንዲህ ነው።

## ፺፫ የሮምን ሃይማኖት እንደ ኣጠፉ

1 ሶስት ወራት ቆይተው ወደ ሀገረ ኢትዮጵያ ከመጣች በሁዋላ፣
በእብራውያን ኣቆጣጠር በመጀመሪያው ወር መባቻ፣ በፅርእ
በታርምን፣ በግእዝ ሚያዝያ ስድስት ቀን እነዚህን ህጎችና ስሞች
ፅፈው የደብተራ ኦሪት ህግ በሚደረግበት፣ የኢትዮጵያ ነገስታትና
የሮም ነገስታት ክብር በሚታወቅበት ለሁዋለኛው ዘመን መታሰቢያ
ኣስቀመጡት። እነሱ ወንድማማቾች ናቸውና።
2 በክርስቶስ በማመን በመጀምሪያ በሃዋርያት ስብከት በትክክል
ኣመኑ። እስከ ቆስጠንጢኖስና ንግስት እሌኒ እፀ መስቀሉን እስከ
ኣወጣችበት እስከ መቶ ሰላሳ ኣመትም በኣንድነት ኖሩ።
3 ከዚያ በሁዋላ ከጥንት የሰው ልጅ ጠላት የሆነው ሰይጣን ተነሳ።
የሮሜን ሰዎችንም ኣሳታቸው። የክርስቶስን ሃይማኖትንም ኣረከሷት።
4 በእግዚኣብሄር ቤተ ክርስቲያንም ላይ ወንድሙን ኣቤልን ይገድል
ዘንድ በቃየል ልብ ቅናትን ያስገባ ሰይጣን በልባቸው ቅናትን

www.ethiopianorthodox.org

ውስተ ልቡ ለቃየን ከመ ይቅትል እኍሁ አቤልሃ። ወከማሁ ወደየ
ውስተ ልቦሙ አቡሆሙ ዲያብሎስ ፀራ ለጽድቅ ወጸላኤ ሠናያት
5 በከመ ይቤ ዳዊት
ወነበቡ ዐመፃ ውስተ አርያም።
ወአንበሩ ውስተ ሰማይ አፉሆሙ።
ወአንሶሰወ ውስተ ምድር ልሳኖሙ።[84]
6 ዘለሊሆሙ ኢያእመሩ እምኀበ መጽኡ፣ ወኢያእመሩ ኀበ የሐውሩ።
ለፈጣሪሆሙ በልሳኖሙ ይውሕኩ። ወይጸርፉ ላዕለ ስብሐቲሁ።
7 እንዘ አምላክ ውእቱ ቃለ እግዚአብሔር ወረደ እመንበረ መለኮቱ።
ወለብሰ ሥጋ አዳም ወእግዚአብሔር ውእቱ ቃል።
8 ወበይእቲ ሥጋ ተሰቅለ ከመ ይቤዝዎ ለአዳም በዕልወቱ። ወዐርገ
ውስተ ሰማይ ወነበረ ዲበ መንበረ መለኮቱ በይእቲ ሥጋ እንተ
ነሥአ።
ወካዕበ ይመጽእ በስብሐት። ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ።
ወይፈድዮ ለኩሉ በከመ ምግባሩ። ለዓለመ ዓለም አሜን።
9 ወንሕነሰ ነአምን ከመዝ። ወንገኒ ለቅድስት ሥላሴ። ወእለሰ
ኢየአምኑ ከመዝ ውጉዛን እሙንቱ በቃለ እግዚአብሔር ንጉሠ ሰ
ማያት ወምድር በዝ ዓለም ወበዘይመጽእ ዓለም።
10 ወንሕነሰ ጸናዕነ በርትዕት ሃይማኖት እንተ አበው ሐዋርያት።
ወአወፈዩነ ሃይማኖተ እንተ ቤተ ክርስቲያን። ወከማሁ ትነብር
ኢትዮጵያ ምስለ ሃይማኖታ እስከ ምጽአተ እግዚእነ ኢየሱስ
ክርስቶስ። ዘሎቱ ስብሐት ለዓለመ ዓለም አሜን።

## ፯ወ፩ ቀዳሚ ጸብአ ንጉሠ ኢትዮጵያ

1 ወእምዝ ተንሥኡ ለጸብእ እምድኅረ ፫ አውራኀ እምነ ሀገረ ምስፍና
ምስለ ማክዳ እሙ፣ ወጽዮን እግዝእቱ። ወሌዋውያን ይጸውርዋ
ለታቦተ ሕግ ምስለ ንዋየ ሐቢቶሙ።
2 ወእንዘ የሐውሩ በብዙኀ ግርማ ከመ አሜሃ በደብረ ሲና አመ
ያወርዳ እግዚአብሔር እምሰማያት ለጽዮን በቅድስና ኀበ ሙሴ
ወአሮን ወከማሁ ይጸውርዋ ለታቦተ ሕግ አዛርያስ፣ ወኤልምያስ
ወባዕዳን ደቂቀ ኀይለ እስራኤል እንዘ የሐውሩ በየማና ወበፀጋማ፣
በገቦሃ፣ በፍጽማ፣ ወበከዋላሃ እንዘ ይሴብሑ ወይዜምሩ እንዘ
መሬታውያን ከመ ኀይለ ሰማያውያን። ወወሀቦሙ እግዚአብሔር ቃለ
ወዜማ መንከረ እስመ ሠምረ እግዚአብሔር ከመ ይሰባሕ ቦሙ።
3 ወበጽሑ እምሀገረ ምስፍና። ተዐየኑ በማየ አበው። ወበነገህ አጥፍእዋ
ለብሔረ ዛው/ ዋ/ ምስለ ሐድያ። እስመ ጋዝ ባ ምስሌሆሙ
እምቀዳሚ። ወእምዝ አጥፍእዎሙ ወቀተልዎሙ በአፈ ኀጺን።
4 ወኀለፉ እምህየ ወተዐየኑ ጌርሳ። ወካዕበ አጥፍኡ ሀገረ ሰባድዕት
እለ ገጸሙ ሰብእ ወዘነበ አድግ ውስተ ሐቋሆሙ።

---

[84] መዝ.73፥8-9

- 105 -

በጨመረባቸው በንስጥሮስ፣ በአርዮስና በህባስ አፍ ጥርጣሬን
አመጣ። የፅድቅና የመልካም ነገር ጠላት አባታቸው ዲያቢሎስም
በልባቸው ቅናትን ጨመረ።
5 ዳዊት፣ አመፃን በሰማይ ላይ ተናገሩ፣
አፋቸውንም በሰማይ አኖሩ፣
አንደበታቸውም በምድር ውስጥ ተመላለሰ።[84] እንዳለው
6 እራሳቸው ከወዴት እንደመጡና ወዴት እንደሚሄዱ የማያውቁ
በአንደበታቸው ፈጣሪያቸውን ያውካሉ። በክብሩም ላይ ይሳደባሉ።
7 የእግዚአብሄር ቃል አምላክ ሳለ ከመንበረ መለኮቱ ወረደ።
የአዳምንም ስጋ ለበሰ። ይህም ቃል እግዚአብሄር ነው።
8 አዳምንም ከስህተቱ ይታደገው ዘንድ በዚህች ስጋ ተሰቀለ። ወደ
ሰማይም ወጣ። በመንበረ መለኮቱም በነሳት ስጋ ተቀመጠ።
ደግሞም በህያዋውና በሙታን ይፈርድ ዘንድ በክብር ይመጣል።
ለእያንዳንዱም እንደ ስራው ይከፍለዋል። ለዘላለሙ አሜን።
9 እኛ እንደዚህ እናምናለን። ለቅድስት ስላሴም እንሰግዳለን።
እንደዚህ የማያምኑ ግን በሰማያትና በምድር ንጉስ በእግዚአብሄር
ቃል በዚህ አለምና በሚመጣው ዓለም የተወገዙ ናቸው።
10 እኛ ግን በአባቶች ሃዋርያት የቀናች ሃይማኖት ፀናን። የቤተ
ክርስቲያን ሃይማኖትንም ሰጠን። እንዲሁም ኢትዮጵያ ክብር
ይግባውና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ሚመጣበት እለት ድረስ
ከሃይማኖቷ ጋር ትኖራለች። ለዘላለሙ አሜን።

## ፺፩ የኢትዮጵያ ንጉስ የመጀመሪያው ጦርነት

1 ከሶስት ወራት በሁዋላ ከእናቱ ከማክዳና ከእመቤቱ ከፅዮን ጋር
ከምስፍንና አገራቸው ለጦርነት ተነሱ። ሌዋውያንም ታቦተ ህጓን
ከንዋየ ቅድሳቱ ጋር ይሸከሟት ነበር።
2 ሲሄዱም ያኔ እግዚአብሄር ፅዮንን በቅድስና ከሰማያት ወደ
ሙሴና ወደ አሮን ባወረዳት ጊዜ እንደ ነበረው አዛርያስ፣
ኤልምያስና ሌሎችም የእስራኤል ሃያላን ልጆች በቀኝና በግራ፣
በፊቷና በሁዋላዋ ሁነው መሬታውያን ሳሉ ፍፁም እንደ
ሰማያውያን እያመሰገኑ ይሸከሟት ነበር። እግዚአብሄርም
የሚያስደንቅ ድምፅና ዜማን ሰጥቷቸው ነበር። ሊመሰገንባቸው
ወዷልና።
3 ከሃገረ ምስፍናቸው ደረሱ። በአበው ወንዝም ሰፈሩ። ጠዋትም ዛዋ
(ዝዋይ?)ን ከሃድያ ጋር አጠፏት። ከመጀመሪያው ከእነሱ ጋር ጠብ
ነበራትና። ከዚህ በሁዋላ በጦር መሳሪያ አጠፏት። ገደሏቸውም።
4 ከዚያም አለፉ። ጌርሴምም ሰፈሩ። ፊታቸው የሰው፣ ሁዋላቸው
የአህያ ጅራት የነበረባቸውን የእፉኝትንም አገር አጠፉ።

---

[84] መዝ.73፥8-9

www.ethiopianorthodox.org

5 ወገብኡ ወተዐየኑ ውስተ ሀገረ ጽዮን። ወነበሩ ባቲ እስከ ፫
አውራኀ። ወእንሥኡ ሰረገላቲሆሙ ወበጽሑ ሀገረ ምስፍና። ወእምህየ
በአሐቲ ዕለት በጽሑ ሀገረ ሳባ ወአጥፍእዋ ለኖባ።
6 ወእምህየ ተዐየኑ ሳባ ወአጥፍኡ እስከ ደወለ ግብጽ። ወኮነ ግርማ
ዐቢይ ለንጉሠ ኢትዮጵያ እስከ ያመጽኡ አምኃ ንጉሠ ምድያም
ወንጉሠ ግብጽ።
7 ወበጽሑ ውስተ ሀገረ ምስፍና። ወእምህየ ተዐየኑ አብአት። ወጸብኡ
ውስተ ባሕረ ህንደኬ። ወአብአ ንጉሠ ህንደኬ፣ አምኃ፣ወጋዳ። ወሰ
ገደ ለሊሁ ለንጉሠ ኢትዮጵያ።
8 ወኀበ ኵሉ ዘፈቀደ ወጸብአ አልቦ ዘይመውእ ዘእንበለ ዘይመውእ
ለሊሁ።
9 ወእለ ያስተሐይጽዎ በውስተ ትዕይንቱ ከመ ይስምዑ ዜና ወይነግሩ
ለሀገሮሙ። ወኢይክሉ ረዊጸ በሰረገላ። እስመ ለሊሃ ጽዮን ታደክም
ኀይሎሙ ለፀር።
10 ወንጉሥሰ ዳዊት ምስለ ሠራዊቱ ወሠራዊተ ሠራዊቱ ወኵሎሙ እለ
ይትኤዘዙ በቃሉ ይረውጹ በሰረገላ ዘእንበለ ደዌ ወሕማም፣ ዘእንበለ
ረኀብ ወጽምእ፣ ዘእንበለ ሐፍ ወድካም ይበጽሑ በአሐቲ ዕለት
መጠነ ምሕዋረ ፫ አውራኀ።
11 ወአልቦ ወኢምንትኒ ዘየኀጥኡ እምዝ ሰአሉ በኀበ እግዚአብሔር
በውስተ ጽዮን ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር። እስመ ለሊሁ ይነብር
ምስሌሃ። ወመልአኩ ይሜግባ። ወማኅደሩ ለሊሃ።
12 ወለንጉሥ ዘይትለአክ ኀበ ደብተራሁ ለእመ ሖረ በኵሉ ፍኖቱ
ወበገቢረ ፈቃዱ ይትገበር ኵሉ ዘፈቀደ፣ ወዘኀለየ በልቡ፣ ወዘአንጸረ
በአጽባዕቱ። ኵሉ ይትገበር በቃሉ። ወኵሉ ይፈርሆ። ወውእቱሰ
አልቦ ዘይፈርህ። እስመ እደ እግዚአብሔር ምስሌሁ እንተ ተዐቅቦ
ሌሊተ ወመዐልተ። እስመ ገብረ ፈቃዶ። ወውእቱኒ ይገብር ሎቱ።
ወየዐቀቦ እምኵሉ እኩይ ለዓለመ ዓለም አሜን።
13 ዘንተ ረከብኩ እመጻሕፍት ዘቤተ ሶፍያ ዘቁስጥንጥንያ። ወይቤልዎ
እለ ህየ ሊቃነ ጳጳሳት አማንኬ ዝንቱ ዘተጽሕፈ እመዋዕለ ሰሎሞን
ንጉሥ። ወይቤ ደማትዮስ ዘእንጾኪያ እወ ይመስል እስከ ዕለተ ሞቱ
ለሰሎሞን ዘተጽሕፈ። ወእምድኅረ ሞቱስ ለሰሎሞን እምባዕዳን
ነቢያት ዘተጽሕፈ አምሳሉ።

## ፺ወ፩ ኀበ ኀብረ ክብሩ ለንጉሠ ኢትዮጵያ

1 ወበእንተሰ ክብረ ነገሥት አእመርነ ወጠየቅነ ከመ ይከብር ንጉሠ
ኢትዮጵያ፣ ንጉሠ ጽዮን ውእቱ። ወበኵርኒ ውእቱ እምዘርዐ ሴም።
ወማኅደሩሂ ውስተ ጽዮን ለእግዚአብሔር ውእቱ። ወበህየ ይሰብር
ኀይለ ኵሎሙ ፀሩ ወጸላእቱ።
2 ወእምድኅሬሁ ንጉሠ ሮም መሲሁ ለእግዚአብሔር በእንተ ዕፀ
መስቀል።

5 ተመልሰውም በፅዮን አገር ሰፈሩ። እስከ ሶስት ወርም ተቀመጡ።
ሰረገሎቻቸውንም አስነስተው ሃገረ ምስፍናቸው ደረሱ። ከዚህም
ተነስተው በአንድ ቀን ከሳባ አገር ደረሱ። ኖባንም አጠፏት።
6 ከዚህ በሁዋላ በሳባ ሰፈሩ። እስከ ግብፅ አውራጃ ያለውን ሁሉ
አጠፉ። ለኢትዮጵያም ንጉስ የምድያምና የግብፅ ንጉስ ገፀ በረከት
እስኪያመጡ ድረስ ታላቅ መፈራት ሆነ።
7 ከምስፍናቸውም አገር ደረሱ። በአብአት ሰፈሩ። በህንደኬ አገርም
ተዋጉ። የህንደኬ ንጉስም ስጦታና ግብር አገባ። እሱም ለኢትዮጵያ
ንጉስ ሰገደ።
8 በወደደውና በተዋጋበት ሁሉ ድል ከሚያደርግ በቀር እሱን ድል
የሚያደርገው አልነበረም።
9 ከከተማው ዜናውን ሰምተው የሚያቃልሉትም ለአገራቸው ይነግሩ
ዘንድ በሰረገላ ሊሮጡ አይቻላቸውም ነበር። እራሷ ፅዮን የጠላቱን
ሃይል ታደክም ነበርና።
10 ንጉስ ዳዊት ግን ከሰራዊቱና ከሰራዊቱ ሰራዊት ጋር፣ በቃሉ
ከሚታዘዙት ሁሉ ጋር በሰረገላ ያለ ደዌና ህማም፣ ያለ ራብና
ጥም፣ ያለ ላብና ድካም የሶስት ወራት መንገድ በአንድ ቀን
ይደርሳሉ።
11 በእግዚአብሄር ታቦተ ህግ በፅዮን ውስጥ ከእግዚአብሄር ዘንድ
በሚለምኑት የሚያጡት አልነበረም። እሱ ከእሷ ጋር ይኖራልና።
መላኩም ይጠብቃታል። ማደሪያው ናትና።
12 ወደ ድንኳኑ የሚላከው ንጉስ በሄደበት መንገድ ሁሉና ፈቃዱንም
በማያደርግ በኩል ያሻውና በልቡ ያሰበው፣ በጣቱም ያመለከተው
በቃሉ ይደረጋል። ሁሉ ይፈራዋል። ሌትና ቀን የምትጠብቀው
የእግዚአብሄር እጅ ከእሱ ጋር ናትና። እሱ ግን የሚፈራው
አልነበረም። ፈቃዱን አድርጓልና። እሱ ይሰራለታል። ለዘላለሙም
ከክፉ ሁሉ ይጠብቀዋል። አሜን።
13 ይህንንም ቁስጥንጥንያ ውስጥ በምትገኘው በሶፍያ ቤተ መንግስት
አገኘሁ። በዚያ ያሉ ሊቃነ ጳጳሳትም "ይህ ነገር እውነት ከንጉስ
ሰሎሞን ጀምሮ የተፃፈ ነው?" አሉት። የአንፆኪያው ድማትዮስም
"አዎን እስከ ሰሎሞን እለተ ሞት የተፃፈ ይመስላል። የቀረው
ደግሞ ከሰሎሞን ሞት በሁዋላ ከሌሎች ነቢያት ተፅፏል" አለ።

## ፺፩ የኢትዮጵያ ንጉስ ክብር እንደ ተባበረ

1 ስለ ነገስታት ክብርም የኢትዮጵያ ንጉስ ክብር ከሁሉ እንዲበልጥ
አወቅን፣ ተረዳን። እሱ የፅዮን ንጉስ ነው። የሴም ዘርና በኩርም
ነው። መኖሪያውም በእግዚአብሄር ማደሪያ በፅዮን ነው። የጠላቱንና
የተቃዋሚዎቹን ሁሉ ሃይልም በዚሁ ይሰብራል።
2 ከእሱ ቀጥሎ በእፀ መስቀሉ ምክንያት የሮም ንጉስ የእግዚአብሄር
ሹም ነው።

www.ethiopianorthodox.org

3 ወመንግሥተ እስራኤልሰ እምእመ ተወልደ/ት/ ባሕርይ እምኔሆሙ
ወእምባሕርይ ካዕበ ተወልደ ፀሐየ ጽድቅ ተሰዊሮ በሥጋ ዚኣሃ።
ወእመሰ ኢተሰወረ በሥጋ ሰብእ እመ ኢተርእየ ለአዕይንተ መዋቲ
ለቢሶ ሥጋነ ተመሰለ ኪያነ። ወአንሶሰወ ምስሌሆሙ። ወገብረ
ተአምረ ወመንክረ በማእከሌሆሙ። አንሥአ ሙታኒሆሙ። ወፈወሰ
ድውያኒሆሙ። ወአብርሀ አዕይንተ ዕውራኒሆሙ። ወከሠተ እዝነ
ጽሙማኒሆሙ። ወእለ ለምፅ አንጽሐ። ወርኁባነ አጽገበ። ወብዙኀ
ተአምረ ወመንክረ ገብረ ዘተጽሕፈ ወዘኢተጽሕፈ። በከመ ይቤ
ዮሐንስ ወንጌላዊ ወልደ ዘብደዎስ ሶበሰ ተጽሕፈ ኩሉ ዘገብረ
ኢየሱስ እመ ኢያግመሮ ዓለም ጥቀ መጻሕፍቲሁ ዘእምተጽሕፈ።[85]
4 ወዘንተ ኩሉ ሶበ ርእዩ ደቂቀ እስራኤል ዐላውያን አምሰልዎ ከመ
ሰብእ። ወቀንዎ ላዕሌሁ በዘርእዩ ወሰምዑ። ወሰቀልዎ ዲበ ዕፀ
መስቀል። ወቀተልዎ ወተንሥአ እሙታን በሣልስት ዕለት። ወዐርገ
ሰማያተ በስብሐት ዲበ መንበረ መለኮት። ወተወፈየ እምኀበ አብ
መንግሥተ ዘኢየኀልቅ። ለዓለመ ዓለም ላዕለ መንፈሳውያን
ወመሬታውያን ወላዕለ ኩሉ ፍጥረት።
ከመ ለስሙ ይግነይ ኩሉ ልሳን
ወይስግድ ኩሉ ብርክ።[86]
ወይኴንን ሕያዋነ ወሙታነ
ወይፈድዮ ለኩሉ በከመ ምግባሩ።
5 አሜሃኬ ሀለዎሙ ለአይሁድ ይርአይዎ ወይትኀፈሩ ወይትኳነኑ
በእሳት ዘለዓለም።
6 ወንሕነሰ እለ አመነ በርትዕት ሃይማኖት ዲበ መንበርነ ንሄሉ።
ወንትፌሣሕ ምስለ መምህራን ሐዋርያት ለእመ ሖርነ በፍኖተ
ክርስቶስ ወበትእዛዛቲሁ።
7 ወሶበ ሰቀሉ መድኀኔ ዓለም ኮኑ ዝርዋነ። ወመንግሥቶሙ ኮነት
ብዱተ ወኀልቀ ወተሠረዉ እስከ ለዓለመ ዓለም።
8 ወይቤሉ ኩሎሙ ማኅበረ ቅዱሳን ጥዩቀ በአማን የዐቢ ወይትሌዐል
ወይከብር ንጉሠ ኢትዮጵያ እምኩሎሙ ነገሥተ ምድር በእንተ
ክብራ ወዕበያ ለጽዮን ሰማያዊት። ወእግዚአብሔር አፍቀሮሙ ለሕዝበ
ኢትዮጵያ እስመ ዘእንበለ ያእምሩ ሕጎ ሠረዉ ጣዖቶሙ።
9 ወእለሰ ተውህቦሙ ሕገ እግዚአብሔር ገብሩ ጣዖተ። ወሰገዱ
ለአማልክት ዘይጸልእ እግዚአብሔር። ወበደኃሪ አመ ተወልደ ከመ
ይቤዝዎ ለአዳም ገብረ ተአምረ ወመንክረ በቅድሜሆሙ። ወኢአምኑ
ቦቱ ኢ በስብከቱ ወኢ በስብከተ አበዊሁ።
10 ወሕዝበ ኢትዮጵያሰ አምኑ በ፩ ረድእ መሀይምን። ወበእንተዝ
አፍቀሮሙ እግዚአብሔር ፈድፋደ ለሕዝበ ኢትዮጵያ።
11 አውሥኡ ወይቤልዎ ጳጳሳት ሠናየ ነበብከ። ወርቱዕ ቃልከ። ወጥዩቀ
ፈከርከ። ወተርጐምከ ለነ በከመ ይቤ ጳውሎስ አኮኑ ዘርዐ አብርሃም
አልዐለ ውእቱ ዘርዐ ሴም ኩሎሙ ነገሥተ ምድር እሙንቱ።

[85] ዮሐ.21፡25
[86] ፊልጵ.2፡10:ኢሳ.15፡23

- 107 -

3 የእስራኤል መንግስት ግን እንቁ ከእነሱ ከተወሰደች በሁዋላ
እውነተኛ ፀሃይ በእሷ ስጋ ተሰውሮ ከእንቁዋ ተወለደ። በሰው ስጋ
ባይሰወር ኑሮ ለመዋቲ ኣይኖች ባልታየም ነበር። ስጋችንን ለብሶ
እኛን መሰለ። ከእኛም ጋር ተመሳሰለ። በመካከላቸውም ተኣምራትና
ድንቅ ነገርን ኣደረገ። ሙቶችን ኣስነሳ። የእውራንንም ኣይኖች
ኣበራ። የደንቆሮዎችንም ጆሮ ከፈተ። ለምፃሞችን ኣነፃ። የተራቡትን
ኣጠገበ። የተፃፉና ያልተፃፉ ብዙ ታምራት ኣደረገ። የዘብደዎስ
ልጅ ወንጌላዊው ዮሃንስ እንዳለው[85] ኢየሱስ ያደረገው ተኣምራት
ቢፃፍ የተፃፉትን መፅሀፍት ዓለም ፈፅሞ ባልቻለውም ነበር።
4 የማያምኑ የእስራኤል ልጆች ይህን ሁሉ ባዩ ጊዜ መሰላቸው።
በእሱም ላይ ባዩትና በሰሙት ቀኑበት። በእንጨት መስቀልም
ሰቀሉት። በሶስተኛውም ቀን ከሙታን ተነሳ። በክብርም ወደ ሰማይ
ኣረገ። በመንበረ መለኮትም ተቀመጠ። ለዘላለሙ የማያልቅ
መንግስት በሰማያውያንና በመሬታውያን በፍጥረትም ሁሉ ላይ
ከኣብ ተሰጠው። እንደበት ሁሉ ለስሙ ይገዛ ዘንድና ጉልበትም
ሁሉ ይንበረከክ ዘንድ፣[86] ህያዋንና ሙታንንም ይገዛ ዘንድና ለሁሉም
እንደ ስራው ይከፍለው ዘንድ መንግስት ተሰጠው።
5 ያንጊዜ ኣይሁድ ያዩታል። ያፍራሉ በዘላለም እሳትም
ይፈረድባቸዋል።
6 እኛ በቀናች ሃይማኖት ያመን ግን በዙፋናችን እንኖራለን።
በክርስቶስ መንገድና በትእዛዞቹ ከሄድን ከመምህራኖቻችን ከሃዋርያት
ጋር እንደሰታለን።
7 የዓለምን መድሃኒት በሰቀሉ ጊዜ የተበተኑ ሆኑ። መንግስታቸውም
የተፈታች ሆነች። ኣለቀ። ለዘላለሙም ተነቀሉ።
8 የቅዱሳን ማህበርም ሁሉ ፈፅሞ የበለጠና የገነነ እንደሆነ በእውነት
ታወቀ፣ተረዳ ኣሉ። እግዚኣብሄርም የኢትዮጵያን ህዝቦች ወደዳቸው።
ህጉን ሳያውቁ ጣኦቶቻቸውን ነቅለዋልና።
9 የእግዚኣብሄር ህግ የተሰጣቸው ጣኦትን ኣደረጉ። እግዚኣብሄር
ለሚጠላቸው ጣኦታት ሰገዱ። በሁዋለኛው ዘመንም ኣዳምን
ያድነው ዘንድ በተወለደ ጊዜ በፊታቸው ተኣምራትንና መንክራትን
ኣደረገ። በእሱ ስብከትም በኣባቶቹ ስብከትም ቢሆን ኣላመኑበትም።
10 የኢትዮጵያ ህዝቦች ግን በኣንድ ኣማኝ ደቀ መዝሙር ኣመኑ።
ስለዚህ እግዚኣብሄር የኢትዮጵያን ህዝቦች ፈፅሞ ወደዳቸው።
11 ሊቃነ ጳጳሳትም መልሰው "መልካም ተናገርክ። ቃልህም እውነት
ነው። ኣስረድተህም ተረጎምክ" ኣሉት። "ጳውሎስ 'የኣብርሃምን ዘር
ከፍ ከፍ ኣደረገ' እንዳለው የምድር ነገስታት ሁሉ የሴም ዘርና
የእግዚኣብሄርም ምርጦች ናቸው። ስለ ሰው ልጆች ምህረት
ለክረምቶችና ለዝናሞች፣ ለኣትክልትና ለፍሬዎች፣ ለህዝቦችና ለኣገሮ
ች፣ ለነገስታትና ለመኳንንት፣ ለሰው፣ ለእንስሳትና ለአእዋፍ

[85] ዮሃ.21፡25
[86] ፊልጵ.2፡10፡ኢሳ.45፡23

www.ethiopianorthodox.org

ወኀሩያኒሁ ለእግዚአብሔር ሰብአ ኢትዮጵያ። እስመ ማኀደሩ
ለእግዚአብሔር ኮነት ህየ ጽዮን ሰማያዊት ታቦተ ሕጉ ወታቦተ
ኪዳኑ እንተ ረሰያ ለምሥሃል በእንተ ምሕረተ ውሉደ ሰብእ፣
ለክራማት ወለዝናማት ለአትክልት ወለፍሬያት ለአሕዛብ
ወለበሐውርት፣ ለነግሥት ወለመኳንንት ለሰብእ ወለእንስሳ ለአዕዋፍ
ወለአራዊት።
12 አውሥአ ወይቤሎሙ ጎርጎርዮስ ጳጳስ፣ ገባሬ መንክር በአማን
ተውህበት ለነ መድኀኒት ለኵልነ ሕዝበ ክርስቲያን ለእለ አመነ ባቲ
ለእግዝእትነ ማርያም አምሳሊሃ ለጽዮን ሰማያዊት። እስመ ኀደረ
እግዚአብሔር ውስተ ከርሠ ድንግል። ወተወልደ እምኔሃ ዘእንበለ
ሩካቤ። ወበአጽባዕተ እግዚአብሔር ተጽሕፉ ዐሠርቱ ቃላት ዘሕግ
ተገብረ ውስተ ጽዮን ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር።
13 ወይእዜኒ ሀቡ ንንግር ትንቢቶሙ ለነቢያት አበዊነ፣ ቀደምት ቅዱሳን
እምእሪተ ሙሴ ወነቢያት በእንተ ክርስቶስ መድኀኒነ ከመ ይስምዑ
ደኃሪ ትውልድ ፍካሬ ዜና ዘንዜንዎሙ በእንተ ተርጕሞ መጻሕፍት።
ነአኀዝኬ እምርእሰ መጽሐፍ። ወንለቡ በመንፈስ።
14 በከመ ይቤ ዳዊት በመንፈስ ቅዱስ ውስተ ርእሰ መጽሐፍ ተጽሕፈ
በእንቲአየ።[87] አውሥአ ወይቤ ምንት ውእቱ ርእሰ መጽሐፍ።
አውሥኡ ወይቤልዎ ዝውእቱ እሪት ዘተጽሕፈ በእንተ ክርስቶስ
ወልደ እግዚአብሔር። ወይቤ በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ
ወምድረ።[88] ወህልው እምትካት። ወምድርሰ ኢኮነት ድሉተ አላ
ድሙራን ጽልመት፣ ወነፋስ፣ ወማይ፣ ወጊሜ፣ ወመሬት ኩሎሙ
ድሙራን። ወመንፈሰ እግዚአብሔር ይጼልል መልዕልተ ማይ።[89]
15 ዘንተሰ ዘይቤ በቃለ እግዚአብሔር ተፈጥሩ ሰማያት ወምድር ወመንፈሰ
እግዚአብሔር ኀደረ ላዕለ ኵሉ ፍጥረት ብሂል።

## ፺ወ፮ በእንተ ትንቢት ዘክርስቶስ

1 ወካዕበ ሰበከ ሙሴ በእሪት ወይቤ፣ ነቢየ እነሥእ ለክሙ ዘከማየ
እምአኀዊክሙ። ወስምዕዎ ለውእቱ ነቢይ። ወኵሉ ነፍስ እንተ ኢትሰ
ምዖ ለውእቱ ነቢይ ይእቲ ነፍስ ለትሠሮ እምሕዝባ።[90]
2 ወዘንተ ይቤ በእንተ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር። ወካዕበ ተነበየ በእንተ
ስቅለቱ ወይቤ፣ ሶበ አመንደብዎሙ አክይስት ለደቂቀ እስራኤል አውየዉ
ኀበ ሙሴ። ወሙሴሂ አውየወ ኀበ እግዚአብሔር። ከመ ያድኅኖሙ
እምአርዌ ምድር። ወይቤሎ ግበር ሥዕለ ከይሲ ዘብርት። ወስቅሎ ኀበ
ይትኤመርዎ። ወኵሉ ዘነሰኮ ከይሲ ይነጽሮ ለውእቱ ሥዕለ ብርት
ወይሕየው። ወሶበ ተሀከዩ ነጽሮ ይመውቱ። ወእለሰ ነጸርዎ ወአምኑ
የሐይዉ።[91]

---

[87] መዝ.40.7
[88] ዘፍጥ.1፣1
[89] ዘፍጥ.1፣2
[90] ዘዳግ.18፣18
[91] ዘኁል.21፣7

- 108 -

ለመግለጻ ያደረጉት የህጉና የኪዳኑ ታቦት ሰማያዊቷ ፅዮን እዚህ ናትና
የኢትዮጵያ ሰዎች የእግዚአብሄር ምርጦች ናቸው። አሉት።
12 ተአምር ሰሪው ጳጳስ ጎርጎርዮስም መልሶ "በእውነት ህዝበ ክርስቲያኖች
ለሆንና በሰማያዊቷ ፅዮን ምሳሌ በሆነችው በቅድስት ድንግል ማርያም
ላመነ ሁሉ ለመዳን ተሰጠች። እግዚአብሄር በድንግል ሆድ አድሮአልና።
ያለ ግንኙነት ከእሷ ተወልዷልና። አስሩ ቃላተ ሕግም በእግዚአብሄር
ጣቶችም ተፃፉ። በእግዚአብሄር ታቦተ ህግ በፅዮንም ሆኑ" አላቸው።
13 "አሁንም የቀደሙት አባቶቻችን ቅዱሳን ነቢያት ከሙሴና ከነቢያት ኦሪት
ጀምሮ ስለ መድሃኒታችን ክርስቶስ የሁዋላ ትውልድ ይሰማ ዘንድና
መፃህፍቱንም ስለ መተርጎም የምነግራቸውን የምስራች ትርጉም እንናገር
ዘንድ ፍቀዱልን።
14 ዳዊት በመንፈስ 'በመፅሃፍ ርእስ ስለ እኔ ተፃፈ'[87] እንዳለው ከመፅሃፍ
ርእስ እንጀምር። በመንፈስ እናስተውል" አላቸው። መልሶም "የመፅሃፍ
ርእስ ማለት ምንድን ነው?" አለ። እነሱም መልሰው "ስለ እግዚአብሄር
ልጅ ስለ ክርስቶስ የተፃፈ ኦሪት ነው። '.በመጀመሪያ እግዚአብሄር ሰ
ማይንና ምድርን ፈጠረ'[88] ከጥንትም ነበሩ። ምድር ግን የተዘጋጀች
አልነበረችም። ጨለማ፣ ነፋስ፣ ውሃ፣ ጉም፣ መሬትና ሁሉም ተቀላቅለው
ነበሩ። የእግዚአብሄር መንፈስም በውሃ ላይ ይንሳፈፍ ነበር"[89] አሉት።
15 ይህንን ያለበት "በእግዚአብሄር ቃል ሰማያትና ምድር ተፈጠሩ።
የእግዚአብሄር መንፈስም በፍጥረት ሁሉ ላይ አደረ" ማለት ነው።

## ፺፮ ስለ ክርስቶስ ትንቢት

1 ሙሴ ደግሞ "ከወንድሞቻችሁ ውስጥ እንደ እኔ ያለ ነቢይ
ያስነሳላችሁዋል። ያንንም ነቢይ ስሙት። ያንን ነቢይ ያልሰማች
ነፍስ ከህዝቧ ተለይታ ትጥፋ"[90] በማለት ሰበከ። ይህንንም ስለ
እግዚአብሄር ልጅ ስለ ክርስቶስ አለ።
2 ደግሞም ስለ ስቅለቱ ትንቢት ተናገረ። የእስራኤልን ልጆች እባቦች
ባስቸገሯቸው ጊዜ ሙሴ ጮሀ። ከእባብ ያድናቸው ዘንድ ወደ
እግዚአብሄር አቤት አለ። እግዚአብሄርም "የብረት እባብ ምስል
አድርግ። በሚመለከቱበትም ቦታ ስቀለው። እባብ የነከሰው ሁሉ
ይህንን የብረት ስእል አይቶ ይዳን። መመልከቱን እንቢ ያሉ
ይሞታሉ። ያዩትና ያመኑበት ይድናሉ"[91] አለው።

---

[87] መዝ.40፣7
[88] ዘፍጥ.1፣1
[89] ዘፍጥ.1፣2
[90] ዘዳ.18፣18
[91] ዘሁ.21፣8

www.ethiopianorthodox.org

3 ወከማሁ ክርስቶስ ለእለ ተሀከዩ ወኢአምኑ ቦቱ የኀልቁ በሲኦል።
ወእለሰ አምኑ ወሰምዑ ይወርሱ ምድረ ሕይወት ዘለዓለም። ኀበ
አልቦ ደዌ ወሕማም ዘለዓለም።
4 ወዘከመሂ ተሀየይዎ ለክርስቶስ ቃለ እግዚአብሔር ንሕነ ናየድዐከሙ።
ሶበ ሐመይዎ ለሙሴ ደቂቀ እስራኤል እንዘ ይብሉ ለባሕቲቱኑ
ለሙሴ ዘተናገሮ እግዚአብሔር። ወንሕነሰ እፎ ዘኢንሰምዕ ቃለ
እግዚአብሔር ከመ ንእመን ቦቱ።
5 ወሰምዐ እግዚአብሔር ማእምረ አልባብ ሐሜቶሙ ለደቂቀ
እስራኤል። ወይቤሎ ለሙሴ ወአንተሰ በዝየ ትስእል ሥርየተ
ለሕዝብከ። ወእሙንቱሰ ሐመዩከ እንዘ ይብሉ ለነሰ እፎ
ዘኢይትናገረነ እግዚአብሔር።[92] ወይእዜኒ ለእመ አምኑኒ ይምጽኡ
ኀቤየ ምስሌከ ዝየ። ወበሎሙ ከመ ያንጽሑ ርእሶሙ ወይኅጽቡ
አልባሲሆሙ ወይዕርጉ ዐበይተ እስራኤል ከመ ይስምዑ ዘአነ
እኤዝዞሙ ወይስምዑ ቃልየ ወይግበሩ ትእዛዝየ ዘአነ አዘዝኩ።
6 ወተአዚዞ ሙሴ ነገሮሙ ለደቂቀ እስራኤል። ወሰገዱ ሕዝብ
ለእግዚአብሔር ወአንጽሑ ርእሶሙ በ፫ ዕለት። ወዐርጉ ውስተ ደብረ
ሲና ሰብዓ አእሩገ እስራኤል።[93] ወወፅኡ እምትዕይንት። ወዐርጉ
ውስተ ደብረ ሲና። እንዘ ይትረሐቁ መጠነ ምንዳፈ ሐፅ ቆሙ
በበአሐዱ በአንጻረ ቢጹ። ወእሙንቱሰ መጠነ ቦሙ ፈተኑ ምግባሮሙ
ወኢክህሉ ዐሪገ ውስተ ቆባር ምስለ ሙሴ። ወአኀዞሙ ረዐድ
ወድንጋጼ። ወደፈኖሙ ጽላሎተ ሞት። ወሰምዑ ቃለ ቀርን፣
ወእንዚራ፣ ወጽልመት፣ ወነፋስ።
7 ወቦአ ሙሴ ውስተ ቆባር። ወተናገረ ምስለ እግዚአብሔር። ወሰምዑ
ኵሎሙ ዐበይተ እስራኤል ውእተ ቃለ እግዚአብሔር። ፈርሁ
ወርዕዱ ወኢክህሉ ቀዊመ እምብዝኀ ፍርሀት ዘውስተ ልቦሙ።
8 ወሶበ ወጽአ ሙሴ ወይቤልዎ ኢንሰምዓ ለዛቲ ቃለ እግዚአብሔር
ከመ ኢንሙት በድንጋጼ። ወናሁ አእመርነ ከመ ተናገረከ
እግዚአብሔር። ወለእመቦ ዘይነግረከ አንተ ስማዕ ወንግረነ። ወኩነነ
አፈ በኀበ እግዚአብሔር ወንከውኖ ሕዝበ ዚአሁ።
9 ትሬእዩኑ ዘከመ ክህድዎ ለክርስቶስ ወይቤሉ ኢንሰምዮ ለውእቱ ቃል
ከመ ኢንሙት በድንጋጼ። ወቃልሰ ዘእግዚአብሔር ክርስቶስ ውእቱ።
ወአሜሃ ዘይቤሉ ኢንሰምዮ ለውእቱ ቃል ኢነአምኖ ለክርስቶስ
ብሂል።

[92] ዘኍል.12፡2
[93] ዘኍል.11፡16-24፡ዘጸአ.19

- 109 -

3 እንደዚሁም ክርስቶስን እንቢ ያሉና ያላመኑበትም በሲኦል
ያልቃሉ። ያመኑና የሰሙ ደዌና ህማም የሌለበትን የዘላለም
ህይወትን ይወርሳሉ።
4 የእግዚአብሄርን ቃል ክርስቶስን ችላ ያሉት ሁሉ የሆኑትን
እንነግራችሁዋለን። የእስራኤል ልጆች ሙሴን ብቻውን ነው።
"እግዚአብሄር የተናገረው እናምንበት ዘንድ የእግዚአብሄር ቃል
የምንሰማው እንዴት ነው? " ብለው ሙሴን ባሙት ጊዜ የሆነውን
እንነግራችሁዋለን።
5 ልብን የሚያውቅ እግዚአብሄር ይህንን ሃሜታቸውን ሰማ።
እግዚአብሄርም ሙሴን "አንተ እዚህ የህዝብህን ሃጢአት ስርየት
ትለምናለህ። እነሱ ግን እኛን ለምን አያናግረንም ሲሉ አሙህ"[92]
አለው። "አሁንም ካመኑ ከአንተ ጋር ወደዚህ ወደ እኔ ይምጡ።
እራሳቸውን ያነፁና ልብሳቸውን ያጥቡ ዘንድ ንገራቸው። እኔ
የማዝዛቸውንም ይሰሙ ዘንድ የእስራኤል ታላላቆች ወደ ተራራው
ይውጡ። ቃሌን ይሰሙና ያዘዝሁትን ትእዛዜን ያደርጉ ዘንድ። "
6 ሙሴም ታዝዞ ለእስራኤል ልጆች ነገራቸው። ህዝቡም
ለእግዚአብሄር ሰገዱ። ሶስት ቀንም ያህል ራሳቸውን አነፁ። ሰባ
የእስራኤል ሽማግሎች ወደ ሲና ተራራ ወጡ።[93] ከከተማም ወደ
ሲና ተራራ ሄዱ። ጦር ተወርውሮ የሚደርስበትን ያህል ርቀው
ቆሙ። እያንዳንዱ በጓደኛው ፊት ቆመ። እነሱ ግን ልክ
ነበራቸው። ምግባራቸውንም ፈተኑ። ከሙሴ ጋር ግን ወደ ጉሙ
ሊገቡ አልቻሉም። ፍርሃትና ድንጋጤ ያዛቸው። የሞት ጥላም
አጠላባቸው። የእንቢልታና የነጋሪትን፣ የነፋስና የጨለማን ድምፅ
ሰሙ።
7 ሙሴም ወደ ጭጋጉ ውስጥ ገባ። ከእግዚአብሄርም ቃል ሰሙ።
ፈሩ። ተንቀጠቀጡ። በልባቸው ውስጥ ካለው ፍርሃትም የተነሳ
መቆም አልተቻላቸውም።
8 ሙሴም በወጣ ጊዜ "በድንጋጤ እንዳንሞት ይህችን የእግዚአብሄርን
ቃል አንሰማትም። እነሆ አሁን እግዚአብሄር እንደተናገረህ
አወቅን። የሚነግርህ ካለ አንተ ስማና ትነግረናለህ።
በእግዚአብሄርም ዘንድ አፍ ሁነን። የእሱም ህዝብ እንሆናለን"
አሉት።
9 ክርስቶስን እንደካዱት አያችሁ? "በድንጋጤ እንዳንሞት ይህንን
ቃል አንሰማውም" አሉ። ይህ የእግዚአብሄር ቃል ግን ክርስቶስ
ነው። "ያኔም ይህንን ቃል አንሰማውም" ማለታቸው "ክርስቶስን
አናምነውም" ማለታቸው ነው።

[92] ዘሁ.12፡2
[93] ዘሁ.11፡16-24

www.ethiopianorthodox.org

10 ወካዕበ ሰአለ ሙሴ ኀበ እግዚአብሔር ወይቤ አርእየኒ ገጸከ።[94]
ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ እስመ አልቦ ዘይክል ርእየ ገጽየ
ወየሐዩ። ወባሕቱ ከመ መጽሔት ሚጥ ገጸከ ለምዕራብ። ወትሬእ
በውስተ ኮኵሕ መጽሔተ ገጽየ።
11 ወሶበ ርእየ ሙሴ ጽላሎተ ገጹ ለእግዚአብሔር በርሀ ገጹ ምስብዒተ
እምነ ፀሐይ እስከ ኢይክሉ ደቂቀ እስራኤል ነጽሮተ ገጹ ዘእንበለ
በግላ። ወርእየ አሜሃኒ ከመ ኢፈተዉ ይርአዩ ገጸ እግዚአብሔር አላ
ይቤልዎ ግበር ለነ ግላ ከመ ኢንርአይ ገጸከ።[95]
12 ወዘንተ ሶበ ይቤሉ ይትዐወቅ ከመ ጸልእዎ ለክርስቶስ ሰሚዐ ቃሉ
ወርእየ ገጹ።
13 ወዓዲ ሶበ አዕረገ አብርሃም ለይስሐቅ ወልዱ ውስተ ደብረ ቀርሜሎስ
አውረደ እምሰማያት ቤዛ ይስሐቅ በግዐ። ወይስሐቅሰ ኢተጠብሐ አላ
ተጠብሐ በግዕ ዘወረደ እምሰማያት። እስመ አብርሃም ይተረጎም
በእግዚአብሔር አብ። ወይስሐቅኒ ይተረጎም አምሳሊሁ ለክርስቶስ ወልድ።
ወአመ ይወርድ እምሰማያት ለመድኀኒተ አዳም ወደቂቁ ኢተጥብሐ
መለኮት ዘወረደ እምሰማያት አላ ተጠብሐት ሥጋሁ እንተ ለብሰ
በእንቲአነ። ይእቲ ምድራዊት እንተ ለብሰ እማርያም ትሌብዉኑ ወትጤይቁ
ዘንተ አርአያ ወአምሳል ለምድራዊ ይስሐቅ ወልደ አብርሃም ዘኮነ
መሥዋዕቱ ለፈቃደ አቡሁ ኮነ ሎቱ ቤዛሁ በግዕ ሰማያዊ ወተቤዘወ ወልደ
አብርሃም።
14 ወለዘሰ ወረደ ወልደ እግዚአብሔር ኮነ ቤዛሁ ለመለኮት ሥጋሁ
ለምድራዊ።[96] ወሞተ በሥጋሁ እንዘ ኢየሐምም መለኮቱ። ወተውላጠ ኮነ።
መዋቲት ኮነት ሕይወተ በትንሣኤሃ ምስለ መለኮት። ወገሃደ ተዐውቀ
ዕበይነ ለሰብእ በእንተ ዘቤዘወነ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር። ወፈድፋደ
ናከብራ በምድርኒ ወበሰማይኒ ለዛቲ እግዝእትነ ወላዲተ አምላክ ማርያም
ድንግል።
15 ወስምዑ ዝኒ ፍካሬ ቀዳማዊ ብእሲ ዘውእቱ አቡነ አዳም። ዘእንበለ
ትድምርት ወሩካቤ እምዐፅመ ገቦሁ ተፈጥረት ሔዋን እምብእሲ። ወይእቲ
ኮነቶ ቢጾ። ወሰሚዓ ቃለ ሕብል እምዕድዉ ለአዳም ኮነቶ ቀታሊተ
በዐሊወ ትእዛዝ። ወበምሕረቱ እግዚአብሔር አብ ፈጠራ ለባሕርይ በውስተ
ከርሡ ለአዳም።
16 እንጺሖ ሥጋሃ ወቀዲሶ አኅደረ ላዕሌሃ። ለመድኀኒቱ ተወልደት ዘእንበለ
ጥልቀት። እስመ ግብራ ለንጽሕት ዘእንበለ ርስሐት። ወይእቲ ፈደየት
ዕዳሁ። ዘእንበለ ትድምርት፣ ወዘእንበለ ሩካቤ ወለደት በሥጋ ሰማያዊ
ንጉሠ። ወውእቱ ተወልደ እምኔሃ ወሐደሳ ለሕይወት በንሥሐ ሥጋሁ።
ወቀተሎ ለሞት በሥጋሁ ንጽሕት። ወተንሥአ ዘእንበለ ሙስና። ወአንሥአነ
ምስሌሁ ኀበ ኢመዋቲት መንበረ መለኮት። ወአዕረገነ ኀቤሁ። ወተወለጥነ
ሕይወተ በሥጋነ መዋቲት። ወረከብነ ሕይወተ እንተ ኢትመውት በስሕተተ
አዳም። ተመንደብነ ወበትዕግሥተ ክርስቶስ ተፈወስነ። በዕልወተ ሔዋን

[94] ዘጸ.33፥18-23
[95] ዘፀ.34፥33
[96] ምን ማለታቸው እንደሆነ ግልጽ አይደለም።



10 ደግሞም ሙሴ "ፊትህን አሳየኝ"[94] ሲል ወደ እግዚአብሄር ለመነ።
እግዚአብሄርም ሙሴን "ፊቴን አይቶ መዳን የሚቻለው የለምና
ፊትህን ወደ ምእራብ መልስና በአለቱ ውስጥ እንደ መስተዋት
የፊቴን ስእል ታያለህ" አለው።
11 ሙሴም የእግዚአብሄርን የፊቱን ነፀብራቅ ባየ ጊዜ የእስራኤል
ልጆች ፊቱን ማየት እስኪሳናቸው ድረስ ከፀሃይ ሰባት እጅ በራ።
ያን ጊዜም የእግዚአብሄርን ፊት ያዩ ዘንድ እንዳልወደዱ ብቻ ሳይሆን
"ያንተንም ፊት እንዳናይ መሸፈኛ አድርግልን"[95] እንዳሉት ተመለከተ።
12 ይህንንም ሲሉ ክርስቶስን እንደጠሉት፣ ቃሉን መስማትና ፊቱን
ማየት እንደ ጠሉ ይታያል።
13 ደግሞም አብርሃም ልጁን ይስሃቅን ወደ ቀርሜሌዎስ ተራራ
ባወጣው ጊዜ የይስሃቅ ቤዛ የሆነው በግ ከሰማያት አወረደ። ከሰ
ማያት የወረደ በግ ታረደ እንጂ ይስሃቅ አልታረደም። አብርሃም
በእግዚአብሄር አብ ይተረጎማል። ይስሃቅ በክርስቶስ እግዚአብሄር
ወልድ ይተረጎማል። ለአዳምና ለልጆቹ መድሃኒት ከሰማያት
በወረደ ጊዜ ፈፅሞ ስለ እኛ ሲል የለበሰው ስጋው ታረደ እንጂ
ከሰማያት የወረደው መለኮት አልታረደም። ይህች ከማርያም
የለበሳት ምድራዊት ናት። ለአባቱ ፈቃድ መስዋእት በሆነው
ለአብርሃም ልጅ ለይስሃቅ የሆነውን አርአያና ምሳሌ ትረዳለህ።
ሰማያዊ በግ መድሃኒት ሆነለት። የአብርሃምንም ልጅ ዳነ።
14 ለወረደው ለእግዚአብሄር ልጅ ግን ምድራዊው ስጋ ለመለኮት
ታዳጊው ሆነ።[96] በመለኮቱ ሳይታመም በስጋው ሞተ። ተለዋጭም
ሆነ። ሙዋቿ በትንሳኤዋ ለመለኮት ህይወት ሆነች። የእግዚአብሄር
ልጅ ክርስቶስ ስለታደገን የሰዎች ታላቅነት በግልፅ ታወቀ።
ይልቁንም ይህችን እመቤታችንን የአምላክ እናት ድንግል ማርያምን
በምድርም በሰማይም እናከብራታለን።
15 ይህንን የመጀመሪያውን ሰው፣ የአባታችንን የአዳምን ምሳሌ ስሙ።
ያለ ሩካቤና ያለ ግንኙነት ሄዋን ከወንዱ የጎድን አጥንት
ተፈጠረች። ጓደኛም ሆነችው። ከአዳም ጠላትም የሸንገላ ቃል
ሰምታ ህግን በመተላለፍ ጠላት በሆነችው እግዚአብሄር አብ
በቸርነቱ በአዳም ሆድ ውስጥ እንቁዋ ተፈጠረች።
16 ስጋዋን አንፅቶና ቀድሶ አደረባት። ያለ ርኩሰት ለመድሃኒት
ተወለደች። ያለ ርስሃት ንፅህት አድርጓታልና፤ ያለ ሩካቤና
ግኙኝነት እዳውን ከፈለች። በስጋም ሰማያዊ ንጉስን ወለደች።እሱም
ከእሷ ተወለደ። በስጋም ንስሃ ለደህንነት አደሳት። ሞትንም
በንፅህት ስጋው ገደለው። ያለ መበስበስም ተነሳ። ከእሱም ጋር
ወደ ማትሞት መንበረ መለኮቱ አነሳን። ወደ እሱም ሳበን።
በመዋቲ ስጋችንም በህይወት ተለወጥን። የማትሞት ህይወትን

[94] ዘፀ.33፥18-23
[95] ዘፀ.34፥33
[96] ምን ማለታቸው እንደሆነ ግልጽ አይደለም።

www.ethiopianorthodox.org

ሞትነ ወተቀበርነ። ወበንጽሓ ለማርያም ከበርነ ወተለዐልነ እስከ
አርያም።
17 ተነበየ ካዕበ ሕዝቅኤል በእንተ ማርያም ወይቤ፣ ርኢኩ ኆኅተ
በምሥራቅ። ኅቱም በዐቢይ መንክር ማኅተም። ወአልቦ ዘቦአ
ውስቴታ ዘእንበለ እግዚአ ኃያላን። ቦአ ውስቴታ ወወፅአ።[97]
18 ዝኒ ፍካሬሁ ስምዑ። ዘይቤ ርኢኩ ኆኅተ በአማን ኆኅተ አንቀጸ ሰ
ማይ ሙባእሙ ለቅዱሳን ውስተ መንግሥተ ሰማያት። ወበምሥራቅ
ሶበ ይብል በእንተ ንጽሓ ወአዳም ሥና ይብልዋ አንቀጸ አድኅኖ
ወይብልዋ ምሥራቅ ዘይኄጽርዋ ቅዱሳን በፍሥሓ ወበሐሤት።
19 ወዕጹታ ዘይቤ በእንተ ንጽሐ ድንግልናሃ። ወበእንተ ዘይቤ በዐቢይ
መንክር ማኅተም ዝኒ ያርኢ ገሃደ በእግዚአብሔር ዐቢይ መንክር
በመንፈስ ቅዱስ ተኀትመት። ወዘይቤኒ አልቦ ዘቦአ ውስቴታ
ዘእንበለ እግዚአ ኃያላን ቦአ ወወፅአ። ውእቱኬ ፈጣሬ ሰማያት
ወምድር ፈጣሬ መላእክት ወሰብእ ወአጋእዝት እግዚአ ኃያላን
ውእቱ ፍሬ መለኮት ዘለብሰ ሥጋነ እምኔሃ። ክርስቶስ ቦአ ወወፅአ
እንተ ኀቤሃ ዘእንበለ ሙስና።
20 ወካዕበ ተነበየ ሙሴ በእንተ ማርያም ወይቤ ርኢኩ ጳጦሰ በደብረ
ሲና እንተ ኢያውዐያ እሳት በላዒ።[98] ወፍካሬሁ ለዝንቱ እሳት
መለኮት ወልደ እግዚአብሔር። ወዕፀ ጳጦስ ዘትነድድ ወቈጽላ
ኢትውዒ ዛቲ ይእቲ ማርያም።

## ፺ወ፮ ኀበ አንጐርጐሩ እስራኤል[99]

1 ወካዕበ አንጐርጐሩ ደቂቀ እስራኤል በእንተ ተከህኖ ቅድመ
እግዚአብሔር እንዘ ይብሉ ንሕነሰ አኮኑ እስራኤል ንሕነ ዘርዐ
አብርሃም። ወእፎ ዘኢንሠውዕ ንሕነ ከማሆሙ በውስተ ደብተራ
ስምዕ በኀበ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ጽዮን ቅድስት በመዓጥንት
ወበዕጣን ወበቅድሳት ዘእንበለ ሙሴ ወአሮን እኁሁ ወደቂቆሙ።
2 ወንሕነሰ አኮኑ ሕዝብ እለ ኀረየነ ከማሆሙ ወንገብር ፈቃዶ።
ወሰሚዖ ሙሴ ይቤሎሙ ግበሩኬ ዘፈቀድክሙ። ወሐሩ ወአግበሩ
ሊቃናተ እስራኤል ሰብአ ማዕጠንታተ በዘየዐጥኑ ለጽዮን ወይሴብሑ
ለእግዚአብሔር። ወነሥኡ እምአብያቲሆሙ ዕጣነ ወፍሕመ
በማዕጠንት። ወሐሩ ወቦኡ ውስተ ቅድስተ ቅዱሳን ከመ ይዕጥኑ።
ወሶቤሃ ወደዩ ዕጣነ። በአሐቲ ውዝዋዜ ማዕጠንት ወፅአ ነበልባል
እመዓጥኒሆሙ። ወውዕዩ ሶቤሃ ወተመስዉ ከመ ሠምዕ በቅድመ ገጸ
እሳት። ከማሁ ተመስው ከመ ሣዕር ይቡስ ሶበ ይረክቦ ነበልባለ
እሳት።

[97] ሕዝ.44፥1
[98] ዘጸ.3፥2
[99] ዘኍ ምእ12፥14 ይመልከቱ።

- 111 -

አገኘን። በአዳም ስህተቶች ተቸገርን። በክርስቶስ ትእግስት ዳን።
በሄዋን ክህደት ሞትን። ተቀበርንም። በማርያም ንፅህናም ከበርን።
እስከ ሰማይም ከፍ ከፍ አልን።
17 ደግሞ ህዝቅኤል "በታላቅና በድንቅ ማህተም የተዘጋ በርን አየሁ።
ከሃያላንም ጌታ በቀር ወደ ውስጧ የገባ የለም። እሱ ግን በውስጧ
ገባ፤ ወጣም"[97] ብሎ ስለ ማርያም ትንቢት ተናገረ።
18 ትርጓሜውን ስሙ። "በርን አየሁ" ያለው በእውነት የቅዱሳን
የመንግስተ ሰማያት መግቢያ፣ የሰማይ በር መግቢያ ናት።"በምስራቅም"
ያለው ስለ ንፅህናዋና ስለ አማረው ደም ግባቷ ነው። የመዳኛ በር
ይሏታል። በፍፁም ደስታ የሚያዩዋትም ምስራቅ ይሏታል።
19 "የተዘጋጀች" ያለውም ስለ ድንግልናዋ፣ ስለ ንፅህናዋ ነው።
በታላቅና ድንቅ ማህተም ያለው በግልፅ የእግዚአብሄርን ታላቅ
ድንቅ ስራ ያሳያል። በመንፈስ ቅዱስ ታተመች። ያለ ሃያላን ጌታ
ወደ ውስጧ የገባ የለም።እሱ ግን ገባ። ወጣም። እሱ የመላእክትና
የሰው የጌቶችም ፈጣሪ ነው። የሃያላን ጌታ ነው። ከእሷ ስጋችንን
የለበሰ፣ የመለኮት ፍሬ ክርስቶስ ገባ። ያለ ጥፋትም ወጣ።
20 ደግሞም ሙሴ ስለ ማርያም "በሲና ተራራም የሚያቃጥል እሳት
ያላቃጠላት ቁጥቋጦ አየሁ"[98] ሲል ትንቢት ተናገረ። የዚህ እሳት
ትርጉምም የእግዚአብሄር ልጅ መለኮት ነው። የምትነድና ቅጠሏ
የማይቃጠል የቁጥቋጦው እንጨትም ማርያም ናት።

## ፺፮ እስራኤል እንደ አጉረመረሙ[99]

1 ደግሞም የእስራኤል ልጆች "እኛስ የአብርሃም ዘሮች እስራኤላውያን
አይደለንም? ታዲያ እኛስ በምስክሩ ድንኳን ውስጥ በእግዚአብሄር
ታቦተ ህግ በቅድስት ፅዮን ዘንድ በማእጠንትና በእጣን በቅድስናም
ያለ ሙሴና ወንድሙ አሮን እንዲሁም ልጆቻቸው ለምን አንሰ
ዋም? እንደነሱ እግዚአብሄር የመረጠን ህዝቦች አይደለንምን?
ፈቃዱንስ እናደርግ የለምን?" ሲሉ በእግዚአብሄር ፊት ስለማገልገል
አጉረመረሙ። ሙሴም ሰምቶ "የወደዳችሁትን አድርጉ" አላቸው።
2 የእስራኤል አለቆችም ሄዱ፤ ፅዮንንም የሚያጥኑበትና እግዚአብሄርን
የሚያመሰግኑበት ሰባ ማእጠንትን አዘጋጁ። ከቤታቸውም እጣንና
ፍህምን በማእጠንቱ ወሰዱ። ሄደውም ያጥኑ ዘንድ ወደ ቅድስተ
ቅዱሳኑ ገቡ። እጣንንም ጨመሩ። በመጀመሪያዋ የማእጠንት
ውዝዋዜ የእሳት ነበልባል ከማእጠንቱ ወጣ። ወዲያውኑ ተቃጠሉ።
ሰምም በእሳት ፊት እንዲቀልጥ እንዲሁ ቀለጡ። ደረቅ ሳር

[97] ህዝ.44፥1
[98] ዘፀ.3፥2
[99] ዘሁ.ምእ.12፥14 ይመልከቱ።

www.ethiopianorthodox.org

ከማሁ ውዕዩ ምስለ ንዋየ ቅድሳቲሆሙ። ወአልቦ ዘተርፈ ዘእንበለ
መዓጥኒሆሙ።
3 ወይቤ እግዚአብሔር ቀድስዎን ሊተ ለእሉ መዓጥንት ለደብተራየ።
ወይኩን ለመሥዋዕትየ እስመ ተቀደሰ በሞተ ዚአሆሙ።
4 ማዕጠንትሰ ማርያም ይእቲ። ወፍሕምኒ ክርስቶስ ወልደ
እግዚአብሔር መለኮት ውእቱ። ወጼና ዕጣን መዐዛሁ ለክርስቶስ።
ዘቦ መዐዛሁ ሐዋርያት ወነቢያት ወሰማዕታት ወፈላስያን መነኑ
ዓለመ። ወወረሱ መንግሥተ ሰማያት ወአሕባሊሃ ለማዕጠንት። ሰ
ዋስው ዘርእየ ያዕቆብ በዘቦቱ የዐርጉ ወይወርዱ ተአዚዞሙ ባቲ
ወምስለ ጢሰ ዕጣን የዐርግ ዲበ መንበረ እግዚአብሔር ጸሎቶሙ
ለንጹሐን።
5 ወሶበ አውዐዮሙ ነበልባል ለኃጥአን ሐመይዎሙ ሕዝብ
አዝማዲሆሙ ለእለ ኀልቁ። ወይቤልዎሙ ለሙሴ ወለአሮን
አኀለቅምምዎሙ ለነ ለሊቃውንቲነ። ወነሥኡ እብነ ከመ
ይውግርዎሙ ለሙሴ ወለአሮን።
6 ወተምዕዐ እግዚአብሔር መዐተ ላዕለ እስራኤል። ወአስቈረረ ከመ
ፀርቀ ትክቶ ለምክረ ዳታን ወአቤሮን ደቂቀ ቆሬ። ወቀጸባ ቃለ
እግዚአብሔር ለምድር። ወፈትሐት ምድር አፉሃ ወውኅጠቶሙ ምስለ
ኵሉ ዘዚአሆሙ፣ ወአንስቲያሆሙ፣ ወደቂቆሙ፣ ወእንስሳሆሙ ወረዱ
ውስተ ሲኦል ሕያዋኒሆሙ። ወተሐትመት ምድር በመልዕልቴሆሙ።
ወለሕዝብሰ እለ ኅብሩ ምስሌሆሙ ሰሚዖሙ ሐሚተ ዚአሆሙ ፈነወ
ሎሙ እግዚአብሔር ብድብደ። ወሞቱ በአሐቲ ጊዜ። ወቦኡ ሙሴ
ወአሮን በዕጣን ወበማእጠንት።
7 ወበከዩ በኀበ እግዚአብሔር። ወአስተስረዩ ለሕዝብ እንዘ ይብሉ
ተዘከር እግዚእ አብርሃምሃ ፍቁረከ ወይስሐቅሃ ቍልዔከ
ወእስራኤልሃ ቅዱሰከ። እስመ ዘርዖሙ ንሕነ ውሉደ ሕዝብከ።
አቍርር መዐተከ እምኔነ። ወፍጡነ ስምዐነ ወኢታማስነነ። ወአእትት
መቅሠፍተ እምላዕለ ሕዝብከ።
8 ወእግዚአብሔር መሓሪ ርእየ የውሃቶ ለሙሴ ወመሐሮሙ። ወነበቦ
እግዚአብሐር ለሙሴ ወይቤሎ ንግሮሙ ለዝንቱ ሕዝብ ወበሎሙ
ቀድሱ ርእሰክሙ፣ ወአምጽኡ በበአብያተ አበዊክሙ በትረ፣ ወጸሐፉ
ከመ ታእምሩ በትሮሙ። አንተ ወአሮን እኁከ ወእምቤትክሙኒ
ይጽሐፍ አሮን በትሮ ወበትረከሰ ኢትጽሐፍ እስመ ፍጽምት
ትእምርት ለደቂቀ ሕዝብከ፣ ቅስት ለዐላውያን ወለኵሎሙ እለ
አምኑሰ ትእምርተ ሕይወት። ወሶበ ጸሐፍከ ይእዜ ምስሌሆሙ
ይብሉከ ዛቲሰ እምትካት ገባሪተ መንከር በቃለ እግዚአብሔር
እምይቤሉ ሶበ አርአይኩ ተአምረ በውስቴታ አላ ለቤተ አቡከ
ጸሐፍ በትረ አሮን።

- 112 -

በእሳት ነበልባል እንዲቃጠል ከንዋየ ቅድሳታቸው ጋር እንዲሁ
ተቃጠሉ። ያለማጠኛም የቀረ አልነበረም።
3 እግዚአብሄርም አለ። "በእነሱ ሞት ተቀድሰዋልና እነዚህን
ማእጠንቶች ለድንኳኑ ቀድስልኝ። ለመስዋእትም ይሁን።"
4 ማእጠንቱ ማርያም ናት። ፍህሙም የእግዚአብሄር ልጅ ክርስቶስ
መለኮት ነው። የእጣኑ መአዛ የአላቸውም አለምን የናቁና
መንግስተ ሰማያትን የወረሱ የክርስቶስ መአዛዎች የሆኑ ሃዋርያት፣
ነቢያትና ሰማእታት ናቸው። የማጠኛዋ ሃብሎችም በእሷ ተይዘው
መላእክት ሲወጡባትና ሲወርዱባት ያእቆብ ያያት መሰላል ናት።
የንፁሃንም ፀሎታቸው ከእጣን ጢስ ጋር ወደ እግዚአብሄር መንበር
ያርጋል።
5 ነበልባሉም ሃጥአንን ባቃጠላቸው ጊዜ ያለቁት ሕዝቦች ዘመዶች
ሙሴንና አሮንንም ሊቃውንቶቻችንን አስጨረሱን ሲሉ አሟቸው።
ይወግሯቸው ዘንድም ድንጋይ አነሱ።
6 እግዚአብሄርም በእስራኤል ላይ ከባድ ቁጣን ተቆጣ። የቆሬም
ልጆች የዳታንና የአቤሮንን ምክር እንደ ደም ጨርቅ ተፀየፉት።
የእግዚአብሄር ቃልም ምድርን ጠቀሳት። ምድርም አፍዋን ከፈተች።
እያንዳንዳቸውንም ከሴቶቻቸው፣ ከልጆቻቸውና ከእንስሳዎቻቸው ጋር
ዋጠቻቸው። ወደ ሲኦልም በህይወታቸው ወረዱ። ምድር በላያቸው
ላይ ተደፋች። የእነሱን ሃሜት ሰምተው ከእነሱ ጋር በተባበሩት
ህዝቦችም እግዚአብሄር ቸነፈር ላከባቸው። በአንድ ጊዜም ሞቱ።
7 ሙሴና አሮንም ከእጣንና ማእጠንት ጋር ገቡ። ወደ
እግዚአብሄርም "አቤቱ ወዳጅህን አብርሃምንና ይስሃቅን ቅዱስህንም
እስራኤልን አስብ። እኛ ዘሮቻቸውን የህዝቡም ልጆች ነንና።
መአትህን አቀዝቅዘው። ፈጥነህም ስማን። አታጥፋንም። ከህዝብህም
ላይ መቅፍትን አስወግድ" ሲሉ ለህዝቡ አለቀሱ።
8 ይቅር ባይ እግዚአብሄርም የሙሴን ቅንነት ተመለከተ። ይቅርም
አላቸው። እግዚአብሄርም ሙሴን "ይህን ህዝብ እራሳችሁን ቀድሱ።
በየነገዳችሁም ብትራችሁን አምጡ ብለህ ንገራቸው" አለው። "የማን
ብትር እንደሆነ ታውቁም ዘንድ አንተና ወንድምህ አሮን በብትሩ
ላይ ይፃፍ። በአንተ ብትር ላይ ግን አይፃፍ። ለህዝብህ ልጆች
ፍፁም ምልክት ናትና ለማያምኑት ጦር፣ ለሚያምኑት ግን
የደህንነት ምልክት ናት። ዛሬም ከእነሱ ጋር ከፃፍክ በእሷ
ታምራት በማሳይበት ጊዜ ይህች ከመጀመሪያውም በእግዚአብሄር
ቃል ተአምር ሰሪ ናት ይላሉና ስለ አንተ ነገድ በአንተ ሳይሆን
በአሮን ብትር ፃፍ" አለው።

www.ethiopianorthodox.org

## ፺ወ፰ በእንተ በትረ ሙሴ ወአሮን[100]

1 ወነገሮሙ ሙሴ ዘንተ ወአምጽኡ በበአብያተ አበዊሆሙ እለ ኀረዩ ለንጽሕ። ወኮነ ፲ወ፪ አብትረ ወጸሐፈ ሙሴ አብትሪሆሙ በአስማተ አበዊሆሙ። በትረ አሮን ተጽሕፈት በሌዊ። ወበትረ ከርሚን ተጽሕፈ በይሁዳ። ወበትረ አዶንያስ ተጽሕፈት በሮቤል። ወኩሉ ቤተ እስራኤል ከማሁ ተጽሕፉ አብትሪሆሙ በበአስማተ አበዊሆሙ።

2 ወይቤሎ እግዚአብሔር ውግር ኀበ ጽዮን ኀበ ደብተራ ዘመርጡል። ወዕፀው ህየ እስከ ነግህ። ወንሥአን በቅድሜሆሙ። ወሀቦሙ ለለበትሮሙ ለለአብያተ አበዊሆሙ። ለለአስማቲሆሙ ዘጽሑፍ ውስተ በትሩ ወዘተረክበ ትእምርት በውስተ በትሩ ውእቱ ኀረይኩ ይኩነኒ ካህነ። ወነገሮሙ ሙሴ ዘንተ ነገረ። ወገብሩ በከመ አዘዞሙ እግዚአብሔር።

3 ወእምዝ ሶበ ጸብሐ ነሥአ። ወመጽኡ ኩሉ አእሩገ እስራኤል ወአሮን። ወቦአ ሙሴ በቅድሜሆሙ። ወአልዐሎን ለአብትር። ወአምጽአን ቅድመ ኩሉ ሕዝብ። ወተረክበት በትረ አሮን ምስለ ፍሬ ወጽጌ ከርካዕ እንተ ትምዕዝ ሠናየ መዐዛ።

4 ወይቤሎሙ ሙሴ ርእዩኬ ዛቲ በትር ዘኀረየ እግዚአብሔር እምላክክሙ። ኪያሁ ፍርሁ ወተቀነዩ ሎቱ። ወሰገዱ ኩሉ ሕዝብ ለእግዛብሔር።

5 በትርኬ ይእቲ ማርያም። ወዘእንበለ ትስተይ ማየ ዘሠረፀት ጽጌ ዘእንበለ ዘርዐ ብእሲ ዘተወልደ እምኔሃ ቃለ እግዚአብሔር።

6 ወዘይቤ ኀረይኩ አርኢ ትእምርተ ወይኩነኒ ካህነ ውእቱ እግዚአብሔር ኀረያ ለማርያም እምኩሉ ተዓይነ እስራኤል በከመ ተነበየ ዳዊት አቡሃ ያበድሮን እግዚአብሔር ለአናቅጸ ጽዮን እምኩሉ ተዓይኒሁ ለያዕቆብ። ወመትልው ይቤ ነኪር ነገሩ በእንቲአኪ ሀገረ እምኩሉ ትዕይንተ እስራኤል።[101] ወአናቅጺሃ ሶበ ይብል አርምሞ አፉሃ ወንጽሓ ከናፍሪሃ ወስብሓት ዘይወፅእ እምአፉሃ ከመ ጸቃውእ ዘይውሕዝ እምከናፍሪሃ ወንጽሓ ድንግልናሃ ዘእንበለ ጥልቀት ወዘእንበለ ሙስና ወርኩስ እምቅድመ ትለደኒ ወእምድኅረ ወለደተኒ ንጽሕትኒ ወቅድስትኒ። ወከማሁ ከመኒ እስከ ለዓለም ወበሰማያትኒ ንጽሕት ምስለ መላእክት ታንሶሱ።

7 ወይእቲ በትረ አሮን ህሉት ይእቲ ውስተ ጽዮን ምስለ ጎሞር መና ምልእት። ወምስለ ክልኤ ጽላት እለ ተጽሕፋ በአጽባዕተ እግዚአብሔር። ወጽዮን ሰማያዊት መንፈሳዊት መልዕልቴሆሙ። ጽዮን እንተ ግብራ ወኅብራ ነኪር። እንተ ለሊሁ ገባሪሃ ወኬንያሃ ለማኅደረ ስብሐቲሁ።

[100] ዘኍ.ምእ17 ይመልከቱ።

[101] ?



## ፺፰ ስለ ሙሴና ስለ አሮን ብትር[100]

1 ሙሴም ይህንን ነገራቸው። በየነገዳቸውም ስም ለንፅህና የመረጧቸውን አመጡ። አስራ ሁለት ብትሮችም ሆኑ። ሙሴም ብትሮቹን በየነገዱ አባት ስም ፃፈ። የአሮንም ብትር በሌዊ ተፃፈች። የእስራኤል ነገዶችም ሁሉ. እንዲሁ ብትሮቻቸን በየነገዳቸው አባት ስም ፃፉ።

2 እግዚአብሄርም ሙሴን "በአዳራሹ ድንኳን በፅዮን ዘንድ አስቀምጠው። እስከ ነግህም ድረስ ዝጋው። በፊታቸውም ውሰዳቸው። የእያንዳንዳቸውንም ብትር በየነገዱ እንደተፃፈው በየስማቸው ስጣቸው። በብትሩ ውስጥ ምልክት የተገኘበትን አገልጋይ ይሆነኝ ዘንድ እሱን መረጥኩ" አለው። ሙሴም ይህንን ነገር ነገራቸው። እግዚአብሄርም እንዳዘዛቸው አደረጉ።

3 ከዚህ በሁዋላ በነጋ ጊዜ ሁሉም የእስራኤል ሽማግሌዎች መጡ። ሙሴም በፊታቸው ገባ። ብትሮችንም ከፍ ከፍ አደረጋቸው። በህዝቡም ሁሉ ፊት አመጧቸው። የአሮንም ብትር ከፍሬና መልካም መአዛ ከምትሰጥ የለውዝ አበባ ጋር ተገኘች።

4 ሙሴም "ተመልከቱ። ይህች በትር አምላካችሁ እግዚአብሄር የመረጣት ናት። እሱን ፍሩ። ተገዙለትም" አላቸው። ህዝቡም ሁሉ ለእግዚአብሄር ሰገዱ።

5 በትሪቱ ማርያም ናት። ውሃ ሳትጠጣ ማበቧ ቃለ እግዚአብሄር ከእሷ ያለ ወንድ ዘር ለመወለዱ ምልክት ነው።

6 በብትሩ ምልክትን አሳይበት ዘንድ የመረጥኩት እሱ ካህን ይሁኝ ያለው እግዚአብሄር ከእስራኤል ከተሞች ሁሉ ማርያምን መረጣት። አባቷ ዳዊት እግዚአብሄር ከያእቆብ ከተሞች ሁሉ የፅዮንን በሮች ያስቀድማል። ደግሞም "የእግዚአብሄር አገር ሆይ ከእስራኤል ከተሞች ሁሉ ስለ አንች ነገሩ ድንቅ ነው"[101] ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ በሮቿ ያለውም የአፏን ዝምታ፣ የከንፈሯን ንፅህና፣ ከከንፈሯ እንደሚፈስ የማር ወለላ ከአፏ የሚወጣ ምስጋና፣ የድንግልናዋ ንፅህና፣ ያለ ርኩሰት፣ ያለ ጥፋትና ርኩሰት የሆነን የድንግልናዋን ንፅህና ነው። ሳትወልደኝም ከወለደችኝም በህዋላ ንፅህት ናት። ቅድስትም ናት። ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ዘላለሙ እንዲሁ። በሰማያትም ንፅህት ናትና ከመላእክት ጋር ትመላለሳለች።

7 ይህች የአሮን ብትር ምሉእ ከሆነች ከመና መስፈሪያና በእግዚአብሄር ጣቶች በተፃፉ ከሁለት ፅላቶች ጋር ነበረች። ስራዋና ክብሯ አስደናቂ የሆነችውና እሱ ራሱ ሰሪዋና ተጠባቢዋ የሆነችው መንፈሳዊቷና ሰማያዊቷ ፅዮንም በላያቸው ላይ ነበረች።

[100] ዘሁ ምእ 17 ይመልከቱ።

[101] ?

www.ethiopianorthodox.org

8 ወይቤሎ ለሙሴ ግበር ታቦተ እምዕፅ ዘኢይነቅዝ። ወትለብጦ
በወርቅ ጽሩይ እንተ ኩለንታሁ። ወርቅሰ ጽርየተ መለኮት ዘወረደ
እምሰማያት። እስመ መለኮት ይእኀዝ ኩሎ ሰማያተ ወምድረ።
ወከማሁ በወርቅ ተለብጠት ታቦት ማኅደረ ለጽዮን ሰማያዊት።
9 ወታቦት ትተረጐም ማርያም። ወዕፅ ዘኢይነቅዝ ይተረጐም ክርስቶስ
መድኅኒነ። ወኅሞር እንተ ይእቲ መሶበ ወርቅ እንተ ውስተ ታቦት
ትትረጐም ይእቲ ማርያም። ወመና ዘውስተ መሶብ ሥጋሁ
ለክርስቶስ ይተረጐም። ዘወረደ እምሰማያት በቃለ እግዚአብሔር
ዘተጽሕፈ ውስተ ክልኤ ጽላት ይተረጐም ክርስቶስ ወልደ
እግዚአብሔር።
10 ወጽዮን መንፈሳዊት ትተረጐም ብርሃነ መለኮት መንፈሳዊት። ባሕርይ
እንተ ተገምረት ውስተ ታቦት በከመ ዕንቈ ባሕርይ እንተ ተኀቱ
ዘብዙኀ ሤጣ ወይእኀዛ ዘአጥረያ ውስተ እዴሁ፣ ወይፀብጣ ወያገምራ
ውስተ እዴሁ፣ ወእንዘ ሀለወት ውስተ እዴሁ ቦአ ወተገምረ
ውስቴታ።
11 ወባሕርዩ ዘአጥረየ ይተረጐም ቃለ እግዚአብሔር ክርስቶስ ወእንተ
ተእኀዘት ባሕርይ መንፈሳዊት ትተረጐም ማርያም ወላዲተ ብርሃን፣
ዘእምኔሃ ተሠገወ አክራጦስ ዘአልቦቱ ቱስሕት በውስቴታ ገብረ
ማኅፈደ ለርእሱ እምሥጋሃ ንጹሕ ወተወልደ እምኔሃ ብርሃን
ዘእምብርሃን አምላክ ዘእምአምላክ ዘተወልደ በፈቃዱ ወኢተገብረ
በእደ ካልእ አላ ለርእሱ ገብረ ማኅፈደ በእንተ ዘኢትትረከብ ጥበብ
እንተ ዕዱት እምሕሊና ሰብእ።
12 ወካዕበ አመ አውፅኦሙ እግዚአብሔር ለእስራኤል እምግብፅ ጸምኡ
ማየ በቃደስ ወአንጐርጐሩ ወበከዩ ኀበ ሙሴ። ወሖረ ሙሴ ኀበ
እግዚአብሔር ወአይድዖ ዘንተ ለእግዚአብሔር። ወይቤሎ
እግዚአብሔር ንሣእ በትረከ ወዝብጣ ለይእቲ እዝኀ። ወዘበጣ ሙሴ
ኑኃ ወግድማ በአርኣያ ትእምርተ መስቀል። ወውኅዙት ፲ወ፪
አፍላግ። ወሰትዩ እምኔሃ። ወረወዩ ሰብኦሙ ወእንስሳሆሙ።
ወሰትዮሙ ተለወቶሙ ይእቲ ኰኲሕ።
13 ወኰኲሕሰ ይተረጐም በክርስቶስ። ወአፍላግ ሐዋርያት። ወዘሰትዩ
ትምህርተ ሐዋርያት። ወበትርኒ ዕፀ መስቀል። ወኰኲሕሰ በከመ
ይቤ በወንጌል ዘሣረረ ዲበ ኰኲሕ ኢይትሐወክ እምአጋንንት።
14 ወካዕበ ይቤ አነ አንቀጽ። ወካዕበ ይቤ አነ ዴዴ። ወርእዩሂ ዘከመ
ከፈሎሙ ለአርዳኢሁ እንዘ ይብል ወለእለ እምድኅሬሆሙ ጳጳሳተ
ወማኅበረ ክርስቲያን እንተ ኰኲሕ። ይቤሎ ለጴጥሮስ ወላዕሌከ
አሐንጾሙ ለሕዝበ ክርስቲያን።[102] ወዓዲ ይቤ አነ ኖላዊ አባግዕ።
ወሎቱኒ ይቤሎ ሥልሰ ረዐይኬ አባግዕየ።
5 ወካዕበ ይቤ አነ ጕንደ ዐፀደ ወይን። ወሎሙኒ ይቤሎሙ አንትሙ
አዕጹቂሁ ወአሕሩጊሁ። ወበትረ ሙሴኒ እንተ ባቲ በዘገብረ

---

[02] ማቴ16፥18



8 ሙሴንም ከማይነቅዝ እንጨት ታቦትን ስራ። በጠራ ወቅም
ትለብጠዋለህ አለው። መለኮት ሰማያትንና ምድርን ሁሉ ይይዛልና
ሁለንተናው ወርቅ ማለት ከሰማያት የወረደው የመለኮት ፅርየት
ነው። እንዲሁም የሰማያዊቷ ፅዮን ማደሪያ የሆነችው ታቦትም
በወርቅ ተለበጠች።
9 ታቦት በማርያም ትተረጎማለች። የማይነቅዝ እንጨትም
በመድሃኒታችን ክርስቶስ ይተረጎማል። በታቦቱ ውስጥ ያለችው
መሶበ ወርቅም በማርያም ትተረጎማለች። በመሶቡ ውስጥ ያለው
መናም ከሰማያት ወርዶ በእግዚኣብሄር ቃል በሁለቱ ፅላቶች
በተፃፈው በእግዚኣብሄር ልጅ በክርስቶስ ይተረጎማል።
10 መንፈሳዊቷ ፅዮን በብርሃነ መለኮት ትተረጎማለች። እንደምታበራና
ዋጋዋም ብዙ እንደሆነ የገዛት በእጁ እንደሚይዛት፣ ጨብጠም እጅ
እንደሚያደርጋት፣ በእጁም እያለች በታቦት ውስጥ የተደረገችው
መንፈሳዊቷ እንቁ ናት።
11 እንቁዋንም የገዛት በእግዚኣብሄር ቃል በክርስቶስ ይተረጎማል።
የተያዘችው መንፈሳዊት እንቁም በብርሃን እናት ማርያም
ትተረጎማለች። በውስጡ ቅልቅል የሌለበት ወይን ጠጅ ከእሷ
ተወለደ። ከንፁህ ስጋዋ ለራሱ ቤትን አዘጋጀ። ከብርሃን የተገኘ
ብርሃን፣ ከኣምላክ የተገኘ ኣምላክም ከእሷ ተወለደ። እሱም
የተወለደው በፈቃዱ ነው። በሌላ እጅ ኣልሆነም። ነገር ግን በሰው
ስለማትገኘውና ከሰው ህሊና ስለ ራቀች ጥበብ ለራሱ ቤትን ሰራ።
12 ደግሞም እግዚኣብሄር እስራኤልን ከግብፅ ባወጣቸው ጊዜ በቃደስ
ውሃ ተጠሙና ኣጉረመረሙ። ወደ ሙሴም ኣለቀሱ። ሙሴም ወደ
እግዚኣብሄር ሄደ። ይህንንም ለእግዚኣብሄር ነገረ። እግዚኣብሄርም
"ይህችን ባልጩት ምታት" ኣለው። ሙሴም በቁመቷና በወርዷ
በትምህርተ መስቀል ኣይነት መታት። የኣስራ ሁለት ምንጮች ውሃ
ፈለቀች። ከእሷም ጠጡ። ሰዎቻቸውና እንስሳዎቻቸውም ረኩ።
ከጠጡም በህዋላ ይህች ኣለት ተከተለቻቸው።
13 ኣለቱ በክርስቶስ፣ ምንጮቹም በሃዋርያት ይተረጎማል። የጠጡት
በሃዋርያት ትምህርት። ብትርም በእፀ መስቀሉ ይተረጎማል። ኣለት
"በኣለት ላይ የሰራ በኣጋንንት ኣይታወክም" ብሎ በወንጌል እንደ
ተናገረው።
14 ደግሞም "እኔ በር፣ ደጅም ነኝ" ኣለ ለደቀ መዛሙርቱና ከእነሱም
በሁዋላ ላሉት ጳጳሳት፣ ለክርስቲያን ቤተ ሰብ ሁሉ እንዲህ ሲል
ኣደላቸው። ጴጥሮስንም "ኣንተ ኣለት ነህ፣ በኣንተም ላይ ህዝበ
ክርስቲያንን እሰራቸዋለሁ"[102] ኣለው። ደግሞም "እኔ የበጎች እረኛ ነኝ"
ኣለ። እሱንም ሶስት ጊዜ "በጎቼን ጠብቅ" ኣለው።
15 ደግሞም "እኔ የወይኑ ቦታ ግንድ ነኝ" ኣለ። እነሱን ደግሞ "እናንተ
ቅርንጫፎችና ሃረጎች ናችሁ ኣላቸው። ሙሴ ተኣምር የሰራበት

---

[102] ማቴ.16፥18

www.ethiopianorthodox.org

ተአምረ[103] ትተረጐም ዕፀ መስቀል በዘአድኅኖ ለአዳም ወለደቂቁ
እምሥቃየ አጋንንት።
16 ወበከመ ሙሴ ዘበጠ ባቲ ማየ ተከዚ ወረሰያ ደመ ወቀተለ
ዓሣቲሆሙ ከማሁ ክርስቶስኒ በመስቀሉ ቀተሎ ለሞት ወአውፅኦሙ
እምውስተ ሲኦል።
17 ወበከመ ሙሴ ዘበጠ በበትሩ ውስተ ነፋሳት ወጸልመት ኲላ ምድረ
ግብጽ እስከ ፫ ዕለት ወ፫ ሌሊት ወ፫ ሌሊተ ጽልመት ዘያርመሰ
ምስ እስከ ኢይትነሥኡ እምስካቢሆሙ ወከማሁ ክርስቶስኒ ተሰቂሎ
ዲበ ዕፀ አብርሀ ጽልመተ። አልቦ እምሰብእ ወተንሥአ እምውታን
በሣልስት ዕለት ወሣልስት ሌሊት። ወበከመ በትረ ሙሴ ኮነ ሚጠት
ወወልጦት በቃለ እግዚአብሔር እንዘ ይብስት ኮነት ዘነፍስት ወካዕበ
እንዘ ነፍስ ኮነት ይብስተ ወከማሁ ክርስቶስኒ በዕፀ መስቀሉ ረሰየ
ሕይወተ ለሕዝበ ክርስቲያን እለ አምኑ ቦቱ ረሰየ በትእምርተ
መስቀል ከመ ይሰደዱ መንፈሰ አጋንንት እስመ ተውላጠ ኮኑ
አጋንንት ወክርስቲያን እሙንቱ እንዘ መንፈሳውያን ኮኑ ኅሱራነ
በተዐድዎ ትእዛዘ እግዚኦሙ ኮኑ ስዱዳነ በኀይለ መስቀሉ። ወንሕነኒ
ኮነ መንፈሳውያነ በነሢአ ሥጋሁ ወደሙ ህየንቴሆሙ። ለእለ ተሰዱ
መንፈሳውያን ወኮነ ንሕነ ሰባሕያነ እለ አመነ በመስቀሉ
ወበትንሣኤሁ ቅድስት።
18 ወበከመ ሙሴ ዘበጠ አድባረ ወአምጽአ መቅሠፍተ በትእዛዘ
እግዚአብሔር ሰፊሖ እዴሁ ምስለ በትሩ ከማሁ ክርስቶስኒ
አውፅኦሙ ለአጋንንት እምላዕለ ሰብእ በኀይለ መስቀሉ ሰፊሖ እዴሁ
ዲበ ዕፀ መስቀል። ሶበ ይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ዝብጥ
በበትርከ ዝንቱ ብሂል ዕትብ በማዕተበ መስቀሉ ለክርስቶስ ብሂል።
ወሶበ ይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ስፋሕ እዴከ ዝኒ ብሂል ከመ
በስፍሐተ እዴሁ አድኀነነ ክርስቶስ እምተቀንዮ ለጸላኢ። ወወሀበነ
ሕይወተ እንቲአሁ በስፍሐተ እዴሁ በዲበ ዕፀ መስቀል ብሂል።
19 ወእመኒ ይጸብኡ አማሌቅ ምስለ እስራኤል ዐርገ ሙሴ ውስተ
ደብር ወአሮን ምስሌሁ ዐርጉ ከመ ይጸልዩ እስመ ተኀየሉ አማሌቅ።
ወአዘዞ እግዚአብሐር ለሙሴ ወይቤሎ ስፋሕ እዴከ እስከ ይረክቡ
ኀይለ እስራኤል። ወይቤ በውስተ ኦሪት ኮና ርቡባተ እዴሁ ለሙሴ
እስከ ዕርበተ ፀሐይ።[104]
20 አላ ባሕቱ ክቡዳት እደዊሁ ለሙሴ ወሶበ የዐፅቦ አውረደ እዴሁ እምዘ ሰ
ፍሐ ይወፅኡ ወይመውእዎሙ ፀሮሙ ወሶበ ያሌዕል እዴሁ ወይሰፍሕ
በርቱዕ ይትመውኡ አማሌቅ ወይሰድድዎሙ እስራኤል ወይመውእዎሙ
ለፀሮሙ አማሌቅ።
21 ወዘንተ ሶበ ርእዩ አሮን ወሆር ነደቁ እብነ በየማኑ ወበፀጋሙ ለሙሴ
ወአፅገዉ እደወ ሙሴ ላዕለ አእባን ዘነደቁ አሮን እንተ የማኑ ወሆር
እንተ ፀጋሙ ወአኀዝዎ ዲበ መታክፍቲሆሙ ከመ ኢያግብእ እዴሁ እምዘሰ
ፍሐ።

[103] ዘፀአ.7 ይመልከቱ
[104] ዘፀኦ.17፥8-16

በትርም[103] ኣዳምንና ልጆቹን ከኣጋንንት ስቃይ በኣዳነበት በእፀ
መስቀል ትመሰላለች።
16 ሙሴም የተከዜን ውሃ እንደ መታበትና ደም እንዳደረጋት
እንስሳዎቻቸውንም እንደገደለ እንዲሁም ክርስቶስ በመስቀሉ ሞትን
ገደለው። ከሲኦል ውስጥም ኣወጣቸው።
17 ሙሴም በብትሩ በነፋሳት ውስጥ እንደመታ የግብፅ ምድር ሁሉ
እስከ ሶስት ቀንና ሶስት መኣልት ከመኝታቸው መነሳት
እስኪያቅታቸው ድረስ የሚርመሰመስ ጨለማ እንደሆነ። እንዲሁም
ክርስቶስ በእፀ መስቀል ተሰቅሎ ከሰው ጨለማን ኣበራ ። በሶስት
ቀንና ሶስት ሌሊት ከሙታን ተነሳ። የሙሴ በትርም በእግዚኣብሄር
ቃል ተመልሳና ተለውጣ ደረቅ ሁና ሳለች፣ ህይወት ያላት
እንደሆነች፣ ህይወት ያላት ሳለች ደረቅ እንደሆነች፣ እንዲሁም
ክርስቶስ ላመኑት ህዝበ ክርስቲያን በእፀ መስቀሉ ህይወትን
ኣደረገ። የኣጋንንት መናፍስት እንዲሰደዱ ኣደረገ። ኣጋንንትና
ክርስቲያን ተለዋዋጮች ሁነዋልና። ክርስቲያኖችም መንፈሳውያን ሳሉ
የጌታቸውን ትእዛዝ በመተው የጎሰቆሉ ይሆናሉ። እኛም በተሰ
ደዱት መንፈሳውያን ምትክ ስጋውንና ደሙን በመቀበል
መንፈሳውያን ሆንን። በመስቀሉና በተቀደሰችው ትንሳኤው ያመን
እኛም ኣመስጋኞች ሆን።
18 ሙሴም በእግዚኣብሄር ትእዛዝ እጁን ዘርግቶ ተራሮችን መትቶ
መቅሰፍትን እንዳመጣ፣ እንዲሁም ክርስቶስ እጁን በመስቀል ላይ
ዘርግቶ ከሰዎች ላይ ኣጋንንትን ኣስወጣቸው። እግዚኣብሄር ሙሴን
"እጅህን ዘርጋ በብትር ምታ" ሲል በክርስቶስ እፀ መስቀል ኣማትብ
ወይም ባርክ ማለት ነው። እግዚኣብሄርም ሙሴን "እጅህን ዘርጋ"
ኣለው ማለት ክርስቶስ በእፀ መስቀል ላይ እጁን በመዘርጋት
ከጠላት ከመገዛት ኣዳነን። የእሱንም ህይወት ሰጠን ማለት ነው።
19 እስራኤልም ከኢኣማንያን ጋር ሲጣሉ ሙሴ ወደ ሲና ተራራ
መጣ። ኣሮንም ኣብሮ ሊፀልዩ ወጡ። ኣማሌቃውያን በርትተውባቸው
ነበርና። እግዚኣብሄርም እስራኤል ሃይልን እስኪያገኙ ድረስ እጅህን
ዘርጋ ሲል ሙሴን ኣዘዘው። በኦሪትም መፅሃፍ "የሙሴ እጆች
ፀሃይ እስኪገባ ድረስ የተዘረጉ ሆኑ"[104] ኣለ።
20 ነገር ግን የሙሴ እጆች ሲደክሙ ሲቸገርም እስራኤላውያን
ያልቃሉ። ጠላቶቻቸውም ያሸንፏቸዋል። እጁን ሲያነሳ ቀጥ
ኣድርጎም ሲዘረጋ ኣማሌቃውያን ይሸነፋሉ። እስራኤልንም
ያሳድዷቸዋል። ጠላቶቻቸውን ኣማሌቃውያንም ያሸንፏቸዋል።
21 ይህንንም ባዩ ጊዜ ኣሮንና ሆር በሙሴ ቀኝና ግራ ድንጋይ
ከመሩ። የሙሴን እጆች በከመሩት ድንጋይ ላይ ኣስደገፈው እጁን
ከተዘረጋችበት እንዳይመልስ የቀኙን ኣሮን፣ የግራውን ሆር
በትከሻዎቻቸው ላይ ያዙት።

[103] ዘፀኣ.7 ይመልከቱ።
[104] ዘፀኣ.17፥8-16

www.ethiopianorthodox.org

22 ወዘንተ እፌክር ለክሙ ጸብአ አማሌቅሰ ምስለ እስራኤል ጸብአ
መሃይምናን ምስለ አጋንንት ውእቱ። ወዘእንበለ ይሰቀል ክርስቶስ
ሞእዎሙ ለቀደምት ወሶበ ሰፍሐ እደሁ ዲበ ዕፀ መስቀል በእንተ
ኀጢአተ አዳም ወደቂቁ ወሶበ ሰፍሐ እደሁ ወተቀነወ እራት
ሞእዎሙ እለ ይትዐተቡ በመስቀሉ ለክርስቶስ።
23 ሰፍሐ እደሁ ለሙሴ ይተረጎሙ ስቅለቱ ለክርስቶስ ወዘነደቁ
አእባን አሮን ወሖር ይተረጉም ዕፀ መስቀል ወቅንዋት ወአሮን
ይተረጉም በፊያታዊ ዘየማን ወሆር በፊያታዊ ዘፀጋም ወአማሌቅ
ይትረጉም በአጋንንት ወንጉሦሙ ለአማሌቅ ይተረጉም በሰይጣን
ወአሜሃ ዘተመውኡ ውእቶሙ በትንሣኤሁ ለክርስቶስ ወበመስቀሉ
ሞእናሆሙ ለአጋንንት ወለሰይጣን።
24 ወካዕበ እመ ይወፅኡ እስራኤል እምግብፅ ወፅኡ ውስተ ማይ
መሪር።[105] ወኀጥኡ ዘይሰትዩ እምረተ ማዩ። ወቀዳሚ ነጐርጓር
አንጐርጐሩ በእንተ ምረተ ማይ። ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ
ንሣእ በትረከ ወደይ ውስቴቱ። ወዕተቦ ይምነ ወፅግመ። ወርኢ
በዝንቱ። ሶበ ይቤሎ እግዚአብሔር ይኩን ጥዑመ እመ ኢኮነኑ
ጥዑመ። ወባሕቱ ያርኢ ከመ በትእምርተ መስቀል ይሤኒ ኩሉ።
ወማይ መሪር ይከውን ጥዑመ ወኩሉ ዘማሰነ በኀይለ መስቀሉ
ለኢየሱስ ክርስቶስ ይከውን ሠናየ ወአዳመ።
25 ወባዕድኒ በዘእነግረከ እምካልአን ነቢያት በእንተ ስቅለቱ ይቤ
ዳዊት፣ ቀነዉኒ እደውየ ወእገርየ።[106] ዝኒ ገሀደ አርአየ በእንተ
ቅንዋተ እደዊሁ ወእገሪሁ ወካዕበ ይቤ አስተዩኒ ብሒአ ለጽምእየ።[107]
ዝኒ ገሀደ አርአየ ከመ ሰረበ ብሒአ በእንተ ስሕተቱ ለአዳም።
26 መንፈሰ ሕይወት ዘነፍሐ ላዕሌሁ ለአዳም ሰረበ ብሒአ ወእድ እንተ
ሣረረታ ለምድር ተቀነወት ዘበእንቲአሁ ለአዳም ተትሐተ ተወልደ
አያያተ ገብር ነሚአ።

## ፺ወ፱ በእንተ ፪ አግብርት

1 እስመ ብእሲ ንጉሥ ከመ ዘቦቱ ፪ አግብርት አሐዱ ዕቡይ ወጽኑዕ።
ወአሐዱ ትሑት ወድኩም። ወተገየሉ ውእቱ ዕቡይ ለውእቱ
ትሑት። ወዘበጦ ወቀተሎ ወሰለቦ።
2 ወርእዮሙ ንጉሥ እምልዑል መንበሩ። ወካዕበ ውእቱ ንጉሥ ወሪዶ
አኀዞ ለውእቱ ዕቡይ። ወዘበጦ፣ ወቀጥቀጦ፣ ወአሰሮ፣ ወወደዮ ውስተ
ቤተ ጽልመት።
3 ወለውእቱሰ ትሑት ወድኩም ገብሩ አንሥኦ፣ ወሐቀፎ፣ ወነገፎ ጸበሎ
ወኀፀቦ። ወሶጠ ቅብዐ ወወይነ ለቍስሉ ወጸዐኖ ዲበ አድጉ
ወአብጽሖ ውስተ ሀገሩ። ወአዕረጎ ዲበ መንበሩ። ወአንበሮ በየማኑ።

---

[105] ዘፀአ.15፡822-27
[106] መዝ.22፡16
[107] መዝ.69፡21

- 116 -

22 አማሌቃውያን ከእስራኤል ጋር ያደረጉት ጠብ ምእመናን
ከአጋንንት ጋር ከሚያደርጉት ጠብ ጋር ይመሳሰላል ስል
እተረጉምላችሁዋለሁ። ክርስቶስ ሳይሰቀል የመጀመሪያዎቹን
የመጨረሻዎቹ አሸነፏቸው። እጁን በአዳምና በልጆቹ ሃጢያት
ምክንያት በመስቀል ላይ በዘረጋ ጊዜና እጁን በተቸነከረ ጊዜ
በክርስቶስ መስቀል የሚባረኩት አሸነፏቸው።
23 የሙሴ እጅ መዘርጋት በክርስቶስ ስቅለት ይተረጎማል። አሮንና
ሆር የሰሩአቸው ድንጋዮች በእፀ መስቀልና በችንካሮች ይተረጎማሉ።
አሮንም በቀኝ በኩል በተሰቀለው ሽፍታ፣ ሆርም በግራ በኩል
በተሰቀለው ሽፍታ ይተረጎማሉ። የአማሌቅም ንጉስ በሰይጣን
ይተረጎማል። አማሌቃውያን መሸነፋቸውም በክርስቶስ ትንሳኤና
በመስቀሉ አጋንንትን ማሸነፋችን ነው።
24 ደግሞም እስራኤል በወጡ ጊዜ ወደ መራራ ውሃ ወጡ።[105]
ከውሃውም ምሬት የተነሳ የሚጠጡት አጡ። የመጀመሪያውም
ማጉረምረም በውሃው መራራነት የተነሳ ነው። እግዚአብሄርም ሙሴ
ን "ብትርህን ውሰድና በውስጡ ጨምረው። ወደግራና ቀኝም
ባርክ" አለው። እግዚአብሄር እንዲሁ "የጣፈጠ ይሁን" ቢል
የሚጣፍጥ ሊሆን አይችልም ነበርን? አይደለም። ሁሉ በትእምርተ
መስቀል እንዲያምር ያሳያል። የጠፋውም ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ
መስቀል ሃይል ያማረ ይሆናል።
25 ደግሞም ከሌሎች ነቢያት ስለ ስቅለቱ ዳዊት "እጆቼንና እግሮቼን
ቸነከሩኝ"[106] አለ። ይህም በግልፅ የእጆቼንና የእግሮቼን መቸንከር
አሳየ። ደግሞም "ለጥማቴ ሆምጣጤ አጠጡኝ"[107] አለ። ይህም
በግልፅ በአዳም ስህተት ምክንያት ሆምጣጤ እንደ ጠጣ አሳየ።
26 በአዳም ላይ የህይወት እስትንፋስን እፍ ያለው መንፈስ ሆምጣጤን
ጠጣ። ምድርን የሰራቻት እጅ ተቸነከረች። በአዳም ምክንያት
የባሪያ አምሳል ይዞ ተወለደ።

## ፺፱ ስለ ሁለቱ ባሪያዎች

1 አንድ ንጉስ፣ አንድ ትቢተኛና ብርቱ የሆነና ሌላው ደግሞ ትሁትና
ደካማ የሆነ ሁለት ባሪያዎች ነበሩት። ትቢተኛውም በትሁቱ ባሪያ ላይ
በረታበት። መታውና ገደለው። ሰለበውም።
2 ንጉሱም ከታላቅ ዙፋኑ ላይ ሆኖ አያቸው። ወርዶም ትእቢተኛውን
ያዘው። መታው። ቀጠቀጠው። አስሮም በጨለማ ቤት ውስጥ ጨመረው።
3 ያንን ደካማና ትሁት ባሪያውን አነሳው፤ አቀፈው፤ ትቢያውንም
አራገፈለት። አጥቦም ቅባትና ለቁስሉ ወይን አፈሰሰበት። በአህያው ላይ

---

[105] ዘፀአ.15፡22-27
[106] መዝ.22፡16-17
[107] መዝ.69፡21

www.ethiopianorthodox.org

4 ንጉሥሰ ክርስቶስ ውእቱ በአማን። ወአግብርትኒ ዘእቤ ሰይጣን ዕቡይ
ወአዳም ትሑት።
5 ወርእዮ ዘከመ ተኀየሉ ወአውደቆ ወረደ እምልዑል መንበሩ
ወአንሥኦ ለአዳም ገብሩ። ወአሰሮ ለሰይጣንሰ ውስተ ረዓደ ሲኦል
ወለሥጋ አዳም አንበሮ ዲበ መንበረ መለኮት። አዕበዮ ወአልዐሎ
ወአክበሮ። ወተሰብሐ እምነ ኩሎሙ እለ ፈጠረ መላእክት ወሊቃነ
መላእክት እልፍ አእላፋት ወትእልፌተ አእላፋት መንፈሳውያን።
6 እስመ አውደቆ ለዕቡይ ወአንሥኦ ለትሑት አኅሰሮ ለዕቡይ ወአክበሮ
ለትሑት አስቈረሮ ለዕቡይ። ወአፍቀሮ ለትሑት ተሀየዮ ለዝጉር
ወመሐሮ ለነዳይ እምልዕልና። አውደቆ ለዕቡይ። ወእመሬት አንሥኦ
ለምስኪን። እምክብሩ ነሠቶ ለኀያል። ወእሙስና አንሥኦ ለነዳይ።
እስመ ኀቤሁ ክብር ወኀሣር። ለዘፈቀደ ያከብር። ወለዘፈቀደ
ያኀስር።

## ፲ በእንተ እለ ተዐደዉ መላእክት

1 ወቦ ካዕበ ማላእክትሂ እለ ተምዕዖሙ እግዚአብሔር እስመ አእመሮ
ሙ ማእምረ ልብ ዘሐመይዎ ለአዳም እንዘ ይብሉ እምድኅረ
አፍቀሮ እግዚአብሔር ወወሀቦ ኪያነሂ ከመ ንትለአኮ ወእንስሳ
ወአራዊተ ወዓሣተ ባሕር ወአዕዋፈ ሰማይ ወኩሎ ፍሬያተ ወዕፀወ
ገዳም ወዓዲ ሰማያተ ወምድረ። ወወሀቦ ሰማየኒ ከመ ተሀቦ ዝናመ።
ወምድረኒ ከመ ተሀቦ ፍሬያተ። ወዓዲ ፀሐየ ወወርኀ ወሀቦ ፀሐይኒ
ከመ ያብርህ ሎቱ በመዐልት። ወወርኅኒ ከመ ያብርህ ሎቱ
በሌሊት። ለሐኮ በአጻብኢሁ። ወፈጠሮ በአምሳሊሁ ወሰዐሞ። ወነፍሐ
ላዕሌሁ መንፈሰ ሕይወት። ወይቤሎ ወልድየ በኵርየ ወፍቁርየ።
ወሤሞ ውስተ ገነት ከመ ይብላዕ ወይትፈጋዕ ዘእንበለ ደዌ
ወሕማም ዘእንበለ ጻማ ወስራሕ። ወአዘዞ ከመ ኢይብላዕ እምእሐቲ
ዕፅ። ወዘንተ ኩሎ እምድኅረ አወፈዮ ተዐደወ ወበልዐ እምይእቲ
ዕፅ። ወኮነ ጽሉአ ወምኑነ። ወሰደዶ እምገነት። እምይእዜሰ ቀበጸ
ተስፋሁ። እስመ ተዐደወ ትእዛዘ ፈጣሪሁ።
2 ወአውሥኦሙ እግዚአብሔር ለመላእክት እለ ሐመይዎ ከመዝ
ለአዳም። ወይቤሎሙ ለምንት ከመዝ ተሐምይዎ ለአዳም። እስመ
ሥጋ ወደም ውእቱ። ወሐመድ ወመሬት ውእቱ።
3 ወአውሥኡ መላእክት ወይቤልዎ ንንብብኑ ቅድሜከ እግዚእ
ኀጢአቶ ለአዳም።
4 ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ንብቡ ወእሰምዐከሙ። አነሂ ወአወስእከሙ
በእንተ አዳም ገብርየ። እስመ ተኬነወ እግዚአብሔር በእንተ አዳም።
እስመ ይቤ ፈጠርክዎ እመሬት። ወኢይገድፎ ለልሕኩትየ።



ጫነው። ወደ አገሩም አደረሰው። በዙፋኑም ላይ አወጣው።
በቀኙም አስቀመጠው።
4 በእውነት ንጉስ የተባለው ክርስቶስ ነው። ባሪያዎች የተባሉትም
እኩዩ ባሪያ የሰይጣን፣ ትሁቱ ባሪያ የአዳም ምሳሌዎች ናቸው።
5 ንጉሱም ትቢተኛው ባሪያ በትሁቱ ባሪያ እንደ በረታበትና እንደ
ጣለው ተመለከተ። ከታላቅ ዙፋኑም ላይ ወረደ። ባሪያውን አዳምን
አስነሳው። ሰይጣንንም ከሲኦል በታች አሰረው። የአዳምን ስጋ
በመንበረ መለኮት ላይ አስቀመጠው። አከበረው። ከፍ ከፍም
አደረገው። ከፈጠራቸው ሁሉ እልፍ አእላፋት ሺ እልፍ
መንፈሳውያን ከሊቃነ መላእክትም ይልቅ አከበረው።
6 ትእቢተኛውን አዋርዶታልና። ትሁቱንም አክብሮታልና። የተዋረደውን
አከበረው። ትእቢተኛውም ቸል ቸል አለው። ደሃውን ይቅር
አለው። ትእቢተኛውን ከታላቅነት አዋረደው። ትእቢተኛውን
ጣለው። ደሃውን ከመሬት አስነሳው። ሃያሉንም ከክብሩ አዋረደው።
ደሃውንም ከጥፋት አዳነው። ክብርና ሃሳር ከእሱ ዘንድ ነውና።
የወደደውን ያከብረዋል። የወደደውንም ያዋርደዋል።

## ፲ የእግዚአብሄርን ትእዛዝ ስለ ተላለፉ መላእክት

1 ከመላእክትም ውስጥ እግዚአብሄር የተቆጣባቸው አሉ። ምክንያቱም
አዳምን እግዚአብሄር ከወደደውና እኛ እንድንላከው ከሰጠው
በሁዋላ እንስሳትን፣ አራዊትን፣ የባህር አሶችንና የሰማይ ወፎችን፣
ፍሬዎችን፣ እንጨቶችን፣ ሰማያትንና ምድርን ከሰጠውና ሰማይም
ዝናምን፣ ምድርም ፍሬዎችን እንድትሰጠው ካደረገ በሁዋላ
ፀሃይንና ጨረቃን ከሰጠውና ፀሃይ በቀን፣ ጨረቃም በሌሊት
እንዲያበሩለት ከአደረገ በሁዋላ፣ በእጁ ከሰራውና በምሳሌም
ከፈጠረው ከሳመውም በሁዋላ፣ በላዩም ላይ የህይወት እስትንፋስን
እፍ ካለበትና የበኩር ልጄና ወዳጄ ካለውና በገነትም ውስጥ
ከሾመው በሁዋላ፣ ያለ በሽታና ህማም፣ ያለ ድካምና ውጣ ውረድ
ይበላ ዘንድና ደስ ይሰኝ ዘንድ በገነት ከሾመው በሁዋላ፣ ከአንዲት
እንጨትም በቀር ሁሉንም እንዲበላ ካዘዘውና ይህንን ሁሉ ከሰጠው
ይህንን ተላልፎ ከዚያች እንጨት ከበላ በሁዋላ የተጠላና የተናቀ
ሆነ። ከገነትም አባረረው። ከዚያ በሁዋላ ተስፋ ቆረጠ። የፈጣሪውን
ትእዛዝ ተላልፏልና አሉ።
2 አዳምን ያሙትን መላእክት እግዚአብሄር "ለምን እንደዚህ
ታሙታላችሁ? አዳም ስጋና ደም ነውና። አመድና መሬትም
ነውና" ሲል መለሰላቸው።
3 መላእክትም መልሰው "አቤቱ እኛ በፊትህ የአዳምን ሃጢአት
እንፈፅመው ኑሮአል?" ሲሉ መለሱለት።
4 እግዚአብሄርም "ተናገሩ፣ እኔም እሰማችሁአለሁ። ስለ ባሪያዬ ስለ
አዳምም እመልስላችሁአለሁ" አላቸው። እግዚአብሄር ስለ አዳም

www.ethiopianorthodox.org

እምጻእከዎ እምኀበ ኢሀሉ። ወኢይሬስዮ ስላተ ጸላኢሁ ለግብረ
እደውየ።
5 ወይቤሉ እሙንቱ መላእክት ስብሐት ለከ እግዚኦ እስመ አእመርከነ
ማእምረ አልባብ ከመ ሐመይናሁ ለአዳም በእንተ ዘተዐደወ ትእዛዘ
ዚኣከ ከመ ኢይብላዕ እምአሐቲ ዕፅ እምድኅረ አመስፈንኮ ላዕለ
ኵሉ ዘፈጠርከ ወሤምኮ ላዕለ ኵሉ ግብረ እደዊከ።
6 ወሶበ እመ ኢነገርኮ ወእመ ኢአዘዝኮ ከመ ኢይብላዕ እምይእቲ ዕፅ
እመ ኢኮኖ ጌጋየ ወሶበኒ በልዐ በኀጢአ መብልዕ እመ ኢኮኖ
ጌጋየ ። አላ አጠየቆ ቃለከ ወትቤሎ አመ በሊዐ ትበልዕ እምዝንቱ
ዕፅ ሞተ ትመውት።[108]
7 ወውእቱሰ እምድኅረ ሰምዐ ዘንተ ጠብዐ ወበልዐ ኢያኅጣእኮ
ዘይበልዕ ጥዑመ ፍሬያተ እምነ ገነት። ወኢያኅጣእኮ ዘይናዝዞ ወቢጸ
ዘይረድኦ ከማሁ። ወዘንተ ኵሎ ወአእመርከነ ወከሠትከነ ለከ ከመ
ተዐደወ ትእዛዘከ።
8 አውሥአሙ መሓሪ ወመፍቀሬ ምሕረት ህየንተ አዳም ወይቤሎሙ
አንትሙሰ ፩ ሕሊና ፈጠርኩክሙ ለስብሐት እምእሳት ወነፋስ።
ወሎቱሰ ፈጠርክዎ ምክዕቢተ ዚኣክሙ እመሬት ወእማይ እምነፋስ
ወእሳት። ወኮነ ዘሥጋ ወደም። ወቦቱ ፲ ሕሊናት። ፭ ዘሠናያት።
ወ፭ ዘእኩይ። ወለእመ አጥብዐ ልቡ ለሠናይ የሐውር በሕሊና
ሠናይ። ወለእመሰ አስሐቶ ዲያብሎስ የሐውር ኀቤሁ በፍኖት
እኩይ።
9 ወአንትሙሰ አልብክሙ ባዕደ ሕሊና ዘእንበለ ስብሐትየ ዘእንበለ
ውእቱ ዕቡይ ዘአሥረፃ ለእከይ። ወኮነ እኩየ። ወተሰዕረ
እማኅበርክሙ። ወአንትሙኒ ለምንት ትትዔበዩ ላዕለ አዳም። ወሶበ
ኮንክሙ ከማሁ ወፈጠርኩክሙ እማይ ወእመሬት እምኮንክሙ ሥጋ
ወደመ ወእም አፈድፈድክሙ እምኔሁ ዐሊወ ትእዛዝየ ወክሒደ
ቃልየ።
10 ወይቤልዎ ስብሐት ለከ እግዚኦ። ሐሰ ለነ ኢንትዐደው ትእዛዘከ።
ወኢነዐሉ ቃለከ። እስመ ንሕነ መንፈሳውያን ለሕይወት። ወውእቱሰ
መሬታዊ ለእበድ። ወይእዜኒ እመ ንክል ጥዩቀ ፍትነነ ወአመክረነ
ከመ ታእምር ለእመ ንክል ዐቂበ ቃልከ።
11 ወሶበ ከመዝ ተመክሑ ይቤሎሙ እግዚአብሐር መፍቀሬ ሰብእ
እምከመሰከ ተስሕትክሙ በዐሊወ ቃልየ ግፍዕክሙ ላዕለ ርእስክሙ።
ሐረረት ገሀነም ወእሳት ወተይ ወመርቄ ወአውሎ ምንባሪክሙ እስከ
ዕለት ዐባይ ትትዐቀቡ በሰናስል ዘኢይትፈታሕ ወኢይሰበር እስከ
ለዓለም።
12 ወለእመሰ ጥዩቀ ዐቀብክሙ ቃልየ ወገበርክሙ ትእዛዝየ ትነብሩ
በየማንየ ወበፀጋምየ። እስመ ኵሉ ዘሞአ ኀየለ። ወዘሰ ተመውአ
ተኀየለ።

108 ዘፍጥ.2፥17



ተጠብ፯ልና። "ካፈር ሰራሁት። የእጄንም ስራ አልተወውም። ካልነበረበት
አመጣሁት።የእጄንም ስራ የጠላቶቹ መዘባበቻ አላደርገውም" ብ፯ልና።
5 መላእክቱም "አቤቱ ለአንተ ምስጋና ይገባል። ልብን የምትመረምር
እንደ መሆንህ መጠን አዳምን በፈጠርከው ሁሉ ላይና በእጅህ
ስራ ሁሉ ላይ ከሾምከው በሁዋላ ከአንዲት እፅ ግን እንዳይበላ
ያዘዝከውን የአንተን ትእዛዝ እንደ ተላለፈ ያማነውን ሃሜት
አውቀሃል።
6 ከዚህች እንጨት እንዳይበላ ባልነገርከውና ባላዘዝከው በደል
ባልሆነበትም ነበር። መብል አጥቶ ቢበላ ኑሮ ሃጢአት ባልሆነበት
ነበር። ነገር ግን በቃልህ አስረዳህው። ከዚህች እንጨት ብትበላ
የሞት ሞትን ትሞታለህ[108] አልከው።
7 እሱ ግን ይህንን ከሰማ በሁዋላ ጨክኖ በላ። ከገነትም ውስጥ
የሚመገባቸው የጣፈጡ ፍሬዎችን አላሳጣህውም። የሚያረጋጋውና
የሚረዳው እንደ እሱ ያለ ጓደኛ አላሳጣህውም። ይህንን አልን።
አንተም ይህንን አሳወቅህን። ትእዛዝህንም እንደ ተላለፈ
ገለፅክልን" አሉት።
8 ቸርና ይቅርታን ወዳጅ አምላክም ስለ አዳም ሆኖ መለሰላቸው።
አላቸውም። "እናንተ አንድ ሃሳብ ናችሁ። እኔም ለምስጋና
ከእሳትና ነፋስ ፈጠርኳችሁ። እሱ ግን ከእናንተ እጥፍ ከመሬትና
ከውሃ ከነፋስና ከእሳት ፈጠርኩት። ከስጋና ከደምም ሆነ። አምስቱ
የመልካም፣ አምስቱ የክፉ የሆኑ አስር ህሊናዎች አሉት። ልቡ
ለበጎ ከጨከነ በመልካም ህሊና ይሄዳል። ዲያቢሎስ ካሳተው ግን
በክፉ መንገድ ወደ እሱ ይሄዳል።
9 እናንተ ክፋትን ካስገኛት ከትእቢተኛው የተለየ ህሊና የላችሁም።
እሱ ግን ክፉ ሆነ። ከማህበራችሁም ተሻረ። እናንተስ ታዲያ ለምን
በአዳም ላይ ትኮራላችሁ። እንደ እሱ ብትሆኑ ኑሮ፣ ከውሃና
ከመሬት ፈጥሬአችሁ ቢሆን ኑሮ ስጋና ደም በሆናችሁ ነበር።
ትእዛዜንና ቃሌን በመተላለፍ ከእሱ በበለጣችሁ ነበር።"
10 እነሱም "አቤቱ ምበጋና ለአንተ ይገባል። ትእዛዝህን እንደ
አንተላለፍና ቃልህንም እንዳንሽር ወዮልን። እኛ ለህይወት
መንፈሳዋውያን ነንና። እሱ ግን ለእብደት መሬታዊ ነው። ዛሬም
ደግሞ እንችል እንደሆነ ፈፅመህ ፈትነን። ሞክረንም" አሉት።
11 እንዲህ በተመኩ ጊዜ ሰውን ወዳጁ እግዚአብሄር "ቃሌን በመተላለፍ
ብትሳሳቱ ግፋችሁ በራሳችሁ ላይ ነው። ገሃነም ትቃጠላለች። እሳት፣
ድኝ፣ በረዣና አውሎ መኖሪያችሁ ይሆናል። እስከ ታላቂቱ ቀን ድረስ
በማይፈታ ሰንሰለት ታስራችሁ ትጠብቃላችሁ። እስከ ዘላለሙም አይሰ
በርም።
12 በእርግጥ ቃሌን ብትጠብቁና ትእዛዜን ብታደርጉ ግን በቀኙና በግራዩ
ትቀመጣላችሁ። ያሸነፈ ሁሉ ይበረታል፤ የተሸነፈም ይደክማል።

108 ዘፍጥ.2፥17

www.ethiopianorthodox.org

13 እስመ ሰይጣንሂ አልቦ ኀይለ ዘእንበለ ዳእሙ ዘያሠርፅ ውስተ
ሕሊና ወኢይኤዝዝ ወኢያጌብር ወኢይዘብጥ ወኢይስሕብ ወኢይእኀዝ
ወኢይትዋሣእ።
14 አላ በጽሚት ያሰርፅ ውስተ ሕሊና ወዘተሠጥዎ ለኀሊና እኩይ
ይሬስዮ ለሀጕል ወእመሰ ሞአ ለኀሊና እኩይ ረከበ ሞገሰ ወይከውኖ
ምዝጋና እስከ ለዓለም።
15 ወአንትሙኒ በከመ ፈቀድክሙ ይኩን ላዕሌክሙ ኀሊና ሰብእ ወሥጋ
ሰብእ። ወባሕቱ ዑቁ ርእሰክሙ። ኢትትዐደዉ እምቃልየ።
ወኢትዕልዉ ትእዛዝየ። ወኢታርኵሱ ርእሰክሙ። ኢበመብልዕ
ወኢበመስቴ ወኢበዝሙት ወኢበዘኮነ ኢትዕድዉ እምቃልየ።
16 ወሶቤሃ ተውህቦሙ ምስለ ቃሉ ሥጋ ወደም ወልበ እጓለ
እመሕያው ወተወርዉ እመልዕልተ ሰማይ ወወረዱ ምድረ ኀበ እበደ
ዘፈኖሙ ለደቂቀ ቃየን ምስለ ኵሉ ኪኖሙ ዘተኬነዉ በእበደ
ዝሙቶሙ ወማኅሌቶሙ በከበሮ ወበመሰንቆ ወበእንዚራ ወበረዓም
ብዙኅ ምስለ ይባቤ ወማኅሌት።
17 ወአዋልዲሆሙኒ ህየ ሀለዋ ወይትዋነያ ዘእንበለ ኀፍረት። እስመ
ተምዕዛ ሎሙ ወአደማሆሙ ወሆካ ኀሊናሆሙ። ወኢተዐገሡ አሐተ ሰ
ዐተ። አላ ነሥኡ ሎሙ ለርእሶሙ እምኔሆን ዘኀረዩ አንስትያ።
ወአበሱ ምስሌሆን። እስመ እግዚአብሔር ኢየዐርፍ ውስተ ልበ
ዕቡያን ወሐማይያን። አላ የዐርፍ ውስተ ልበ ትሑታን ወየዋሃን።
ወበወንጌልሂ ነገረ እንዘ ይብል አሌ ሎሙ ለእለ ያጸድቁ
ርእሶሙ።[109] ወይሜንኑ ቢጾሙ። ወካዕበ ይቤ እስመ እግዚአብሔር
ያፈቅሮሙ ለትሑታን። ወያኀሥሮሙ ለእለ ያዐብዩ ርእሶሙ።
18 ወሶቤሃ ተምዕዖሙ እግዚአብሔር ወአሰሮሙ ውስተ ረዐደ ሲኦል
እስከ ዕለተ ፍዳ። በከመ ይቤ ሐዋርያ ለመላእክቲሁ አቢሶሙ ጥቀ
ኢመሐኮሙ አላ ውስተ ደይን አንበሮሙ። ወተአሠሩ ለዕለት
ዐባይ።[110] ሞአ ቃለ እግዚአብሔር ዘተኬነወ በልሕኵቱ አዳም።
ወተሞውኡ እለ ሐመይዎ ወተሳለቁ ላዕሌሁ ለአዳም።
19 ወእለሰ ትስሕቱ ቦቶን መላእክት አዋልደ ቃየን ፀንሳ ወስዕና ወሊደ
ወሞታ። ወእለ ውስተ ከርሦንሂ ቦ እለ ሞቱ። ወቦ እለ ወፅኡ
ሠጢጦሙ ከርሠ እሞሙ ወፅኡ እንተ ሕንብርቲሆን።
20 ወሶበ ልህቁ ወተሐፅኑ ኮኑ ረዐይተ እለ ኑኖሙ ይበጽሕ እስከ
ደመናት። ወበእንቲአሆሙ ወበእንተ ኀጥአን አንኀ መዐቶ ላዕሌሆሙ
እግዚአብሔር ወይቤ ኢይንበር መንፈስየ ላዕሌሆሙ ዘእንበለ ፻ወ፳
ዓመት።[111] ወአኅለቆሙ በማየ አይኅ ሎሙኒ ወለኵሎሙ ኀጥአን እለ
አልቦሙ አሚነ በቃለ እግዚአብሔር ወእለሰ አምኑ በቃለ
አበዊሆሙ ወገብሩ ፈቃዶ አልቦ ዘረከቦሙ እኩይ እምውእቱ አይኅ

[109] ሉቃ.18፥9
[110] 2ጴጥ.2፥4
[111] ዘፍጥ.6፥2-4



13 ሰይጣንም ደግሞ በሰው ሃሳብ ውስጥ ክፉት እንዲሰርፅ ያደርጋል
እንጂ ሌላ ሃይል የለውም። አያዝዝም። አያስርም። አይመታም።
አይጎትትም። አይዝም። ቃል በቃል አይናገርም።
14 ግን ቀስ ብሎ በህሊና ያሰርፃል። ክፉውን ህሊና የተቀበለውን
ለጥፋት ያደርገዋል። ክፉውን ህሊና ካሸነፈ ግን ሞገስን አገኘ።
ለዘላለሙም ምስጋና ይሆንለታል።
15 እናንተም እንደ ወደዳችሁ በላያችሁ ላይ የሰው ህሊናና የሰው
ስጋ ይሁንባችሁ። ነገር ግን ከቃሌ እንዳትተላለፉና ትእዛዜን
እንዳትክዱ ለራሳችሁ እወቁ። በመብልም ቢሆን፣ በመጠጥም ቢሆን፣
በሆነውም ነገር እራሳችሁን አታርክሱ። ከቃሌ አትተላለፉ"አላቸው።
16 ወዲያውኑ ከቃሉ ጋር ስጋና ደም፣ የሰው ልብም ተሰጣቸው።
ከሰማይም ወደ ምድር ተጣሉ። ወደ ቃየን ልጆች ዘፈንና፣ ዝሙት
እብደት፣ በከበሮ፣ በመሰንቆና በእንዚራም በብዙ ጩሀት ወደሆነው
ዘፈናቸውና እልልታቸው ሄዱ።
17 ሴቶች ልጆቻቸውም ከዚያ ነበሩ። ያለ ሃፍረትም ይጫወቱ ጀመር።
ሽቶ ተረብርበው ደስ አሰኝተዋቸው ነበርና ህሊናዎቻቸውም
ታወኩ። እያንዳንዳቸው ለራሳቸው የመረጧቸውን ሚስቶች ወሰዱ
እንጅ አንድ ሰአት እንኳን መታገስ አልተቻላቸውም። ከእነሱም
ጋር በደሉ። "እግዚአብሄር በተዋረዱትና በየዋሃን ልብ ያድራል
እንጂ በትእቢተኞችና በየዋሃን አያድርምና እራሳቸውን የሚያፀድቁ፣
ጓደኞቻቸውንም የሚንቁ ወዮላቸው"[109] ሲል በወንጌል ተናገረ።
ደግሞም እግዚአብሄር የተዋረዱትን ይወዳቸዋል። እራሳቸውንም ከፍ
የሚያደርጉትን ይንቃቸዋል አለ።
18 ያንጊዜም እግዚአብሄር ተቆጣባቸው።በሲኦል መውረጃም እስከ ፍርድ
ቀን አሰራቸው። ሃዋርያው "እስከ ፍርድ ቀን አስቀመጣቸው።
ለታላቁ ቀንም ታሰሩ እንጂ አልራራላቸውም"[110] መላእክቱ ፈፅመው
በድለዋልና እንዳለው አዳምን በመስራት የተጠበበው የእግዚአብሄር
ቃል አሸነፈ። ያሙትና በአዳም ላይ የተሳለቁት ተሸነፉ።
19 መላእክት የተሳሳቱባቸው የቃየል ሴቶች ልጆችም ፀነሱ።
መውለድም ተሳናቸው። ሞቱም። ከፅንሶቹም የሞቱ ነበሩ።
የእናቶቻቸውንም ሆድ ቀደው የወጡ ነበሩ። በእንብርቶቻቸው ወጡ።
20 ባደጉም ጊዜ ቁመታቸው እስከ ደመናት የሚደርስ ሃይለኞች ሆኑ።
በሃጥአንና በእነሱ ምክንያት እግዚአብሄር መአቱን አራዘመ።
"መንፈሴ ከመቶ ሃያ አመት በላይ በእነሱ አይኖርም"[111] አለ።
እነሱንና በእግዚአብሄር ቃል እምነት የሌላቸውን ሃጥአንን ሁሉ
በጥፋት ውሃ ጨረሳቸው። በአባቶቻቸው ቃል ያመኑና ፈቃዱን
ያደረጉ ከዚህ የጥፋት ውሃ ያገኛቸው ክፉ ነገር አልነበረም።

[109] ሉቃ.18፥9
[110] 2ጴጥ.2፥4
[111] ዘፍጥ.6፥2-4

www.ethiopianorthodox.org

አላ አድኅኖሙ እንዘ ይብል ለእመ አመንከ ቃልየ ትክል ድኂነ
እምአይኅ።
20 ወይቤ ኖኅ አመንኩ እግዚኦ ቃለከ ወአይድዐኒ በዘእድኅን በዕፀ
ትድኅን እማይ ወይቤ እፎ እግዚእየ ወይቤሎ ግበር ታቦተ ርብዕተ
ወጽርባ ወግበር ላቲ ፫ ውሣጥያተ ወባእ ውስቴታ ምስለ ኵሉ
ቤትከ።[112] ወአምነ በቃለ እግዚአብሔር ወገብረ ወድኅነ።

21 ወበእንተዝ ስምዑኒ እፌክር ለክሙ። ሶበ አዘዞ እግዚአብሔር
እምወሀቦ ክንፈ ከመ ንስር። ወእምአዕደዎ ብሔረ ሕያዋን ምስለ
ኵሉ ቤቱ እስከ ያቁርር መዐተ ላዕለ ኀጥኣን እለ ኢየአምሩ ቃለ
እግዚአብሔር ወቃለ አበዊሆሙ አው አምአዕረጎ እስከ አየር አው
እምአዘዞ ለማየ አይኅ ከመ አረፍት ከመ ኢይቅረባ ለአሐቲ ደብር
ኀበ ያነብሮ ለኖኅ ወለደቂቁ ወለእለ ፈቀደ አራዊተ ወእንስሳ ከመ
ኢይድፍኖሙ።

22 ወባሕቱ ዘንተ አእምሩ ከመ ሠምረ እግዚአብሔር በዕፅ ዘተቀደሰ
ኮነ መድኀኒተ ፍጥረቱ። እሉ ታቦት ወዕፀ መስቀል። ይቤሎ ግበር
በዘ ትድኅን። ዛቲኬ ታቦት ዘቤተ ክርስቲያን። ወሶበኒ ይቤሎ ግበር
ርብዕተ ያርኢ ዝኒ ከመ በርባዔ ትእምርተ መስቀል። ፬ መአዝኒሃ
ለታቦት። ዝውእቱ አቅርንተ ምሥዋዕ በከመ አዘዞ ለሙሴ ይግበር
ታቦተ እምዕፅ ዘኢይነቅዝ።

23 ወአነ እቄድሶ ለከ በይእቲ ግብረ እደየ ሰማያዊት መንፈሳዊት።
ወአንተኒ ቀድስ ርእሰከ እምግሙና ወርኵስ ወዝሙት ወቂም
ወሐሰት ምስለ እጐከ ወቤትከ ንጹሕ። በንጹሕ ሠዕ ሊተ። ወአነ
እትዌከፍ ለከ እምድኅረ ቀደስከ ርእሰከ ወቤተከ። አዝዞሙ ለኵሉ
ሕዝብ ይቀድሱ ርእሶሙ።

24 እስመ ቅድሳትየ ለቅዱሳን ዘንተኬ ተኀሥሥ ታቦተ ኪዳንየ እንተ
ፈጠርክዋ ለስብሐትየ ወለእመ መጻእክሙ በንጹሕ ልብ በፍቅር
ወበሰላም ዘእንበለ ተቃጽቦ ወተሐምዮ ወአርታዕክሙ ልበክሙ ሊተ
ወለቢጽክሙ እሰምዐክሙ ጸሎተክሙ ወአፀምዕ ስእለተክሙ በኵሉ
ዘተጋነይክሙ ሊተ ወእመጽእ ወእሄሉ ምስሌክሙ። ወአንሶሱ
ማእከሌክሙ። ወአኀድር ውስተ አልባቢክሙ። ወትከውኑኒ ሕዝብየ።
ወእከውነክሙ አምላከክሙ በጽድቅ።

[112] ዘፍጥ.6፥14…

- 120 -

"ነገር ግን ቃሌን ብታምኑ ከጥፋት ውሃ መዳን ትችላላችሁ" ሲል
ኣዳናቸው።
20 ኖህም "ኣቤቱ ቃልህን ኣምኛለሁና የምድንበትን ንገረኝ" ኣለው።
እሱም "ከጥፋት ውሃ በእንጨት ትድናለህ ኣራት ፎቅ ያላትን
መርከብም ስራ። ጥረባት። ሶስት ክፍልም ኣድርግላት። ከቤተ ሰ
ብህም ሁሉ ጋር ወደ ውስጥ ግባ"[112] ኣለው። በእግዚኣብሄርም
ቃል ኣምኖ ሰራ። ዳነም።
21 ይህንንም እተረጉምላችሁዋለሁና ስሙኝ። እግዚኣብሄር ቢያዝዝ
የእግዚኣብሄርን ቃልና የኣባቶቻቸውን ቃል ባላመኑት ሃጥኣን ላይ
መኣቱን እስኪያቀዘቅዝ ድረስ እንደ ኣሞራ ክንፍን በሰጠውና
ከቤተሰቡ ሁሉ ጋር ብሄረ ህያዋን ባሻገረው እስከ ኣየርም
ባወጣው ነበር። ወይም ኖህንና ልጆቹን ከሚያስቀምጥበት ተራራ
ኣጠገብ እንደ ግድግዳ እንዳይቀርብ የጥፋት ውሃን ባዘዘው ነበር።
እንዲሁም የወደዳቸውን ኣራዊትና እንስሳ እንዳይደፍናቸው ባዘዘው
ነበር።
22 ነገር ግን እግዚኣብሄር በቀደሰው እንጨት የፍጥረቱን ድህነት
ሊያደርግ እንደ ወደደ ኣወቁ። እነሱም መርከቢቱና እፀ መስቀሉ
ናቸው። የምትድንበትን ታቦት ኣድርግ ኣለው። ይህችም የቤተ
ክርስቲያን ታቦት ናት። ኣራት ክፍል ኣድርገህ ስራ ሲለውም
ትምህርተ መስቀል ኣራት ማእዘን እንደሆነ ያሳያል። እሊህም
ሙሴን ከማይነቅዝ እንጨት ታቦት እንዲሰራ እንዳዘዘው የታቦትም
ኣራት ማእዘን ኣቅርንተ ምስዋእ የሚባሉት ናቸው።
23 "እኔም ዳግም በዚህች ሰማያዊትና የእጄ ስራ እቀድስሃለሁ።
ኣንተም ደግሞ ከእድፈት፣ ከርኩሰት፣ ከዝሙት፣ ከቂም፣ ከሃሰት፣
ወንድምህና ከንፁህ ወገንህ ጋር ራስህን ቀድስ። በንፅህና ሰዋልኝ።
እራስክንም ከቀደስክ በሁዋላ እኔ እቀበልሃለሁ። ህዝቡም ሁሉ
እራሳቸውን ይቀድሱ ዘንድ እዘዛቸው" ኣለው።
24 "ቅድስናየ ለቅዱሳን ነውና ለምስጋናየ የፈጠርኳት የቃል ኪዳኔን
ታቦት ይህንን ትፈልጋለች። በንፁህ ልብ፣ በፍቅርና በሰላም፣ ያለ
መጠቃቀስና ያለ መተማማት ብትመጡና ልባችሁን ለእኔና
ለባልንጀሮቻችሁ ብታቀኑልኝ፣ ፀሎታችሁን እሰማችሁኣዋለሁ።
በተገዛችሁልኝ መጠን ሁሉ ልመናችሁን ኣዳምጥላችሁዋለሁ።
እመጣና ከእናንተ ጋር እኖራለሁ። በመካከላችሁም እመላለሳለሁ።
በልባችሁም ውስጥ ኣድራለሁ። ህዝቤ ትሆኑኛላችሁ። እኔም
በእውነት ኣምላካችሁ እሆናችሁዋለሁ።"

[112] ዘፍጥ.6፥14

www.ethiopianorthodox.org

## ፲ወ፭ በእንተ ህላዌ ኩሉሄ

1 ወካዕበ ይቤሎ ግበር ላቲ ዐፀደ ቀዳሚ ደደ ከመ ኢይባእ ህየ
ሥኡብ ወርኩሰ ወዘኢኮነ ንጹሐ እስመ አነ እሄሉ ኀቤሃ ወአኮ ህየ
ባሕቲታ አላ ኀበ ኩሉ አምሳሊሃ ኀበ ይጼዋዕ ስምየ በንጹሕ።
2 ሀሎኩ ምስለ ዳንኤል ውስተ ግብ ወሀሎኩ ምስለ ዮናስ ውስተ
ከርሠ ዐንበሪ። ወሀሎኩ ምስለ ዮሴፍ ውስተ ግብ። ወሀሎኩ ምስለ
ኤርምያስ ውስተ ዐዘቅተ ዐምዐም።
3 ሀሎኩ አዐምድ ታሕተ መትሕተ ታሕቲት ከመ ኢይሰጠሙ አድባር
መትሕተ ማያት። ወሀሎኩ መትሕተ ማያት ከመ ኢይሰጠሙ ላዕለ
እሳት ወተይ። ሀሎኩ አዐምደ መትሕተ እሳት ወተይ ከመ ኢይሰ
ጠሙ መልዕልተ ነፋሳት ወዛሕል። ሀሎኩ መትሕተ ነፋሳት ወዛሕል
ከመ ኢይሰጠሙ መትሕተ ጽልመት። ወመትሕቴሃኒ ለጽልመት
ወለቀላያት አነ አዐምድ።
4 ወኀቤየ ያሰምክ ኩሉ ፍጥረት። ወኪያየ ይጸወን ኩሉ ዘፈጠርኩ።
ሀሎኩ መልዕልተ ምድር። ወሀሎኩ አጽናፈ ዓለም። እሰፍን ኩሉ።
ሀሎኩ በአየር ማኅደርየ።
5 ወሀሎኩ መልዕልተ ሰረገላ ኪሩቤል። እሴባሕ ወትረ እምኩሉ
መላእክት ወሰብእ ቅዱሳን። ወሀሎኩ መልዕልተ አርያም። እመልእ
ኩሉሄ። ሀሎኩ መልዕልተ ፯ ሰማያት። እሬኢ ኩሉ ወእፈትን ኩሉ
ወአልቦ ዘይሴወር እምኔየ። አነ ህልው ውስተ ኩሉ መካን።
6 ወአልቦ ባዕደ አምላክ ዘእንበሌየ። በሰማይ በላዕሉ ወበምድር
በታሕቱ። አልቦ ዘይመስል ኪያየ ይቤ እግዚአብሔር። እደየ ሣረረታ
ለምድር ወየማንየ አጽንዐታ ለሰማይ። አነ ምስለ ወልድየ ወመንፈስ
ቅዱስ።

## ፲ወ፮ በእንተ ቀዳሚ

1 በከመ ዳዊት ተነበየ በአፈ መንፈስ ቅዱስ እንዘ ይብል ምስሌከ
ቀዳማዊ በዕለተ ኀይል።[113] ማዕዜ ይእቲ ዕለተ ኀይል ብሂል። አኮኑ
አመ ፈጠረ ክርስቶስ ቃለ አብ ሰማየ ወድረ።
2 እስመ ይቤ ሙሴ ውስተ ርእሰ መጽሐፍ በቀዳሚ ገብረ
እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ።[114] ለብዉኬ በቀዳሚ ብሂል በክርስቶስ
ብሂል። ቀዳሚ ትርጓሜሁ ክርስቶስ። ይቤ ዮሐንስ ወልደ ዘብዴዎስ
ሐዋርያ በእንተ ክርስቶስ ዝ ውእቱ ቀዳሚ ዘሰማዕነ ወዘርኢነ

---

[113] መዝ.110፥3
[114] ዘፍጥ.1፥1



## ፲፭ ለዘላለም ስለ መኖር

1 ደግሞም አለ። "ተዳዳፊ፣ ርኩስና ንፁህ ያልሆነ ከዚህ እንዳይገባ
በመጀመሪያው በር አጥር አድርግልኝ። እኔ ከእሷ ጋር
እኖራለሁና። ከእሷ ጋር ብቻ ሳይሆን ስሜ በንፁህ በሚጠራበትና
እሷን ከመሰለው ሁሉ ጋር በዚያ አለሁና እሷ ብቻዋን
አይደለችም።
2 ከዳንኤል ጋር በጉድጓድ፣ ከዮናስ ጋር በአሳ ነባሪ ሆድ፣ ከዮሴፍ
ጋር በጉድጓድ ውስጥ፣ ከኤርምያስም ጋር በቆሻሻ መጣያ ውስጥ
ነበርኩ።
3 ከውቅያኖስ በታች ያሉት ተራሮች እንዳይደረመሱ ከሁሉም በታች
ምሰሶ ሆንኩ። በእሳት ድኝ ላይ እንዳይፈሱ በውሃዎች በታች ምሰ
ሶ ሆኛለሁ። በነፋሳትና በዝገት በጨለማም ቦታ እንዳይሰጥሙ እኔ
በእሳትና በድኝ በታች ምሰሶ ሆኜ በዚያ አለሁ። በጨለማውና
በውቅያኖስም በታች እንዳይሰጥሙ እኔ በነፋሳትና በዝገት
በጨለማም ቦታ ምሰሶ ሆኜ በዚያ አለሁ።
4 ፍጥረት ሁሉ በእኔ ላይ ይደገፋል። የፈጠርኩትም ሁሉ እኔን
መከታ ያደርጋል። በምድር በታች አለሁ። በዓለምም ዳርቻ አለሁ።
በሁሉ ላይ እሆን ዘንድ በማደሪያዬ በሰማይ አለሁ። በሰረገላዎች
በኪሩቤልም ላይ አለሁ።
5 ከሁሉም መላእክትና ከቅዱሳን ሰዎች ሁልጊዜ እመሰገናለሁ። ከሰ
ማይ በላይ አለሁ። ሁሉንም እመላለሁ። ከሰባቱ ሰማያት በላይ
አለሁ። ሁሉን አያለሁ። ሁሉን እፈትናለሁ። ከእኔ የሚሰወር
የለም። በቦታ ሁሉ እኖራለሁ።
6 ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ የለም። በላይ በሰማይ፣ በታችም በምድር
ቢሆን እኔን የሚመስል የለም። እግዚአብሄርም አለ። ምድርን
እጄ ሠራቻት። ቀኜም ሰማይን አፀናቻት። እኔ ከወልድና ከመንፈስ
ቅዱስ ጋር አለሁ።"

## ፲፮ ስለ መጀመሪያው

1 ዳዊት በመንፈስ ቅዱስ አፍ "ቀዳማዊ ከአንተ ጋር በሃይልህ ቀን"[113]
ሲል እንደተናገረ ይህች የሃይል ቀን የተባለች መች ናት? የአብ ቃል
የሆነው ክርስቶስ ሰማይና ምድርን የፈጠረባት ቀን አይደለችምን?
2 ሙሴም በመጽሃፉ "መጀመሪያ እግዚአብሄር ሰማይና ምድርን
ፈጠረ"[114] ብሏልና። በመጀመሪያ ማለት ትርጉሙ በክርስቶስ ማለት
ነው። ሃዋርያው የዘብዴዎስ ልጅ ዮሃንስ ስለ ክርስቶስ "ከመጀመሪያ

---

[113] መዝ.110፥3
[114] ዘፍጥ.1፥1

www.ethiopianorthodox.org

ወዘጠየቅነ ወዘገሠሣ እደዊነ። ወንዜንወክሙ ከመ ኮነ ክፍልነ ምስሌሁ
ወአንትሙኒ እለ አመንክሙ በቃልነ ትከውኑ ክፍለ ምስሌነ።[115]
3 ወበከመ ይቤ ሉቃስ ረድእ በግብረ ሐዋርያት ቀዳሚሁ ለነገር ገበርነ
በእንተ ኩሉ።[116] ወዘንተ ዘይቤ ክርስቶስ ኮነ ቤዛ ኩሉ ወንሕነኒ
አመነ ቦቱ።
4 ወማርቆስ ወንጌላዊ ውስተ ርእሰ መጽሐፉ ጸሐፈ ወይቤ ቀዳሚሁ
ለወንጌለ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር።[117] ወዝንቱኒ ብሂል
ክርስቶስ። ስብከትኒ ለነቢያት ወሐዋርያት ወኀበርነ በጸጋሁ።
5 ወካዕበ ዮሐንስ ወንጌላዊ ጸሐፈ እንዘ ይብል ቀዳሚሁ ቃል ውእቱ።
ወውእቱ ቃል ኀበ እግዚአብሔር ውእቱ።[118] ወዳግመ አጠየቀ ቃሉ
ወይቤ። ወከማሁ ቀዳሚሁ እግዚአብሔር ውእቱ ቃል። ይእዜኒከ
ጠይቅ ከመ ውእቱ ቃለ አብ ክርስቶስ ውእቱ። በዘቦቱ ገብረ ሰ
ማየ ወምድረ ወኩሎ ፍጥረተ ውእቱ ፈጠረ። ወዘእንበሌሁሰ አልቦ
ዘኮነ ወኢምንትኒ።[119] ይቤ ወኮኑ ወውእቱ አዘዘ ወተፈጥሩ።
6 ወሣልስ ክብር ስማዕ። ወበእስትንፋሰ አፉሁ ኩሉ ኀይሎሙ። ዝኒ
ያርኢ ለመንፈስ ቅዱስ ዘተብህለ ጥዩቀ።
7 ወምንተ ንብል ንብከዮሙ አሌ ሎሙ ለአይሁድ ወለአረሚ እለ
ዐውከኩ እምጽድቅ ወአበዩ ገንየ ለፍቅረ እግዚአብሔር እንተ አፍቀሮ
ለሰብእ በጊሩቱ። እስመ እምድኅረ ተገድፈ አዳም በዕልወቱ አድኅኖ
በዕበየ ምሕረቱ ተሰቂሎ ዲበ ዕፀ መስቀል ወተቀኒዎ በቅንዋት
እደዊሁ ሰፊሖ እራሒ በትሕትና አጽኒኖ ርእሶ በእንቲአነ። ሐመ
ዘኢይደልዎ ሕማም በዕበየ መለኮቱ ዘለዓለም ሞተ ከመ ይሥዐሮ
ለሞት ደክመ ከመ ያጽንዖ ለድኩም መሬታዊ። ጸሚአ ሰረበ ብሒአ
ተከሊሎ አክሊለ ሦክ። ኢፈርሀ ወኢኀፍረ ኀሳረ ወጽዕለተ ወምራቀ
ዘርኩሳን አይሁድ። ተጸፍዐ ተኰርዐ ተረግዘ ተቀነወ ተፀርፈ ተጽዕለ
እንዘ አምላክ ውእቱ ወመላኬ ሞት ወወሀቤ ክብር። ወበእንተዝኬ
ተዐገሠ ኩሎ ኀሳረ ድኩምሰ ወኀሡር ያኀዝኖ ሶበ መነንዎ
ወጸዐልዎ። ወለጽኑዕሰ ወለክቡር ምንት ያኀዝኖ ለእመ ሐሰው
ላዕሌሁ።

[115] 1ዮሐ.1፥1
[116] ዮሐ.1፥1
[117] ማር1፥1
[118] ዮሐ.1፥1
[119] ዮሐ.1፥1-3



የነበረውንና የሰማነውን፣ በአይኖቻችንም ያየነውን፣ የተመለከትነውንና
እጆቻችንም የዳሰሱትን እናወራላችሁዋለን። ህብረታችንም ከእሱ ጋር
እንደሆነ እናወራላችሁዋለን። እናንተም በቃላችን ያመናችሁ ከእኛ ጋር
ህብረት ይኖራችሁዋል"[115] አለ።
3 ደቀመዝሙር ሉቃስም በሃዋርያት ስራ "የነገሩን መጀመሪያ አደረግን"[116]
እንዳለው ይህንን ያለው ክርስቶስ የሁሉ ቤዛ ሆነ። እኛም አመንበት።
4 ወንጌላዊው ማርቆስ በመፅሃፉ መጀመሪያ "የእግዚአብሄር ልጅ
የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መጀመሪያ"[117] ሲል ፃፈ። ይህም ማለት
ክርስቶስ ማለት ነው። ስብከቱም የነቢያትና የሃዋርያት ነው።
በፀጋውም ተባበርን።
5 ደግሞም ወንጌላዊው ዮሃንስ "በመጀመሪያ ቃል ነበር። ያም ቃል
በእግዚአብሄር ዘንድ ነበር"[118] ብሏልና። እንደገናም አስረገጠ፣ አለም።
"በመጀመሪያ እግዚአብሄር ቃል ነበር" በማለት ይህ የአብ ቃል
ሰማይና ምድርን የፈጠረበት ክርስቶስ ነው። "ፍጥረትንም ሁሉ
እሱ ፈጠረ። ያለ እርሱ ግን ምንም ምን አልሆነም"[119] ሆኑ።
አዘዘ፣ ተፈጠሩም።
6 ሶስተኛውንም ክብሩን ስማን። ሃይላቸው ሁሉ በአፉ ትንፋሽ ነው።
ይህ ያለውም በግልፅ ለመንፈስ ቅዱስ እንደተባለ ያሳያል።
7 እንግዲህ ምን እንላለን? እውነትን እንቢ ላሉና ሰውን በቸርነቱ
ለወደደው ለእግዚአብሄር ፍቅር አንገዛም ላሉ፣ ለአይሁድና
ለአህዛብ ወዮላቸው እያልን እናለቅስላቸዋለን። ሰው በመተላለፉ
ከወደቀ በሁዋላ በምህረቱ ብዛት በእፀ መስቀሉ ተሰቅሎ አዳነው።
በመለኮቱ ታላቅነት ለዘላለሙ ህማም የማይገባው እጆቹን በችንካር
ተቸነከረ። ስለእኛ ራሱን ዝቅ ዝቅ አድርጎ ታመመ። ሞትን
ይሽረው ዘንድ ሞተ። ደካማውን ያበረታው ዘንድ ደከመ።
ተጠምቶ ሆምጣጤ ጠጣ። የእሾህ አክሊል ደፍቶ እንኳ አልፈራም።
ስድብና ሃሳርን፣ የርኩሳንና የአይሁድን ምራቅ አላፈረም። አምላክና
የሞት ገዥ ክብርም ሰጪ ሆኖ ሳለ ፊቱን በጥፊ፣ እራሱን
በመዶሻ ተመታ። ተራቆተ፣ ተቸነከረ፣ ተሰደበ፣ ተጠላ። ሲንቁትና
ሲጠሉት ደካማና ጎስቋላ የሆነ ያሳዝነዋል።
8 እሱ ራሱ አምላክነቱን፣ ክብሩንና እራሱንም ያውቃል። እሱን ግን
የሚያውቀው የለም። የሁሉ ፈጣሪ ነውና። ቢያውቁ ኖሮ የክብርን
ጌታ ባልሰቀሉት ነበር። እሱም "አባት ሆይ የሚያደርጉትን
አያውቁምና ይቅር በላቸው"[120] አለ።

[115] 1ዮሃ.1፥1
[116] የሃዋ.ስ.1፥1
[117] ማር.1፥1
[118] ዮሃ.1፥1
[119] ዮሃ.1፥1-3
[120] ሉቃ.23፥34

www.ethiopianorthodox.org

እመ ኢሰቀልዎ ለእግዚእ ስብሐት። ወይቤ በምሕረቱ ሥረይ ሎሙ አባ
እስመ በዘኢያእምሩ ይገብሩ።[120]
9 ፈጣሪሆሙ በፍጥረት ይመስሉ። ወቀተሉ ፈላሴ ዘኢኮነ እምፍጥረት መዋቲ።
10 ወኢኮነ እምዝ ተገብረ በእድ አላ ውእቱስ ለሊሁ ገባሪ ወለሊሁ ፈጣሪ።
ብርሃን ዘእምብርሃን አምላክ ዘእምአምላክ[121] ወልድ ዘእምአብ ኢየሱስ
ክርስቶስ። ለሊሁ ምስካይ። ለሊሁ መሴስይ። ለሊሁ መጋቢ። ውእቱ ዘሀገሩ
ላዕለ ዘልዑል መልዕልተ ኩሉ ተትሕተ።
11 በከመ ይቤ ኢሳይያስ በሊኀ ቃል እምነቢያት ትሑት ብእሲሁ። ወራእዩ
ምኑን ከመ ሥርው በምድር ጽምእት ተሰዊሮ መጽአ በሥጋ ምድራዊት።
አኀዜ ኩሉ ወመድኀኔ ኩሉ።[122]
12 ወዳዊትሰ ያስተሜንዮ እንዘ ይብል፤ በሥንከ ወበላህይከ። ወካዕበ ይቤ
ይሤኒ ላህዩ እምውሉደ እጓለ እመሕያው። ወካዕበ ይቤ
ተከዕወ ሞገስ እምከናፍሪከ። ወካዕበ ይቤ
አርትዕ ተሠራህ ወንግሥ።
በእንተ ጽድቅ ወርትዕ ወየውሀት። ወካዕበ ይቤ በእንተ አይሁድ ፀራ
ለጽድቅ። አሕፃከ ስሑል ኀያል። ውስተ ልቦሙ ለጸላእተ ንጉሥ።[123] ውስተ
ልቦሙስ ይረትዕ ይርግዝዎሙ ይቤ ለእለ ኢይፈቅዱ ያንግሡኒ።
ያምጽእዎሙ ቅድሜየ ወይርግዝዎሙ።
13 ወካዕበ ይቤ ኢሳይያስ በእንተ አይሁድ፤ኀሠሥክዎሙ ወኢረከብክዎሙ።
ጸዋዕክዎሙ ወኢተሰጥዉኒ። አፍቀርክዎሙ ወጸልኡኒ።[124]
14 ወካዕበ ዳዊትኒ ይቤ
ፈደዩኒ እኪተ ህየንተ ሠናይት።
ወጸልኡኒ ህየንተ ዘአፍቀርክዎሙ።[125]
15 ወካዕበ ይቤ ኢሳይያስ፤ በአፉሆሙ ያፈቅሩኒ። ወበልቦሙሰ ነዋኀ ይርኅቁ
እምኔየ፤ ወከንቶ ያመልኩኒ።[126]
16 ወበከመ ይቤ ሙሴ፤
እሙንቱ አምዕዑኒ በአማልክቲሆሙ።
ወአነ አቀንኦሙ በዘኢኮነ ሕዝብ።
እስመ ሕዝብ ኀጉላነ ምክር እሙንቱ።[127]
17 ወእለሰ ይብሉ አልብነ ሕግ ተውህቦሙ ሕግ እስመ ለኩሉ ወሀቤ ሕግ
እግዚአብሔር። ወፈደዮሙ እግዚአብሔር በከመ እከዮሙ ለአይሁድ። ወገብረ
ሎሙ እግዚአብሔር በከመ የውሃቶሙ ለአሕዛብ። እስመ መሓሪ ውእቱ
ወመስተሣህል። ለእለ ይጼውዕዎ ወይትመኀፀኑ ቦቱ ወያነጽሑ ርእሶሙ
እምኩሉ ርኩስ በውስተ ቤተ ክርስቲያኑ ወበውስተ ታቦተ ሕጉ
ለእግዚአብሔር። ወእለ ይበክዩ ወይኔስሑ ያፈቅሮሙ።

---

[120] ሉቃ.23፥34
[121] ጸሎተ ሃይማኖት
[122] ?
[123] መዝ.45፥3-4
[124] ኢሳ.45፥12
[125] መዝ.109፥5
[126] ኢሳ.29፥13
[127] ?

- 123 -

9 ፈጣያሪያቸውን በፍጥረት ይመስላሉ። ከሙታንና ከፍጡራን ወገን
ያልሆነውን መፃተኛውን ገደሉ።
10 እሱ ግን ከተፈጠሩትት ወገን አይደለም። እሱ ራሱ ሰሪ፤እሱ ራሱ
ፈጣሪ፤ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፤ ከአምላክ የተገኘ አምላክ[121]፤ የአብ
ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እሱ መጠጊያ፤ እሱ መጋቢና ሲሳይ
አቅራቢ ነው። አገሩ ከላይ የሆነው ከሁሉም በላይ ታላቅ ነው።
11 ልሳኑ ሰይፍ የሆነው ኢሳያስ "ሰውየው ትሁት ነው። ሲያዩትም
የተናቀ ነው። ውሃ በተጠማች ምድር ውስጥ እንዳለች ስር
በምድራዊት ስጋ ተሰውሮ መጣ። ሁሉን የያዘና የሁሉ መድሃኒት
የሆነው በምድራዊት ስጋ መጣ"[122] አለ።
12 ዳዊትም "በቁንጅናህና በውበትህ"በማለት መልከ መልካም ያደርገዋል።
ደግሞም "ውበትህ ከሰው ልጆች ይልቅ ያምራል። ሞገስ በከንፈሮ
ችህ ፈሰሰ" አለ። እንደገናም ስለ የዋህነትና ስለ ፅድቅ አቅና፤
ተከናወን፤ ንገስም።"[123] አለ። የፅድቅ ጠላት ስለ ሆኑት አይሁድም
"ሃያል ሆይ በልባቸው ውስጥ ሊወጓቸው ይገባል። ሊያነግሱኝ
የማይወዱትን ከፊቴ አምጥተው ይውጓቸው" አለ።
13 ደግሞም ኢሳያስ ስለ አይሁድ "ፈለግሁአቸው፤ አላገኘሁአዋቸውም።
ጠራሁአቸው፤ አቤት አላሉኝም። ወደድኳቸው፤ ጠሉኝ"[124] አለ።
14 ዳዊትም "ስለ መልካም ፈንታ ክፉ ከፈሉኝ። ስለ ወደድኳቸው ግን
ጠሉኝ"[125] አለ።
15 ኢሳይያስም "በአፋቸው ይወዱኛል። በልባቸው ግን ከእኔ ብዙ
ይርቃሉ። በከንቱ ያመልኩኛል"[126] አለ።
16 ሙሴም "እነሱ በጣኦቶቻቸው ያስቆጡኛል። እኔም ደግሞ ህዝቤ
ባልሆነው አስቀናቸዋለሁ። ምክር የሌላቸው ህዝቦች ናቸውና"[127]
አለ።
17 ህግ የለንም ለሚሉት ህግ ተሰጣቸው። ለሁሉም ህግ ሰጪ
እግዚአብሄር ነውና። እግዚአብሄርም ለአይሁድ እንደ ክፋታቸው
ከፈላቸው። ለአህዛብም እንደ የዋህነታቸው አደረገላቸው።
ለሚጠሩትና ለሚማፀኑበት፤ እራሳቸውንም በቤተ ክርስቲያንና
በእግዚአብሄር ታቦተ ህግ ውስጥ ከርኩሰት ለሚያነፁ፤ ቸርና ይቅር
ባይ ነው። የሚያለቅሱ ትንና የሚፀፀቱትን ይወዳቸዋል።

---

[121] ጸሎተ ሃይማኖት
[122] ?
[123] መዝ.45፥2-4
[124] ?
[125] መዝ.109፥5
[126] ኢሳ.29፥13
[127] ?

www.ethiopianorthodox.org

18 በከመ ይቤ እስጢፋኖስ እምነ ፯ አርድእት ወካዕበ በውስተ ፸
ፈድፋደ ፯ እምኔሆሙ እለ ተኀርዩ ለግብር ምስለ ፲ወ፪ ሐዋርያት
ለግብረ መልእክት ምስለ ሲላስ ወበርናባስ ወማርቆስ ወሉቃስ
ወጳውሎስ። ወውእቱ እስጢፋኖስ ይቤሎሙ ለአይሁድ እንዘ ይቀውም
ለስምዕ። እንዘ ይቀትልዎ ይቤሎሙ ለአይሁድ እንዘ ያርእዮሙ
እበዶሙ በእንተ ዘኢዐቀቡ ትእዛዘ እግዚአብሔር ነሚአክሙ አሪተ
በሥርዐተ መላእክት ኢዐቀብክሙ። ወይቤ በግብር ሰሚያሙ ዘንተ
አብዱ ወሐቀዩ ስነኒሆሙ።[128]
19 አጽምዑኒኬ በእንተ ዘይቤ ሥርዐተ መላእክት አሪተ ኢዐቀብክሙ
አርኣያሃ ወጽላሎታ ለእንተ በሰማይ። እንተ በሰማይሰ ኢየሩሳሌም
አግዓዚት ማኀደሩ ለልዑል እንተ ኢትትዐወቅ ኅብራ ወግብራ በልበ
መዋቲ። ወውስቴታ መንበሩ ለልዑል በእሳት ክሉል።
20 ወ፬ እንስሳ ይጸውሩ በውስተ መካኖሙ ዘውእቱ ፮ ሰማይ።
ወየዐርግ መንበር ለ፯ ሰማይ ማኀደረ አብ። ወህየ ይነብር ዘሀሉ
ምስለ አቡሁ ወመንፈሱ ቅዱስ ማሕየዊ ኩሉ። ወአምሳለ መንበር
ዘቅድስት ኢየሩሳሌም ዛቲ ይእቲ ታቦት ዘቤተ ክርስቲያን ወአምሳለ
ኢየሩሳለም እንተ በሰማያት ዛቲ ይእቲ ቤተ ክርስቲያን እንተ
አሕዛብ።

## ፲ወ፫ በእንተ አቅርንተ ምሥዋዕ

1 ታቦትሰ አቅርንተ ምሥዋዕ ውእቱ። ኀበ ይሠውዑ ቅዱሳን ካህናት
ወዘያነብሩ ዲቤሁ ጠረጴዛ አምሳለ ኀበ ተቀብረ በውስተ ጎልጎታ
መቃብር ወዘመልዕልተ ጠረጴዛ ጽርስፎራ አምሳለ አጽርጌ።
2 ዘውእቱ ሥጋሁ ለአማኑኤል አክራጦስ ንጹሕ ዘአልቦቱ ቱስሕት
እንተ ነሥአ መድኀኒነ እማርያም ዘይቤሎሙ ለሐዋርያቲሁ ቅዱሳን
ብልዑ ሥጋየ። ወዘሰ ኢበልዐ ሥጋየ አልቦ ክፍል ምስሌየ።
ወአልቦ ሕይወት ዘለዓለም። ወዘሰ በልዐ ሥጋየ እመኒ ሞተ የሐዩ
ለዓለም።[129] ወተሳተፈ ሥጋየ ወደምየ ወኮነ መዋርስትየ ወይብሎ
ለአቡየ አንተ አቡነ ዘበሰማያት ወአብነ ይሰጠዎ እንዘ ይብሎ
ወልድየ አንተ።
3 ወአክሊል እንተ መልዕልተ ውእቱ ጽርስፎራ አምሳለ እብን እንተ
ሐተምዎ አይሁድ ላዕለ መቃብር።
4 ወሶበ ይብል ካህን ፈኑ መንፈሰ ቅዱሰ ይትፌነው መንፈስ ቅዱስ
ወይከውን ሥጋሁ ለእግዚእነ ፍጹመ። ወሶበ ተመጠውነ ንከውን ሱ ቱፋነ
ለሥጋ ወደም ለእግዚእነ ወመድኀኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ
እግዚአብሔር ሕያው ወመንፈስ ቅዱስ እምይእዜ ወእስከ ለዓለም።
ወንግሩኬ ለለአሐዱ አሐዱ ከመ ኢይትመክሑ ላዕሌነ ዕውራነ ልብ
አይሁድ ፀርነ ወፀረ እግዚአብሔር አምላክነ። ወይብሉ ብዙኀ
አማልክቲሆሙ ወሰገዱ ለዕፀው።

---

[128] የሐዋ.7፥53-54
[129] ማቴ.26፥26

- 124 -

18 ከሰባው አርድእት አንዱ የሆነውና ከሰባውም መካከል ከአስራ ሁለቱ
ጋር ለተልኮ ስራ እንዲያገለግሉ ከተመረጡት ከሰብአቱ ማለትም
ከበርናባስ፣ ከማርቆስ፣ ከሉቃስና ከጳውሎስ ጋር የተመረጠው
እስጢፋኖስ ለምስክርነት ሲቆምና ሲገድሉት አይሁድን "የእግዚአብሄርን
ትእዛዝ ስላልጠበቁ እብደታቸውን ሲያሳያቸው በመላእክት ስርኣት ህግን
ተቀብላችሁ በተግባር አልጠበቃችሁትም" አላቸው። ይህንንም ሰምተው
አበዱ። ጥርሳቸውንም አፋጩ[128]።
19 በመላእክት ስርኣት ኦሪትን አልጠበቃችሁም ስላለውም ልተርጉምላችሁ
አድምጡኝ። ኦሪት በሰማይ ላለችው አርኣያዋና ነፀብራቋ ናት። በሰ
ማይም ያለች ነፃይቱ ኢየሩሳሌም ናት። ህብሯና ስራዋ በሟች አእምሮ
የማይታወቅ ሰማያዊት ኢየሩሳሌም ናት። በውስጧም በእሳት የተከበበ
የልኡል መንበር አለ።
20 አርባእቱ እንስሳትም በቦታቸው ማለትም በስድስተኛው ሰማይ ሆነው
መንበሩን ይሸከማሉ። መንበሩም እስከ ሰባተኛው ሰማይ ማለትም እስከ
አብ መኖሪያ ይደርሳል። ከአባቱና የሁሉ ህይወት ከሆነው ከቅዱስ
መንፈሱ ጋር ያለውም ወልድ ከዚሁ ይኖራል። የቅድስት ኢየሩሳሌም
መንበር አምሳልም የቤተ ክርስቲያን ታቦት ናት። በሰማያት ያለችው
የኢየሩሳሌም አምሳል የአህዛብ ቤተ ክርስቲያን ናት።

## ፲፫ ስለ መሰዊያው ንዋየ ቅድሳት

1 ታቦት ቅዱሳን ካህናት የሚሰውበት የመሰዊያ ንዋየ ቅድሳት ነው።
በላዩ ላይ የሚያስቀምጡት ጠረጴዛ ደግሞ በጎልጎታ የተቀበረበት
መቃብር ምሳሌ ነው።
2 በጠረጴዛው ላይ ያለው ህብስት የበኩረ ህብስቱ የአማኑኤል ስጋ
ምሳሌ ነው። ንፁሁና ቅልቅል የሌለበት የወይን ጠጅም
መድሃኒታችን ከማርያም የነሳው ደም ምሳሌ ነው። ይሄውም
ለቅዱሳን ሃዋርያት "ስጋየን ብሉ። ስጋየን ያልበላ ከእኔ ጋር
አንድነትና የዘላለምም ህይወት የለውም። ስጋየንና ደሜን የተካፈለ
ግን ወራሼ ይሆናል"[129] አባቴንም በሰማይ የምትኖር አባታችን ሆይ
ይለዋል። አብም አንተ ልጄ ነህ ሲል ይቀበለዋል።
3 በዚህ መባእ ህብስት ላይ ያለው አክሊልም አይሁድ በመቃብሩ
ላይ አትመው ያኖሩት ድንጋይ ምሳሌ ነው።
4 ካህኑም "መንፈስ ቅዱስን ላክ" ሲል መንፈስ ቅዱስ ይላካል።
ፍፁም የጌታችንም ስጋ ይሆናል። በተቀበልንም ጊዜ ከህያው
እግዚአብሄር ልጅ ከጌታችንና መድሃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ
ስጋና ደም ጋር አንድ እንሆናለን። ከመንፈስ ቅዱስም ጋር አንድ
እንሆናለን። ከአሁን ጀምሮ ለዘላለሙ።

---

[128] የሃዋ.ስ.7፥53-54
[129] ማቴ.26፥26

www.ethiopianorthodox.org

5 ወይብሉ ተዘሜሮሙ ኀበ ነገረ ኢሳይያስ ነቢይ ለመንፈቁ ትሰግዱ
ወበመንፈቁ ትጠብሱ ሥጋ ወትበልዑ።[130] ይብል ኢሳይያስ ከመዝ
በእንተ እለ ይሰግዱ ለግልፎ ወለጣዖት። ወይብሉ እሉ አማልክቲነ
ወፈጠሩነ ይብልዎሙ። ወይሰግዱ ሎሙ ከመ እግዚአብሐር
አምላኮሙ። እሉኬ እለ ያስሕትዎሙ አጋንንት በእከዮሙ።
6 ወዳዊትኒ ይቤ በእንቲአሆሙ፤ አማልክቲሆሙ ለአሕዛብ አጋንንት።
ወእግዚአብሔርሰ ሰማያተ ገብረ። አሚን ወሠናይት ቅድሜሁ።[131]

## ፲ወ፬ ካዕበ በእንተ ታቦት ወነገረ ዕልዋን

1 ወበእንተ ታቦትሰ አድኀኖ ለኖኅ በታቦት። ወተናገሮ ለአብርሃም
በኀበ ዕፀ መንበር። ዘውእቱ ዕፀ ዘኢይነቅዝ ወአድኀኖ ለይስሐቅ
በዘተእኀዘ በዕፀ ሳቤቅ በግዕ። ወአብፀሎ ለያዕቆብ በሠለስቱ አብትረ
ዕፀው እለ ወደየ ኵሳኵሰ ውስተ ማይ።
2 ወበከተማ በትሩ ለያዕቆብ ተባረከ ዮሴፍ። ወለሙሴኒ ይቤሎ ግበር
ታቦተ እምዕፀ ዘኢይነቅዝ በአምሳሌሃ ለጽዮን ታቦተ ኪዳን። ወዳዊትኒ
አመ ይነሥኣ እምሀገረ ሰማርያ አንበራ ለታቦተ ሕግ ውስተ ሐዲስ
ታቦት። ወተፈሥሐ በቅድሜሃ እስመ ረሰያ ለታቦት መድኀኒተ
እምትካት። ወተገብረ ባቲ በአርአያ ወአምሳል ብዙኀ ተአምር
ወመንክር።
3 ስምዑኒ ወጥዩቀ እከሥት ለክሙ በከመ ወሀበ እግዚአብሔር
መድኀኒተ በዕፀ መስቀሉ በውስተ ታቦተ ሕጉ። እምቀዳሚ እስከ
ደኀሪ በዕፅ ኮነ መድኀኒቱ ለአዳም።
4 እስመ በዕፅ ኮነ ቀዳሚ ስሕተቱ። ወበዕፅ ረሰየ ሎቱ መድኀኒተ
እምትካት። እስመ ለሊሁ እግዚእ ፈጣሪ ወሀቤ ሕይወት ወሞት
ወኵሉ ይትገበር በቃሉ ወለኵሉ ውእቱ ፈጠረ።
5 ወያጸድቆ ለዘይትቀነይ በንጹሕ በውስተ ታቦተ ሕጉ ንጽሕት። እስመ
ተሰምየት ምስሐል ወካዕበ ተሰምየት ምምሕፃነ ወተሰምየት
ምስትሥራየ ኀጢአት። ተሰምየት መድኀኒተ። ወተሰምየት አንቀጸ
ሕይወት። ተሰምየት ምክሐ ወተሰምየት ሀገረ ምስካይ። ተሰምየት
ሐመረ። ወተሰምየት መርሶ መድኀኒት። ተሰምየት ቤተ ጸሎት።
ወተሰምየት ምስትሥራየ ኀጢአት። ለዘሰአለ በንጹሕ በውስቴታ ከመ
ይሰአልዎ በንጹሕ ወኢያርኵሱ ሥጋሆሙ።
6 እስመ ንጹሐ ያፈቅር እግዚአብሔር። እስመ ውእቱ ማኅደር
ለንጹሐን ለእለ ይበውኡ ውስተ ማኅደሩ ወይትአኀዙ በቅድስት
ታቦት ወይጸልዩ ኀቤሁ በኵሉ ልቦሙ። ወይሰምዖሙ ወያድኅኖሙ
አመ ዕለተ ምንዳቤሆሙ። ወይገብር ፈቃዶሙ። እስመ አምሳለ
መንበሩ አስተማሰላ በቅድስት ታቦት።

[130] ኢሳ.44፥16
[131] መዝ.96፥5-6

5 ነቢዩ ኢሳይያስ "ለግማሹ ትሰግዳላችሁ። በግማሹ ደግሞ ስጋ
ትጠብሳላችሁ፣ ትበላላችሁም"[130] ብሎ እንደተናገረ አይነ ልቡናቸው
የጠፋ ጠላቶቻችንና የአምላካችን የእግዚአብሄር ጠላቶች አይሁድ
እንዳይዘባበቱብን ይህንን ለእያንዳንዱ ንገሩ። ኢሳይያስ እንዲህ
ያለው ለጣኦትና ለምስል የሚሰግዱትን ነው። ምስሎቹን
አማልክቶቻችን ይሏቸዋል። ፈጠሩንም ይሏቸዋል። እንደ አምላካቸው
እንደ እግዚአብሄርም አድርገው ይሰግዱላቸዋል። እሊህም አጋንንት
በክፋታቸው የሚያስቷቸው ናቸው።
6 ዳዊትም ስለ እነሱ "የአህዛብ አማልክት አጋንንት ናቸው።
እግዚአብሄር ግን ሰማያትን ሰራ። ምስጋናና መልካም ነገር በፊቱ
ነው"[131] አለ።

## ፲፬ ስለ ታቦትና ስለ ከሃዲዎች ነገር

1 ስለ ታቦት ግን ኖህን በመርከብ አዳነው። አብርሃምን በማይነቅዝ
የመንበሩ እንጨት ስር አናገረው። ይስሃቅንም በአረግ ሬሳ በተያዘ
በግ ታደገው። ያእቆብንም በውሃ ውስጥ በጨመራቸው ሶስት
የእንጨት ብትሮች ሃብታም አደረገው።
2 ዮሴፍም በያእቆብ ብትር ጫፍ ተባረከ። ሙሴን በቃል ኪዳኑ
ታቦት በፅዮን አምሳል ከማይነቅዝ እንጨት ታቦትን ስራ አለው።
ዳዊት ታቦተ ህግን ከሰማርያ ሲወስዳት በአዲስ ታቦት ውስጥ
አስቀመጣት። በፊቷም ተደሰተ። ታቦትን ከጥንት ጀመሮ መድሃኒት
አድርጓታልና። በብዙ አርአያና ምሳሌ ብዙ ተአምርና ድንቅ ነገር
ተደርጎባታልና።
3 አስረድቼ እገልፅላችሁአለሁና ስሙኝ። እግዚአብሄር መድሃኒትን
በእፀ መስቀሉና በታቦተ ህጉም ውስጥ እንዳደረገ የአዳምም ድህነት
ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በእንጨት ሆነ።
4 የመጀመሪያው ስህተቱ በእንጨት ነውና ድህነቱን ከድሮ ጀመሮ
በእንጨት አደረገለት። እሱ ራሱ ጌታ፣ ፈጣሪ ህይወትና ሞትም
ሰጪ ነውና። ሁሉ በቃሉ ይደረጋል ሁሉን እሱ ፈጠረ።
5 ንፅህት በሆነችው በታቦተ ህግም ውስጥ በንፁህ የሚገዛውን ሁሉ
ያፀድቀዋል። መማለጃ ተብላለችና። ምግዚት ተባለች። መሰዊያም
ተባለች። የሃጢአት ማስተስረያም ተባለች። የመጠጊያ አገርም
ተባለች። መርከብ ተባለች። የድህነት ድልድይ ተባለች። ቤተ
ፀሎት ተባለች። ስጋቸውን እንዳያረክሱ በንፁህ ይለምኑት ዘንድ
በእሷ በንፁህ ለሚለምኑት የሃጢአት ማስተስረያ ሆነች።
6 እግዚአብሄር ንፁህን ይወዳልና ወደ ቤቱ ለሚገቡና በቅድስት
ታቦት ለሚያዙ፣ በሙሉ ልባቸው ወደ እሱ ለሚፀልዩና ለንፁሆች
ማደሪያ ነው። እሱም በችግራቸውም ቀን ይሰማቸዋል።

[130] ኢሳ.44፥16
[131] መዝ.96፥5-6

www.ethiopianorthodox.org

7 ወቦ እለ ታበውኡነ እንዘ ይትሜሰሉ ኪያነ ክርስቲያነ። ወኢየኀድጎሙ
ስሕተት በዘአሥረፀ ሎሙ አቡሆሙ ዲያብሎስ። ወይብል ከመዝ
ርቱዕሰ ንስግድ በውስተ ጽዮን ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር። ቀዳሚኒ
ይእቲ። ወይእዜኒ ዛቲ አምሳሊሃ ወፍሬሃኒ ወላዲተ መድኀን ማርያም
ርቱዕ ንስግድ ላቲ። እስመ ተባረከ በስመ ዚአሃ ታቦተ ሕጉ
ለእግዚአብሔር።
8 ወለሚካኤል ወለገብርኤል ርቱዕ ንስግድ። ወአውሥአሙ ሊቀ ጳጳሳት
ጌርሎስ ወይቤሎሙ። ወዘንተ ሶበ ይቤሎሙ ንሕነኒ ንብሎሙ ምንተ
ይቤ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዘ ይሜህሮሙ ለእለ አምኑ ቦቱ።
መጽአ ፩ እምአፍአ ወይቤሎ ነዮሙ አቡከ ወእምከ አፍአ የኀሡከ።
አውሥአ መፍቀሬ ሰብእ ክርስቶስ ወሰፍሐ እደሁ ኀበ እለ ይሜህሮ
ሙ ወይቤ እንዘ ኢይፈልጥ ወኢይሌሊ ዕደ ወአንስተ። ወይቤ ነዮሙ
አቡየ ወእምየ ወአኀውየ። ኩሉ ዘሰምዐ ቃልየ ወገብረ ፈቃደ አቡየ
ውእቱ አቡየኒ ወእምየኒ ወእኅትየኒ።
9 አ ዕውረ ልብ አይሁዳዊ ትሬኢኑ ምሕረቶ ወአፍቅሮቶ ሰብአ ሶበ
ይብል ከመዝ ኢፈለጠ ወኢሌለየ። አላ ይቤሎሙ አኀውየ። እስመ
ያፈቅሮሙ ለእለ ያፈቅርዎ ወየዐቅቡ ትእዛዞ። ወዓዲ በእንቲአሁ
መጠው ነፍሶሙ ለሞት እንዘ የአምሩ ምረራ ለሞት ሰማዕት
ወፈላስያን እለ የዐቅቡ ትእዛዞ ለእግዚአብሔር። ወአፍቀርዎ በኩሉ
ልቦሙ። ወውእቱኒ ያፈቅሮሙ። ወዘተሐንጸ መቃብሪሆሙ ዘውእቱ
መርጡል ወዘትሐንጸ ቤተ ክርስቲያን በስሞሙ ወዘቀደሱ ጳጳሳት
ታቦታተ በስሞሙ ኩሉ ቅዱስ በውስተ ቤተ መቅደሱ
ለእግዚአብሔር። ወዘሰአለ ሰብእ በስሞሙ ይሰምዖ እግዚአብሔር
በንጹሕ ዘእንበለ ርስሐት ወጥልቀት በትሕትና ወየውሃት እለ
ይጼልዩ ኀበ ዘተቀደሰ ታቦት እመሂ በስመ ሰማዕት ወእመሂ በስመ
መላእክት ወእመሂ በስመ ጻድቃን ወእመሂ በስመ ደናግል ወእመሂ
በስመ ቅዱሳት አንስት ሶበ ተቀደሰ ይወርድ መንፈስ ቅዱስ
ላዕሌሆሙ።
10 ወይመይጦ ለዕፅ ይኩን ሰማያዌ በከመ ሜጣ ለበትረ ሙሴ በቃሉ።
ወኮነት ዘነፍስ። ወአፍርሀቶ ለሙሴ እግዚእ።
11 ወበከመ ሰገደ ዮሴፍ ውስተ ከተማ በትሩ ለያዕቆብ እንዘ ሀሉ
ቅድሜሁ ኢያጸምዎ አላ በተአምኖ አቡሁ ሰገደ ውስተ ከተማ
በትሩ። ወዝኒ ዘጸሐፈ ሙሴ ትንቢት ለደኃሪ መዋዕል ከመ ናእምር
ከመ ይትቄደሱ ታቦታት በስመ ሰማዕት ወጻድቃን እስመ እንዘ
ይሬእዮ ሰገደ ለከተማ በትሩ።
12 ወካዕበ እነግረከ ዘተጽሕፈ በእንተ ትንቢቱ ለፈርዖን። ሙሴ ገብረ
በትሮ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር። ረሰዮ አርዌ ምድር። ወአዘዞሙ
ፈርዖን ለመሠርያን ከመ ይግበሩ ከማሁ አብትሪሆሙ ለሰብአ ሐራስ።
ወገብሩ አብትሪሆሙ ፫ አክይስተ እለ ይትሐወሳ በሥራይ በቅድመ
ሙሴ ወአሮን ወበቅድመ ፈርዖን ወዐበይተ ግብፅ። ወበልዐቶሙ
በትረ ሙሴ ለአብትረ መሠርያን እስመ እማንቱ ሕስዋነ ስም።



ያድናቸዋልም። ፈቃዳቸውንም ያደርጋል። የተቀደሰችውንም ታቦት
በመንበሩ አስመስሎ ሰርቷታልና።
7 እኛን ክርስቲያኖችን መስለው የገቡ አባታቸው ዲያቢሎስ ካነቃው
ስህተት አይርቁም። እኛ ግን በእግዚአብሄር ታቦተ ህግ በፅዮን
ውስጥ እንሰግድ ዘንድ ይገባል። መጀመሪያዋም እሷ ናት። ዛሬም
አሁንም እሷ ናት። ምሳሌዋም ፍሬዋም የመድሃኒታችን እናት
ማርያም ናት። እንሰግድላት ዘንድ የእግዚአብሄር ታቦተ ህግ በእሷ
ስም ተባርካለች።
8 ለሚካኤልና ለገብርኤልም እንሰግድ ዘንድ ይገባል። ሊቀ ጳጳሳት
ቄርሎስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
ላመኑበት ሲያስተምራቸው አንድ ሰው ከውጪ መጥቶ "አባትህና
እናትህ እየፈለጉ በውጪ ናቸው" ሲለው ምን አለ? ሰው
አፍቃሪው ክርስቶስ ወደ ሚያስተምራቸው እጁን ዘርግቶ
ሳይለያይና ሳይነጥል "እነሆ አባቴና እናቴ ወንድሞቼም። ቃሌን
የሰማ የአባቴንም ፈቃድ ያደረገ ሁሉ እሱ አባቴ፣ እናቴና
እህቴም ነው አለ" አላቸውም።
9 አንተ ልበ ጥፉ አይሁዳዊ ምህረቱንና ሰውን መውደዱን
ታያለህን። ወንድሞች አላቸው እንጂ ፈፅሞ አለየም። የሚወዱትንና
ትእዛዙን የሚጠብቁትን ይወዳቸዋልና። ደግሞም የሞትን መራራነት
እያወቁ ስለ እሱ ህይወታቸውን ለሞት የሰጡ ሰማእታትን፣
ስደተኞችንና የእግዚአብሄርን ትእዛዝ በልባቸው ሁሉ የጠበቁትን
ሁሉ ይወዳቸዋል። መቃብራቸው ማለትም አውደ ሰማእታትና
በስማቸው ቤተ ክርስቲያን የተሰራላቸው፣ ጳጳሳት በስማቸው
ታቦታትን የባረኩላቸውና በእግዚአብሄር ቤተ መቅደስ ውስጥ
ያለው ሁሉ ቅዱስ ነው። እግዚአብሄር በስማቸው የሚፀልዩትን
ሁሉ ይሰማቸዋልና። ያለ ርኩሰትና ጉድፍ በንፅህናና በትህትና
በየዋሃትም በተቀደሰው ታቦት በሰማእትም ስም ቢሆን፣
በመላእክትም ስም ቢሆን፣ በፃድቃንም ስም ቢሆን፣ በደናግልም
ስም ቢሆን፣ በቅዱሳት አንስትም ስም ቢሆን በሚቀደስበት ጊዜ
መንፈስ ቅዱስ በሚፀልዩት በላያቸው ላይ ይወርዳል።
10 የሙሴን ብትር በቃሉ እንደ ለወጣትና ህይወት ያላት ሁና ሙሴን
እንዳስፈራራቸው እንዲሁም እንጨቱን ወደ ሰማያዊነት ይለውጠዋል።
11 ዮሴፍ በፊቱ ሳለ አባቱን ያእቆብን በማመን ያለ መታከት
በብትሩ ጫፍ ሰገደ፣ አልደከመምም። ሙሴም ታቦታት በሰ
ማእታትና በፃድቃን ስም እንዲቀደሱ ይህንን ትንቢት ለሚመጣ
ትውልድ ፃፈ። እያዩ ለብትሩ ጫፍ ሰገዷልና።
12 ደግሞም ስለ ፈርኦን ስለ ተፃፈው ትንቢት እነግርሃለሁ። ሙሴ
ብትሩን እግዚአብሄር እንዳዘዘው አደረገ። እባብም አደረገው።
ፈርኦንም ጠንቋዮቹን የማርተኞቹን ብትሮች እንዲሁ እንዲያደርጉ
አዘዘ። እነሱም በሙሴና በአሮን በፈርኦንና በግብፅ ታላላቆቹ ሁሉ
ፊት በስራይ የሚንቀሳቀሱ ሶስት እባቦችን አደረጓቸው። የሙሴም
በትር የጠንቋዮችን ብትር በላቻቸው። እነሱ በስም ዋሾዎች

www.ethiopianorthodox.org

ለአርአያ ዐይነ ሰብእ በሥራይ ገብሩ። ወዘሰ ኮነ በቃለ
እግዚአብሔር ይመውእ ኵሎ ሥራየ ዘተገብረ። ወአልቦ ዘይረክቦ
እኩይ እስመ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ዘይሜግቦ ወያሰንዮ ለዘይታመን
በርቱዕ ልብ ዘእንበለ አስትቶ።
13 በከመ ይቤ ጳውሎስ በተአምኖ ድኅኑ አበው ቀደምት። ፈቀደ
ወአጠየቀ በበስሞሙ እምአዳም ወኖኅ ወአብርሃም ወእስከ ረአብ ዘማ
እንተ ተወክፈቶሙ ለሰብእ ዐይን።
14 ወአንተኒ ኦ ዕውር አይሁዳዊ ኢትሌቡኑ በውስተ ሕግ ዘታነብብ
ዘውእቱ ዘትትአመን ኦሪትከ እንዘ ኢትክል አስልጦ ትእዛዛቲሃ
ወርጉም አንተ ባቲ እስመ ይብሉ ኵሎሙ እለ የሐውሩ ባቲ።
ለእመ ኢአቀቡ ዘጽሑፍ ውስቴታ ርጉመ ለይኩን ይብለከ ወለነሰ
ለእለ አመነ በክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ኀረየነ ጸጋ
እግዚአብሔር እንዘ ይብል ዘአምነ ወዘተጠምቀ ይድኅን።[132]

## ፻ወ፭ በእንተ አሚነ አብርሃም

1 ወአንተሰ ኢትሌቡ ከመ በአሚን ይጸድቁ ከመ አብርሃም ወዳዊት
ወኵሎሙ ነቢያት በበመትልው እለ ተነበዩ በእንተ ምጽአቱ ለወልደ
እግዚአብሔር።
2 ወይቤ አብርሃም በመዋዕልየኑ እግዚኦ ትፌኑ ቃለከ ዲበ ምድር።
ወይቤሎ እግዚአብሔር አልቦ ኢበጽሐ ጊዜሁ አላ አርእየከ አምሳለ
ምጽአቱ።
3 ወባሕቱ ዕዱ ዮርዳኖስ ወተጠመቀ እንዘ ተዐዱ ወበጻሕ ሀገረ
ሳሌም። ወትረክቦ ለመልከ ጼዴቅ። ወአነ እኤዝዞ ያርኢከ ተአምሪሁ
ወአምሳሊሁ። ወገብረ ከማሁ። ወረከቦ ለመልከ ጼዴቅ። ወወሀቦ
ምሥጢረ ኅብስት ወወይን።[133] ውእቱ ዘተገብረ በፋሲካነ ለመድኃኒትነ
በእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ። ዝኬ ውእቱ ተምኔቱ ወትፍሥሕቱ
ለአብርሃም። ዐዊዶ ምሥዋዐ ዘገብረ መልከ ጼዴቅ ነሢኦ ጸበርተ
ወበቀልተ በዕለተ ሰንበት በተአምኖኬ ከመ ተፈሥሐ ርኢ።
ወበተአምኖ ጸድቀ ርኢ። ኦ አይሁዳዊ ዕውር እንዘ ብከ አዕይንተ
ኢትሬኢ። ወእንዘ ብከ ዕዝነ ኢትሰምዕ። በከመ ይቤ በእንቲአክሙ
ኢሳይያስ ነቢይ ያሩ አዕይንቲሆሙ። ወተጸለለ ልቦሙ ከመ ኢይለብዉ
ወኢይሣህሎሙ።[134]

## ፻ወ፮ ትንቢት በእንተ ምጽአቱ ለክርስቶስ

1 ወበእንተሰ ምጽአቱ ስማዕ ዘከመ ተነበዩ ፩ ፩ ዘአዳም ለሰሚያት
በእንተ ምጽአቱ ተነበየ ኢሳይያስ ወይቤ ወልድ ተወልደ ለነ። ሕፃን

---

[132] ማር.16፥16

[133] ዘፍጥ.14፥18

[134] ኢሳ.6፥10

- 127 -

ናቸውና። በሰው ኣይን ብቻ በምታት እንዲሁ ኣደረጉ። በእግዚኣብሄር
ቃል የሆነ ግን የተደረገ ስራይን ሁሉ ያሸንፋል። የሚያገኘው ክፉ ነገር
የለም።
13 ጳውሎስ "ኣበው ቀደምት በእምነት ዳኑ" እንዳለው ከኣዳምና ከኖህ
ከኣብርሃምም ጀምሮ ሰላዮችን እስከ ተቀበለቻቸው እስከ ጋለሞታዋ ረኣብ
ድረስ እያንዳንዳቸውን በየስማቸው ሊያስረዳ ወደደ።
14 ኣንተ እውር ኣይሁዳዊ በምታነበው ህግ ውስጥ ማለትም ትእዛዛቱን
መፈፀም ሳትተው በምታምነው ኦሪትህ ውስጥ የምታነበውን
ኣታስተውለውምን? ኣንተ በእሷ የተረገምህ ነህ። በእሷ የሚኖሩት ሁሉ
እንደዚሁ የተረገሙ ናቸው። በውስጧ ያለውን የማይጠብቅ የተረገመ ነው
ተብሎብሃልና። እኛን ግን በእግዚኣብሄር ልጅ በክርስቶስ የእግዚኣብሄርን
ፀጋ ያመነና የተጠመቀ ይድናል[132] ሲል መረጠን።

## ፻፭ ስለ ኣብርሃም እምነት

1 ኣንተ ግን እንደ ዳዊትና እንደ ኣብርሃም እንዲሁም በየተራ ስለ
እግዚኣብሄር ልጅ መምጣት ትንቢት እንደ ተናገሩ ነቢያቶች
በእምነት እንዲፀድቁ ኣታስተውልምን?
2 ኣብርሃምም "ኣቤቱ በዘመኔ ቃልህን ወደ ምድር ትልካለህን?"
ኣለው። እግዚኣብሄርም "የኣመጣጡን ምሳሌ ኣሳይሃለሁ እንጂ
ኣሁንስ ኣይደለም። ጊዜው ኣልደረሰም" ኣለው።
3 "ነገር ግን ዮርዳኖስን ተሻገር። ስትሻገርም ተጠመቅ። ኢየሩሳሌምም
ድረስ። መልከ ፄዴቅንም ታገኘዋለህ። እኔም ፃድቁንና ምሳሌውን
ያሳይህ ዘንድ ኣዝዘዋለሁ" ኣለ። እንዲሁም ኣደረገ። መልከ
ፄዴቅንም ኣገኘው። የህብስትንና የወይንንም ምስጢር ሰጠው።[133]
ይሄውም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ለድህነታችን በፋሲካችን
የተደረገው ነው። የኣብርሃም ምኞቱና ደስታው ይህ ነው። በሰ
ንበት ቀን ሰሌንና ዘንባባ ይዞ መልከ ፄዴቅም ያደረገውን መሰ
ዊያው በመዞር በእምነት እንደ ተደሰተ ተመልከት። ነቢዩ ኢሳይያስ
ስለ እናንተ እንዳያስተውሉ፣ እንዳልምራቸውም ኣይኖቻቸው ጠፉ፤
ልባቸውም ተደፈነ።"[134] እንዳለ ኣይን እያለህ የማታይ፣ ጆሮ
እያለህ የማትሰማ ኣይሁዳዊ ሆይ! እይ።

## ፻፮ ስለ ክርስቶስ መምጣት ትንቢት

1 ስለ ኣመጣጡም እያንዳንዳቸው የተናገሩትንና ለመስማትም
ያማረውን ስማ። ስለ መምጣቱ ኢሳይያስ "ወንድ ልጅ

---

[132] ማር.16፥16

[133] ዘፍጥ.14፥18

[134] ኢሳ.6፥10

www.ethiopianorthodox.org

ተውህበ ለነ። ሥልጣን ጽሑፍ ዲበ መትከፍቱ። ውእቱ አምላከ
ጽኑዐ ምኵናን። ንጉሥ ዐቢየ ምክር። ስሙ ወትርጓሜሁ ዘንተ
ይብል ገሀደ። ወልደ እግዚአብሔር ተወልደ። ዘመንግሥቱ ጽሑፍ
እምቅድመ ዓለም ወይጠብብ እምነ ኵሉ ይብለከ።[135]
2 ወካዕበ ተነበየ ወይቤ ኢሳይያስ ናሁ ቍልዔየ ዘኀረይኩ ዘሠምረት
ነፍስየ ደቢሁ። ወይትዌከሉ አሕዛብ ቦቱ።[136] ወካዕበ ዝኒ ያሌብወነ
ከመ መንፈሰ እግዚአብሔር ውእቱ ክርስቶስ ቃለ አብ ዘለብሰ
ሥጋነ ወተወልደ ለነ።
3 ወአምኑ ቦቱ አሕዛበ ሮሜ ወኢትዮጵያ ወባዕድኒ ኵሉ አሕዛብ።
ወለእስራኤልሰ ሕዝበ ይብሎሙ።
4 ወካዕበ ተነበየ ወይቤ ብዙኃን ይተልውከ ድኅሬከ እቾንዘ ቅኑታን
ሐቋሆሙ ወእሱራን ድኅሪተ በሰናስል። ወይጼልዩ ኀቤከ። ወይሰግዱ
ለከ። እስመ እግዚአብሔር አንተ። ወኢያአመርናከ ወዘንተኒ በእንተ
ሰማዕት ወእለ ይከውኑ ገዳማውያን ወፈላስያን እለ እሱራን
አልባቢሆሙ በትእዛዙ። ወይጼልዩ ሎቱ እስመ ድልው ዐስቦሙ
ለክልኤሆሙ። ሰማዕት ወፈላስያን ብሂል ወኢያእመርናከሰ እስመ
ተአዎርዎ እስራኤል ወሰቀልዎ ወአበዩ ሐዊረ በጽድቁ።
5 ወካዕበ ተነበየ ወይቤ እግዚአብሔር ይወጽእ ወይትዌከሉ ወያአምሩ
አሕዛብ። ወዘንተኒ መጽአ ክርስቶስ ወአበይዎ አይሁድ ወአምኑ ቦቱ
አሕዛብ ብሂል።
6 ወካዕበ ተነበየ ወይቤ ጽንዑ ዕደው ድኩማን ወብረከ ፅቡሳን።
ወተፈሥሑ ዕንቡዛነ ልብ። እስመ እግዚአብሔር መጽአ ዘይፈዲ ዕዳነ
ወያድኅነነ ወይከሥት አዕይንተ ዕውራን ወያሰምዕ ዕዝነ ጽሙማን
ወያረውጽ እግረ ሐንካሳን ወያነብብ ልሳነ በሃማን ይነቡ።[137]
7 ወዘንተኒ ዘተብህለ እለ ተስሕቱ በሰጊድ ለጣዖት ወእለ ምውታን
በኀጢአት።
8 ወእለ ተጸለለ ልብክሙ ወኢታእምሩ ዘፈጠረክሙ ተፈሥሑ ዮም።
መጽአ ዘይፈዲ ኀጢአተ አዳም ርስዮ ዕዳ ዚአሁ። ተሰቂሎ ዘእንበለ
ኀጢአት ቀተሎ ለሞት በሞቱ። ወርእዩ ዕውራን። ወሖሩ ሓንካሳን።
ወሰምዑ ጽሙማን። ወተናገሩ ርቱዐ በሃማን።
9 ወዓዲ ተንሥኡ ምውታን ብሂል በከመ ተነበየ ዳዊት ነቢይ ወይቤ፣
እግዚአብሔርሰ ገሃደ ይመጽእ።

135 ?

136 ኢሳ.42፥1

137 ኢሳ.35፥3

- 128 -

ተወለደልን። በትከሻው ላይ ስልጣን የተፃፈበት ህፃን ተሰጠ። እሱ
ኣምላክ ነው። ፍርዱ ፅኑ የሆነ ንጉስ ነው። ምክሩ ታላቅ ነው።
ስሙና የስሙም ትርጓሜ ይህንኑ ይናገራል። የእግዚኣብሄር ልጅ
ተወለደ። መንግስቱም ከኣለም በፊት የተፃፈ ነው። ከሁሉም በፊት
ይጠበባል"[135] ይልሃል።
2 ደግሞም ኢሳይያስ "እነሆ የመረጥኩት፣ ነፍሴ እሱን የወደደችና
ኣህዛብም የሚተማመኑበት ወዳጄ"[136] ሲል ስለ እርሱ ትንቢት
ተናገረ። ይህም ደግሞ ስጋችንን የለበሰውና የተወለደልን የኣብ
ቃል ክርስቶስ የእግዚኣብሄር መንፈስ እንደሆነ ያሳስባል።
3 የኢትዮጵያና የሮም እንዲሁም ሌሎች ህዝቦች ኣመኑበት።
እስራኤልን ግን ህዝብ ይላቸዋል።
4 ደግሞም "ብዙዎቹ ወገባቸውን ታጥቀውና በሁዋላቸውም በገመድ
ታስረው በሁዋላህ ይከተሉሃል። ወደ ኣንተም ይፀልያሉ። ይሰ
ግዱልሃልም። ኣንተ እግዚኣብሄር ነህና። ነገር ግን ኣላወቅንህም"
ሲል ትንቢት ተናገረ። ይህንንም ስለ ሰማእታትና ገዳማዊያን ስለ
ሚሆኑ፣ ስለሚሰደዱም ልባቸው በትእዛዝ ስለታሰሩ ወደ እሱ ስለ
ሚፀልዩ ነው። ሰማእታት ስደተኞች ዋጋቸው ተዘጋጅቶላቸዋል።
ኣላወቅንህም ስላሉት ማለትም እስራኤል ችላ ስለኣሉቱና ስለ
ሰቀሉት፣ በፅድቁም መሄድን እንቢ ስላሉ ነው።
5 ደግሞም "እግዚኣብሄር ይመጣል። ኣህዛብም ጠበቃ ያደርጉታል።
ያምኑበታልም" ሲል ትንቢት ተናገረ። ስለዚህም ክርስቶስ መጣ።
ኣይሁድም እንቢ ኣሉት። ኣህዛብ ግን ኣመኑበት ማለት ነው።
6 ደግሞም "እናንተ የጉልበት ደካሞችና ሃንካሳን ወንዶች በርቱ።
ልበ ጥፉዎችም ደስ ይበላችሁ። ብድራችንን የሚከፍለን እግዚኣብሄር
መጥቷል፤ ያድነናልም። የእውሮችን ኣይኖች ያበራል። የደንቆሮዎችንም
ጆሮዎች ይከፍታል። የሃንካሶችንም እግሮች እንዲሮጡ፣ የዱዳዎችንም
ኣንደበቶች እንዲናገሩ ያደርጋል"[137] ሲል ትንቢት ተናገረ።
7 ይህም የተባለው ለጣኦት በመስገድ ለተሳሳቱትና በሃጢኣት
ለሞቱትም ነው።
8 "ልባችሁ የተጋረደውና የፈጠራችሁን የማታውቁ ዛሬ ደስ
ይበላችሁ። የኣዳምን በደል የራሱ በደል አድርጎ የሚከፍል
መጥቷልና። ያለ ሃጢኣት ተሰቅሎ ሞትን በሞቱ ገደለው። እውሮ
ች አዩ። ኣንካሳዎችም ሄዱ። መስማት የተሳናቸው ሰሙ። መናገር
የተሳናቸው ኣስተካክለው ተናገሩ።"
9 ደግሞም ነቢይ ዳዊት፣
እግዚኣብሄር በግልፅ ይመጣል።

135 ?

136 ኢሳ.42፥1

137 ኢሳ.35፥3

www.ethiopianorthodox.org

ወአምላክነሂ ኢያረምም።[138]
10 በከመ ተነበየ ኤርምያስ ወይቤ ይወርድ እግዚአብሔር ዲበ ምድር
ወያንሶሱ ምስለ ሰብእ ከማነ።[139]
11 በከመ ተነበየ ሕዝቅኤል ነቢይ ወይቤ እመጽእ አነ አምላኮሙ
ወአንሶሱ ማዕከሎሙ። ወየአምሩኒ ከመ አምላኮሙ።[140]
12 ወበከመ ተነበየ ዳዊት ወይቤ
ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር።[141]
ባረክናክሙ በስመ እግዚአብሔር።[142]
13 በከመ ተነበየ ዕንባቆም ወይቤ
እግዚአብሐርሰ እምቴማን ይመጽእ።
ወቅዱስኒ እምደብረ ፋራን ወእምአህጉረ ይሁዳ።[143]
14 በከመ ተነበየ ኤልያስ ነቢይ ወይቤ በሐዲስ ሥርዓት ይመጽእ
እግዚአብሔር ኀቤነ።[144]
15 በከመ ተነበየ ኢዩኤል ነቢይ ወይቤ፣ አማኑኤል ሰማያዊ ይመጽእ
ወያድኅን ተግባሮ ዘለሐኰ በእዴሁ እምእደ ዲያብሎስ ተዐጋሊ
ወአጋንንቲሁ መስሕታን።[145]
16 ወበከመ ተነበየ ዳዊት ነቢይ ወይቤ፣
ያስተርኢ አምላከ አማልክት በጽዮን።[146]
ወካዕበ ይቤ፣
እምነ ጽዮን ይብል ሰብእ።
ወብእሲ ተወልደ በውስቴታ።
ወውእቱ ልዑል ሣረራ።[147]
17 ወበከመ ተነበየ ሰሎሞን ወልዱ ወይቤ፣ አማን ይሄሉ እግዚአብሔር
ምስለ ሰብእ ወያንሶሱ ዲበ ምድር።
18 ወበከመ ተነበየ አቡሁ ዳዊት ወይቤ፣
ወይወርድ ከመ ጠል ውስተ ፀምር።
ወከመ ነጠብጣብ ዘያንጠበጥብ ዲበ ምድር።
ወይሠርፅ ጽድቅ መመዋዕሌሁ።[148]

---

[138] መዝ.50፥3
[139] ?
[140] ዘሌ.26፥12.ሕዝ.37፥27፥2ቆሮ.6፥16
[141] መዝ.118፥26
[142] መዝ.129፥8
[143] እንባ.3፥3
[144] ኤር.31፥31
[145] ?
[146] መዝ.50፥2
[147] መዝ.87፥5
[148] መዝ.72፥6-6



አምላካችንንም ዝም አይልም።[138] እንዳለው የሞቱት ተነሱ።
10 ኤርምያስ፣ "እግዚአብሄር ወደ ምድር ይወርዳል። እንደ እኛ ካሉ
ሰዎች ጋርም ይመላለሳል"[139]ሲል ትንቢት እንደተናገረ።
11 ነቢዩ ህዝቅኤልም፣ "እኔ አምላካቸው እመጣለሁ። በመካከካቸውም
እመላለሳለሁ። አምላካቸው እንደሆንኩ ያውቁኛል" [140]ብሎ ትንቢት
እንደተናገረ።
12 ዳዊትም፣
በእግዚአብሄር ስም የሚመጣ የተባረከ ነው።[141]
በእግዚአብሄር ስም ባረክናችሁ።[142] ብሎ እንደ ተናገረ።
13 እንባቆምም፣
እግዚአብሄርስ ከቴማን ይመጣል።
ቅዱስም ከፋራን ተራራና ከይሁዳ አገሮችም ይመጣል።[143]
ብሎ በትንቢት እንደ ተናገረ።
14 ነቢዩ ኤርምያስም "እግዚአብሄር በአዲስ ስርአት ወደ እኛ
ይመጣል"[144] ሲል በትንቢት እንደ ተናገረ።
15 ነቢዩ ኢዩኤልም "ሰማያዊው አማኑኤል ይመጣል። በእጁ የሰራውን
ስራውን ከሸንጋዩ ከዲያቢሎስና ከሚያስቱት አጋንንት እጅ
ያድናል"[145] ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ።
16 ነቢዩ ዳዊትም፣
የአማልክት አምላክ በፅዩን ይታያል።[146] ደግሞም ሰው
እናታችን ፅዮን ይላል። በውስጧም ሰው ተወለደ። እሱም
ልኡል ነው፣ መሰረታትም።[147] ብሎ በትንቢት እንደ
ተናገረ።
17 ልጁ ሰሎሞንም "በእውነት እግዚአብሄር ከሰው ጋር ይኖራል።
በምድርም ላይ ይመላለሳል" ብሎ በትንቢት እንደ ተናገረው።
18 አባቱ ዳዊትም
በግምጃ ላይ እንዳለ ልምላሜ ይወርዳል።
በምድርም ላይ እንደ ሚንጠባጠብ ነጠብጣብ ያንጠባጥባል
በዘመኑም እውነት ይወጣል።[148] ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ።

---

[138] መዝ.50፥3
[139] ኤር.32፥38
[140] ዘሌ.26፥12.ሕዝ.37፥27፥2ቆሮ.6፥16
[141] መዝ.118፥26
[142] መዝ.129፥8
[143] እንባ.3፥3
[144] ኤር.31፥31
[145] ?
[146] መዝ.50፥2
[147] መዝ.87፥5
[148] መዝ.72፥6-7

www.ethiopianorthodox.org

19 ወበከመ ተነበየ ሰሎሞን ወልዱ ወይቤ
ይትወለድ መድኅን እምጽዮን።
ወያአትት ኀጢአተ እምያዕቆብ።[149]
20 ወበከመ ተነበየ ሆሴዕ ነቢይ ወይቤ፣ እመጽእ ኀቤኪ ጽዮን ወአንሶሱ
ማእከሌኪ ኢየሩሳሌም ይቤ እግዚአብሔር ቅዱሰ እስራኤል።[150]
21 ወበከመ ተነበየ ሚክያስ ነቢይ ወይቤ፣ ያስተርኢ ቃለ እግዚአብሔር
በኢየሩሳሌም ወሕግ ይወጽእ እምጽዮን።[151]
22 ወበከመ ተነበየ ሆሴዕ ነቢይ ወይቤ፣ ያስተርኢ እግዚአብሔር ዲበ
ምድር። ወየኀድር ምስለ ሰብእ ከማነ።[152]
23 ወበከመ ተነበየ ኤርምያስ ነቢይ ወይቤ፣ ይትፌኖ መድኅን እምጽዮን።
ወያአትት ኀጢአተ እም ሕዝበ እስራኤል።[153]
24 ወበከመ ተነበየ ሚልክያስ ነቢይ ወይቤ፣ ይመጽእ እግዚአብሔር
እምሰማይ። ወየኀድር ውስተ ጽርሑ።[154]
25 ወበከመ ተነበየ ዘካርያስ ነቢይ ወይቤ፣ ተፈሥሒ ወለተ ጽዮን። ናሁ
ሕያው አነ ወአኀድር ውስቴትኪ። ፡ ይቤ እግዚአብሔር ቅዱሰ
እስራኤል።[155]
26 ወበከመ ተነበየ ሚክያስ ነቢይ ወይቤ ናሁ እግዚአብሔር ይመጽእ።
ወያበርህ ለእለ ይፈርህዎ። ወፀሐየ ጽድቅ ስሙ።[156]
27 ወበከመ ተነበየ ሆሴዕ ነቢይ ወይቤ፣ ይመጽእ እግዚአብሔር ላዕሌኪ
ኢየሩሳሌም። ወያስተርኢ ውስቴትኪ።[157]
28 ወበከመ ተነበየ ነቢይ ወይቤ፣
የሐዩ ወይሁብዎ እምወርቀ ዐረብ።
ወዘልፈ ይጼልዩ በእንቲኣሁ።[158]
ወይከውን ምስማከ ለኩሉ ምድር።
ውስተ አርእስተ አድባር።[159]

---

[149] ኢሳ.59፥20
[150] ዘካ.2፥10
[151] ሚክ.4፥2
[152] ?
[153] ·ኤር.31፥11-12
[154] ሚልክ.4፥1
[155] ዘካ.19፥9
[156] ሚልክ.4፥2
[157] ኢሳ.60፥2
[158] መዝ.18.9
[159] መዝ.72፥15



19 ልጁ ሰሎሞንም
መድሃኒት ከፅዮን ይወለዳል።
ለያእቆብ ሃጢአትን ያስወግዳል።[149] ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ።
20 ነቢዩ ሆሴእም "የእስራኤል ቅዱስ እግዚኣብሄር ፅዮን ሆይ ወደ
ኣንች እመጣለሁ። ኢየሩሳሌም ሆይ በመካከልሽ እመላለሳለሁ"[150]
ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ።
21 ነቢዩ ሚክያስም "የእግዚኣብሄር ቃል በኢየሩሳሌም ይገለጣል።
ህግም ከፅዮን ይወጣል"[151] ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ።
22 ነቢዩ ሆሴእም "እግዚኣብሄር በምድር ላይ ይታያል። እንደ እኛ
ካሉ ሰዎችም ጋር ያድራል "[152] ሲል ትንቢት እንደ ተናገረ።
23 ኤርሚያስም "መድሃኒት ከፅዮን ይላካል። ሃጢኣትንም ከእስራኤል
ህዝቦች ያስወግዳል"[153] ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ።
24 ነቢዩ ሚልክያስም "እግዚኣብሄር ከሰማይ ይወጣል። በኣዳራሹም
ያድራል"[154] ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ።
25 ነቢዩ ዘካርያስም የእስራኤል ቅዱስ እግዚኣብሄር የፅዮን ሴት ልጅ
ሆይ! እነሆ ደስ ይበልሽ። እኔ ህያው ነኝ። በውስጥሽም
አድራለሁ አለ"[155] ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ።
26 ነቢዩ ሚክያስም "እነሆ ኣሁን እግዚኣብሄር ይመጣል። ለሚፈሩትም
ያበራላቸዋል። ስሙም እውነትኛ ፀሃይ ነው"[156] ብሎ ትንቢት እንደ
ተናገረ።
27 ነቢዩ ሆሴእም "ኢየሩሳሌም ሆይ! እግዚኣብሄር በላይሽ ላይ
ይመጣል፤ በውስጥሽም ይታያል"[157] ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ።
28 ነቢዩም፣
ለዘላለም ይኖራል፤
ከኣረብም ወርቅ ይሰጡታል፤
ዘወትርም ወደ እሱ ይፀልያሉ።[158]
በተራሮችም ራስ ለምድር ሁሉ መጠጊያ ይሆናል።[159] ብሎ
ትንቢት እንደ ተናገረ።

---

[149] ኢሳ.59፥20
[150] ዘካ.2፥10
[151] ሚክ.4፥2
[152] ?
[153] ኤር.31፥11-12
[154] ሚልክ.3፥1
[155] ዘካ.2፥10
[156] ሚልክ.4፥2
[157] ዘካ.1፥16
[158] መዝ.18፥9

www.ethiopianorthodox.org

29 ወበከመ ተነበየ ኢዮብ ጻድቅ ወይቤ፣ እግዚአብሔር ያንሶሱ ዲበ
ምድር። ወየሐውር ዲበ ባሕር ከመ የብስ።[160]
30 ወበከመ ተነበየ ዳዊት ወይቤ፣ አጽነነ ሰማያተ ወወረደ።[161]
31 ወበከመ ተነበየ ኢሳይያስ ነቢይ ወይቤ፣ ናሁ ድንግል ትፀንስ
ወትወልድ ወልደ። ወትሰምዮ ስሞ አማኑኤል።[162]
32 ወበከመ ተነበየ ዳዊት ነቢይ ወይቤ፣
ወለድኩከ እምከርሥ እምቅድመ ኮከበ ጽባሕ።[163]ወካዕበ ይቤ
እግዚአብሔር፣
ይቤለኒ ወልድየ አንተ።
ወአነ ዮም ወለድኩከ።[164]
33 ወበከመ ተነበየ ጌዴዎን ወይቤ፣ ናሁ ይወርድ ከመ ጠል ውስተ ፀምር።[165]
34 ወበከመ ተነበየ ዳዊት ነቢይ ወይቤ፣ እግዚአብሔር ሐወፀ እምሰማይ
ላዕለ እጓለ እመሕያው
ወእምድልው ጽርሐ መቅደሱ።[166]
35 በከመ ተነበየ ሙሴ ነቢይ ወይቤ፣
ወይብሉ ኩሎሙ ውሉደ እግዚአብሔር ጽኑዕ ውእቱ።
እስመ ይትቤቀል ደመ ደቂቁ።[167]
36 ወበከመ ተነበየ ዳዊት ወይቤ፣
ወበህየ አበቍል ቀርነ ለዳዊት።
ወአስተደሉ ማኅቶተ ለመሲሕየ።
ወአለብሶሙ ኀፍረተ ለጸላእቱ።
ወቦቱ ይፈሪ ቅድሳትየ።[168]
37 ወበከመ ይቤ ሆሴዕ ነቢይ፣ ኢትፍራህ እስመ ኢትትኀፈር
ወኢትደንግፅ በእንተ ዘሰባሕከ።
ወካዕበ ይቤ፣ ስምዑኒ ስምዑኒ ሕዝብየ እስመ ፍትሕየ ርቱዕ።
እመጽእ ወአኀድር ምስሌክሙ። ወይትዌከሉ አሕዛብ በብርሃንየ።[169]
እስመ አሕዛብ ኮኑ ፍቁራኒሁ ለክርስቶስ።
38 ወበከመ ይቤ ዳዊት ነቢይ፣
ሕዝብ ዘኢየአምር ተቀንየ ሊተ።
ውስተ ምስማዐ ዕዝን ተሰጥዉኒ።[170] ወለአይሁድሰ ይቤሎሙ፣
ውሉደ ነኪር ሐሰዉኒ።

---

[160] ?
[161] መዝ.18፥9
[162] ኢሳ.7፥14
[163] መዝ.110፥3
[164] መዝ.2፥7
[165] መሳ.6፥37
[166] መዝ.33፥13
[167] ዘዳ.32፥43
[168] መዝ.132፥17
[169] ኢሳ.54፥4
[170] መዝ.18፥43

- 131 -

29 ፃድቁ ኢዮብም "እግዚአብሄር በምድር ላይ ይመላለሳል፤ በባህርም
ላይ ይሄዳል"[160] ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ።
30 ነቢዩ ዳዊትም "ከሰማያት ዝቅ ዝቅ አለ፤ ወረደም"[161] ብሎ
ትንቢት እንደ ተናገረ።
31 ነቢዩ ኢሳያስም "እነሆ ድንግል ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤
ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች"[162] ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ።
32 ነቢዩ ዳዊትም "ከንጋት ኮከብ አስቀድሞ ከሆድ ወለድኩህ።"[163]
እንደገናም "አንተ ልጄ ነህ። እኔ ዛሬ ወለድኩህ"[164] ብሎ ትንቢት
እንደ ተናገረ።
33 ጌደዎንም "እነሆ እንደ ጤዛ በታጨደ መስከ ላይ ይወርዳል"[165]
ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ።
34 ነቢዩ ዳዊትም "እግዚአብሄር ከሰማይ ከተዘጋጀው ቤተ መቅደሱ
ሆኖ የሰው ልጆችን ተመለከተ"[166] ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ።
35 ነቢዩ ሙሴም "ሁሉም የእግዚአብሄር ልጆች ብርቱዎች ናቸው፤
የልጆቹን ደም ይበቀላልና"[167] ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ።
36 ዳዊትም፣ በዚያ ለዳዊት ቀንድን አበቅላለሁ፣
ለቀባሁትም ሰው መብራትን አዘጋጃለሁ፣
ጠላቶቹንም እፍረትን አለብሳቸዋለሁ፣
በእርሱ ግን ቅድስናየ ያብባል[168] ብሎ ትንቢት እንደ
ተናገረ።
37 ነቢዩ ሆሴእም፣ "አታፍርምና አትፍራ፤ ስለ አመሰገንከም
አትፀናም። ደግሞም ህዝቦቼ ሆይ ስሙኝ፤ ፍርደ ቅን ነውና።
እመጣለሁ፤ ከእናንተም ጋር አድራለሁ፤ አህዛብም በብርሃናችን
ይታመናሉ፤ የክርስቶስ ወዳጆች ሁነዋልና"[169]
38 ነቢዩ ዳዊትም፣
የማላውቀው ህዝብ ተገዛልኝ፤ በጆሮ ሰምተው ተገዙልኝ።[170] እንደ
አለ። አይሁድን ግን፣

---

[159] መዝ.72፥15
[160] ?
[161] መዝ.18፥9
[162] ኢሳ.7፥14
[163] መዝ.110፥3
[164] መዝ.2፥7
[165] መሳ.6፥37
[166] መዝ.33፥13 መዝ.33፥13
[167] ዘዳግ.32፥43
[168] መዝ.132፥17
[169] ኢሳ.54፥4
[170] መዝ.18፥43

www.ethiopianorthodox.org

ውሉደ ነኪር በልዩ።
ወሐንከሱ በፍኖቶሙ።
ሕያው እግዚአብሔር ወቡሩክ አምላኪየ።[171]
ሕያው እግዚአብሔር ሶበ ይብለከ በእንተ መለኮቱ ይነግር። ወቡሩክ
አምላኪየ ሶበ ይብለከ በእንተ እንተ ለብሰ ሥጋ ይነግር።
39 ወካዕበ ይቤ በእንተ እንተ ለብሰ ሥጋ በኢሳይያስ ነቢይ፣ መኑ
ዝንቱ መካሕ ዘይወጽእ እምኤዶም። አዶናይ ዘወረደ እምሰማይ
ወይለብስ ዘባሶር ግሩም።[172] መካሕ ሶበ ይብል ዘመዐዛሁ ሠናይ።
ወአዶናይ ብሂል ቃለ አብ ዘእምቅድመ ዓለም። ወልደ እግዚአብሔር
ይለብስ ዘባሶር ግሩም። ሶበ ይብል ሥጋሁ ለአዳም ገሀደ ያርኢ።
40 ወበከመ ተነበየ ዳዊት ነቢይ እንዘ ይብል በእንተ ሕዝበ ክርስቲያን፣
በልዎሙ ለአሕዛብ ከመ እግዚአብሔር ነግሠ።
ወአጽንዓ ለዓለም ከመ ኢታንቀልቅል።[173] ወካዕበ ተነበየ በእንተ
ምጽአቱ ኀበ አሕዛብ ወይቤ፣
እምቅድመ ገጹ ለእግዚአብሔር እስመ ይመጽእ።
ይመጽእ ወይኴንና ለምድር።
ወይኴንና ለዓለም በጽድቅ።
ወለአሕዛብኒ በርትዕ።[174]
41 ወበከመ ተነበየ ኢሳይያስ ነቢይ ወይቤ፣ እግዚአብሔር ጸባኦት መከረ
ይስዐር ጽዕለቶሙ ለአሕዛብ። ወያኅሥሮሙ ለክቡራን ዐበይተ
ምድር።[175]
ወዓዲ አትለወ ትንቢቶ ወይቤ፣ ይመጽእ ወየሐንጽ ቤቶ። ወያድኅን
ሕዝቦ።[176] ወዓዲ ወሰከ ወይቤ፣ ወውእተ አሜረ ይሠርፅ እምሥርወ
እሴይ። ዘተሠይመ መልአከ አሕዛብ። ወይትዌከሉ ቦቱ አሕዛብ።
ወይከውን ክብር ምዕራፊሁ ለዓለም።[177]
42 ወበከመ ተነበየ ዳዊት ወይቤ፣
ዘምሩ ለእግዚአብሔር ዘየኀድር ውስተ ጽዮን።
ወንግርዎሙ ለአሕዛብ ምግባሮ።[178]
43 ወበከመ ተነበየ ሰሎሞን ወልዱ ወይቤ በእንተ መድኀኒነ አማኑኤል
ፀሐየ ጽድቅ፣ እምቅድመ አውግር ወለደኒ።

---

[171] መዝ.18፥45-46
[172] ኢሳ.63፥1
[173] መዝ.96፥10
[174] መዝ.96፥13፥98፥9
[175] ?
[176] ኢሳ.11፥1
[177] ኢሳ.11፥10
[178] መዝ.105፥1-2



የባእድ ልጆች ደለሉኝ፤
የባእድ ልጆች አረጁ፤
በመንገዳቸውም ተሰናከሉ፤
እግዚአብሄር ህያው ነው፤
አምላኬም ቡሩክ ነው።[171] ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ።
እግዚአብሄር ህያው ነው ሲል ስለ መለኮቱ ይናገራል። አምላኬም
ብሩክ ነው ሲል ስለ ለበሰው ስጋ ይናገራል። ደግሞም ስለ ለበሰ
ው ስጋ በነቢዩ ኢሳያስ "ከኤዶም የሚወጣውና ከሰማይ የወረደ
ትምክህተኛ ጌታ ይህ ማነው? ከሰማይ የሚወጣና ግሩም ስጋን
የለበሰ ትምክህተኛ ይህ ማነው?"[172] መአዛው ጣፋጭ ጌታ ማለትም
ግሩም ስጋን የለበሰና ከቅድመ አለም በፊት ጀምሮ የእግዚአብሄር
ልጅ የሆነ የአብ ቃል ማለት ነው። ይሄውም የአዳምን ስጋ
በማለቱ በግልፅ ይታወቃል።
39 ነቢዩ ዳዊትም ስለ ህዝበ ክርስቲያን፣
እግዚአብሄር በአህዛብ መካከል ነገሰ በሏቸው። እንዳይናወጥም
አለሙን እርሱ አፀናው።[173]
ሲል ትንቢት እንደ ተናገረ። ደግሞም ወደ አህዛብ ስለ መምጣቱ፣
በእግዚአብሄር ፊት ይመጣል፤
በምድርም ላይ ሊፈርድ ይመጣልና፤
እርሱ አለምን በፅድቅ፣ አህዛብንም በቅንነት ይፈርዳል።[174]
በማለት ትንቢት ተናገረ።
40 ደግሞም ነቢዩ ኢሳይያስ፣ "ያለና የሚኖር እግዚአብሄር የአህዛብን
ስድባቸውን ያስወግድ ዘንድ መከረ፣ የከበሩትንም የምድር
ታላላቆችን ያዋርዳቸው ዘንድ ፈለገ"[175]ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ።
41 ደግሞም "ይመጣና ቤቱን ይሰራል፣ ህዝቡንም ያድናል"[176] ሲል
ትንቢቱን አስከተለ። ደግሞም "ያን ጊዜ የአህዛብ ገዥ የተባለው
ከእሴይ ግንድ ይበቅላል፤ አህዛብም ይተማመኑበታል፤ የአለምም
ማረፊያ ክብር ይሆነዋል።"[177] ሲል ጨምሮ ተናገረ
42 ደግሞም ዳዊት፣ በፅዮን ለሚያድረው ለእግዚአብሄር ዘምሩ፤
ስራውንም ለአህዛብ አውሩ።[178] ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ።
43 ደግሞም ልጁ ሰሎሞን ስለ መድሃኒታችን ስለ እውነተኛው ፀሃይ
ስለ አማኑኤል "ከተራሮች በፊት ወለደኝ፣ አገሮችን ከማጸናወኑና

---

[171] መዝ.18፥45-46
[172] ኢሳ.63፥1
[173] መዝ.96፥10
[174] መዝ.96፥13፥98፥9
[175] ?
[176] ኢሳ.11፥1
[177] ኢሳ.11፥10
[178] መዝ.105፥1-2

www.ethiopianorthodox.org

ወእምቅድመ ይጣእጥእ ወይግበር በሐውርተ ወእምቅድመ ዓለም
ሣረረኒ። ዘእንበለ ምድረ ይግበር ወዘእንበለ ቀላያተ ይግበር
ወዘእንበለ ይፃእ እንቅዕተ ማያት ወያስተርኢ ሥነ ጽጌያት
ወእምቅድመ ይንፋሕ ነፋሳተ አየር እግዚአብሔር ፈጠረ ለምግባሩ
ቅድመ ገጹ። ወሀሎኩ አስተዋድድ ምስለ አቡየ።[179]
44 ወበከመ ተነበየ አቡሁ ዳዊት ወይቤ፣
እምቅድመ ፀሐይ ሀሎ ስሙ።
ወእምቅድመ ወርኅ ለትውልደ ትውልድ።[180]
45 ወበከመ ተነበየ ሰሎሞን ወልዱ ወይቤ፣ አመ ጽኑዐ ይገብር
መልዕልተ ደመናት ወአመ ያነብር ምንባረ አረፋተ አጽናፈ ሰማያት
ወአመ ያነብራ ለባሕር በዐቅማ ወእምቅድመ ይሣርር መንበሮ
መልዕልተ ነፋሳት ወአመ ጽኑዐ ይገብር መሠረታተ ምድር ሀሎኩ
ምስሌሁ አስተዋድድ እለ ውእቱ ለእንተ ይትፌሣሕ ወትረ እንተ
ጸብሐት ወእትሐሠይ ምስሌሁ በኩሉ ጊዜ በቅድመ ገጹ።[181]
46 ወበከመ ተነበየ ኢዮብ ነቢይ ወይቤ፣ ዘውእቱ ገጸ አምላኪየ ምሥራቅ
ወእምቅድመ ፀሐይ ብርሃኑ። ወይትዌከሉ አሕዛብ በስሙ።[182]
47 ወበከመ ተነበየ ኢሳይያስ ነቢይ ወይቤ፣ ኢትዝክሩ ዘትካት።
ወኢተኀልዩ ዘቀዲሙ። ናሁ አነ እገብር ሐዲስ ዘይእዜ ይሠርቅ።
ወከመ ታእምሩ እገብር ፍኖተ ውስተ በድው። ወአውኀዝ ማየ
ውስተ ገዳም። ወይድኀሩኒ አራዊተ ገዳም ወዕጓለ አዕዋፍ ወሴሬኒሲ።
እስመ ወሀብኩ ማየ ውስተ በድው። ወአውኀዝኩ ውስተ ገዳም ከመ
አስትዮሙ ለሕዝብየ። ወለኀሩያንየ እለ አጥረይኩ ከመ ይንግሩ
ስብሐትየ ወይግበሩ ትእዛዝየ።[183]
48 ወበከመ ተነበየ ሰሎሞን ወይቤ፣ መኑ ዐርገ ውስተ ሰማይ ወወረደ።
ወመኑ አስተጋብአ ነፋሳተ ውስተ ሕፅኑ። ወመኑ ዘዐቈረ ማያተ
በልብሱ። ወመኑ ሰፈረ ማየ ባሕር በሕፍኑ። ወሰማየኒ በስዝሩ።
ወመኑ ስሙ። ወመኑ ስመ ወልዱ።[184]
49 ወበከመ ተነበየ ሚክያስ ነቢይ ወይቤሎሙ ለአይሁድ፣ ኢይሠምር
መሥዋዕተክሙ። ወኢይትመጠው ቁርባነ እምኔክሙ። እስመ እምሥራቀ
ፀሐይ እስከ ዐረብ ይሴባሕ ስምየ። በውስተ ኩሉ አሕዛብ ወበኩሉ
በሐውርት ይትቄረብ ዕጣን ለስምየ። ዐቢይ በውስተ ኩሉ ይቤ
እግዚአብሐር ዘኩሉ ይመልክ።[185]

[179] ምሳ8፡22
[180] መዝ.72፡5-7
[181] ምሳ8፡30
[182] ሕዝ.43፡1-2
[183] ኢሳ.35፡6-8፡43፡19
[184] ምሳ.30፡4፡ኢሳ.40፡12
[185] ሚልክ.1፡10-11፡

- 133 -

ከመስራቱ ከአለም በፊት ሰራኝ። ምድርን ሳይሰራ፣ ወንዞችንም
ሳይሰራ፣ የወንዞችንም ምንጮች ሳይፈልቁ፣ አበቦች ሳያብቡ፣ የአየር
ነፋሳት ሳይነፍሱ እግዚአብሄር ስራውን በፊቱ ሰራት። ከአባቴም
ጋር አስማማ ነበር[179] ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ።
44 አባቱ ዳዊትም፣
ስሙ ከፀሃይ በፊት ነበር፣
ከጨረቃም በፊት ለለጅ ልጅ።[180] በማለት ትንቢት እንደ
ተናገረ።
45 ልጁ ሰሎሞንም "በደመናት ላይ ሃይልን በሚያደርግበት ጊዜ፣ በሰ
ማዮችም ዳርቻ ግድግዳ ላይ ዙፋኑን ባስቀመጠ ጊዜ፣ ባህርንም
በመጠኗ ባስቀመጣት ጊዜ፣ ዙፋኑንም በነፋሳት ላይ ከመመስረቱ
በፊት፣ የምድርንም መሰረቶች ፅኑአ በሚያደርግበት ጊዜ ከእሱ
ጋር እያስማማሁ ነበርኩ። በነጋ ቁጥር ዘወትር ደስ ከሚሰኝ ከእሱ
ጋር እኔም ዘወትር እደሰታለሁ[181] ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ።
46 ነቢዩ ኢዮብም "የአምላኬ ፊት ምስራቅ ነው፣ ብርሃኑም ከፀሃይ በፊት
ነው፣ አህዛብ በስሙ ይተማመናሉ"[182] ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ።
47 ነቢዩ ኢሳይያስም "የጥንቱን አስታውሱ፣ የፊቱንም አታስቡ፣ እነሆ
እኔ ዛሬ የወጣ አዲስ አደርጋለሁ፣ መንገድን ብምድረ በዳ እንደ
ማደርግ፣ ውሃን በበረሃ እንደማፈስና የዱር አራዊትና የወፍ
ጫጩቶች ሰጎኖችም እንዲያመሰግኑኝ፣ ምስጋናዬን ይነግሩና
ትእዛዜንም ይጠብቁ ዘንድ የመረጥኳቸው ህዝቦቼና ምርጦቼን
አጠጣቸው ዘንድ በምድረ በዳ ውሃን እንደሰጠሁ፣ በበረሃም
እንዳፈሰስኩ ታውቁ ዘንድ"[183] ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ።
48 ሰሎሞንም "ወደ ሰማይ ማን ወጣ? ማንስ ወረደ? ነፋስን በእፍኙ
የሰበሰበ ማነው? ውሃንስ በልብሱ የቋጠረ ማነው? የባህርንስ ውሃ
በእፍኙ የሰፈረው ማነው? ሰማይንም በስንዝሩ የለካ ማነው? ስሙ
ማነው? የልጁስ ስም ማነው?"[184] ብሎ ትንቢት እንደተ ናገረ።
49 ነቢዩ ሚክያስም "ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሄር አይሁድን
አልወዳችሁም። መስዋእታችሁንም አልወድም። ከእጃችሁም ቁርባንን
አልቀበልም። ከፀሃይ መውጫ እስከ መግቢያዋ ድረስ በአህዛብ
ሁሉ በአገር ሁሉ ውስጥ ስሜ ይመሰገናል። ለታላቁም ስሜ በሁሉ
ይቀርባል አለ ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሄር"[185] ብሎ ትንቢት እንደ
ተናገረ።

[179] ምሳ.8፡22
[180] መዝ.72፡5-7
[181] ምሳ.8፡30
[182] ሕዝ.43፡1-2
[183] ኢሳ.43፡19፡35፡6-8
[184] ምሳ.30፡4፡ኢሳ.40፡12
[185] ሚልክ.1፡10-11

www.ethiopianorthodox.org

50 ወካዕበ ይቤ ሚክያስ ነቢይ፣ ሐዲስ ሥርዓት ያስተርኢ ደብረ
እግዚአብሔር። ወጽልመት ውስተ አርእስተ አድባር። ወይትሌዐል
መልዕልተ አውግር። ወይብሉ ንዑ ንዕርግ ውስተ ደብረ
እግዚአብሔር። ወየሐውሩ ኀቤሁ ብዙኃን አሕዛብ። ወይብሉ ንዑ
ንዕርግ ውስተ ደብረ እግዚአብሔር። ወይንግሩነ ፍኖቶ ወንሑር ባቲ።[186]
51 ወበከመ ተነበየ ዳዊት ወይቤ፣
ስምዐኒ ሕዝብየ ወእንግርከ።
እስራኤል እሰምዕ ለከ
አምላክከሰ አምላክ አነ ውእቱ።[187]
52 ወበከመ ተነበየ ሙሴ ነቢይ ወይቤ በእንተ ሥላሴ፣ ስማዕ እስራኤል
አሐዱ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክከ።[188] ወዘንቱሰ ይትፌከር አብ
ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ ውእቱ። አምላክ ዘአሐቲ
መንግሥቶሙ። ወአሐቲ ሥልጣኖሙ። ወአሐተ ይሰግዱ ሎሙ በሰማይ
ወበምድር በባሕር ወበቀላያት። ወሎቱ ስብሐት ለዓለመ ዓለም።
አሜን

## ፲ወ፺ በእንተ በአቱ ኢየሩሳሌም በስብሐት

1 ወበእንተ በአቱ ኢየሩሳሌም በስብሐት ተነበዩ ነቢያት እንዘ ይብል
ኢሳይያስ ነቢይ፣ አብርሂ አብርሂ ኢየሩሳሌም በጽሐ ብርሃንኪ።
ወስብሐ እግዚአብሔር ሠረቀ ላዕሌኪ።[189]
2 ወበከመ ተነበየ ዘካርያስ ነቢይ ወይቤ፣ ተፈሥሒ ተፈሥሒ ወለተ
ዳዊት።[190]
3 ወይቤ፣
እምአፈ ደቂቅ ወሕፃናት አስተዳሎከ ስብሐተ።
በእንተ ጸላኢ።
ከመ ትንሥቶ ለጸላኢ ወለገፋዒ።[191]
4 ወበከመ ተነበየ ሰሎሞን ወይቤ፣
ደቂቅኪ ምሁራን በኀበ እግዚአብሔር።
ወይትፌሥሑ አሕዛብ በውስቴትኪ።[192]
5 ወበከመ ተነበየ ዳዊት አቡሁ ወይቤ፣
ንፍኁ ቀርነ በጽዮን በዕለተ ሠርቅ።
በእምርት ዕለት በዓልነ።
እስመ ሥርዐቱ ለእስራኤል ውእቱ።[193]

---

[186] ኢሳ.2፥3፥ሚክ.4፥2
[187] መዝ.50፥7
[188] ዘዳ.6፥4
[189] ኢሳ.60፥1
[190] ዘካ.9፥9፥ሶፍ.3፥14
[191] መዝ.8፥2
[192] ኢሳ.54፥13

- 134 -

50 ደግሞም ነቢዩ ሚክያስ "በእግዚኣብሄር ተራራ ኣዲስ ልርኣት
ይታያል፤ በተራሮችም ርእሶች ላይ ተዘጋጅታለች፤ በተራራ ላይም
ከፍ ከፍ ይላል፤ ኑ፤ ወደ እግዚኣብሄር ተራራ እንውጣ፤
እንሄድበትም ዘንድ መንገዱን ይንገሩን።"[186] ኣለ።
51 ነቢዩ ዳዊት፣
ህዝቤ ሆይ ስማኝ፤
እስራኤል ሆይ እመሰክርብሃለሁ፤
ኣምላክህስ እኔ ነኝ[187] ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ።
52 ነቢዩ ሙሴም "እስራኤል ሆይ ስማ፣ ኣምላክህ እግዚኣብሄር ኣንድ
ነው"[188] አለ። መንግስታቸውና ስልጣናቸው ኣንድ የሆነና በሰማይና
በምድር በባህርና በቀላያት በኣንድነት የሚሰገድላቸው ኣብ፣
ወልድና መንፈስ ቅዱስ ኣንድ ኣምላክ እንደሆነ ይተረጉማል።
ለእሱ ለዘላለሙ ምስጋና ይገባል ኣሜን በማለት ትንቢት እንደ
ተናገረ።

## ፲ወ፺ ኢየሩሳሌም በምስጋና ስለ መግባቱ

1 ኢየሩሳሌም በምስጋና ስለ መግባቱ ነቢያት ትንቢት ተናገሩ።
ኢሳይያስም "ኢየሩሳሌም ሆይ ብርሃንሽ ደርሷልና ፈፅመሽ ኣብሪ፣
የእግዚኣብሄር ምስጋና በላይሽ ላይ ወጥቷልና"[189] ሲል ትንቢት
ተናገረ።
2 ነቢዩ ዘካርያስም "የፅዮን ልጅ ሆይ ፈፅሞ ደስ ይበልሽ፤ ደስ
ይበልሽ፤ ኢየሩሳሌም ሆይ በደስታ እልል በይ"[190] ብሎ ትንቢት
እንደ ተናገረ።
3 ዳዊትም፣ ከህፃናትና ከሚጠቡ ልጆች ኣፍ ምስጋናን ኣዘጋጀህ፤
ስለ ጠላት ጠላትንና ቂመኛን ለማጥፋት[191] ብሎ እንደ
ተናገረ።
4 ሰሎሞንም "ልጆችሽ ከእግዚኣብሄር ዘንድ የተማሩ ናቸው።
ኣህዛብም በውስጥሽ ደስ ይሰኛሉ"[192] ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ።
5 ኣባቱ ዳዊትም፣
በመባቻ ቀን፣
በከፍተኛው በኣላችን ቀን፣
በፅዮን ውስጥ መለከትን ንፉ፤

---

[186] ሚክ.4፥2፥ኢሳ.2፥3
[187] መዝ.50፥7
[188] ዘዳግ.6፥4
[189] ኢሳ.60፥1
[190] ዘካ.9፥9
[191] መዝ.8፥2
[192] ኢሳ.54፥13

www.ethiopianorthodox.org

6 ወበከመ ተነበየ ዕዝራ ጸሓፊ ወይቤ፤ ፃኡ ግበሩ በዓለ
በትፍሥሕት። ወበልዋ ለወለተ ጽዮን ተፈሥሒ። ነዋ ንጉሥኪ
በጽሐ።[194]
7 ወበከመ ተነበየ ኢሳይያስ ነቢይ ወይቤ፤ ተፈሥሒ ኢየሩሳሌም።
ተፈሥሒ ነዋ ንጉሥኪ በጽሐ። እንዘ ይጼዐን ዲበ ዕድግት።
ዘዕሤቱ ምስሌሁ ወምግባሩ ቅድመ ገጹ።[195]
8 ወበከመ ተነበየ ዳዊት ነቢይ ወይቤ፤ ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ
እግዚአብሔር።[196]
9 ወበከመ ተነበየ ያዕቆብ ወልደ ይስሐቅ ወይቤ፤ ይሁዳ ሰብሑከ
አኀዊከ እደዊከ ላዕለ ዘባናሙ ለጸላእትከ ወይሰግዱ ለከ ደቂቀ
እምከ ወኢየሐጽጽ ምልክና እምይሁዳ ወምስፍና እምአባሉ እስከ
አመ ይረክብ ዘጽኑሕ ሎቱ ወውእቱ ተስፋሆሙ ለአሕዛብ።[197]
10 ወካዕበ ተነበየ ወይቤ፤ ጸዓዳ ስነኒሁ ከመ ዘበረድ። ወፍሡሓት
አዕይንቲሁ ከመ ወይን። ወየኀፅብ በወይን ልብሶ። ወበደመ
አስካል ሰንዱኖ።[198]
11 ወካዕበ ተነበየ እንዘ ይብል፤ ይሁዳ ወልደ አንበሳ ሰከብከ
ወኖምከ። አልቦ ዘያነቅሖ አላ ለሊሁ እስከ ይረክብ ዘነዐወ
እምሕዝአትከ ዕርግ።[199]
12 ወካዕበ ባረኮ ለይሁዳ ወልዱ ያዕቆብ ወይቤሎ ሀሎ ንጉሥ
ዘይወፅእ እምኔከ። ዘየኀፅብ በወይን ልብሶ።[200] ወከቡር ምዕራፊሁ
ለፍቁር። ወፍቁር ብሂል ክርስቶስ ብሂል። ወመሲሕ ብሂል
ክርስቶስ ብሂል። ወኢየሱስ ብሂል መድኀኔ ሕዝብ ብሂል።
13 ወነቢያትሰ ይሰምይዎ በስውር ለክርስቶስ ወይብልዎ ፍቁር። ወይቤ
ኢሳይያስ ኀበ ዕርገቱ በትንቢት ውእተ አሚረ ይወርድ ፍቁር
እምሰማይ። ወየኀሪ ሎቱ ፲ወ፪ ሐዋርያተ።[201]

[193] መዝ.81፥3
[194] ዘካ.9፥9፥ሶፍ.3፥14
[195] ዝኒ ከማሁ
[196] መዝ.118፥26
[197] ዘፍጥ.49፥8-10
[198] ዘፍጥ.49፥11-12
[199] ዘፍጥ.49፥11-9
[200] ዝኒ ከማሁ
[201] ?



ይህም ለእስራኤል ስርአቱ ነው[193] በማለት ትንቢት እንደ
ተናገረ።
6 ፀሃፊው እዝራም "ውጡና በደስታ በአልን አድርጉ፤ የፅዮንንም
ልጅ ንጉስሽ መጥቷልና ደስ ይበልሽ"[194] ሲል ትንቢት እንደ
ተናገረ።
7 ነቢዩ ኢሳይያስም "ኢየሩሳሌም ሆይ! እነሆ ንጉስሽ በአህያ ተጭኖ
መጥአልና ፈፅሞ ደስ ይበልሽ። ዋጋው ከእሱ ጋር ነው። ስራውም
በፊቱ ነው"[195] ሲል ትንቢት እንደ ተናገረ።
8 ነቢዩ ዳዊትም "በእግዚአብሄር ስም የሚመጣ የተባረከ ነው"[196] ብሎ
ትንቢት እንደ ተናገረ።
9 የይስሃቅ ልጅ ያእቆብም "ይሁዳ ወንድሞችህ አንተን ያመሰግኑሃል፤
እጅህ በጠላቶችህ ደንደስ ላይ ነው፤ የአባትህ ልጆች በፊትህ
ይሰግዳሉ፤ በትረ መንግስት ከይሁዳ አይጠፋም፤ የገዥም ዘንግ
ከእግሮቹ መካከል። ገዥ የሆነው እስከሚመጣ ድረስ፤ የአህዛብ
ተስፋቸው እሱ ነው"[197] በማለት ትንቢት እንደ ተናገረ።
10 ደግሞም "ጥርሱ ከበረዶ ነጭ ነው። አይኑም ከወይን ይቀላል።
ልብሱን በወይን ያጥባል። መጎናጸፊያውንም በወይን ደም"[198] ሲል
ትንቢት እንደ ተናገረ።
11 ደግሞም "ይሁዳ የአንበሳ ደቦል ነው፤ እንደ አንበሳ አሸመቀ፤
የሚያድነውን እስኪያገኝ ድረስ፤ ያስነሳው ዘንድ ማን ይችላል?
ከዋሻህ ውጣ አለው"[199] በማለት ትንቢት እንደ ተናገረ።
12 ደግሞም ያእቆብ "ልብሱን በወይን የሚያጥብና ከአንተ የሚወጣ
ንጉስ አለ"[200] ሲል ልጁን ይሁዳን መረቀው። "የወዳጁ ማረፊያው
የከበረ ነው" አለ። ወዳጅ ማለትም ክርስቶስ ማለት ነው። ኢየሱስ
ማለትም የህዝብ መድሃኒት ማለት ነውና።
13 ነቢያት ግን ክርስቶስን በምስጢር አነጋገር ወዳጅ ይሉታል።
ኢሳይያስም እርገተ ኢሳይያስ በተባለው የትንቢት መፅሃፍ "በዚያን
ጊዜ ወዳጁ ከሰማይ ይወርዳል፤ አስራ ሁለት ሃዋርያትንም
ይመርጣል"[201] አለ።

[193] መዝ.81፥3
[194] ዘካ.9፥9
[195] ዝኒ ከማሁ።
[196] መዝ.118፥26
[197] ዘፍጥ.49፥8-10
[198] ዘፍጥ. 11-12
[199] ዝኒ ከማሁ
[200] ?
[201] ?

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

14 ወካዕበ ይቤ፣ ርኢኩ ዕርገቶ ለፍቁር ወልድ እስከ ሳብዕ ሰማይ።
ወእንዘ የተቀበልዎ መላእክት ወሊቃነ መላእክት እንዘ ይትሌዐል
ፈድፋደ እምኔሆሙ።[202]
15 ወዳዊትኒ ይቤ፣ ወፍቁርሰ ከመ ወልድ ዘ፩ ቀርኑ። ወካዕበ ይቤ
ወእምአቅርንት ዘ፩ ቀርኑ ለብሕቱትየ። ወካዕበ ይቤ ወይትሌዐል
ቀርንየ ከመ ዘ፩ ቀርኑ።[203] አቅርንትሰ ይተረጐም በመንግሥታተ
ዓለም። ወዘይትበሀልሂ ዘ፩ ቀርኑ ለመንግሥቱ አልቦ ዘይትቃረኖ።
እስመ መላኬ ነገሥት ውእቱ። ለዘፈቀደ ይስዕር ወለዘፈቀደ ይሠይም።
16 በከመ ይቤ ዳዊት ወእምክቡዳነ አቅርንት ዘእምኔሆሙ
አስተፌሥሐከ።[204] ወዝንቱ ዘተብህለ እምክቡራን ነገሥት አንተ
ትከብር ወትትፌሣሕ ብሂል።
17 ወበከመ ተነበየ ዕንባቆም እንዘ ይብል፣
አቅርንት ውስተ እደዊሁ።
ወረሰየ ፍቁረ በጽንዐ ኀይሉ።[205] ወዝንቱኒ ብሂል አኀዜ ሥልጣነ
ነገሥት በቅንዋት። ተቀነወ እራሁ ዘሕይወተ ኩሉ ውስቴቶን
እትዝ። ዘገብረ ክርስቶስ በጽንዐ ኀይሉ ፍቁር ብሂል።

## ፲ወ፰ በእንተ እከየ ይሁዳ ዕልው

1 ወበእንተ እከዩ ለይሁዳ ረሲዕ ተነበዩ ነቢያት። ወይቤ ዳዊት
በእንቲኣሁ፣
ለብእሲ ዓማፂ ይንዕዎ እኪት ለአማስኖ።[206]
ወካዕበ ይቤ
ወይገብእ ጻማሁ ዲበ ርእሱ።
ወትወርድ ዓመፃሁ ዲበ ድማሁ።[207]
2 ወበከመ ተነበየ ሰሎሞን ወልዱ ወይቤ፣ ብእሲ አብድ ወዓማፂ
የሐውር ፍናዋተ ዘኢኮና ርቱዐተ። ወውእቱሰ ይቀጽብ በዐይን
ወይደምር በእግር። ወይሁብ ትእምርተ በቅጽበተ አጻብዕ ወበአጽንኖ
ከናፍር። ወዕሉት ልቡ ትጌሊ እኪተ በኩሉ ጊዜ። ዘከመዝ ብእሲ
ያመጽእ ሐከከ ወቀትለ ወከዒወ ደም በዓመፃ ወኢያመስጥ
እምደይን።[208]
3 ወበከመ ተነበየ ዳዊት አቡሁ ወይቤ፣
ነገረ ጌጋይ አውፅኡ ላዕሌየ።
ዘኖመሰ ኢይነቅሕኑ እንከ።

---

[202] ዕርገተ ኢሳይያስ
[203] መዝ.22፡20-21
[204] መዝ.92፡10
[205] እንባ.3፡4
[206] ምሳ.19፡16
[207] መዝ.7፡16
[208] ምሳ.6፡7



14 ደግሞም "መላእክትና ሊቃነ መላእክት ሲቀበሉትና ከእነሱም ፈፅሞ
ከፍ ከፍ ሲል የወዳጄንና የብላቴናየን እርገቱን እስከ ሰባተኛው ሰ
ማይ ድረስ አየሁ"[202] አለ።
15 ዳዊትም "ወዳጁስ አንድ ቀንድ እንዳለው ልጅ ነው" አለ።
ደግሞም "ከቀንዶች ሁሉ ተለይቶ ለብቻው የሆነ ቀንድ" አለ።
ደግሞም "ቀንዱ አንድ ቀንድ እንዳለው ከፍ ከፍ ይላል" አለ[203]።
ቀንዶች በኣለም መንግስታት ይተረጎማሉ። አንድ ቀንድ ማለትም
መንግስቱን የሚቀናቀነው የለም ማለት ነው። የነገስታት ገዥ
ነውና። የወደደውን ይሾመዋል። ያልወደደውን ይሽረዋል።
16 ዳዊትም "ዝሆን ጥርሶች ኣዳራሽ ደስ ያሰኙሃል"[204] ኣለ። ይህም
የተባለው ከከበሩ ነገስታት ኣንተ ትከብራለህ ማለት ነው።
17 እንባቆምም "ስልጣኖች በእጁ ናቸው፤ ወዳጅንም በሃይሉ ብርታት
አደረገ"[205] ብሎ ትንቢት እንደተናገረ ይህም የነገስታትን ስልጣን
ያዥና የሁሉም ህይወት በውስጣቸው ያለውን እጆቹ በችንካር
ተቸነከረ ማለት ነው። ክርስቶስ በሃይሉ ብርታት ያደርገው
ማለትም በፍቅሩ ማለት ነው።

## ፲፰ ስለከሃዲው ስለ ይሁዳ ክፋት

1 ስለ ሃጥኡ ይሁዳም ክፋት ነቢያት ትንቢት ተናገሩ። ዳዊትም ስለ
እሱ፣ ኣመፀኛውን ክፋት ልታጠፋው ትፈልጋለች። [206]
ደግሞም በደሉ ወደ እርሱ ይመለሳል፤
ኣመፃውም በራሱ ላይ ትወርዳለች[207] ኣለ።
2 ልጁ ሰሎሞን ሰነፍና "ክፉ ሰው ቀና ያልሆኑ መንገዶችን
ይሄዳል" ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ። "እሱ በኣይን ይጠቅሳል፣
በእግርም ይጨምራል። ምልክትን በእጁ ጥቅሻ በቃልም በማስረገጥ
ይሰጣል። ከሃዲ ልቡም ሁልጊዜ ክፋትን ታስባለች። እንደዚሁ ያለ
ሰው ሁከትን ግድያንና በበደልም ደም መፍሰስን ያመጣል።
ከመከራ ኣያመልጥም"[208] ብሎ ትንቢት እንደተናገረ።
3 ኣባቱ ዳዊትም፣
በእኔ ላይ ክፋትን ያስባሉ፤
ደግሞም የሰላሜ ሰው የታመንሁበት፤

---

[202] ?
[203] መዝ.22፡20-21
[204] መዝ.92፡10
[205] እንባ.3፡4
[206] ምሳ.19፡16
[207] መዝ.7፡16
[208] ምሳ.6፡7

www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

ብእሴ ሰላምየ ዘኪያሁ እትአመን።
ዘይሴሰይ እክልየ አንሥአ ሰኰናሁ ላዕሌየ።[209]
4 ወበከመ ተነበየ ኢሳይያስ ነቢይ ወይቤ፣
አሌ ሎቱ ለብእሲ ዓማፂ ዘያመጽአ ለመንሱት።[210]
5 ወካዕበ ይቤ ያአትትዎ ለኀጥእ ከመ ኢይርአይ ስብሐተ
እግዚአብሔር።[211]
ወበከመ ተነበየ ዳዊት ነቢይ ወይቤ፣
ይነብብ ኀጥእ በዘያስሕት ርእሶ።
ወአልቦ ፍርሀተ እግዚአብሔር ቅድመ አዕይንቲሁ።[212]
6 ወበከመ ተነበየ ሰሎሞን ወልዱ ወይቤሎ፣ ፀዋግ ብእሲ ሐከከ
ያመጽእ ለሀገር። ወያመጽእ በእንቲኣሁ ተሀጕሎተ ወዝብጠተ
ወቅጥቃጤ ዘኢየሐፁ። እስመ ይትፌሣሕ በኵሉ ዘይጸልእ
እግዚአብሔር።[213]
7 ወበከመ ተነበየ ሙሴ ነቢይ ወይቤ፣ ኢይፈቅድ እግዚአብሔር
ይስረይ ዘእንበለ ዘያፈደፍድ በቀለ ላዕሌሁ ወያነብር መቅሠፍተ
ዲቤሁ። ወይከውን ላዕሌሁ ዘጽሑፍ ውስተ ዝንቱ መጽሐፍ
መርገም። ወይደመሰስ ስሙ እምታሕተ ሰማይ።[214]
8 ወበከመ ተነበየ ዳዊት ነቢይ ወይቤ፣
ጥቡዕ ልቡ ለቀቲል።
አብደራ ለመርገም ወትምጽኦ።
አበያ ለበረከት ወትርሐቅ እምኔሁ።[215]
9 ወበከመ ተነበየ ኤርምያስ ነቢይ በእንቲኣሁ ወይቤ፣ ብእሲ ፀዋግ
ይትሀጐል በእንተ ፍቅረ ብሩር። ወይሬኢ ጽልመተ በእንተ
ጕህሉቱ።[216]
10 ወበከመ ተነበየ ኢዮብ ወይቤ በእንቲኣሁ፣ ይዘርዎ መሠንዮ ፈጣሪሁ።
ወይየብስ ሥረዊሁ በታሕቴሁ። ወይትነገፍ ጽጌ በመልዕልቴሁ።
ወይጠፍእ እምድር ዝክሩ። ወይርኀቅ ስሙ ነዋኀ። ወያፈልስዎ
ውስተ ጽልመት ከመ ኢይርአይ ብርሃነ። ለብእሲ ዓማፂ ይጠፍእ
ቤቱ።[217]

---

[209] መዝ.41፥9
[210] ኢሳ.10፥1
[211] ኢሳ.26፥9-10
[212] መዝ.36፥1
[213] ?
[214] ዘዳግ.29፥20
[215] መዝ.109፥17
[216]?
[217] ኢዮ.18፥16

- 137 -

እንጀራየን የበላ በእኔ ላይ ተረከዙን አነሳ[209] ብሎ
ትንቢት እንደ ተናገረ።
4 ነቢዩ ኢሳይያስም "ጥፋትን የሚያመጣት ክፉ ሰው ወዮለት"[210] ሲል
ትንቢት እንደ ተናገረ። ደግሞም "የእግዚአብሄርን ክብር እንዳያይ
ያስወግዱት"[211] አለ።
5 ነቢዩ ዳዊትም፣ ሃጢኣተኛ በራሱ ላይ የሚያስት ነገርን ይናገራል፤
ፈሪሃ እግዚኣብሄርም በኣይኖቹ ፊት የለም[212] ብሎ
ትንቢት እንደ ተናገረ፤
6 ልጁ ሰሎሞንም "ክፉ ሰው ለኣገር ጥፋትን ያመጣል። በእሱም
ምክንያት ጥፋትን፣ ዱላንና የማይድን ስብራትንም ያመጣል፤
እግዚኣብሄር በሚጠላው ሁሉ ደስ ይሰኛልና" ብሎ ትንቢት እንደ
ተናገረ።
7 ነቢዩ ሙሴም "እግዚኣብሄር በቀሉን በላዩ ላይ ከመጨመርና መቅሰ
ፍትንም ከማምጣት በቀር ሃጢኣቱን ሊተውለት ኣይሻም"[213] አለ።
"በዚህም መፅሃፍ የተፃፈው መርገም በላዩ ላይ ይፈፀማል፤ ስሙም
ከሰማይ በታች ይፋቃል"[214] ሲል ትንቢት እንደ ተናገረ።
8 ነቢዩ ዳዊትም፣ ልቡ ለመግደል ጨካኝ ነው፤
መርገምንም ኣስቀድሚታልና ትምጣበት፤
በረከትንም እንቢ ኣላት፤
ከእሱም ትራቅ[215] ሲል በትንቢት እንደ ተናገረ።
9 ነቢዩ ኤርሚያስም ስለ እሱ፣ "ጠማማ ሰው ስለ ገንዘብ ፍቅር
ይጠፋል፤ ስለ ሽንገላውም ጨለማን ያያል"[216] ብሎ ትንቢት እንደ
ተናገረ።
10 ነቢዩ ኢዮብም ስለ እርሱ፣
ፈጣሪ አሳምሮ ይዘረዋል፤
ነገር ግን በታች ያሉት ስሮች ይደርቃሉ፤
ኣበባ በላዩ ላይ ይረግፋል፤
መታሰቢያውም ከምድር ይጠፋል፤
ታላቁ ስሙም ይጠፋል፤
ብርሃንንም እንዳያይ ወደ ጨለማ ይወስዱታል[217]
ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ።

---

[209] መዝ.41፥9
[210] ኢሳ.10፥1
[211] ?
[212] መዝ.36፥1
[213] ?
[214] ዘዳግ.29፥20
[215] መዝ.109፥17
[216] ?

www.ethiopianorthodox.org

11 ወበከመ ተነበየ ሆሴዕ ወይቤ በእንቲአሁ፣ ሰምዑኒ ደቂቀ እስራኤል
እስመ አልቦ ጽድቅ ወአልቦ ምሕረት ወአልቦ ፍርሃተ እግዚአብሔር
ውስተ ልቡ ዘእንበለ ሐሰት ወሰርቅ ወቀትል ወዝሙት።[218]
12 ወበከመ ተነበየ ዳዊት ነቢይ ወይቤ፣
ወሰይጣን ይቁም በየማኑ። ወካዕበ ይቤ፣
ወሚመቶሂ ይንሣእ ባዕድ።[219]
13 ወሙሴኒ ረገመ በሕግ ወይቤ፣
ርጉመ ለይኩን ኩሉ ዘይነሥእ ሕልያነ ከመ ይቅትል ደመ ንጹሐ።
ወይበል ኩሉ ሕዝብ አሜን ወአሜን።[220]
14 ወካዕበ ተነበየ ዕንባቆም ነቢይ እንዘ ይብል፣ መኩንንኒ አለበወ
በእንተዝ ዕልወተ ሕግ። ወኢይወፅእ ፍትሐ ጽድቅ። እስመ ኀጥእ
ይትዔገሉ ለጻድቅ በእንተዝ። ይወፅእ ፍትሕ ግፍቱዕ።[221]
15 ወበከመ ተነበየ ዳዊት ነቢይ ወይቤ፣
ይሬኢ ኀጥእ ወይትመዐዕ።
ወየሐቂ ስነኒሁ ወይትመሰው።[222]
16 ወበከመ ተነበየ ሰሎሞን ወልዱ ወይቤ፣ ጽሉእ በኀበ እግዚአብሔር
መዳልወ ዓመፃ።[223]
17 ወበከመ ተነበየ ኤርምያስ ነቢይ ወይቤ በእንተ ይሁዳ፣ ድልው ሊተ
አስብየ ሠላሳ ብሩረ።[224]

## ፪ወ፱ በእንተ ስቅለቱ

1 ወካዕበ ተነበዩ ነቢያት በእንተ ስቅለቱ ለክርስቶስ። ወበከመ ተነበየ
ሙሴ ቃልዔሁ ለእግዚአብሔር ወይቤ ትሬእዩ መድኀኒተክሙ ስቁለ
ዲበ ዕፅ። ወኢተአምኑ ቦቱ።[225]
2 ወበከመ ተነበየ ዳዊት ወይቤ፣
አኀዙኒ ከለባት ብዙኃን።
ቀነዉኒ እደውየ ወእገርየ።
ወኍለቊ ኩሉ አዕጽምትየ።
እሙንቱሰ ጠዪቆሙ ወተዐወሩኒ።
ወተካፈሉ አልባስየ ለርእሶሙ።

[218] ሆሴ 4፥1-2
[219] መዝ.109፥6-8
[220] ዘፀ.23፥8
[221] እንባ.1፥4
[222] መዝ.112፥10
[223] ምሳ.11፥1
[224] ዘካ.11፥13
[225] ?

- 138 -

11 ሆሴም ስለ እሱ፣
"እስራኤል ልጆች ሆይ ስሙኝ። ከሃሰት፣ ከስርቆት፣ ከመግደልና
ከዝሙት በቀር እውነት የለም፤ ምህረትም የለም፤ የእግዚኣብሄር
ፍርሃትም የለም"[218] ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ።
12 ነቢዩ ዳዊትም "በቀኙ ሰይጣን ይቁም" ብሎ ትንቢት እንደ
ተናገረ። ደግሞም "ሹመቱን ባእድ ይውሰዳት"[219] አለ።
13 ሙሴም በህግ "ንፁህ ደምን ለማፍሰስ መማለጃ የሚቀበል ርጉም
ይሁን" ሲል ረገመ። ህዝቡም ሁሉ "ኣሜን ወኣሜን" ይበል[220]።
14 ደግሞ ነቢዩ እንባቆም "ፈራጁ ስለዚህ ህግ መተላለፍ ኣሳሰበ፤
የእውነት ፍርድም ኣይወጣም። ሃጥእ ፃድቁን ይቀማዋልና፤ ስለዚህ
ጠማማ ፍርድ ይወጣል"[221] ብሎ ትንቢት ተናገረ።
15 ነቢዩ ዳዊትም፣
ሃጥእ ያያል፤ ኣይቆጣም።
ጥርሱን ያፏጫል፤ ይቀልጣልም[222] ብሎ ትንቢት እንደ
ተናገረ።
16 ልጁ ሰሎሞን "የኣባይ ሚዛን በእግዚኣብሄር ዘንድ የተጠላ ነው"[223]
ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ።
17 ነቢዩ ኤርሚያስም ስለ ይሁዳ፣ "ዋጋየ ሰላሳ ብር ተዘጋጅቶልኛል"[224]
ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ።

## ፪፱ ስለ ስቅለቱ

1 ደግሞም ነቢያት ስለ ክርስቶስ ስቅለት ትንቢት ተናገሩ።
የእግዚኣብሄር ወዳጅ ሙሴ "መድሃኒታችሁን በእንጨት ላይ ተሰ
ቅሎ ታዩታላችሁ፤ ኣታምኑበትምም"[225] ሲል ትንቢት እንደተናገረ።
2 ዳዊትም፣ ብዙ ውሾች ከበቡኝ፤
እጆቼን ቸነከሩኝ፤
ኣጥንቶቼ ሁሉ ተቆጠሩ፤
እነርሱም ኣዩኝ፤ ተመለከቱኝም።
ልብሶቼንም ለራሳቸው ተካፈሉ።

[217] ኢዮ.18፥16
[218] ሆሴ.4፥12
[219] መዝ.109፥6-8
[220] ዘፀ.23፥8፤ዘዳግ27፥25
[221] እንባ.1፥4
[222] መዝ.112፥10
[223] ምሳ.11፥1
[224] ዘካ.11፥13
[225] ?

www.ethiopianorthodox.org

ወተዐፀዉ ዲበ ዐራዝየ።[226]

3 ወበከመ ተነበየ ኢሳይያስ ነቢይ በእንተ ትስብእቱ ወስቅለቱ
ለክርስቶስ ወይቤ፣ እግዚኦ መኑ የአምነነ ቃለነ። ወለመኑ ተከሥተ
መዝራዕተ እግዚአብሔር። ወነገርነ ከመ ሕፃን በቅድሜሁ። ወከመ
ሥርው በውስተ ምድር ጽምእት። አልቦ ላህይ ወአልቦ ራእይ።
ወራእዩሂ ምኑን ወትሑት እምኩሉ ሰብእ ብእሲሁ ቅሡፍ ውእቱ
ወሕሙም እስመ ሜጠ ገጾ ወአስተሐቀርዎ።[227]
4 ወበከመ ተነበየ ሰሎሞን ወይቤ፣ ንቅትሎ ለጻድቅ እስመ ክቡድ ለነ።
ይትቃወሞን ለምግባራቲነ። መዝለፌ ኮነነ ለሕሊናነ። ወሰቆራረ ኮነ
ይትቃወሞን ለምግባራቲነ። መዝለፌ ኮነነ ለሕሊናነ። ወሰቆራረ ኮነ
ሎቱ በኀጣውኢነ።[228] ወካዕበ ደገመ ወይቤ፣ ወልድየ ኢያስሕቱከ ሰ
ብእ ረሲዓን። ለእመ ይቤሉከ ነዐ ምስሌነ ተሳተፍ። ንድፍን ደመ
ንጹሐ ወንንሣእ በርበሮ ወይኩነነ አሐደ ቁናማተ ለኩልነ አግኅሥ
ርእሰከ እማእሰሮሙ እስመ አኮ በከ ዘይረብቡ ለአዕዋፍ
መሥገርት።[229]

5 ወበከመ ተነበየ ዳዊት ወይቤ፣
ወወደዩ ሐሞተ ውስተ መብልዕየ።
ወአስተዩኒ ብሒአ ለጽምእየ።[230]

6 ወበከመ ተነበየ ኢሳይያስ ነቢይ ወይቤ፣ ውእቱ ነሥአ ደዌነ። ወፆረ
ሕማመነ። ወበቍስለ ዚአሁ ሐየውነ። ወርኢናሁ ሕሙመ ወቀኍስለ
በሕማም። ወውእቱሰ ኢከሠተ አፉሁ በሕማሙ። ወመጽአ ይጠባሕ
ከመ በግዕ በቅድመ ዘይቀርፆ ከማሁ ኢከሠተ አፉሁ በሕማሙ እስከ
ይነሥእዋ ለነፍሱ። ወኢየአምርዋ ለልደቱ በኀጢአተ ሕዝብየ።
በጻሕኩ እስከ ለሞት።[231]
7 ወበከመ ተነበየ ኤርምያስ ነቢይ ወይቤ፣ ወነሥኡ ሜጠ ለክቡር ፴
ብሩረ ዘአክበርዎ እምደቂቀ እስራኤል ወይቤለኒ እግዚአብሔር ደዮ
ውስተ ሕንቅርት ወፍትኖ ለእመ ኮነ ንጹሐ። ወወሀብዎ ለገራህተ
ለብሓዊ በከመ አዘዘኒ እግዚአብሔር እንብብ።[232]
8 ወበከመ ተነበየ ኢሳይያስ ነቢይ ወይቤ፣ ጐለቍዎ ምስለ ኀጥኣን
ወአግብእዎ ለሞት።[233]

---

[226] መዝ.22፥16
[227] ኢሳ.53፥1-3
[228] ጥበብ.2፥12
[229] ምሳ.1፥10
[230] መዝ.69፥21
[231] ኢሳ.53፥4
[232] ዘካ.11፥13
[233] ኢሳ.53፥12

- 139 -

በቀሚሴም ላይ እጣ ተጣጣሉ[226] ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ።
3 ነቢዩ ኢሳይያስም ስለ ክርስቶስ ትስብእትና ስቅለት "አቤቱ ቃላችንን
ማን ያምናል? የእግዚአብሄርስ ክንድ የተገለፀው ለማን ነው? በእሱም
ዘንድ ነገራችን እንደ ልጅ ነው። በምድርም ውስጥ ተጠምታ እንዳለች
ስር ነው። ወዝና ለዛ የለውም። መልኩም የተናቀ፣ ከሰው ሁሉም
የተዋረደ ነው። ሰውየው የተቀሰፈ ነው፤ የታመመም ነው። ፊቱን
መልሷል፣ አቃለውታልምና፤ ቁም ነገርም አላሉትምና"[227] ብሎ ትንቢት
እንደ ተናገረ።
4 ሰሎሞንም "ፃድቁን እንግደለው፤ ከብዶብናልና። ስራችንንም
ይቃወማልና። ህሊናችንንም የሚዘልፈን ሆኗልና፤ በሃጢኣታችንም
ምክንያት የተጠላ ሆነ"[228] ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ። ደግሞም
"ልጄ ሆይ! ክፉ ሰዎች አያስቱህ፤ ከእኛ ጋር ና፣ ተባበር፤ ንፁህ
ደምን እንደብቅ፤ ዘረፋም እንውሰድ፤ ለሁላችንም አንድ አቁማዳ
ማከማቻ ይሁንልን ቢሉህ ከምክራቸው እራስህን አግልል። ለወፎች
ወጥመድ እንደ ሚዘረጉ አይደለምና"[229] ሲል ትንቢት ተናገረ።
5 ዳዊትም፣ በምግቤ ውስጥ ሃሞትን ጨመሩ፤
ለጥማቴም ሆምጣጤን አጠጡኝ።[230] ብሎ ትንቢት እንደ
ተናገረ።
6 ነቢዩ ኢሳይያስም "ደዌአችንን ወሰደ። ህማማችንንም ተሸከመ።
በእሱም ቁስል ዳን። ታሞና በህማምም ቆስሎ አየነው። እሱ ግን
በህማሙ አፉን አልከፈተም። ሊታረድ መጣ፣ በግ በሸላቹ ፊት
እንዲሁ በህማሙ ጊዜ ነፍሱን እስኪወስዱት አፉን አልከፈተም።
ትውልዱንም አያውቁትም። በህዝቤ ሃጢኣት እስከ ሞት ደረስኩ"[231]
ሲል ትንቢት እንደ ተናገረ።
7 ነቢዩ ኤርሚያስም "ከእስራኤል ልጆች ሁሉ ያከበሩትን፣ የክቡሩን
የሽያጭ ዋጋ ሰላሳ ብር ተቀበሉ። እግዚኣብሄርም ወደ ጭንቅ
አስገባው። ንፁህ እንደሆነም ፈትነው አለኝ። ለሸክላ ሰሪውም እርሻ
ሰጡት። እግዚኣብሄርም እንዳዘዘኝ እናገራለሁ"[232] ሲል ትንቢት
እንደ ተናገረ።
8 ነቢዩ ኢሳይያስም "ከሃጥኣን ጋር ቆጠሩት። ለሞትም አሳልፈው
ሰጡት"[233] ሲል ትንቢት እንደ ተናገረ።

---

[226] መዝ.22፥16
[227] ኢሳ.53፥1-3
[228] ?
[229] ምሳ.1፥10
[230] መዝ.69፥21
[231] ኢሳ.53፥4
[232] ዘካ.11፥13
[233] ኢሳ.53፥12

www.ethiopianorthodox.org

9 ወበከመ ተነበየ ዳዊት ነቢይ ወይቤ፣
በዝጐ እለ ይጸልኡኒ በዐመፃ።
ወፈደዩኒ እኪተ ህየንተ ሠናይት።[234]
10 ወበከመ ተነበየ ዘካርያስ ነቢይ ወይቤ፣ ወህለዎሙ ይርአይዎ ለዘሰ
ቀልዎ ወወግእዎ። ወብዙኀ ዘእምተነግረ ወተዘመረ ትንቢተ ነቢያት
በእንተ ምጽአቱ ወስቅለቱ ወሞቱ ወትንሣኤሁ ወዕርገቱ ወዳግም
ምጽአቱ በስብሐት። ወባሕቱ ኅዳጠ ዘከርነ ትንቢተ ነቢያት ለእለ
ትሰምዑ ወተአምኑ ወትሌብዉ ንሕነ በበ፩ ዘከርነ።[235]
11 በከመ ተብህለ በሐዋርያት በወንጌል መራሕከነ ወበነቢያት
ናዘዝከነ[236]። እስመ ነገረ ነቢያት ያረትዕ ሃይማኖተ ኑፋቃን።

## ፲ወ፲ በእንተ ትንሣኤሁ

1 ወካዕበ በእንተ ትንሣኤሁ ተነበየ ዳዊት ወይቤ፣
ይእዜ እትነሣእ ይቤ እግዚአብሔር።
እሬሲ መድኀኒተ ወአግህድ ቦቱ።[237] ወካዕበ ይቤ፣
ተንሥእ እግዚእ ወኰንና ለምድር።
እስመ አንተ ትወርስ በኵሉ አሕዛብ።[238]ወካዕበ ተነበየ ወይቤ፣
ተንሥእ እግዚእ ርድአነ።
ወአድኅነነ በእንተ ስምከ።[239]
ወደገመ ወይቤ፣
ይትነሣእ እግዚአብሔር ወይዘረዉ ፀሩ።
ወይጕየዩ ጸላእቱ እምቅድመ ገጹ።[240] ወካዕበ ተነበየ ወይቤ
ወተንሥአ እግዚአብሔር ከመ ዘንቃሕ እምንዋም።
ወከመ ኀያል ወኅዳገ ወይን።[241]
2 ወበከመ ተነበየ ኢሳይያስ ነቢይ፣ ያእትት ሕማመ እምነፍሱ። እስመ
ኢገብረ ኀጢአተ። ወኢተረክበ ሐሰት ውስተ አፉሁ። ወያርእዮ
ብርሃነ ወያጸድቆ ለዘይትቀነይ ለጽድቅ ወለሠናይ። ወለብዙኃን
ኀጢአቶሙ ውእቱ ይደመስስ። እስመ ኢገብረ ኀጢአተ።

---
[234] መዝ.35፥12
[235] ዘካ.12፥10
[236] ቅዳሴ
[237] መዝ.12፥5
[238] መዝ.82፥8
[239] መዝ.44፥26
[240] መዝ.68፥1
[241] መዝ.78፥65



9 ዳዊትም፣ በአመፃ የሚጠሉኝ በዙ፤
ስለ በጎ ነገርም ክፉ ነገርን መለሱልኝ[234] ብሎ ትንቢት
እንደ ተናገረ።
10 ነቢዩ ዘካርያስም "የሰቀሉትንና የወጉትን ያዩት ዘንድ አላቸው"[235] ብሎ
ትንቢት እንደተናገረ፣ ስለ ምፅአቱ፣ ስለ ስቅለቱና ስለ ሞቱ፣ ስለ
ትንሳኤውም ስለ እርገቱና ስለ ሁለተኛውም የክብር ምፅአቱ የተተነበየው
የነቢያት ትንቢት ብዙ በተነገረና በተዘመረ ነበር። ነገር ግን የምትሰ
ሙትንና የምታምኑትንም የነቢያት ትንቢት በያንዳንዱ በጥቂቱ ብቻ
ጠቅሰን።
11 በሃዋርያት "በወንጌል መራሀን፣ በነቢያትም አፅናናሀን"[236] ተብሎ እንደ
ተነገረ የነቢያት ነገር የተጠራጣሪዎችን ሃይማኖት ያቀናልን ዘንድ
ከእያንዳንዱ ጠቅሰን።

## ፱፲ ስለ ትንሳኤው

1 ደግሞም ስለ ትንሳኤው ዳዊት፣
እግዚአብሄር ዛሬ እነሳለሁ፤
መድሃኒትንም አደርጋለሁ፤
በላዩም እገለጣለሁ ይላል[237] ሲል ትንቢት ተናገረ። ደግሞ
አቤቱ ተነስ፤
ምድርን ፍረዳት፤
አንተ በአህዛብ ሁሉ ላይ ትወርሳለህና[238] አለ። ደግሞም፣
አቤቱ ተነስ፤ እርዳን።
ስለ ስምህም አድነን[239] ሲል ትንቢት ተናገረ።
ደግሞም እግዚአብሄር ይነሳል፤
ጠላቶቹም ከፊቱ ይበተናሉ[240]ሲል ትንቢት ተነገረ። ደግሞም፣
እግዚአብሄር ከእንቅልፍ እንደ ነቃ ኅልማሳ ተነሳ፤ ስካሩ
እንደለቀቀው ጀግና።[241] ብሎ ትንቢት ተናገረ።
2 ነቢዩ ኢሳያስም "ከነፍሱ ህማምን ያስወግድ ዘንድ ሃጢአትን አላደረገም፣
በአፉም ውስጥ ሃሰት አልተገኘም። ብርሃንን ያሳየዋል፣ ለእውነትና
ለመልካምም የሚገዛውን እውነተኛ ያደርገዋል። ብዙ ሃጢያታቸውንም እሱ
ይደመስሰዋል። ሃጢአትንም አላደረገምና፣

---
[234] መዝ.35፥12
[235] ዘካ.12፥10
[236] ቅዳሴ
[237] መዝ.12፥5
[238] መዝ.82፥8
[239] መዝ.44፥26
[240] መዝ.68፥1
[241] መዝ.78፥65

www.ethiopianorthodox.org

ወኢተረክበ ሐሰት ውስተ አፉሁ።[242]
3 ወበከመ ተነበየ ዳዊት ነቢይ ወይቤ፣ እስመ ኢተኀድጋ ውስተ ሲኦል
ለነፍስየ።[243]
4 ወበከመ ተነበየ ሰሎሞን ወልዱ ወይቤ፣ ወይትሌዐል ፀሐየ ጽድቅ
ወይምነ የዐውድ ወይገብእ ውስተ መካኑ።[244]

## ፻፲ወ፩ በእንተ ዕርገቱ ወዳግም ምጽአቱ

1 ወበከመ ተነበዩ ነቢያት ኵሎሙ ወአበው ቀደምት ብዙኀ በእንተ
ዕርገቱ ወዳግም ምጽአቱ ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ[245]።
2 ወዳዊትኒ ይቤ በእንተ ዕርገቱ፣
ዐረገ ውስተ አርያም ፄዊወከ ፄዋ።
ወወሀብከ ጸጋከ ለዕጓለ እመሕያው።[246] ወካዕበ ይቤ እግዚአብሔር፣
ወፂእየ እገብእ ወእትመየጥ እንተ ቀላየ ባሕር።[247]ወካዕበ ይቤ፣
ዘምሩ ለእግዚአብሔር ዘዐርገ ውስተ ሰማይ
ሰማይ ዘመንገለ ጽባሕ።[248]
3 ወበከመ ተነበየ አሞጽ ነቢይ ወይቤ፣ መሲሕ ዘይገብር ጊዜ በጽሐ
ወይትሌዐል እምድር ውስተ አርያም። ወእግዚአብሔር ስሙ ዘኵሎ
ይመልክ።[249]
4 ወበከመ ተነበየ ዳዊት ነቢይ ወይቤ፣
ተለዐልከ እግዚኦ በኀይልከ።
ንሴብሕ ወንዜምር ለጽንዕከ።[250]
5 ወበከመ ተነበየ ዘካርያስ ነቢይ ወይቤ፣ ወይቀውማ እገሪሁ ውስተ
ደብረ ዘይት ጽባሒሃ ለኢየሩሳሌም።[251] ወተጽዕነ ላዕለ ኪሩቤል
ወሠረረ በክነፈ ነፋስ።[252]
6 ወበከመ ይቤ ዳዊት፣

[242] ኢሳ.ምእ.53፣
[243] መዝ.16፥10
[244] ሚልክ.4፥2
[245] ጸሎተ ሃይማኖት
[246] መዝ.68፥18
[247] መዝ.68፥22
[248] መዝ.68፥32-33
[249]
[250] መዝ.21፥13
[251] ዘካ.14፥4
[252] መዝ.18፥10



በአፉም ውስጥ ሃሰት አልተናገረም"[242] ሲል ትንቢት እንደ ተናገረ።
3 ነቢዩ ዳዊት "ነፍሴን በሲኦል ውስጥ አትተዋትም"[243] ሲል ትንቢት
እንደ ተናገረ።
4 ልጁ ሰሎሞንም እውነተኛ ፀሃይ ከፍ ከፍ ይላል፤ ወደ ቀኝም
ይዞራል። ወደ ቤቱም ይመለሳል"[244] ሲል ትንቢት እንደ ተናገረ።

## ፻፲ወ፩ ስለ እርገቱና ዳግመኛም ስለ መምጣቱ

1 ነቢያት ሁሉና ብዙዎች የቀደሙ አባቶች ስለ እርገቱና ስለ ዳግም
ምፅአቱ "በህያዋንና በሙታን ላይ ይፈርዳል"[245] በማለት ትንቢት
እንደተናገሩ።
2 ዳዊትም ስለ እርገቱ፣
ምርኮን ማርከህ ወደ ሰማይ ወጣህ፤
ፀጋህንም ለሰው ልጆች ሰጠህ።[246] አለ።
ደግሞ እግዚአብሄር ወጥቼ እገባለሁ፤
በባህር ወንዝም በኩልም እመላለሳለሁ[247] አለ። ደግሞም
በምስራቅ በኩል ወደ አለው ሰማይ ለወጣው ለእግዚአብሄር
ዘምሩ[248] አለ።
3 ነቢዩ አሞፅም "በደረሰበት የሚሰራ ገዥ። ከምድር ወደ ላይም
ከፍ ከፍ ይላል። ስሙም ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሄር ነው"[249] ሲል
በትንቢት እንደ ተናገረ።
4 ነቢዩ ዳዊት
አቤቱ በጉልበትህ ከፍ ከፍ አልክ፤
ለብርታትህ እንዘምራለን፣ እናመሰግናለንም[250] ብሎ በትንቢት
እንደ ተናገረ።
5 ነቢዩ ዘካርያስም "እግሮቹ የኢየሩሳሌም ምስራቅ በምትሆን በደብረ
ዘይት ይቆማሉ"[251] "በኪሩቤል ተጫነ። በነፋስም ክንፍ በረረ"[252]
ብሎ ትንቢት እንደ ተናገረ።
6 ዳዊትም፣

[242] ኢሳ.ምእ.53፣
[243] መዝ.16፥10
[244] ሚልክ.4፥12
[245] ጸሎተ ሃይማኖት
[246] መዝ.68፥18
[247] መዝ.68፥22
[248] መዝ.68፥32-33
[249] ?
[250] መዝ.21፥13
[251] ዘካ.14፥4
[252] መዝ.18፥10

www.ethiopianorthodox.org

አርኅዉ ኖኅተ መኳንንት።
ወይትረኀዋ ኖኃት እለ እምፍጥረት።
ወይባእ ንጉሠ ስብሐት።
መኑ ውእቱ ዝንቱ ንጉሠ ስብሐት።
እግዚአብሔር ኀያል ወጽኑዕ
እግዚአብሔር ኀያል በውስተ ጸብእ
ወካዕበ አጠየቀ ወይቤ
አርኅዉ ኖኅተ መኳንንት።
ወይትረኀዋ ኖኃት እለ እምፍጥረት
ወይባእ ንጉሠ ስብሐት።
መኑ ውእቱ ዝንቱ ንጉሠ ስብሐት።
ኀያል ወጽኑዕ እግዚአብሔር
እግዚአብሔር ኀያል በውስተ ጸብእ
እግዚአብሔር አምላክ ኀያላን ውእቱ ዝንቱ ንጉሠ ስብሐት።[253]
7 ወበእንተ ምጽአቱ ዳግመ፣ ይኴንን ሕያዋነ ወሙታነ።[254] ዘሎቱ ስብሐት ለዓለመ ዓለም አሜን።
8 ወበከመ ተነበየ ዘካርያስ ነቢይ፣ ውእተ አሚረ ይመጽእ እግዚአብሔር አምላኪየ። ወኲሎሙ ቅዱሳኒሁ ምስሌሁ።[255]
9 ወበከመ ተነበየ ዳዊት ነቢይ ወይቤ፣
ምዕረ ነበበ እግዚአብሔር ወዘንተ ከመ ሰማዕኩ።
እስመ ዘእግዚአብሔር ሣህል።
ወዚኣከ እግዚኦ ኀይል።
እስመ አንተ ትፈድዮ ለኲሉ በከመ ምግባሩ።[256]
10 ወበከመ ተነበየ ዳንኤል ነቢይ ወይቤ፣ ርኢኩ በራእየ ሌሊት። ወናሁ መጽአ ከመ ወልደ እጓለ እመሕያው ኀበ ብሉየ መዋዕል። ወተውህበ ሎቱ ምኲናን ወክብር ወመንግሥት። ወኲሎሙ አሕዛብ ወነገድ ወበሐውርት ተቀንዩ ሎቱ። ወምኲናኑኒ ዘአልቦ ማኅለቅት። እስከ ለዓለመ ዓለም። አሜን።[257]
11 ወኲሎሙ ነቢያት ተነበዩ። ወአልቦ ዘኮነ ዘእንበለ ትንቢተ ነቢያት። ወኲሉ ነገሩ ዘኮነ ወዘይከውን ዘተገብረ ወዘይትገበር ዘቀዳሚ ወዘደኃሪ ወእስከ ዳግም ምጽአቱ። ወአኮ በቃል ባሕቲቱ ዘተነበዩ ወዘተናገሩ አላ በሥጋሆሙኒ አርአዩ ዘምስለ ትንቢት።
12 ወኮነ ረኀብ በምድረ ከነአን። ወወረደ አቡነ አብርሃም ውስተ ምድረ ግብጽ። ወገብአ ምስለ ብዙኅ ብዕል ወክብር ዘእንበለ ጥልቀት።[258]

253 መዝ.24፤7-10
254 ጸሎተ ሃይማኖት
255 ዘካ.14፤5
256 መዝ.62፤7
257 ዳን.7፤13
258 ዘፍጥ.12፤10

- 142 -

መኳንንት ሆይ በሮቹን ክፈቱ፤
ከጥንት ጀምሮ የነበሩ በሮች ይከፈቱ፤
የክብርም ንጉስ ይግባ።
ይህ የክብር ንጉስ ማነው?
ይህ የክብር ንጉስ ሃያሉና ፅኑው እግዚኣብሄር ነው።
እግዚኣብሄር በጠብ ውስጥ ሃያል ነው።
ደግሞም እንደገና፣ መኳንንት ሆይ በሮቹን ክፈቱ፤
ከጥንት ጀምሮ የነበሩ በሮች ይከፈቱ፤
የክብርም ንጉስ ይግባ።
ይህ የክብር ንጉስ ማነው?
ይህ የክብር ንጉስ የሃያላን አምላክ እግዚኣብሄር ነው[253] ኣለ።
7 ስለ ዳግም ምፅኣቱም "በህያዋንና በሙታን ላይ ይፈርዳል። ለእሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ምስጋና ይገባል ኣሜን"[254]
8 ነቢዩ ዘካርያስም፣ "በዚያን ጊዜ ኣምላኬ እግዚኣብሄር ይመጣል፤ ቅዱሳንንም ሁሉ ከእሱ ጋር"[255] ሲል ትንቢት እንደ ተናገረ።
9 ዳዊትም፣ እግዚኣብሄር ፈፅሞ ተናገረ፤
ይህንንም ፈፅሞ ሰማሁ።
ይቅርታ የእግዚኣብሄር ነውና።
ሃይልም የኣንተ ነውና።
ኣንተ ለእያንዳንዱ እንደ ስራው ትከፍለዋለህ[256]
በማለት እንደ ተናገረ።
10 ነቢዩ ዳንኤልም "በሌሊት ራእይ እንዲህ ኣየሁ። እነሆ እንደ ሰው ልጅ ያለ በዘመናት ወደ ሸመገለው መጣ። ግዛት፣ ክብርና መንግስትም ተሰጠው። ኣህዛብ ሁሉ ነገዶችና ኣገሮችም ሁሉ ተገዙለት። ግዛቱም ከዘላለም እስከ ዘላለም ፍፃሜ የለውም"[257] በማለት እንደ ተናገረ።
11 ነቢያትም ሁሉ ትንቢት ተናገሩ። ያለ ነቢያትም ትንቢት የሆነ የለም። የሆነውና የሚሆነው የተደረገውና የሚደረገው የፊተኛውና የሁዋለኛው እስከ ዳግም ምፅኣቱ ድረስ ያለውን ነገር ሁሉ የተነበዩት በቃል ብቻ ኣይደለም። ከትንቢት ጋር በስጋቸውም ኣሳዩት እንጂ።
12 ረሃብም በከነኣን ምድር ሆነ። ኣባታችን ኣብርሃም ወደ ግብፅ ወረደ። ያለ መጉደፍደፍ ከብዙ ሃብትና ከብዙ ክብር ጋር ተመለሰ።[258]

253 መዝ.24፤7-8
254 ጸሎተ ሃይማኖት
255 ዘካ.14፤5
256 መዝ.62፤7
257 ዳን.7፤13
258 ዘፍጥ.12፤10

www.ethiopianorthodox.org

13 ወከማሁ ወረደ መድኀኒነ ወአድኀነ ቤተ ክርስቲያኑ ማኅበረ
አሕዛብ። ወዐርገ ነሢአ ክብረ ወስብሐተ።

## ፻፲ወ፪ በእንተ ዘአርአዩ ነቢያት በሥጋሆሙ

1 ተአዘዘ ይስሐቅ ለአቡሁ ወይቤ ዕቅጸኒ ወተሦዐ እንዘ ኢይመውት
ተቤዘዎ በግዕ ዘወረደ እምሰማያት።[259] ወከማሁ ወልደ እግዚአብሔር
ተአዛዜ ለአቡሁ ኮነ እስከ ለሞት። ወተአስረ በፍቅረ ሰብእ።
ወተቀነወ ወተረግዘ። ወኮነ ቤዛነ ወልደ እግዚአብሔር። ወመለኮቱ
ኢሐመ።
2 ወበከመ ያዕቆብ ወልዱ ፈለሰ ምድረ ላባ ሀገረ እኁወ እሙ ምስለ
በትሩ ባሕቲታ ወበህየ ገብረ ብዙኀ እንስሳ ወአጥረየ ንጹሐ ወርኩሰ
ወወለደ ፲ወ፪ ደቂቀ ወከሠተ ጥምቀተ ወገብአ ውስተ ብሔሩ ኀበ
ነሥአ በረከተ እምኀበ ይስሐቅ አቡሁ።[260] ወከማሁ እግዚእነ ክርስቶስ
ወረደ እምሰማያት ባሕቲታ ቃለ መለኮት።
3 ወበትረ ያዕቆብሰ በዘይሬኢ አባግዒሁ ይእቲ እግዝእትነ ማርያም
መድኀኒትነ። ወካዕበ ትተረጐም ዕፀ መስቀል እንተ ባቲ ተሰቂሎ
አድኀነ መርዔቶ ወአጥረየነ እለ እምአይሁድ ወአረሚ ወአሕዛብ
ወኀረየ ሎቱ ፲ወ፪ ሐዋርያተ ወአእመኑ በኲሉ ምድር ወበሐውርት።
ወዐርገ ሰማያተ ኀበ አቡሁ።
4 ወበከመ ፈለሰ ሙሴ ብሔረ ምድያም ወበህየ ተናገሮ ምስለ
እግዚአብሔር ወአእሚሮ ተምሂሮ አሚነ ዘበትንሣኤ ምውታን
ዘበአበዊሁ አብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ ወበይእቲ በትሩ ተበዊሖ ከመ
ይግበር ተአምረ ወወለደ ክልኤተ ደቂቀ።[261]
5 ወዝኒ ያርኢ ገሃደ ከመ በሥላሴ ንድኅን። በከመ ነበበ አፉሁ
ለእግዚአብሔር አነ አምላከ አብርሃም ዘንተ ዘአብ ወአምላከ ይስሐቅ
ዘንተ ዘወልድ ወአምላከ ያዕቆብ ሰበ ይብል ዘንተ ዘመንፈስ ቅዱስ
ያርኢ ገሃደ ሥላሴ ጥዩቀ። ኢኮንኩ አምላከ ምውታን አላ አምላከ
ሕያዋን እስመ ኲሎሙ ሕያዋን በኀቤሁ ለእግዚአብሔር።[262]
ወበዝንቱኒ ተዐውቀ ትንሣኤ ምውታን።

[259] ዘፍጥ.22፥9-18
[260] ዘፍጥ.ምእ28፥29
[261] ዘፀአ.3፥6
[262] ማቴ22፥32

- 143 -

13 እንዲሁም መድሃኒታችን የአህዛብ ማህበር የሆነችውን ቤተ
ክርስቲያንን ለማዳን ወረደ። ክብርና ምስጋና ይዞ አረገ።

## ፻፲፪ ነቢያት በስጋቸው እንደ አሳዩ

1 ይስሃቅም ለአባቱ ታዝዞ እሰረኝ አለው። ተሰዋም። ሳይሞትም ከሰ
ማያት የወረደ በግ አዳነው።[259] እንዲሁም የእግዚአብሄር ልጅ እስከ
ሞት ድረስ ለአባቱ ታዛዥ ሆነ። በሰው ፍቅር ታሰረ፣ ተቸነከረ፣
ተወጋ፣ የእግዚአብሄር ልጅም መድሃኒታችን ሆነ። መለኮቱም
አልታመመ።*
2 ልጁ ያእቆብም ወደ እናቱ ወንድም ወደ ላባ ከብትሩ ጋር ተሰዶ
በዚያ ብዙ እስንሳት እንዳፈራ፣ ንፁሃንና ርኩሳንን እንደ አፈራ፣
አስራ ሁለት ልጆችንም እንደ ወለደ፣ ጥምቀትንም ገልፆ ከአባቱ
ከይስሃቅ በረከትን ወደ ተቀበለበት ወደ አገሩም እንደ ተመለሰ፣[260]
እንዲሁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመለኮት ቃል ጋር ብቻ ከሰ
ማያት ወረደ።
3 መንጋዎቹን የሚጠብቅባት የያእቆብ በትር መድሃኒታችንና
እመቤታችን ማርያም ናት። ደግሞም ተሰቅሎ መንጋዎቹን
በሚጠብቅበት በእፀ መስቀል ትተረጎማለች። እኛንም ከአይሁድ፣
ከአረማውያንና ከአህዛብም ዋጀን። ለእራሱም አስራ ሁለት
ሃዋርያትን መርጦ በምድርና በአገሮች ሁሉ አሳምኖ ወደ አባቱ
ወደ ሰማይ አረገ።
4 ሙሴም ወደ ምድያም ምድር እንደ ተሰደደ፣ በእዚያም
ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋግሮና የአባቶቹን የአብርሃምን፣ የይስሃቅንና
የያእቆብን ትንሳኤ ሙታን ተምሮና አውቆ በዚህችም ብትሩ
ተአምራትን ለማድረግ ስልጣን ተቀብሎ ሁለት ልጆችን ወለደ።[261]
5 ይህም በስላሴ እንደ ምንድን በግልፅ ያሳያል። የእግዚአብሄር አፍ
ስለ አብ እኔ የአብርሃም አምላክ ነኝ፣ ስለ ወልድ የይስሃቅ
አምላክ ነኝ፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ የያእቆብ አምላክ ነኝ አለ።
ይህንን ባለ ጊዜ ስላሴን ጠንቅቆ ያስረዳል። "የህያዋን እንጂ
የሙታን አምላክ አይደለሁም"[262] ማለቱም ሁሉም በእሱ
በእግዚአብሄር ዘንድ ህያዋን ስለሆኑ ነው። በዚህም የሙታን
ትንሳኤ ታወቀ።

[259] ዘፍጥ22፥9-18
* ይህ ትክክለኛ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት አይደለም።
ትክክለኛው ትምህርት ክርስቶስ በስጋ ታመመ ነው። ፩ጴጥ.4፥1
[260] ዘፍጥ.ምእ.28፥29
[261] ዘፀአ.ምእ.2፥15
[262] ማቴ.22፥32

www.ethiopianorthodox.org

6 ዮናስ ተገንዘ ወተወድየ ውስተ ከርሠ አንበሪ።[263] ወወረደ መድኀኒነ
ውስተ ልበ ምድር። ወተንሥአ በሣልስት ዕለት።
7 ወዳንኤልኒ ተወድየ ውስተ ግበ አናብስት። ወኀተምዎ በማኅተሞሙ።
ወተንሥአ ዘእንበለ ይብልዕዎ። ወከማሁ እግዚእነኒ ተወድየ ውስተ
መቃብር። ወኀተምዎ አይሁድ በማኅተሞሙ እንዘ ይመስሎሙ
ዘየኀትሙ ምሥራቀ ፀሐይ ከመ ኢይብራህ።
8 አአብዳን ህጉላን ፅሩፋን ዕውራን ዕንቡዛን ትብሉኑ ከመ ኢይምጻእ
ወኢይፃእ መንፈስ ሕይወት። ወኀፍሩ አይሁድ። ወወፅአ ከመ ያብርህ
ለነ ለእለ አመነ ቦቱ።
9 ዮሴፍ ተሠይጠ በእደ አኀዊሁ።[264] ወእግዚእነ ተሠይጠ በእደ ይሁዳ።
ወበኀበ ተሠይጠ አድኀኖሙ ለአኃዊሁ እምረኀብ። ወክርስቶስኒ
አድኀነነ ለእለ አመነ ቦቱ። ወረሰየነ መዋርስቲሁ ወአኀዊሁ።
10 ወበከመ ዮሴፍ ወሀቦሙ ርስተ ለአዝማዲሁ በምድረ ጌሤም።[265] ከማሁ
ይሁቦሙ ማኅደረ ለጻድቃን ምድረ ርስት ለዘለዓለም።
11 ወካዕበ በእንተ ትንሣኤ ሙታን አነ እሁበከ ትእምርተ ከመ ታእምር
ወትለቡ ወትጠይቅ በአምሕርተ ነገሩ ትሌቡ።
12 አብርሃም ሶበ ቦአ በምድረ ርስት አቅደመ ተሣይጦ መቃብር ኀበ
ያስተጋብእ አብድንተ አዝማዲሁ ወውሉዱ ወብእሲቱ ከመ ይኅበር
ተንሥአ ምስሌሆሙ። ወቀበርዋ በህየ ለሣራ ብእሲቱ ወካዕበ ለሊሁ
ተቀብረ በህየ እስመ ነቢይ ውእቱ[266] አእሚሮ ከመ ይትነሣእ ምስለ
ዘመዱ። ወካዕበ ተቀብሩ ይስሐቅ ምስለ ርብቃ ብእሲቱ።
13 ወእምዝ ወረደ ያዕቆብ ምድረ ግብፅ ምስለ ፸ወ፮ ነፍስ በእንተ
ረኀብ ወበእንተ ዮሴፍ ወልዱ እስከ በዝኀ ወኮነ ኍልቆሙ ፯ ፼
አጋር እለ ድልዋን ለጸብእ ዘእንበለ አንስት ወደቂቅ።[267]
14 ወሞተ ያዕቆብ በህየ በሠናይ ርስዕ። ወይቤሎ ለዮሴፍ ወልዱ
አምሕሎ አምሕለከ በሕይወተ አበውየ ወአምላኪየ ሐዳሲሃ ለሕይወትየ
ከመ ኢትቅብሩኒ ውስተ ዛቲ ሀገር ዘእንበለ ውስተ መቃብረ አበውየ
ከመ ይኩን ሞትየ ምስሌሆሙ። ወሕይወትየ ዓዲ ምስሌሆሙ። ዑቅኬ
በዝ አያተ ነገር።[268]
15 ወጸሮ ወልዱ ዮሴፍ ለእስራኤል። ወቀበሮ ኀበ መቃብረ አበዊሁ።
እስመ ፈርሀ መሓላሁ ዘአምሐሎ።
16 ወካዕበ ሶበ ሐመ ዮሴፍ በግብጽ ጸውዖሙ ለአኀዊሁ ወለደቂቁ
ወአምሐሎሙ ከመ ኢይኅድጉ አዕፅምቲሁ ውስተ ምድረ ግብጽ እላ ከመ
ሶበ ሐወጸክሙ እግዚአብሔር ንሥኡ ምስሌክሙ።

[263] ዮና.1፥15
[264] ዘፍጥ.36፥28፥39፥1
[265] ዘፍጥ.47፥1-6
[266] ዘፍጥ.23፥25
[267] ዘፍጥ.ምእ.39-50
[268] ዘፍጥ.47፥29

- 144 -

6 ዮናስ ተገንዞ በኣሳነባሪ ሆድ ውስጥ ተጣለ። መድሃኒታችንም ወደ
ምድር ልብ ወረደ። በሶስተኛውም ቀን ተነሳ።[263]
7 ዳንኤልም በኣንበሶች ጉድጓድ ተጣለ። በማህተማቸውም ኣተሙት።
ሳይበሉትም ወጣ። እንዲሁም ጌታችን ወደ መቃብር ተጣለ።
ኣይሁድም ከመብራት ለመከልከል የፀሃይ መውጫን እንዲያትሙ
እንዲሁ በማህተማቸው ኣተሙት።
8 እናንተ ዋሾዎች፣ የተዋረዳችሁ እውሮችና ልበ ጥፉዎች፣ የህይወት
መንፈስ እንዳይመጣና እንዳይወጣ ትላላችሁን? ኣይሁድም ኣፈሩ።
ለእኛ ላመንበትም ያበራልን ዘንድ መጣ።
9 ዮሴፍም በወንድሞቹ እጅ ተሸጠ።[264] ጌታችንም በይሁዳ እጅ
ተሸጠ። በተሸጠበትም ወንድሞቹን ከረሃብ ኣዳናቸው። እኛንም
ያመንነውን ኣዳነን። ወራሾቹና ወንድሞቹም ኣደረገን።
10 ዮሴፍም ለዘመዶቹ በጌሴም ምድር ርስትን እንደ ሰጠ[265] እንዲሁም
ለፃድቃን ቤትንና የዘላለም ምድረ ርስትን ይሰጣቸዋል።
11 ደግሞም ስለ ትንሳኤ ሙታን ታውቅና ልብ ታደርግ፣ ትረዳም
ዘንድ እኔ ምልክትን እሰጠዋለሁ በነገሩ ምልክቶችን ታስተውላቸዋለህ።
12 ኣብርሃም ወደ ምድረ ርስት በገባ ጊዜ ይተባበር ዘንድ
የዘመዶቹንና የምሽቱን በድን የሚያከማችበት መቃብር መግዛትን
ኣስቀደመ። ሚስቱን ሳራንም በዚያ ቀበሩኣት። ነቢይ ነውና
ከዘመዶቹ ጋር እንዲነሳ ኣውቆ እሱ እራሱም በዚያ ተቀበረ።[266]
ደግሞም ይስሃቅ ከሚስቱ ከርብቃ ጋር በዚያው ተቀበሩ።
13 ከዚህ በሁዋላ ያእቆብ ከሰብኣ ሰባት ነፍሶች ጋር በረሃብ
ምክንያት ስለረሃብና ስለ ልጁ ዮሴፍ ወደ ግብፅ ምድር ወረደ።
እስከ በዛና ቁጥራቸው ከሴቶችና ከልጆች ሌላ ስድስት መቶ ሺ
ለጦር የተዘጋጁ እስከ ሆኑ ድረስ በዚያ ቆዩ።[267]
14 ያእቆብም በዚያ በመልካም ሽምግልና ሞተ። ልጁን ዮሴፍንም
"በኣባቶቼ መቃብር እንጂ በዚህች ኣገር እንዳትቀብሩኝ በኣባቶቼ
ህይወትና ህይወቱን በኣስደሰታት በኣምላክ ኣምልሃለሁ። ሞቴም
ህይወቴም ከእነሱ ጋር እንዲሆን የዚህን ነገር ምሳሌ እወቁ"
ኣለው።[268]
15 ልጁ ዮሴፍም እስራኤልን ተሸከመው። በኣባቶቹ መቃብር ቀበረው።
ያማለውን መሃላ ፈርቷልና።
16 ደግሞም ዮሴፍ በግብፅ በታመመ ጊዜ ወንድሞቹንና ልጆቹን
ጠርቶ "እግዚኣብሄር በጎበኛችሁ ጊዜ ከእናንተ ጋር ውሰዱኝ።

[263] ዮና.1፥15
[264] ዘፍጥ.36፥28፥39፥1
[265] ዘፍጥ.47፥1-6
[266] ዘፍጥ.ምእ.23፥25፥9
[267] ዘፍጥ ምእ.39-50
[268] ዘፍጥ.50፥7

www.ethiopianorthodox.org

ወደምሩ አዕፅምትየ ውስተ መቃብረ አበውየ።[269]

## ፻፲ወ፫ በእንተ ሰረገላ ወመግረሬ ፀር

1 አውሥኡ ወይቤልዎ ሊቃነ ጳጳሳት ለጎርጎርዮስ ገባሬ መንክራት። ናሁኬ ጠየቅነ ወአለበውከነ ከመ ክብሩ ወዐብዩ ነገሥተ ኢትዮጵያ በእንተ ጽዮን።

2 ወካዕበ ዐብዩ ነገሥተ ሮም በእንተ ቅንዋት ዘገብረት ልጓመ እሌኒ። ወኮና መግረሬ ፀር ለንጉሠ ሮም። ወለንጉሠ ኢትዮጵያ ኮና ሰ ረገላ። ወውእቱኒ ሞአ ፀሮ።

3 ወካዕበ ንግረነ እስከ ማዕዜኑ ይነብር መግረሬ ፀር ኀበ ንጉሠ ሮም ወሰረገላ ምስለ ጽዮን ኀበ ንጉሠ ኢትዮጵያ። ንግረነ እስመ ከሠተ ለከ እግዚአብሔር ዘኮነ ወዘይከውን ራእየ ወትንቢተ ከመ ሙሴ ወኤልያስ።

4 አውሥአ ወይቤሎሙ አነ እከሥት ለክሙ። ለንጉሠ ሮም ሶበ ተዐደወ ወአምዕዖ ለእግዚአብሔር በውስተ ሃይማኖት ዛቲ እንተ ሠራዕነ ሃይማኖተ ሀሉ ይትዐደዎ ዘይመጽእ ንጉሥ በሮሜ ወያኀብር ምስሌሁ ፩ ሊቀ ጳጳሳት። ወይዌልጥዋ ወይገፈትዕዋ ለነገረ ፲ወ፪ ሐዋርያት። ወያፈልስዋ ውስተ ፍትወተ ልቦሙ። ወይሜህሩ በፈቃዶሙ። ወይመይጥዎ ለመጽሐፍ ውስተ ግዕዞሙ። በከመ ይቤ ሐዋርያ በዘለሊሆሙ አትክሉ ርእሶሙ ከመ ሰዶም ወገሞራ።[270]

5 ወእግዚእነሂ ይቤሎሙ በወንጌል ለአርዳኢሁ ተዐቀቡ እምእለ ይመጽኡ ኀቤክሙ በአልባሰ አባግዕ ወእንተ ውስጠሙሰ ተኩላት ወመሰጥ።[271]

6 ወሶበ አዕለውዋ ለሃይማኖት ትትህየድ እምኔሆሙ መግረሬ ፀር። ወመንበረ ጴጥሮስኒ አልቦ ዘይነብር ዲቤሃ እለ ወለጡ ሃይማኖትነ እስመ ይትዐረቅ አማውቲሆሙ ለሊቃነ ጳጳሳቲሆሙ ለእመ ነበሩ በሕሡም ሃይማኖት ዲቤሃ። እስመ ይትኤዘዝ መልአከ እግዚአብሔር ዘየዐቅባ ለመንበረ ጴጥሮስ በሮሜ። ወለመግረሬ ፀርኒ የሀይዳ እግዚአብሔር እምኔሁ።

7 ለንጉሥ ዘኢየዐቅብ ሃይማኖተ ይጸብእዎ ፋርስ ወስሙ ይመስለኒ መርቅያኖስ ዕልወ ሃይማኖት ወይከብቶ ንጉሠ ፋርስ ዘስሙ ሄሬኔዎስ ወይነሥእ ምስለ ፈረሱ ንጉሥ ወበፈቃደ እግዚአብሔር ይትሀወክ ፈረስ ዘቦቱ መግረሬ ፀር ወይበውእ ውስተ ባሕር ወየኀልቅ በህየ።

---

[269] ዘፍጥ.50፥25

[270] ?

[271] ማቴ.7፥15



ኣጥንቶቼንም ከኣባቶቼ መቃብር ጨምሩ እንጂ በዚህ በግብፅ ምድር እንዳትተውኝ" ሲል ኣማላቸው።[269]

## ፻፲፫ ስለ ሰረገላና ስለ መግረሬ ፀር

1 ሊቃነ ጳጳሳትም ለተኣምር ሰሪው ጎርጎርዮስ መልሰው ኣሉት። "የኢትዮጵያ ነገስታት በፅዮን ምክንያት እንደ ከበሩና ከፍ ከፍ እንዳሉ ኣወቅን። ኣንተም ኣስረዳህን።

2 የሮም ነገስታትም እሌኒ በልጓም ስላሰራችው ቅንዋት ከፍ ከፍ ኣሉ። ይህም ለሮም ንጉስ መግረሬ ፀር እንደ ሆነው ሰረገላም ለኢትዮጵያ ንጉስ መግረሬ ፀር ሆነው። እሱም ጠላቱን ኣሸነፈ።

3 ደግሞም ለሮም ንጉስ መግረሬ ፀር፣ ለኢትዮጵያ ንጉስ ሰረገላ ከፅዮን ጋር የሚቆዩለት እስከመቼ ነው? እግዚኣብሄር እንደ ሙሴና ኤልያስ የሆነውንና የሚሆነውን ራእይና ትንቢት ገልፆልሃልና ንገረን" ኣሉት።

4 እሱም መልሶ "የሮም ንጉስ በዚህች በወሰንናት ሃይማኖት ምክንያት ተላልፎ እግዚኣብሄርን ባስቆጣው ጊዜ ነው ብየ እኔ እነግራችሁዋለሁ። በሮም የሚመጣ ንጉስ ይህችን የሰራትን ሃይማኖት ያፋልሳታል። ከእሱም ጋር ኣንድ ሊቀ ጳጳሳት ይተባበራል። የኣስራሁለቱን ሃዋርያትም ትምህርት ይለውጧታል፤ ይገለብጧታልም። ወደ ግል ሃሳባቸው ፈቃድ ይተረጉሙታል። በፈቃዳቸውም ያስተምራሉ። ሃዋርያው እነሱ እራሳቸውን ሰዶምና ገሞራን እንዳስመሰሉ መፅሃፍንም ወደ ባህላቸው ይለውጡታል"[270] እንዳለ።

5 ጌታችንም በወንጌል ለተማሪዎቹ 'የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውስጣቸው ግን ተኩላና ነጣቂዎች ከሆኑት ተጠበቁ'[271] ኣላቸው።

6 ሃይማኖትንም በካዱት ጊዜ መግረሬ ፀራቸው ከእነሱ ትወሰዳለች። ሃይማኖታችንንም ከለወጡት በጴጥሮስ ወንበር ላይ የሚቀመጥ የለም። በከፋች ሃይማኖት ሆነው በሮም ባለች በጴጥሮስ ወንበር ቢቀመጡ የሊቃነ ጳጳሳቶቻቸው ኣንጀት ይራቆታ። መግረሬ ፀሩንም እግዚኣብሄር ከእሱ ይቀማልዋል።

7 ሃይማኖትን የማይጠብቀውንም ንጉስ ፋርሶች ይወጉታል። ስሙም ሃይማኖትን የካደ መርቅያኖስ ይመስለኛል። ስሙ ሃሌኔዎስ የተባለ የፋርስ ንጉስም ይሸሽገዋል። ከንጉሱ ፈረስ ጋርም ይይዘዋል።

---

[269] ዘፍጥ.50፥25

[270] ማቴ.1o፥15

[271] ማቴ.7፥15

www.ethiopianorthodox.org

ወቅንዋትሰ ታበርህ ህየ በውስተ ባሕር። እስከ ይመጽእ ክርስቶስ
ዳግመ በዐቢይ ስብሐት በደመና ሰማይ ምስለ ኀይል። ዘንተኬ
አርአየኒ እግዚአብሔር በውስተ ግብ።
ወበእንተ ንጉሠ ኢትዮጵያ ወጽዮን መርዓተ ሰማይ ወሰረገላ
በዘይረውጹ አነ እነግረክሙ ዘከሠተ ሊተ አምላኪየ። ወአለበወኒ
ትነብር በርትዕት ሃይማኖት እስከ ምጽአተ እግዚእነ። ወአልቦ
ዘትጸንን እምቃለ ሐዋርያት። ወንሕነ በከመ ሠራዕነ ትሄሉ እስከ
ኀልቀተ ዓለም።
10 ወአውሥእዎ ለገባሬ መንክራት ወይቤልዎ አመኬ ይመጽእ ሰ
ማልያል ይትኀበልኑ ውሕከ ሃይማኖቶሙ ለኢትዮጵያ ዘውእቱ
ሐሳዌ መሲሕ።
11 እውሥአ ወይቤ አልቦ አኮኑ ተነበየ ዳዊት ወይቤ፣ ኢትዮጵያ
ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር።[272] ወዘንተ ዘይቤ ኢየዐልዉ
ወኢይዌልጡ ዘንተ ሃይማኖተነ ወሥርዓተነ ወዘእለ እምቅድሜነ
መምህራነ ሕግ ሐዋርያት።

## ፻፲ወ፬ በእንተ ግብአታ ለጽዮን

1 ወታቦተ ሕጉኒ ለእግዚአብሔር ጽዮን ቅድስት ትነብር ህየ እስከ
ውእቱ አሚር። አመ ይነብር እግዚእነ ውስተ ደብረ ጽዮን።
ወትመጽእ ጽዮን ወታስተርኢ ለኵሉ ድሉታ ወሕንጽታ በከመ ቀፈላ
ሙሴ በ፫ ማኅተም። በከመ ይቤ በሕግ ዘብሉይ ወዘሐዲስ በስምዐ
፪ወ፫ ይቀውም ኵሉ ነገር።[273]
2 ወእሜሃ ይቤ ኢሳይያስ ነቢይ ምውታን ይትነሥኡ ወየሐይው እለ
ውስተ መቃብር። እስመ ጠል ዘእምኀቤከ ሕይወቶሙ ውእቱ።[274]
3 ወሶበ ተንሥኡ ምውታን በጠለ ምሕረቱ ዘይሰቅያ ለምድር ይቀውሙ
ቅድሜሁ ምስለ ምግባራቲሆሙ ዘገብሩ።
4 ወይመጽኡ ሄኖክ ወኤልያስ እንዘ ሕያዋን ከመ ይኩኑ ለስምዕ።
ወሙሴ ወአሮን እምነ ምውታን ሐይው ምስለ ኵሉ። ወይፈትሑ
መዛግሒሃ ወያርእይዎሙ ለአይሁድ ሰቃልያን። ወይወቅስዎሙ
ወይዛለፍዎሙ በእንተ ዘዐለዉ ቃለ እግዚአብሔር።
5 ወይሬእዩ ዘጸሐፈ ሎሙ በእደሁ ቃላተ ለትእዛዙ። ወመና ዘከመ ሴሰ
ዮሙ ዘእንበለ ጻማ ምስለ መሥፈሩ ጎሞር።

---

[272] መዝ.68፥31

[273] ዘዳግ.19፥15፡ማቴ18፥16፡ዮሐ.8፥17፡2ቆሮ.8፥1

[274] ኢሳ.68፥18-19



በእግዚአብሄር ፈቃድ መግረሬ ፀር ያለበት ፈረሱ ይታወካል። ወደ
ባህርም ውስጥ ይገባል። በዚህም ያልቃል።
8 ቅንዋቷ ግን ክርስቶስ ዳግመኛ በታላቅ ክብርና በሃይል በሰማይ
ደመና እስኪመጣ ድረስ ታበራለች። ይህንንም እግዚኣብሄር በዋሻ
ውስጥ ሳለሁ ኣሳየኝ ኣላቸው።
9 ስለ ኢትዮጵያ፣ስለ ፅዮንና ስለ ሰማይ ስርኣትና ስለ መረጣት ሰ
ረገላ ኣምላኪ የገለፀልኝንና እንዳስተውል ያደረገኝን እነግራችሁዋለሁ።
እስከ ጌታችን ምፅኣት ድረስ በቀናች ሃይማኖት ትኖራለች።
ከሃዋርያትም ቃል የምናዘነብልበት ምክንያት የለም። እኛም እንደ
ሰራነው እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ ትኖራለች።"
10 ተኣምር ሰሪውንም መልሰው "ሃሳዊ መሲህ ሰማልያል በሚመጣበት ጊዜ
የኢትዮጵያውያንን ሃይማኖታቸውን ያውካል ይባላል?" ሲሉ ጠየቁት።
11 እሱም መልሶ ኣይደለም ዳዊት "ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ
እግዚኣብሄር ትዘረጋለች"[272] ሲል ትንቢት ኣልተናገረም? ይህንም
ያለው ከእኛ በፊት የነበሩት ሃዋርያትና የህግ መምህራን የሰሩትን
ይህንን ሃይማኖትና ስርኣት ኣይከዱትም፣ ኣይለውጡትም ሲል ነው
ኣላቸው።

## ፻፲፬ ስለ ፅዮን መመለስ

1 የእግዚኣብሄር ታቦተ ህግ ቅድስት ፅዮንም እዚሁ ትቀመጣለች። ጌታችን
በደብረ ፅዮን በሚቀመጥበት ጊዜ በብሉይና በሃዲስ ህግ "ነገር ሁሉ
በሁለትና በሶስት ምስክርነት ይፀናል"[273] እንደ ተባለው ሙሴ በሶስት
ማህተም እንዳተማት ሆና ተዘጋጅታ መጥታ ለሁሉ ትታያለች።
2 ስለዚያን ጊዜም ነቢዩ ኢሳያስም "ሙታን ይነሳሉ፣ በመቃብር
ውስጥ ያሉት ህይወት ይዘራሉ። ከኣንተ ዘንድ ያለ ጠል
ህይወታቸው ነውና"[274] ኣለ።
3 "ምድርን በሚያጠጣት በይቅርታው ጠል ሙታን በሚነሱበት ጊዜ
ከሰሩኣቸው ስራዎቻቸው ጋር በፊቱ ይቆማሉ።"
4 ሄኖክና ኤልያስም በህይወታቸው ለምስክርነት ይመጣሉ። ሙሴና
ኣሮንም ከሌሎች ከሙታን ከተነሱት ጋር ይመጣሉ።
መዝጊያዎችንም ይከፍታሉ። ሰቃልያን ኣይሁድንም ይታዩዋቸዋል።
ይወቅሷቸዋልም። ስለ ተላለፉት የእግዚኣብሄር ቃል ሁሉ
ይዘልፏቸዋል።
5 በእጁ የፃፈላቸውን የትእዛዙን ቃላትና ያለ ድካም ጎመር በተባለው
መስፈሪያ ለክቶ መናን እንደመገባቸው ያያሉ። ለመድሃኒታቸውም

---

[272] መዝ.68፥31

[273] ዘዳግ.19፥15፡ማቴ.18፥16፡ዮሃ.8፥17፡2ቆሮ.8፥1

[274] ኢሳ.38፥18-19

www.ethiopianorthodox.org

ወመንፈሳዊት ጽዮን ለመድኅኒቶሙ ዘወረደት። ወበትረ አሮን እንተ
ሠረፀት[275] በአምሳለ ማርያም።

## ፻፲ወ፰ በእንተ ቅስተ እስራኤል

ወያወሥአሙ ወይብሎሙ ለምንት ክህድክሙኒ ወዐለውክሙኒ ወሰ
ቀልክሙኒ ዘንተ ኵሉ ዘገበርኩ ለክሙ።
ወአድኅንኩክሙ ወረድየ እምሰማይ እምሰይጣን ወእምግብርናተ ፈርኦን
2 ወበእንቲኣክሙኒ መጻእኩ ወአንትሙሰ ርእዩ ዘከመ ቀነውክሙኒ
ወረገዝክሙኒ።
ወይትነሥኡ ወይኳንንዎሙ ፲ወ፪ሐዋርያት እንዘ ይብልዎሙ
3 አስማዕናክሙ ወኢሰማዕክሙ ትንቢተ ነቢያት ወስብከተነ ለነ
ለሐዋርያት ወይበክዩ ወይኔሥሑ በኀበ ኢይበቍዕ ወየሐውሩ ውስተ
ኵነኔ ዘለዓለም ምስለ ዲያብሎስ አቡሆሙ ዘአመክሮሙ ወአጋንንቲሁ
መስሕታን ይትሐተሙ ረሲዓን።
ወእለሰ አምኑ ወተጠምቁ ቦቱ በቅድስት ሥላሴ ወተመጠዉ ሥጋሁ
4 ወደሞ ይከውኑ ሎቱ አግብርተ በኵሉ ልቦሙ እስመ አልቦ ዘይክል
ጸሊአ ሥጋሁ ግሙራ።
ወይምሕር በእንተ ሥጋሁ
5 ይጸርሕ ሥጋ ክርስቶስ በውስተ ሥጋነ። ወይምሕር በእንተ ሥጋሁ
ወደሙ። እስመ ኮንዎ ውሉደ ወአኃዊሁ። ወእመኒቦ ዘአበሱ ይትኴነኑ
መጠነ አበሳሆሙ በእሳት።
ለዘቀሊል ጸሩ ቀሊል ኵነኔሁ። ወለዘክቡድ ጸሩ ፍድፉድ ኵነኔሁ።
6 አሐቲ ዕለት መንፈቀ ዕለት ወበ፫ ሰዓት ዘዕለት ወበ፩ ሰዓት
ዘዕለት በኀበ እግዚአብሔር መጠነ ፼[276] ዓመት። ቦ ዘይትኴነን
መጠነ ዕለት ወቦ ዘያሜክርዎ ወያስተናጽሕዎ እምነ አበሳሁ።

## ፻፲ወ፱ በእንተ ሰረገላ ኢትዮጵያ

ወአውሥእዎ ወይቤልዎ ሊቃነ ጳጳሳት ናሁኬ ነገርከነ በእንተ መግረሬ
1 ፀር ዘሮሜ። ወይእዜኒ ንግረነ በእንተ ሰረገላ ዘኢትዮጵያ። ወእመሂ
ይነብር ደኃሪ እስከ ምጽአተ ክርስቶስ ከመ ነገርከነ በእንተ ጽዮን
ወበእንተ ሃይማኖቶሙ ወከማሁ እመ ይነብር ሰረገላሆሙ
ወይቤሎሙ አልቦ ሀለዎ ይሰወር። ወካዕበ ዘንተ ስምዑኒ
2 እንግርክሙ። ሀለዎሙ ንስቲተ ያነሥኡ ርእሶሙ አይሁድ ላዕለ
መሃይምናን በናግራን ወበአርማንያ። ወእምድኅረዝ መዋዕል ወዘንተ



[275] ዘኍ.17፥18
[276] ፲፻ የሚልም አለ።2ጴጥ.3፥8



የወረደችውን መንፈሳዊቷ ፅዮንንም ያዩዋታል። በማርያምም ኣምሳል
የለመለመችውን የአሮንን በትር[275] ያዩዋታል።"

## ፻፲፰ ስለ እስራኤል ወቀሳ

1 እሱም መልሶ ይላቸዋል። "ስለምን ከዳችሁኝ? ለምንስ ወነጀላችሁኝ?
ለምንስ ሰቀላችሁኝ? ይህን ሁሉ ያደረግሁት ለእናንተ ነው።
2 ከሰማይ ወርጄ ከሰይጣንና ከፈርኦን ባርነት ኣዳንኳችሁ። ስለ
እናንተም መጣሁ። እናንተ ግን እንዴት እንደ ቸነከራችሁኝና
እንዴት እንደወጋችሁኝ እዩ።"
3 ኣስራ ሁለቱ ሃዋርያትም ይነሳሉ። "የነቢያትን ትንቢት ነገርናችሁ።
ነገር ግን ኣልሰማችሁም። የእኛን የሃዋርያትንም ስብከት
ኣልተቀበላችሁም" ሲሉ ይፈርዱባቸዋል።
4 እነሱም ያለቅሳሉ። የማይጠቅምም ፀፀት ይፀፀታሉ። ከፈተናቸው
ኣባታቸው ከዲያብሎስና ከኣሳሳቶቹ ኣጋንንት ጋር ወደ ዘላለም
ፍርድ ይሄዳሉ። ሃጢኣተኞችም ይዘጋሉ።
5 ያመኑና በቅድስት ስላሴ የተጠመቁ፣ ስጋውንና ደሙንም የተቀበሉ፣
በልባቸው ሁሉ ባሪያዎች ይሆኑለታል። ስጋውን ፈፅሞ መጥላት
የሚቻለው የለምና። የክርስቶስ ስጋውና ደሙ በስጋችን ውስጥ
ይጮሃል። ስለ ስጋውም ስለ ደሙም ይቅር ይላል። ልጆቹና
ወንድሞቹ ሆነዋል። የበደሉም ካሉ በበደላቸው መጠን በእሳት
ይፈረድባቸዋል።
6 በደሉ ቀላል ለሆነ ፍርዱም ቀላል ነው። በደሉ ለከበደ ፍርዱም
ከባድ ነው። በእግዚኣብሄር ዘንድ ኣንዲት ቀን እንደ ኣስር ሺ[276]
ዓመት ነው። ኣንድ ቀን የሚፈረድበት ኣለ። ግማሽ ቀን
የሚፈረድበት ኣለ። የቀን ሶስት ሰኣት የሚፈጅበት ኣለ። የቀን
ኣንድ ሰኣት የሚፈጅበትም ኣለ። በኣመክሮም ከኣበሳው የሚያነፁት
ኣለ።

## ፻፲፱ ስለ ኢትዮጵያ ሰረገላ

1 ሊቃነ ጳጳሳቱም መልሰው "ስለ ሮም መግረሬ ፀርስ እነሆ
ነገርከን። ኣሁን ደግሞ ስለ ኢትዮጵያ ሰረገላ ንገረን ስለ ፅዮን
ሃይማኖታቸን እንደ ነገርከን እስከ ሁዋለኛው እስከ ክርስቶስ
ምፅኣት ሰረገላቸው ይቆይ እንደሆነ ንገረን" ኣሉት።
2 እሱም መልሶ "የለም እሱ ይሰወራል። ደግሞም ስሙኝ ይህንን
እነግራችሁዋለሁ። ከዚህ ጊዜ በሁዋላ ለጥቂት ጊዜ ኣይሁድ

[275] ዘኍ.17፥8
[276] ፲፻ የሚልም ተገኝቷል።2ጴጥ.3፥8

www.ethiopianorthodox.org

ይገብር በፈቃዱ እግዚአብሔር ከመ ያኀልቆሙ። እስመ አርማንያ ደወለ ሮም ወናግራን ደወለ ኢትዮጵያ።

## ፻፲ወ፯ በእንተ ንጉሠ ሮምያ ወንጉሠ ኢትዮጵያ

1 ወይትለአኩ ንጉሠ ሮምያ ወንጉሠ ኢትዮጵያ ወሊቀ ጳጳሳት
ዘእስክንድርያ ከመ ያኀልቅዎሙ እንዘ ርቱዕ ሃይማኖቶሙ ለሰብአ ሮ
ም። ወያነሥኡ ጸብአ ከመ ይጽብእዎሙ ለፀረ እግዚአብሔር አይሁድ።
2 ወያኀልቅዎሙ ንጉሠ ሮሜ ለኤንያ ወንጉሠ ኢትዮጵያ ለፊንሐስ።
ወያመዘብሩ ብሔሮሙ ወያሐንጹ አብያተ ክርስቲያናት በህየ።
ወየሐርድዎሙ ለነገሥተ አይሁድ በተፍጻሚተ ዛቲ ቀመር ፲ወ፪
አቅማር። አሜሃ ትትፌጸም መንግሥቶሙ ለአይሁድ። ወትረትዕ
መንግሥተ ክርስቶስ እስከ ምጽአተ ሐሳዌ መሢሕ።
3 ወእሙንቱሰ ነገሥት ዮስጢኖስ ንጉሠ ሮሜ ወካሌብ ንጉሠ ኢትዮጵያ
ይትራከቡ ክልኤሆሙ በኢየሩሳሌም። ወይሠርዑ ቀርባነ ሊቃነ
ጳጳሳቲሆሙ። ወይቄርቡ ወያኀብሩ ሃይማኖተ በፍቅር። ወይትወሀቡ
አምኃ ወሰላመ። ወይትካፈሉ ምድረ እመንፈቃ ለኢየሩሳሌም በከመ
ነገርነ ውስተ ርእሰ ዝንቱ መጽሐፍ ቀዳሚ።
4 ወካዕበ በእንተ ፍቅር ይደምሩ ስመ መንግሥት። ይደምሩ ፩ ዘኀረዩ
በሃይማኖት እምነገሥተ ሮም በውስተ ዕፃ ዘይሰመይ ምስለ ዳዊት
ወሰሎሞን አበዊሆሙ ከመ ይሰመይ ንጉሠ ኢትዮጵያ ወንጉሠ ሮሜሂ
ከማሁ ይነሥእ ስመ ንጉሠ ኢትዮጵያ። ወይደምር ውስተ ዕፃ ዘይሰ
መይ ምስለ ዳዊት ወሰሎሞን አበዊሆሙ በአምሳለ ፬ ወንጌላውያን
ወራብዕሰ ፩ ዘኀረዩ በሀገሮሙ።
5 ወከመዝ እምድኅረ ኀብሩ ወአርትዑ ሃይማኖተ ይትማከሩ ከመ
ኢያሐይዉ አይሁድ ወየኀድጉ ህየ በበውሉዶሙ። ወንጉሠ ኢትዮጵያሰ
የኀድግ ህየ ወልደ ዘበኩሩ ዘስሙ እስራኤል። ወይገብእ ብሔሮ
በፍሥሓ። ወሶበ በጽሐ ቤተ መንግሥቱ ያአኵቶ ለእግዚአብሔር
ፈድፋደ። ወይበጽዕ ሥጋሁ ለመሥዋዕተ ስብሐት ለአምላኩ። ወጥቀ
ይትዌከፎ እግዚአብሔር እስመ ኢያረኵሰ ሥጋሁ እምድኅረ ገብአ።
አላ የሐውር በውስተ ደብር በንጹሕ ልብ።
6 ወያነግሥ ወልዶ ዘይንእስ ዘስሙ ገብረ መስቀል። ወውእቱሰ የዐሉ
ርእሶ።
7 ወሶበ ነገርዎ ለንጉሠ ናግራን ወልደ ካሌብ ይመጽእ ከመ ይንግሥ
ኀበ ጽዮን ወገብረ መስቀልኒ ያነሥእ ሠራዊተ ወየሐውር በሰረገላ
ወይትራከቡ በኀበ መጽብበ ባሕረ ሊባ ወይትቃተሉ። ወበእሐቲ



በናግራንና በአርማንያ ባሉት ምእመናን ላይ እራሳቸውን ከፍ ከፍ ያደርጉ ዘንድ አላቸው። እግዚአብሄርም ይጨርሳቸው ዘንድ ይህንን በፈቃዱ ያደርጋል። ምክንያቱም አርማንያ የሮም፣ ናግራንም የኢትዮጵያ አውራጃዎች ናቸውና" አላቸው።

## ፻፲፯ ስለ ሮም ንጉስና ስለ ኢትዮጵያ ንጉስ

1 የሮም ሰዎች ገና ሃይማኖታቸው የቀና ሳለ የሮም ንጉስና
የኢትዮጵያ ንጉስ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳትም ይፈጅዋቸው ዘንድ
ይላካሉ። የእግዚአብሄር ጠላቶችን አይሁድን ይወጓቸው ዘንድ
ጦርነትን ያስነሳሉ።
2 የሮም ንጉስ ኤንያንን፣ የኢትዮጵያ ንጉስም ፊንሃስን ይፈጅዋቸዋል።
አገራቸውንም ያፈርሳሉ። ቤተ ክርስቲያኖችንም በዚያ ይሰራሉ።
አስራ ሁለት ቀመሮች ባሏት በዚህች ቀመር ፍፃሜም የአይሁድ
ነገስታትን ያርዷቸዋል። ያንጊዜ የአይሁድ መንግስት ትፈፀማለች።
ሃሳዊ መሲህም እስኪመጣ ድረስ የክርስቶስ መንግስት ትቀጥላለች።
3 ዮስጢኖስ የተሰኘው የሮም ንጉስና ካሌብ የተባለው የኢትዮጵያ
ንጉስ ሁለቱም በኢየሩሳሌም ይገናኛሉ። ሊቃነ ጳጳሳቱም ቁርባንን
ይሰራሉ። ይቆርባሉም። በፍቅርም ሃይማኖታቸውን ያስተባብራሉ።
ፍፁም ሰላምታንም ይለዋወጣሉ። በዚህ መፅሃፍ መጀመሪያ እንደ
ተነገረን ከኢየሩሳሌም አጋማሽ ጀምሮ ምድርን ይካለላሉ።
4 ደግሞም ስለ ፍቅር የመንግስቶቻቸውን ስም አንድ ያደርጋሉ። ከሮ
ም ነገስታት ውስጥ በሃይማኖት የመረጡትን አንዱ የኢትዮጵያ
ንጉስ ይባል ዘንድ ከአባቶቻቸው ከዳዊትና ከሰሎሞን ጋር የሚያስ
ይመውን አንዱን በእጣ ይመርጣሉ። የሮም ንጉስም* የኢትዮጵያን
ንጉስ ስም ይይዛል። ከአባቶቻቸው ከዳዊትና ከሰሎሞን ጋር
ከሚሆነው እጣ ጋር ይጨምራሉ። በአራቱ ወንጌላውያንም ምሳሌ
ይሆናሉ። አራተኛው ግን ከየአገራቸው አንዳንድ ነው።
5 ከተባበሩና ሃይማኖታቸውን ካቀኑ በሁዋላ አይሁድ በህይወት እንዳይኖሩ
ይማከራሉ። ልጆቻቸውንም እዚያ ይተዋሉ። የኢትዮጵያ ንጉስም ስሙ
እስራኤል የሆነውን የበኩር ልጁን እዚያ ይተዋል። ወደ አገሩም በደስታ
ይመለሳል። ወደ ቤተ መንግስቱም በደረሰ ጊዜ እግዚአብሄርን ፈፅሞ
ያመሰግነዋል። ስጋውንም ለአምላኩ ለእግዚአብሄር ምስጋና መስዋእት
ይሳላል። እግዚአብሄርም ፈፅሞ ይቀበለዋል። በንፁህ ልቡና ወደ ገዳሙ
ይመልሰዋል። ከተመለሰም በሁዋላ ስጋውን አያረክስም።
6 ስሙ ገብረ መስቀል የሆነውንም ትንሹን ልጁን ያነግሰዋል። እሱም
ይሸገራል።
7 ለናግራንም ንጉስ "የካሌብ ልጅ ከፅዮን ሊነግስ ይመጣል" ብለው
በተናገሩት ጊዜና ገብረ መስቀልም ሰራዊቱን ይዞ በሰረገላ በሄደ ጊዜ

* ፀሃፊው በዚህ አንቀፅ ለማለት የፈለጉት ግልፅ አይደለም።

www.ethiopianorthodox.org

ሌሊት ይጼልዩ ክልኤሆሙ እምሠርክ እስከ ነግህ ሶበ ጸንየሙ
ቀትል።
ወሶበ በከዩ ኀቤሁ በአንብዕ ይኄጽር እግዚአብሔር ኀበ ጸሎተ
ክልኤሆሙ። ወጸሎተ አቡሆሙ ንሱሕ እንዘ ይብል ውእቱኒ
መልህቅ። ወቆመ ከመ ይግበር ፈቃደ አቡሁ። ወለውእቱኒ መንእስ
አፍቀሮ አቡሁ። ወጸለየ ኀበ እግዚአብሔር ወይቤሎ ለገብረ መስቀል
ኅረይ ለከ እምሰረገላ ወእምጽዮን። ወአፍትዎ ከመ ይንሣእ ጽዮንሃ
ወይንግሥ ገሃደ ዲበ መንበረ አቡሁ።
ወለእስራኤልኒ አፍተዎ ከመ ይኅረይ ሰረገላ ወይንግሥ በኅቡእ።
ወኢይትረአይ ወይፌንዎ ኀበ ኵሎሙ እለ ተዐደዉ ትእዛዘ
እግዚአብሔር።
0 ወአልቦ ዘየሐንጽ አብያተ ወይነብር በደብተራት። ወአልቦሙ ጻማ
ዘሥራሕ ወኢጻማ በፍኖት። ወመዋዕሊሆሙኒ ካዕበተ ሰብእ።
ወከመዝኬ የኄይሉ ወይዌስቁ ወይወግኡ ኀበ ዘጸልአ እግዚአብሔር።
1 ከመዝ ገብረ እግዚአብሔር ለንጉሠ ኢትዮጵያ ክብረ ወሞገሰ
ወአዕበዮ እምኵሎሙ ነገሥተ ምድር በእንተ ዕበያ ለጽዮን ታቦተ
ሕጉ ለእግዚአብሔር ጽዮን ሰማያዊት። ወይረስየነ እግዚአብሔር ከመ
ንግበር ሥምረቶ መንፈሳዊተ ወያድኅነነ እመዐቱ ወይክፍለነ
መንግሥቶ አሜን።
2 ወአውሥኡ ወይቤልዎ በአማን ሠናየ ነበብከ እስከ ከማሁ ተከሥተ
ለከ በረድኤተ መንፈስ ቅዱስ ነገርከነ ኵሎ ዘኮነ ወአኀበርከ ምስለ
መጽሐፈ ደማትዮስ ዘሮሜ። ወተነበይከ ለነ ዘይከውንሂ ለ፪ አህጉር።
መራዕወ ክርስቶስ አብያተ ክርስቲያናት ንስታስያ ወአርቃድያ
ወማሬና ወኢትዮጵያ አህጉር ዐበይት ዘእግዚአብሔር ዘበውስቴቶን
መሥዋዕት ወቊርባን ንጹሕ ይትገበር በኵሉ ጊዜ።
13 እግዚአብሔር ይጸግወነ በረከቶሙ ለኵሎሙ ቅዱሳን ወሰማዕት።
ለዓለመ ዓለም አሜን። ክርስቶስ ንጉሥነ ወክርስቶስ ሕይወትነ
ለዓለመ ዓለም አሜን። ወአሜን።

14 ወተብህለ በክታበ ዐረቢ አውፃእናሃ እምልሳነ ቅብጢ ለዐረቢ
እመንበረ ማርቆስ ወንጌላዊ መምህር አበ ኵልነ ወአውፃእናሃ
በ፻፺፰ወ፱ ዓመተ ምሕረት ውስተ ሀገረ ኢትዮጵያ በመዋዕለ ገብረ
መስቀል ንጉሥ ወሰንሁ ላሊበላ በመዋዕለ አባ ጊዮርጊስ ጳጳስ ኄር
ወአስተተ እግዚአብሔር አውፅኦታ ወተርጕሞታ ኀበ ነገረ ሐባሲ ።
15 ወሶበ ኀለይኩ ዘንተ ለምንት ኢተርጕምዋ አበልዕዝ ወአበፈጠረግ እለ
አውፅእዋ እቤ ዘንተ እስመ ወፅአት በመዋዕለ ዛጓ ወኢተርጕምዋ
እስመ ትብል ዛቲ መጽሐፍ እለሰ ይነግሡ እለ ኢኮኑ እስራኤል
ተዐድዎ ሕግ ውእቱ።

- 149 -

በሌባ ባህር ስርጥ ይገናኛሉ። ይዋጋሉም። ጦርም በበረታባቸው
ጊዜ ሁለቱም ከምሽት እስከ ነግህ ይፀልያሉ።
8 ወደ እሱም በእንባ ባለቀሱ ጊዜ ወደ ፀሎታቸውና ወደ ተነሳሂው
የአባታቸው ፀሎት ይመለከታል። ታላቁ ልጁም የአባቱን ፈቃድ
ሊያደርግ ይቆማል። ታናሹንም አባቱ ወደደው። ወደ
እግዚአብሄርም ፀለየ። ገብረ መስቀልንም "ከሰረገላና ከፅዮን ለራስህ
ምረጥ" አለው። ፅዮንን ይወስድ ዘንድና በግልፅም በአባቱ ዙፋን
ይነግስ ዘንድ ደስ አሰኘው።
9 እስራኤልንም ሰረገላን ይመርጥ ዘንድና በስውርም ይነግስ ዘንድ፣
ሳይታይም የእግዚአብሄርንም ትእዛዝ ወደ ተላለፉት ይልከው ዘንድ
ደስ አሰኘው።
10 ቤቶችን የሚሰራ፣ በድንኳኒችም የሚቀመጥ የለም። የስራ ድካምና
የመንገድ ድካም የለባቸውም። እድሜያቸውም የሰው እጥፍ ነው።
እግዚአብሄር የጠላውንም ይቀማሉ። ቀስታቸውንም ወርውረው
ይወጋሉ።
11 እግዚአብሄር ለኢትዮጵያ ንጉስ እንደዚህ ያለ ክብርና ግርማን
አደረገ። ስለ እግዚአብሄር ታቦተ ህግ ስለ ሰማያዊቷ ፅዮንም
ከምድር ነገስታት ሁሉ ከፍ ከፍ አደረገው። እግዚአብሄር
መንፈሳዊት ፈቃዱን እንድንፈፅም ያብቃው። ከመአቱ ያድነን።
ከመንግስቱ ተካፋይ ያድርገን።
12 መልሰውም "በመንፈስ ቅዱስ ርዳታ እንደዚህ ተገልፆልሃልና
በእውነት መልካም ተናገርከ። የሆነውን ሁሉ ነገርከው። ከሮሙ
ከደማትዮስ መፅሃፍ ጋርም ተባበርከ። በውስጣቸው ሁልጊዜ ንፁህ
መስዋትና ቁርባን የሚሰዋባቸው የእግዚአብሄር ታላላቅ አገሮችና
የክርስቶስ ሙሽሮች ለሆኑ፣ ለሁለቱ አገሮች አብያተ ክርስቲያናት
ለንስታስያ፣ ለአርቃድያ፣ ለማሬና ለኢትዮጵያ የሚሆነውን ትንቢትም
ተናገርከልን" አሉት።
13 እግዚአብሄር የሁሉንም ቅዱሳንና ሰማእታት በረከታቸውን ይስጠን።
ለዘላለሙ አሜን። በክርስቶስ ንጉሳችን በህይወታችንም በክርስቶስ
ለዘላለሙ አሜን።
14 በአረብኛውም ደብዳቤ "ከወንጌላዊውና የሁላችንም መምህር ከሆነው
ከማርቆስ መንበር በአራት መቶ ዘጠኝ ዓመተ ምህረት* የቅፅል
ስሙ ላሊበላ በሆነው በንጉስ ገብረ መስቀል ዘመንና በቸሩ
ጳጳሳችን በአባ ጊዮርጊስ ዘመን ከኮፕት ቋንቋ ወደ አረብኛ
ተረጎምናት" ተባለ። እግዚአብሄርም ወደ ኢትዮጵያ መምጣቷንና
ወደ አበሻ ቋንቋም መተርጎሟን ችላ አሰኝ።
15 እኔም "ያወጧት አባልእዝና አበፈጠረግ ያልተረጎሟት ለምን ይሆን"
ብዬ ባሰብኩት ጊዜ "በዘመነ ዛጓ ስለወጣች እና ይህች መፅሃፍ
እስራኤላውያን ሳይሆኑ መንገስ ህግን መተላለፍ ነው ስለ ምትል

* ይህ ኣ.ም. ከዛሬው ኣቆጣጠር ጋር ኣይቀራረብም።

www.ethiopianorthodox.org

ወሶበ ይከውን በመንግሥተ እስራኤል እምአውፅእዋ ወተረክበት በናዝሬት።

ወጸልዩ ላዕሌየ ለገብርክሙ ይስሐቅ ነዳይ። ወኢትሒሱኒ በእንተ ኢያርትዖ ነገረ ልሳን። እስመ ብዙኀ ጻመውኩ በእንተ ክብራ ለሀገረ ኢትዮጵያ በእንተ ፀአታ ለጽዮን ሰማያዊት ወበእንተ ክብረ ንጉሠ ኢትዮጵያ። እስመ እነሂ ተስእልክዎ ለመኰንን ርቱዕ ፍቁረ እግዚአብሔር ያዕቢክ እግዚእ። ወአፍቀረ ወይቤለኒ ግበር። ወገበርኩ እግዚአብሔር ይረድአኒ ወኢፈደየኒ በከመ አበሳየ።
ለገብርክሙ ይስሐቅ ጸልዩ። ወለእለ ጻምዉ ምስሌየ በፀአተ ዛቲ መጽሐፍ እስመ ተመንደብነ ፈድፋደ አነ፣ ወይምርሐነ አብ፣ ወሕዝበ ክርስቶስ፣ ወእንድርያስ፣ ወፊልጶስ፣ ወመሓሪ አብ፣ ይምሐሮሙ እግዚአብሔር በመንግሥተ ሰማያት ምስለ ኵሎሙ ቅዱሳን ወሰማዕት። ወይጽሐፍ ስሞሙ ውስተ መጽሐፈ ሕይወት። ለዓለመ ዓለም አሜን። ወአሜን።
ወእምድኅረ ተወልደ መድኀኒነ እሉ ነገሥት ባዜን፡ ጽንፍ አሰግድ፡ ባሕር አሰግድ፡ ግርማ ሰፍር፡ ሰርዓዳ፡ ኵሉ ለጽዮን፡ ሰርጓይ፡ ዘርአይ፡ በጋማይ፡ ዛን አሰግድ፡ ጽዮን ሕግ፡ ማአበልጋድ፡ ሳፍ፡ አርዓድ፡ አግዳር፡ አብርሀ ወአጽብሐ አኀው ፍቁራን፡ አስፍሐ፡ አርፍድ ወአምሲ አኀው፡ አርዓዳ፡ ሰልዓዶባ፡ ወአልዐሜዳ፡ ታዜና፡ ካሌብ፡ ገብረ መስቀል፡ ቈስጠንጢኖስ፡ በዘጋር፡ አስፋሕ፡ አርማሕ፡ ዣን አስፍሕ፡ ዣን ሰገድ፡ ፍሬ ሠናይ አድርዓዝ፡ አይዙር፡ ማዕዳይ፡ ከላውድዮስ፡ ግርማ አስፋ፡ ዘመዝ፡ ድግና ሚካኤል፡ በደግዝ፡ አርማኅ፡ ሕዝበ አናኒ፡ ድግና ዛን፡ አንበሳ ውድም፡ ድል ነዓድ።
ወእምድኅሬሁ ተሀይደ መንግሥት ለሕዝበ እለ ኢኮኑ እምነገደ ዳዊት ወሕዝበ እስራኤል። በከመ ይቤ እግዚአብሔር አነ አቀንኦሙ በዘኢኮነ ሕዝብ።
ወእምድኅሬሁ አግብአ ሎሙ ይኩኖ አምላክ ያግባ ጽዮን፡ ባሕር ሰገድ፡ ሕዝብ አርዓድ፡ ቅድመ ሰገድ፡ ዣን ሰገድ፡ ውድም አርዓድ፡ ዐምደ ጽዮን።

- 150 -

በዚሁ ምክንያት ኣልተረጎሚትም" ኣልኩ። እስራኤላውያን በነገሱበት
ወቅት ቢሆን ግን በተረጎሚት ነበር። በናዝሬትም ተገኘች።
16 ለእኔም ለባሪያችሁ ለምስኪኑ ይስሃቅ ፀልዩልኝ። በቋንቋውም ጥራት
ኣትንቀፉኝ። ስለ ኢትዮጵያ ክብር፣ ስለ ሰማያዊቷ ፅዮን
መውጣትና ስለ ኢትዮጰያ ንጉስ ክብር ብዙ ደክሜኣለሁና። እኔም
ደግሞ ርቱእ ሃይማኖትና የእግዚኣብሄር ወዳጅ የሆነውን ያእቢክ
እግዚእን ለመንኩት። እሱንም ደስ ኣሰኘው። "ኣድርግም" ኣለኝ።
እግዚኣብሄርም እየረዳኝ ፈፀምኩት። እንደ ጥፋቴም ኣልከፈለኝም።
17 ለእኔ ለባሪያችሁ ለይስሃቅና ይህችን መፅሃፍ ለማውጣት ከእኔ ጋር
ኣብረው ለደከሙና ኣብረውም ለተቸገሩ ለይምርሃነ ኣብ፣ ለህዝበ
ክርስቶስ፣ ለእንድርያስ፣ ለፊልጶስና ለመሃሪ ኣብ ፀልዩልን።
እግዚኣብሄር በመንግስተ ሰማያትና ከሌሎች ቅዱሳንና ሰማእታት
ጋር ነፍሳቸውን ይማር። ስማቸውንም በመፅሃፈ ህይወት ይፃፍ።
ለዘላለሙ ኣሜን።
18 መድሃኒታችን ከተወለደ በሁዋላ የነገሱት ነገስታት ባዜን፣ ፅንፈ
ኣሰግድ፣ ባህረ ኣሰግድ፣ ግርማ ስፍር፣ ስርዓዳ፣ ኩሉ ለፅዮን፣ ሰ
ርጓይ፣ ዘርኣይ፣ በጋማይ፣ ዣን ኣሰግድ፣ ፅዮን ህግ፣ ማኣስበጋድ፣
ሳፍ፣ ኣርኣድ፣ ኣግደር፣ የተወደዱ ወንድሞች ኣብርሃና ኣፅብሃ፣
ኣስፍሃ፣ ወንድማማቶች ኣርፍድና ኣምሴ፣ ኣርኣዳ፣ ሰልኣደባ፣
ኣልኣሜዳ፣ ታዜና፣ ካሌብ፣ ገብረመስቀል፣ ቈስጠንጢኖስ፣ በዘጋር፣
ኣስፋህ፣ ኣርማህ፣ ዣን ኣስፍህ፣ ዣን ሰገድ፣ ፍሬ ሰናይ፣
ኣድርኣዝ፣ ኣይዙር፣ ጋዳይ፣ ከላውድዮስ፣ ግርማ ኣስፋ፣ ዝመዝ፣
ድግና ሚካኤል፣ በደግዝ፣ ኣርማህ፣ ህዝበ ኣናኒ፣ ድግናዠን፣
ኣንበሳ ውድም፣ ድልነኣድ ናቸው።
19 ከዚህ በሁዋላ እግዚኣብሄር "እኔም ህዝቤ ባልሆነው ኣስቀናቸዋለሁ"
ብሎ እንደተናገረ መንግስት ከእነሱ ተወሰደች። ከዳዊት ዘርና
ከእስራኤልም ነገድ ላልሆኑት ተሰጠች።
20 ከዚያም በሁዋላ ይሁኖ ኣምላክ መለሰላቸው። ያግባ ፅዮን፣ ባህር
ኣሰግድ፣ ህዝበ ኣርእድ፣ ቅድመ ኣሰግድ፣ ዣን ሰገድ፣ ውድም
ኣርእድ፣ ዓምደ ፅዮን ናቸው።

www.ethiopianorthodox.org

## አረብኛ ክብረ ነገስት

የዳዊት መንግስት ከልጁ ከእስራኤል ንጉስ ከሰሎምን ወደ ንጉሱ አገር ማለትም ወደ ኢትዮጵያ ለምን እንደ ተላለፈ ምክንያቱን የሚያብራራ።

በእስራኤል ላይ ከገዛው፣ ከአባቱ ከእሴይ ልጅ፣ ከዳዊት ሞት ሁዋላ ሰሎሞን የእግዚአብሄር ምስጋና ይግባውና ፈቃድ በሆነ ጊዜ፤ ጠንካራ ፍላጎቱ መሰረት የእግዚአብሄርን ቤተ መቅደስ መስራቱን ጀመረ ጊዜ ድንጋዮቹ በከፍተኛ ጠርብ እንዲሰሩ አዘዘ።

ሆኖም ሰራተኞች የድንጋዮቹ መጥረቢያ መሳሪያዎች እየተሰበሩባቸው ·ንጋዮቹን ለመጥረብ አልቻሉም። በዚህን ምክንያት በጥበቡ አንድ ነገር ንዲፈጥርና ለሰራተኞቹም ስራው እንዲቀልላቸው እንዲያደርግ ወደ ሰ ·ሞን ጮሁ።

ሰሎሞንም ፀጋውን እንዲልክለት ጥበቡን እንዲገልፅለት የጥበብ ታ የሆነውን እግዚአብሄርን ለመነ። ከዚህ በሁዋላ አዳኞቹን ጠርቶ ንድ ወጣት ንስር እንዲይዙ አዘዛቸው። በትእዛዙም መሰረት ወጣት ስር አመጡለት። ለተጠቀሰውም ወጣት ንስር ለሶስቱ ቅልጥመ ረጃጅም ግሮቹ የሚመጥን የድንጋይ ሳጥን እንዲሰራ አዘዘ። ንስሩንም ከቤተ ›ንግስት አደባባይ እንዲያመጡትና በመዳቡ ቀፎ እንዲያስገቡት አዘዘ። ንስሩ ሁለት ክንፎች ከተጠቀሰው ቀፎ ሲወጡ ቀፎው ከምድር ከፍ ከፍ ለ።

ከዚያ በሁዋላ የንስሩ አባት ወደ ተራራማው አገር በመጣና ልጁም ዚያ እንዳልነበረ ባየ ጊዜ እጅግ ታወከ። ልጁንም ለመፈለግ በምድር ·ሪያ ተሽከረከረ። ወደ ኢየሩሳሌምም ዘቅዝቆ ተመለከተ። ልጁንም ተጠቀሰው ሳጥን አገኘ። ነገር ግን አውጥቶ የሚወስድበት መንገድ ላገኘምና ከመሬት ምስራቅ በምትገኘው በእግዚአብሄር ገነት አቅጣጫ ረረ።

በገነት አጋማሽ መንገድ ላይም ለመሸከም የተዘጋጀ አንድ እንጨት ገኘ። ይህንኑ ይዞ በታላቁ ሃዘን ወደ ተጣለው ልጁ ገሰገሰ። ኢየሩሳሌም ስኪደርስ ድረስ ፀጥታ አላገኘም። እንደ ደረሰም እንጨቱን በመዳቡ ጥን ላይ ጣለው። በዚህም ወቅት የእግዚአብሄር ምልክት ሆነ። ሳጥኑ ሁለት ተሰነጠቀ። ልጁም ብቅ አለ። ንስሩም ተሸክሞት ወደ ቤቱ ረረ።

ሰሎሞንና የእስራኤልም ልጆች ይህንን ድንቅ ነገር ባዩ ጊዜ ምፃቸውን ከፍ አድርገውሰብአዊ ፍጡር ያልቻለውን ለአንድ ኢሰብአዊ ስር ይህንን ጥበብ የሰጠ ሁሉን ቻይ እግዚአብሄርን አመሰገኑ።

ከዚህ በሁዋላ ንጉስ ሰሎሞን አናጢዎቹ ይህንን ቅዱስና የተባረከ ንጨት ወስደው ድንግጋዮቹ እንዲፈለጡ ከሚሹበት ቦታ ምልክት ያደርጉ የተጠቀሰውን እንጨት እንዲያስቀምጡበት አደረገ። ድንጋዮቹም ሃይለ እግዚአብሄር አናጢዎቹ ከሚሹበት ቦታ ተፈለጡ። በዚህም ምክንያት ስራው ቀለለለት። ሰሎሞንም እግዚአብሄር የቤተ መቅደሱን ስራ ንደ ፈቀደ አወቀ። የቤተ መቅደሱም ስራ ባለቀ ጊዜ ይህንኑ እንጨት



ከቤተ መንግስቱ ፊት ለፊት ከአምዶች ላይ አስቀመጠው። የቤተ መቅደሱም ስራ ከተፈፀመ በኋላ ከእንጨቱ ይወጣ የነበረው ሃይል አቆመ። ከዚያ በኋላ እንጨቱ በክብር አልተጠበቀም።

የዳዊትና የልጁ የሰሎምን ግዛት ወደ ተባረከችው አገር ወደ ኢትዮጵያ፣ እንዲተላለፍ የእግዚአብሄር ፈቃድ በሆነ ጊዜ ወንጌል ንግስተ አዜብ በዚህ ትውልድ ላይ ልትፈርድ ትነሳለች። የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ከምድር ዳርቻ መጥታለችና።[277] እንዳለው ንግስቲቱ ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞ እንድታደርግ አንቀሳቀሳት። ጥንት የኢትዮጵያ ግዛት በንጉሱ ሴቶች ልጆች እጅ ነበር። የዚህች ንግስት እናት እሷን በፀነሰች ጊዜ አንድ የሰባና እግሩ ያማረ ፍየል አየች። በመጎምጀትም እንዴት ያምራል? አለች። እንደ ነፍሰ ጡሮች ባህርይ በፍየሉ ፍፁም ጎመጀች። ስለዚህ የተጠቀሰችው ሴት ልጅ በናቷ ማህፀን ስትፈጠር አንዱ እግሯ የሰው ሌላው እግሯ ደግሞ የፍየል እግር ሆነ። የተመሰገነውና የሁሉ ፈጣሪ ሃያሉ ታላቁና ሁሉንም ቻይ ነውና ይህች እንግዳ ፍጡር ወደ ዓለም በመጣችና እናቷ ባሳደገቻት፣ ልጅቷም ባደገች ጊዜ ባልተስተካከለ የእግሯ አፈጣጠር ምክንያት ባል ሳታገባ በድንግልና ቆየች። ከላይ እንደተጠቀሰው ጥበቡን ለመስማት ወደ ሰሎሞን ለመሄድ ያሰበችውም በተመሰገነው የእግዚአብሄር እውቀት ውስጥ አስቀድሞ ተወሰኖ ስለነበር ነው። ምስጢሩም የዳዊት መንግስት እስከ ዓለም ፍፃሜ ተጠብቆ እንዲኖር ነው። ዳዊት ከእግዚአብሄር በሆነ መንፈስ ቅዱስ እንደ ተናገረው

"ጌታ ለዳዊት እውነተኛ መሀላን ማለ።
ከመሃላውም ፈቀቅ አይልም።
ከሆድህ ፍሬ በዙፋንህ ላይ አስቀምጣለሁ።
ልጆችህ ኪዳኔን የአስተማሩትንም ምስክርነቱን ከጠበቁ፣
ልጆቻቸው በዙፋንህ ይቀመጣሉ።[278] ከዚህም ሌላ በመዝሙርና በሌሎችም ይህንን የሚናገሩ ብዙ ጥቅሶች ይገኛሉ።[279] ይሄውም እነሱ ኪዳኑን ሲያፈርሱ እውነቱን ሳይጠብቁ በተጠበቀው መሲህ ሳያምኑ ሲቀሩ እግዚአብሄር ትንቢቱን ክህነቱንና መንግትን ከእነሱ ይወስዳል።

የተጠቀሰችው ንግስት በመጣችና ንጉሱ ሰሎሞንም በሰላዮች አንድ እግሯ የፍል እግር እንደሆነ ካረጋገጠ በኋላ እሷን ሳይጠይቅ እግሯን ለማየት ኩሽት አዘጋጀ። ዙፋኑን ከቤተ መቅደሱ አደባባይ አዘረጋ። የቤተ መቅደሱን ግቢ በውሃ ለመሙላት የውሃው ቧንቧ እንዲከፈት አዘዘ። እንዲሁም ሆነ። የተጠቀሰው ያ ንስር ከገነት ያመጣው እንጨት ከቤተ መቅደሱ ግቢ ይገኝ ነበር። ማንም ሳያውቅ በውሃ ተነከረ። ሁሉን አስቀድሞ በሚያውቅ አምላካዊ ጥበብ እንደዚሁ ታቅዶ ነበርና።

ንግስቲቱ ወደ ቤተ መቅደሱ በር እየጋለበች በመጣችና ውሃውንም አስቀድማ ባየች ጊዜ በበቅሎዋ ሆና ወደ ንጉሱ ለመግባት ፈለገች። ነገር ግን ይህ የእግዚአብሄር ቤተ መቅደስ እንደሆነና ማንም

[277] ማቴ.12፥42
[278] መዝ.132፥11
[279] ይህ ጥቅስ በተጨማሪም የእስራኤል መንግስት እንደሚቆራረስ ያስረዳል።

www.ethiopianorthodox.org

መጋለብ እንደማይጎበኘው ተገለፀላት። ከዚህ በሁዋላ ተከታይዋና ገልጋይዋ ደግፈዋት ከሰረገላዋ እንድትወርድ ተደረገ። በውሃው ውስጥ መራመድ እንድትችልም እጅዋን አውጥታ የቀሚሷን ጠርዝ ከፍ ከፍ ደረገች።

ንጉሱ ሰሎሞንም እሷን ሳይለምን እግሯን ለማየት ቻለ። እሷም ግቢው ውሃ ውስጥ ስትሄድ እግሯ ያነን እንጨት ነካ። ይህም እንደ ፍየል እግር ያለው እግሯ ያነን እንጨት በነካ ጊዜ የእግዚአብሄር ሃይል ታየ። የፍየል እግር የሚመስለው እግሯ ልክ እንደ ወንድሙ ሌላው እግር ሆነ። በእሷ ላይ የተፈፀመው ሃይልም ወዲያውኑ ታወቃት። ታላቅ ደርሃትና ድንጋጤም መጣባት። በኋላ ግን ፈፅሞ ደስ አላት። ወደ ንጉሱ ሰሎሞንም እስክትደርስ ድረስ በውሃው ላይ መሄደን ቀጠለች።

እሱም በደስታ ተቀበላት። ከዙፋኑም ተነሳ። አክብሮትንም ሰጣት። ጎኑም አስቀመጣት። እሷም ከአለም ዳርቻ የመጣችው ኢየሩሳሌም ፀሎት ማድረስና የእሱንም ጥበብ ለመስማት እንደሆነ አበሰረችው። "ወደዚህ ወደ አስደሳቹ ግዛትህ ስመጣ አንዱ እግሬ የፍየል እግር ነበር። በውሃው ላይ በእግሬ በምሄድበት ጊዜ እግሬ አንድ ጠጣር ነገር ዳሰሰ። ወዲያውኑም አንደ ወንድሙ ትክክል ሆነ። በዚህም ምክንያት ታላቅ ፍርሃትና ድንጋጤ መጣብኝ። ነገር ግን ሁሉን በሚችል በእግዚአብሄር የተደረገልኝ ታላቅ ምህረት ደስታ ተሰማኝ" በማለት ሁለቱንም እግሮቿን አሳየችው። እሱም የእሷን የፍየል እግር አይቶ ውሃውን በማድረግ ብቻ ፈረዳትን ተአምር ሰሪ የሆነውን እግዚአብሄርን አመሰገነ።

ከዚህ በሁዋላ ውሃው እንዲመለስ አደረገ። የቤተ መቅደሱም ግቢ ታየ። በእግሯ የረገጠችውም እንጨት ታየ። ሰሎሞንም የእንጨቱን ታሪክ ነገረከላት።

እሷም ጉዳዩን ካወቀች በኋላ እንጨቱ እንዲከበር አደረገች። በብር ቀለበትም ለበጠችው። ንጉሱ ሰሎሞንም እሷ እንደዚህ ስታደርግ አይቶ በዚሁ አይነት የብር ቀለበት ለበጠው። በጌታ ቤተ መቅደስም የክብር ስፍራ እንዲያገኝ አደረገ። እንዲሁም ሆነ። ለፀሎት ወደ ቤተ መቅደስ የመጡና ታሪኩንም የሰሙ የሰሎሞን የመንግስቱ ተከታዮች ይህንን የታወቀ እንጨት በብር ቀለበት ለበጡት። ከሰሎሞን ዘመን ጀምሮ እስከ ክርስቶስ ልደት በሰላሳ ብር ቀለበት ለበጡት።

ምስጋና ይግባውና እግዚአብሄር የማዳኑን ስራ ለመፈፀምና አዳምንና የዘሩን መዳን የእግዚአብሄርንም ክብር ለመቀነስ ከሚሻው የተረገመው ጠላት ስራ ለማዳን ፈቃዱ በሆነ ጊዜ ይሁዳና ሊቃነ ካህናቱ አታላዮች የአይሁድ ህዝብ ክርስቶስን ሞት ሊፈርዱበትና እሱም አሳልፎ ሊሰጥአቸው ተስማሙ። ሊቃነ ካህናቱም የተጠቀሰውን ሰላሳ ብር ሊሰጡት ፈደታ ገቡ። በሌሊትም ልከው የተጠቀሰውን እንጨት አስመጡ። የተጠቀሰውንም ብር ወስደው ለይሁዳ ሰጡት። እሱም ወንጌላዊው እንደ ፈው[280] ተቀበለ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስንም አሳልፎ ሰጣቸው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የፈረዱበት እለት ማለትም አርብ ጎህ ሲቀድ ይህን

0 ማቴ.26፥14፡ማር.1410፡ሉቃ.22፥3-6



እንጨት ወሰዱ። ከእንጨት ጠራቢ ዘንድም መስቀል አድርገው አሰሩት። መድሃኒታችንንም በዚያ ላይ ሰቀሉት። ይህም ዮሃንስ አፈ ወርቅ ያለው ትክክል እንደሆነ ያረጋግጣል።

አዳምም በገነት ባለው የፍሬ መብል ብቻ በደለ። ከክብሩም ተዋረደ። ከገነትም ተባረረ። ሰይጣንም በእሱና በዘሩ ላይ ስልጣን ተቀበለ። ነገር ግን በእግዚአብሄር ውሳኔና በዚህም የገነት እንጨት ድህነቱን አገኘ። ይህም እንጨት እራሱ የነገስታት ንጉስ መጥቶ እስኪስ ቀልበትና አዳምንና ልጆቹን ከተረገመው ስልጣኑ እስከ ኣዳነ ድረስ በነገስታት ዘንድ በክብር ቆየ። ቀደም ሲል የእንጨት ፍሬ ወደ በደል እንደጨመረ ሁሉ። ስለዚህ ነቢዩ ዳዊት በመዝሙር እግዚአብሄር በእንጨት ላይ ገዥ እንደሆነ ለህዝቦች ንገሩ አለ። ይህም እንጨት የጌታ ስጋ ከፍ ከፍ ስለተደረገበት ከበረ። ፍሬያማም ሆነ። ምክንያቱም በሞት ያጋደሙት እንደገና ተነስቷልና። ይህም ምሳሌ ለነገስታትና ለቀሩት ምእመናን እስከ ዘላለሙ ጋሻና ብርታት ነው። ይሁዳ ግን የተጠቀሰውን ሰላሳ ብር ለተረገሙት አይሁድ በተነላቸው። ከዚያም ታንቆ ሞተ[281] በገንዘብ ስስትም ከህይወት ተሰናበተ። አይሁድም ወስደው የሸክላ ሰሪውን የእርሻ ቦታ ለእንግዶች መቃብር ገዙበት።[282] እስከ ዛሬም አለ። እስከ ዚህ ድረስ ስለ እንጨቱ ታሪክ ነው።

አሁን ወደ ጀመርነው የዳዊት መንግስት ወደ ኢትዮጵያ ስለ ተላለፈበት ታሪክ እንመለስ። ንጉስ ሰሎሞን ለንግስቲቱ የክብር አቀባበል ካደረገ በኋላ እሷንና ተከታዮቿን ሰራዊቷንም በአንድ ቤተ መንግስት እንዲያርፉ አደረገ። እሷም ጥበቡን ለመስማት በየቀኑ ትጎበኘው ነበር።

ሰሎሞንም በሴት ፍቅር የተነደፈ ነበርና በእሱ ዘንድ ጉብኝቷን ባዘወተረች ጊዜ ፈቃዱን እንድትፈፅምለት ጠየቃት። እሽታንም ይጠባበቅ ነበር። እሷ ግን "እኔ ድንግል ሆኜ መጣሁ። ድንግልናየንና ክብሬን አጥቼ ወደ አገሬ እመለሳለሁን? በዚህስ ምክንያት በመንግስቴ ላይ ስድብን አመጣለሁን?" አለችው እንጂ ለጊዜው ፈቃዱን አልፈፀመችም።

እሱም "እኔ አንችን እንደ ህግ ሚስት አድርጌ አገባሻለሁ። እኔም ንጉስ አንችም ንግስት እንሆናለን" ሲል መለሰላት። ለዚህም ቢሆን አስደሳች መልስ አልሰጠችውም። እንደገናም አላት። " ይልቁንስ ከእኔ ጋር አንድ ውል አድርጊ። በመኝታ ውስጥ ከፍራሼ እያለሁ በነፃ ፈቃድሽ ላውቅሽ እችላለሁ። አንቺም በህገ መንግስቱ መሰረት ሚስቴ ትሆኛለሽ" በዚህ ምክንያት ድንግልናዋን ከመደፈር ለመጠበቅ በዚህ ውል ተስማማች። ይህም ምስጋና በሚገባውና ባለፀጋ በሆነው በእግዚአብሄር ፈቃድ ሆነ። በርካታ ቀናትም አለፉ። አሳቧንም በጥበቡ ገነባው። ነገር ግን ምኞቱን እንድትፈፅምለት ከመጠባበቅ ወደ ሁዋላ አላለም። እሷንም በእጅ የሚዳስስና ተጨባጭ ምክር መስጠቱ አስደሰታት።

281 ማቴ.27፥3 -5
282 ማቴ.27፥6-8

www.ethiopianorthodox.org

ከዚህ በሁዋላ ወጥ ቤቶቹን ጠራና ለእሱና ለንግስቲቱ የሚያቃጥል ወጥ እንዲሰሩ አዘዛቸው። ለዚህም የተዘጋጀ ቅመማ ቅመሞችን ሰጣቸው። ወጥ ቤቶቹም በትእዛዙ መሰረት ፈፀሙ።

ንግስቲቱም የሚያቃጥለውን ወጥ ከተመገበች በኋላ ቀዝቃዛ ውሃ ጠየቀች። ቀንም ሌሊትም በብዛት ጠጣች። ነገር ግን ሁሉም ምንም አልረዳትም።

በሶስተኛው ክፍለ ሌሊትም ከንግስቲቱ አጠገብ ምንም አይነት የሚጠጣ ውሃ እንዳይተው በውስጥም በውጭም ላሉት የቤተ መንግስት ሰዎች ምስጢራዊ ትእዛዝ ተላለፈ። አንድ ሰው ቢያሳይ ወይም ከራሱ ውሃ ቢሰጥ ያለምንም ፍርድ ይገደላል። ማንም በሌሊት የሚጠጣ ውሃ ቢጠይቅ ከንጉሱ መኝታ ቤት በቀር ሌላ የትም ቦታ እንደማይገኝ እንዲነግሩ አዘዘ።

ሌሊትም በሆነ ጊዜ የንግስቲቱ ቆሽት በውሃ ጥም አረረ። ውሃ ትጠጣ ዘንድ ፈለገች። ነገር ግን ምንም አላገኘችም። ፀጥታም አጥታ ወዲያና ወዲህ ተወራጨች። ለሞትም ቀረበችና ወደ ተከታዮቿ ጮኸች። ነገር ግን ትጠጣ ዘንድ ውሃ አላገኙላትም። የጠነከረው ጥሟም እጅግ ባሸነፋት ጊዜ ትጠጣ ዘንድ በቤተ መንግስት ውሃ ያለውን ሰው ፈለገች። ሆኖም የጠየቀቻቸው ሰዎች ሁሉ "የጥምሽን ነበልባል ለማጥፋት ውሃ ከንጉሱ መኝታ ክፍል በቀር እንዳታገኝ በመንግስትሽ እንምላለን" አሏት።

ከዚህ በሁዋላ ወደ ማረፊያ ክፍልዋ ተመለሰች። ነገር ግን ፀጥታ አላገኘችም። ነፍሷና ስጋዋም ሊለዩ ቀረቡ። ህይወቷንም ሳተች። ፈጥናም ተነሳች። በእሱም ዘንድ ውሃ ካለው ትጠጣ ዘንድ ቀስ ብላ ወደ ሰሎሞን ገባች። ለእሷ ያንቀላፋ ይምሰላት እንጂ ይሰማ ነበር። ከውሃውም በብዙ ጠጥታ ጥሟን ቆረጠች፣ ነፍሷም ገባች። ከሞት አገርም የተመለሰች መሰላት። ከዚህ በሁዋላ ወደ ማረፊያዋ ልትመለስ ስትል ፈጥኖ ተነሳና ከሁዋላዋ ጎተት አድርጎ "በህገ መንግስታችን መሰረት በእውነት ሚስቴ ሆነሻል" አላት። በእሱና በእሷ መካከል ስላለውም ውል አስታወሳት። እሷም ቀደም ሲል በተስማማችው መሰረት ፈቃዱን ፈፀመችለት።

ከእሱም ከፀነሰች በኋላ "ወደ አገሬና ወደ መንግስቴ ለመሄድ እሻለሁ። እግዚአብሄር ይህንን ህፃን በደህና እንዲወለድ ቢፈቅድ ስለ ልጁ የማደርገው ምንድን ነው?" ስትል ጠየቀችው።

እሱም "የጌታ ፈቃድ ሆኖ ወንድ ልጅ ብትወልጂ ሲያድግ ወደ እኔ ትልኪዋለሽ። እኔም ንጉስ አደርገዋለሁ። የአንችንም መንግስት ይወርሳል። ሴት ልጅ ከሆነች ግን በአንችው ዘንድ ትሁን" አላት። እሷም መልሳ "ወደ አንተ ስልክልህ ልጅህ መሆኑን እንዴት ታውቃለህ?" አለችው። እሱም አንድ ቀለበት ሰጣትና "ይህንን ቀለበት አኑሪው። አንችም በመካከላችን የምናደርገውን የቃል ኪዳን ውል ችላ ላትይ ቃል ግቢ። ሃያሉ የአብርሃም፣ የይስሃቅ፣ የያዕቆብና የዳዊትም አምላክ በእኔና በአንቺ መካከል ምስክር ነው ። እሱ ልጄ እንደሆነ እንዳውቅና



እንዳነግሰው ወደ አንችም እንድመልሰው ቀለበቱን እንዲያደርገው አድርጊ" አላት።

እሷም ይህንን የቃል ኪዳን ውል ተቀበላ ከእሱ ጋር ተሰነባበተች። በእግዚአብሄርም ሰላም ታጅባ ከሰራዊቷ ጋር ተጓዘች። ወደ አገሯም እንደ ተመለሰች የፅንሷን ወራቶች አሳለፈች። ወንድ ልጅን ወለደች። ከፍተኛ ደስታም ተሰማት። ስሙንም በአያቱ ስም ዳዊት አለችው። በመልካም አስተዳደግም አሳደገችው። ከእለታት አንድ ቀንም ወደ ወጣትነት እድሜ በደረሰና የአእምሮ ብስለትም ባገኘ ጊዜ እንደ አባቱም ብልህና ጠቢብ በሆነ ጊዜ እናቱን፣ "እናቴ ሆይ! አባቴ ማነው? እኔ ገና ትንሽ ሳለሁ ሙቷል?" ብሎ ጠየቃት። እሷም "ውድ ልጄ አባትህ በህይወት አለ እሰ-ም የእግዚአብሄር ነቢይና የእስራኤል ንጉስ የነበረው የዳዊት ልጅ ሰሎሞን ነው። ግዛቱም በኢየሩሳሌም ነው። አስተውል። ለእኔ ብቻ የተጠበቀው የአባትህ መንግስቱ ማህተም በእኔ ዘንድ አለ። በዚሁ አማካኝነት በፈቃደ እግዚአብሄር አንተ በኢትዮጵያ ምድር ላይ ንጉስ እንድትሆን። ካሁንም ጀምሮ አንተ እንጂ የምገዛው እኔ አይደለሁም። አንተ ንጉስ፣ የንጉስ ልጅ ነህና" አለችው። ይህም በጣም አስደሰተው። ምስጋናውንም ገለፀ። ከዚያም "ራስህን አዘጋጅ፣ ስጦታና ወታደርም አዘጋጅ። ትሰግድ ዘንድና ጥበቡን ታይ ዘንድ እንዲሁም በመካከላችን እግዚአብሄር ምስክር ሆኖ በእኔና በእሱ መካከል ባለው ስምምነት መሰረት እንዲያነግስህ ወደ ኢየሩሳሌም ሂድ" አለችው። የአባቱንም ቀለበት በቀኝ እጁ አደረገችለት። በእግዚአብሄርም ፈቃድ ተነሳ ከሰራዊቱና ከንጉሳዊ ገፀ በረከት ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ።

ሰሎሞንም አንድ ንጉስ እሱን ለመውጋት በመንገድ ላይ እንደሆነ ሲሰማ የእሱንም ሰራዊት እንዲንቀሳቀስ አደረገ። ያኛውም ወደ ቤተ መንግስት በር ሲደርስ ልጁ መሆኑን ሰሎሞን ገና አላወቀም ነበር። ወጣቱም እንደደረሰ የአባቱ በቅሎ ተጭና ሲያይ ሰሎሞን ወደ ተቀመጠበት ገሰገሰ። በፉከራም ጎራዴውን መዘዘ።

ሰሎሞንም ይህንን ባየ ጊዜ ነገሩ ከበደው። ሁለቱ ሲገናኙ ብቻ ስለዚህ ነገር ማለለት። በቅሎውን ስለ መጋለቡና ሰይፉንም በእጁ ስለመጨበጡ ገልፆ ተናገረ እንጂ እንዲታወቅ አላደረገም። "እኔ ገና በእናቴ ማህፀን ሳለሁ በመንግስቱ ላይ ንጉስ አድርጎ የሾመኝ የዚህ ቀለበት ጌታ ነው። ይህም ደግሞ በእግዚአብሄር ፈቃድ ሆነ" አለው። ሰሎሞንም ቀለበቱን ከተመለከተና ነገሩንም ካረጋገጠ በሁዋላ ፍፁም ደስታ አደረገ። ከዙፋኑም ተነሳ። አንገቱንም አቀፈው። ቀጥሎም ውድ ልጄ ሆይ! የዳዊት ልጅ ሆይ! እንኳን ደህና መጣህ በማለት በከፍተኛ ድምፅ ጮኸ። ወዲያውም የአባቱን የዳዊትን ዘውድ ጫነለት። በአባቱ በዳዊት ዙፋን ላይም አስቀመጠው። መለከቶች ተነፉ። አዋጅ ነጋሪዎችም ጮሁ። የሰሎሞንና የእስራኤል ንጉስ፣ የዳዊት ልጅ ንጉስ ዳዊት ነው። ዝናውም ወጣ። ዜናውም ማለት የሰሎሞን ልጅና የንግስት አዜብ ልጅ ወደ አባቱ ወደ ሰሎሞን እንደመጣ፣ አባቱ በዳዊት መንግስት ላይ እንደ ሾመው፣

www.ethiopianorthodox.org

ዘውድ እንደ ደፋለትና በዙፋኑም ላይ እንዳስቀመጠው ወደ ሁሉም የእስራኤል ነገዶች ተሰራጨ።

ሰሎሞን ባሰራውና ባስመረቀው ቤተ መቅደስ ውስጥ በእግዚአብሄር እጅ የተፃፉት ሁለቱ የድንጋይ ፅላቶች የነበሩት ታቦተ እግዚአብሄርና እንዲሁም የአሮን መቋሚያና በወርቅና በወርቅ ሃር የተለበጠች የመና መያዣ መሶበ ወርቅ ነበሩ።

ህዝቡም አንድ ምልክት ነበራቸው። ካህናቱ በፀለዩና ፀሎታቸውንም ሁሉን ለሚችለው አምላክ ካቀረቡ፣ የፀሎት ስነ ስርአታቸውንም ካጠናቀቁ በሁዋላ የእግዚአብሄር ታቦተ ህግ ከምድር ከፍ ከፍ ትል ነበር። በዚህም እግዚአብሄር ፀሎታቸውን እንደ ተቀበለላቸው ያረጋግጣሉ። ነገር ግን እነሱ የፀሎት ስነ ስርአታቸውን ሲያጠናቅቁ ታቦቷ ካልተነሳች ከእነሱ ወይም ከህዝቡ ሃጢያት እንደ ተሰራ ያውቃሉ። ይህም ሲሆን ፀሎታቸውን ወደ ጌታ ይቀጥላሉ። ሃጢአቱን የሰራውንም ይመረምራሉ። ከዚህ ሁዋላ ታቦቷ ከተነሳች እግዚአብሄር እነሱን ከተቆጣበት ቁጣው እንደ ተመለሰ ያውቃሉ። ታዲያ የሰሎሞን ልጅ ለመፀለይ ወደ ጌታ ቤተ መቅደስ ሲገባ ታቦቷ ተነሳች። ይህንንም አስደናቂ ስራ አይቶ በጣሙን አሳሰበው። ታቦቷንም ወደ አገሩ ለመውሰድ አቀደ። ከአባቱ ከእስራኤል ንጉስ ከሰሎምን ጋር በቆይታ ተነጋገረ። ለአባቱም "ታቦቷን ወደ አገሬ ለመውሰድ እሻለሁ" አለው። ይህኛውም "ልጄ ሆይ! እሷን መሸከም የሚችሉ ካህናት ብቻ ስለሆኑ ይህንን ማድረግ አትችልም። ከካህናት በቀር እሷን የሚዳስስ ሁሉ ወዲያውኑ ይሞታል። ከዚህም በቀር የእስራኤል ልጆች ከጠላት የሚድኑት በእግዚአብሄር ታቦት ነው" አለው። ነገር ግን ብላቴናው በዚህ ንግግር ደስ ባለመሰኘት "እኔ ከአንተ ወርቅም ሆነ ብር አልሻም። ወርቁ በአገሬ በብዛት ሞልቷልና። ስለዚህ በመንገደ ከምትጠብቀኝና ለመንግስቴና ለሰ ራዊቴ ረዳት ከምትሆነኝ ከእግዚአብሄር ታቦት በቀር ከአንተ የምሻው የለኝም" አለው።

ከዚያም አባቱ እንዲህ ሲል መለሰለት። "ልጄ ሆይ! ሁሉን በሚችል በእግዚአብሄር ፈቃድ ከሆነ ማለት አንተ እሷን እንድትወስድ ቀላል አይሆንልህም። አንተ ታቦቷን ስትወስድ እኔ እንዳውቅ አታድርግ። ከወደድከም ከእኔ አትሰናበት። ምክንያቱም የእስራኤል ታላላቅ ካህናቱና አዛውንቱ በእግዚአብሄር መሃላ ያስምሉኛልና። እኔም በእግዚአብሄር ስም ከማልኩ መሃላየን መጠበቅ አለብኝ" አለው።

ከዚህ በሁዋላ ወጣቱ ንጉስ አንድ የእንጨት ሰራተኛ አስመጣ። በፅላቱም ርዝመትና ስፋት ልክ አንድ እንጨት እንዲሰራለት ከአደረገ በሁዋላ በዚያው ሌሊት ሰራተኛውን ገደለው። እንዲሁም ሌሎችን ሰራተኞች አስመጣ። እንደ ታቦተ ህጉም ሁሉ እንጨቱን በወርቅ እንዲለብጡለት አደረገ። እነዚህም ሰራተኞች የፊተኛው ሰራተኛ እድል እንዲደርሳቸው አደረገ ማለት አስገደላቸው። እሱም ጉዞ ሲጀምር አባቱ ሰሎሞን አያውቅም ነበር። በተቃራኒው ግን አራት ካህናትን አስጠርቶ ከጉዞው በፊት ፀሎታቸውን ለመጠየቅ እንዳስመጣቸው ገለፀላቸው። እንዲፀልዩለትም



ወርቅ ሰጣቸው። ምንጊዜም በፀሎታቸው እንዲያስቡት ከግምጃ ቤት ውጪ ሆኖ ስጦታ እንዲሰጣቸው አደረገ።

በሚሄድበትም ቀን ማታ ለመሰናበት ተሰበሰቡ። ወደ ግል ቤተ መንግስቱ ክፍልም አስገባቸው። ገብተው ሳሉ በእግር ብረት አሳሰራቸውና ወታደሩ ያለ ነጋሪት ወደ ፊት እንዲጓዝ አስደረገ። በእጃቸው የጦር መሳሪያ የያዙ አገልጋዮቹንም ከእሱ ጋር ወሰደ። በእግር ብረት የታሰ ሩትን ካህናትም እንዳይሮጡ አስይዞ ከእግዚአብሄር ቤተ መቅደስ ታቦተ ህጉን እንዲሸከሙና በእሷ አምሳል የተሰራችውን ታቦት ከእሷ ቦታ እንዲያስቀምጡ አዘዛቸው። ካህናቱንም አሸክሞ በሌሊት ተጓዘ። ከአባቱም አልተሰናበተም። አባቱንም ስለጉዞው አላሳወቀም። ይህም በተመሰገነውና ወሃቤ ፀጋ በሆነው በእግዚአብሄር ርዳታ ሆነ። ምክንያቱም ከሆዱ ፍሬ በዙፋኑ ላይ እንዲያስቀምጥለት ለዳዊት በገባው ቃል መሰረት የተቀደሰ ችው ታቦቱ የዳዊት መንግስት እስከሆነ ድረስ ለዘላለሙ ተጠብቃ እንድትኖር ነው።

እንዲሁም ወጣቱ የሰሎሞን ልጅ በእግዚአብሄር ርዳታ ታጅቦ ተጓዘ። ሲነጋም የእስራኤል ልጆችና ካህናት ለፀሎት ባላቸው ልማድ መሰ ረት የእግዚአብሄርን ቤተ መቅደስ ተመለከቱ።

ካህናቱ የፀሎቱን ስነ ስርአት ከፈፀሙና ሁሉን ለሚችለው ልመናቸውን ካቀረቡ በሁዋላ ፅላቷ ከፍ ከፍ አላለችም። ከቦታዋም አልተንቀሳቀሰችም። ከዚህ በሁዋላ "ሃጢአት ተሰርቷል" ሲሉ ተናገሩ። ሶስት ቀናትም ሙሉ ሲፆሙና ሲፀልዩ ጀመሩ። ከዚህም ጋር በህዝቡ መካከል ማን ወንጀል እንደሰራ ይመረምሩ ጀመር። ሆኖም ምንም አላገኙም። ከዚህ በሁዋላ ካህናቱ ወደ ፅላቱ ገቡ። "የእግዚአብሄር ያለህ ምን አይነት አለመታደል ነው? ምን አይነትስ አስደንጋጭና አሳዛኝ ነገር ነው?" አሉ።

የቃል ኪዳኑን ታቦትና የእግዚአብሄርን ቅድሳትም ባጡና ፅላቷም ተቀምጣ ከነበረበት ቦታ ባዶ ሆኖ ባገኙ ጊዜ "ትልቅ ማታለል ተፈፅሟል" አሉ። የንጉስ ሰሎሞን ልጅም እንደ ወሰዳት አወቁ። ካህናቱና ከእስራኤል ነገዶች ውስጥ በዚህ ነገር የተባበሩ እንዳሉ መረመሩ። ነገር ግን ፅላቷን የወሰዱትን ካህናት ለማግኘት አልቻሉም። ሆኖም ካህናቱ ውስጥ አንዳንዶቹ በመጉደላቸው ቀደም ሲል የተገመተው እርግጠኛ እንደሆነ ታወቀ።

ከዚህ በሁዋላ ካህናቱና የእስራኤል ታላላቆች በቃል ኪዳኑ ታቦት መጥፋት እያለቀሱና እያዘኑ፣ ሙሾም እያወጡ፣ ወደ ንጉሱ ሰሎሞን ሄደው "ታቦቷን እንዲወስድ ያዘዝከው አንተ ነህ?" አሉት። እሱንም ልቅሶና ጬኸት ፈነቀለው። በዚህም እለት ታላቅ የሃዘን ቀን አደረገ። ለማንም እንዲህ ያለ ፈቃድ እንዳልሰጠና ከእሱም እንዳልተሰናበተ ስለ ጉዞውም እንደማያውቅ፣ ጉዞውም በስንት ሰአት እንደሆነ እንደ አላወቀ ማለላቸው። ከዚህ በሁዋላ እነሱም እንዲህ ሲሉ መለሱለት። "ንጉስ ለዘላለም ይኑር። ይህ በአንተ ፈቃድና ትእዛዝ ካልሆነ እንድናሳድዳቸውና

www.ethiopianorthodox.org

ቅድስቷንም ታቦት ከእነሱ እንድንወስድ፣ እነሱንም ወደ ከበረው ቤተ መቅደስ እንድንመልሳቸው የታጠቁ ወታደሮች ስጠን" ሲሉ መለሱለት።

ከዚያ በሁዋላ ወታደር፣ ገንዘብና ስንቅንም ሰጣቸው። እነሱም ለመፈለግ ጉዞ ጀመሩ። ጉዞአቸውንም ሳያቋርጡ ለአርባ ቀናት ቀጠሉ። በጉዞአቸውም ላይ ከንግድ የሚመለሱና ከእነሱ ፊት ለፊት የሚመጡ ነጋዴዎችን አግኝተው የታቦቷን ነገር ማለትም እነሱ ያዩት ነገር እንዳለ ጠየቋቸው። እነሱም በዚሁ ነገር መልሰው "አንድ ታላቅ ንጉስን ከበርካታ ሰራዊቱ ጋር አይተናል። ከእነሱም ጋር የእግዚአብሄር ታቦት አብራ ነበረች። ከረጅም ጊዜም በፊት በብርቱ ነፋስ እንደሚነዳ ጉም ሆነው ተመሙ። በኋላቸው የቀሩት ሌሎች ሰዎች ደግሞ በዚሁ ዕለት አርባ ቀናት የሚያስሄድ መንገዶችን ወደ ሁዋላቸው እንደተው ነገሩን" አሏቸው። ከዚህ በሁዋላ እነዚህ ጉዳያቸው ያልተሳካላቸው በፍርሃት፣ በማልቀስ፣ በፀፀትና ፀፀታቸውም ምንም ሳይረዳቸው ተመለሱ።

ወጣቱም ሄደ። በደህናውም ወደ አገሩ በደረሰ ጊዜ እናቱ ስለ እሱ ከመንግስቷ ተሰናበተች። እሱም በአባቱ የዳዊት ዙፋን ተቀመጠ። የኢትዮጵያ መንግስትም ለዘላለሙ ለዳዊት ዙፋን ሆነ። የእግዚአብሄር የቃል ኪዳን ታቦትም በእነሱ ዘንድ ቆየች።

የእግዚአብሄር ታቦት ታሪክና እንዴት ወደ ኢትዮጵያ እንደ ገባች ምክንያቱ ይህ ነው። ይሄ የሆነው እስከ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እሱ የማዳኑን ስራ በምድር ላይ ፈፅሞ፣ አዳምንና ልጆቹን አድኖ፣ ወደ ሰማይም ባረገ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ በስሙ ወንጌልን በመላው ዓለም እንደ ሰበኩ፣ ስለ ንግስት ህንደኬ ጃንደረባውም እንደ አመነ፣ እንደ ተጠመቀ፣ ወደ አገሩም እንደተመለሰ፣ ከዚያም የክርስቶስን ወንጌል እንደሰበከና ሁሉም ሃይማኖትን እንደተቀበሉ ይተረካል።

ከዚያም በሁዋላ ከሰባቱ አንዱ ፓርሜናስ[283] መጣ። እሱም እነሱን አጠመቃቸው። ቀሳውስትንና ዲያቆናትንም ሾመላቸው። ሊቀ ጳጳሳቸውም ለወንጌላዊው ማርቆስ መንበር ተጠሪ እንዲሆን ወሰነ። ከዚያ በሁዋላ የኦርቶዶክስ ሃይማኖትን በምድረ ኢትዮጵያ ተቀብሉ ግዛቱም ከዳዊት እስከ ዓለም ፍፃሜ ይሆናል። ውዳሴ፣ ምስጋና፣ ጌትነት፣ ክብርና ስግደት ለስሉስ ቅዱስ ይገባል።

በቀደሙት የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርኮች ዜና መዋእል የተገኘው ይህ ነው። ለፍጡሮቹ ማስተዋልንና አእምሮን የለገሰ እሱ የተመሰገነ ይሁን። ፀጋው ከእኛ ጋር ለዘላለሙ ይሁን። አሜን።

ተ ፈ ፀ መ

[283] ፊልጶስ ለማለት

## ማረሚያ

ገፅ ፮ አንቀፅ 3 ቀጥሎ ባለው አንቀፅ ተተክቷል።

እንደሚታወቀው የዳዊት ልጅ ንጉስ ሰሎሞን ሞቶ የሰሎሞን ልጅ ሮብአም በ931 ቅ.ል.ክ. ሲነግስ የተስፋው መንግስት ለሁለት ተከፈለ። ሰሜኑ ክፍል እስራኤል ደቡቡ ደግሞ ይሁዳ ተብሉ ሁለት መንግስት ሆነ። የሰሜኑ መንግስት ከ12 ነገድ ውስጥ 10 ነገድ ሲያካትት ደቡቡ ደግሞ በሁለት ነገዶች (ይሁዳና ብንያም) ብቻ ቀጠለ። የዳዊት ልጆች ድርሻ የነበረው ይሄው ሁለት ነገዶችን ብቻ ያቅፍ የነበረው የደቡቡ ክፍል ነበር።

ገፅ 29 ምእራፍ ፴፮ አርእስቱ "ኀበ ተራከበ ምስለ ወልዱ ንጉስ ሰሎሞን" ተብሎ ይስተካከል።

ገፅ 33 ምእራፍ ፴፫ አርእስቱ ላይ ንጉሱ ልጁን ከልጆቻቸው ጋር ለመላክ እንደ "ሞከረ" የሚለው እንደ "መከረ" ተብሎ ይነበብ።

ገፅ 122 ግእዙ ገፁ መጨረሻ ላይ

8. እስመ ለሊሁ ያአምር መለኮቶ። ወያአምር ክብሮ። ወያአምር ርእሶ። ወሎቱሰ አልቦ ዘያአምሮ። እስመ ገባሬ ኩሉ ውእቱ። ወሶበሰ አእመሩ የሚል ተቆርጦ ስለ ቀረ በዚህ መሰረት ተስተካክሎ እንዲነበብ እናሳስባለን።

www.ethiopianorthodox.org